# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ

ለአፍሪካ መጋቢዎች የተዘጋጀ መመሪያ

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ

## ለአፍሪካ መጋቢዎች የተዘጋጀ መመሪያ

ዴንዚል አር ሚለር ፣ አርታኢ
ጀፍሪ ኔልሰን ፣ ተባባሪ አርታኢ
ቶድ ቸርችል፣ ተባባሪ አዘጋጅ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ ፤ የአፍሪካ መጋቢዎች መመሪያ
The Pentecostal Pastor's Manual: A Guide for African Pastors

© የቅጂ መብት 2022 በአፍሪካ ሆፐ፣ ስፐሪንግፊልድ፣ ሚዙሪ፣ አሜሪካ። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የዚህ መጽሐፍ የትኛውም ክፍል ሊባዛ፣ በመጽሔቶች፣በጋዜጦች በግምገማዎች ውስጥ ካሉ ግምገማዎች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ከሚውሉ አጫጭር ጥቅሶች በስተቀር ያለ የቅጂ መብት ባለቤቱ የቅድሚያ የጽሁፍ ፈቃድ በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ (ኤሌክትሮኒክ፣ ሜካኒካል፣ ፎቶ ኮፒ፣ ቀረጻ ወይም ሌላ) ይተላለፋል።

በልዩ ሁኔታ ካልተገለጹ በስተቀር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የቅጂ መብት በ1973፤ 1978፤ 2011፤ በቢቢሊካ Inc. ሁሉም መብቶች በዓለም ዙሪያ የተጠበቁ ናቸው።

የአርታኢ ኮሚቴ፡-
ዴንዚል አር. ሚለር (ዲሚን) አርታኢ
ጀፍሪ ኔልሰን (ፒ ኤች ዲ) ፣ ተባባሪ አርታዒ
ቶድ ቸርችል፣ ተባባሪ አዘጋጅ

የትርጉም ኮሚቴዎች፡-
ፓስተር ማቴዎስ ካሳዬ መኩሪያ (አስተባባሪ)
አክሊሉ ኩማ ፉፋ (ተርጒሚ)
ኤርሚሻ በየነ ጴጥሮስ (ዋና አርታኢ)
ገስጥ አሰግደው ገ/መስቀል (ተባባሪ አርታኢ)

ካታሎግ ውሂብ፡-
ዴንዚል አር. ሚለር አርታኢ፣ 1946
የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ፤ ለአፍሪካ መጋቢዎች መመሪያ
አር ሚለር ከጀፈርሪ ኔልሰን እና ቶድ ቸርችል

1. ተግባራዊ ሥነ-መለኮት ፣
2. መጋቢያዊ ሥነ-መለኮት፣
3. መጽሃፍቶች እና፣
4. ማኑዋሎች፡፡

የህትመት ስራ፡- አፍሪካ ሆፐ ህትመት ስራ
580 ምዕራብ ማዕከላዊ ጎዳና
ስፐሪንግፊልድ፣ ሚዙሪ፣ አሜሪካ 65802

Published by Africa's Hope
580 West Central Ave
Springfield, Missouri, USA 65802

ኢ-መጽሐፍ (E-book) በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የተዘጋጀ

# ውጫ


ማውጫ ........ 3
አበርካቾች ዝርዝር ........ 5
መቅድም በራንደል ታር ........ 7
መቅድም በዶ/ር በርናባስ ምቶከምባል ........ 9
መግቢያ ........ 11

**ክፍል 1 ~ የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ ብቃቶች**

ምዕራፍ 1 ~ ልምድ ያለው ሰው ........ 17
ምዕራፍ 2 ~ የመንፈሱ ሰው ........ 25
ምዕራፍ 3 ~ የመልካም ሥነ ምግባር ሰው ........ 33
ምዕራፍ 4 ~ በሙላት የተዘጋጀ ሰው ........ 41

**ክፍል 2 ~ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዩች**

ምዕራፍ 5 ~ የአገልግሎት ቅድሚያ ........ 51
ምዕራፍ 6 ~ በግል ሕይወት ቅድሚ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች ........ 59
ምዕራፍ 7 ~ ቤተሰብን ቅድሚያ ማድረግ ........ 67
ምዕራፍ 8 ~ ጸሎትን ቅድሚያ ማድረግ ........ 75

**ክፍል 3 ~ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እምነት**

ምዕራፍ 9 ~ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን ያምናል ........ 85
ምዕራፍ 10 ~ የጴንጤቆስጤያዊ እውነትን ይደግፋል ........ 93
ምዕራፍ 11 ~ የጴንጤቆስጤያዊ ልምምድ እና ተግባርን ያበረታታል ........ 101
ምዕራፍ 12 ~ የጴንቆስጤ ትውፊቶችን ማክበር ........ 109

**ክፍል 4 ~ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የግል ሕይወት**

ምዕራፍ 13 ~ በመልካም ስርዓት የሚተዳደር ሕይወት ........ 119
ምዕራፍ 14 ~ ጤናማ ግንኙነቶች ........ 127
ምዕራፍ 15 ~ ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ........ 133

**ክፍል 5 ~ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የአደባባይ አገልግሎት**

ምዕራፍ 16 ~ በመንፈስ የተቀባ ጸሎት ........ 143
ምዕራፍ 17 ~ ውጤታማ ትምህርት ........ 151
ምዕራፍ 18 ~ ቤተ ክርስቲያንን በአምልኮ መምራት ........ 159
ምዕራፍ 19 ~ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጴንጤቆስጤያዊ ሪቫይቫል መምራት ........ 167
ምዕራፍ 20 ~ አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት ........ 175
ምዕራፍ 21 ~ በመንፈስ ኃይል ማገልገል ........ 183
ምዕራፍ 22 ~ በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ መሳተፍ ........ 191

**ክፍል 6 ~ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ እረኛ**

ምዕራፍ 23 ~ የመጋቢያዊ አገልግሎትን መረዳት ....201
ምዕራፍ 24 ~ በጎችን መንከባከብ ....209
ምዕራፍ 25 ~ አካሉን ማጠናከር ....215
ምዕራፍ 26 ~ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማማከር ....223
ምዕራፍ 27 ~ መንጋውን መጠበቅ ....231

**ክፍል 7 ~ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ መሪ**

ምዕራፍ 28 ~ የጴንጤቆስጤያዊ አመራር .... 241
ምዕራፍ 29 ~ የአገልጋይ መሪነት ....249
ምዕራፍ 30 ~ ባለ ራዕይ መሪ ....257
ምዕራፍ 31 ~ ተልዕኮ መር አመራር .... 265

**ክፍል 8 ~ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ አስተዳዳሪ**

ምዕራፍ 32 ~ ሰነዶችን፣ ፋይናንስን እና ንብረትን ማስተዳደር ....273
ምዕራፍ 33 ~ አሳታፊ አመራርን መፍጠር ....281
ምዕራፍ 34 ~ የቤተ ክርስቲያን ዘርፎዎችን መምራት ....289
ምዕራፍ 35 ~ የቤተ ክርስቲያን አባልነትን መከታተል .... 297

**ክፍል 9 ~ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ተልዕኮ**

ምዕራፍ 36 ~ የአዲስ ኪዳን ስትራቴጂን መረዳት .... 307
ምዕራፍ 37 ~ የጠፉትን በወንጌልን መድረስ ....315
ምዕራፍ 38 ~ ማህበረሰብን ማገልገል ....323
ምዕራፍ 39 ~ አዲስ አጥቢያ ቤተክርስቲያ መትከል ....331
ምዕራፍ 40 ~ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተልዕኮ ፕሮግራምን ማጎልበት .... 339

**ክፍል 10 ~ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እና ሥነ ሥርዓቶች፣ የጌታ ዕራት እና የጥምቀት ሥርዓት**

ምዕራፍ 41 ~ የጋብቻ እና የቀብር ሥርዓትን ማስፈጸም ....349
ምዕራፍ 42 ~ የውሃ ጥምቀት፣ የጌታ ራትን፣ ልጆችን ማስረከብ እና ሹመትን ማከናወን .... 357

**አባሪዎች**

አባሪ 1 ~ የእምነት መግለጫ የዓለም ጉባኤ እግዚአብሔር ህብረት .... 367
አባሪ 2 ~ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች ....371
አባሪ 3 ~ የመጽሐፍ ቅዱስ አጽሮተ ቃላት ....373

# አበርካቾች ዝርዝር

ለዚህ መጽሐፍ አስተዋጽዖ ያደረጉ ሰዎች ዝርዝር ከዚህ በታች ሰፍሮ ይገኛል። የእያንዳንዱ ማጣቀሻ መጨረሻ በቅንፍ ውስጥ ያለው ቁጥር(ዎች) የሚያመለክተው ይህ ሰው አስተዋፅዖ ያበረከተውን ምዕራፍ(ችን) ነው።

---

አዳዬ አዩ (ፒ ኤች ዲ) የቶጎ ጉባዔ እግዚአብሔር ቤተክርስትያን ዋና ጸሀፊ (29)

አማ ኡቼቹኩ የአፍሪካ ጉባዔ እግዚአብሔር ሕብረት የዓለም ተልዕኮዎች ኮሚሽን ምክትል ሊቀ መንበር (40)፣

ባንዳ የሊፔንጋ ፣ የዛምቢያ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተክርስትያን ጠቅላይ ተቆጣጣሪ፣ (33)፣

ቦገሪ ሪቻርድ (ፒ ኤች ዲ) ክሪስት ቻፐል ኢንተርናሽናል የጋራ መስራች ፣ ካምፓላ፣ ኡጋንዳ ፤ ፓን አፍሪካ ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ ፋኩልቲ አባል (6)፣

ቦምቦኮ ሴሲል (ፒ ኤች ዲ) የመካከለኛው አፍሪካ ክልላዊ ተወካይ እና የጴንጤቆስጤያዊ ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት ማህበር በአፍሪካ (APTEA) አባል (14፣ 32)

ቦምቦኮ ማርሴል (ፒ ኤች ዲ) የምዕራብ አፍሪካ ከፍተኛ የስነ-መለኮት ትምህርት ቤት ሊቀመንበር እና የቦርድ አባል ሎሜ፣ ቶጎ (14፣ 32)

ቺፓኦ ላውረንስ፣ (ፒ ኤች ዲ) የማላዊ ጉባኤ እግዚአብሔር ዩኒቨርስቲ የነገረ መለኮት ፋኩልቲ እና አገልግሎት ምስረታ ዲን ፣ (34)

ቸርችል፣ ቶድ በዲሞክራቲክ ኮንጎ የAGWM ሚስዮናዊ፣ የአፍሪካ ሆፐ (30)

ዳፐሊክስ አውንንቺስት ፒኤችዲ. በኮትዲቭዋር የጉባኤ እግዚአብሔር ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚዳንት፣ (10)

ጃኩቲ ሚትሪ የቶጎ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን ፕሬዚዳንት እና የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር ማኅበር የቀድሞ ፕሬዚዳንት (15).

ዱቤ አንድሪው (ፒኤችዲ.)የማላዊ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ፕረዚዳንት (11)

ፍሊንጃ ዱቲ ሰባኪ፣ (ፒኤችዲ) የምዕራብ አፍሪካ ከፍተኛ የስነመለኮት ትምህርት ቤት አካዳሚክ ዲን፣ ሎሜ፣ ቶጎ (27)

ፍሪምፖንግ-ማንሶ ፖል፣ (ፒኤችዲ) የጋና የጉባኤ እግዚአብሔር ጠቃላይ ተቆጣጣሪ (37)

ናንቹ ዲዛይር ቤቺ (ፒኤችዲ) የኮትዲቭዋር የጉባኤ እግዚአብሔር ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ ፕሬዚዳንት ፣ ቲዎሎጂካል እና የካታድጂ የመጋቢን ተቋም ዳይሬክተር፣ አይቮሪ ኮስ (23).

## አበርካቾች ዝርዝር

ኪቶቶ ፣ ዲና የፊሊፐ ኪቶቶ ባለቤት ኬንያ ጉባኤ እግዚአብሔር ጠቅላይ ተቆጣጣሪ (7)

ኪቶቶ ፣ ፊሊፐ ኬንያ ጉባኤ እግዚአብሔር ቻንስለር ጠቅላይ ተቆጣጣሪ ፣ KAG ምስራቅ ዩኒቨርሲቲ (7)

ኩዎ ጂሚ (ፒኤችዲ) ጉባኤ እግዚአብሔር ላይቤሪያ ጠቅላይ ተቆጣጣሪ ኤምሪተስ፣ የላይቤሪያ ጉባኤ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ፕሬዚደንት (21፣ 41)

ሌቤሎ ጎርደን (ፒኤችዲ) ደቡብ አፍሪካ የዓለም አቀፍ ጉባኤ እግዚአብሔር ጠቅላይ ፕሬዝዳንት ፣ (26)

ሉስያ፣ ኤንሰን፣ ዲሚን ምክትል ቻንስለር፣ የማላዊ ጉባኤ እግዚአብሔር ዩኒቨርሲቲ (28)

መባ፣ አርተር፣ ፒኤችዲ. የመጀመሪያ ምክትል ፕሬዝደንት ፣ ጉባኤ እግዚአብሔር ፣ ጋቦን (2፣ 18)

ምቢዋን ፣ ዳንኤል ጠቅላይ ተቆጣጣሪ፣ የሙሉ ወንጌል ተልዕኮ፣ ካሜሩን (25)

ሚለር፣ ዴንዚል አር.፣ ዲሚን AGWM ሚስዮናዊ ፤ ዳይሬክተር፣ የሐዋርያት ሥራ በአፍሪካ ተነሳሽነት አገልግሎት (1፣ 3፣ 8፣ 16፣ 20፣ 36)

ንሰምበ ሎየላ፣ እስራኤል። መጋቢ፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወንጌላዊ ማዕከል፣ ኪንሻሳ ፤ የቀድሞ ጉባኤ እግዚአብሔር ማህበር ጠቅላይ ተቆጣጣሪ፣ ፣ ዲሞክራቲክ ኮንጎ (22)

ንዳይሳባ ጀሮም። ፕረዚደንት፡ ቡሩንዲ ጉባኤ እግዚአብሔር ህብረት (24)

ኔልሰን፣ ጄፍሪ፣ ፒኤችዲ. AGWM ሚስዮናዊ ፤ የቀድሞ ምክትል ቻንስለር፣ KAG ምስራቅ ዩኒቨርሲቲ፣ ናይሮቢ፣ ኬንያ (5፣ 12፣ 39)

ንጋቦንዚዛ አማኑኤል። ሩዋንዳ ጴንጤቆስጤያዊ ጉባኤ እግዚአብሔር ምክትል ጠቅላይ ተቆጣጣሪ፣ (38)

ኒባ፣ ፊሊክስ (ፒኤችዲ ) ካሜሩን የውጭ ተልእኮዎች ዳይሬክተር የሙሉ ወንጌል ተልዕኮ (13)

ኦጋንያ ንጎዚ ሴሲሊያ፣ (ፒኤችዲ) በኤክስቴንሽን የስነ-መለኮት ትምህርት አስተባባሪ (TEE)፣ ጉባኤ እግዚአብሔር ሥነ መለኮትነት ትምህርት ቤት፣ ኡማሂያ፣ ናይጄሪያ (17)።

ሳዋዶጎ ጄፍቴ፣ (ዲሚን) ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የቡርኪናፋሶ ጉባኤ የእግዚአብሔር ፤ ዳይሬክተር፣ የኩብሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት (4፣ 42)።

ሴባስቲአኦ ፍራንሲስኮ የአንጎላ ጉባኤ የእግዚአብሔር ፕሬዝዳንት፣ (9)

ስሚዝ፣ በርናርድ፣ ኤም.ኤ. የAGWM ሚስዮናዊ በቶጎ (15)

ስዋይ፣ ሮን ጠቅላላ ገንዘብ ያዥ፣ የታንዛኒያ ጉባኤ የእግዚአብሔር ፤ (35)

ተርኒ ማርክ ኤም.ኤ. AGWM ሚስዮናዊ ፤ ምዕራብ አፍሪካ ከፍተኛ የስነ-መለኮት ትምህርት ቤትፕሬዝዳንት ፣ ሎሜ፣ ቶጎ (19)

ዋት ሲ. ፒተር፣ (ኤች.ዲ.)በደቡብ አፍሪካ ጉባኤ የእግዚአብሔር ሊቀመንበር 31)

# መቅድም በራንደል ታር

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ ለሚቀጥሉት አመታት ለአፍሪካ መጋቢያን ጠቃሚ ግብአት ሆኖ እንደሚያገለግል ተስፋ የተጣለበት መጽሀፍ ነው። የአፍሪካ ቤተክርስቲያን ለረጅም ጊዜ የአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች በልዩ ሁኔታ የሚዳስስ ጽሁፍ ስትፈልግ ኖራለች።

በዚህ ሥራ ዶ/ር ዴንዚል አር ሚለር እና የአርታኢ ቡድኑ ዶ/ር ጄፍሬሪ ኔልሰን እና ቶድ ቸርችል በእውነት አስደናቂ በሆነ መልኩ የዘመናችንን የአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ጉዳዮችን የሚዳስሱ የአፍሪካ መሪዎቸን ሥራ አሰባስበዋል። "የአበርካቾች ዝርዝር" እንደሚያመለክተው እነዚህ የቤተዕምነት መሪዎች፣ መሪ መጋቢዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች እና ሴሚናሪየም አስተዳዳሪዎች እና አስተማሪዎች፣ የተልእኮ መሪዎች፣ የቤተ ክርስቲያን ተወካዮች፣ ወንጌላውያን፣ እና ሌሎችም አካቶአል።

የእነዚህ መሪዎች የዳበረ ልምድ እና እውቀት ለዚህ ሥራ ትልቅ እሴት ጨምሮአል። ከእነዚህ ወገኖች እና መሪዎች ጋር እንዳገለገለ ሰው እኔ በግሌ እንደ መሪ ታማኝነታቸውን፣ ለክርስቶስ እና ለተልእኮው ያላቸውን ፍቅር እና በሁሉም የአፍሪካ ጥግ ቤተ ክርስቲያንን ተተክሎ ለማየት ያላቸውን ፍላጎት ማረጋገጥ እችላለሁ። በተጨማሪም የአርታዒ ቡድኑ ራሱ ስለ አፍሪካ እና ህዝቦቿ የሚያወሱ በርካታ እውቀት እዚህ መጽሐፍ ውስጥ አካቷል። እያንዳንዳቸው ለብዙ ዓመታት በደቡብ፣ በምስራቅ ወይም በመካከለኛው አፍሪካ ሚስዮናዊ በመሆን አገልግለዋል።

ይህ መጽሐፍ በመላ አፍሪካ የሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በመምራት ላይ የሚገኙትን መሪዎችን አገልግሎት እንደሚያጠናክር ተስፋ ተጥሎበታል። እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እና የኤክስቴንሽን ሥልጠና ፕሮግራሞች የሚመሩ ብሎም የወደፊት አገልግሎት በመዘጋጀት ላይ ያሉት ጨምሮ እንደሚረዳ ይታመናል። መጽሐፉ አንድ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አገልግሎቱ እንዲሳካ እና ዘላቂ የሆነ ፍሬ እንዲያፈራ በሚያግዙ ተግባራዊ በሆኑ ምሳሌዎች የተሞላ መጽሐፍ ነው።

የዚህ መጽሐፍ አንዱ የተለየ ግብና ትኩረት በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ ወንድ ወይም ሴት መጋቢያን በሥነ ምግባር ተምሳሌት እንዲሆኑ ለማገዝ ነው። ሌላው አስፈላጊ አጽንዖት አንድ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሁል ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንደሚያስፈልገው ለማሳሰብ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በአፍሪካ ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች ወንጌልን ለመስማት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እምነት እንዲመጡ እድል እንዲሰጣቸው ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር በተሰጠው ተልዕኮ ላይ ትኩረት እንድታደርግ የሚረዳ መጽሐፍ ነው።

“የብልጽግና ወንጌል” እየተባለ የሚጠራው በአፍሪካ ውስጥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ከእግዚአብሔር ተልእኮ ወደ ግላዊ በረከት ፍለጋ እየመራ ባለበት ጊዜ ፣ የዚህን መጽሐፍ ጠንካራ የእግዚብሔር ተልእኮ ላይ ትኩረት ማድረጉን ማየት አበረታች ነው። የዚህ መጽሐፍ አስተዋጽዖ አበርካቾች የቃሉ እውነተኛ ፈጻሚዎች፣ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች እና የክርስቶስን ታላቅ ተልዕኮ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ አተኩረው ለመኖር የሚፈልጉ ናቸው።

ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት ከአፍሪካ ቤተክርስቲያን ጋር ሰርቻለሁ፡፡ ከመጀመሪያም ከልጅነቴ ጀምሮ እድገቴ አፍሪካ ውስጥ ነው፡፡ ካደኩ በሓላም በምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ከ35 ዓመታት በላይ

## መቅድም በራንደል ታር

በሚስዮናዊነት በማገልገል ኑሬአለሁ። በየትኛውንም ዋጋ በመክፈል የጠፉትን ለማዳን ሕይወታቸውን በቀደሱ በሺዎች በሚቆጠሩ አፍሪካውያን ወንዶችና ሴቶች እግዚአብሔር ያደረገውን ማየት እጅግ አስደናቂ ነው። ይህ መጽሐፍ ውጤታማነታቸውን ለማሳደግ እንደሚረዳ አምናለሁ። ጸሎቴ ይህ መጽሐፍ በሺዎች በሚቆጠሩ መጋቢያን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እጅ በአፍሪካ ውስጥ ሲገባ ማየት እና የእግዚአብሔር መንግስት በአህጉሪቱ በላቀ መንገድ ሲሰፋ ማየት ነው።

በመንፈስ የታጠቁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የሰለጠኑ መሪዎች በእውነት የአፍሪካ ተስፋ ናቸው።

~ መጋቢ ራንዴል ታር
የአፍሪካ ሆፕ ዋና ዳይሬክተ

# መቅድም በዶ/ር በርናባስ ምቶከምባል

በአፍሪካ ያሉ አብዛኞቹ የጴንጤቆስጤ ፓስተሮች ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን ሲጽፍ የነበረውን የአዕምሮ ሁኔታ መለየት ይችላሉ።

> ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ። የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው(2ቆሮ. 11:26-28)።

የግል ሁኔታቸው ከጳውሎስ ሊለያይ ቢችልም፣ አብዛኞቹ በአፍሪካ ያሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን "በሁሉም በኩል መጨነቅ" የሚለውን ስሜት ሊረዱት ይችላሉ (4፡8)።

በአፍሪካ ካሉት ሙያዎች ቤተክርስቲያንን በመጋቢነት ከማገልገል በላይ የሚፈትኑ ሙያዎች ቢኖሩም ጥቂት ናቸው። አንድ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ብቃቱን የሚጠይቁ በርካታ የህይወት እና የአገልግሎት ዘርፎችን አስቡ። መጋቢያኑ የእግዚአብሔርን መንጋ በብቃት መንከባከብ፣ እንዲሁም የራሳቸውን የግል እና የቤተሰብ ጉዳዮች መምራት መቻል አለባቸው። መጋቢያኑ ብቁ ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎች፣ አማካሪዎች እና አስተዳዳሪዎች መሆን አለባቸው። እናም ይህንን ሁሉ እያደረጉ አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት ለማድረግ የተሰጠውን የጌታችንን ትእዛዝ በመፈጸም ቤተ ክርስቲያናቸውን መምራት መቻል አለባቸው። ዝርዝሩ ሊቀጥል ይችላል። ለዚህ ነው የዚህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ መምጣት በጣም እጅግ አስፈላጊ የሆነው።

ለረጅም ጊዜ ከአፍሪካዊ እና ከጴንጤቆስጤያዊ እይታ አንጻር የተጻፈ አጠቃላይ የመጋቢ መመሪያ እንደሚያስፈልግ አምን ነበር። በመሆኑም የአፍሪካ ሆፕ ላደረገው ስራ በጣም አመስጋኝ ነኝ። በተለይ አበረታች የሆነው ደግሞ ይህ ማኑዋል የተፃፈው ከአህጉሪቱ በተውጣጡ በሳል የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እና መሪዎች በመሆኑ ድስ ብሎኛል። መመሪያው ከሥነ-መለኮት አኳያ ጤናማ፣ በሚስዮን ላይ ያተኮረ እና በተግባራዊ መልኩ ጠቃሚ ነው። ይህ ማኑዋል ስለ ጴንጠቆስጤ ህይወት እና አገልግሎት የከበረ ግንዛቤዎችን ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ይሰጣል። በአህጉሪቱ የሚገኙ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያንን ወደ በለጠ ውጤታማ አገልግሎት ለመምራት ይረዳል። አስቀድሞ የመጋቢዎቻችንን ግንዛቤ በማጠናከር የሚመሩትን አብያተ ክርስቲያናት ይደግፋል።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ ከ2021 እስከ 2030 "አስርት የሪቫይቫል ዓመታት" ለተባው የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር (AAGA) አጽንዖት በተለየ ጠቃሚ እንደሚሆን እጠብቃለሁ። በእነዚህ አሥር ዓመታት ውስጥ በመላው አፍሪካ የሚገኙ የጉባኤ እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ጌታ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በቤተክርስቲያን ላይ እንዲያፈስ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ራሳቸውን ሰጥተዋል፣ ይህም በአፍሪካ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ መነቃቃትን እያስገኘ አለ፤ ይህም ከክርስቶስ መምጣት በፊት አማኞች ወንጌልን ወደ እያንዳንዱ ነገድ፣ ሀገር እና ሕዝቦች እንዲወስዱ ያስችለቸዋል።

## መቅድም በዶ/ር. በርናባስ ምቶከምባል

አስርት የሪቫይቫል ዓመታት ውስጥ በተለይም በሰሜን አፍሪካ እና በአፍሪካ ቀንድ የጉባኤ እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ቅዱስ በመታጠቅ፣ እግዚአብሔርን በመምሰል፣ የደቀ መዝሙርነት ስልጠና፣ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ባህል ዘለል ተልእኮዎች ላይ ያተኩራሉ ተብሎ ይታሰባል። እኔ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ማኑዋል ታላቁን ተልእኮ ለመወጣት መጋቢያን ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲመሩ በመርዳት በዋጋ ሊተመን የማይችል መሳሪያ ሆኖ እንደሚደግፍ አምናለሁ። ጌታ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ መጽሐፉ ለብዙ አመታት በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተክርስቲያንን መጋቢያንን መጥቀሙን ይቀጥላል።

በመላው አፍሪካ ለሚገኙ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢዎች እና አገልጋዮች ይህን መጽሐፍ እንዲጠቀሙበት በደስታ እመክራለሁ።

~ ዶክተር በርናባስ ምቶከምባሊ
የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር ማሕበር ሊቀመንበር

# መግቢያ

በአፍሪካ ያለች ቤተ ክርስቲያን እንዴት እያደገች እንዳለች በመጥቀስ አንድ የአፍሪካ መሪ የሚከተለውን ተናግሮአል "እግዚአብሔር የአፍሪካን ቤተ ክርስቲያን እየባረከ ያለው የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን አሕዛብን ትባርክ ዘንድ ነው!" እኛ በአፍሪካ ሆፐ የሐዋርያት ሥራ 1፡8 ተነሳሽነት በዚህ ሃሳብ በሙሉ ልብ እንስማማለን። እግዚአብሔር የአፍሪካን ቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የጠራት ለእንደዚህ አይነት ጊዜ እንደሆነ እናምናለን (አስቴር 4፡14) ፤ በአፍሪካ ያለችው ጴንጤቆስጤያዊ ቤተክርስቲያን ታላቅ ሚስዮናዊ ጥሪ አላት። በዘመኑ መጨረሻ የመከሩ ጌታ ከሰማይ ከመመለሱ በፊት ታላቁን ተልእኮ ለመፈጸም በሙላት ይሳተፉ ዘንድ ኃይል ለማስታጠቅ መንፈሱን በህዝቡ ላይ እያፈሰሰ ነው (ማቴ. 24፡14፤ ሐዋ. 1፡8-11)።

ይህንን ለማድረግ የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ መሆን አለባት። ጠንካራ ለመሆን ደግሞ ፣ ጠንካራ አመራር ሊኖራት ይገባል። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ የተዘጋጀው ይህንን ፍላጎት ለማሟላት ነው። ማኑዋሉ በአፍሪካ ያሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን ዓላማ ለመፈጸም የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማስታጠቅ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የእኛ ልባዊ ተስፋ ይህ መጽሐፍ በመላው አህጉር በሚገኙ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እጅ ውስጥ የሚገኝ ውድ መሣሪያ ይሆናል የሚል ነው። ማኑዋሉ ስድስት የመምሪያ መርሆችን በማሰብ ተዘጋጅቷል፡-

**1. በአመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።** የዚህ ማኑዋል ጸሐፍት እና አዘጋጆች መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በጥብቅ ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ለሕይወት እና ለተልእኮ የክርስቲያኖች ሁሉ በቂ መመሪያ ነው። ስለዚህ የመጽሐፉ አዘጋጆች በዚህ ማኑዋል ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ፅንሰ-ሀሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ በጥብቅ መመስረት አለበት ብለው ያምናሉ።

**2, በአጽንዖት ጴንጤቆስጤያዊያዊ ነው።** መጽሐፉ የተጻፈው በጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ነው። ማኑዋሉ ያለምንም ማመንታት የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያንን ልዩ ስጋቶች ከጴንጤቆስጤያዊ እይታ አንጻር ለመፍታት ያለመ ነው። የመጽሐፉ አስተዋፅዖ አድራጊዎችም የተረጋገጠ አገልግሎት ያላቸው በሳል የጴንጤቆስጤያዊ መሪዎች ናቸው። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባላቸው ልምምድ እና በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ባላቸው ግንዛቤ፣ እነዚህ ወንዶች እና ሴቶች አገልጋዮች የጴንጤቆስጤያዊ ህይወት እና አገልግሎት አቀራረብን በልዩ ሁኔታ ተቀብለዋል። በመሆኑም ይህ አመለካከት በዚህ ማኑዋ ውስጥ ተንጸባርቆአል።

**3. በትኩረት ሚስዮናዊ ነው።** የዚህ ማኑዋል አዘጋጆች ክርስቶስ እያንዳንዱን የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እና ቤተ ክርስትያን በእግዚአብሔር ተልእኮ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ አዟል ብለው ያምናሉ።

የእግዚአብሔር ተልእኮ ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት በምድር ላይ ካሉ ነገዶች፣ ቋንቋዎች እና አሕዛብ ሁሉ ሰዎችን መዋጀት እና ወደ ራሱ መጥራት ነው (ማቴ. 24:14፤ ራዕ. 5:9)። ክርስቶስ በታላቁ ተልዕኮው የእግዚአብሔርን ተልእኮ ጠቅለል አድርጎ ገልጿል (ማቴ. 28፡18-20፤ ማር. 16፡15-17፤ ሉቃስ 24፡47-49፤

ዮሐንስ 20፡21-22፣ ሐዋ. 1፡8)። ይህ ሚስዮናዊ አጽንዖት በመጽሐፉ ውስጥ በስፋት ትኩረት ተሰጥቶታል።

**4. በአውዳዊነቱ አፍሪካዊ ነው።።** የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ የተጻፈው በአፍሪካ ላሉ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ናቸው። ፀሃፊዎቹ አፍሪካውያን መጋቢያን አገልግሎቶቻቸውን በተለየ አፍሪካዊ ሁኔታ እንደሚያከናውኑ እና ይህን የሚያደርጉት በአፍሪካ በተለመዱ ተግዳሮቶች እና ስጋቶች ውስጥ መሆኑን ይረዳሉ። እያንዳንዱ ምዕራፍ የተፃፈው ይህንን አውድ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

**5. በስፋቱ ሁሉን አቀፍ ነው።** ይህ መጽሐፍ አሁን ባለንበት ጊዜ በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ያጋጠሟቸውን በርካታ ጉዳዮች ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። አዘጋጆቹ መጽሐፉ በአህጉሪቱ ውስጥ ባሉ መጋቢዎች እጅ ውስጥ እጅግ የሚፈለግ ግብአት እንደሚሆን ተስፋ ያደርጋሉ።

**6. ትግበራን ታስቦ የተዘጋጀ ነው።** ይህ ማኑዋል የመጋቢያዊ ሥነ-መለኮትን እና ንድፈ-ሐሳብን የሚመለከት ቢሆንም እዚህ ውስጥ የሚሰጡት ትምህርቶች በጣም ተግባራዊ እንዲሆኑ ታልመው የተዘጋጁም ናቸው። የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢያን ምን ማድረግ እንዳለበት እና ለምን ይህን ማድረግ እንዳለበት ብቻ ሳይሆን አገልግሎቶቻቸውን በብቃት እንዴት ማከናወን እንደሚችሉ የበለጠ ያብራራል።

## የጹሑፍ ሂደቱ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መመሪያ በመጀመሪያ የታለመው በዶ/ር ጆን ኢስተር የአፍሪካ ሆፐ ዋና ዳይሬክተር ነበር። ዶ/ር ጆን ይህንን ማኑዋል እንዲያዘጋጁ የሥራ ኮሚቴ በመሰየም ለስራው መሰረት ጣሉ። በኃላም ዶ/ር ኢስተር በመጋቢ ራንዲ ታር ሲተኩ የአገልግሎቱ አዲሱ ዳይሬክተር ፕሮጀክቱን በሙሉ ልብ በመቀበል አስቀጠሉት።

የኮሚቴው የመጀመሪያ ተግባር መጽሐፉ የሚያብራራባቸውን ርእሶች አጠቃላይ ዝርዝር ማጠናቀር ነበር። ይህ ሰፊ ጥናትና የብዙ ሰአታት ግልጽ ውይይትን ያካተተ ትልቅ ስራ ነበር። የርዕሰ ጉዳዮቹ ዝርዝርም ከአህጉሪቱ በተውጣጡ ቁልፍ የአፍሪካ መሪዎች እና አስተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጥበት ተደረገ። በመጨረሻም የዚህ መጽሐፍ ምዕራፎች የሆኑት አርባ ሁለቱ ርዕሶች ተመረጡ። የምዕራፍ ርእሰ ጉዳዮች ከተወሰነ በኋላ ኮሚቴው እነዚህ ምዕፎች በአሥር አብይ ርዕሶች እንዲከፈሉ በመወሰኑ የመጽሐፉ አሥር ክፍሎች ያሉት እንዲሆን ተደረገ።

የትኞቹ ርዕሶች እንደሚሸፈኑ እና የት እንደሚገኙ እና በመጽሐፉ ውስጥ የት እንደሚካተቱ ከወሰንን በኋላ፣ ኮሚቴው የተለያዩ ምዕራፎችን እንዲጽፉ ከአፍሪካ ቁልፍ የሆኑ የጉባኤ እግዚአብሔርን መጋቢያን፣ አስተማሪዎች እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መረጠ። በአፍሪካ ብዙ የኖሩ እና ያገለገሉ ጥቂት አሜሪካውያን ሚስዮናውያንም እንዲጽፉ ተጋበዙ። የእነዚህ ፀሐፊዎች ስም ከእያንዳንዳቸው አጭር የሕይወት ታሪክ ንድፍ ጋር በመጽሐፉ ፊት ለፊት ባለው " አበርካቾች ዝርዝር" ውስጥ ይገኛል።

ጸሐፊዎቹ ሥራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ጹሁፋቸውን ለኮሚቴው ለግምገማ እና አርትዖት አቅርበዋል። ከዚያም ኮሚቴው ይዘትን እና ከሌሎች ምዕራፎች ጋር ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ እያንዳንዱን ምዕራፍ መርምሯል። የኮሚቴው ግብም እያንዳንዱ ምዕራፍ ለጴንጤቆስጤ እና ለመጽሐፉ ሚስዮናዊ ዓላማ አስተዋጾ ማበርከቱን እና የአጻጻፍ ስልቱ በስራው ውስጥ ወጥነት ያለው ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ ነበር። የአርትዖት ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ምዕራፉ በመጽሐፉ ውስጥ ተካቷል

## የተወላጠ ስም አጠቃቀም

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያንን ሲጠቅስ “እርሱ ወይም እርሷ” ስለሚለው ሐረግ አጠቃቀም ጥቂት መባል አለበት። ይህ አጠቃቀም የተመረጠው በመላው አፍሪካ በሚገኙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣው የሴት መጋቢያን አገልግሎታቸው የተከበረ እና ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንዲያውቁ ነው።

የጴንጤቆስጤያዊ ንቅናቄ ገና ከጅምሩ ለሴቶችን አገልግሎት ከፍተኛ ቦታ የሰጠ ነበር። ጴንጤቆስጤያዊያን ወንዶችን ለአገልግሎት ብቁ የሚያደርገው ያው መንፈስ ሴቶችንም ብቁ እንደሚያደርግ ያምናል። ይህንንም እምነት በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ ባለው በኢየሱስ ንግግር ላይ ይመሰርታሉ፤ በዚህ ክፍል ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ለሁሉም አማኞች ማለትም ለወንዶችም ለሴቶችም እንደሆነ የገለጠበት ክፍል ነው። ሴቶችንም ጨምሮ መንፈስን የሚቀበል ሁሉ ፣ ስለ ክርስቶስ ለመመስከር ኃይልን ይቀበላል። ይህ ምስክርነት የወንጌል አዋጅን  የሚጨምር ነው።

ጴንጤቆስጢያዊያን ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ዕለት የጠቀሰውን የነቢዩ ኢዩኤልን ተስፋ ይጠቅሳሉ፤ “በመጨረሻው ዘመን፣ እግዚአብሔር፣ መንፈሴን በሰው ሁሉ ላይ አፈሳለሁ ይላል። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ… በዚያም ወራት በባሪያዎቼ በወንዶችና በሴቶች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ። -29)። ጴንጤቆስጢያዊያን ይህንን ቃል በዚህ “የመንፈስ ዘመን” እግዚአብሔር መንፈሱን በሰዎች ሁሉ ላይ በሚያፈስስበት በዚህ ጊዜ ሊታመኑበት እና ሊተገበሩ እንደሚገባ እንደ ዓለም አቀፋዊ መርሆ ይወስዱታል።

በታሪክ፣ በእንግሊዝኛ የሚጽፉ ሰዎች ለወንዶችም ለሴቶችም ሲናገሩ በአጠቃላይ “እርሱ” የሚለውን ተውላጠ ስም ተጠቅመዋል። ግራ መጋባትን ለማስወገድ የዚህ ማኑዋል አዘጋጆች የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያንን ሲጠቅሱ “እርሱ ወይም እርሷ” የሚሉትን ሁሉን አቀፍ ቃላት ለመጠቀም መርጠዋል። ለንባብ አመቺ እንዲሆን፣ “እነርሱ” የሚለው የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም አንዳንድ ጊዜ ነጠላውን “እርሱ” ወይም “እርሷን” ምትክ አድርጎ መጠቀምን ይጠይቃል። ይህ በዛሬው ጊዜ በእንግሊዝ ጸሐፍት ዘንድ በሰፊው ተቀባይነት ያለው አሠራር ሲሆን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው የአዲሲቱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፣ 2011 እትምን አካሄድ በመከተል ነው።

## ይህንን መጽሐፍ እንዴት መጠቀም ይቻላል

ስሙ እንደሚያመለክተው፣ ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው እንደ መመሪያ ነው፣ ወይም በአፍሪካ ውስጥ ላሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የአገልገሎት መመሪያነት እንዲውል ታስቦ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉን በተለያዩ ጠቃሚ መንገዶች መጠቀም ይቻላል። በመጀመሪያ መጽሐፉን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ማንበብ ያስፈልጋል። መጽሐፉን ሙሉ በሙሉ ማንበብ በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጹትን ጽንሰ-ሐሳቦች ሰፋ ያለ እይታ እንዲኖረን ያደርጋል። እንዲሁም በአፍሪካ ውስጥ ስላለው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ባለ ብዙ ገፅታ ስራ ሰፊ ግንዛቤን ይፈጥራል።

መጽሐፉን በምታነብበት ጊዜ፣ ያስተዋልካቸው እና በተለይም ለራስህ ህይወት እና አገልግሎት የሚጠቅሙ ግንዛቤዎችን ለመጻፍ እንዲቻል እስክሪብቶ እና ማስታወሻ ደብተር  መያዝ ይኖርብሃል። እንዲሁም በርዕሱ ላይ የግል ሃሳቦችህን መጻፍ ያስፈልጋል። አሁን በአገልግሎት ላይ እየከወንክ ባለህበት መንገድ ላይ ልታደርጋቸው የሚገቡ አንዳንድ ማሻሻያዎችን ልብ ማለትም ያስፈልጋል:: በመጨረሻም፣ እና ከሁሉም በላይ፣ ስታነብ፣ የመንፈስን ድምጽ ማዳመጥ ያስፈልጋል። ከዚያ ማስታወሻ ደብተርህን እንደ የጸሎት መመሪያ እና እንደ ፍኖተ ካርታ ለግል እና ለአገልግሎት እድገት መጠቀም ትችላለህ።

መግቢያ

መጋቢዎች ይህንን ማኑዋል እንደ ማመሳከሪያ ስራ መጠቀምም ይችላሉ። እንደ ሰርግ፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ የምክር ክፍለ ጊዜ፣ የአመራር ስብሰባ ወይም ሌላ ዝግጅት ያሉ ልዩ አጋጣሚዎች ሲቀርቡ፣ አዳዲስ ግንዛቤዎችን እና አጋዥ መመሪያዎችን ለማግኘት ተገቢውን ምዕራፍ ወይም ምዕራፎችን መከለስ ይችላሉ። ወይም አንድ አሳሳቢ ችግር ለመፍታት እርዳታ በሚፈልጉበት  ጊዜ ወይም በአዲስ አገልግሎት ሲገጥማቸው ይህን ችግር የሚዳስሱ ምዕራፎች ለማግኘት የርዕስ ማውጫውን ላይ ያለውን ዝርዝር በመመልከት ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ርእሶች መዳሰስ ይችላሉ።

በመጨረሻም፣ ይህ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች እና ሴሚናሮች ውስጥ ባሉ አስተማሪዎች እንደ መማሪያ መጽሐፍ ወይም እንደ ተጨማሪ ንባብ ለመጋቢ አገልግሎት ክፍል ሊጠቀሙበት ይችላሉ። መጽሐፉ በተለይ ለአጭር ጊዜ ስልጠና ለሚሠጡ ትምህርት ቤቶች እንደ ስርጭት ጣቢያዎች ወይም የቤተክርስቲያን ተከላ ትምህርት ቤቶች ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ እኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ማኑዋል ማኔጂንግ ኮሚቴ ይህንን ስራ የአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እንዲጠቀሙበት እንመክራለን። ጸሎታችን እግዚአብሔር አፍሪካውያን መጋቢያንን ለመጪዎቹ አስርት ዓመታት እንዲባርክ፣ እንዲጠቀምባቸው እና ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን መንግሥት በአፍሪካ ለማስፋፋት እና በአፍሪካ ቤተክርስቲያን በኩል አሕዛብን ወደ እርሱ መንግስት ለማፍለስ  ጠቃሚ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ነው።

በአክብሮት
~ ዶ/ር ዴንዚል አር ሚለር፤  አርታኢ
~ ዶ/ር ጄፍሪ ኔልሰን ፤ ተባባሪ አርታኢ
~ መጋቢ ቶድ ቸርችል፤ ተባባሪ አርታኢ

# ~ ክፍል 1 ~

# የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ ብቃቶች

# ~ ምዕራፍ 1 ~

# ልምድ ያለው ሰው

በታዋቂው ዩኒቨርሲቲ ሕክምናን የተማረ ሰው በዓይነ ሕሊናህ ይታይህ። ይህ ሰው ጥሩ የሚባል ትምህርት ቤት በቀዶ ጥገና የተማረ እና በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ምርጥ መጽሃፎችን ያነበበ ሰው ነው። ነገር ግን ይህ ሰው  ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት ቀዶ ጥገና አድርጎ አያውቅም። ታዲያ ይህ ሰው ቀዶ ጥገና እንዲያደርግህ ትፈልጋለህ? በጭራሽ! አንድ ሰው የቀዶ ጥገና ሐኪም ለመሆን የሚፈልግ ከሆነ ልምድ ባለው የቀዶ ጥገና ሐኪም ስር ብዙ ቀዶ ጥገናዎችን በማድረግ ተግባራዊ ልምድ ማግኘት አለበት።

በተመሳሳይ መልኩ፤ አንድ ሰው ወደ መጋቢነት አገልግሎት ከመግባቱ በፊት እርሱ ወይም እርሷ ልምድ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ይህ ልምድ መንፈሳዊ እና ተግባራዊ መሆን አለበት። በዚህ ምዕራፍ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚያስፈልገውን ልምድ እንጠቁማለን።

## መንፈሳዊ ልምምድ

ለማንኛውም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ልምምድ አስፈላጊ መነሻው ነው። ከሁሉም በላይ እርሱ ወይም እርሷ ከክርስቶስ ጋር ጥልቅ ግላዊ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል። ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሲመርጥ፣ “ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ” አድርጓል (ማርቆስ 3፡14)። ከእርሱ ጋር ሲራመዱ እና ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ እርሱን እንደሚመስሉ ያውቅ ነበር። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- “ነገር ግን በሚገባ የተማረ ሰው ሁሉ እንደ መምህሩ ይሆናል” (ሉቃስ 6፡40)። ይህ አባባል ዛሬም ለኛ ተመሳሳይ መልእክት አለው፡፡ ከክርስቶስ ጋር ጊዜያችንን በቃሉ እና በጸሎት ስናሳልፍ እርሱን እንመስላለን(2ቆሮ. 3፡18)። እርሱን ከማገልገላችን በፊት፣ እርሱን መምሰል አለብን፤ እርሱን ለመምሰልከእርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ አለብን።

የጴንጤቆስጤያዊ እንቅስቃሴ የተመሰረተው የዛሬዎቹ አማኞች በአዲስ ኪዳን ሐዋርያት እና ሌሎች ደቀ መዛሙርት እንዳደረጉት ህይወትን የሚቀይር መንፈሳዊ ልምምዶች ሊኖራቸው እንደሚችል በማመን

ነው። ጴንጤቆስጤያዊዊያን እንደሚያስተምሩት ትክክለኛ ትምህርት አስፈላጊ ቢሆንም ትምህርት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ከምንም በላይ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ሊኖረው ያስፈልጋል። እንደዚህ አይነት ግንኙነት አለመኖር ከአገልግሎት ብቃት ያወርዳል፡፡ ይህ ግንኙነት በመንፈሳዊ ልምምድ የሚመሰረት ልምምድ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌሎችን የሚያገለግሉ ሰዎች አስቀድመው እግዚአብሔርን በመገናኘት ጉዟቸውን የጀመሩ ናቸው። አብርሃም የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማ (ዘፍ. 12፡1-3)። ሙሴ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ እግዚአብሔርን አገኘው (ዘፀ. 3፡1-4)። ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በቤተ መቅደሱ ከፍ ከፍ ብሎ አየው (ኢሳ. 6፡1-5)። ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሱስ ጋር አብረው ተጓዙ (ማር 3፡13-14)። ጳውሎስም ከሞት የተነሳውን ክርስቶስን በደማስቆ መንገድ አገኘው (ሐዋ. 9፡1-5)።

በተመሳሳይ መልኩ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መሆን የሚፈልግ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አራት አስፈላጊ ግንኙነቶች ሊኖሩት ይገባል፡-

## አዲስ ልደት

ኒቆዲሞስ የሃይማኖት መሪ ነበር። እርሱ ወግ አጥባቂ ፈሪሳዊ እና የአይሁድ ገዥ ምክር ቤት አባል የነበረ ሰው ነው ። ከእነዚህ መስፈርቶች ግን አንዳቸውም ቢሆኑ በቂ አልነበሩም። ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ "ዳግመኛ መወለድ አለብህ" (ዮሐንስ 3፡7) አለው። ኢየሱስ ኒቆዲሞስ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት "መግባት" እንደማይችል ወይም "ተካፋይ መሆን እንደማይችል" ነገረው (ቁ. 3-5)።

እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በእውነት ዳግም መወለድ አለበት። እርሱ ወይም እርሷ በሕይወታቸው ውስጥ ኢየሱስን ያገኙበትን፣ ከኃጢአታቸው ንስሐ የገቡበትን እና እንደ ጌታቸው እና አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉበትን ጊዜ መመስከር መቻል አለባቸው። በዚያን ጊዜ ነው ኢየሱስ በሕይወታቸው ዙፋን ላይ ትክክለኛ ቦታ ያገኘው፣ እናም እንደገና የተወለዱት። ጳውሎስ "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል (2 ቆር. 5፡17፣ )።

ዳግመኛ ተወልደሃልን? ማንነትህ ከውስጥ ወደ ውጭ ተለውጧልን? ካልሆነ፣ ይህ አሁን ማድረግ ትችላለህ። ይህ የሚሆነውም ከኃጢአታችን ስንመለስ እና እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን ስንጸልይ ነው። ለድነት በክርስቶስ ላይ ብቻ ሙሉ እምነት ይኑርህ እና የህይወትህ ጌታ ትክክለኛ ቦታውን እንዲወስድ ጋብዘው። ክርስቶስን እንደ አዳኝህ ለመቀበል፣ በሙሉ ልብህ እመን፣ እናም ይህን ጸሎት በቅንነት ጸልይ፡-

"ኢየሱስ ሆይ፣ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የዓለም አዳኝ እንደሆንክ በእውነት አምናለሁ። ለኃጢአቴ እንደሞትክና እንደ ተነሣህ አምናለሁ። ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ፣ እና ባንተ ካለ እምነት በስተቀር፣ ለዘለአለም የጠፋሁ እንደሆንኩ አውቃለሁ። እባክህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ እና አዳኜ እና ጌታዬ ሁን። አሁን አንተን ለመከተል ሁሉንም እተዋለሁ። በሕይወቴ ዘመን ሁሉ አገለግልሃለሁ። ወደ ልቤ ግባ እና የህይወቴ ጌታ ሁን። በስምህ እጸልያለሁ። አሜን።

## በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ ጥቂት ቀደም ብሎ ደቀ መዛሙርቱን "ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በከተማው ቆዩ" ብሎ አዘዛቸው (ሉቃስ 24፡19)። በመንፈስ ቅዱስም እስኪጠመቁ ድረስ በኢየሩሳሌም ይጠብቁ ነበር (ሐዋ 1፡4)። እነዚህ ሰዎች እንደገና ተወልደዋል። የኢየሱስን ትምህርት በእግሩ ስር

ተቀምጠው ተምረዋል፣ ተአምራቱንም አይተዋል። በዓለም ሁሉ ወንጌልን እንዲሰብኩ አዟቸው የነበር ቢሆንም በወቅቱ ዝግጁ አልነበሩም።

ኢየሱስ እንዲሰሩት የሰጣቸው ተግባር በራሳቸው ጉልበት ሊሠሩት ከሚችሉት በላይ ትልቅ ነበር። በእግዚአብሔር ኃይል መሞላት ነበረባቸው። በመሆኑም ኢየሱስ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" የሚል ተስፋን ሰጣቸው (ሐዋ. 1፡8)፡፡

መንፈስ በመጀመሪያ በደቀ መዛሙርቱ ላይ መጣ እና በጴንጤቆስጤ ቀን ሞላባቸው። በዚያ ቅጽበት፣ በልሳኖች ተናገሩ እናም ጠንካራ ተቃውሞ ቢገጥማቸውም ክርስቶስን በብቃት ለማወጅ የሚያስፈልጋቸውን ኃይል እና ድፍረት ተቀበሉ። በተመሳሳይ መልኩ በአገልግሎት የጌታን መመሪያ መከተል የሚፈልግ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አለበት።

ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንዴት መጠመቅ እንደምንችል ነግሮናል። እርሱም "የሰማይ አባት ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን ይሰጣል!" ሲል ቃል ገብቶል። (ሉቃስ 11፡13)። በመሆኑም ማንም ሰው በቀላሉ በእምነት በመጠየቅ የመንፈስን ኃይል መቀበል ይችላል። ይህ ጥያቄ ታዲያ ሶስት ቀላል የእምነት ደረጃዎችን ያካትታል፡-

1. **በእምነት ጠይቅ።** እግዚአብሔርን መንፈሱን እንዲሰጥህ በመጠየቅ ጀምር። ኢየሱስ ስለ መንፈስ ስጦታ ሲናገር፣ "ለምኑ ይሰጣችሁማል። ፈልጉ ታገኙማላችሁ ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል" (ሉቃስ 11፡9)። ስትጠይቅ፣ እግዚአብሔር ጸሎትህን እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ እመን፤ በለመንከውም ሰአት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላህ እመን። ልብህን ለእግዚአብሔር አስፉ እና መንፈስ በእናንተ ላይ እንደሚመጣ ተረዳ። መንፈስ ቅድስን ስራ በግል ህይወታችን መለማመድ ከጀመርን በኋላ፣ ሁለተኛውን የእምነት እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ እንደሆናለን።

2. **በእምነት ተቀበ**ል። ኢየሱስ በመቀጠል "የሚለምን ሁሉ ይቀበላል" በማለት ቃል ገብቷል (ሉቃስ 11፡10) በሌላ ጊዜም "በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" (ማር. 11፡24) በማለት አስተምሯል። እግዚአብሔር ጸሎትህን እንደሚቀበል እና በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላህ እመን። ይህን በምታደርግበት ጊዜ፣ የመንፈስን ህልውና ከውስጥህ እንዳለ አስተውል (ዮሐንስ 7፡38)። ከዚህ ቀጥሎ ሶስተኛውን የእምነት እርምጃህን ውሰድ።

3. **በእምነት ተናገር።** መጽሐፍ ቅዱስ በጴንጤቆስጤ ዕለት "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ተናገሩ" (ሐዋ. 2፡4፣ አጽንዖት ተጨምሯል) ይላል። ይህ ሲሆን የምትናገራቸው ቃላት የራስህ አይሆኑም ፤ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣሉ። ከውስጥ ከመንፈስህ ይወጣሉ (1ቆሮ. 14፡2)። ጸሎቱም በማትረዳው ቋንቋ ይሆናል። ይህ ለእናንተ እና ለቤተ ክርስቲያን ለእርሱ እንድትናገር ስልጣን እንደሰጠህ የእግዚአብሔር ምልክት ነው። አምላክ ይመስገን! አሁን በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቃችኋል።

## መለኮታዊ ጥሪ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መሆን ከስራ ምርጫ በላይ የሆነ የእግዚአብሔር ጥሪ ነው። ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር "እርሱ አንዳንዶቹን ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ" (ኤፌ. 4፡11) ሲል ጽፏል። ከአራቱ የአገልግሎት ሚናዎች ጋር መጋቢዎች በክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። ጌታ ራሱ መጋቢ አድርጎ የሚሾመውን ይመርጣል። ከዚያም ይጠራል ከዚያም ያሰማራል። ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት "እኔ

መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ እንድትሄዱና ፍሬ እንድታፈሩ ፍሬያችሁም እንዲኖር ሾምኋችሁ።(ዮሐንስ 15፡16)

ጌታ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ጥሪ በተመለከተ ሦስት ጠቃሚ እውነቶችን ገልጧል፡-በመጀመሪያ ምርጫውን የሚያደርገው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ገልጿል። ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በራሱ የተመረጠ አይደለም። እርሱ ወይም እርሷ በክርስቶስ ተመርጠዋል። ኢየሱስ ሰዎችን ለአገልግሎት ሥራ የሚመድበው እርሱ እንደሆነ ገልጿል። ቀጥሎም "እኔ መረጥኩህ፣ ሾምኩህም" ይላል። ክርስቶስ ማን እንደሚያገለግል ብቻ ሳይሆን የስራ ድርሻዎችን አስቀምጣል እና እነዚያን ስራዎች እንዲያሟሉ ሰራተኞችን ይመድባል።

በመጨረሻም የመረጣቸውንና የሾማቸውን ያሰማራቸዋል። ኢየሱስ "ሄዳችሁ ፍሬ እንድታፈሩ ሾምኋችሁ" በማለት ንግግሩን ጨርሷል። እርሱ የመከሩ ጌታ ነው፡ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" ብሎ ያዘዘን እርሱ ነው። በሌላ አነጋገር እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በራሳቸው የተመረጡ፣ የተሾሙ ወይም በራሳቸው የተላኩ አይደሉም። ይልቁንም በእግዚአብሔር የተመረጡ፣ በእግዚአብሔር የተሾሙ እና በእግዚአብሔር የተላኩ ናቸው። የእኛ ድርሻ ድምፁን መስማት፣ ለስልጣኑ መገዛት እና ጥሪውን መታዘዝ ነው።

የእግዚአብሔር ጥሪ በተለያዩ መንገዶች ሊመጣ ይችላል። እግዚአብሔር ስሙን በድምፅ ሲጠራ እንደሰማው ሳሙኤል (1ሳሙ. 3፡1-11) በአስደናቂ ሁኔታ ሊመጣ ይችላል። ብዙ ጊዜ ግን፣ የእግዚአብሔርን ጥሪ በአንድ ሰው በውስጥ ማንነቱ በየዋህነት እና መንቀጥቀጥ የሚመጣ የአገልግሎት መነሳሳት ነው። ይህ የኤልያስ ተሞክሮ ነበር። ነቢዩ በኃይለኛው ነፋስ፣ በመሬት መንቀጥቀጥ ወይም በእሳቱ ውስጥ የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰማም። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደ "የዋህ ሹክሹክታ" (1 ነገሥት 19፡12) ሰማ።

ይህ ለአገልግሎት መነሳሳት ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ከሚናገረው "ውስጣዊ መረዳት" ጋር አብሮ ይመጣል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በኃይል ያድጋል፣ ይህም የብርቱ ፍላጎትን ስሜት ይፈጥራል። ብላቴናው ኢየሱስ ለወላጆቹ "በአባቴ ቤት መሆን ነበረብኝ" (ሉቃስ 2፡49) በማለት ለወላጆቹ ሲነግራቸው እንዲህ ተሰምቶት መሆን አለበት። ጳውሎስ ይህንን ውስጣዊ ግፊት ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች "የምሰብከው ግዴታዬ ስለ ሆነ ነው፤ ወንጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ።!" ሲል (1 ቆሮ. 9፡16) ገልጿል። ነቢዩ ሚክያስ ይህን ጥልቅ ውስጣዊ እምነቱን እንዲህ ሲል ገልጾታል "እኔ ግን፣ለያዕቆብ በደሉን፣ ለእስራኤልም ኀጢአቱን እነግር ዘንድ ኀይልን፣ በእግዚአብሔር መንፈስ፣ ፍትሕና ብርታት ተሞልቻለሁ" (ሚክ. 3፡8)። ለመንፈስ ድምጽ በእምነት እና በመታዘዝ ምላሽ ስንሰጥ፡፡ እግዚአብሔር ሕይወታችንን ለወንጌል ስብከት ሥራ እንድንሰጥ እንደጠራን በእርግጠኝነት እስክናውቅ ድረስ እምነታችን ማደግ አለብን።

## ህያው ግንኙነት

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጣይነት ያለው ህያው ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ልምድ የአንድ ጊዜ ክስተት ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። አንድ ነጠላ ልምምድ ምንም ያህል አስደናቂ ቢሆን የክርስትናን ሕይወት ማቆየት አይችልም። በጴንጤቆስጤ ቀን መንፈስን የተለማመዱ የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት እንኳ በመንፈስ ተደጋጋሚ መሞላት አስፈልጎቸዋል (ሐዋ. 4፡8፣ 31፤ 5፡8)።እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጣይነት ያለው የግል ጉዞን ማዳበርን መማር አለብህ። ጳውሎስ በገላትያ ለነበሩት አዲስ ክርስቲያኖች "በመንፈስ የምንኖር ከሆን፣ በመንፈስ እንመላለስ" **(ገላ. 5፡25)** ሲል ጽፏል። በዚያው ደብዳቤ ላይ "ይህን

ያህል የማታስተውሉ ናችሁን? በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ ፍጹም ለመሆን ትጥራላችሁን?" (ገላ. 3፡2)) አንድ ጊዜ በመንፈስ መሞላት ብቻ በቂ አይደለም፣ "በመንፈስ ተሞልተህ" መኖር አለብህ (ሉቃስ 4፡1፤ የሐዋርያት ሥራ 6፡3፤ 7፡55፤ 11፡24)።

ኢየሱስ ይህንን ግንኙነት በእርሱ መኖር በማለት ገልጾታል (ዮሐንስ 15፡4)። በክርስቶስ መኖር በቃሉ እና በፍቅሩ መኖርን ያካትታል (ቁ. 7፤9)። እርሱም ትእዛዛቱን መጠበቅ (ቁ. 10) እና በመንፈስ መኖርን ያካትታል (1ኛ ዮሐንስ 2:27፤ 4፡13)።

# ተግባራዊ ተሞክሮ

አንዳንድ ችሎታዎች ከመጽሃፍቶች በንባብ ብቻ መማር አይቻልም። አንድ ሰው እንዴት እንደሚዋኝ የመጽሔት ጽሑፍን በማንበብ ግንዛቤ ሊያገኝ ይችላል። ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ጥልቀት በሌለው ስፍራ ውስጥ መዋኘት ከመለማመዱ በፊት ጥልቀት ወዳለው መዋኛ ቢገባ ሞኝነት ይሆናል። ለጴንጤቆስጤያዊ አገልግሎትም ተመሳሳይ ነው። የአካዳሚያዊ ጥናት ብቻውን በበቂ ሁኔታ ለመጋቢ አገልግሎት ሊያዘጋጅህ አይችልም። ወደ አገልግሎት ከመግባትህ በፊት ተግባራዊ ልምድ መቅሰም አለብህ። እንደዚህ አይነት ልምድ ማግኘት የምትችለው በተጨባጭ በአገልግሎት ላይ በመሳተፍ ብቻ ነው።

በደቡባዊ አፍሪካ በሚገኝ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አዳዲስ አመልካች ተማሪዎች "የመግቢያ ማመልከቻ" እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። አስተዳደሩ ከዚህ ቅጽ የተገኘውን መረጃ ተጠቅሞ የአመልካቹን ትምህርት ቤት ለመግባት ብቁነት ይወስናል። ከተለመዱት የግል እና የአካዳሚክ ጥያቄዎች ጋር፣ አመልካቹ በእራሳቸው የእጅ ጽሁፍ የግል ምስክርነታቸውን እንዲጽፉ ይጠየቃሉ። በዚህ ምስክርነት አመልካቹ አራት ጉዳዮችን እንዲመልሱ ይጠየቃሉ። (1) ክርስቶስን እንደ አዳኛችሁ እንዴት እንዳወቃችሁት ተናገሩ። (2) ጌታ በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንዳጠመቃችሁ እና መጠመቃችሁ ህይወታችሁን እንዴት እንደለወጠው ተናገሩ። (3) የአገልግሎት ጥሪን እንደላቸው እንዲገልጹ፤ እና (4) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዴት ንቁ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ መግለጽ ነው።

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ "የመጨረሻውን ጥያቄ የምንጠይቀው የተግባር ተሞክሮ ውጤታማ የአገልጋዮች ሥልጠና አስፈላጊ አካል እንደሆነ ስለምናምን ነው" የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል። ቀጥሎም እዚህ ትምህርት ቤታችን ለአገልግሎት ለመዘጋጀት ብቻ ሳይሆን በአገልግሎት ላይ የሆኑትን ማሰልጠን ላይ ትኩረት እናደርጋለን ይላሉ። መደበኛ ስልጠና አስፈላጊ ቢሆንም ብቻውን ለመጋቢ አገልግሎት ፈጽሞ አያዘጋጅህም። በአገልግሎት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የተግባር ልምድ ልታገኝ ይገባል።

ተግባራዊ ልምድ እስኪታገኝ ድረስ ጉባኤን በመጋቢነት ለመምራት መሞከር አይሞከርም። እንደዚህ አይነት ልምድ በአጥቢያ ቤተ ክርስትያን በብስለት እና በመንፈስ በተሞላ መጋቢ መሪነት ስር በማገልገል ልታገኝ ትችላለህ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መጋቢ፣ "በቅርቡ የተለወጠ መሆን የለበትም" (1 ጢሞ. 3፡6) ሲል ነግሮታል። አክሎም መጋቢው "በውጭ ሰዎች ዘንድ መልካም ስም ሊኖረው ይገባል" (ቁ. 7) ይለዋል። በአገልግሎት ውስጥ አራት አስፈላጊ የተግባር ተሞክሮዎች የምንላቸውን ፣ የመመስከር ልምድ፣ የመስበክ እና የማስተማር ልምድ፣ የመስጠት እና የጸሎት ልምድ እንደሚከተለው በዝርዝር እናያቸዋለን ፡

## የመመስከር ልምድ

በመጀመሪያ፣ ለመጋቢነት አገልግሎት ስትዘጋጅ የመመስከር ሥራ ልምድ መቅሰም አለብህ። ወንጌልን ለሌሎች በማካፈል የተካንክ መሆን አለብህ። እንደዚህ ያለ ምስክርነት ከላይ እንደተገለጸው በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ተፈጥሯዊ ውጤት ነው። ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር እረኛው "[በጎቹ]

ይቀድማል፣ በጎቹም ይከተሉታል" (ዮሐንስ 10፡4) ብሏል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አንተም ተመሳሳይ ሁኔታ ማድረግ አለብህ። ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ከበጎቻችሁ ቀድማችሁ ብትሄዱ እነርሱ ይህንን ልምምድ ይከተላሉ። ነገር ግን መመስከር ካልቻላችሁ ምእመኖቻችሁ የማይመሰክሩ ይሆናሉ።

የማንኛውም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አንዱ ሀላፊነት በመንፈስ የታጠቀ የሚስዮናውያን ቤተ ክርስትያን በሌለባቸው ቦታዎች አዳዲስ ክርስቲያናትን በመትከል የራሱን ወይም የእርሱን ጉባኤ መምራት ነው። ስለዚህ የአጥቢያ ጉባኤን አመራር ከመውሰድህ በፊት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ዘመቻዎች መሳተፍ አስፈላጊ ነው። ይህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጥረት፣ የተማርክበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ወይም ሌላ አገልግሎት ሊሆን ይችላል። ይህ ተግባራዊ ተሞክሮ መውሰድ የምንመራው ቤተ ክርስቲያን ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል እንዴት ማንቀሳቀስ እንደሚቻል ለማወቅ ይረዳል።[1]

## የስብከት እና የማስተማር ልምድ

በተጨማሪም፤ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ እና በማስተማር ልምድ መቅሰም አለበት። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች በማስተላለፍ ረገድ የተካነ ካልሆነ እንዴት የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያንን በብቃት መምራት ይችላል? ጳውሎስ አንድ መጋቢ "ማስተማር መቻል" እንዳለበት ለጢሞቴዎስ አሳስቦታል (1 ጢሞ. 3፡2)። በተጨማሪም ጢሞቴዎስን ሁል ጊዜ ቃሉን ለመስበክ እንዲዘጋጅ በእምነት ይመክረዋል (2ጢሞ 4፡2)።

የማስተማር እና የስብከት ልምድ የምትቀስምበት አንዱ መንገድ በአጥቢያ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ሰንበት ትምህርት ቤትን ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን ለማስተማር ፈቃደኛ መሆን ነው። ሌላው መንገድ የቤት ውስጥ ህብረት ቡድንን መምራት ነው። በእነዚህ መንገዶች በመሪው መጋቢ ስር በመሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክቶችን ማዘጋጀት እና መስበክን መለማመድ ይችላሉ። የስብከት ልምድ ለመቅሰም የሚረዳን ሌላው ጥሩ መንገድ በአደባባይ የመመስከር አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ ነው። ይህንንም በታማኝ የቤተ ክርስቲያን አባላትን በማደራጀት እና በገበያ ቦታዎች እና በቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ ባሉ ሌሎች ህዝብ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች በመሄድ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ማካሄድ ትችላላችሁ።[2]

## የመስጠት ልምድ

ሦስተኛ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መሆን የሚፈልግ ሰው አስራቱን በታማኝ ለእግዚአብሔር ስራ የመስጠት ታሪክ ሊኖረው ይገባል። አስራቱን መስጠት የማይወድ ጎስቋላና የተጨናነቀ ሰው፤ ለጋስ የሆነውን እግዚአብሔርን በፍጹም ሊወክል አይችልም። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "በነጻ ተቀበላችሁ በነጻ ስጡ"ሲል አበረታቷቸዋል። (ማቴ. 10፡8) በተመሳሳይ ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞችን "እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንድከተል የእኔን ምሳሌ ተከተሉ" ሲል መክሯቸዋል። የቤተ ክርስቲያን አባላት በእምነት የተሞላ

[1] እነዚህ ጉዳዮች በምዕራፍ 37፡ "የጠፉትን በወንጌል መድረስ" እና ምዕራፍ 39፡ "አዲስ አብያተ ክርስቲያናት መትከል" ላይ በዝርዝር ተብራርተዋል።

[2] በስብከትና በማስተማር ረገድ ተጨማሪ ማስተዋል ለማግኘት ምዕራፍ 16:- "በመንፈስ የተቀባ ስብከት" እና ምዕራፍ 17:- "ውጤታማ ትምህርት" የሚለውን ተመልከት።

ልግስናህን ሲመለከቱ እነርሱ ደግሞ ፍላጎቶቻቸውን ሁሉ እንደሚያሟላላቸው በማመን ለእግዚአብሔር ሥራ በልግስና እንዲሰጡ ይበረታታሉ (ፊልጵ. 4፡19)። በውጤቱም የእግዚአብሔር ሥራ ይሳካል።

## የጸሎት ሕይወት ልምድ

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ተግባራዊ የሆነ የጸሎት ልምድ ሊኖረው ይገባል። ጸሎት ለሁሉም የጴንጤቆስጤያዊ አገልግሎት መሠረት ነው። የአንድ ሰው የጸሎት ልምድ የሚጀምረው እራስን ለጸሎት ሕይወት በማስገዛት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ እንዴት ብዙ ጊዜ "ወደ ምድረ በዳ ስፍራ ሄዶ ይጸልይ ነበር" በማለት ስለ ኢየሱስ የጸሎት ህይወት ይነግረናል(ሉቃስ 5፡16)። ውጤታማ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን አንተም እንዲሁ ማድረግ አለብህ። ከሰማይ አባታችን ጋር ለመገናኘት በየእለቱ ጊዜ መመደብን መማር አለብን።[3]

እንዲሁም ከሌሎች ጋር በጸሎት መሳተፍ ያስፈልጋል። በጸሎት ቡድኖች፣ ጸሎት ጉዞዎች እና በአዳር የጸሎት ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ ይህንን ማድረግ ይቻላል። በእነዚህ ልምምዶች፣ ለሌሎች ለመጸለይ እራስዎን በማዘጋጀት የሚመጣ ልምምድ ነው። ልምድ ልታገኝባቸው የሚገቡ ሁለት ሌሎች ቦታዎች ለታመሙ እና ለተጎዱ ሰዎች እንዲፈወሱ መጸለይ እና ከአማኞች ጋር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ መጸለይ ነው።[4]

---

[3] ስለ ጴንጤቆስጤ መጋቢ የአምልኮ ሕይወት፣ ምዕራፍ 8ን ተመልከት፡-"የጸሎት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ" እና ምዕራፍ 15፡ "ጠንካራ የአምልኮ ልማድ" የሚለውን ተመልከት።

[4] እነዚህ ልምዶች በምዕራፍ 19 ውስጥ በበለጠ ዝርዝር ተሸፍነዋል፡- "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" እና ምዕራፍ 21፡ "በመንፈስ ኃይል ማገልገል" የሚለውን ተመልከት።

# ~ ምዕራፍ 2 ~

# የመንፈሱ ሰው

በአንድ የአፍሪካ ሀገር የእግዚአብሔርን ጥሪ ያስተዋለ አንድ ወጣት ነበር። ይህ ወጣት በሕይወቱ ላይ የእግዚአብሔር ጥሪ እንደተሰማው ለመጋቢው ነገረው። መጋቢው እግዚአብሔር በወጣቱ ሕይወት ላይ ያደረገውን ጥሪ ተገንዝቦ ስለነበር በአቅራቢያው ባለ ከተማ ውስጥ ባለ አጥቢያ ቤተክርስቲያን መደበው። መጋቢውም ለወጣቱን "ይህን ቤተ ክርስቲያን አሳድገህ በአካባቢው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን መትከል አለብህ" አለው። ወጣቱ በጋለ ስሜት ተሞልቶ ቤተሰቡን ወደ ከተማው በማዛወር ወደ ሥራው አቀና። በቦታውም ጠንክሮ በመስራት የተቻለውን ሁሉ አደረገ። ይሁን እንጂ እምብዛም ስኬት አልነበረውም። ከዚያም ወጣቱ በልቡ ተጨማሪ እውቀትና ስልጠና እንደሚፈልግ አስተዋለ። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገባ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ወጣቱ የእግዚአብሔርን ቃል አጠና። የበለጠ በተማረ መጠን የበለጠ በራስ የመተማመን ስሜቱ እየጨመረ ሄደ። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተብሎ ስለሚጠራው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምድም ተማረ። ወጣቱ መንፈስን በትጋት ስለ ፈለገ ብዙም ሳይቆይ ልክ 120 ደቀ መዛሙርት በጴንጤቆስጤ ቀን እንደተሞሉት እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ (ሐዋ. 2፡1-4)።

ከዚያም አስተማሪዎቹ በመንፈስ ኃይል እንዴት እንደሚመላለስ ስላስተማሩት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲመለስ ነገሮች ተለዋወጡ። አሁን በስልጣን እና በቅንነት ማገልገል ስለጀመረ ሰዎች ተፈወሱ ድነውም ብዙዎች ወደ ክርስቶስ መጡ። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን እያደገችና እየጠነከረች መጣች። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን መትከል ቻለ። ይህ ታሪክ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እውነተኛ ወንድ ወይም ሴት የመንፈሱ ሰው መሆን ለምን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል።

የመጨረሻው ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንዴት መንፈሳዊ እና ተግባራዊ ልምድ ያለው ሰው መሆን እንዳለበት ይናገራል። ይህ ምዕራፍ ደግሞ እነዚህን ጉዳዮች በሰፊው ይዳስሳል። ምዕራፉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ስለ መንፈስ ቅዱስ እና ስለ ሥራው ፣ ሊኖረው ስለሚገባው መሠረታዊ ግንዛቤ ያብራራል። በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የግል ጉዞውን እና አገልግሎቱንም ይመለከታል።

# መንፈስን ይረዳል

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እውነተኛ የመንፈስ ቅዱስ ሰው ለመሆን አራት ነገሮችን መረዳት ያስፈልጋል፡-

## መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ መረዳት

በመጀመሪያ፣ መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ መረዳት ያስፈልግሃል። በዚህ ዘመን ጴንጤቆስጤያዊያንን ጨምሮ እጅግ በጣም ብዙ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ ግልጽ ግንዛቤ የላቸውም። ብዙዎች መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ግልጽ ያልሆነ የተፈጥሮ ኃይል አድርገው ይመለከቱታል። የጴንጤቆስጤ መጋቢ ግን መንፈስ ቅዱስ በእውነት እግዚአብሔር መሆኑን ተረድቶ ማስተማር አለበት። መንፈስ ቅዱስ የቅድስት ሥላሴ ሦስተኛው አካል ነው (ማቴ. 28፡19፤ 2ቆሮ. 13፡14)። አብ አምላክ እንደሆነ ወልድም አምላክ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው። እንደ እግዚአብሔር አብ እና ወልድ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ያስባል (ሐዋ. 15፡28)፣ ይናገራል (ሐዋ. 1፡16)፣ ይመራል (ሮሜ. 8፡14)፣ እና ሊያዝን ይችላል (ኤፌ. 4፡30)።መንፈስ ቅዱስ እኔ ባይ አካል ስለሆነ እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ከእርሱ ጋር ግላዊ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል (ዮሐ. 14፡16-18፤ 2ቆሮ. 13፡ 14)።

በተጨማሪም፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መንፈስ ቅዱስ የተልእኮ መንፈስ መሆኑን ተረድተህ ማስተማር አለብህ።መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን የማዳን ተልዕኮ በምድር ላይ የሚፈጽም የስላሴ አካል ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚህ ተልዕኮ ከእርሱ ጋር እንዲተባበሩ የበለጠ ኃይልን ይሰጣል፣ ያነሳሳል እና ይመራል (ሐዋ. 1፡8)።

## መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚሰራ መረዳት

መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ ከማወቅ በተጨማሪ እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ አለብህ። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በምድር ላይ ለመፈጸም በእግዚአብሔር ተልዕኮ መር ሕዝብ ላይ በቤተ ክርስቲያን በኩል ይሰራል። ኢየሱስን ሥራውን እንዲፈጽም ኃይል እንደሰጠው (ሉቃስ 4፡17-19፤ የሐዋርያት ሥራ 10፡38)፤ በተመሳሳይ መንገድ የኢየሱስ ተከታዮች ሥራቸውን እንዲፈጽሙ ኃይል ይሰጣቸዋል (ሐዋ. 1፡8፤ ዮሐንስ 14፡12)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እነዚህን እውነቶች በግልፅ ተረድተህ አሳማኝ በሆነ መንገድ ማስተማር አለብህ።[1]

በዚህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በትክክል ለመረዳት ሦስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽንሰ-ሐሳቦችን መረዳት አለብህ፡-

**1. የእግዚአብሔር ተልዕኮ።** በመጀመሪያ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን እንደ ተልዕኮ ሰጪ አምላክ እንደሚያቀርበው መረዳት አለብህ። የእግዚአብሔር ተልእኮ አንዳንድ ጊዜ ሚሲዮ ዴ ተብሎ ይጠራል፤ ይህውም በላቲን የእግዚአብሔር ተልዕኮ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ተልእኮ በምድር ላይ ካሉ ነገዶችና ቋንቋዎች እና አሕዛብ ሁሉ ሰዎችን መዋጀት እና ወደ ራሱ መጥራት ነው (ራዕ. 5፡9)። ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር መሳሪያ ሆና ተልእኮውን ለመፈጸም ትኖራለች።

---

[1] በዚህ ርዕስ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 10ን "የጴንጤቆስጤ እውነትን ይደግፋል" እና ምዕራፍ 11፡ "የጴንጤቆስጤ ልምድ እና ልምምድ ያበረታታል" የሚለውን ተመልከት።

ኢየሱስ ታላቅ ተልእኮውን ሲሰጥ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በልብ ይዞ ነበር፡- “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” (ማቴ. 28፡19-20፤ ዝኒ ከማሁ. ማርቆስ 16፡15-16፣ ዮሐንስ 20:21))

እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን ህዝብ ስለ ተልእኮው ለማስተማር እራስህን መስጠት አለብህ። እንዲሁም ያንን ተልእኮ ለመፈፀም ስላላቸው ሚና ማስተማር አለብህ።

**2. የመንፈስ ጥምቀትና ሚስዮናዊ ተፈጥሮ።** የእግዚአብሔርን ተልእኮ ከመረዳት በተጨማሪ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ተልእኮውን ለመፈጸም የመንፈስን ጥምቀት አስፈላጊ ሚና መረዳት አለብህ።እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያጠምቀው ተልእኮውን እንዲፈጽሙ ለማስቻል መሆኑን መረዳት አለብህ (ሉቃስ 24፡49)። ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከተቀበለ በኋላ ነው (ሉቃስ 3፡21-23፤ 4፡17-19፤ ሐዋ. 10፡38)። ዛሬም ደቀ መዛሙርቱን በተመሳሳይ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲቀበሉ ይጠብቃል (ሐዋ. 1፡4-8)።

**3. ለተልዕኮ ማነቃነቅ።** በተጨማሪም እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የምታገለግለውን ሕዝብ ወደ መንፈስ ጥምቀት ስትመራ፣ በመንፈስ ለታጠቀ ተልእኮ እያዘጋጀችኋቸው እንደሆነ መረዳት አለብህ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ” (ሉቃስ 24፡ 49) ብሎ ባዘዛቸው ጊዜ ከፊታቸው ለሚጠብቀው ተልዕኮ እያዘጋጃቸው ነበር (ቁ. 47-48)። ጳውሎስም ለአሥራ ሁለቱ የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት “ ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?” ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ(ሐዋ. 19፡2) በኤፌሶን እና በቀሪው በትንሿ እስያ የወንጌል አገልግሎት ከእርሱ ጋር ለመቀላቀል ያላቸውን ዝግጁነት እየመረመረ ነበር (ቁ. 10)።

ዛሬም እኛም እንዲሁ በተመሳሳይ መንገድ ለተልኮ መነቃቃት ያስፈልገናል። የምናገለግለውን ህዝብ ወደ መንፈስ ጥምቀት በመምራት፣ በመንፈስ ሃይል ለተሞላ ምስክርነት፣ ለቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ለተልእኮ እያዘጋጀናቸው መሆኑን መረዳት አለብን።

## የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍን መፍታት

ሦስተኛ፣ በአፍሪካ ውስጥ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ተልዕኮአዊ ተፈጥሮ እና ዓላማ መረዳት አለብህ። እኛ ጴንጤቆስጤያዊያን ከሌላው ቡድን የሚለየን የሐዋርያት ሥራ መጽሀፍን የምንተረጉምበት መንገድ ነው። ጴንጤቆስጤያዊያን ተከታዮች ያልሆኑት በአጠቃላይ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ቤተክርስቲያን እንዴት እንደጀመረች እና ተልእኮዋን እንደፈፀመች የሚገልጽ ጥንታዊ ታሪክ አድርገው ይመለከቱታል። እንደ እነርሱ ከሆነ የሐዋርያት ሥራ ፣ እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ እና በዚያ በሩቅ ዘመን እንዴት እንደሠራ ብቻ የሚናገር እንደሆነ ያስባሉ። ጴንጤቆስጤያዊዊያን ግን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን እግዚአብሔር እንዴት በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን መሥራት እንደሚፈልግ መደበኛ ልምምድ የሚመሰርት አድርገው ይመለከቱታል።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የሐዋርያት ሥራ ከጥንታዊ ታሪክ መጽሐፍነት የበለጠ ፋይዳ እንዳለው ይረዳል። ሐዋሪያት ሥራ ለመጨረሻ ዘመን ተልዕኮ በመለኮታዊ አነሳሽነት የተዘጋጀ የስትራቴጂ መመሪያ ነው ብለን እናምናለን ። በሐዋርያት ሥራ መጽሀፍ በኩል ፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም ሞዴል መንገድ እና ስልት ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። ያ ስልት ኢየሱስ ለቤተክርስቲያን በሰጠው የመጨረሻ ቃል ውስጥ ተጠቃልሏል፡- “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ

ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (ሐዋ. 1፡8)።

ይህ ቁጥር (ሐዋ. 1፡8) በመጽሐፉ ውስጥ የተደጋገመውን በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ታጥቆ-ምስክርነት የመስጠትን አሰራር ያሳያል። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የምናገኘው እያንዳንዱ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ታሪክ ያለምንም ልዩነት በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ታጥቆ-ምስክርነት የመስጠትን አስከትሏል። ይህንን ፅንሰ ሀሳብ መረዳት የሐዋርያት ሥራን ለመገንዘብ እና ቤተክርስቲያናችሁን በመንፈስ ለታጠቀ ተልዕኮ ለማነቃነቅ ቁልፍ ነው።

## ጴንጤቆስጤያዊ ማለት ምን ማለት ነው

በመጨረሻም፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጴንጤቆስጢያዊ መሆን ምን ማለት እንደሆነ በግልፅ መረዳት አለብህ። እውነተኛ ጴንጤቆስጤያዊነት አንድ የተለየ የአምልኮ ዘይቤ መምረጥ ወይም በታምራት ከመሳብ የበለጠ ነገር ነው። የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያንን የእግዚአብሔር የመጨረሻው ዘመን በመንፈስ የታጠቀ የሚስዮናውያን ንቅናቄ ነው። ስለዚህ እውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ኢየሱስ በወንጌል ያስቀመጠውን አገልግሎት መርሕ እና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሐዋርያት እና በሌሎች ደቀመዛሙርት ከኢየሱስ የተከተሉትን የአገልግሎት ስርዓት ለመከተል ቁርጠኛ መሆን ማለት ነው። እርሱ ወይም እርሷ ለአራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶች ቁርጠኛ ናቸው፡-

1. **ተመሳሳይ መልእክት።** በመጀመሪያ ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሐዋርያትና ወንጌላውያን እንዳደረጉት ያንኑ ተመሳሳይ መልእክት በታማኝነት ለማወጅ ቁርጠኛ ነው። ያ መልእክት ወንጌል ነው። በፊልጶስ አገልግሎት ላይ ተገልጧል። ፊልጶስ "በሰማርያ ወዳለች ከተማ ወርዶ መሲሑን [ወይም ክርስቶስን] ሰበከ" (ሐዋ. 8፡5፤ ቁ. 12)። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ቤተክርስቲያን የክርስቶስን የኃጢያት ክፍያ ሞት እና ትንሳኤ መልእክት ከማወጅ ወደኋላ አትልም ነበር (ዝከ. 2፡22-24፤ 3፡15፤ 4፡10-12)። በተጨማሪም ሐዋርያት ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡና በወንጌል እንዲያምኑ ያለማቋረጥ ጥሪ አቅርበዋል (ዝከ. 2:38፤ 16:31፤ 20:21፤ 26:20)። ዛሬም እንዲሁ ማድረግ አለብን።

2. **ተመሳሳይ ተልዕኮ።** ሁለተኛ፣ ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንዳደረገችው ተመሳሳይ ተልዕኮ ለመከተል ቁርጠኛ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ያ ተልእኮ በሐዋርያት ሥራ 1፡8 በጥሩ ሁኔታ ተጠቃሎል። በዚያም ኢየሱስ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፤ እስከ ምድር ዳርቻም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ያለበት ነው። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ቤተክርስቲያንን ያለማቋረጥ ድንበሯን እንደምትገፋ፣ ወደ አዲስ ግዛቶች እንደምትሸጋገር እና በመንፈስ ታጥቃ ምሥራቹን እንደምትሰብክ ያሳያል። እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተም ለዚሁ ሥራ ቤተክርስቲያንህን መምራት አለብህ።

3. **ተመሳሳይ ልምዶች።** ሦስተኛ፣ ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሐዋርያት እንዳደረጉት መንፈሳዊ ልምምዶችን ያበረታታል። እነዚያ ተሞክሮዎች ሕይወትን የሚቀይር ድህነትን (ሐዋ. 2:41፤ 8:5-6፤ 9:1-8)፣ በመጥለቅ የውኃ ጥምቀት (2:41፤ 8:13፣ 36-38፤ 9:17-19) 16፡33)፣ በልሳኖች በመናገር የሚረጋገጥ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ (ዝከ. 2:4፤ 10:44-46፤ 19:6)፣ የፈውስ ተአምራት (ዝከ. 3:1-10፤ 5:12- 16፤ 20፡7-12)፣ እና ከአጋንንት እስራት የመዳን ተአምራት (ዝከ. 8፡7፤ 16፡16-18) ያካትታል። በተመሳሳይ መለኪያ የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተደገፈ ተአምር ወይም መንፈሳዊ ልምድን አይቀበልም።

**4. ተመሳሳይ ዘዴዎች።** በመጨረሻም፣ ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሐዋርያትና ሌሎች በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ይጠቀማል። እነዚህ ዘዴዎች በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ የወንጌል ማወጅ እውነተኛ የልብ መነካት፣ እምነትን፣ እና ንስሐ ፍሬ ማፍራትን ያካትታሉ (ሐዋ. 2፡14-41፤ 8፡13)። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በተጨማሪ እግዚአብሔር ቃሉን በምልክቶች፣ ከእነዚህም የንግግር የፈውስ እና የመዳን ተአምራትን ጨምሮ (ዝከ. 5፡12-16፤ 10፡44-47፤ 14፡6-10) እንዲያጸና ይጠብቃል።2

በተጨማሪም፣ ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መንፈስ ቅዱስ በተልእኮው እንዲመራው ይጠብቃል (ሐዋ. 8፡29፤ 10፡9-20፤ 16፡6-10)። ይህ ምሪት በውስጣዊ መረዳት ሊመጣ ይችላል (ዝከ. 8:29፤ 10:19)፣ በህልሞች (ዝከ. 2:17፤ 16:9)፣ እና በራእዮች (ዝከ. 9:10-16፤ 10:9-20) ሊገለጥ ይችላል። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሐዋርያት የተጠቀሙበት ዋነኛው የወንጌል አገልግሎት ዘዴ በመንፈስ ኃይል የታጠቁ የሚስዮናውያን አጥቢያዎችን በመትከል የክርስቶስን መልዕክት ወደ አካባቢው ለማድረስ ነበር።[3]

# በመንፈስ መመላለስ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ እና እንዴት እንደሚሰራ መረዳት ብቻ ሳይሆን እርሱ ወይም እርሷ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስር መኖርን መማር አለባቸው። ጳውሎስ በገላትያ ያሉትን አዳዲስ አማኞች "በመንፈስ ከጀመራችሁ በኋላ በሥጋ ልትጨርሱ ትፈልጋላችሁን?" ሲል ሞግቶቸዋል (ገላ. 3፡3))። ይህን ሲልም ክርስቲያናዊ አካሄዳቸውን እንዴት እንደጀመሩ እያሳሰባቸው ነበር። የጀመሩት በመንፈስ በመወለድ እና በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ነበር። አሁንም "ከመንፈስ ጋር እንዲèዙ" ይጠበቅባቸው ነበር (5፡25)። ይህ በአፍሪካ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እውነተኛ ዓላማ መሆን አለበት።

ይህንን ለማድረግ ሁለቱ አስፈላጊ መንገዶች በመንፈስ በመጸለይ እና የመንፈስ ፍሬዎችን በማዳበር ነው፡-

## በመንፈስ መጸለይ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ብዙ ዓይነት ጸሎቶች ይናገራል እነርሱም፡- ምልጃ፣ ልመና፣ ኑዛዜ፣ አምልኮ፣ ምስጋና እና ሌሎችም ይገኙበታል። በመንፈስ የሚደረግ ጸሎት ግን በተለየ ሁኔታ በመንፈስ የተሞላውን የሕይወት ጉዞ ለመደገፍ ተስማሚ ነው። ጳውሎስ ስለ እንደዚህ አይነት ጸሎት በኤፌሶን 6፡18 ተናግሯል። በተጨማሪም፣ በሮሜ 8፡26 እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል። በመንፈስ የሆነ ጸሎት ስንል በመንፈስ ቅዱስ የተነሳሳ፣ በመንፈስ የተቀባ እና በመንፈስ የሚመራ ማንኛውም ጸሎት ሊሆን ቢችልም ብዙውን ጊዜ በልሳን የሚጸለይ ጸሎትን የሚያመለክት ነው (1ቆሮ. 14፡14-15)። እንደ ጥበበኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ይህንን ኃይለኛ መንፈሳዊ መሳሪያ ደጋግመህ መጠቀም አለብህ (2ቆሮ. 10፡4-5)።[4]

---

[2] በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ለማወቅ ምዕራፍ 16: "በመንፈስ የተቀባ ስብከት" እና ምዕራፍ 21: "በመንፈስ ኃይል ማገልገል" የሚለውን ተመልከት።

[3] በመንፈስ የታገዘ የሚስዮናውያን አጥቢያ ስለ መትከል ለበለጠ፣ ምዕራፍ 39፡ "አዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል" የሚለውን ተመልከት።

[4] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር የጸሎት ሕይወት ለበለጠ፣ "የጸሎት ቅድሚያ የሚሰጠው" ምዕራፍ 8ን ተመልከት።

### የመንፈስ ፍሬ

መንፈሳዊ ጉዞህን የምታጠናክርበት ሌላው አስፈላጊ መንገድ የመንፈስን ፍሬ ማፍራት ነው። ጳውሎስ ይህንን ፍሬ “ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃነት እና ራስን መግዛት” (ገላ. 5፡22-23) በማለት ገልጿል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የኢየሱስን ሃይል ማወቅ ብቻ ሳይሆን ህይወትህ የእርሱን ባህሪ ማንጸባረቅ አለበት። ፍሬ የሌለው ስጦታዎች “እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል” ይሆናሉ (1ቆሮ. 13፡1)። በታዕምራት እና ድንቅ ወደ ክርስቶስ ሊመጡ ያልቻሉ ብዙዎች በፍቅር ተግባራት እንዲያምኑ ማድረግ ይቻላል። በመንፈስ በመመላለስ (ገላ. 5፡16) እና በክርስቶስ በመኖር በሕይወትህ መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት ትችላለህ (ዮሐ. 15፡4)።

# በመንፈስ ማገልገል

ኢየሱስም እንዲህ ሲል መስክሯል፣ “የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣ እርሱ ቀብቶኛልና” ሉቃስ 4፡18)። የጌታውን ምሳሌ በመከተል፣ ጳውሎስ የራሱን አገልግሎት “የመንፈስን ኃይል መግለጥ” (1ቆሮ. 2፡4) ሲል ገልጿል። በተመሳሳይ፣ አንተ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አገልግሎትህን ለመፈጸም እራስህን መስጠት አለብህ። እንደ ጳውሎስ ብቁ የመንፈስ አገልጋይ ለመሆን መጣር አለብህ (2ቆሮ. 3፡6)።

እንደዚሁ መንፈስ ቅዱስ በህይወትህ እና በአገልግሎትህ እና በምትመራው ሕዝብ ውስጥ እየሰራ ያለውን (ወይም ለመስራት አለመቻሉን) ለመለየት ምንጊዜም ንቁ መሆን አለብህ። የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና መገኘት የሌለበትን ማንኛውንም ባዶ ሃይማኖታዊ ስርዓትን አጥብቀህ መቃወም አለብህ (2ጢሞ. 3፡5)፡፡ ለእውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርት፣ ልምምድ እና ተግባር አጥብቀህ መሞገት አለብህ (ይሁዳ 1፡3)።[5] ይህንን ማድረግ የምትችልባቸው ሶስት መንገዶች የመንፈስ ቅዱስን ቅባት በመከታተል፣ የመንፈስን ምሪት በመፈለግ እና የመንፈስ ስጦታዎች በመሻት ነው። የሚከተለው በዝርዝር ያየዋል፡-

### የመንፈስ ቅዱስን ቅባት መከተል

እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የመንፈስን ቅባት በጉጉት መከታተል አለብህ። ሁል ጊዜ ለመስበክ፣ ለማስተማር እና በእግዚአብሔር ፊት ለማገልገል መፈለግ አለብህ። ያም ማለት፣ ህይወትህን እንዲጠቀምበት በጥብቅ በመጸለይ እና ለመንፈስ ቅዱስ እራስህን ለመስጠት መወሰን አለብህ። ይህም በበለጠ ስልጣን እና ኃይል ለማገልገል ያስችልሀል። የመንፈስ ቅብዐት በጣም የደነደነ ልብ ያለውን ሰው እንኳን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ እና ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንዲመሰክር ያደርጋል።

[5] በምዕራፍ 21 “በመንፈስ ኃይል ውስጥ ያለ አገልግሎት ላይ ስለ መንፈስ ኃይል አገልግሎት የበለጠ ማንበብ ትችላለህ፡

## የመንፈስን መመሪያ መፈለግ

በተጨማሪም፣ በአገልግሎት ውስጥ እንዲመራህ የጌታን መንፈስ ማመን አለብህ። ይህ የኢየሱስና የሐዋርያቱ ተግባር ነበር። ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መንፈስ ቅዱስ በእውነት የእግዚአብሔር ተልዕኮ መሪ መሆኑን ይረዳል። የተልእኮው አስፈላጊነት እና ብልጫ የሚረዳው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

መንፈስ ፊልጶስን ወደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ (ሐዋ. 8፡26-38)፣ ጴጥሮስን ወደ ቆርኔሌዎስ ቤተሰብ (10፡9-25) እና ጳውሎስንና የሚስዮናውያን ቡድኑን ወደ ምዕራብ አውሮፓ መራ (16፡6-40)። ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት ሆነን ከድምፁ ጋር የምንስማማ ከሆነ ዛሬም እንዲሁ ያደርጋል የጌታ መንፈስ ለክርስቶስ በምናደርገው ስራ ይመራናል።[6]

## የመንፈስ ስጦታዎችን በብርቱ መፈለግ

ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞች "የመንፈስን ስጦታ በብርቱ ፈልጉ" (1 ቆሮ. 14፡1) ሲል አሳስቧቸዋል። እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የመንፈሳዊ ስጦታዎችን አሰራር በራስህ ህይወት እና በቤተ ክርስቲያን ህይወት ውስጥ በመጋቢነት በማዳበር የሐዋርያውን መመሪያ መከተል አለብህ። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተቀበለው ቅባት በአገልግሎት የሚገለጠው በእነዚህ ስጦታዎች ነው። ጳውሎስ ስለ ስጦታዎች አሠራር በ1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ላይ ተናግሯል። ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥም እንዲሁ አድርጓል። ጳውሎስ ለአምልኮ በተሰበሰበው ጉባኤ የጸጋ ስጦታዎች አሠራር እንዴት እንደሚሆን ሲያተኩር (1ቆሮ. 14፡23-26)፣ ሉቃስ ደግሞ የጸጋ ስጦታዎች በግንባር ቀደምት የስብከተ ወንጌል እና ቤተ ክርስቲያን ተከላ ላይ እንዴት እንደሚሠሩ ያሳያል።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው የመጨረሻ መልእክት ላይ በእምነት ለሆነው ልጁ "በእጆቼ መጫን የተቀበልኸውን በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታቀጣጥል አሳስብሃለሁ" ሲል ይጎተጉተው ነበር(2ጢሞ. 1፡6)። ጢሞቴዎስን የመንፈስ ቅዱስ ሰው እንዲሆን አጥብቆ ያሳስበዋል። በአፍሪካ ውስጥ ያለ ማንኛውም የጴንጤቆስጤ መጋቢ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን ምክር ቢከተል መልካም ነው። የተሰጠህን የመንፈስ ቅዱስን "መልካሙን አደራ" በቅርበት መጠበቅ አለብህ (2ጢሞ. 1፡14)። ይህን ስታደርግ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተህ ለእግዚአብሔር ተልእኮ መሰጠትህን ማረጋገጥ አለብህ። በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ቅባት አገልግሎትህን ለመፈጸም መጣር አለብህ።

---

[6] የመንፈስ ስጦታዎች በምዕራፍ 19 በመንፈሱ ሃይል ማገልገል በሚል ተብራርቷል። በአባሪ 2 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች ከነትርጉማቸው ተዘርዝረዋል።

# ~ ምዕራፍ 3 ~

# የመልካም ሥነ ምግባር ሰው

ወጣት ሴት ልጅን በማስረገዙ የታሰረው ነብይ" እንዲህ አይነት የሚረብሽ አርዕስት በደቡብ አፍሪካ በሚገኙ ጋዜጦች ላይ ማየት የተለመደ ነው። ጽሑፉ በመቀጠል በአሥራ አራት ዓመት ዕድሜ ላይ የሚገኙ አንዳንድ ልጃገረዶች በአንድ የታወቀ "ክርስቲያን ነቢይ" እንዴት እንዳረገዙ ይናገራል። ልጃገረዶቹ የሰባኪውን ሕገወጥ ሥነ ምግባር አስመልክቶ ለሥልጣናት ሪፖርት አድገውም ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ እንዳለፉት በታሪክ ውስጥ እንደሚታወሱት ቅሌቶች ቤተክርስቲያን በዚህም ትዋረዳለች፣ የእግዚአብሔር ሥራ ይጎዳል፣ እና የክርስቶስ ስም ይዋረዳል።

ነገር ግን፣ የቤተ ክርስቲያንን እድገት በጣም የሚያደናቅፉት እንደዚህ ያሉ በግልጽ የታዩ አሳፋሪ ኃጢአቶች አይደሉም። ትንንሾቹ የተደበቁ ናቸው። አካን በስውር ኃጢአት ሠርቷል፣ ነገር ግን ኃጢአቱ መላውን ጉባኤ ነካ (ኢያሱ 7፡1-12)። በተመሳሳይም አንድ መጋቢ የሚፈጽማቸው ስውር በደል መላውን ጉባኤ ሊጎዳ ይችላል። በሥነ ምግባር ማነስ የተነሳ ብዙዎቹ የተቀቡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ውርደትን አምጥተዋል ፤ ከአገልግሎትም ራሳቸውን አግልለዋል።

መልካም ስነምግባር እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ አገልግሎት የተመሰረተበት መሰረት ነው። ያለዚህ መሠረት ፣ ሁሉም ነገር በመጨረሻ ተፍረክርኮ ይወድቃል። ዘላቂ አገልግሎት በችሎታ፣ በውበት፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በትምህርት ውጤት፣ ወይም በካሪዝማቲክ ቅባት ላይ ሊገነባ በፍጹም አይችልም። ዘላቂ አገልግሎት በመልካም ሥነ ምግባር መሰረት ላይ በጥብቅ መገንባት አለበት። ከምንም ነገር በላይ፣ ምዕመናን በመጋቢያቸውን መተማመን መቻል አለባቸው።

# የሥነምግባር አስፈላጊነት

የጌንጤቆስጤያዊ መጋቢ የላቀ ሥነ ምግባር ያለው ሰው መሆን አለበት። ጳውሎስ በኤፌሶን ባለችው ቤተክርስቲያን መጋቢ ሆኖ ሲያገለግል ለነበረው ለጢሞቴዎስ፣ አርአያነት ያለው ሕይወት እንዲመራ አሳስቦ ጽፏል።

2 እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ኤጲስቆጶስ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዐት የሚኖር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ማስተማር የሚችል፣ 3 የማይሰክር፣ የማይጣላ ግን ጨዋ የሆነ፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገንዘብንም የማይወድ ሊሆን ይገባዋል 2 ጢሞ 3፡2-3።

ጳውሎስ ስለ መጋቢ ሥነ ምግባር ቲቶን መክሯዋል፡-

7 ኤጲስቆጶስ የእግዚአብሔር ሥራ ባለ ዐደራ እንደ መሆኑ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባል፤ ይኸውም ትምክሕተኛ፣ ግልፍተኛ፣ ሰካራም፣ ጨቅጫቃና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጥቅም የሚሮጥ ሊሆን አይገባም። 8 ከዚህ ይልቅ እንግዳ ተቀባይ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፣ ራሱን የሚገዛ፣ ቅን፣ ቅዱስና ጠንቃቃ ሊሆን ይገባል። ቲቶ ፲፡ 7-8

በሁለቱም ዝርዝሮች፣ ጳውሎስ በዋናነት ከብቃት ይልቅ የሥነ ምግባር ጉዳዮችን እንዴት እንደተናገረ አስተውል። ብቃት ለጴንጤቆስጤ መጋቢ ጠቃሚ ቢሆንም ሥነ ምግባር ግን ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው።

# የሥነ ምግባር ትርèሜ

እንግዲህ ሥነ ምግባር የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ሥነ ምግባር ስለ አንድ ሰው የሞራል አቅጣጫን ይናገራል። ሥነ ምግባር በውስጣችን የተገነባው ስብዕና ነው። ለክርስቲያን ሥነ ምግባር ክርስቶስን መምሰል ነው። ሥነ ምግባር አንድ ሰው ጫና ሲገጥመው ምን እንደሚያደርግ (ወይም ምላሽ እንደሚሰጥ) ይወስናል። ሥነ ምግባር ማንም ተመልካች በሌለበት ጊዜ የምንሆነው ወይም የምናስበው ማለት ነው። ሌላው ሥነ ምግባርን የሚገልጸው ቃል ቅንነት ነው። ቅንነት ስለ ሥነ ምግባራዊ ጤናማነት ወይም ሙሉነት ይናገራል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ከስማችን ይልቅ ለባህሪያችን መጨነቅ አለብን። ምክንያቱም ስም ሌሎች እኛ ነን ብለው የሚያስቡትን ሲያሳይ፣ ባህሪያችን እውነተኛ ማንነታችን ነው። ሳሙኤል የዳዊትን ታላቅ ወንድም በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ ለመቀባት በተፈተነ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠውን ማስጠንቀቂያ አስታውስ። ነቢዩ "ሰው ፊትን ያያል፣ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" (፲ሳሙ. 16፡7) ብሏል። ሳሙኤል በመጨረሻ ዳዊትን ንጉሥ አድርጎ የቀባው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚፈልግ ሰው ስለነበር ነው (፲ሳሙ 13፡14፤ ሐዋ. 13፡22)።

አምላካዊ ባሕርይ በጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሕይወት እና ተግባር ውስጥ በሦስት ወሳኝ ቦታዎች ራሱን እንደሚከተለው ይገለጣል፡-

### እውነተኝነት

እውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የኢየሱስን ፈለግ ለመከተል ይመርጣል፣ "እርሱም ኃጢአት አላደረገም፣ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም" (፲ጴጥ. 2፡22)። ውሸት መናገር ከአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በጣም ቀላሉ መንገድ ቢሆንም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ሁሉ

እውነተኛ ነው። በሌላ መንገድ፣ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመዋሸት ፈቃደኛ አይሆንም ። ጳውሎስ የኤፌሶን ክርስቲያኖችን "ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፤" (ኤፌ. 4፡25) በማለት አሳስቧቸዋል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በማህበረሰብ ውስጥ እንደዚህ ያለ መልካም ስም እንዲኖርህ መጣር አለብህ፣ ይህ ሲሆን በምትናገርበት ጊዜ ሁሉ ሰዎች እውነትን እንደምትናገር እርግጠኞች ይሆናሉ። በገበያ ላይ ስትናገር ማመን ካልቻሉ፣ ከመድረክ ላይ ስትናገር እንዴት ሊያምኑህ ይችላሉ? ሁልጊዜ "እውነትን በፍቅር የሚናገር" (ኤፌ. 4፡15) ሰው ሆነህ መታወቅ አለብህ።

## የፋይናንስ ታማኝነት

እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በሁሉም ግንኙነቶችህ ውስጥ እውነተኛ መሆን አለብህ፣ ደግሞም በሁሉም ገንዘብ የሚያካትቱ ግንኙነቶችህ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ታማኝ መሆን አለብህ። ይህም ከእግዚአብሔር፣ ከቤተ ክርስቲያን ጋር እና ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ካሉ ጋር ያለን የገንዘብ ግንኙነት ይጨምራል። ይህን የምታደርገው እግዚአብሔር እንደሚመለከት ስለምታውቅ እና ከሁሉም በላይ እርሱን ማስደሰት ስለምትፈልግ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን አሥራትንና ቍርባንህን ልትዘርፍ እምቢ ማለት ይገባል (ሚል. 3፡8)።

አንዳንድ መጋቢዎች የቤተ ክርስቲያናቸው አባላት አሥራት እንዲከፍሉ ይጠይቃሉ፣ እነርሱ ራሳቸው ይህን ለማድረግ አሻፈረኝ ይላሉ። ይህን ሲያደርጉ እግዚአብሔርን መዝረፍ ብቻ ሳይሆን የልባቸውን ሽንገላ ይገልጣሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰው ከሆንክ ንስሐ ግባና ትክክለኛውን ተግባርም አድርግ (ሐዋ. 26፡20)።

በተጨማሪም፣ በቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አያያዝ ረገድ ታማኝ መሆን አለብህ። መጋቢ መሆንህ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ እንደፈለክ እንድትጠቀም መብት አይሰጥህም። ቤተ ክርስቲያን የምትቀበለውን ሁሉንም መባ እና አስራት በትጋት መጠበቅ አለብህ። ደግሞም ሁሉም ገንዘቦች ለተሰጡት ዓላማ ብቻ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አለብህ። ለምሳሌ፣ ለተልእኮ የተሰጠን ገንዘብ መኪና ለመግዛት፣ ወይም ለስብከተ ወንጌል የተሰጠ ገንዘብ የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ ለመጠገን መጠቀም አግባብ አይደለም። ከዚህም የሚከፋው ለድሆች የተሠጠውን ገንዘብ መውሰድ ነው። ይህን ማድረግ ከከረጢቱ እንደዘረፈው ይሁዳ ለራሳችሁ ጥቅም ማዋል ይሆናል (ዮሐ. 12፡6)።

በተጨማሪም፣ እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ከቤተ ክርስትያን ውጭ ካሉት ጋር በሚያደርጉት የገንዘብ ግንኙነት ታማኝ መሆን አለብህ። የላቀ ታማኝነት ያለው ሰው በመሆንህ መታወቅ አለብህ። መስረቅ፣ ማጭበርበር ወይም የተበደርከውን ገንዘብ ዘግይተህ መመለስ በፍፁም የለብህም። ይህ ከሆነ በቤተ ክርስቲያን ላይ ጥፋት ያመጣል ። ሰዎች ከክርስቶስ መልእክት እንዳይሰሙ ያደርጋል።

## የጾታ ግንኙነት ንጽሕና

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በግንኙነቶችህ ውስጥ እውነተኛ መሆን እና በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ታማኝ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ በማንኛውም ጊዜ ከተቃራኒ ጾታዎች ጋር በጥንቃቄ መመላለስ አለብህ። ለጋብቻ ቃልኪዳንህ ታማኝ መሆን አለብህ እና "ከክፉውን ሁሉ አስወግድ" (1 ተሰ. 5፡22)።

"ሽማግሌዎችን እንደ እናቶች፣ ቆነጃጅቶችንም እንደ እህቶች በፍጹም ንጽሕና ያዝ" (1 ጢሞ. 5፡2)። ይህንን ማድረግ ከሚስትህ በስተቀር ከሴት ጋር ብቻዎን አለመቀመጥን ማረጋገጥ ይጠይቃል። በተጨማሪም ከሚስትህ ውጪ ከማንም ሴት ጋር በግዴለሽነት በንግግር ወይም በእንቅስቃሴ ከሚፈጠር

ስሜታዊ ትስስር መጠበቅ ይኖርብሃል። መርሁ ለሴት መጋቢያንም ከወንዶች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይም ተመሳሳይ ነው።

የክርስቶስ አገልጋይ እንደመሆንህ መጠን ጳውሎስ የሰጠውን ምክር በቁም ነገር ልትመለከት ይገባል፡- “3 ማንኛውም የዝሙት ወይም የርኵሰት ወይም የስስት ነገር ከቶ በመካከላችሁ አይነሣ፤ ይህ ቅዱስ ለሆነው ለእግዚአብሔር ሕዝብ አይገባምና“ (ኤፌ. 5:3)።

# ሌሎች ተጨማሪ አስፈላጊ ሥነ ምግባሮች

እንደ እግዚአብሔር ተወካይ፣ ሌሎች መለኮታዊ ባሕርያትን ለማዳበር መሻት አለብህ። የሚከተለው ሊጠቀሱ የሚገባቸው አምስት ባህሪያት ናቸው እነርሱም ድፍረት፣አስተማማኝነት፣ትህትና፣ርህራሄ እና ልግስና ናቸው።

## ድፍረት

ድፍረት ማለት ተግዳሮት፣ ችግር ወይም አደጋ ቢያጋጥም ትክክል የሆነውን ለማድረግ የሞራል ጥንካሬ መኖር ማለት ነው። አደጋን መውሰዱ፣ ለበጎ ነገር ጸንቶ ለመቆም እና ወደፊት መንገድ የሌለ በሚመስል ጊዜ እግዚአብሔርን መታመን ድፍረት ነው። ኔልሰን ማንዴላ በህይወት ታሪካቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- “ድፍረት የፍርሃት አለመኖር ሳይሆን በፍርሃት ላይ ድል መቀዳጀት መሆኑን ተረዳሁ። ደፋር ሰው የማይፈራ ሳይሆን ያንን ፍርሃት የሚያሸንፍ ነው”

ድፍረት የፈሪነት ተቃራኒ ነው። ፈሪነት የተጋነነ ለራስ የመጨነቅ ውጤት ነው ፤ ድፍረት የሚወለደው ለሌሎች በማሰብ ነው። ፈሪነት አንድ ሰው ትክክል የሆነውን ለማድረግ ወይም ለመናገር ያለውን ችሎታ አዳጋች ያደርገዋል ፤ ድፍረት ግን በአደጋ ፊት እውነትን ለመጠበቅ ያስችላል። ሙሴ በፈርዖን ፊት ቆሞ የግብፅ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነፃ እንዲያወጣ ሲጠይቅ በድፍረት ነበር (ዘፀ. 5፡7)። ኢየሱስ ለመስቀል ውርደትና ስቃይ በትህትና ራሱን ሲሰጥ በድፍረት ነበር (ዕብ. 12፡2)። እስጢፋኖስም ለአይሁድ መሪዎች መሲሃቸውን እንደገደሉ ሲነግራቸው በድፍረት ነበር (ሐዋ. 7፡51-52)።

ራሳችንን በውስጣችን ለሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ካስገዛን፣ ለክርስቶስ ለመቆም እና ስሙን ለሁሉም ለማወጅ የሚያስፈልገንን ድፍረት ይሰጠናል። ጴጥሮስና ዮሐንስ ዛቻ ሲደርስባቸው “አሁንም ጌታ ሆይ፤ ዛቻቸውን ተመልከት፤ ባሪያዎችህም ቃልህን በፍጹም ድፍረት መናገር እንዲችሉ አድርጋቸው” ብለው ጸለዩ። ለጸሎታቸው ምላሽ፣ እግዚአብሔር በመንፈስ ሞላባቸው፣ እናም “የእግዚአብሔርን ቃል በድፍረት ተናገሩ” (ሐዋ. 4፡29-31)። አንተም እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጥሪህን በታማኝነት ለመፈጸም የሚያስፈልግህን ድፍረት እንድታገኝ በመንፈስ ለመሞላት እና በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ መሆን መፈለግ አለብህ።

## አስተማማኝነት

በተጨማሪም፣ እንደ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ወይም አስተዳዳሪ፣ ታማኝ መሆን አለብህ። ጌታ ሙሉ እምነትን በአንተ ላይ ማድረግ መቻል አለበት (ቲቶ 1፡7፤ 1ጴጥ. 4፡10)። ጳውሎስ “አደራ የተሰጣቸው ታማኝ እንዲሆኑ ያስፈልጋል” (1 ቆሮ. 4፡2) በማለት ጽፏል። ስለዚህ ህይወትህ እንደ አስተማማኝነት፣ ሰዓት አክባሪነት፣ ትጋት እና ጽናት ያሉ ባህሪያትን ማሳየት አለበት። እንደዚህ አይነት ባህሪያት በመንፈስ ከተሞላ ጉዞ የሚመጡ ፍሬዎች ናቸው (ገላ. 5፡22)።

ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎች " ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ኤጲስቆጶሳት አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ፤ በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ" (ሐዋ. 20፡28)። እንደ መጋቢዎች፣ ጌታ የወንዶች እና የሴቶች ነፍስ አደራ ሰጥቶናል። አንድ ቀንም በዚህ ጉዳይ ስለ ታማኝነታችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን (ዕብ. 13፡17)። ያዕቆብ በጥብቅ ያስጠነቅቃል:- " ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፤ ምክንያቱም እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ እንደምንቀበል ታውቃላችሁ" (ያዕቆብ 3፡1)።

## ትህትና

ክርስቶስን እንደሚመስል ሰው፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ትሑት መሆን አለበት (ኤፌ. 5፡1)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ብሏቸዋል:- " በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም። ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤27 የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፤28 የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና"" (ማቴ. 20፡26-28)።

በትዕቢት እና በራስ ወዳድነት ተሞልቶ፣ ከማገልገል ይልቅ ሌሎች እንዲያገለግሉት የሚፈልግ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ማየት እንዴት ያስጨንቃል። እንዲህ ያለው አመለካከት ጌታችን ከገለጠው ትሕትና ጋር ተቃራኒ ነው። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች እንዲህ ሲል ጽፏል:- "በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤6 እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤ 7 ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ 8 ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ (ፊልጵ. 2:5-8))። ትዕቢተኛ እና አለቃ ልሁን ባይ እንዲገለገል ይጠይቃል ፤ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው መጋቢ ግን ሌሎችን በትህትና ማገልገል ያስደስተዋል።

## ርህራሄ

እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የርህራሄ ሰው መሆን አለብህ። ርህራሄ ፍቅርን በተግባር መግለጥ ነው። ሩህሩህ ለተቸገሩት ተቆርቋሪነቱን ያሳያል። ርህራሄ በእግዚአብሔር ፍቅር የተሞላ ሰው ልብ ውጫዊ መግለጫ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር "ሕዝቡም እረኛ እንደሌለው በግ ተጨንቀውና ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ጊዜ አዘነላቸው" (ማቴ. 9፡36)።

ኢየሱስ በመራራቱ የህዝብን መንፈሳዊ እና አካላዊ ፍላጎቶች ለማሞላት ተነሳሳ። የእግዚአብሔር መንጋ እረኞች እንደመሆናችን መጠን ለሕዝቡም ሆነ ክርስቶስን ለማያውቁ ከፍቅር የመነጨ ርኅራኄ ማሳየት አለብን። ርኅራኄ ሌሎችን በችግር ጊዜ እንድንንከባከብ ያደርገናል፣ እናም ወንጌልን ለሁሉም እንድንሰብክ ያነሳሳናል።

እንደ እግዚአብሔር ወንድ እና ሴት አገልጋዮች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምናደርገው ቀጣይነት ያለው ጉዞ ሌሎችን እንድንወድ እና እንድንከባከብ ሊያነሳሳን ይገባል። ጳውሎስ "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ፈሰሰ" (ሮሜ 5፡5) በማለት አብራርቷል። ከሌሎች ይልቅ በክርስቶስ መንፈስ ተሞልተናል የምንል የክርስቶስን ርህራሄ ለሌሎች ማሳየት አለብን።

## ልግስና

ለዕውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የመጨረሻው አስፈላጊ ሥነ ምግባር ልግስና ነው። የመጀመሪያዎቹ አማኞች በበዓለ ሃምሳ ቀን በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው የተነሣ የልግስና መንፈስ ነበራቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነርሱ እንዲህ ይላል:- " ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም

ሁሉ የጋራ አደረጉ። 45 ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ያህል ይሰጡት ነበር" (ሐዋ. 2፡44-45)። በተመሳሳይ መልኩ በመንፈስ የተሞላን መጋቢዎች፣ ያለንን ለሌሎች ለማካፈል ፈቃደኛ መሆን አለብን። እጃችን ለእግዚአብሔር ስራ፣ ለቤተክርስቲያን አገልግሎትና እና ለተቸገሩት ሊዘረጋ ይገባል።

ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን በላካቸው ጊዜ፣ " በሽተኞችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ" (ማቴ. 10:8) አላቸው። እንዲህ ዓይነቱ ልግስና ተላላፊ ነው። ህዝቡ የመጋቢውን ነፃነት ሲያዩ ልባቸውን እና ቦርሳቸውን እንዲከፍቱ እና ለጋስ እንዲሆኑ ይበረታታሉ። ይህ የልግስና ባሕል ቤተክርስቲያንን፣ በዙሪያው ያለውን ማኅበረሰብ እና በመጨረሻም የምድርን አሕዛብን በኃይል ይነካል።

# የሥነ ምግባር ግንባታ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከላይ የተገለጸውን መለኮታዊ ባሕርይ እንዴት ማዳበር ይችላል? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ይሰተዋላል፡፡ ይህን የምናደርገው የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል ነው። እርሱ ለሕይወትና ለአገልግሎታችን አብነት ነው። ዮሐንስ " ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል" በማለት ጽፏል (1 ዮሐንስ 2፡6)።

እንደ ጳውሎስ ንግግር "ክርስቶስን ልንለብስ" ይገባል (ቆላ. 3፡12-17፤ ሮሜ. 13፡14)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "ተከተሉኝ" ብሎ ባዘዛቸው ጊዜ (ማርቆስ 4፡19) እርሱን እንዲመለከቱት እና እርሱን እንዲመስሉ እየነገራቸው ነበር። ይህን ሲያደርጉ ወደ እርሱ መልክ ይለወጣሉ (ሮሜ. 8፡29፤ 2ቆሮ. 3፡ 18)። ህይወታቸው ቀስ በቀስ እንደ እርሱ ህይወት ይሆናል። እርሱ በመንፈስ ኃይል እንደኖረ እነርሱም መኖር ይጀምራሉ፣ እንዳሰበው ያስባሉ እና እንደወደደው ይወዳሉ (2ጴጥ. 1፡3-4)። ትክክለኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መሆን ከፈለግክ እንደ ኢየሱስ ለመሆን ወስን።

አሥራ ሁለቱ ኢየሱስን ሲከተሉ ፊት ከነበራቸው ሕይወት ይልቅ የበለጠ ሕይወት መለማመድ ጀመሩ። በፊት እነርሱ አሳ አጥማጆች ብቻ ነበሩ። ነገር ግን እርሱን ሲከተሉ እንደ ጌታቸው ሰው አጥማጆች ሆኑ። በሌላ አነጋገር የኢየሱስን ባሕርይ ያዙ። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት አንዳንድ ጊዜ ይህንን ሂደት መንፈሳዊ ግንባታ ብለው ይጠሩታል።

ነገር ግን በራስ ጥረት ወይም በፈቃዳችን ኃይል ክርስቶስን መምሰል እንችላለን ብለን ማሰብ የለብንም። የእግዚአብሔር እርዳታ ሊኖረን ይገባል። የእርሱን እርዳታ ለማግኘት ሦስት መንፈሳዊ ትምህርቶችን መለማመድ አለብን፡-

**በክርስቶስ መኖር**

በመጀመሪያ፣ በእርሱ በመኖር አምላካዊ ባህሪን ስናዳበር የክርስቶስን እርዳታ እናገኛለን። ክርስቶስን መምሰል የምንችለው በክርስቶስ በመኖር ብቻ ነው። ኢየሱስ " ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ካልሆነ በቀር ብቻውን ፍሬ ሊያፈራ አይችልም" ብሎዋል (ዮሐ. 15፡4)። በክርስቶስ መኖር ማለት በቃሉ እና በመገኘቱ አማካኝነት ከእርሱ ህይወትን መጋራት ማለት ነው። ይህንን የምናደርገው ማያቋርጥ ጸሎት፣ አዘውትረን መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት እና በማሰላሰል እና ፍላጎቶቻችንን ሁሉ እንደሚያሟላልን በእርሱ በመታመን ነው።

**እግዚአብሔር መቅረብ**

በየቀኑ ወደ እርሱ በመቅረብ የክርስቶስን ባህሪ የበለጠ ማዳበር እንችላለን። ያዕቆብ “ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል” (ያዕቆብ 4፡8) በማለት አረጋግጦልናል። በክርስቶስ እንደምንኖር ሁሉ በጸሎት፣ በአምልኮ እና በታመነ አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር እንቀርባለን። ወደ ክርስቶስ ስንቀርብ እርሱን ወደ መምሰል እንለወጣለን። ጳውሎስ እንዲህ ሲል እንደጻፈው፦ “ እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው” (2ቆሮ. 3፡18)።

**በመንፈስ መመላለስ**

በመጨረሻም፣ በመንፈስ በመመላለስ የክርስቶስን ባህሪ እናዳብራለን። በመንፈስ መመላለስ ማለት ለመንፈስ ቅዱስ በመገዛት ሕይወትን መራመድ ነው። ትእዛዙን ማክበር ነው። ጳውሎስ “በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰናል” (ሮሜ. 15፡16) ብሏል። ይህም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ኢየሱስ ለመኖር የሚያስፈልገንን ኃይል ይሰጠናል ማለት ነው። ጳውሎስ የገላትያ ክርስቲያኖችን “በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አታድርጉ”ሲል አበረታቷቸዋል (ገላ. 5፡16)።

---

ሰሎሞን እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “ያለህን ሁሉ ዋጋ ቢያስከፍልህም ማስተዋልን አግኝ። ተንከባከባት ከፍ ከፍ ታደርግሃለች እቀፏት ታከብርሃለች” (ምሳ. 4፡7-8)። ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ  ብዙ ማለት ይቻላል። ምንም እንኳን ያለህን ሁሉ የሚያስከፍልህ ቢሆንም የክርስቶስን ባህሪን አግኝ ተንከባከበው ከፍ ከፍም ያደርግሀል፤እቅፍ አድርገው ክብርን ታመጣልሃል። ከምንም በላይ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ወንድ ወይም ሴት በጥሩ ሥነ ምግባር የታነጸ መሆን አለበት።

# ~ ምዕራፍ 4 ~

# በሙላት የተዘጋጀ ሰው

እንደ ማንኛውም ድርጅት፣ ቤተክርስቲያንም ለወንጌል ሥራ በሚገባ በተዘጋጁ ሰዎች መመራት ይኖርባታል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅ አንድ ወንጌላዊ በአንድ ወቅት “ወንጌልን ለመስበክ ሦስት ዓመት ብቻ እንዳለኝ ባውቅ ኖሮ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን አመታት በዝግጅት አሳልፋለሁ” ብሏል። አንድ የተሳካለት መጋቢ ደግሞ፣ “ስኬት የሚገኘው እድል ከዝግጅት ሲገጥም ነው” በማለት በጥበብ አስቀምጦታል። ሁለቱም ሰዎች በወንጌል አገልግሎት የመዘጋጀት አስፈላጊነት ላይ አጽንዖት ሲሰጡ እንመለከታለን ።

ጳውሎስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እረኛ አድርጎ ለሾመው ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፎለታል፡- “ማንም ኤጲስቆጶስነትን ቢፈልግ፣ መልካም ሥራን ይመኛል” (1 ጢሞ. 3፡1)። ጳውሎስ በመጋቢነት ሚና ለማገልገል ብዙ ቅድመ ሁኔታዎችን ጠቅሷል። ከነዚህ ሁኔታዎች አንዱ፣ “በቅርብ የተለወጠ መሆን የለበትም” (ቁ. 6) ነበር።

በዚህ ክፍል ውስጥ “በቅርብ ጊዜ የተለወጠው” ተብሎ የተተረጎመው የግሪክኛ ቃል *ኒዮፊትስ* ሲሆን ትርጉሙ ቀጥተኛ ትርጉሙ “አዲስ የተተከለ” ወይም “መጀመሪያ” ማለት ነው። ይህ ጳውሎስ መጋቢ ማለትም፣ “ሽማግሌ” ወይም በግሪክ ፕሬስባይቴሮስ በማለት ከተጠቀመበት ስያሜ ጋር ተቃራኒ ነው፣ ፕሬስባይቴሮስ ስለ ልምድ እና ብስለት ይናገራል፣ ያ ደግሞ መዘጋጀትን ያመለክታል (1ጢሞ. 5፡17-19፤ ቲቶ 1፡5)። ጳውሎስ መጋቢ ከክርስቶስ ጋር በሚያደርገው ጉዞ ጀማሪ መሆን የለበትም ይላል። በተቃራኒው እርሱ ወይም እርሷ በእምነት የበሰሉ እና ለአገልግሎት ስራ በሚገባ የተዘጋጁ መሆን አለባቸው ማለቱ ነው።

አንድ ወጣት የጴንጤቆስጤያዊ ሰባኪ በአንድ ወቅት ለአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር “ስልጠና አያስፈልገኝም ፤ የሚያስፈልገኝ ደቀ መዛሙርት እንደ ጴንጤቆስጤያዊ ቀን

እንደተቀበሉት በመንፈስ መታጠቅ ብቻ ነው“ ብሎ ነገረው። ይህ ግን ሞኝነት ነው። ወጣቱ ሰባኪ ሊገነዘበው ያልቻለው ከጴንጤቆስጤ ቀን በፊት አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ጋር ሦስት ዓመታት ማሳለፋቸውን ነው። ወጣቱ አገልጋይ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመታጠቅን አስፈላጊነት ሲገመግም ትክክል ቢሆንም፣ ለአገልግሎት መንፈሳዊ፣ ምሁራዊ እና ተግባራዊ ዝግጅት አስፈላጊ ስለመሆኑ ባለው አመለካከት ሚዛን የሳተ ነበር።

ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን “ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለቱን ” መረጠ (ማርቆስ 3፡14)። ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን እንዲሰብኩ ከማዘዙ በፊት፣ ከእነርሱ ጋር ለሥራው ሲያዘጋጃቸው በርካታ ጊዜያት አሳልፏል።

ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢን በአግባብ የመዘጋጀት አስፈላጊነት ያብራራል። በተጨማሪም ዝግጅት የሚያስፈልጉትን አንዳንድ ቦታዎችን ይለያል። ከዚያም መጋቢው አስፈላጊውን ዝግጅት እንዴት እንደሚያገኝ እና እንደሚያስጠብቅ ይናገራል።

# ዝግጅት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

የመጋቢያዊ አገልግሎት ዝግጅት፤ አገልጋዮች ጥሪያቸውን በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስፈልጉትን አስፈላጊ ክህሎቶች እና አመለካከቶች እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል። እንደ የመጋቢው ስንቅ እና ትጥቅ ሊታሰብ ይችላል። በቂ ዝግጅት ማድረግ ስራህን በብቃት ለመስራት ብቻ ሳይሆን በጭንቀት ወይም በአደጋ ጊዜ ሳትወድቅ ጸንተህ እንዴት ማገልገል እንዳለብህ ያስገነዝባል። ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ቢያንስ በአምስት መንገዶች በአግባቡ መዘጋጀት አለበት፡-

**በመንፈስ መዘጋጀት**

ከሁሉም በላይ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለሥራው በመንፈስ ዝግጁ መሆን አለብህ። ራስህ የእግዚአብሔርን ጸጋ ካልተለማመድክ እንዴት ለሌሎች ማስተላለፍ ትችላለህ? ስለዚህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሆነህ ስታገለግል በእውነት ዳግመኛ ተወልደህ (ዮሐ. 3፡3-7) እና በመንፈስ ቅዱስም ተሞልተህ መሆን አለበት (ሐዋ. 1፡8፤ ኤፌ. 5፡18)። በተጨማሪም፣ በታማኝነት ክርስቶስን የሚያከብር ህይወት መኖር አለብህ (1ኛ ዮሐንስ 2፡6)፣ እና ለክርስቶስ እና ለተልእኮው ሙሉ በሙሉ መሰጠት አለብህ (ማቴ.16፡24)።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ “የአካል ብቃት ልምምድ ለጥቂት ነገር ይጠቅማልና፤ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራስን ማሠልጠን ግን ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለሁለቱም ይጠቅማል” (1 ጢሞ. 4፡8) በማለት አሳስቦታል። ጳውሎስ ይህንን የሥልጠና ዘይቤ ተጠቅሞ ለመጋቢነት አገልግሎት ለመዘጋጀት የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ የሕይወት ስርዓት ያሳያል (1ቆሮ. 9፡24-27)። አንድ አትሌት ራሱን ወይም እራሷን ለውድድር ለማዘጋጀት በደንብ ማሰልጠን እንዳለበት ሁሉ መጋቢውም ራሱን ወይም ራሷን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ስራ ማዘጋጀት አለበት። ለመሰልጠን ፈቃደኛ ያልሆነው የእግር ኳስ ተጫዋች እራሱን ከቡድኑ ያስወግዳል። በተመሳሳይ መልኩ፣ መንፈሳዊ የሕይወት ስርዓት ለመከተል ፈቃደኛ ያልሆነው መጋቢ ራሱን ወይም ራሷን ከአገልግሎት ያገላል።

**በቃሉ መዘጋጀት**

በሁለተኛ ደረጃ፣ ውጤታማ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት የተዘጋጀህ መሆን አለብህ። ይህ ማለት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥልቅ ግንዛቤ ሊኖርህ ይገባል። የማንኛውም መጋቢ ዋና ተግባር የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት በማስተማር መንጋውን መመገብ ነው።

ውጤታማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ቅዱሳን በክርስቶስ እንዲበስሉ ያደርጋል (1ጴጥ. 2፡2)፣ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንዲፋለሙ በቃሉ ያስታጥቃቸዋል (ሐዋ. 20፡28-29)፤ እና ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ ያስታጥቃቸዋል (ኤፌ. 4፡11-12)። ጳውሎስ አንድ መጋቢ "ማስተማር መቻል" እንዳለበት ሁለት ጊዜ ለጢሞቴዎስ መንገሩ የማይደንቀው በዚህ ምክንያት ነው (1 ጢሞ. 3:2፤ 2 ጢሞ. 2:24)። ውጤታማ የማስተማር አገልግሎት ሊገነባ የሚችለው በሰፊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ላይ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትክክል ለማስተማር "የእውነትን ቃል" እንዴት በትክክል መተርጎምና በሥራ ላይ ማዋል እንዳለብህ ማወቅ አለብህ (2 ጢሞ. 2፡15)።

### *የሥነ ምግባር ዝግጁነት*

በመቀጠል፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለአገልግሎት በምግባር ዝግጁ መሆን አለብህ። ክርስቶስን የሚያከብር ቅዱስ ሕይወት መኖር አለብህ። ጳውሎስ ኤጲስቆጶስ የእግዚአብሔር ሥራ ባለ ዐደራ እንደ መሆኑ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባል፤ ይኸውም ትምክሕተኛ፣ ግልፍተኛ፣ ሰካራም፣ ጨቅጫቃና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጥቅም የሚሮጥ ሊሆን አይገባም (ቲቶ 1፡7) ሲል ጽፏል። አክሎም አንድ መጋቢ " የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ …ገንዘብንም የማይወድ ሊሆን ይገባዋል" (1 ጢሞ. 3:2) ሲል ለጢሞቴዎስ ነግሮታል። በእነዚህ የሕይወት ዘርፎች ድል ያላደረገ ሰው ራሱን ወይም ራሷን በአገልግሎ ሊቀጥል አይችልም። ያ ሰው በነዚህ የሞራል ጉድለቶች ላይ ድል እስኪያገኝ ድረስ ከአገልግሎት ራሱን ማግለል አለበት።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ብዙ የህይማኖት መሪዎችን ካጠመዱ እና ከሩጫ ካሰናከሉ ሶስት ታላላቅ ኃጢአቶች ነቅተህ መጠበቅ አለብህ። እነዚያ ሦስቱ ታላላቅ ምግባሮች ስግብግብነት (ገንዘብን መውደድ)፣ ፍትወት (ህጋዊ ያልሆነ ምኞት) እና ዓለማዊ ምኞት (የመደነቅ እና ሌሎችን የመቆጣጠር ፍላጎት) ናቸው። ምንም አይነት የካሪዝማም ወይም ቅባት  በእነዚህ መሰናክሎች ምክንያት የመጣን ሽንፈትን ሊሸፍን አይችልም።

ጳውሎስ ለገላትያ አማኞች በጻፈው ደብዳቤ፣ ለኃጢአተኛ ምኞት ከመሸነፍ አስጠንቅቋቸዋል (ገላ. 5፡19-21)። ይልቁንም የመንፈስን ፍሬ ማፍራት እንዲያፈሩ አሳስቦቸዋል (ቁ. 22-23)። ጳውሎስ ከሥነ ምግባር ሽንፈት ወደ ሥነ ምግባራዊ ድል የሚወስደውን መንገድ ገለጠላቸው፡- የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቅለውታል። 25 በመንፈስ የምንኖር ከሆን፣ በመንፈስ እንመላለስ (ቁ. 24-25)። ሐዋርያው በመቀጠል የገላትያ ሰዎችን "በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ ከቶ አታድርጉ" ሲል መክሯቸዋል (ቁ. 16)

### *የአዕምሮ እና የስሜት ዝግጅት*

በመጨረሻም አገልግሎትህን በብቃት ለመወጣት በአእምሮ እና በስሜት ለሥራ ዝግጁ መሆን አለብህ። በሌላ አነጋገር፣ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማሰብ መቻል አለብህ፣ እናም ስሜትህን መቆጣጠር እና ለሚገጥሙህ ፈተናዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት አለብህ።

ጳውሎስ ለቲቶ እንዲህ ሲል ጽፏል " የእግዚአብሔር ሥራ ባለ ዐደራ እንደ መሆኑ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባል፤ ይኸውም ትምክሕተኛ፣ ግልፍተኛ፣ ሰካራም፣ ጨቅጫቃና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጥቅም የሚሮጥ ሊሆን አይገባም።  ከዚህ ይልቅ… ራሱን የሚገዛ፣ ቅን፣ ቅዱስና ጠንቃቃ ሊሆን ይገባል።" (ቲቶ 1፡7-8)። ሐዋርያው ለጢሞቴዎስ በጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ ላይ ባለ ዐደራ "የማይነቀፍ፣ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዐት የሚኖር፣ " (1 ጢሞ. 3:2) ሲል አክሎ ተናግሯል። ከላይ ያሉት እያንዳንዳቸው የተመረጡት የባህርይ መገለጫዎች ስለ አእምሮአዊ እና ስሜታዊ ብስለት እንዴት እንደሚናገሩ ልብ በል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እነዚህን ባህሪያት በራስህ ህይወት እና አገልግሎት ለማዳበር መጣር አለብህ።

# የመዘጋጃ መንገዶች

ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የጥሩ ዝግጅትን ጥቅም በማወቅ ለአገልግሎት ራሱን ለማዘጋጀት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ይህንን ለማድረግ ሦስት መንገዶችን እንመልከት-

## በተግባራዊ ልምድ

በመጀመሪያ፣ ተግባራዊ ልምድ በመውሰድ ራስህን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ትችላለህ። የሚከተሉት ልምድ ለማግኘት የሚጠቅሙ ሶስት መንገዶችን እንመልከት።

1. **በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል።** አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትህን የምትጀምርበት ትክክለኛ ቦታ ነው። ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እየተሳተፉ ሳለ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሚስዮናዊነት አገልግሎት መራቸው (ሐዋ. 11፡25-26፤ 13፡1-3)። በተጨማሪም ጳውሎስ ብዙ የሚስዮናውያን አጋሮቹን የመለመለው በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ከሚያደርጉት ነበር። ለምሳሌ ጢሞቴዎስን ከልስትራን ቤተ ክርስቲያን ወሰደ (16፡1-2)፣ ሱሲጳጥሮስን ከቤርያ፣ አርስጥሮኮስንና ሰኮንደስን ከተሰሎንቄ፣ እና ጋይዮስን ከደርቤ (20፡4) ወስዷል። እነዚህ ሰዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዴት ማገልገል እንደሚችሉ ተምረዋል። አገልጋይነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ለሰፋፊ አገልግሎት ተመርጠዋል።

ስለዚህ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን እንደሚዘጋጅ ሰው ፣ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል እድሎችን መፈለግ አለብህ። የአገልግሎት እድሎች በሚፈጠሩበት ጊዜ በጎ ፈቃደኛ ለመሆን ዝግጁ መሆን አለብህ። አጥቢያ ጉባኤ አገልግሎቶች ውስጥ በመሳተፍ ጠቃሚ ልምድ ታገኛለህ፣ መንፈሳዊ ስጦታዎችህ ይገለጣሉ፣ ሥነ ምግባር ይዳብራል እና ሰፊ የአገልግሎት ጥሪ እንዳለህም ይረጋገጣል።

2. **ልምድ ባለው መጋቢ ስር ማገልገል።** ለጴንጤቆስጤያዊ አገልግሎት የዝግጅት ሌላው ውጤታማ ዘዴ የአማካሪነት ስልጠና ነው። የአማካሪነት ስልጠና ጀማሪ አገልጋይ በአንጋፋው መጋቢ እይታ ስር በማገልገል እና ከእርሱ ወይም ከእርሷ የመማር ሂደት ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያሠለጠናቸው በዚህ መንገድ ነው (ማርቆስ 3፡14-15)። “ተከተሉኝ፤ ሰው አጥማጆች አደርጋችኋለሁ” አላቸው። (ማርቆስ 1፡17)። ከኢየሱስ ጋር ሲመላለሱ እና ሲያገለግሉ፣ ማገልገልን ተማሩ። ኢየሱስም “ነገር ግን በሚገባ የተማረ ሰው ሁሉ እንደ መምህሩ ይሆናል” (ሉቃስ 6፡40) በማለት አብራርቷል።

ሌሎች የአማካሪነት ስልጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች ሙሴ እና ኢያሱ (ዘፀ. 24፡12-13)፣ ዔሊ እና ሳሙኤል (1ሳሙ. 2፡11)፣ ኤልያስ እና ኤልሳዕ (1 ነገ. 19፡19-21) እና ጳውሎስ እና ሚስዮናዊው ይሄውም ጢሞቴዎስን፣ ቲቶን፣ ሉቃስን እና ሌሎችን ጨምሮ ናቸው። ልምድ ባለው መጋቢ ስር ማገልገል ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ግንዛቤ እንድታገኝ እና ስለ እረኝነት ሥራ እንድትማር ያስችልሃል።

3 **ከአገልግሎት ቡድኖች ጋር በመተባበር።** በአገልግሎት ቡድኖች ውስጥ ከሌሎች ጋር በመጠመድ ጠቃሚ ተሞክሮ ማግኘት ትችላለህ። እነዚህ ቡድኖች የጸሎት ቡድኖችን፣ የወንጌል አገልግሎት ቡድኖችን፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ቡድኖችን እና ሌሎችንም ሊያካትቱ ይችላሉ። በቡድን ውስጥ ከሌሎች ጋር የመሥራት አንዱ ጥቅም በአገልግሎት ውስጥ ከወገኖች ጋር ተስማምቶ መሥራት እንድትችል ለመማር ይረዳል።

## መደበኛ ባልሆነ ትምህርት

ራስህን ለአገልግሎት የምታዘጋጅበት ሌላው መንገድ “መደበኛ ባልሆነ ትምህርት” ነው። መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ትምህርት ቤት ገብተን ከምንማረው ውጭ የሚከሰት ትምህርት ነው። መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት ስላልተደገፈ በግዴለሽነት ወይም በቸልተኛ ሊታይ አይገባም። ሆን ተብሎ ከተሰራበት ውጤታማ ሊሆን ይችላል። መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን፣ መጽሃፎችን እና መጣጥፎችን ማንበብ፣ ኮንፈረንስ ላይ መገኘት እና መማርን እና ሌሎችንም ሊያካትት ይችላል፡-

**1. የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት።** የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መደበኛ ያልሆነ አንዱ ጠቃሚ የሥልጠና ዘዴ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በየአመቱ ማንበብ ጠቃሚ ልምምድ ነው። ከቅዱሳት መጻህፍት አጠቃላይ ፍሰት ጋር እንድትተዋወቅ ይረዳል። ሌላው ጠቃሚ መንገድ አንድን የተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ደጋግሞ በማንበብ ነው። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር “መጽሐፍ ቅዱስን የማወቅ ሚስጥሩ ማንበብ ሳይሆን እንደገና ማንበብ ነው” ብለዋል። አንድን መጽሐፍ ብዙ ጊዜ ስታነብ በውስጡ ስለያዘው በርካታ እውነቶች የበለጠ ማስተዋል ትችላለህ።

መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብ ባለፈ ስልታዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልማድ ማዳበር ያስፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብ ባለፈ ስልታዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልማድ ማዳበር ትፈልጋለህ። ከተቻለ ካርታዎችን የያዘ ጥሩ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣የመፅሃፍ መግለጫዎች እና መግቢያዎች ፣የጽሑፍ አስተያየት፣ መጣጥፎች እና ሰሌዳዎች ማግኘት አለብህ።[1]

**2 መጽሐፎችን እና ጽሑፎችን ማንበብ።** እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሊያገኝ የሚችለው ሌላው ጠቃሚ የሥልጠና ዘዴ የተመረጡ መጻሕፍትንና መጣጥፎችን በጥንቃቄ ማንበብ ነው። አንድ ሰው “መሪዎች አንባቢዎች ናቸው” ሲል በትክክል ተናግሯል። ስለዚህ ትጉ አንባቢ መሆን አለብህ። ዕለታዊ ንባብ አዕምሮን ለማነቃቃት ፣ ለማስፋት እና የአስተሳሰብ ችሎታን ለማዳበር ይረዳል። እንዲሁም ስለ ህይወት እና የአገልግሎት ፈተናዎች አዳዲስ ግንዛቤዎችን ይሰጣል። በተጨማሪም የማንበብ ልማድ የቃላት አጠቃቀምን ለመጨመር ይረዳል፤ ይህ ደግሞ የንግግር ችሎህን ያሳድጋል።

ነገር ግን የምታነበውን በምትመርጥበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ። በዛሬው ጊዜ በአፍሪካ የሚገኙ ብዙ መጻሕፍትና ጽሑፎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ጽንሰ-ሐሳቦችን እና የኑፋቄ ልማዶችን ያስተዋውቃሉ (1 ጢሞ. 4:7፤ 2 ዮሐንስ 1:7-8)። ከእንደዚህ አይነት መጽሐፍት መራቅ አለብህ።

**3. ኮንፈረንስ እና ሴሚናሮች ላይ መገኘት።** በመጋቢዎች ጉባኤዎች እና ሴሚናሮች ላይ በመገኘት የአገልግሎት ክህሎትዎን የበለጠ ማዳበር ይቻላል። እነዚህ ስብሰባዎች ብዙውን ጊዜ መጋቢያን የአገልጋይነት ክህሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ለመርዳት የሚያቅዱ ናቸው። ተስፋ የቆረጡ መጋቢያንን ለማነሳሳት እና በቅዱሳት መጻሕፍት እና በቤተ ክርስቲያን ሥራ ላይ አዳዲስ ግንዛቤዎችን እንዲያገኙ ለመርዳት የበለጠ ያገለግላሉ። ሴሚናሮች በተጨማሪም የቤተ እምነት ዕቅዶችን ለመጋቢያን ያሳውቃሉ፣ እና በአገልግሎት አንድ ላይ በተጠመዱ መካከል አስፈላጊ የሆነውን የቡድን ስራ ስሜት ለማዳበር ይረዳሉ።

---

[1] አንድ ጥሩው የጴንጤቆስጤ ጥሩ የጥናት ጹሑፍ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ የሙሉ ሕይወት ጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ ”በመንፈስ ሕይወት የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ” ወይም “መጽሐፍ ቅዱስ” በመባልም ይታወቃል። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

## በመደበኛ ስልጠና

በመጨረሻም፣ ከተቻለ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ መደበኛ ስልጠና ማግኘት አለብህ። መደበኛ ስልጠና በቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶች እና ተቋማት በኩል የሚሰጥ ስልጠና ነው። የመደበኛ ስልጠና እድሎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

1. **ዓለማዊ ትምህርት።** የመጀመሪያ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና ምናልባትም የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአፍሪካ ላሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ወሳኝ ነው። እነዚህ ተቋማት ተማሪዎችን ለዘመናዊው ዓለም ህይወት ለማዘጋጀት ይረዳሉ። በእነርሱ ውስጥ፣ ተማሪዎቹ ማንበብ፣ መጻፍ እና የሂሳብ ስራዎችን ይማራሉ.። ስለ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ እና ሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮችን ይማራሉ። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢነት አገልግሎ ለሚዘጋጅ፣ የት/ቤት ጥናት ጥቅሙ እጅግ የላቀ ነው። የማወቅ ጉጉት ለመቀስቀስ፣ አስተሳሰብን ለማስፋት እና በህብረተሰቡ ውስጥ ወቅታዊ ጉዳዬችን ለማሳወቅ ያግዛሉ።

2. **የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋማት እና ኮሌጆች።** ከተቻለም በዕውቅና ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ወይም ኮሌጅ ማጥናት የበለጠ አስፈላጊ ነው። ለሕክምና ተማሪ መደበኛውን የሕክምና ሥልጠና ችል ማለት ምንኛ ሞኝነት ነው! በተመሳሳይ መልኩ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን አላማ ያለው ሰው መደበኛውን የአገልጋይነት ስልጠና ውድቅ ማድረግ ሞኝነት ነው። ብዙ ቤተዕምነቶች መጋቢያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲማሩ ያስገድዳሉ። ቤተ ክርስቲያን ብታስገድድም ባታስገድድም ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መደበኛ የአገልጋዮች ሥልጠና መከታተል አለበት።

3. **የኤክስቴንሽን ጥናቶች።** አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች የኤክስቴንሽን እና በተልዕኮ ትምህርቶችን ይሰጣሉ። እነዚህ ትምህርቶች በአካል፣ በፖስታ ወይም በኢንተርኔት በኩል ሊቀርቡ ይችላሉ። መጋቢው እቤት እያለ እና በአገልግሎት ላይ እያለ ስልጠና እንዲያገኝ አመቺ ናቸው። በመሆኑም መጋቢው እውቀቱን እና ችሎታውን የሚያጎለብትበት ጥሩ መንገድ ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ በመላው አፍሪካ የሚገኙ የጉባኤ እግዚአብሔር አቢያተ ክርስቲያናት ከ300 በላይ የአገልጋዮች ማሰልጠኛ ተቋማትን ያስተዳድራሉ። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ለጉባኤ እግዚአብሔር እና የየጉባኤ እግዚአብሔር ላልሆኑ ተማሪዎች ስልጠና ይሰጣሉ። የአጥቢያህ መጋቢ በአካባቢህ ያለውን ትምህርት ቤት (ወይም ትምህርት ቤቶችን) እንድታገኝ ሊረዳህ ይችላል።

4. **የድህረ ምረቃ ጥናቶች።** በአፍሪካ ያሉ አንዳንድ የጴንጤቆስጤያዊ አገልጋዮች የድህረ ምረቃ ወይም የሴሚናሪ ትምህርት ለመከታተል ይፈልጋሉ። ይህ በተለይ በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች እና ሴሚናሮች ውስጥ ለሚያስተምሩት አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ እውቅና ባለው የጴንጤቆስጤያዊ ሴሚናሪ የድህረ ምረቃ ትምህርት መከታተል ደግሞ አስፈላጊ ነው። በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ በርካታ የጉባኤ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያናት የማስተርስ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አሉዋቸው። የዶክትሬት ጥናት በፓን አፍሪካ ቲዎሎጂካል ሴሚናሪ (PAthS) በኩል ይሰጣል። PATHS ሙሉ እውቅና ያለው ሴሚናር ሲሆን በሎሜ፣ ቶጎ በሚገኘው የጉባኤ እግዚአብሔር የሚተዳደር፣ በሌሎች የአፍሪካ አገሮችም የተስፋፋ ነው። ጥናቶች በእንግሊዝኛ እና በፈረንሳይኛ ይሰጣሉ።

# ዘላቂ ዝግጅት

በእውነቱ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለአገልግሎት የሚደረግ ዝግጅት አያልቅም። የዕድሜ ልክ ተማሪ መሆን አለብህ። ሕይወትህ ቀጣይነት ባለው ልህቀት ፍለጋ መታወቅ አለበት። ጳውሎስ ይህን ሁሉ

አግኝቻለሁ ወይም ፍጹም ሆኛለሁ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ እኔን የራሱ ያደረገበትን ያን፣ እኔም የራሴ ለማድረግ እጣጣራለሁ ይላል (ፊልጵ.3፡12)።

ይህ ልህቀት ፍለጋ በህይወትህ ሁሉ መቀጠል አለበት። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ለመኖር በመፈለግ እና በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት እና ቅዱሳት መጻህፍትን በማሰላሰል መንፈሳዊ ትምህርቶችን በመለማመድ እራስህን በመንፈሳዊ ሕይወት ማዘጋጀቱን መቀጠል አለብህ።[2] መደበኛ በሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት፣ እና መንፈስ ቅዱስ ከመራህ፣ የተሻለ ስልጠናን በመከታተል እራስህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልክ ማዘጋጀቱን መቀጠል አለብህ።[3]

በተጨማሪም እራስህን በሥነ ምግባር ሕይወት ለማሳደግ ያለማቋረጥ መሻት አለብህ። ሰሎሞን አረማመድህን በጥንቃቄ እያሰብክ ልብህን ከክፉ ጠብቅ ይላል (ምሳ. 4፡23-27)።[4] በመጨረሻም፣ እንደ ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እራስህን በእውቀት እና በስሜት ብስለት ማዘጋጀቱን መቀጠል አለብህ። ይህንንም በመደበኛ ንባብና በማጥናት እና የእግዚአብሔር መንፈስ እና ቃል በሕይወታችን በኃይል እንዲሠሩ በመፍቀድ የክርስቶስን መልክ እንዲመስል በመፍቀድ (2ቆሮ. 3፡18) ማድረግ ትችላለህ።

---

[2] ስለ መንፈሳዊ ዝግጅት ተጨማሪ“ጠንካራ የማደር ልማድ”ሚለውን ምዕራፍ 15ን ተመልከት፡

[3] የጴንጤቆስጤ ፓስተር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ስላለው ግንኙነት ለበለጠ፣ “መጽሐፍ ቅዱስን ያምናል” የሚለውን ምዕራፍ 9ን ተመልከት።

[4] ስለ ሥነ ምግባራዊ ዝግጅት ተጨማሪ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 3ን ተመልከት፡ “የመልካም ሥነምግባር ሰው”።

# ~ ክፍል 2 ~

# ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዬች

# ~ ምዕራፍ 5 ~

# የአገልግሎት ቅድሚያ

አንድ አንጋፋ መጋቢ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር ተቀምጦ ሳለ አንድ ተማሪ እንዲህ ሲል ጠየቀው፡- “መጋቢ፣ እንዴት እንዲህ ያለ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን መገንባት ቻልክ? የአገልግሎት ስኬትህ ምክንያት ምንድን ነው?” መጋቢው የሰጠው መልስ ተማሪዎቹን ያስገረመ ነበር። “የተሻለ ነገር ለማድረግ ጥሩ የምትለውን መተው አለብህ” አላቸው። ግራ የተጋባውን የተማሪዎቹን ፊት ሲመለከት፣ “በህይወት ውስጥ ልታደርጋቸው የምትችላቸው ብዙ ጥሩ ነገሮች አሉ። ዓለም ብዙ ፍላጎቶችን ታቀርብላችኋለች። የቤተክርስቲያናችሁ አባላት እና ሽማግሌዎች ከእናንተ የሚጠብቁት ነገር አለ። ሌሎች መጋቢያን የሚያደርጉትን እንዲሁ እንድታደርጉ ይጠብቃሉ።

አንጋፋው መጋቢ በመቀጠል፣ “እነዚህ ሁሉ ነገሮች ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ወንድ ወይም ሴት፣ ‘ጌታ ሆይ፣ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?’ ብለህ ጠይቀው፤ ከዚያም አንዴ የእግዚአብሔርን ድምፅ ከሰማህ የሚናገረውን ለማድረግ መቁረጥ አለብህ። ሌሎች የሚሉት እና የሚያስቡት ነገሮች ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚነግርህ ነገር የተሻለ ነው። ሌሎች ነገሮችን ማድረግ እንድትችል የሚረዱህን ሰዎችን እግዚአብሔር ወደ ቤተ ክርስቲያናችሁ ያመጣል። አንተ ግን ምንጊዜም አምላክ እንድታደርግ ያዘዘህን ነገር በማድረግ ላይ ማተኮር አለብህ።

አንጋፋው መጋቢ የአገልግሎትን ቅድሚያ ስለማስቀመጥ እያወራ ነበር። ቅድሚያ የሚሰጠው በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፣ አንድ ሰው ሌሎች አነስተኛ አስፈላጊ ነገሮችን ከማድረግ በፊት የሚያደርገው ነገር ነው ።

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅድሚያ

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከይሁዳ ወደ ገሊላ እየሄዱ ነበር። ኢየሱስ በመንገድ ላይ ቆም ብሎ፣ "በሰማርያ ላልፍ ይገባኛል" (ዮሐንስ 4፡4) አላቸው። ይህ ሁኔታ ደቀ መዛሙርቱን ግራ ሳያጋባቸው አልቀረም ምክንያቱም ወደዚያ ለመድረስ ከዋናው ጎዳና ወጥተው መሄድ ነበረባቸው። ወደ ሲካር ከተማ ሲደርሱ ኢየሱስ በሰማርያ በኩል ማለፍ ያለበት ለምን እንደሆነ አወቁ። የመዳንን መልእክት ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ አንዳንድ የጠፉ ሰዎች ነበሩ። እናም ለደቀ መዛሙርቱ መከሩን ስለማጨዱ አስተማራቸው።

በሌላ ጊዜ፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ "ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ" ብሏቸዋል (ማቴ. 16፡18)። በኋላም "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" ብሎ አዘዛቸው (ማቴ. 28፡19)። በእያንዳንዱ በእነዚህ አጋጣሚዎች ኢየሱስ ለራሱም ሆነ እነርሱ ስላስቀመጣቸው ቅድሚያዎች እየተናገረ ነው።

ሐዋርያት የጌታቸውን ምሳሌ በመከተል ለአገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች አስቀምጠዋል። ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች ክርስቶስ የሰጣቸውን ሥራ መሥራት ነበር። አንድ ቀን የቤተ ክርስቲያን አባላት ቅሬታ ይዘው ወደ ሐዋርያት መጡ። መበለቶቻቸው በየዕለቱ በሚደረገው የምግብ አከፋፈል ችላ ይባሉ ነበር፤ ሐዋርያትም ችግሩን እንዲፈቱላቸው ይፈልጉ ነበር። ሐዋርያት ግን ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች አስቀድመው አስቀምጠው ነበር ስለዚህም ለሕዝቡ እንዲህ ሲሉ መለሱ፡ - "እኛ የማእዱን አገልግሎት ለማስተናገድ ስንል የእግዚአብሔርን ቃል አገልግሎት መተው አይገባንም" (ሐዋ. 6፡2)።

ችላ የተባሉትን መበለቶችን መንከባከብ ጥሩ እና አስፈላጊ ነገር ቢሆንም ክርስቶስ ሐዋርያቱን እንዲያደርጉ ያዘዘው አልነበረም። ስለዚህ እነርሱ ለጸሎትና ለስብከት ቅድሚያ እየሰጡ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናትን እንዲመርጡ ጠይቀዋል። በዚህም ምክንያት "የእግዚአብሔር ቃል ተስፋፋ። በኢየሩሳሌም ያሉ የደቀ መዛሙርት ቍጥር በፍጥነት ጨመረ፣ ብዙ ካህናትም ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ" (ቁ. 7)።

ይህ ምዕራፍ ዛሬ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በአገልግሎት ቅድሚ ሊሰጡዋቸው ስለሚገቡ አስፈላጊ ጉዳይ ያብራራል።

# የአገልግሎት ቅድሚያዎችን መወሰን

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? እርሱ ወይም እርሷ ሊያደርጋቸው የሚችላቸው ብዙ መልካም ነገሮች ቢኖሩም፣ የግድ ማድረግ ያለባቸው ጥቂት ነገሮች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ሰባቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች (1) የእግዚአብሔርን ተልእኮ ማገልገል፣ (2) የእግዚአብሔርን ጥሪ መፈጸም፣ (3) የጠፉትን መድረስ፣ (4) የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ፣ (5) መጸለይ፣ (6) የጴንጤቆስጤያዊ እሴቶችን መጠበቅ እና (7) የእግዚአብሔር ሕዝብ ለአገልግሎት ማስታጠቅ ናቸው። እነዚህን የአገልጋዮች ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እያንዳንዳቸውን በጥልቀት እንመልከታቸው፡-

## የእግዚአብሔርን ተልእኮ ማገልገል

ከሁሉ በፊት፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለማገልገል ቅድሚያ መስጠት አለበት። ኢየሱስ ከምድረ በዳ ከተፈተነ በኋላ ወደ ገሊላ ተመለሰ። በዚያም በናዝሬት ወደሚገኘው ምኩራብ ገባና "የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆችም ወንጌልን እሰብክ ዘንድ... የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል" የሚለውን የኢሳይያስ ጥቅልል ማንበብ ጀመረ። (ሉቃስ 4፡18-19) ኢየሱስ ለህይወቱ እና ለአገልግሎቱ የአባቱን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ያውቃል።

አብ ተልዕኮውን ለማገልገል እንደላከው ተረድቶል። አብ ነፍሱንም ለሰው ሁሉ ቤዛ አድርጎ እንዲሰጥ ልጁን ልኮ ነበር (ማቴ. 20፡28)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እንደ ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለማገልገል እራስህን መስጠት አለብህ። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ "አብ እንደ ላከኝ እኔ እልካችኋለሁ" ብሏቸዋል (ዮሐንስ 20፡21)። እግዚአብሔር ኢየሱስን ተልዕኮውን ለማገልገል ወደ ዓለም እንደላከው ሁሉ፣ ኢየሱስ አሁን አንተን በተመሳሳይ ወደ ዓለም ልኮሃል። የእግዚአብሔር ተልእኮ፣ አንዳንድ ጊዜ ሚሲዮ ዴኢ እየተባለ የሚጠራው፣ በምድር ላይ ካሉ ነገዶች፣ ቋንቋዎች እና ህዝቦች ሁሉ ሰዎችን መዋጀት እና መጥራት ነው (ራዕ. 5፡9)።[1]

## የእግዚአብሔርን ጥሪ መፈፀም

ሁለተኛ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በእርሱ ወይም በእርሷ ህይወት ላይ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመፈጸም ቅድሚያ መስጠት አለበት። ኢየሱስ ትኩረቱን ከአብ ጥሪ ላይ አንስቶ አያውቅም። በአስጨናቂው ሰዓት እንኳ፣ "ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይፈጸም" (ሉቃስ 22፡42) በማለት ወደ አባቱ ጸለየ። በተመሳሳይ መልኩ፣ በአፍሪካዊው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢም የእግዚአብሔርን ጥሪ በእርሱ ወይም በእርሷ ህይወት ላይ መረዳት አለበት፣ እናም ጥሪውን ለመፈጸም መጣር አለባቸው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አገልጋዮቹ የሚሮጡበትን መንገድ አዘጋጅቷል። እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ያንን የራሱን መንገድ ማግኘት አለበት። መንገዱን እስክትጨርስ ድረስ በዚያ መንገድ ልትቆይ ይገባል (ዕብ. 12፡1-2፤ 2 ጢሞ. 4፡7)።

## የጠፉትን መድረስ

ሦስተኛ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የጠፉትን ለመድረስ ቅድሚያ መስጠት አለበት። ይህ ኢየሱስ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነበር። "የሰው ልጅ የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን መጣ" ብሎ መስክሯል (ሉቃስ 19፡10)። ክርስቶስን ለመከተል ለሚፈልጉ ሁሉ የጠፉትን መድረስ ቀዳሚ መሆን አለበት። ኢየሱስ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር. 16፡15) በማለት አዞአል።

ይህ የክርስቶስ ትእዛዝ ከሰማይ እስኪመለስ ድረስ ጸንቶ ይኖራል (ማቴ. 24፡14)። እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በመንፈስ ለታጠቀ የስብከተ ወንጌል እና ተልዕኮ ቤተክርስቲያንን በማስተባበር መምራት አለብህ። ይህንን፤ በሁለት መንገዶች ማድረግ ትችላለህ፡፡

በመጀመሪያ፣ ወንጌልን ለሌሎች በንቃት በማካፈል፣ ወደ ጌታ ለመምራት ባለህ ፍላጎት ለቤተ ክርስቲያን ምሳሌ መሆን አለብህ። የቤተ ክርስቲያኑ አባላት አንተ ስትመሰክር ሲያዩ፣ እነርሱም እንዲመሰክሩ ይበረታታሉ። ሁለተኛ፣ ለተልዕኮ በልግስና በመስጠት፣ እና ወንጌል ላልደረሳቸው የአፍሪካ እና ሌሎች ሕዝቦች ከልብ በመጸለይ ለጠፉት ያለህን አሳቢነት ማሳየት አለብህ። ቤተ ክርስቲያንንም ማስተባበር አለብህ። በቤተ ክርስቲያኑ መርሃ ግብር እና በጀት አወጣጥ ውስጥ የስብከተ ወንጌል እና ተልእኮ ዋና ቅድሚያ መስጠት አለብህ።[2]

---

[1] የእግዚአብሔርን ተልእኮ መፈጸም አስመልክቶ ስለ ጴንጤቆስጤ መጋቢ ሚና ለበለጠ፣ ምዕራፍ 31 "ተልእኮ አመራር" እና ምዕራፍ 40 እና "በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተልእኮ ፕሮግራም ማዘጋጀት ይመልከቱ።

[2] የጠፉትን ስለማግኘት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 37ን ተመልከት፡- "የጠፉትን ወንጌላዊነት" ተመልከት።

## ቃሉን መስበክ

አራተኛ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን ቃል ለማወጅ ቅድሚያ መስጠት አለበት። ጳውሎስ በእምነት ልጁን ጢሞቴዎስን "ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም " (2 ጢሞ. 4:2)። ቃሉን መስበክ ወንጌልን ለጠፉት ማወጅ እና አማኞችን በጌታ መንገዶች ማስተማር እና ማበረታታትን ያካትታል። ኢየሱስ " "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር. 16፡15) በማለት አዘዘ። እንዲሁም "በጎቼን ጠብቅ" (ዮሐ.21፡17) በማለት አዝዟል። ለመስበክ እና የእውነትን ቃል በትክክል ለመያዝ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ አለብህ (2ጢሞ. 2፡15)። ይህን ለማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል በጉጉት የምትማር መሆን አለብህ።[3]

## መጸለይ

አምስተኛ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለጸሎት ቅድሚያ መስጠት አለበት። በቁርጠኝነት የመጸለይን ህይወት መለማመድ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለህ ጥገኝነት ያሳያል። ይህን በማድረግ የኢየሱስንና የሐዋርያትን ፈለግ እየተከተልክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር፣ በምድር ላይ በኖረበት ዘመን፣ "ጸሎትንና ልመናን ከታላቅ ጩኸትና ከእንባ ጋር አቀረበ፤" (ዕብ. 5:7፤ ማር. 1:35፤ ሉቃስ 5:16)። ስለ ሐዋርያት ሲናገር "ያለ ማቋረጥ ተግተው ይጸልዩ ነበር" (ሐዋ. 1፡14፤ 3፡1፤ 6፡2-4፤ 10፡9)።

ጸሎት ሁኔታውን ብቻ ሳይሆን የሚጸልይውን ሰውም ይለውጣል። የተሃድሶ አራማጁ ማርቲን ሉተር የጸሎትን ጥቅም የተረዳ ነበር። በአንድ ወቅት "ዛሬ የምሰራው ብዙ ነገር ስላለኝ የመጀመሪያዎቹን ሶስት ሰዓታት በጸሎት አሳልፋለሁ!" ብሎ ተናግሮ እንደነበር ይነገራል። በተመሳሳይ መንገድ ጸሎት በእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሕይወት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን አለበት።[4]

## የጴንጤቆስጤያዊ እሴቶችን መደገፍ

ስድስተኛ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በአገልግሎቱ የጴንጤቆስጤያዊ እሴቶችን ለመጠበቅ መጣር አለበት። የጴንጤቆስጤያዊ እሴቶች አንድን ሰው እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ አማኝ የሚገልጹ በጽኑ ሁኔታ የተያዙ እምነቶች እና ቁርጠኝነት ናቸው። አንድ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሊያከብራቸው የሚገቡ ሶስት ዋና ዋና እሴቶች ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ ለእግዚአብሔር እና ለተልእኮው የጸና ታማኝነት እና ለእግዚአብሔር መንፈስ መንቀሳቀስ ክፍትነት ናቸው።

ይህ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ግልጽነት አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ ማየትን ይጨምራል። ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያቱ ይህንን አስፈላጊነት አጽንዖት ሰጥተዋል።[5] ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከመመለሱ በፊት ተከታዮቹን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፡- "ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ... ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" (ሐዋ. 1፡4-5፤ ሉቃስ 24 :49) ከዓመታት በኋላ፣ ጳውሎስ በኤፌሶን አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ባገኛቸው ጊዜ፣ የጠየቃቸው የመጀመሪያ ጥያቄ፣ "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" የሚል ነበር። (የሐዋርያት ሥራ 19:2))

---

[3] ስለ የጴንጤቆስጤ መጋቢ የስብከት አገልግሎት ተጨማሪ ለማግኘት ምዕራፍ 16ን ተመልከት፡- "በመንፈስ የተቀቡ ስብከት።

[4] ስለ ጴንጤቆስጤ መጋቢ የጸሎት ህይወት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 8ን ተመልከት፡ "የጸሎት ቅድሚያ የሚሰጠው።

[5] ስለ ጴንጤቆስጤ እሴቶች ለበለጠ፣ ምዕራፍ 10ን ተመልከት፡ "የጴንጤቆስጤ እውነትን ይደግፋል"፤ ምዕራፍ 11: "የጴንጤቆስጤ ልምድ እና ልምምድ ያበረታታል"; እና ምዕራፍ 12፡ "የጴንጤቆስጤ ትውፊቶችን ያደንቃል"

ኢየሱስ እና ሐዋርያት ሁሉም አማኞች በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ አጥብቀው ይናገሩ ነበር ምክንያቱም ይህ ልምምድ “በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳም ሁሉ፣ በሰማርያ፣ እስከ ምድር ዳርም ድረስ” የክርስቶስ ምሥክር እንዲሆኑ ኃይል እንደሚሰጣቸው ስለሚያውቁ ነው (የሐዋርያት ሥራ 1:8) ።

## የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማስታጠቅ

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን ህዝብ ለአገልግሎት ማሰልጠን ቅድሚያ መስጠት አለበት። ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ መጋቢነት ከሚጫወተው ዋና ተግባር አንዱ “[የክርስቶስን] ሰዎች ለአገልግሎት ሥራ ማስታጠቅ” እንደሆነ ይገነዘባል (ኤፌ. 4፡12)። ይህ ማለት አንተ እንደ መጋቢ በጎቹን ከመንከባከብ የበለጠ ነገር ማድረግ አለብህ፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ጠቃሚ የመንግሥቱ አካላት እንዲሆኑ ማሳደግ አለብህ ማለት ነው። ስለዚህ በአገልግሎትህ ደቀ መዛሙር ማድረግን ቅድሚያ መስጠት አለብህ።[6]

# የአገልግሎት ቅድሚያዎች መከታተል

ከላይ ያየናቸውን ሰባት የጴንጤቆስጤ መጋቢን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች ከመረመርክህ አሁን እንደራስህ ልትወስዳቸው መወሰን አለብህ። ስለ እነዚህ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች በመፅሃፍ ውስጥ ማንበብ አንድ ነገር ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በልብህ ገጾች ላይ እንዲጽፋቸው መፍቀድ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ይህ እንዲሆን እነዚህን መርሆች ቅድሚያ ወደ ሚሰጣቸውን ነገሮች የመቀየር ሂደት እና እነዚያን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ወደ አገልግሎት ተግባራት ለመቀየር ቃል መግባት ያስፈልጋል። ይህንን ሂደት እንመልከተው:-

## ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለመመስረት

ሂደቱ የሚጀምረው ብቃት ያለው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን ትጋት እንደሚያስፈልግ በማወቅ ነው። የአገልጋይነት ብቃት የሚገኘው ከረጅም ጉዞ በስተ መጨረሻ ነው እና እንደማንኛውም ጉዞ፣ ይህ ጉዞ የሚጀምረው መድረሻን በመምረጥ ነው። መድረሻ ላይ ለመድረስ እቅድ ማውጣት እና በመተግበር ያስፈልጋል። ከላይ የተጠቀሱትን ሰባት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች በራስህ አገልግሎት እና በቤተክርስቲያንህን አገልግሎት ውስጥ ለመመስረት ለጉዞው መሰጠት ያስፈልግሃል።

ሰባቱን በአገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች በማስታወሻ ደብተር ውስጥ በመመዝገብ ጉዞውን መጀመር ትችላለህ። ከዚያ ይህንን ዝርዝር እንደ ዕለታዊ የጸሎት መመሪያ መጠቀም ይቻላል። በየቀኑ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ስትጸልይ እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀሳቦች በመንፈስህ ውስጥ እንዲያስቀምጥ እግዚአብሔር ጠይቅ። ይህን ካደረግክ ለውጥ ይመጣል። መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች በልብህ ጽላት ላይ መጻፍ ይጀምራል። በሃሳብ ደረጃ የነበሩት እነዚህ ነገሮች ከጊዜ በኋላ ወደ አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ሆነው በተግባር መገለጥ ይጀምራሉ።

ስትጸልይ፣ “በአሁኑ ጊዜ ለአገልግሎት ቅድሚያ የምሰጣቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?” ብለህ ራስህን ጠይቅ። አሁን በአገልግሎት ቅድሚያ የምትሰጠውን ለማወቅ አሁን ላይ ጊዜህን እና ጉልበትህን የምታፈሰውባቸው ልምዶች ምንድን ናቸው ብለህ ጠይቅ። ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ነገሮች ዘርዝር።

[6] የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስለማሳደግ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 16:- “ውጤታማ ትምህርት” እና ምዕራፍ 25: “ሰውን ማጠናከር” የሚለውን ተመልከት።

ከዚያም "እነዚህ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ኢየሱስና ሐዋርያቱ ካስቀደሙት ነገሮች ጋር የሚጣጣሙት እንዴት ነው? ቀጥሎ፣ በራስህ ግምገማ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እራስዎን ይጠይቅ።

የእግዚአብሔርን ተልእኮ በማገልገል ረገድ ምን ያህል እየሰራሁ ነው?

- በሕይወቴ እና በምመራው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ላይ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመፈጸም ምን ያህል እየሰራሁ ነው?
- በአካባቢዬ እና በዓለም ዙሪያ የጠፉትን ለመድረስ ምን ያህል እየሰራሁ ነው?
- የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ ረገድ ምን ያህል እየሰራሁ ነው?
- የግል የጸሎት ሕይወቴ እና የምመራው የቤተ ክርስቲያን የጸሎት አገልግሎት ምን ያህል ውጤታማ ነው?
- በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ የጴንጤቆስጤያዊ እሴቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ምን ያህል እየሰራሁ ነው?
- የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት በማስታጠቅ ረገድ ምን ያህል እየሰራሁ ነው?

መልሶችህን በማስታወሻ ደብተርህ ውስጥ ፃፍ። ቀጥሎ "በሕይወቴና በአገልግሎቴ እነዚህን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እያንዳንዳቸውን በተሻለ መንገድ ለማሳካት የተለየ ምን ማድረግ አለብኝ?" ብለህ ራስህን ጠይቅ። እንደገና፣ መልሶችህን በማስታወሻ ደብተርህ ውስጥ ፃፍ እና በእነርሱ ላይ በየቀኑ መጸለይህን ይቀጥል።

## ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች መተግበር

እነዚህን በአገልጋዮች ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች እንደራስህ ከተቀበልክ በኋላ፣ ወደ ራስህ አገልግሎት እና ወደ ቤተክርስቲያን አገልግሎት መተግበር መጀመር አለብህ። ይህንን ለማድረግ የሚከተሉትን ስልቶች መጠቀም ያፈልጋል፡-

**1. ግንዛቤህን አሳድግ**። ስለ እነዚህ ሰባት በአገልግሎት ቅድሚያ ስለ ሚሰጣቸውን ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ግንዛቤ መጨመር ያስፈልግሃል። ቅዱሳት መጻሕፍትን በመፈለግ እና በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በተጨማሪ በማጥናት ይህንን ማድረግ ይቻላል። ኢየሱስ እውነትን በመፈለግ "ቅዱሳት መጻሕፍትን በትጋት እንድንማር" አዞናል (ዮሐንስ 5፡39)። ስታነብ "መንፈስ ቅዱስ ምን እያለኝ ነው?" ብለህ ራስህን ጠይቅ። አዲስ ግንዛቤዎችዎን በማስታወሻ ደብተርህ ውስጥ ፃፍ። ከተቻለ በእነዚህ ርዕሶች ላይ ጥሩ መጽሃፎችን ማግኘት እና ማንበብ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።[7]

ስለ እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ያለህን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዳህ ሌላው መንገድ ስለነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ብዙ ጊዜ መስበክና ማስተማር ነው። ይህ ስልት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያለህን ግንዛቤ ከማሳደጉም በላይ አባሎቻችህን ለቀጣዩ እርምጃ ማለትም እነዚህን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ቤተክርስቲያን አገልገሎት ተግባራዊ ለማድረግ ያዘጋጃል።

**2 እቅድ ማውጣት።** በመቀጠል፣ እነዚህን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች በራስህ አገልግሎት እና በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ ማውጣት ያፈልጋል። ይህንን ለማድረግ

---

[7] በአፍሪካ ሆፕ ዲስከቨሪ ተከታታይ ሥራ የታተመው በፖል ዮርክ የተዘጋጀው የተልዕኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አንዱ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው።

ስለ እያንዳንዱ ቅድሚያ ስለ ሚሰጣቸውን ጉዳዬች የቤተክርስቲያንን ግንዛቤ ማሳደግ ያስፈልጋል። የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመለስ መጀመር ትችላለህ።

- የእግዚአብሔርን ተልእኮ በተሻለ መንገድ ለማገልገል ቤተክርስቲያኔን ለመምራት ምን ማድረግ አለብኝ?
- የእግዚአብሔርን ጥሪ በህይወቴ እና በምመራው ቤተክርስቲያን በተሻለ መንገድ ለመታዘዝ ምን ማድረግ አለብኝ?
- ቤተክርስቲያንን የጠፉትን በብቃት ለመድረስ እንዴት መምራት አለብኝ?
- በቤተክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በተሻለ ሁኔታ ለመስበክ እና ለማስተማር ምን ማድረግ አለብኝ?
- በቤተክርስቲያን ውስጥ ጸሎትን የበለጠ ለማበረታታት ምን ማድረግ አለብኝ?
- ቤተክርስቲያንን ወደ ታላቅ የጴንጤቆስጤያዊ ልምድ እና ትግበራ ለመምራት ምን ማድረግ አለብኝ?
- የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት በተሻለ ሁኔታ ለማስታጠቅ ምን ማድረግ አለብኝ?

መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ ውስጥ ፃፍ እና በተደጋጋሚ ገምግም።

**3. እቅድህን ተግብር።** ቀጥሎ እቅድህን መተግበር አለብህ.። ይህ ማለት ያቀረብከውን ስልቶች ተግባራዊ ለማድረግ ወደፊት መሄድ ያስፈልጋል ማለት ነው። በእቅድህ ወደፊት በምትራመድበት ጊዜ፣ ያለማቋረጥ ደጋግመህ እድገትህን መገምገም ያስፈልጋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በእቅዱ ላይ አስፈላጊውን ማስተካከያ አድርግ።

ስኬትን በአንድ ጀምበር እንደማታገኝ አስተውል። ስኬት ጊዜ ይወስዳል፣ በመሆኑም ችግሮች ሲመጡ መጽናት ያስፈልጋል።. ይህን ካደረግህ ከጊዜ በኋላ ቤተክርስቲያን መለወጥ ትጀምራለች። ክርስቶስ እንድትሆን ያሰባት ኃያል ቤተክርስቲያን ትሆናለች። በሐዋርያው ቃል ተበረታታ “በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት ተስፋ ካልቈረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን” (ገላ. 6:9)።

---

በአፍሪካ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤ መጋቢ በአገልግሎቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ከኢየሱስ እና ከሐዋርያት ጋር ማስማማት አለበት። ከዚያም እነዚህ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች አገልግሎታቸውን እንዲመሩ መፍቀድ አለባቸው። ይህ ሂደት የሚያታግል ሊሆን ቢችልም፣ ጥረት ማድረግ ግን ተገቢ ነው። የጴንጤቆስጤ መጋቢ ለክርስቶስ በማደር፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመስጠት እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመጋቢ የአገልግሎት ግቦቹን ማሳካት ይችላል።

# ~ ምዕራፍ 6 ~

# በግል ሕይወት ቅድሚ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች

የእናቴ ልጆች ተቆጡኝ፤ የወይን ተክል ቦታዎችም ጠባቂ አደረጉኝ፤ የራሴን የወይን ተክል ቦታ ተውሁት" (መኃልየይ 1:6)። የሱላማዊቷ ልጃገረድ አሳዛኝ ቃላት ናቸው። ሱላማዊቷ የሌሎችን እርሻ በመንከባከብ የተጠመደች ስለነበር የራሷን አትንከባከብ ነበር። የምታወራው ግን ስለ ወይን አልነበረም ፤ ስለ ህይወቷ እያወራች ነበር። ከሌሎች ጋር ብዙ ጊዜ ታሳልፍ ስለነበር የራሷ ሕይወት በእንክርዳድ ተሞላ።

በሚያሳዝን ሁኔታ ይህ ተመሳሳይ ሁኔታ ዛሬ በአፍሪካ ውስጥ ያሉትን የብዙ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ህይወት ሊገልጽ ይችላል። የአገልግሎት ጉዳዮችን በመከታተል እና የሌሎችን ፍላጎቶችን በማገልገል ብዙ ጊዜ ያሳልፋሉ ሆኖም ራሳቸውን ለመንከባከብ ጊዜ የላቸውም። በውጤቱም ሁሉም ተጎጂ እየሆነ ነው ያለው። የገዛ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ተሟጦ የሚመሩት አብያተ ክርስቲያናትም ተዳክመዋል።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቅ ሾመው። በኋላም ለወጣቱ ባልደረባው ሲጽፍለት፣ "ለሕይወትህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፣ ራስህንና የሚሰሙህንም ታድናለህና " ይለዋል (1 ጢሞ. 4:16)። በዚህ መንገድ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በአደባባይ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወቱም ጭምር ጠንቃቃ እንዲሆን መክሮታል። አስተዋይ መጋቢ በምዕራፍ 5 ላይ እንደተገለጸው የአገልግሎቱን ቅድሚያ መለየት ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ ለራስ እንክብካቤም ቅድሚያ ይሰጣል። ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤ መጋቢ ሊሰጥ የሚገባውን ስድስት የግል ሕይወት ቅድሚያዎችን ይመረምራል።

# ክርስቶስን የማወቅ ቅድሚያ

ከሁሉም በላይ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከክርስቶስ ጋር ያለውን ግንኙነት ማስቀደም አለበት። አንድ መጋቢ ለሌሎች ክርስቶስን ከማሳወቁ በፊት እራሱ በደንብ ሊያውቀው ይገባል። አንድ ሰው ሌላውን ሰው ከማያውቀው ሰው ጋር እንዴት ያስተዋውቃል?

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ክርስቶስን በእውቀት እና በልምምድም ማወቅ አለብህ። በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ማን እንደሆነ እና ምን እንዳደረገ መረዳት አለብህ። በግል ግንኙነት ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖርህ ይገባል።

## ማንነቱን ማወቅ

ክርስቶስን ማወቅ ስለ እርሱ መያዝ ያለብንን እውነትን ማወቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማንነቱ እና ለምን ወደ ምድር እንደ መጣ የሚለውን ለመረዳት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚከተለውን ያስተምራል።

- እርሱ የሁሉም ነገር ፈጣሪ የዘላለም የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ1፡1-4)።
- በሥጋ የተገለጠ አምላክ ነው (1ጢሞ. 3፡16)።
- እርሱ “መሲሑ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ” ነው (ማቴ. 16፡16)።
- እርሱ ወደ አብ የሚመራ “እውነትና ሕይወት መንገድ” ነው (ዮሐ. 14:6)

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ለምን ወደ ምድር እንደ መጣ ይነግረናል፦

- “የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን” መጣ (ሉቃስ 19፡10፤ ዝከ.1 ጢሞ. 1፡15)።
- “ለማገልገል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ” መጣ።(ማር. 10:45፣ ዮሐንስ 12:27፣ ቲቶ. 2:13-14)
- “የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ መጣ” (1ዮሐ. 3፡8፤ ዕብ.2፡14)።
- “[እኛ] ሕይወት እንዲኖረን እና እንዲሞላልን” መጣ።

## እርሱን በግል ማወቅ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ኢየሱስን ማን እንደሆነ እና ለምን እንደመጣ ማወቁ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም፣ ያ በቂ አይደለም። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ክርስቶስን በግል ማወቅ አለብህ። ጌታን በግል ማግኘት አለብህ እና ከእርሱ ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ሊኖርህ ይገባል።

ጳውሎስ ስለዚህ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ በሕይወቱ በመነሳት ውስጥ ተናግሯል። በፊልጵስዩስ ላሉት አማኞች እንዲህ ሲል ጽፏል፣ “ ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኀይል እንዳውቅ፣ በሥቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመኛለሁ” (ፊልጵ. 3፡10)። ጳውሎስ ክርስቶስን ለማወቅ ያለው ፍላጎት በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ከእርሱ ጋር ድል ለመንሳት ብቻ ሳይሆን በመከራውም ለመካፈል የተዘጋጀ ነበር። ለእርሱ ለመሞት እንኳን ዝግጁ ነበር። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ክርስቶስን የማወቅ የጳውሎስን መሻት መጋራት አለበት።

## እርሱን ማወቅ

ክርስቶስን ማወቅን ማስቀደምን በሦስት መንገዶች ልትለማመድ ትችላለህ፡-

**1. በግል ልምምድ።** ሰው ክርስቶስን በመጀመሪያ ሊያውቅ የሚገባው ከእርሱ ጋር በግል በመገናኘት ነው። ይህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢንም ጨምሮ ለሁሉም የሚሆን መርህ ነው። የጠርሴሱ ሳውል ስለ ክርስቶስ ያውቅ ነበር ፤ ነገር ግን በደማስቆ መንገድ እስኪያገኘው ድረስ የግል ልምምድ አልነበረውም (ሐዋ. 9፡1-9)። በደማስቆ መንገድ ሳኦል "ጌታ ሆይ ማን ነህ?" ብሎ ጮኸ። ኢየሱስም "አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ" ብሎ መለሰ (ቁ. 5)። የሳኦል ሕይወት በዚያች ቅጽበት ተለወጠ። ክርስቶስን እንደ ጌታው እና አዳኙ አወቀው። በዚያች ቅጽበት፣ የቤተ ክርስቲያን አስከፊ አሳዳጅ የነበረው ሰው የቤተ ክርስቲያን ዋንኛ አራማጅ ሆነ።

ጳውሎስ ስለዚህ ተሞክሮ ሲናገር "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል" ሲል ጽፏል። (2ቆሮ. 5:17) የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በእዚህ መጀመር አለበት። ኢየሱስ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" (ዮሐንስ 3፡3) ሲል ተናግሯል።

**2. በእግዚአብሔር ቃል።** የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ክርስቶስን በደንብ የሚያውቅበት ሁለተኛው መንገድ እርሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በተለይም በወንጌል እና በመልእክታት ውስጥ በመገናኘት ነው። ወንጌሎች ስለ ኢየሱስ ህይወት፣ ስራዎቹ እና ትምህርቱ ይናገራሉ። መልእክቶች ደግሞ ትርጉማቸውን ያስረዳሉ። የወንጌል ትረካዎችን በማንበብ አቧራማ በሆነው የገሊላ ጎዳና ከኢየሱስ ጋር መሄድ ትችላለህ። በእግሩ ስር ተቀምጠህ ትምህርቱን ማዳመጥ ትችላለህ። በመስቀል ላይ ሲሞት ቆመህ መመልከት ትችላለህ። ባዶ የሆነውን የአዳኝህን መቃብር ውስጥ ማየት እና መልአኩ "ተነስቷል! እርሱ እዚህ የለም። "ብሎ ሲጮኽ መስማት ትችላለህ።

አንድ ወጣት የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በልቡ "የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከእርሱ ጋር በመመላለስ እና ከእርሱ እየተማሩ ለሦስት ዓመታት በማሳለፋቸው ህይወታቸው ተለውጧል። እኔም ተመሳሳይ ነገር አደርጋለሁ ።፡የሚቀጥሉትን ሦስት ዓመታት አራቱን ወንጌላት በማንበብና በማሰላሰል አሳልፋለሁ" አለ። በገባው ቃል መሰረት ወጣቱ ሰባኪ የሚቀጥሉትን ሶስት አመታት ወንጌልን በማንበብ አሳለፈ። በየደቂቃው የኢየሱስን ታሪክ በማሰላሰል አሳለፈ። ይህን በማድረጉ ሕይወቱና አገልግሎቱ ፈጽሞ ተለወጠ።

**3. በጸሎት።** የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ኢየሱስን የሚያውቅበት ሦስተኛው መንገድ ጸሎት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ጸሎትን ጨምሮ ስለ ብዙ ዓይነት ጸሎት ይናገራል፣ ልመናን፣ ኑዛዜን፣ ምልጃን፣ እና ምስጋናን ያካተተ ነው፡፡ ሆኖም ፓስተሩ ኢየሱስን የበለጠ እንዲያውቅ የሚረዳው የጸሎት ዓይነት የሕብረት ጸሎት ነው። ያዕቆብ ስለዚህ ዓይነት ጸሎት ተናግሯል። "ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ እርሱም ወደ እናንተም ይቀርባል" (ያዕቆብ 4፡8) ሲል አሳስቧል። ሙሴ የኅብረት ጸሎትን የተለማመደ ሰው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሴ ሲናገር ከእግዚአብሔር ጋር "ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር እግዚአብሔር (ያህዌ) ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት ይነጋገር ነበር" (ዘጸ. 33፡11) ይላል።

የማርታ እህት ማርያም ለዚህ ዓይነቱ ጸሎት ጥሩ ምሳሌ ነች። ኢየሱስ ቤቷን ሲጎበኝ እግሩ ስር ተቀምጣ የሚናገረውን ሁሉ በጥሞና ታደምጥ ነበር። እህቷ ግን ማርያምን ሰነፍ ነች በማለት ከሰሰቻት። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ማርያምን "[እርሷ] የሚበልጠውን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም" (ሉቃስ 10፡38-42) በማለት አመስግኗታል። ኢየሱስን ማወቅ የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቅድሚያ መሆን አለበት። ይህ አሰራር በህይወቱ እና በአገልግሎቱ መለማመድ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

# በመንፈስ መራመድን ማስቀደም

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ክርስቶስን ማወቅ ብቻ ሳይሆን እርሱ ወይም እርሷ በመንፈስ መራመድ እና መኖርን ማስቀደም አለባቸው። ጳውሎስ በገላትያ ያሉትን ክርስቲያኖች "በመንፈስ የምንኖር ከሆነ በመንፈስ እንመላለስ" (ገላ. 5፡25) በማለት መክሯቸዋል።

## በመንፈስ መመላለስ ምን ማለት ነው፡፡

በመንፈስ መመላለስ ቢያንስ ሦስት ትርጕሜ ሊይዝ ይችላል።

1. **በመንፈስ መሞላት።** በመጀመሪያ፣ በመንፈስ መመላለስ ማለት በመንፈስ መሞላት ማለት ነው (ሐዋ. 1፡4-8)። በሌላ አነጋገር አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ከመመላለስ በፊት እርሱ ወይም እርሷ በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርት እንደተቀበሉት በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለባቸው (ሐዋ. 2፡1-4)። መንፈሱን ከተቀበሉ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ኃይል መኖር እና ማገልገል ጀመሩ። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለሆነው አገልግሎታቸው አስደሳች ታሪክ ይናገራል። እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ይህን ጠቃሚ ልምድ ሊኖረው ይገባል።

2. **በመንፈስ መመራት።** ሁለተኛ፣ በመንፈስ መመላለስ በመንፈስ መመራት ማለት ነው። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጆሮውን ወይም ጆሮዋን ለመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ክፍት ማድረግ አለበት። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ሲናገር መታዘዝ አለባቸው። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ። ከዚያም በመንፈስ ይመራ ነበር (ሉቃስ 3፡21-22 ፤ 4፡1 )። ጳውሎስ እና የሚስዮናውያን ቡድኑ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዋል (ሐዋ. 16፡6-10)። ዛሬም ቢሆን ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በተመሳሳይ መልኩ በመንፈስቅዱስ መመራት አለበት። እንደ ኢየሱስ እና ጳውሎስ አንተም በመንፈስ ቅዱስ መመራት አለብህ።

3. **በመንፈስ ኃይል ማገልገል።** በመጨረሻም፣ በመንፈስ መመላለስ ማለት በመንፈስ ኃይል ማገልገል ማለት ነው። ኢየሱስ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (ሐዋ. 1፡8)። በኢየሱስም ሆነ በሐዋርያቱ ላይ የሆነው ይህ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በመንፈስ ኃይል ማገልገል ጀመሩ (ለምሳሌ፣ ሉቃስ 3፡21-22 ከ 4፡14፤ ሐዋ. 4፡31-33)። በመንፈስ ስትመላለስ፣አንተም መንፈሱ ለአገልግሎትህ ኃይል እንዲሰጥህ መጠበቅ ትችላለህ።

## በመንፈስ መመላለስ እንዴት ይቻላል ፤

አንዳንዶች ይጠይቃሉ ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በመንፈስ መኖር እና መመላለስን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ አለብኝ? በመጀመሪያ፣ ከላይ እንደተብራራው፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትህን በትክክል ማረጋገጥ አለብህ። በመንፈስ ለመሞላትህ፣ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን መጥቀስ ትችላለህ። የመጀመሪያው መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥህ በልሳኖች ትናገራለህ (ሐዋ. 2፡4፤ 10፡44-46፤ 19፡6)። ሁለተኛው ስለ ክርስቶስ ለመመስከር ኃይልን ትቀበላለክ (ሐዋ. 1፡8፤ 4፡31)።

አንዴ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላህ፣ ልብህን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በማስገዛት መኖር አለብህ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ክርስቲያኖች ያደረጉት ይህንኑ ነው። በመጀመሪያው የኢየሩሳሌም ጉባኤ፣ ሐዋርያት እና ሽማግሌዎች የአህዛብ አማኞችን ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀልን በተመለከተ ውሳኔ ሲሰጡ " ለመንፈስ ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶናል" በማለት ነበር የጀመሩት (ሐዋ. 15፡28)። አንባቢዎቻቸው ውሳኔ ከማድረጋቸው በፊት የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እንደሰሙ እንዲያውቁ ፈልገው

ነበር። በመንፈስ እንድትመላለሱ እና እንድትኖሩ የሚረዳችሁ አንዱ ልምምድ በየቀኑ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመጸለይ ጊዜ ማሳለፍ ነው (ሮሜ. 8፡26-27፤ ኤፌ. 6፡18)።[1]

# ለግላዊ እድገት ቅድሚያ መስጠት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ክርስቶስን ከማወቅ እና በመንፈስ ከመመላለስ በተጨማሪ ለግል እድገት ቅድሚያ መስጠት አለበት። እርሱ ወይም እርሷ ለጌታ የተሻለ ሆነው ለመገኘት ያለማቋረጥ መጣር አለባቸው። ጳውሎስ ሕይወትን ከሩጫ ጋር በማመሳሰል በቆሮንቶስ የነበሩትን ክርስቲያኖች የላቀ ብቃት እንዲያሳዩ አሳስቧቸዋል። “ በሩጫ ውድድር የሚሮጡ ብዙዎች እንደሆኑ፣ ሽልማቱን የሚቀበለው ግን አንዱ ብቻ እንደሆነ አታውቁምን? ስለዚህ ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ። (1 ቆሮ. 9፡24)። በተመሳሳይ መልኩ የቆላስይስ ሰዎችን “የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉት ቄጥራችሁ በሙሉ ልባችሁ አድርጉት” (ቆላ. 3፡23) በማለት አሳስቧቸዋል።

እንዲህ ያለው የልህቀት አመለካከት ከአያት ቅድመ አያቶች አይወረስም ወይም እጅን በመጫን አይተላለፍም። በአገልግሎት የላቀ ብቃትን ለማግኘት ትኩረትን፣ ቁርጠኝነትን እና በስርዓት የሚመራ ሕይወትን ይጠይቃል። በመንፈሳዊ ሕይወት የላቀ ደረጃን መፈለግ ከሌላ ሰው የተሻለ ለመሆን መሞከር አይደለም። ይልቁንም፣ ጌታን በማገልገል ረገድ ከሁሉ የተሻለውን ራስህን መሆን የሚያመለክት ነው።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የላቀ ደረጃን መከተል ካለበት ነገር አንዱ የጥናት ልማዱን ማዳበር ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ በአንዳንድ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን መካከል ጥናትን የማንቋሸሽ ጥረቶች አሉ። በመንፈስ ስጦታ የተገኘን ዕውቀት በብቸኝነት በማጉላት፣ በትጋት እና በጥናት የሚገኘን እውቀት ዝቅ ያደርጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን “የአስተዋይ ልብ ዕውቀትን ይገበያል፤የጠቢብም ጆሮ አጥብቆ ይሻታል” (ምሳ. 18፡15) በማለት ያስተምራል።

ስለዚህ እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣በቅዱስ ቃሉን እውቀት ለመጨመር ያለመታከት መጣር አለብህ። በተመሳሳይ ሁኔታም በህብረተሰብ ውስጥ ወቅታዊ ሁኔታዎችን መከታተል አለብህ። ከዚያም ሁለቱን በማጣመር ትንቢታዊ በሆነ መልኩ መጽሀፍ ቅዱሳዊ እውነትን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማዛመድ ትችላለህ። በተጨማሪም፣ መልካም ስም ያላቸው ደራሲያን ጸፉትን መጽሐፎችን ማንበብ ልማድ ማድረግ አለብህ። ይህ ልምምድ የማሰብ ችሎታን ያሳድጋል። በጥናት የላቀ መሆን በአገልግሎት የላቀ ውጤት ለማምጣት ይረዳል።

# ራስን የመንከባከብ ቅድሚያ

በአንድ ወቅት፣ አንድ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከፍተኛ ድካም እና የሰውነት ህመም አጋጠመው። አንዳች ገዳይ በሽታ ያዘኝ ብሎ በመስጋት ወደ ሐኪም ሄደ። ይሁን እንጂ ሐኪሙ ከመረመረ በኋላ ምልክቱ የመጣው በጭንቀት ምክንያት እንደሆነ ነገረው። ሐኪሙ እረፍት እና ጤናማ አመጋገብ አዘዘለት። ብዙም ሳይቆይ ፓስተሩ በአገልግሎት ጉልበቱን መልሶ አገኘ።

የአፍሪካ መጋቢያን ታታሪ ሠራተኞች መሆናቸው ይታወቃል። ይሄ ጥሩ ነው። ይሁን እንጂ ሁሉምን ነገር ለመሆን ከመሞከር መጠንቀቅ አለባቸው። የደከመ መጋቢ ለቤተሰብ እና ለቤተ ክርስቲያኑ ዕዳ ሊሆን

[1] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር የጸሎት ህይወት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 8ን ተመልከት፡ “የጸሎት ቅድሚያ የሚሰጠው።

ይችላል። ውጥረት የፓስተሩን የመጸለይ፣ የማጥናት እና የመስበክ ችሎታን ሊያሽመደምድ ይችላል። በባህሪው ላይ የበለጠ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። ለምንም ትኩረት የሌለው እና ለሰዎች የማይጨነቅ እንዲመስል ሊያደርግ ይችላል። በጉባኤው ውስጥ ብስጭት ሊያስከትል ይችላል። ይህም በመጋቢው ላይ የበለጠ ጭንቀት ይፈጥራል።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን አንዳንድ ጊዜ ዕረፍትን አይፈልጉም። ለማረፍ ጊዜ ከወሰዱ፣ ለጥሪያቸው ታማኝ እንዳልሆኑ ይሰማቸዋል። ኢየሱስ ግን እረፍት እንደሚያስፈልግ ተረድቷል በአንድ ወቅት ለደቀ መዛሙርቱ "እስቲ ብቻችሁን ከእኔ ጋር ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ እንሂድና ጥቂት ዕረፉ" ብሏቸው ነበር (ማር. 6፡31)።

ለአገልግሎቱ የሚቀና መጋቢ እግዚአብሔር ራሱ በፍጥረት በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ ማስታወስ ይኖርበታል (ዘፍ. 2፡2)። ይህን ያደረገው ስለደከመ ሳይሆን ለሰው ልጅ ምሳሌ ስለሚሆን ነው። ኢየሱስ "ሰንበት ስለ ሰው ተፈጠረች እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም" ብሏል (ማር 2፡27)። እግዚአብሔር ሕዝቡ ፈጣሪያቸውን የሚያከብሩበት፣ እና የሕይወትን ፍላጎት ለመጋፈጥ የሚያስፈልጋቸውን ጥንካሬ የሚያገኙበት ሰንበትን አዘጋጅቶ ነበር። የሰንበት ዕረፍት መርህን ከጣስን፤ በአገልግሎት ላይ ውጤታማ እንዳንሆን ያደርጋል።

ስለዚህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በየሳምንቱ አንድ ቀን ለእረፍት እና ለብርታት መመደብ አለበት። እርሱ ወይም እርሷ ይህ የመጋቢው የእረፍት ቀን፣ ወይም የመጋቢው ሰንበት መሆኑን ለህዝቡ ማሳወቅ አለበት። ፓስተሩ ቀኑን ከትዳር ጓደኛው እና ከልጆች ጋር በመዝናናት ማሳለፍ ይኖርበታል።[2]

# የግል ሕይወት ቅድስና ቅድሚያ

በምስራቅ አፍሪካ በሚታተም ጋዜጣ ላይ አንድ ታዋቂ መጋቢ ሚስቱን በዝሙት ምክንያት እንደፈታት የሚናገር አንድ ጽሑፍ ወጣ። ይህ ሰው ይቅር ሊላት ፈቃደኛ አልሆነም እና እንደገና ለማግባት መረጠ። ይህ መጋቢ ያደረገውን አይቶ፣ አንድ ሰው ለሚስቱ፣ "ፓስተሩ ሚስቱን ከፈታ፣ አንቺ ምንድን ነሽ?" በማለት እርሱም ሚስቱን ፈትቶ ወደ ሌላ ሴት ሄደ። እንደ መጋቢ የአንተ ድርጊት አንተ በምትመራው ሕዝብ ተግባር ላይ በመልካምም ሆነ በመጥፎ ተጽእኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እግዚአብሔር አርአያነት ላለው ኑሮ ጠርቶሃል። ጴጥሮስ " ነገር ግን የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤ 16ምክንያቱም "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ተብሎ ተጽፎአል" (1ጴጥ. 1፡15-16)። ጳውሎስ አንድ መጋቢ " 2እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ኤጲስቆጶስ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዐት የሚኖር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ማስተማር የሚችል፣ 3የማይሰክር፣ የማይጣላ ግን ጨዋ የሆነ፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገንዘብንም የማይወድ ሊሆን ይገባዋል" በማላት ጽፏል (1 ጢሞ. 3፡2-3)። አክሎም አንድ መጋቢ "በውጭ ሰዎች ዘንድ መልካም ምስክርነት ሊኖረው ይገባል" (ቁ. 7) ብሏል። ለቲቶ፣ ሐዋርያው አንድ ሽማግሌ "በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፣ ራሱን የሚገዛ፣ ቅን፣ ቅዱስና ጠንቃቃ ሊሆን ይገባል" ብሏል (ቲቶ 1፡7-8)።

በአፍሪካ መጋቢዎች ትልቅ ክብር አላቸው። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በቀጥታ በቃላቸው ወይም በሚናሩት ንግግር ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በሕይወታቸው ወይም በሚያደርጉት ነገር ደግሞ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ብዙውን ጊዜ መጋቢያን የሚያደርጉት ነገር

[2] ስለራስ እንክብካቤ ተጨማሪ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 13ን ተመልከት፡ "በጥሩ ሁኔታ የተያዘ ሕይወት።

ከሚናገሩት የበለጠ ተፅዕኖ ይኖረዋል። አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል በአንድ ወቅት ለመጋቢው፣ “የምትሰራው ነገር ጮክ ብሎ ይናገራል የምትናገረውን መስማት አልችልም“ ብሎታል። ስለዚህ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የቅድስና ህይወት መኖርን ከቀዳሚ ጉዳዮችዎ ውስጥ አንዱን ማድረግ አለብህ።

# የጊዜ አጠቃቀም ቅድሚያ

ጴንጤቆስጤያዊዊያን በአምልኮ ውስጥ ነጻነትን እና ስሜትን መግለጽን ተገቢ አድርገው ይመለከታሉ። ከዚህ ቀደም ያልተለማመዱትን የመንፈስ አሰራርን ለማስተናገድ አይቸገሩም። እነዚህ እሴቶች ጥሩ ናቸው ደግሞም በጭራሽ መተው የለባቸውም። ሆኖም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለደካማ ጊዜ አያያዝ እንደ ሰበብ ሊጠቀምባቸው አይገባም። እግዚአብሔር በእጃችሁ ያስቀመጠውን ገንዘብ በባላደራነት እንደምታስተዳድሩ ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ጊዜ የባለ አደራ አስተዳዳሪ ናችሁ። ስለዚህ ጊዜን በአግባቡ ለማስተዳደር መትጋት አለብህ።

አንዳንድ መጋቢያን በጊዜ አጠቃቀም ላይ ደካሞች ናቸው ስብሰባ እና ቀጠሮዎ ሲሆን ዘግይተው በመምጣት ይታወቃሉ። እነዚህ መጋቢያን ለሚመሩት ቤተ ክርስቲያናት አሉታዊ ምሳሌ ናቸው። የግድየለሽነት ባህሪያቸው በሰዎች ዘንድ ያላቸውን እምነት ቀንሶዋል። እንዲህ ያለ ነገር የቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ ልማድ ሲሆን ደግሞ እድገቷን ያደናቅፋል።

በሌላ በኩል ጥሩ የጊዜ አጠቃቀም ቤተ ክርስቲያንን በብቃት እንድትመራ ያስችልሃል። ለጥናት፣ ለአስተዳደራዊ ጉዳዬች፣ ለጉብኝት፣ ለምክር እና ለቤተሰብ ጉዳዮች ጊዜ መመደብ ትችላለህ። ውጤታማ የጊዜ አያያዝ እንደ የዕለት ተዕለት ግብ ማስቀመጥ ፣ የሥራ መዘርዝር መፍጠር ፣ በአስፈላጊነት እና አጣዳፊነት ላይ በመመስረት ቅድሚያ መስጠት እና እያንዳንዱን ተግባር ለማጠናቀቅ የጊዜ ገደብ ማበጀትን ያካትታል።

እንደ ጴንጤቆስጤ ፓስተር፣ ህይወትህን የምትኖርበት መንገድ እና አገልግሎትህን ስለምትመራበት መንገድ ዓላማ መር መሆን አለብህ። በግል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ሆን ብለህ ለይተህ ማስቀመጥ አለብህ። ከዚያ እነዚህን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ጠብቀህ መኖር አለብህ። እነዚህን ነገሮች ብታደርግ አንተም የምትመራውም ህዝብም ይባረካል።

# ምዕራፍ 6 በግል ሕይወት ቅድሚ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች

`

# ~ ምዕራፍ 7 ~

# ቤተሰብን ቅድሚያ ማድረግ

በምስራቅ አፍሪካ የሚገኝ የአንድ ትልቅ ከተማ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የአያቱን አሳዛኝ ታሪክ እንዲህ ሲል ተናግሮአል። ለብዙ ዓመታት አያቱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያንን እረኛ ሆነው አገልግለዋል። ነገር ግን አያቱ ቤተሰቡንና እምነቱን ጥሎ ሦስት ሚስቶች አገባ። በዚህ አሳዛኝ ውድቀት ምክንያት ይህን ታሪክ ከሚናገረው መጋቢ እናት በስተቀር፣ ከልጆቹ መካከል አንዳቸውም ጌታን አልተከተሉም። ባለታሪኩ መጋቢ አሁን፣ "እኔ የእናቴ ታማኝነት ውጤት ነኝ። ጌታን እንድከተል ተጽዕኖ ያደረገችኝ እርሷ ነች" ይላል። ዛሬ ይህ መጋቢ በቤተሰብ ጉዳዮች ላይ በማስተማር እና በመስበክ ይታወቃል።

የሚያሳዝነው ብዙዎች የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን አንዳንድ ጊዜ በትዳራቸው እና ከልጆቻቸው ጋር ችግር ይገጥማቸዋል። በዚህ ምክንያት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመንከባከብ ላይ ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ለመጋቢው በእርሱ ወይም በእርሷ የቤተሰብ ሕይወት ስኬታማ መሆን ከሁሉ በላይ ቀዳሚ ነው። በቤት አስተዳደር መውደቅ ደግሞ ሙሉ በሙሉ መውደቅ ነው። የቀደሙት ሁለት ምዕራፎች የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አገልግሎት እና በግል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ሲያወሳ፤ ይህ ምዕራፍ ደግሞ ለቤተሰባቸው ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች ይመለከታል።

## በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ግንኙነቶች

መጽሐፍ ቅዱስ መጋቢው ከቤተሰቡ ጋር ስላለው ግንኙነት ይናገራል። ጳውሎስ ስለ መጋቢው እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "ልጆቹን ታዛዥና አክባሪ አድርጎ በማሳደግ የገዛ ቤተሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳድር ሊሆን ይገባል" ቀጥሎም "አንድ ሰው የራሱን ቤት ማስተዳደር ካላወቀበት፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊጠብቅ ይችላል" በማለት ይጠይቃል (1 ጢሞ. 3፡4-5) መጽሐፍ ቅዱስ ለባሎች፣ ለሚስቶች እና ለልጆች የሚሰጠው ልዩ ልዩ መመሪያዎች በመጋቢው ቤተሰብ ላይም ይሠራል (ዘፍ. 2፡24፤ ማር. 10፡6-9፤ 1 ቆሮ. 11፡3፤ ኤፌ. 5፡22-33፤ 6፡1-4፤ ቆላ. 3፡18-21፤ 1 ጴጥ. 3፡1-7)።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ቅደም ተከተል

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የቤት ህይወትህ በቅዱሳት መጻህፍት መሰረት መሆን አለበት። ባሕል ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚቃወምበት ጊዜ፣ ከትዳር ጓደኛህና ከልጆችህ ጋር ያለህ ግንኙነት ከአምላክ ቃል ትምህርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ መሆኑን በማረጋገጥ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ቃል መገዛት አለብህ።

ለምሳሌ፡- አብዛኞቹ የአፍሪካ ባህሎች ባልን ማንም እንደማይቃወመው ቤተሰቡ ገዥ አድርገው ይመለከቱታል። የባል ቃል ምንም ያህል ምክንያታዊነት የጎደለው ቢሆንም በፍፁም ሊጠየቅ አይገባም። ኢየሱስ ግን የተለየ አመራር አሳይቷል። ስለ ራሱ ሲናገር፣ "የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም" (ማር.10፡45) ብሏል።

ጌታ እንደ ክርስቲያን ባል ከአንተ የሚጠብቀውን ዓይነት አመራር ሞዴል አሳይቶል። በቤተሰብ ውስጥ ያለህ አመራር በትህትና እና ለሚስት እና ለልጆች ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ አሳቢነት መገለጽ አለበት። ጳውሎስ ባሎችን " ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ" (ኤፌ. 5፡25) በማለት በዚህ የአገልጋይነት መሪነት መሪ ሃሳብ ላይ አብራርቷል።

ጳውሎስ የክርስቲያን ቤት እንዴት መታዘዝ እንዳለበት ገልጿል፡- " ክርስቶስ፣ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና" (ኤፌ. 5፡23)። በሌላ ቦታ ሐዋርያው እንዲህ ሲል ጽፏል፡- "ባሎች ሆይ፤ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ መራራም አትሁኑባቸው።20 ልጆች ሆይ፤ ይህ ጌታን ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ ለወላጆቻችሁ በሁሉም ነገር ታዘዙ፤ 21አባቶች ሆይ፤ ተስፋ እንዳይቈርጡ ልጆቻችሁን አታስመርሯቸው" (ቆላ. 3፡19-21)። በዚህ ዓይነት ሥርዓት ባለው ሁኔታ ትዳራችሁ ሊያድግና ልጆቻችሁም ሊያድጉ ይችላሉ።

## የጋራ መገዛት

መጽሐፍ ቅዱስ በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት እርስ በርስ የመገዛት መሆን እንዳለበት ያስተምራል። ጳውሎስ ባሎችና ሚስቶች "ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት የተነሣ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ" ሲል ጽፏል (ኤፌ. 5:21)። ባል የሚስት ራስ ቢሆንም ልክ እንደ ኢየሱስ ራሱን በፈቃደኝነት ለፍላጎቷ ማስገዛትና በትሕትና ማገልገል ይኖርበታል። እርሷም እንዲሁ ከእርሱ ጋር ማድረግ አለባት። እንደዚህ አይነት ትህትና እንደ መጋቢነት ያለውን ደረጃህን ከመቀነስ ይልቅ፣ ለቤተሰብ ያለው አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን እና በማህበረሰብ ውስጥ ያለህን አቋም ያሳድጋል።

## ፍቅር እና አክብሮት

በተጨማሪም ከቤተሰብህ ጋር ያለህ ግንኙነት በጋራ ፍቅር እና መከባበር መታወቅ አለበት። ጳውሎስ ባሎችን "ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት እና ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ ሚስቶቻችሁን ውደዱ" (ኤፌ. 5፡25) በማለት አሳስቧቸዋል። በኋላም "ሆኖም ከእናንተ እያንዳንዱ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ ይውደድ፤ ሚስትም ባሏን ታክብር" (ቁ. 33) በማለት አክሎ ተናግሯል። የተገላቢጦሹም እውነት ነው። ሚስት ባሏን መውደድ አለባት፣ ባልም ሚስቱን ማክበር አለባት። እነዚህን ነገሮች ሲያደርጉ መጋቢው እና ቤተሰቡ ለሌሎች አርአያ መሆን ይችላሉ።

***ትክክለኛነት***

በተጨማሪም፣ ከቤተሰብብህ ጋር ያለህ ግንኙነት በእውነተኛነት መታወቅ አለበት። ይህ ማለት በአደባባይ እንደምትናገረው ቤት ውስጥ አንድ አይነት ሰው መሆን አለብህ። በትዳር ጓደኛህ እና በልጆችህ ሕይወት ውስጥ ለሚሆነው ነገር ልባዊ ፍላጎት ማሳየት አለብህ። ልጆቹ እቤት ውስጥ ሲሆኑ የአባታቸውን ወይም የእናታቸውን ድምጽ እንጂ የእንግዳ ሰባኪ ድምጽ መስማት የለባቸውም።

# ለሴት መጋቢዎች ፈተናዎች

ለሴት መጋቢያን እና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁ የተለየ ምክር ያስፈልጋል።. በአፍሪካ ያሉ ያገቡ ሴት መጋቢያን ልዩ እና ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ አሉ። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሩ እንደ ጠራቸው ፤ ቤትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ባሎቻቸውን እንዲያከብሩ እና ለሥልጣኑ እንዲገዙም ጠርቷቸዋል። ይህ በአንድ ላይ ለማስተዳደር አስቸጋሪ ሁኔታ ሊሆን ይችላል።፡

በተጨማሪም ምንም እንኳን በብዙ ቦታዎች ይህ አመለካከት እየተለወጠ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ባህሎች የሴት አመራርን ይቃወማሉ ። በውጤቱም፣ አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባላት የሴት መጋቢ መሪነትን ለመከተል ወይም አንዳንድ የመጋቢነት ሥራዎችን እንድትፈጽም ፈቃደኞች አይደሉም።

ስለዚህ በተለይ ባለቤቱ መጋቢ የሆነች ባል፣ ሚስቱን በአገልግሎቷ መደገፉ በጣም አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ጊዜ ራሱን ዝቅ ለማድረግና ከአካባቢው ባሕል ጋር የሚቃረኑ በሚመስሉ በብዙ መንገዶች ለማለፍ ፈቃደኛ መሆን አለበት። ለምሳሌ በሥራዋ ጫና ምክንያት ጊዜ ስታጣ፣ ራሱን ዝቅ ለማድረግ፣ ለመደገፍና በሚችለው መንገድ ለመርዳት ፈቃደኛ መሆን አለበት። በሌላ በኩል እርሷ ባሏን፣ ልጆቿንና የቤት ውስጥ ግዴታዋን ችላ ለማለት የአገልጋይነት ተግባሯን እንደ ሰበብ መጠቀም የለባትም።

ይህ በሴቷ መጋቢ እና ባሏ በኩል ልዩ የሆነ የብስለት ደረጃን ይጠይቃል። ከምንም በላይ አንዳቸው ለሌላው ያላቸውን ግንኙነት ማስቀደም አለባቸው እና እርስ በርሳቸው ጥሩ መግባባትን መማር አለባቸው።

# ቤተሰብን በሚገባ ማስተዳደር

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተ ክርስቲያኑን በአግባቡ ማስተዳደር ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡንም በአግባቡ ማስተዳደር አለበት። ከላይ እንደተገለጸው፣ ጳውሎስ አንድ የበላይ ተመልካች “የገዛ ቤተሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳደር ሊሆን ይገባዋል” ሲል ለጢሞቴዎስ አሳስቦታል (1 ጢሞ. 3፡4)። በኋላም ለቲቶ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- “ሽማግሌ ነቀፋ የሌለበት፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልጆቹም አማኞችና በመዳራት ወይም ባለመታዘዝ ስማቸው የማይነሣ ይሁን” (ቲቶ 1፡6)።

ይህ ኃላፊነት ሚስቱንና ልጆቹን መምራት፣ መጠበቅ እና መንከባከብን ይጨምራል። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት እንደሚያደርግ አንድ ሰው ከሚስቱ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንዳለበት ያስተምራል (ኤፌ. 5፡25-27)። በተጨማሪም፣ የሰማይ አባት ልጆቹን ፍቅር እንደሚጠብቅ፣ ልጆቹን ሊጠብቅ ይገባዋል። ጠቢቡ ሰለሞን፣ “ ልጅን የሚሄድበትን መንገድ አስተምረው፤ በሚሸመግልበት ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ አይልም” (ምሳ. 22፡6) በማለት መክሯል። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የቤተሰብ አመራር ቢያንስ ሶስት ተግባራትን ያካትታል፡-

### መንፈሳዊ እድገት

በመጀመሪያ፣ የቤተሰብህ መንፈሳዊ እድገት መከታተል አለብህ።በመንፈሳዊ ጉዳዮች እንደ ኢዮብ ሆን ብለህ ቤተሰብህን መምራት አለብህ (ኢዮብ 1፡4-5)። ይህን ማድረግ የምትችልበት አንዱ መንገድ ከቤተሰብህ ጋር አዘውትረህ የህብረት ጊዜ እንዲኖርህ ማድረግ ነው። በእነዚህ የአምልኮ ጊዜያት ልጆች እንዲጸልዩ እና ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያነቡ እና እንዲያስታውሱ ማስተማር ይገባል። በተጨማሪም ልጆች ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ እንዲያውቁ እና በመንፈስ ቅዱስም መጠመቃቸውን ማረጋገጥ ግድ ነው።

### የቤተሰብ ሁለንተናዊ እድገት

ሁለተኛ፣ የቤተሰብህን ሁለንተናዊ እድገት መከታተል አለብህ። አንተ እና የትዳር ጓደኛህ ልጆቻችሁን የበሰሉ ጎልማሶች፣ ቁርጠኛ ክርስቲያኖች እና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ምሳሌ መሆን አለባችሁ። በተጨማሪም ልጆቻችሁ ገንዘብን በጥበብ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ማስተማር አለባችሁ። ልጆቻችሁ እያደጉና እየበሰሉ ሲሄዱ፣ ቤተሰብን በማስተዳደር እንዲረዷችሁ መፍቀድ አለባችሁ። በዚህ መንገድ ፍላጎቶችን ከአንገብጋቢ ጉዳዩች መለየት ይማራሉ።

### ማህበራዊ ዕድገት

በመጨረሻም አንተ እና ባለቤትህ የልጆችህን ማህበራዊ እድገት መከታተል አለብህ። ቤተሰቡ ልጆች በማህበራዊ ክህሎታቸው እንዲያድጉ ምቹ ቦታ መሆን አለበት። በጥሩ እና በእኩይ ወዳጅነት መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያውቁ ማስተማር አለብህ። በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዬች ውስጥ ከሌሎች ጋር እንዴት ግንኙነት ማድረግ እንዳለባቸው ማስተማር አለብህ።

## ከትዳር ጓደኛ ጋር በተያያዘ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች

መጽሐፍ ቅዱስ ባል በሚስቱ ላይ ስላለው ኃላፊነት በግልጽ ይናገራል። በእርግጥም እነዚህ ኃላፊነቶች በጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ላይ ይሠራሉ። ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዳለው ሰው ከሚስትህ ጋር ያለህ ግንኙነት የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል።

### ፍቅርን ግለጽ

ጳውሎስ ባል "ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቱን መውደድ" እንዳለበት ጽፏል (ኤፌ. 5፡25)። ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያለው ፍቅር መስዋእትነት ያለው እና ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ነበር። ለሚስትህ ያለህ ፍቅር ተመሳሳይ መሆን አለበት። ለሚስትህ ያለህን ፍቅር በግልም ሆነ በአደባባይ መግለጽ አለብህ። ከእርሷ ጋር ብቻህን ስትሆን "እወድሻለሁ" ብለህ ብዙ ጊዜ መንገር አለብህ። በአደባባይ ስትሆን ለሚስትህ ያለህን ፍቅር በግልፅ መግለፅ አለብህ። ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያን ስትገኙ "ዛሬ እዚህ ባለቤቴ ከእኔ ጋር በመኖሬ ተባርኬያለሁ። እርሷ አስደናቂ ሚስት እና ለልጆቻችን ድንቅ እናት ነች። በጣም አፈቅራታለሁ"ብለህ ማስተዋወቅ ተገቢ ነው።

እነዚህ እና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች ከሚስትህ እና ከቤተክርስቲያንህ ጋር እንድትተሳሰር ይረዳሃል። በተጨማሪም ለሚስትህ ያለህን ፍቅር በተግባርህ ማለትም በመልካም በመናገር፣ከራስህ በማስቀደም እና ኃላፊነቷን እንድትወጣ በማገዝ ማሳየት አለብህ።

### ድጋፍ ማድረግ

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሚስትህን እና ልጆችህን በተመለከተ ያለህ ሁለተኛ ኃላፊነት ለእነርሱ የሚገባውን ድጋፍ መስጠት ነው። ጴጥሮስ ለባሎቻችሁ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "ባሎች ሆይ፤ በኑሮአችሁ ሁሉ ለሚስቶቻችሁ አስቡላቸው፣ ...አክብሯቸው " (1 ጴጥ. 3:7)። ክርስቲያን ወንድ እንደመሆናችሁ መጠን ለሚስትህ እና ለልጆችህ በቂ መጠለያ፣ ምግብና ልብስ በማቅረብ በቁሳቁስ መርዳት ይኖርብሃል። ሚስትህና ትልልቅ ልጆችህ በዚህ ረገድ ሊረዱህ ቢችሉም አንተ ግን የቤትህ ራስ እንደመሆንህ መጠን ዋናውን ኃላፊነት ልትወጣ ይገባል።

ሚስትህን የምትደግፍበት ሌላው አስፈላጊ መንገድ በአገልግሎት የግል ጥሪዋን እንድትኖር በመርዳት ነው። የአንተ መመሪያ መሆን ያለበት፣ "ባለቤቴ አቅሟን እንድትጠቀም መርዳት ካልቻልኩ፣ ቤተ ክርስቲያኔ ተመሳሳይ ነገር እንድታደርግ እንዴት እረዳታለሁ?" የሚል መሆን አለበት። ይህንን ለማድረግ፣ እግዚአብሔር በህይወትህ ላይ ጥሪ እንዳለው ሁሉ በሚስትህ ህይወት ላይ ጥሪ እንዳለው በጽኑ መቀበል አለብህ። ከዚያም እግዚአብሔርን በህይወቷ ያለውን ፈቃድ እንድታስተውል እና እንድትከተል በመርዳት በጸሎት እና በምክር አብራችሁ መሄድ ይኖርባችኃል።

### ጥበቃ ማድረግ

ሚስትህን በተመለከተ ያለህ ሶስተኛው ሃላፊነት እርሷን ከአካላዊ፣ ስሜታዊ እና መንፈሳዊ ጥቃት መጠበቅ ነው። በጣም መሠረታዊ በሆነው መልኩ እርሷን ከአካላዊ ጥቃት መጠበቅ አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ ሚስትን በትዳር ግንኙነት ውስጥ "ደካማ አጋር" ይላታል (1ጴጥ. 3፡7)። በአካል ጠንካራ አጋር እንደመሆንህ፣ ሚስትህን ከአካላዊ ጥቃት ለመጠበቅ ምንጊዜም ዝግጁ በመሆን ሁል ጊዜ ዘብ መቆም አለብህ። ይህንን ማወቋ ደህንነት እንዲሰማት እና ዋጋ እንዲሰጠው ያደርጋታል።

በተጨማሪም ሚስትህን ከስሜታዊ ጉዳት መጠበቅ አለብህ። እንደ አለመታደል ሆኖ ሰዎች የፓስተሩ ሚስት ብዙ ጊዜ የትችት ኢላማ ማድረግ ይወዳሉ። አማቶችህ ወይም አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን አባላት ብዙ ጊዜ እርሷንና ልጆችህን ሊወቅሱ ይችላሉ። ሌሎች ደግሞ ለምታደርገው አድናቆት ማሳየት አይፈልጉ ይሆናል። ይህ ለእርሷን ሊጎዳት ይችላል። በቤተክርስቲያን ውስጥ ይህንን የስሜት ልውውጥ ማስተዋል እና ሚስትህን መጠበቅ አለብህ ፡፡ ደግሞም የምትፈልገውን ስሜታዊ ድጋፍ ልታደርግላት ይገባል።

በመጨረሻም፣ የመጋቢው ሚስት የሰይጣን ዋነኛ ኢላማ ስለሆነች መንፈሳዊ ጥበቃ ልታደርግላት ይገባል። በዙሪያዋ የጸሎት አጥር በመገንባት ይህንን ማድረግ ትችላለህ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በእርሷና በጠላት መካከል ባለው ክፍተት መቆም አለብህ (ሕዝ. 22፡30)።

# ለልጆች ቅድሚያ መስጠት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ልጆቹን ማስቀደም አለበት። ሚስቱን ከመውደድ እና ከመንከባከብ ሃላፊነት ቀጥሎ ልጆቹን የመውደድ እና የመንከባከብ ሃላፊነት አለበት። የሰማይ አባቱ ለእርሱ እንደሚያስብለት ሁሉ እርሱም ለእነርሱ ማሰብ እና መንከባከብ አለበት። "በጌታ ምክርና ተግሣጽ አሳድጓቸው" እንደሚል (ኤፌ. 6፡4)።

ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዳለው ሰው እና እንደ ክርስቲያን አባት ለልጆቻችህ ሦስት ዋና ዋና ኃላፊነቶች አሉብህ፡-

## የእግዚአብሔር ፍቅር ምሳሌ መሆን

በመጀመሪያ፤ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለልጆችህ በምሳሌ ልታሳይ ይገባል። ልጆች አባታቸውን በመመልከት ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን መረዳት ያዳብራሉ። ምድራዊ አባታቸው ደግ እና አፍቃሪ ከሆነ፣ የሰማይ አባታቸውን ደግ እና አፍቃሪ አድርገው ይመለከቱታል። ምድራዊ አባታቸው አምባገነን ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚመለከቱት በተመሳሳይ መንገድ ነው። እንደ ፍቅር፣ አክብሮት፣ አገልግሎት እና መተማመን ያሉ አምላካዊ ባሕርያትን በምሳሌነት ስታሳይ ልጆቻችህ በቤት ውስጥ የምትሰጠውን መመሪያና እርማት ለመቀበል ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የፍቅርን እውነተኛ ተፈጥሮ ይገልጻል፡-

> ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ደግሞም ቸር ነው። ፍቅር አይመቀኝም፤ አይመካም፤ አይታ በይም፤ 5ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም፤ ራስ ወዳድ አይደለም፤ አይበሳጭም፣ በደልን አይቈጥርም። 6ፍቅር ከእውነት ጋር እንጂ በዐመፅ ደስ አይሰኝም። 7ፍቅር ሁል ጊዜ ይታገሣል፤ ሁል ጊዜ ያምናል፤ ሁል ጊዜ ተስፋ ያደርጋል፤ ሁል ጊዜ ጸንቶ ይቆማል።8ፍቅር ከቶ አይወድቅም፤ ነገር ግን ትንቢት ቢሆን ይሻራል፤ ልሳንም ቢሆን ይቀራል፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል። (1 ቆሮ. 13:4-8)

ለልጆቻችሁ ልታሳዩት የሚገባ ፍቅር ይሄ ነው።

## ወደ ክርስቶስ መምራት

የእግዚአብሔርን ፍቅር ከማሳየት በተጨማሪ ልጆችህን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት እንዲኖራቸው መምራት አለብህ። ይህንን ለማድረግ ጥሩ ጊዜ የቤተሰብ የጸሎት ወቅት ነው። በእነዚህ የጸሎት ጊዜያት ውስጥ ልጆች ጌታን እንዲያገኙ ማመቻቸት ትችላለህ። ከዚያ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ለመቀበል ጊዜው ሲደርስ አብረሃቸው በመጸለይ ልትመራቸው ትችላለህ። ከዚህ በኋላ ልጆቹ በምስክርነት እና በውሃ ጥምቀት ስለክርስቶስ ያላቸውን እምነት በይፋ ማወጃቸው አስፈላጊ ነው። እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ የምትችለውን አጋጣሚዎች መፈለግ አለብህ። ከዚያም እምነታቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ልታበረታታቸው ይገባል።[1]

## ባህሪያቸውን ይቅረጹ

የልጆችዎን ባህሪ ለመቅረጽ ግልጽ የሆነ እቅድ ሊኖህ ይገባል። አንተ እና ባለቤትህ ትክክልና ስህተት የሆነውን እና "ከማናቸውም ዐይነት ክፉ ነገር " እንዴት መራቅ እንደሚችሉ ማስተማር አለባችሁ (1 ተሰ. 5:22)። በተጨማሪም ልጆቻችሁ ትሁት፣ ደግ እና ከታማኝነት እና ከትጋት ጋር የበላዮቻቸውን አክባሪ እንዲሆኑ ማስተማር አለባችሁ። ይህ መመሪያ በሕይወታቸው ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ በመርዳት ረገድ ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

በቤት ውስጥ የተቀደሰ ኑሮን በምሳሌነት በማሳየት እና ከልጆች ጋር በሥነ ምግባር ጉዳዮች ላይ በጥንቃቄ በመወያየት እነዚህን ነገሮች ማድረግ ይቻላል። ልጆች ወላጆች ከልባቸው ጽድቅን ሲያደርጉ ሲያዩ በተፈጥሯቸው ያንን መከተል ይፈልጋሉ። አንዳንድ ጊዜ ልጆቻችሁን ከሞኝ እና ጎጂ ከሆኑ ድርጊቶች እንዲመለሱ በፍቅር መንገር ወይም መገሰጽም ያስፈልጋል (ምሳ. 29፡15)።

---

[1] ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ግንዛቤ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 20ን ተመልከት፡ “አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት”።

# ዘመድ አዝማድን መርዳት

እንዲሁም ለአንተ እና ለባለቤትህ ዘመድ አዝማድ ፍቅር እና እንክብካቤን ማሳየት አለብህ። እነዚህ ሰፊ የቤተሰብ አባላት ወላጆችን፣ ወንድሞችን እና እህቶችን፣ የእህቶችን እና የወንድም ልጆችን እና ምናልባትም ሌሎችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- “ስለ ዘመዶቹና ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቻቸው የማያስብ ሁሉ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው” (1 ጢሞ. 5፡ 8)።

ሆኖም የቤተሰብ አባላት ፍላጎት ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚጻረርበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ፣ የቤተሰብ አምልኮ ሥርዓት፣ ግርዛት ወይም የመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልማዶችን ሊጭኑ ይችላሉ። እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች እነዚህን ሃሳቦች በፍቅር ማስረዳት እና፣ በጥብቅ መቃወም ይገባል።

ሌላው የቤተሰብ አባላት በአንተ እና በቤተሰብህ ላይ ጫና የሚሆኑበት መንገድ ለረጅም ጊዜ ቤት በመቀመጥ ነው። በውጤቱም በቤተሰብህ ላይ የገንዘብ፣ የአዕምሮ እና የስሜት ጫና ይፈጠራል። ትልቁ ተግዳሮት ደግሞ ብዙውን ጊዜ በመጋቢው ሚስት ላይ ይሆናል።. በዚህ ምክንያት ባቤትህ ልትሰላች ትችላለች። እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች እንደ ቤት ኃላፊ፣ ሃላፊነት መውሰድ እና በቤተሰብ እና በቤተሰብህ መካከል ጤናማ ድንበርን ማበጀት አለብህ።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን ማሳሰቢያ ከላይ እንደተገለጸው አንድ ሰው ዘመዶቹን “በተለይም ለቤተሰቦቻቸው” መንከባከብ እንዳለበት አስታውስ። ሆኖም ክርስቲያን ወንድ እንደመሆናችሁ መጠን ዋና ኃላፊነታችሁ ለዘመዶቻችሁ ሳይሆን ለሚስትቶቻችሁ እና ለልጆቻችሁ ነው። እንግዲያው ቅር የተሰኘውን ዘመድ “ሥራ ፈት ከሆነ እና በተቀበላችሁት ትምህርት መሰረት ከማይኖ አማኝ ሁሉ ራቅ” (2 ተሰ. 3:6) እንዲሁም “ሊሰራ የማይወድ አይብላ” የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ማሳሰቡ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል (ቁጥር 10)።

አንተና ባለቤትህ ዘመዶቻችሁ ለሚያቀርቡት ጥያቄ ሁሉ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ምን ዓይነት እርዳታ መስጠት እንደሚገባ መወሰን አለባችሁ። ይህን ስታደርግ በመመሪያው ላይ መስማማት ያስፈልጋል፡- ማን የማንን ወገን ይርዳ? እና እርዳታው ለምን ያህል ጊዜ ይዝለቅ? የሚለው ላይ መግባባት አለባችሁ፡፡

የአንተ ዋና ዓላማ ለቤተሰብህ ጨው እና ብርሃን መሆን ነው።ወደ ባህልህ ማድላት ትችላለህ ሆኖም በአገልግሎት ውስጥ ውጤታማ አያደርግህም። ስለዚህ በመርዳት እና ለመርዳት እምቢ ማለት መካከል ያለውን ሚዛን ማግኘት አለብህ። ሆኖም በማንኛውም ጊዜ፣ ቤተሰብህ ለዘመድ አዝማድ አባላት ምስክር ለመሆን መጣር አለበት።

---

እንደ ጴንጤቆስጤ መጋቢ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም ቤተክርስቲያንን እንድትመራ እግዚአብሔር ጠርቶሀል። ነገር ግን ይህንን ስታደርግ የራስህን ቤተሰብ ቸላ ማለት የለብህም። “የጠፋውን ለክርስቶስ አምጥቻለሁ ፤ የራሴን ቤተሰብ ግን አጥቻለሁ“ በማለት በፍፁም መጸጸት የለብህም።

# ~ ምዕራፍ 8 ~

# ጸሎትን ቅድሚያ ማድረግ

እንደ ልማዱ ሙሴ ሊጸልይ ከሰፈሩ ወደ ውጭ ወደ መገናኛው ድንኳን ወጣ። ሕዝቡ ይህን ሲያደርግ ባዩት ቁጥር የሚያደርጉትን ነገር ትተው ወደ ድንኳኑ እስኪገባ ድረስ ይመለከቱት ነበር። ሙሴ በድንኳኑ ውስጥ እያለ ሲጸልይ የደመና ዓምድ ወርዶ በበሩ ላይ ያንዣብባል። ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ ተገርመው ለእግዚአብሔርም ይሰግዳሉ። መሪያቸው ከእግዚአብሔር ጋር ዘወትር እንደሚነጋገር ማወቃቸው ያበረታታቸዋል። ይህ የሙሴ ድርጊት በተለይ ወጣቱ ረዳቱን ኢያሱን ይስበው ነበር። ብዙ ጊዜ ሙሴን ተከትሎ ወደ ድንኳኑ ይሄድ ነበር፤ ሙሴም ሄዶ እንኳን ለረጅም ጊዜ በዚያ ይቀመጥ ነበር። እንደ ሙሴ መሆን ምኞቱ ነበርው (ዘጸ. 33፡8-11)።

ጉባኤን እንደ ጸሎት ወዳድ መጋቢ የሚያነሳ ምንም ነገር የለም። ሰይጣን የአካዳሚክ ዲግሪያችንን አይፈራም። የቤተ ክርስቲያናችንን በጀት ትልቀት ወይም ድንቅ ህንፃዎቻችንን አይፈራም። ዲያብሎስ የሚፈራው ጸሎታችን ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በመንፈስ በተቀባ፣ በእምነት በተሞላ ጸሎት ሲንበረከኩ ሰይጣን እና አጋንንቱ ይንቀጠቀጣሉ። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሌላ ምንም ነገር የላቀ ባይሆን፣ እርሱ ወይም እርሷ በጸሎት ልምምድ የላቀ መሆናቸው ግድ ነው።

## የጸሎት የአኗኗር ዘይቤ

ታላቁ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጅ ማርቲን ሉተር በአንድ ወቅት “ያለ ጸሎት ክርስቲያን መሆን ሳይተነፍሱ የመኖር ያህል ነው” ብሏል። በክርስቶስ ላለ አማኝ ሁሉ እውነት የሆነው ይህ መርህ ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ደግሞ እጥፍ ድርብ እውነት ነው ። ያለ ቁርጠኛ የጸሎት የአኗኗር ዘይቤ አንድ ሰው እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሆኖ ማገልገል አይችልም። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “ሳይታክቱ ሁል ጊዜ መጸለይ እንደሚገባቸው” (ሉቃስ 18፡1) አስተምሯቸዋል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ኢየሱስን እንደ ምሳሌ መውሰድ አለብህ። የጌታ ሙሉ ህይወት እና አገልግሎት በጸሎት የተጥለቀለቀ ነበር። ሉቃስ "ኢየሱስ ግን ብዙ ጊዜ ወደ ብቸኛ ቦታዎች ወጥቶ ይጸልይ ነበር" (ሉቃስ 5፡16) በማለት ጽፏል። በአንድ ወቅት፣ "ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ፣ ሌሊቱንም ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ" (6፡12)። በሌላ ጊዜ ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና ያዕቆብን ይዞ "ለመጸለይ ወደ ተራራ ወጣ" (9፡28)። በእርግጥም፣ ኢየሱስ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይጸልይ ነበር። ልክ እንደ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት ትጉህ የጸሎት ሰው መሆን ይጠይቃል። ያለ ጽኑ የጸሎት ልማድ ማንም በመንፈስ ኃይል ማገልገል አይችልም።

በጸሎት እራስህን ለአገልግሎት ታዘጋጃለህ። በጸሎት በመጠባበቅ ወደ እግዚአብሔር ትቀርባለህ (ያዕቆብ 4፡8፤ ዕብ. 10፡22)። በተጨማሪም ለክርስቶስ ለመኖር የሚያስፈልግህን መንፈሳዊ ጥንካሬ እና አገልግሎትህን በብቃት ለመፈጸም የሚያስፈልግህን ኃይል ታገኛለህ (ኢሳ. 40፡31፤ መዝ. 40፡1-3)።

መጽሐፍ ቅዱስ "በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ" በማለት ያሳስባል (ገላ. 5፡16)። ይህንን ለማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ያለማቋረጥ ህብረት ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲህ ዓይነቱ ኅብረት የሚገኘው በጸሎት ነው። በጸሎት ወቅት መንፈስ ቅዱስ ያናግርሃል እናም ማበረታቻ እና መመሪያ ይሰጥሃል። በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ጸሎት ለመንፈሳዊ ውጊያ የበለጠ ያዘጋጃል (ኤፌ. 6፡12፣ 18)።

# የጸሎት አገልግሎት

የግል የጸሎት ህይወትህን ከማዳበር በተጨማሪ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጸሎትን ሌሎችን የማገልገልያ መንገድ አድርገህ ልትመለከተው ይገባል። በጸሎት ሌሎችን ማገልገል የምትችልባቸው ሦስት መንገዶች አሉ፡-

## በግል ጸሎት ማገልገል

በመጀመሪያ፣ በግል ጸሎት ሌሎችን ማገልገል ትችላለህ። ኢየሱስ ይህን የመሰለ ጸሎት ሚስጥራዊ ጸሎት ብሎ ጠርቶታል። "አንተ ግን ስትጸልይ ወደ ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግተህ በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ፤ " (ማቴ. 6፡6) በማለት አስተምሯል። እዚያ በሚስጥር ቦታ ለሌሎች ፍላጎቶች በመማለድ ጊዜ ማሳለፍ አለብህ። በምትጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር የፍቅር ድካምህን እንደሚመለከት እና ጸሎቶችህን እንደሚመልስ በማወቅ በልበ ሙሉነት እግዚአብሔርን ልትለምን ትችላለህ። በዚያው ክፍል ኢየሱስ "በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል" ሲል ቃል ገብቷል። የምስጢር የጸሎት ጊዜህ ቢያንስ ሦስት ዓይነት ሊሆን ይችላል፡-

**1. የግል ጸሎት።** በመጀመሪያ፣ በግል መጸለይ አለብህ። በሌላ አነጋገር ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ በጸሎት ጊዜ ማሳለፍ አለብህ። ይህ ልምምድ ከጌታ ጋር ያለህን ግንኙነት ያጠናክራል። በመንፈስ ቅዱስ ስትጸልይ እምነትህ ይገነባል እናም በእግዚአብሔር ፍቅር ትጠበቃለህ (ይሁዳ 20-21፤ ሮሜ. 5፡5)። ከጸሎቱ በሚመነጭ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት አገልግሎትህን በተሳካ ሁኔታ መፈጸም ትችላለህ።[1]

**2. የምልጃ ጸሎት።** በመቀጠል፣ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ እንደ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በእግዚአብሔር ፊት ስለሌሎች ፍላጎት በተለይም ከቤተክርስቲያናን ጋር ለተያያዙት ፍላጎቶች እግዚአብሔርን በመለመን ጊዜ ማሳለፍ አለብህ። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ብዙ ጊዜ ይጸልይ ነበር

[1] ወደ አምላክ መቅረብን በተመለከተ ተጨማሪ ለማግኘት ምዕራፍ 15ን "ጠንካራ የግል ሕብረት የማድረግ ልማድ" የሚለውን ተመልከት።

(ዮሐንስ 17፡9)። ለምሳሌ እምነታቸው እንዲጸና ጸለየላቸው (ሉቃስ 22፡32)። በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው ጸለየ (ዮሐ. 17፡11-12፣ 15)፣ ደስታም እንዲኖራቸው (ቁ. 13)። እንዲሁም ስለ መቀደስ ጸለየላቸው (ቁ. 17-19) እና አንድ ሆነው እንዲቀጥሉ (ቁ. 21-23) ጸልዮዋል።

በተመሳሳይም ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ያለማቋረጥ ይጸልይ ነበር። በሮም ላሉት አማኞች "በጸሎቴ ሁል ጊዜ አስባችኋለሁ" (ሮሜ. 1:9-10) ሲል ጽፎአል። ለኤፌሶን ሰዎች "በጸሎቴ ሳስብአችሁ ስለ እናንተ ማመስገንን አላቋርጥም" (ኤፌ. 1፡16፤ ቆላ. 1፡9) ብሏቸዋል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የኢየሱስን እና የጳውሎስን ምሳሌ በመከተል ብዙ ጊዜ በጸሎት ማሳለፍና እና ስለሌሎች መማለድ አለብን።

**3 ጾም እና ጸሎት።** በመጨረሻም፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ብዙ ጊዜ በጾም መጸለይ አለብህ። የጾም እና ጸሎት መንፈሳዊ ልምምድ መንፈስህ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ለማጣመር ይረዳል። በጾም እና ጸሎት ጊዜ ስትወስዱ ሥጋችሁ ወደ መገዛት ይመጣል፣ እናም መንፈሳችሁ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ በግልጽ ለመረዳት ንቁ ይሆናል (ገላ. 5፡16-17)።

## የአንድ ለአንድ ጸሎት

በተጨማሪም፣ ብዙ ጊዜ ሰዎች በግል እንድትጸልይላቸው ሊጠሩህ ይችላሉ። አንድ ለአንድ ጸሎት ማለት አብሮህ ላለ አንድ ሰው ስትጸልይ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው በጸሎት ጊዜያት በቤተ ክርስቲያን ነው። በመጋቢዊ ጉብኝት ወቅት በቤት ውስጥ ወይም በሆስፒታል ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ሊከሰትም ይችላል ወይም ደግሞ በገበያ ቦታ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት ብዙውን ጊዜ እጅ መጫንን ወይም በዘይት በመቀባት መጸለይን ይጨምራል (ሐዋ. 19፡6፤ ያዕ 5፡14)። ሁልጊዜም በእምነት መጸለይን ያካትታል (ያዕቆብ 5፡15)።

የተለመዱት የአንድ ለአንድ የጸሎት ምሳሌዎች ወደ ድህነት ለመምራት ከሰዎች ጋር መጸለይ፣ ሰዎች እንዲፈወሱ መጸለይ፣ ከአጋንንት እስራት ነፃ እንዲወጡ እና በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ከሰዎች ጋር መጸለይ ናቸው። በእነዚህ የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ ብቁ መሆን አለብህ። በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ እምነት እንዳለህ ማሳየት፣ የእምነትና የማበረታቻ ቃላትን መናገር እንዲሁም የምትጸልይላቸው ሰዎች ሸክም ሊኖርህ ይገባል።[2]

## በአደባባይ ጸሎት ማገልገል

አንዳንድ ጊዜ የአደባባይ ጸሎቶችን እንድታደርግ ትጋበዛለህ። አንዳንድ መጋቢያን በየእሁዱ ጠዋት በጉባኤያቸው ላይ መጋቢያዊ ጸሎት ያቀርባሉ። በተጨማሪም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ ቀብር እና ሠርግ ባሉ የአደባባይ ስብሰባዎች ላይ እንዲጸልይ ይጠራል። እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች እንድትጸልይ ስትጠየቅ ጸሎትህን በክብር እና በጸጋ ማቅረብ አለብህ። ይሁን እንጂ የአደባባይ ጸሎትህ ለዕይታ እና ለሥርዓት ብቻ መቅረብ የለበትም። ሁል ጊዜ በእውነት መጸለይ አለብህ። ኢየሱስ "ስትጸልዩ እንደ ግብዞች

---

[2] ስለ ግለሰቦች መጸለይን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 20ን ተመልከት፡ "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት"፤ ምዕራፍ 21: "በመንፈስ ኃይል ውስጥ ማገልገል"; እና ምዕራፍ 22፡ "በመንፈሳዊ ጦርነት ማድረግ። እንዲሁም፣ ሰዎች እንዲፈወሱ፣ በመንፈስ እንዲሞሉ እና ከአጋንንት እስራት እንዲድኑ የሚረዳውን በዴንዚል አር. ሚለር የተጻፈውን የሃይል ግንኙነት፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና ቅባት ውስጥ ማገልገል የሚለውን መጽሐፍ ይመልከቱ። በ DecadeofPentecost.org በ e-book format (PDF) በነፃ ማውረድ ይችላል።

አትሁኑ፤ እነርሱ እንዲታዩ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና" (ማቴ. 6፡5) በማለት አስጠንቅቋል።

# ቤተክርስቲያንን በጸሎት መምራት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የራሱን ወይም የራሷን የጸሎት ህይወት ማዳበር ብቻ ሳይሆን እረኛ በሚሆኑበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ የጸሎት አገልግሎት ማዳበር አለበት።

## ስለ ጸሎት መስበክ እና ማስተማር

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠንካራ የጸሎት አገልግሎት ለማዳበር አንድ አስፈላጊ ቁልፍ ነገር በርዕሱ ላይ ብዙ ጊዜ መስበክ እና ማስተማር ነው። ይህን በማድረግ፣ በራሱ ስለ ጸሎት ብዙ ያስተማረውን የኢየሱስን ምሳሌ መከተል ነው (ሉቃስ 18፡1፤ ማቴ. 6፡5-15)።

ጌታ ከዚህ ቀደም ጸሎቶችን እንዴት እንደመለሰ የሚገልጹትን ምስክርነቶችን በማካፈል ወገኖች እንዲጸልዩ ማበረታታት ትችላለህ። እነዚህ ምስክርነቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክ፣ ወይም ከዘመናዊው ሕይወት ሊወሰዱ ይችላሉ። ተጨማሪ ጊዜ ወስደህ ስለ ጸሎት ጥቅምና ልምምድ ተግባራዊ ትምህርቶችን ማስተማር አለብህ።[3]

## የጸሎት ተምሳሌትነት

ስለ ጸሎት ማስተማር ብቻ ሳይሆን ለምእመናን እንዴት መጸለይ እንዳለባቸውም ተምሳሌት መሆን አለብህ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያስተማራቸው በዚህ አይነት መንገድ ነበር። ኢየሱስ ጸሎትን በቃላት ብቻ ሳይሆን በህይወቱ አሳይቷቸዋል። በፊታቸውም የጸሎትን አኗኗር ምን እንደሚመስል በተግባር አሳይቶል። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ከሰማይ አባቱ ጋር ያለማቋረጥ እንዴት እንደሚመላለስ አስተውለዋል። በአንድ ወቅት፣ ሲጸልይ ከተመለከቱ በኋላ፣ "ጌታ ሆይ፣ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ መጸለይን አስተምረን" ብለው ጠየቁት። (ሉቃስ 11፡1) እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አማኞች "መጋቢ ሆይ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንድንጸልይ አስተምረን እስኪሉ ድረስ እንደዚህ አይነት የጸሎት አኗኗር ሊኖርህ ይገባል።

## ለጸሎት ማደራጀት

በተጨማሪም፣ ቤተ ክርስቲያንህን ለጸሎት ማደራጀት አለብህ። የጸሎት ቡድኖችን በማቋቋም እና የጸሎት ዝግጅቶችን በማቀድ ይህንን እንደሚከተለው ማድረግ ትችላለህ-

**የጸሎት ቡድኖችን መፍጠር።** በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ልዩ የጸሎት ቡድኖች እንዲፈጠሩ ማበረታታት ይገባል። እነዚህ ቡድኖች እንደ የወንዶች እና የሴቶች አገልግሎት፣ የወጣቶች እና ሌሎችም ሆነው ሊዋቀሩ ይችላሉ። እንዲሁም በቤተክርስቲያን፣ በማኅበረሰብ፣ በሃገር፣ ወይም በዓለም ያሉ ልዩ ልዩ የጸሎት ርዕሶችን ትኩረት አድርገው ሊደራጁ ይችላሉ። እነዚህ ፍላጎቶች ማህበራዊ ወይም መንፈሳዊ፣ አካባቢያዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አንዳንድ አባላት ለቤተ ክርስቲያን መነቃቃት መጸለይ

---

[3] ስለ ጸሎት የስብከት እና የማስተማር ርዕሰ ጉዳዩች ለአሕዛብ መማለድ፡ 100 ስለ ሚሲዮናዊ ጸሎት የስብከት መግለጫዎች በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ይገኛል። መጽሐፉን በነጻ በኢ-መጽሐፍ ቅርጸት (PDF) በDecadeofPentecost.org ማውረድ ይችላሉ።

ሊፈልጉ ይችላሉ፣ ሌሎች ደግሞ ለሀገር ሰላም መጸለይ ይፈልጉ ይሆናል። ጸሎት የሚጠይቁ ሌሎች ብዙ ፍላጎቶች ሊታወቁ ይችላሉ።

**የጸሎት ፕሮግራሞችን ማቀድ።** እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ካላንደር ላይ ላይ በርካታ የጸሎት ፕሮግራሞችን ማካተት ያስፈልጋል። መደበኛ የጸሎት አገልግሎቶችን ማቀድ አለብህ፤ ምናልባትም በሳምንቱ አጋማሽ ላይ ይሄን አይነት ጸሎት ማድረግ ተገቢ ነው። እንዲሁም የጸሎት ጉዞ ወይም ልዩ የጸሎት ሳምንት የመሳሰሉ ዝግጅቶችን እና መርሐግብር መንደፍ ጠቃሚ ነው።

ለምሳሌ፡- አንድ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በአመት ሁለት ጊዜ የጾም እና ጸሎት ሳምንት (በጥር እና በሐምሌ ወር) ፕሮግራሞች ማዘጋጀት ይችላል። ለእነዚህ ዝግጅቶች አባላት ከቤተሰባቸው አባላት፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከጎረቤቶቻቸው እና ከስራ ባልደረቦቻቸው የጸሎት ጥያቄዎችን እንዲሰበስቡ ያበረታታቸዋል። ከዚያም እነዚህን ጥያቄዎች በተለየ ሁኔታ በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በመጻፍ በጠዋት እና በማታ የጸሎት ስብሰባዎች ላይ እንዲጸልዩ ለአባላት ያከፋፍላል። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ለቤተ ክርስቲያን እና ለማህበረሰቡ ታላቅ በረከት መጥቶል።

ብዙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት በየዓመቱ እስከ ጴንጤቆስጤ እሑድ ድረስ ተከታታይ የጸሎት ስብሰባዎችን ያዘጋጃሉ። (የጴንጤቆስጤ እሑድ ሁልጊዜ ከትንሣኤ እሑድ ቀጥሎ ባሉት ሰባት ሳምንታት በኋላ ይመጣል።) በእነዚህ ልዩ ስብሰባዎች፣ አባላት እግዚአብሔር መንፈሱን በቤተ ክርስቲያን ላይ እንዲያፈስ ይጸልያሉ። በጴንጤቆስጤያዊ በዓል ወቅት ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንዲታጠቁ ይጸልያሉ (ሐዋ. 1፡8፤ 2፡4)። እንደ መጀመሪያው የጴንጤቆስጤያዊ ቀን (2፡41) ብዙዎች ወደ ጌታ እንዲመጡ ይጸልያሉ።

እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዬች እና መሪዎች ጋር አመታዊ የምሽግ መርሐግብር መያዝ ያስፈልጋል። እንዲህ አይነት ፕሮግራም ስትይዝ ለየትኛውን ጸሎት አፅንዖት መስጠት እንደሚገባ የጌታን ምሪት በትጋት መፈለግ አለብህ።

## ለእግዚአብሔር ተልዕኮ መጸለይ

በአፍሪካ ውስጥ በእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትኩረት መደረግ ያለበት አንድ የጸሎት ርዕስ አለ። የጴንጤቆስጤያዊዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በምድር ላይ እንዲሰፋ እርሱ ወይም እርሷ የምትመራው አጥቢያ ቤተ ክርስትያን አዘውትረው መጸለዩን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህ የኢየሱስ ልመና ነበር፣ እናም ችላ ሊባል አይገባም (ማቴ. 9፡37-38)። ስለዚህ በማህበረሰብህ፣ በአገርህ፣ በአህጉርህ እና በዓለም ውስጥ ላለው የእግዚአብሔር መንግስት እድገት ቤተ ክርስቲያንህን በቁርጠኝነት ጸሎት መምራት አለብህ። በቤተዕምነት ለተላኩ ሚስዮናውያን፣ እንዲሁም በአጥቢያ ሚደገፉት ሚሲዮናዊያን በጸሎት ልታቀርብላቸው ይገባል። በዓለም ላይ ላሉ በሺዎች ለሚቆጠሩ በወንጌል ላልተደረሱ ሰዎች (UPGs) መጸለይ አለብህ።[4]

---

[4] በወንጌል ያልተደረሱ የሰዎች/ ቡድኖች (UPGs) መረጃ በኢንተርኔት ላይ በ www.JoshuaProject.net ላይ ማግኘት ይቻላል.

# የጸሎት ስብሰባ መምራት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የጸሎት ስብሰባን እንዴት በትክክል መምራት እንዳለበት ማወቅ አለበት። ውጤታማ የጸሎት ስብሰባ ለመምራት አንዳንድ ተግባራዊ መመሪያዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

## ቀድሞ ማቀድ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደማንኛውም አስፈላጊ ፕሮግራም፣ ውጤታማ የሆነ የጸሎት ስብሰባ ለማድረግ አስቀድመው ማቀድ ያስፈልጋል። የስብሰባውን ሰዓት እና ቦታ መምረጥ፣ የጸሎት ስብሰባው ዓላማ እና አጽንዖቱ ምን እንደሚሆን በተጨማሪ መወሰን ያስፈልጋል። በስብሰባው ላይ የሚሸፈኑ የጸሎት ነጥቦችን ዝርዝር ማዘጋጀት ስለ እነዚያ የጸሎት ርዕሶች አግባብነት ያለው መረጃ መሰብሰብ ያስፈልግሀ ይሆናል። ከዚያም ይህንን መረጃ በጸሎት ስብሰባ ላይ በተገቢው ጊዜ ከተሳታፊዎች ጋር ማካፈል ያስፈልጋል።

## ጊዜን በአግባብ መጠቀም እና ትኩረት ማድረግ

የጸሎት ስብሰባ ስትመራ፣ ጊዜህን መጠበቅ እና ትኩረት ማድረግ ይኖርብሃል። በሌላ አገላለጽ የጸሎት ስብሰባውን በተወሰነው ጊዜ መጀመር እና ማጠናቀቅ አለብህ። አንዳንድ ሰዎች በሥራ የተጠመዱ ናቸው፣ እና ጊዜያቸውን ስታከብርላቸው ደስ ይላቸዋል። በዚህም ምክንያት፣ በጸሎት ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ እድላቸው ሰፊ ይሆናል።

በተጨማሪም፣ የጸሎት ስብሰባውን ስትመራ፣ ትኩረት ልትሰጥ ይገባል። ይህ ማለት የጸሎት ስብሰባ እዚህ እና እዚያ እንዲረግጡ አለመፍቀድ ፣ ነገር ግን በዓላማው ላይ እንዲቆዩ መርዳት ማለት ነው። በጸሎት ስብሰባ መጀመሪያ ላይ አጭር የቃል እና የአምልኮ ጊዜ ተገቢ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ አብዛኛው የስብሰባው ክፍል በጸሎት ላይ ማተኮር ይኖርበታል።

## ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት መሆን

የጸሎት ስብሰባው በደንብ የተደራጀ እና ትኩረት ያደረገ መሆን ቢገባውም፣ የስብሰባው መሪ ሁል ጊዜ ለመንፈስ ቅዱስ መንቀሳቀስ ክፍት መሆን አለበት። እርሱ ወይም እርሷ ህዝቡ በመንፈስ እንዲጸልዩ ማበረታታት አለበት (ሮሜ. 8፡26-27፤ 1ቆሮ. 14፡15፡ ኤፌ. 6፡18) ለመንፈስ ምሪት እና ለመንፈሳዊ ስጦታዎች መገለጥ ክፍት መሆን አለበት (ሮሜ. 1ኛ ቆሮ.14፡26)።

# ምሳሌነት ያለው የጸሎት ጉባኤ

አንድ ሰው፣ "የጴንጤቆስጤያዊ የጸሎት ስብሰባ ምን መምሰል አለበት?" ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። የዚህ ጥያቄ መልስ የሚገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ የጸሎት ጉባኤ ምሳሌ ይሰጠናል። ይህ የጸሎት ጉባኤ የተካሄደው ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ስደት ላይ ነበረች። የአይሁድ መሪዎች ጴጥሮስንና ዮሐንስን አስረዋቸው ነበር። ከዚያም አስፈራሩዋቸውና በኢየሱስ ስም መስበካቸውን እንዲያቆሙ አዘዟቸው። ሐዋርያቱ ሲለቀቁ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመልሰው የደረሰባቸውን ለአማኞች ነገሩአቸው። ይህን ተከትሎም ክርስቲያኖች መጸለይ ጀመሩ። ጸሎታቸውና የጸሎታቸው ውጤት በሐዋርያት ሥራ 4፡23-31 ተመዝግቧል። ከዚህ

የጸሎት ጉባኤ፣ ዛሬ የጸሎት ስብሰባዎቻችንን እንዴት መምራት እንዳለብን ሦስት ጠቃሚ ትምህርቶችን እንማራለን።

## የጸሎታችን ምንነት

በመጀመሪያ፣ ስለ ጸሎታችን ምንነት ወይም እንዴት መጸለይ እንዳለብን እንማራለን። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚያ የጥንት ክርስቲያን አማኞች ሲናገር "ድምፃቸውን በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ከፍ አድርገው እንዲህ አሉ" (ሐዋ. 4፡24) ይላል። ስለዚህም ጸሎታቸው ብርቱ ነበር ("ድምፃቸውን ከፍ አድርገው") እና በአንድነት ነበር ("ድምፃቸውን በአንድነት ከፍ አደረጉ")። ለመጸለይ ስንሰበሰብ እኛም እግዚአብሔርን አጥብቀን መፈለግ አለብን፤ በአንድነትም መጸለይ አለብን። በተጨማሪም ጸሎታችን በእምነት መቅረብ አለበት (ማር ፲፩፡24)። በዚያ ቀን በኢየሩሳሌም የጸለዩ ሰዎች እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደሚሰማና እንደሚመልስላቸው ሙሉ በሙሉ ይጠብቁ ነበር። እኛም ዛሬ ይሄንኑ ማድረግ አለብን።

## የጸሎታችን ይዘት

በመቀጠል፣ ስለ ጸሎታችን ይዘት ወይም ስለ ምን መጸለይ እንዳለብን እንማራለን። እነዚያ የጥንት ክርስቲያኖች ብዙ ቢያጋጥሟቸውም ጸሎታቸውን በችግራቸው ላይ አላደረጉም። ይልቁንም ትኩረታቸውን በእግዚአብሔር ኃይል እና ታላቅነት ላይ አደረጉ (ሐዋ. 4፡24-25)። የእግዚአብሔርም ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ ጸለዩ (ቁ. 26-28)። በተጨማሪም በስደት ውስጥም ቢሆን እግዚአብሔር ኃይልን እንዲሰጣቸው እና ወንጌልን እንዲሰብኩ ድፍረት እንዲሰጣቸው ጠየቁ (ቁ. 29-30)። እግዚአብሔር "እጁን እንዲዘረጋ" ፣ በመንፈሱ በኃይል እንዲንቀሳቀስ ለመኑ (ሕዝ. 37፡1፤ ሉቃ. ፲፩፡20 ከማቴ. ፲፪፡28፤ ሐዋ. ፲፩፡21)።

## የጸሎታችን ውጤቶች

በመጨረሻም፣ በምንጸልይበት ጊዜ ምን መጠበቅ እንዳለብን እንማራለን:: ልክ እንደ መጀመሪያዎቹ አማኞች የምንጸልይ ከሆነ፣ እኛም በጸሎት ስብሰባዎቻችን ውስጥ እግዚአብሔር መገኘቱን እንዲልክልን መጠበቅ እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ከጸለዩም በኋላ የሚሰበሰቡበት ቦታ ተናወጠ። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ" (ሐዋ. 4፡31)። እነርሱ እንዳደረጉት የምንጸልይ ከሆነ እግዚአብሔር ለእነርሱ ጸሎት ምላሽ በሰጠበት መንገድ ምላሽ እንዲሰጠን መጠበቅ እንችላለን። እርሱን በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላን እና ለጠፉት የክርስቶስ ምስክሮች እንድንሆን ኃይል እንዲሰጠን መጠበቅ እንችላለን።

# ~ ክፍል 3 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እምነት

# ~ ምዕራፍ 9 ~

# ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን ያምናል

በአሜሪካ ሀገር በስፕሪንግፊልድ፣ ሚዙሪ በሚገኘው የአፍሪካ ሆፕ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንፃ ፊት ለፊት ግድግዳ ላይ የተለጠፈ ትልቅ የአፍሪካ ካርታ አለ። በካርታው ላይ እጁን የዘረጋ አፍሪካዊ ሰው ምስል አለ። በሰውየው እጅ መጽሐፍ ቅዱስ አለ፤ ወንጌልን እየሰበከ ነው የሚል መልዕክት ያዘለ ነው። ይህ ምስል በአፍሪካ የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ለሚሰሙዋቸው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት የሚሰብኩ የጴንጤቆስጤያዊ ሰባኪዎችን የሚወክል ነው። ደግሞም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት የበለጠ ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ እንዳሉ እንደማንኛውም መጽሐፍ አይደለም። ታሪክን በትክክል ቢያትትም ከታሪክ መጽሐፍ በላይ ነው። ትክክለኛ ባህሪን ቢያስተምርም ከሥነ ምግባር መጽሃፍ በላይ ነው። ፈላስፋዎች በፅንሰ-ሃሳቦቹ ጥልቀት ቢደነቁም፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የፍልስፍና መጽሐፍ ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔርን ቃል" ይዟል (ሮሜ. 3፡2)። እርሱም የሰውን ልጅ ኃጢአተኛነት ሁኔታ ይገልጣል፣ ደግሞም በክርስቶስ በኩል የመዳን መንገድን ያሳያል። ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ይመረምራል።

# የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ይመለከተዋል?

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ለመጽሐፍ ቅዱስ ከፍ ያለ ክብር አላቸው። ለሰው ልጆች የተሰጠ የእግዚአብሔር መልእክት እና ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያምናሉ። ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም አገልግሎት እና ልምምድ መሠረት ነው። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን አመለካከት "የዓለም ጉባኤ እግዚአብሔር ኅብረት የእምነት መግለጫ" ጠቅለል አድርጎ ገልጾታል። "የቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔርነት" በሚል ርዕስ አንቀጽ 1 ላይ "ቅዱሳን መጽሐፍት፣ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን፣ በእስትንፋሰ እግዚአብሔር ናቸው ፤እግዚአብሔር ለሰው የሰጣቸው መገለጦች ናቸው፣ ስህተት አልባ፣ የአማኝ ማህበረሰብ እምነትና የምግባር ገዢ ባለ ሥልጣን ናቸው (2ጢሞ. 3፡15-17፤ 1 ተሰ. 2፡13፤ 2 ጴጥ. 1፡21)" [1] ሲል ያትታል። ከላይ ያለውን ሃሳብ የበለጠ ለመረዳት ምን ማለት እንደሆነ በአራቱ ክፍሎች ከፍለን በዝርዝር እንመልከተው :-

## በእስትንፋሰ እግዚአብሔር

በመጀመሪያ የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ "ቅዱሳት መጻሕፍት፡- ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን እያንዳንዱ ቃላት በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ ናቸው" ብሎ ያምናል። ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ ናቸው ስንል እግዚአብሔር መንፈስ የፈለገውን ሃሳብ እንዲጽፉ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ በመምራት በነቢያትና በሐዋርያት ላይ ተንቀሳቅሷል ማለታችን ነው። ጳውሎስ "ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው" (2 ጢሞ. 3፡16) ብሎ በጻፈ ጊዜ ይህንን እውነት አረጋግጧል። ጴጥሮስ ይህን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሂደትን በዝርዝር ገልጾታል፡ - "ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጐመው አይደለም፤21 ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም" (2ጴጥ. 1፡20-21)።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው ስንል መለኮታዊ ምሪቱ እስከ ጽሑፉ ቃሎች ድረስ ይዘልቃል ማለታችን ነው። እግዚአብሔር የቅዱሳት መጻሕፍትን ሐሳብ ማነሳሳት ብቻ ሳይሆን ሂደቱን በበላይነት በመቆጣጠር እነዚህ ሀሳቦች የተገለጹባቸውን ቃላቶችን መርጧል። ኢየሱስ ይህንን እውነት ሲናገር፣ " ነገር ግን ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል" (ሉቃስ 16፡17) ሲል ተናግሯል። ስለዚህ እስትንፋሰ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቃል በመንፈስ ቅዱስ የተመረጠ ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ቃላት የተካተቱት እግዚአብሔር ስለፈለገ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ ስለሆነ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ መጠራቱ ተገቢ ነው። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን እንደ "የእግዚአብሔር ቃል" ወይም "የእግዚአብሔር ቃል" በማለት ከአርባ ጊዜ በላይ ይጠቅሳል።

---

[1] አባሪ 1ን ተመልከት፡ "የዓለም ጉባኤ እግዚአብሔር ኅብረት የእምነት መግለጫ"

### የእግዚአብሔር መገለጥ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው መገለጥ" እንደሆነ ያምናል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ፈቃድ በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ገልጧል ማለት ነው። ሰዎች እርሱን፣ ሥራዎቹን እና መንገዶቹን እንዲያውቁ መጽሐፍ ቅዱስን አዘጋጅቷል። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በመስጠት ራሱን የሚገልጥ አምላክ መሆኑን አሳይቷል። እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ያሉ ወንዶችና ሴቶች እርሱንና የማዳን እቅዱን እንዲያውቁ እንደሚፈልግ መጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ ነው።

### ስህተት አልባ

በተጨማሪም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አልባ መሆኑን ያምናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አልባ ነው ማለት ከስህተት የጸዳ ነው ማለት ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላቶች በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ እንደመሆናቸው መጠን ፅንሰ-ሀሳቦቹ እውነት ናቸው፣ መግለጫዎቹም ትክክል ናቸው። መዝሙረኛው "የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው" (መዝ. 18፡30) ብሏል። ኢየሱስ "ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም" (ማቴ. 24፡35) ሲል ይህንን እውነት አረጋግጧል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አልባ መሆኑን ስንናገር፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሊረዳ የሚገባው፣ እየተናገርን ያለነው እጃችን ላይ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዳልሆነ ነው። እያልን ያለነው ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጀመሪያዎቹ የቅጅ (እናት መዝገብ) ባሉ ጽሑፎች ውስጥ ስህተት አልባ እንደሆነ እየጠቀስን ነው። እጃችን ላይ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የሰሩት ሊቃውንት ጽሑፉን በትክክል ለመተርጎም ጠንክረው ሰርተዋል። ቢሆንም፣ ሰው በመሆናቸው ስህተት መፈጠሩ የማይቀር ነው። እነዚህ ስህተቶች ግን ጥቃቅን ናቸው። እጃችን ላይ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመጀመሪያዎቹ ጸሐፊዎች የተገለጠውን የ**እግዚአብሔር** ቃል በትክክል እንደሚያንጸባርቁ እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

### የአማኝ ማኅበረሰብ እምነትና የስነ ምግባር ገዢ ባለ ሥልጣን ነው

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስ የአማኝ ማህበረሰብ "ሥልጣን ያለው የእምነት እና የስነ ምግባር መመሪያ" እንደሆነ ያምናል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው ምን ማመን እንዳለባለበትና እና እንዴት መኖር እንዳለበት ይነግራል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ሥልጣን ያለው ቃል ነው። ይህ ማለት ትምህርቱ መታመን አለበት፣ ትእዛዙም መከበር አለበት ማለት ነው። ንጉሥ ዳዊት ይህንን እውነት ተረድቶ ስለ ነበር የእግዚአብሔርን ቃል "ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን" ብሎ ጠራው (መዝ. 119፡105)።

## የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ያክብረው

ታዲያ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ሊመለከተው ይገባል? እርሱ ወይም እርሷ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚመለከት ምን ዓይነት አመለካከትና አስተያየት ሊኖራቸው ይገባል? መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያመነ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሦስት መንገድ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መቅረብ ይኖርበታል።

## በቅዱስ አክብሮት

የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ከቅዱስ አምላክ ልብ የመነጨ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱስ ስለሆነ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከምንም በላይ በታላቅ አክብሮት ሊይዘው ይገባል። እርሱ ወይም እርሷ የእግዚአብሔርን ቃል ማክበር እና በቅዱስ አክብሮት መያዝ አለባቸው። ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩትን ክርስቲያኖች እንዲህ ያለ አመለካከት ስለነበራቸው አመስግኗቸዋል:- “የእግዚአብሔርን ቃል በተቀበላችሁ ጊዜ... ” (1 ተሰ. 2:13) የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለሚያከብር ቃሉን አስታኮ የፈለገውን ከመናገር እና ትምህርቶቹን ከማዛባት ይቆጠባል። ጴጥሮስ ይህን የሚያደርጉ “ለራሳቸው ጥፋት” እንደሚያደርጉ አስጠንቅቋል (2 ጴጥ. 3፡16)።

## ጥልቅ ፍቅር

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን ማክበር ብቻ ሳይሆን እርሱ ወይም እርሷ ለትምህርቶቹ ልባዊ ፍቅር ሊኖራቸው ይገባል። የመዝሙር 119 መጸሐፊ ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን ፍቅር በሚገባ ሲገልጽ እንመለከታለን። ይህ መዝሙር በ176 ቁጥሮች ስላሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ረጅሙ ምዕራፍ ነው። ምዕራፉ ወደ እግዚአብሔር የቀረበ ጸሎትም ነው።

በዚህ አስደናቂ ጸሎት ላይ ደራሲው ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን ፍቅር ደጋግሞ ገልጿል። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔርን “እኔ እወደዋለሁና፣በትእዛዝህ ደስ ይለኛል” ይለዋል (ቁ. 47)። እንዲሁም አምላክ ቃሉ በሕይወቱ ላይ ምን ተጽዕኖ እንዳሳደረበት ያስታውሷል:- “ነፍሴ ሁልጊዜ ሕግህን ናፈቀች . . . ሥርዓትህ ተድላዬ ነው፤ . . . አማካሪዎቼ ናቸው” (ቁ. 20፣24)። እንደ መዝሙራዊው፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለአምላክ ቃል ልባዊ ፍቅር ሊኖረው ይገባል።

## ብርቱ መተማመን

በተጨማሪም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው ብሎ ስለሚያምን፣ በብርቱ መተማመን ወደ እግዚአብሐየር ቃል መቅረብ ይጠበቅበታል። ቃሉን ማመን እንደሚችሉ ያውቃሉ፤ በተስፋ ቃሉ ላይ እምነት ሊጥል ይችላል። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሙሉ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለሚታመን፣ እንደ አብርሃም፣ እግዚአብሔር የገባውን ቃል በእርግጥ እንደሚፈጽም ሙሉ በሙሉ የሚያምን መሆን አለበት (ሮሜ. 4፡21)።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት መሆኑን ማመኑ ብቻ ሳይሆን ኃይል እንዳለበት ይገነዘባል። አጽናፈ ዓለም የተፈጠረው በእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 1፡1-3)። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ ሲናገር “የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነው። (ዕብ. 4:12) ሁለት ጊዜም ከተሳለ ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው። ጳውሎስ ወንጌልን “ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኀይል ነው” ሲል ገልጾታል (ሮሜ. 1:16)። እነዚህ እና ሌሎች ብዙ ምንባቦች የእግዚአብሔርን ቃል ኃይል መሆኑን ይናገራሉ። ለምሳሌ በነቢዩ በኢሳይያስ በኩል እግዚአብሔር ስለ ቃሉ ሲናገር:- “ ዝናምና በረዶ ከሰማይ ወርዶ፣ምድርን በማራስ፣እንድታበቅልና እንድታፈራ ለዘሪው ዘር፣ለበላተኛም እንጀራ እንድትሰጥ ሳያደርግ፣ወደ ላይ እንደማይመለስ ሁሉ፣11 ከአፌ የሚወጣውም ቃሌ፣በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም፤ነገር ግን የምሻውን ያከናውናል፤የተላከበትንም ዐላማ ይፈጽማል” ይላል(ኢሳ. 55፡10-11)።

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መንገድ እንደሚያሳይ ይነግረናል (መዝ. 119:105)፣ ነፍስን እንደሚያድን (ያዕቆብ 1:21) እምነትን እንደሚፈጥር (ሮሜ 10:17)፣ ዳግም ልደት አንደሚሰጥ (1 ጴጥ. 1:23) ፤ ደግሞም ይቀድሳል (ዮሐ. 17:17)፣ ያንጻል (የሐዋርያት ሥራ 20:32)፣ ይፈውስና ያድናል (መዝ. 107:20)፣ ያጸዳል (ዮሐ. 15:3)፣ ያበለጽጋል (ኢያሱ 1:8) ደስታን ይፈጥራል

(ኤር. 15:16) እና ብዙ ተጨማሪ በረከቶች ይሰጣል። በእነዚህ ወሳኝ እውነቶች ምክንያት፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጠንካራ እምነት ሊኖረው ይገባል።

# መጽሐፍ ቅዱስን የተመለከተ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ኃላፊነቶች

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ አንዳንድ ሀላፊነቶችን ትወስዳለህ። ከእነዚህ ኃላፊነቶች ውስጥ ስድስቱ የሚከተሉት ናቸው፡-

## መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ

በመጀመሪያ፣ ሰፊ የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት ሊኖርህ ይገባል። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለአገልግሎቱ መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቆ ከማወቅ የበለጠ ብቁ የሚያደርገው ነገር የለም። በተቃራኒው ግልብ የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት መጋቢውን ከብቃት እንደሚያጎድለው ይታወቃል። በመሆኑም ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመረዳትን የዕድሜ ልክ ፍለጋ ውስጥ ለመግባት እራስህን መስጠት አለብህ። ይህንን በሦስት መንገዶች ማድረግ ትችላለህ፡-

**1. ዕለታዊ ንባብ፡-** በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ የአምላክን ቃል ማወቅ ትችላለህ። ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ ልማድ ማዳበር አለብህ።[2] በቀን በአማካይ አሥራ አምስት ደቂቃ በማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ዓመት ውስጥ ማጠናቀቅ ትችላለህ። ይህን ልማድ ከቀን ከቀን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀትህ ይጨምራል።

**2. ስልታዊ ጥናት፡-**ስልታዊ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የቅዱሳት መጻሕፍትን እውቀት ማሳደግ ትችላለህ። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይህ ልማድ በቤርያ በአይሁድ አማኞች መካከል እንደነበር ይናገራል። እንዲህ ይላል፡- "ምክንያቱም ነገሩ እንደዚህ ይሆንን እያሉ መጻሕፍትን በየዕለቱ በመመርመር ቃሉን በታላቅ ጉጉት ተቀብለዋል" (የሐዋርያት ሥራ 17:11)። የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ የመመርመርን ልማድ ከቤርያውያንን መኮረጅ ብልህነት ነው።

በተጨማሪም ቅዱሳን ጽሑፎችን በማጥናት ረገድ የሚረዳህ የግል ማመሳከሪያ ቤተ መጻሕፍት መገንባት ያስፈልጋል። ይህ ቤተ መጻሕፍት እንደ ኮንኮርዳንስ፣ ማብራሪያዎችና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች የመሳሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ መጻሕፍትን ማካተት ይኖርበታል። በተጨማሪም ጥሩ የጥናት ጹሑፍ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ማካተት ይገባል። ለምሳሌ በጣም ጥሩ የጴንጤቆስጤያዊ ጥሩ የጥናት ጹሑፍ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ከሚባሉት አንዱ በስፕሪንግፊልድ፣ ሚዙሪ፣ ዩኤስኤ ውስጥ በህይወት አሳታሚዎች የታተመው የሙሉ የሕይወት ጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ነው።[3]

ከተቻለ በጴንጤቆስጤያዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማጠናቀቅ አለብህ። ይህ የቅዱስ ቃሉን እውቀት እና የአገልግሎት ክህሎት እውቀትህን በእጅጉ ይጨምራል። የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በአህጉሪቱ ሰፊ የአገልጋዮች ማሰልጠኛ ተቋማት አሉት።

---

[2] በዚህ ርዕስ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 15ን ተመልከትን "ጠንካራ የግል ሕብረት የማድረግ ልማድ"

[3] አንድ ጥሩው የጴንጤቆስጤ ጥሩ የጥናት ጹሑፍ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ የሙሉ ሕይወት ጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ "በመንፈስ ሕይወት የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ" ወይም "እሳት መጽሐፍ ቅዱስ" በመባልም ይታወቃል። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።ለበለጠ መረጃ፡ https://www.firebible.org/ ይመልከቱ።

እነዚህ ተቋማት አዳሪ እና ተመላላሽ ትምህርት ቤቶች ያካትታሉ። ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች እና በህንድ ውቅያኖስ ተፋሰስ ውስጥ በሁሉም አገሮች ቢያንስ አንድ የጉባኤ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ይገኛል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ጉባኤ እግዚአብሔር እና ጉባኤ እግዚአብሔር ላልሆኑ አገልጋዮች ሥልጠና የሚሰጡ ናቸው።[4]

**3.ማሰላሰል።** መጻሕፍትን በሥልት መያዝ አለብህ። በሳምንት ቢያንስ አንድ አዲስ ጥቅስ ወይም የቅዱስ ቃሉ ምንባብ በቃላችን መያዝ ጥሩ ግብ ነው። በተጨማሪም፣ የምታስተምረውን ወይም የምንሰብከውን ማንኛውንም ፅሁፍ ወይም የቅዱሳት መጻህፍት ክፍል በቃላችን መያዝ ጥሩ ልምድ ነው። ይህ ልምምድ በስብከት ውስጥ የበለጠ ነፃነትን ይሰጠናል። እንዲሁም በልብ የሚያዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በእጅጉ ይጨምራል።

## በመስፈርቶቹ መኖር

ሁለተኛ፤ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደመሆንህ መጠን በመጽሐፍ ቅዱስ መሥፈርቶች መኖር አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም፤ ትምህርቱ ሕይወትህንና አገልግሎትህን እንዲቀርጽ መፍቀድ አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ “ቃሉ የሚናገረውን አድርጉ እንጂ ሰሚዎች ብቻ ሆናችሁ ራሳችሁን አታታልሉ” (ያዕቆብ 1:22፤ ሮሜ. 2:13) ከመዝሙረኛው ጋር፣ “የእውነትን መንገድ መርጫለሁ፤ሕግህንም ፊት ለፊቴ አድርጌአለሁ። 31 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከምስክርነትህ ጋር ተጣብቄአለሁ፤ አሳልፈህ ለውርደት አትስጠኝ ” ብለህ በእውነት መጸለይ ይገባሃል (መዝ. 119፡30-31)።

## የእውነትን ቃል በትክክል ማስረዳት

ሦስተኛ፤ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ “የእውነትን ቃል” በትክክል ለማስረዳት ራስህን መስጠት አለብህ (2ጢሞ. 2፡15)። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል መሆኑን ስለምታምን ቅዱሳት መጻሕፍትን ሆን ብለህ በራስህ ሐሳብ ጋር የማጣመም ፈተናን መቋቋም አለብህ። ለራሳቸው ጥፋት እና ሌሎችን መጥፋት ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያጣምሙ “ዕውቀት የጐደላቸውና ጽናት የሌላቸው ሰዎች ” የሚለውን የጴጥሮስን ማስጠንቀቂያ መስማት ያስፈልጋል (2ጴጥ. 3፡16)። እናም " አንተ ግን ከትክክለኛው ትምህርት ጋር ተስማሚ የሆነውን አስተምር” የሚለውን የቅዱሳት መጻሕፍትን ትእዛዝ በጥንቃቄ ማክበር አለብህ (ቲቶ 2፡1)።

## ተልእኮውን በታማኝነት ለማራመድ

አራተኛ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጸው የእግዚአብሔርን ተልእኮ በግልፅ ለመረዳት እና በትጋት ለማራመድ መቁረጥ አለብህ። እግዚአብሔር ተልዕኮ መር አምላክ እንደሆነ እና በምድር ላይ ያለውን ተልእኮ ለመፈጸም እየሰራ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይህ ተልዕኮ አንዳንድ ጊዜ ሚሲዮ ዴ ይባላል። እግዚአብሔር በምድር ላይ ካሉ ነገድ፣ ቋንቋ እና ሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ለመቤዠትና የመጥራት ተልእኮ አለው (ራዕ. 5፡9)።[5]

እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በዚህ ተልእኮ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር እንድጣመር ቤተ ክርስቲያንህን መምራት አለብህ (ማቴ. 24፡14)። ይህንን ለማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር

[4] በአፍሪካ የሚገኙ የጉባኤ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በአፍሪካ ቲኦሎጂካል ማሰልጠኛ አገልግሎት (ATTS) ድረ-ገጽ https://afri caatts.org/ ላይ ይገኛል።

[5] በአፍሪካ ሆፕ ዲስከቨሪ ተከታታይ ሥራ የታተመው በፖል ዮርክ የተዘጋጀው የተልዕኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አንዱ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው።

ተልእኮ ምን እንደሚያስተምር በግልጽ መረዳት አለብህ። ቤተ ክርስቲያንህንያንን ተልእኮ ለመወጣት የበኩሏን እንድትወጣ ለመምራት እራስህን መስጠት አለብህ።

## ቃሉን ለመስበክ እና ለማስተማር

አምስተኛ፤ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት መስበክ እና ለሕዝብህ ማስተማር አለብህ። ይህን በማድረግህ "በጌታ ጸጋና እውቀት እንዲያድጉ" (2 ጴጥ. 3፡18) ትረዳቸዋለህ። የእግዚአብሔር ሕዝቦች "ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ" መሆናቸውን ታረጋግጣለህ (2 ጢሞ. 3፡17)። ጳውሎስ በእምነት ልጁን ጢሞቴዎስን "ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም" ይለዋል(2 ጢሞ. 4:2)

የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት የሚያስተምር የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ይሸለማል (ማቴ. 24፡ 45-47)። በዚህ ሃላፊነት የወደቀ ደግሞ በጽኑ ይፈረድበታል (ያዕቆብ 3፡1)።

## የተገለጠውን እውነት አጥብቆ መከላከል

በመጨረሻም፣ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተገለጠውን እውነት ለመጠበቅ እና ለመከላከል ዝግጁ መሆን አለብህ። አንተም እንደ ጳውሎስ፣ "ለወንጌል ጠበቃ" መሆን አለብህ (ፊልጵ. 1፡16)። በሐዋርያው አነጋገር፣ "ሌሎችን ትክክል በሆነው ትምህርት እንዲያበረታታና ይህንኑ ትምህርት የሚቃወሙትን ይወቅስ ዘንድ እንደ ተማረው በታመነ ቃል የሚጸና መሆን አለበት" (ቲቶ 1፡9)። ይህንንም በማሰብ ቅዱሳንን ከሐሰተኛ አስተማሪዎች እና ከሐሰት ትምህርቶች በመከላከል የእግዚአብሔርን መንጋ በትጋት መጠበቅ አለብህ (ሐዋ. 20፡28-31)። ይህንን ለማድረግ ጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትን ለቤተ ክርስቲያን በታማኝነት ማስተማር ይገባል። እንዲሁም ከእግዚአብሔር ቃል እውነት የሚያፈነግጡ ማናቸውንም ነገሮች በማጋለጥና በመቃወም መንጋውን መጠበቅ ትችላለህ።[6]

---

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የመጽሐፉ ሰው በመባል መታወቅ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን ማመን አለበት። በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስን ከፍ ባለ ክብር ሊመለከተው ይገባል። የእግዚአብሔርን ቃል አውቆ በትጋት ማስተማር እና ትእዛዛቱን ለእግዚአብሔር ህዝብ መስበክ አለበት።

[6] መንጋውን ስለመጠበቅ ተጨማሪ ለማግኘት ምዕራፍ 27ን ተመልከት፡- "መንጋውን መጠበቅ" የሚለውን ተመልከት።

# ~ ምዕራፍ 10 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ እውነትን ይደግፉል

በአፍሪካ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እርሱ ወይም እርሷ በሚመግቡት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርት እና እምነትን በታማኝነት መያዝ አለባቸው። ይህንን ለማድረግ ጴንጤቆስጤያዊያዊ እንቅስቃሴ የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች በአግባብ መረዳት አለባቸው። መረዳት ብቻ ሳይሆን እነዚህን እውነቶች መጠበቅም መቻልም አለባቸው።

የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርት እና እምነትን በታማኝነት መያዝ በሥነ-መለኮታዊ ክርክር ማሸነፍ ከመቻል የበለጠ ነው። ጉዳዩ ታላቁን ተልዕኮ በተሳካ ሁኔታ ስለ መፈጸም ነው። አንድ ሰው በአማኞች ሕይወት ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚያይበት መንገድ አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዝሙር የማድረጉን የክርስቶስን ትእዛዝ የሚፈጽምበትን መንገድ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል (ማቴ. 28: 18-20)። የመንፈስ ቅዱስን የማስታጠቅ ሥራ በግልጽ ካልተረዳ፣ የታላቁ ተልዕኮ መፈጸም የማይቻል ነው።

አንድ መቁረጫ የጎደለውን መቀስ አስብ። የቀረው መቁረጫ የቱንም ያህል ስለታም ቢሆን በራሱ ከንቱ ነው። ይሁን እንጂ ሁለቱ መቁረጫዎች በአንድ ላይ ሲሆኑ መቀሱ ጥቅም ላይ መዋል ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚሰጠው ትምህርትም እንዲሁ ነው። አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስን የድህነት ሥራ ብቻ አጽንዖት የሚሰጥ ከሆነ (በጳውሎስ መልእክቶች ላይ እንደተገለጸው)፣ በተቃራኒው የማስታጠቁን ሥራ (በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደተገለጸው) ቸል ካለ፣ በአማኞች ሕይወት ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እየቀነሰ ይሄዳል፤ በተጨማሪም የመንግሥቱም ሥራ እየቀነሰ ይሄዳል። ሆኖም ሁለቱም ፅንሰ-ሀሳቦች አንድ ላይ ሲሆኑ ስለ መንፈስ ስራ የበለጠ የተሟላ ግንዛቤ ይኖርሃል። በውጤቱም የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ቃሉ ሙሉ እውነት የእግዚአብሔርን መንፈስ ይለማመዳሉ። የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ በብቃት ለማራመድ ይቻላል።

ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርት የመጠበቅ ሃላፊነት ያትታል። የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርት ስንል በጴንጤቆስጤያዊ ሊቃውንት

ልዩ ትኩረት የተደረገባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች እና ልማዶች ማለታችን ነው። እነዚህ ትምህርትቶች የመንፈስ ቅዱንን አካልነትን እና ግብር በአማኞች ህይወት ውስጥ እንዴት እደሚሰሩ የሚያሳስቡ ናቸው።

በአፍሪካ ያለው የጴንጤቆስጤያዊ እንቅስቃሴ የወንጌል እና የሚስዮናዊነት ግስጋሴውን ለማስቀጠል ከተፈለገ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የጴንጤቆስጤያዊ አስተምህሮዎችን በታማኝነት በቤተክርስቲያናቸው ውስጥ ማስተዋወቅ አለባቸው። በዚህ ጥረት ካልተሳካላቸው እንቅስቃሴው እንደ ሌሎች እንቅስቃሴዎችም በእርግጠኝነት ይዳከማል በጊዜ ሂደትም ይገታል። ይህ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኖቻቸው የጴንጤቆስጤያዊ እምነት ውጫዊ ምልክቶችን ሊይዙ ይችላሉ ፤ ሆኖም በመጨረሻ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እና የሚስዮናዊ ቅንዓትን ያጣሉ። በስተመጨረሻም ቤተክርስትያኒቱ አሁን ላይ አቅም የሌላት ግን መልካም ስም የነበራት ያረጀ ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች (2ጢሞ. 3፡5)።

# መሰረቱን መረዳት

የጴንጤቆስጤያዊ ሊቃውንት ሁሉንም ቅዱሳት መጻሕፍት ለትምህርቶቻቸው መነሻ አድርገው ይመለከቷቸዋል። ነገር ግን፣ ትምህርተ መንፈስ ቅዱስን ለመረዳት ዋና ምንጫቸው የአዲስ ኪዳን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን እንዴት እንደሚሞላ፣ እንደሚያስታጥቅ እና ለመንግሥቱ አገልግሎት እንደሚጠቀም አብርሆት እና ግንዛቤ አግኝተዋል።

የጴንጤቆስጤያዊ ሊቃውንታት ከጴንጤቆስጤያዊ ካልሆኑ ምሁሮች የሚለየው ሥነ-መለኮታዊ አቋም በሐዋሪያ ሥራ መጽሐፍን ንባብ ላይ የተመሰረተው ነው። ጴንጤቆስጤያዊ ያልሆኑ የሐዋርያት ሥራን ታሪክ ብቻ አድርገው ያነቡታል። መጽሐፉ፣ ለእነርሱ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም እንዴት እንደጀመረች እና ከዚያም በሮማ ግዛት ውስጥ እንዴት እንደተስፋፋች በእስትንፋስ እግዚአብሔ የተዘገበ ታሪክ እንደሆነ ያምናሉ። በሌላ አነጋገር ጴንጤቆስጤያዊ ያልሆኑ ሰዎች የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደ መደበኛ ታሪክ ብቻ ይቆጥሩታል፤ በዚያ ወቅት እና ቦታ ማለትም በመጀመሪያው መቶ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመዘገብ አላማ ብቻ እንዳለው ያስባሉ።

ጴንጤቆስጤያዊዊያን ግን የሐዋርያት ሥራን የሚመለከቱት በተለየ መንገድ ነው። መጽሐፉ የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በትክክል ይተርካል በማለት ከሌሎች ወንጌላውያን ጋር ይስማማሉ። ይሁን እንጂ መጽሐፉን እንደ ቅዱስ ታሪክ ባለፈ ያዩታል። ጴንጤቆስጤያዊዊያን ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ እንዴት መሆን እንዳለባት ዘላቂ አርአያ ለመስጠት እንደሆነ ያምናሉ። የሐዋርያት ሥራ ክርስቲያኖች በዚያ ወቅት እና ቦታ ብቻ ሳይሆን በአሁን ጊዜ እና ቦታ እንዴት መኖር እና ማገልገል እንዳለብን የሚያሳይ ዘላቂ ምሳሌ ይሰጠናል። ከሐዋርያት ሥራ እንደምንረዳው ቤተ ክርስቲያን ያለችው በመንፈስ ኃይል ታጥቃ ከአካባቢዋ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ የክርስቶስ ምስክር ለመሆን ነው (የሐዋርያት ሥራ 1፡8)።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደተጠመቁ እና ያ ተሞክሮ ሕይወታቸውን እና አገልግሎታቸውን እንዴት እንደለወጠው ይዘግባል። በሚከተሉት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና ተአምራዊ ምልክቶች ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን የምትፈጽም መሆኗን ያሳያል (5፡12-16፤ 6፡8፤ 15፡12)። በሐዋርያት ሥራ፣ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን አገልጋዮች የመዳንን ወንጌል በድፍረት እንዲያውጁ ጥሪ ያደርጋል፣ ኃይል ይሰጣል እና ወደ አሕዛብ ይልካል። እግዚአብሔርን ሲታዘዙ መንፈስ በስልታዊ መንገድ ይመራቸዋል። የሚስዮናዊነት ሥራቸው ከኃይለኛ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጋር አብሮ የሚፈስ ነበር (2፡4፤ 4፡31)።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የምናየው የመንፈስ ቅዱስ ተልኮ መርነት የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ምን መምሰል እንዳለባት ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ግልጽ የሆነ አርአያ ያስቀምጥለታል።

# ጴንጤቆስጤያዊያንን "ልዩ" የሚያደርጋቸውን ትምህርት ማስተዋወቅ

ጴንጤቆስጤያዊያን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዴት እንደሚቀበል ዘላቂ አብነት እንደሚሰጥ ያምናሉ። የመንፈስ ጥምቀት ልምምድ የሚመጣው አዲስ ልደትን አስቀድመው ለተለማመዱ አማኞች ነው። መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉ ሰዎች መንፈስ እንደሚሰጣቸው በልሳን በመናገር የመስካሪነት ምልክት ይከተላቸዋል። እነዚህን ልዩ የጴንጤቆስጤያዊ አስተምህሮዎችን በአጭሩ እንከልስ።

## ድኅረ ድሕነት የመንፈስ ጥምቀት አስተምህሮ

ድኅረ ድሕነት የመንፈስ ጥምቀት አስተምህሮ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት "ከአዲስ መወለድ የተለየ እና ከዚያ በኋላ የሚከተል" ልምምድ እንደሆነ ይቀበላል።[1] ጴንጤቆስጤያዊ ያልሆኑ ሰዎች ዳግመኛ መወለድን እና የመንፈስ ጥምቀትን እንደ አንድ የመዳን ልምድ ሁለት ክፍሎች አድርገው ይመለከቱታል። ጴንጤቆስጤያዊያን ግን እንደ ተለያዩ እና ተከታታይ ልምምዶች አድርገው ይመለከቷቸዋል። ጴንጤቆስጤያዊያን ይህ እውነት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሦስት ትረካዎች እንዴት እንደተገለጸ ይጠቁማሉ:-

1. **በሰማርያ መንፈስን መቀበል (ሐዋ. 8፡4-17)።** በዚህ ታሪክ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው። የሰማሪያ ሰዎች ቃሉን በጥሞና አዳመጡ፣ መልእክቱን አመኑ፣ ከአጋንንት እስራት ነፃ ወጡ፣ ታላቅ ደስታንም አገኙ፣ እናም በውሃ ተጠመቁ (ቁ. 5-8፤12)። ነገር ግን፣ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት ከጥቂት ቀናት በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ መጥተው እጃቸውን ሲጭኑባቸው ድረስ ነበር (ቁ. 14-17)።

2. **የሳውል (ጳውሎስ) መንፈስ ቅዱስን መቀበል (ሐዋ. 9፡1-19)።** ሳውል ኢየሱስን በደማስቆ መንገድ አገኘው። በዚያን ጊዜ፣ በኢየሱስ ለማመኑ ምልክት የሚሆነው ሁለት ጊዜ "ጌታ" ብሎ መጥራቱ ነው (ቁ. 5፤ 22፡8-10)። በኋላም በመልዕክቱ "በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር፣ ማንም "ኢየሱስ ጌታ ነው" የሚል እንደሌለ እነግራችኋለሁ" (1ቆሮ. 12፡3) በማለት ጽፏል። ሳውል ወዲያውኑ ራሱን ለክርስቶስ አስገዛ ጌታን ወደ ከተማይቱ እንዲገባ ሲያዘው ታዘዘ (ቁ. 6-9)። በዚያም፣ አናንያስ "ወንድም ሳውል" ብሎ ጠራው (ቁ. 17፤ 22፡13)። ከሦስት ቀን በኋላ፣ አናንያስ እጁን በጫነበት ጊዜ፣ ሳውል መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ (ቁ. 17-18)።

3. **አሥራ ሁለቱ የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት መንፈስን መቀበላቸው (ሐዋ. 19፡1-7)።** እነዚህ ሰዎች በኤፌሶን የተጀመረችው ቤተ ክርስቲያን አባላት ሳይሆኑ አይቀሩም (18፡27)። ሉቃስ "ደቀ መዛሙርት" ብሎ ይጠራቸዋል (ቁ. 1)። መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን መልእክት ያመኑ መሆኑ ግልጽ ነበር፣ እናም በክርስቶስ አዳኝነት ላይ እምነት

[1] ከጉባኤ እግዚአብሐየር የእምነት መግለጫ፣ መግለጫ 9: "በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" (አባሪ 2 ተመልከት)።

ነበራቸው። ስለዚህም ጳውሎስ በውኃ አጠመቃቸው (ቁ. 5)። ከዚህ ሁሉ በኋላ "መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ" (ቁ. 6)።

በሦስቱም አጋጣሚዎች፣ በሰዎቹ ድህነትን ማግኘት እና በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ልምምድ መካከል ግልጽ የሆነ የጊዜ ልዩነት ነበር። በተጨማሪም፣ የመንፈስ ጥምቀትን አላማው ለምስክርነት ማስታጠቅ መሆኑ ልምምዱ ከአዲስ ልደት በኋላ ተከትሎ መምጣቱ ምክንያታዊ ያደርገዋል (ሐዋ. 1፡8)።

## በልሳኖች የመናገር ምልክትነት አስተምህሮ

ጴንጤቆስጤያዊያን በመቀጠልም አማኝ መንፈስ ቅዱስን በእምነት ሲቀበል፤ "መንፈስ እንደሚሰጥ በልሳኖች የመናገር ደግሞ እንደ ውጫዊ መነሻና ማስረጃ ያገለግላል።፣ ጴንጤቆስጤያዊያን በልሳኖች የመናገር ምልክትነት ትምህርታቸውን የወሰዱት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ካለው ታሪክ ድምዳሜ በመስራት ነው" [2]

መጽሐፉ አምስት ጊዜ ሰዎች በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ ወይም እንደተጠመቁ ይናገራል። ከእነዚህ በሦስቱ አጋጣሚዎች፣ ጸሑፉ በግልጽ መንፈስ የተቀበሉት መንፈስ ቅዱስ በመሞላታቸው ምክንያት በልሳኖች እንደተናገሩ ይናገራል። የመጀመሪያው ታሪክ የተከሰተው በጴንጤቆስጤ ቀን 120 የሚያህሉ ደቀ መዛሙርት " ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር" (ሐዋ. 2፡4)። ሁለተኛው ምሳሌ የተከናወነው በቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ውስጥ በባሕር ዳርቻ በምትገኝ በቂሳርያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ተሰብሳቢዎቹ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ" ይላል። ይኸውም በልሳን ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ስለ ሰሚቸው ነው" (10፡45-46)። ሦስተኛው ታሪክ የተከናወነው በኤፌሶን ከተማ ሲሆን ጳውሎስ ከአሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ጋር የተገናኘበት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ጳውሎስ እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ"(19፡6) ይላል።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞሉባቸው ሁለት ታሪኮች፣ ጽሑፉ የሚያመለክተው የጸጋው ተቀባዮች በልሳኖች መናገራቸውን ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ በሰማርያ የነበሩት አዲስ አማኞች ሐዋርያት፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ፣ እጃቸውን በጫኑ ጊዜ መንፈስን ተቀበሉ (ሐዋ. 8፡17)። ሉቃስ በልሳን ይናገሩ እንደነበር በግልጽ ባይናገርም፣ ጽሑፉ ግን በጣም አስደናቂ እና አሳማኝ የሆነ ነገር እንደተፈጸመ ይገልጻል። ጠንቋዩ ሲሞን በጣም ከመደነቁ የተነሳ ስጦታውን ለመግዛት ጠየቀ። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ሲሞን ያየው ምልክት እነዚህ አዳዲስ አማኞች በልሳን ሲናገሩ እንደሆነ ይስማማሉ፤ ምክንያቱ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሌላ ስፍራ የተጠቀሰው መንፈስን የመቀበል ምልክት ይህ ብቻ ነው።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላቱ የሚዘግብ የመጨረሻው ታሪክ ሐናንያ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር በጠርሴሱ ሳውል ላይ እጁን ጭኖ በመንፈስ እንዲሞላ ከእርሱ ጋር የሚናገረው ታሪክ ነው (ሐዋ. 9፡17-18)። ጽሑፉ በዚህ ጊዜ ሳውል በልሳን መናገሩን ባይገልጽም፣ ጳውሎስ በልሳኖች ብዙ ጊዜ ይጸልይ እንደነበር በኋላ ላይ መስክሯል (1ቆሮ.14፡18)። በልሳን መናገር የጀመረው በዚህ አጋጣሚ ሳይሆን አይቀርም።

---

[2] ከዓለም ጉባኤ እግዚአብሔር የእምነት መግለጫ፣ መግለጫ 9፡ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" (አባሪ 2 ተመልከት)።

በነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የጴንጤቆስጤያዊ ሊቃውንት በመንፈስ ቅዱስን መታጠቅ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በመንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ሲሞላ በልሳን መናገርን መጠባበቅ እንዳለበት አጥብቀው ይናገራሉ።

# "ሙሉውን ወንጌል" ማወጅ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የጴንጤቆስጤያዊ እውነትን የሚያስተዋውቅበት አንዱ ውጤታማ መንገድ "ሙሉ ወንጌልን" በትምህርቱ እና በስብከቱ ላይ ያለማቋረጥ በማጉላት ነው። ሙሉ ወንጌል የሚለው ቃል በቀደምት ጴንጤቆስጤያዊዊያን የተቀበሉትን ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሀሳብ ያመለክታል። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ "አራት እጥፍ ወንጌል" ወይም "አራት ማዕዘን ወንጌል" በመባልም ይታወቃል። ቀደምት የጴንጤቆስጤያዊ መሪዎች የቤተ ክርስቲያኑ ዋና መልእክት ነው ብለው የሚያምኑትን ለማጉላት እንዲረዳቸው ያሰናዱት ትምህርት ነው።

አራቱ የሙሉ ወንጌል ምሰሶዎች ኢየሱስ ያድናል፤ ኢየሱስ ይፈውሳል ፤ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃል ኢየሱስም እንደገና ይመጣል በሚሉ በአራት አጭር መግለጫዎች ይጠቃለላሉ። የጥንት ጴንጤቆስጤያዊዊያን እነዚህ አራት ቁልፍ አስተምህሮዎች በአብያተ ክርስቲያናት ችላ እንደተባሉ ተሰምቷቸው ነበር፣ እናም እነርሱ ትኩረት ሊሰጣቸው ፈለጉ። የሙሉ ወንጌል ትምህርት ታላቅ ጥንካሬ ኢየሱስን በስብከታችንና በትምህርታችን ማዕከል አድርጎ እንዲቆይ ማድረጉ ነው። በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ብዙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት መንገድ የሳቱ በሚመስሉበት በዚህ ወቅት፣ ወደ እነዚህ አራት አጽንዖቶች ቢመለሱ መልካም ነበር።

## ኢየሱስ ያድናል

የሙሉ ወንጌል የመጀመሪያው ምሰሶ የኢየሱስ እውነተኛ አዳኝነት ነው። እርሱ ብቻ የእግዚአብሔር ልጅ እና የዓለም አዳኝ ነው (ዮሐንስ 20፡31፤ 1ዮሐ.4፡14)። ጴንጤቆስጤያዊዊያን የሰው ልጅ የመዳን ብቸኛው ተስፋ በመስቀል ላይ በፈሰሰው የኢየሱስ ደም እንደሆነ በጽኑ ያምናሉ (ሐዋ. 4፡12፤ ቆላ. 1፡20)። እያንዳንዱ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሰዎች "ንስሐ ግቡና ምሥራቹን እመኑ!" በማለት ስለ ክርስቶስ መስቀል ሁል ጊዜ መስበክ ይጠበቅበታል (የማርቆስ ወንጌል 1:15)።

## ኢየሱስ ይፈውሳል

ሁለተኛው፤ የሙሉ ወንጌል ምሰሶ የኢየሱስ እውነተኛ ፈዋሽ መሆኑ ነው። ጴንጤቆስጤያዊዊያን የመለኮታዊ ፈውስ ተስፋ የወንጌል ማዕከል እንደሆነ ያምናሉ። ከኃጢአት መዳን ሆነ ከበሽታ መዳን በክርስቶስ የኃጢያት ማስተሰረያ ሞት ውስጥ አብሮ የተካተተ መንፈሳዊ በረከት እንደሆነ ያምናሉ። ስለዚህ ፈውስ የአማኞች ሁሉ በረከት ነው (ኢሳ. 53፡4-5፤ ማቴ. 8፡16-7)። በዚህ ምክንያት፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው" (ዕብ. 13፡8) በማለት በድፍረት ይናገራሉ። ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን እንዳዳነና እንደፈወሰ ሁሉ ዛሬም ሰዎችን ያድናል ይፈውሳልም።

## ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃል

ሦስተኛው የሙሉ ወንጌል ምሰሶ ኢየሱስ አማኞችን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃቸዋል፣ ለጠፉትም ምስክሮቹ እንዲሆኑ ኃይል ይሰጣቸዋል የሚል ነው (ሐዋ. 1፡8)። ጴንጤቆስጤያዊያን ሁሉም አማኞች በክርስቶስ ተስፋ ቃል መሰረት በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ መብት እንዳላቸው እና ተስፋውን በትጋት መፈለግ እንዳለባቸው በድፍረት ይናገራሉ (ቁ. 4-5፤ ሉቃ. 24፡49)።

ከላይ እንደተገለጸው፣ ይህ ልምምድ ከአዲስ ልደት የተለየ እና የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚሰጥ በልሳኖች መናገር የመጀመሪያው መሞላትን የሚረጋገጥ ተጨባጭ ማስረጃ ነው (ሐዋ. 2፡4)። እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አዘውትሮ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ላይ መስበክ አለበት። እንዲሞሉም ከሚያገለግሉት ሕዝብ ጋር መጸለይ አለበት።[3]

## ኢየሱስ እንደገና ይመጣል

የሙሉ ወንጌል አራተኛው ምሰሶ፤ ኢየሱስ ዳግም እንደሚመጣ ያለው እውነት ነው። ኢየሱስ ህዝቡን ከእርሱ ጋር ለመውሰድ ከሰማይ እንደሚመለስ ቃል ገብቶል (ዮሐ. 14፡3)። በመምጣቱ በክርስቶስ ያሉ ሙታን በቅድሚያ ይነሣሉ። ያን ጊዜ በሕይወት ያሉት ጌታን ለመገናኘት ከእነርሱ ጋር ይነጠቃሉ (1ተሰ. 4፡16-17፤ 1ቆሮ. 15፡51-52)። ይህ የተባረከ የቤተ ክርስቲያን ተስፋ ነው (ቲቶ 2፡13)።

ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው የተቀበሉ እና በታማኝነትና የታዛዥነት ህይወት የሚኖሩ፣ የክርስቶስን መምጣት መልእክት በደስታ ይቀበላሉ። ነገር ግን፣ ክርስቶስን የሚክዱ በፍርሃት ይቀበሉታል። የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ አማኞች ሁሉንም ኃጢአት እና ዓለማዊነትን እንዲተው እና ጌታን ቅድስና ህይወት እንዲከተሉ በመጥራት የክርስቶስን የመምጣት መልእክት ለሁሉም በድፍረት ማወጅ አለበት። ክርስቶስ በቅርቡ እንደሚመጣ መረዳታቸው የጴንጤቆስጤያዊ ክርስቲያኖች የጠፉ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እንዲሰሩ ያነሳሳቸዋል።

# የጴንጤቆስጤያዊ አገልግሎት

ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የጴንጤቆስጤ ህይወት እና አገልግሎት የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርትን የመጠበቅ ውጤት እንደሆነ ይረዳል። እርሱ ወይም እርሷ የሰው እምነት "የመንፈስን ኀይል በመግለጥ እንጂ፣ በሚያባብል የጥበብ ቃል" (1 ቆሮ. 2፡4-5) እንዳልሆነ ይረዳል። ትክክለኛ እምነት ወደ ትክክለኛው ልምድ ያመራል። ትክክለኛ እምነት እና ልምድ ደግሞ ወደ ትክክለኛው አሠራር ያመራል። ከጴንጤቆስጤያዊ እውነት ጋር ከመጣበቅ የሚገኙ አምስት የጴንጤቆስጤያዊ ሕይወት እና አገልግሎት ምሳሌዎችን እንመልከት፡-

## በመንፈስ የተሞላ ኑሮ

የአንድ ሰው የጴንጤቆስጤያዊ እውነትን የመቀበሉ ተፈጥሯዊ ውጤት በመንፈስ የተሞላ ኑሮ መኖሩ ነው። በመንፈስ እንዲሞሉ ከሕዝቦቻችሁ ጋር ስትሰብኩ እና ስትጸልዩ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወታቸው ውስጥ በኃይል መሥራት ይጀምራል። ለክርስቶስ ውጤታማ ሠራተኞች እንድትሆነ ይቀርጻችᎀል። ስለዚህም የስብከቱን እና የጸሎቱን ጊዜ ህዝቡ በመንፈስ ወደ ተሞላ የሕይወት ጉዞ እንዲያሳድገው ለመነትተሳት እድሉን በሚገባ መጠቀም አለብህ።[4]

## በመንፈስ የሚመራ ጸሎት

---

[3] በመንፈስ እንዲሞሉ ከአማኞች ጋር ስለመጸለይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 20ን ተመልከት፡ "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት።

[4] በዴንዚል አር ሚለር የተዘጋጀው ከመንፈስ ጋር መነዝ የሚለውን መጽሃፍ ከ www.decadeofpentecost.org በነፃ ማውረድ ይችላል።

የጴንጤቆስጤያዊ እውነትን በመድረክ መስበክ እና ማስተማር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈስ ወደተመራ ጸሎት ይመራል። አባሎቻችሁን በመንፈስ ወደተሞላው ሕይወት ስትመሩ እና በመንፈስ እንዴት መጸለይ እንደሚችሉ ስታስተምሯቸው የጸሎት ልማዶቻቸው ይቀየራል። በመንፈስ ምሪት ኃይለኛ ጸሎቶችን መጸለይ ይጀምራሉ። ጳውሎስ ስለ እንደዚህ ዓይነት ጸሎት በሮሜ 8፡26-27 ተናግሯል (1 ቆሮ. 14፡14-15፤ ኤፌ. 6፡18)።[5]

## ኃያል ምስክር

ኢየሱስ፣ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ ምስክሮቼም ትሆናላችሁ" (ሐዋ. 1፡8) በማለት ቃል ገብቷል። ሰዎች በመንፈስ ተሞልተው ወደ መከሩ ሲያመሩ፣ ከበፊቱ በበለጠ ትጋት እና ኃይል መመስከር ይጀምራሉ። አሁንም ህዝቡን በምሥክርነት፣ በቤተ ክርስቲያን ተከላ እና በሌሎች የስብከተ ወንጌል ተግባራት በመግፋት እድሉን በሚገባ መጠቀም አለብህ።

## ንፈሳዊ ስጦታዎች

የጴንጤቆስጤያዊ እውነት በታማኝነት በቤተ ክርስቲያን ማስተማር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መገለጥ ያበረታታል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በጉዳዩ ላይ በማስተማር ይህንን ተግባር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማበረታታት አለብህ።[6] መንፈስ ቅዱስ በአንተ እንዲሰራ በመፍቀድ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን አሠራር የበለጠ ማስተዋወቅ ትችላለህ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገለጥ ብዙ ሰዎች እንዲድኑ፣ እንዲፈወሱ እና በመንፈስ እንዲሞሉ ያደርጋል።

## ሚስዮናዊ ራዕይ

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ እውነትን በታማኝነት ለህዝብህ ስታስተምር፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተልእኮ ራዕይ ይፈጠራል። የቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ እና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት የማድረግ ሃላፊነት እንዳላቸው ሲረዱ፣ ልባቸው ለሰዎች ሁሉ መዳን በኃይል ይነሳሳል። ከዚያም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠንካራ የተልእኮ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ይህንን ራዕይ ማስተዋወቅ አለብህ።[7]

---

የዛሬዋ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያለችውን ቤተ ክርስቲያንን በመንፈስ ቅዱስ ለተቀባ አገልግሎት እና ልምምድ አብነት አድርጋ ትመለከታለች። የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ከቀዳማዊይቱ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ሚስዮናዊ ቅንዓት እና መነሳሳት እና በወንጌል የጠፉትን ለመድረስ የሚያስችል ጠንካራ ስልት ትወስዳለች። ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት

---

[5] የቤተ ክርስቲያን አባላትን እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ስለማስተማር፣ ምዕራፍ 8 "የጸሎት ቅድሚያ" የሚለውን ተመልከት።

[6] አባሪ 2፡ "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት።

[7] በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 40 "የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዎችን ፕሮግራም ማዳበር" የሚለውን ተመልከት።

ባሉት በእነዚህ የመጨረሻ ጊዜያት፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በእምነት፣ በልምድ እና በተግባር በእውነት ጴንጤቆስጤያዊ መሆን አለባቸው። ህዝባቸውንም ተመሳሳይ እንዲሆኑ ማስተማር አለባቸው

# ~ ምዕራፍ 11 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ ልምምድ እና ተግባርን ያበረታታል

አንድ ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በአንድ ወቅት "የጴንጤቆስጤያዊ ሰባኪ መሆን አንድ ነገር ነው፤ ስለ ጴንጤቆስጤያዊ መስበክ ደግሞ ሌላ ነገር ነው" ብሏል። ፓስተሩ ያነሳው ጠቃሚ ነጥብ አገልጋይ በተግባር ጴንጤቆስጤያዊ ሳይኾን በስም ጴንጤቆስጤያዊ ሊሆን እንደሚችል ነው። አንድ መጋቢ እራሱን ወይም እራሷን ከጴንጤቆስጤያዊ ቤተ እምነት ጋር አገለግላለሁ እያለ የጴንጤቆስጤያዊ ልምምድ እና ተግባርን ግን ችላ ሊል ይችላል። ነገር ግን፣ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሚመራው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጴንጤቆስጤያዊ ልምምድ እና ተግባርን በታማኝነት የሚያስተዋውቅ ነው።

በዚህ የመጨረሻ ምዕራፍ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የጴንጤቆስጤያዊ እውነትን የማበረታታት ግዴታውን መርምረናል። በዚህ ምእራፍ ውስጥ የጴንጤቆስጤያዊ ልምምድ እና ተግባርን የማሳደግ ግዴታውን እንነጋገራለን።

## የጴንጤቆስጤያዊ ልምምድን ያበረታታል

በዓለምአቀፍ ደረጃ ያሉ ጴንጤቆስጤያዊያን ፣ በእግዚአብሔር ማመን አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ብቻውን በቂ አይደለም የሚል እምነት አላቸው። ይህን ለማስረዳት ብዙውን ጊዜ የያዕቆብን ቃላት ይጠቅሳሉ፦ "አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠቀጣሉ" (ያዕቆብ 2፡19)።

ጴንጤቆስጤያዊያን፣ በእግዚአብሔር ከማመን ባሻገር፣ አንድ ሰው ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ሊኖረው እንደሚገባ ያስተምራሉ። ያ ግንኙነት የሚመሰረተው እና የሚጠበቀው ከእግዚአብሔር ጋር

ባለው የግል ልምምድ ነው። ከእነዚህ አስፈላጊ ልምምዶች ውስጥ ሦስቱ አዲስ ልደት፣ የመንፈስ ጥምቀት እና ከክርስቶስ ጋር በየዕለቱ መገናኘት ናቸው። እስቲ እነዚህን ሶስት ልምዶች እያንዳንዳቸውን አንተ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ክርስቶስ እንድትመራ በሾመህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ማስተዋወቅ እንዳለብህ እንመርምር።

## አዲስ ልደት

በመጀመሪያ፣ በስብከትህና በትምህርትህ ዳግመኛ መወለድ እንደሚያስፈልግ አጽንኦት ስጥ። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል በእውነት ዳግመኛ መወለዱን መጠየቅ አለብህ። በቤተ ክርስቲያን የሚገለገል ሁሉ ክርስቶስን እንደ አዳኙ ለመቀበል ጥያቄ መቀበሉን ማረጋገጥ አለብህ። ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ይህንኑ ነው። የሃይማኖት መሪውን "ዳግመኛ መወለድ አለብህ" (ዮሐንስ 3፡7) በማለት ሞገተው። ስታስተምር እና ስትሰብክ እነዚህ የኢየሱስ ቃላት በተደጋጋሚ በአንደበትህ ላይ መሆን አለባቸው።

ዳግመኛ መወለድ "ከእግዚአብሔር መወለድ" ነው (ዮሐንስ 1፡13፤ ዝከ. 3፡5፣ 8)። ሰው ከእግዚአብሔር የሚወለደው በትህትና ወደ ክርስቶስ ሲመጣ እና ጌታ እና አዳኝ መሆኑን ሲያውቅ፣ ከኃጢአት ንስሃ ሲገባ እና ሙሉ በሙሉ ለኃጢአት ይቅርታ እና ለመንጻት በእርሱ ሲታመን ነው። በዚያን ጊዜ ሕይወትን የሚቀይር መንፈሳዊ ለውጥ ይከሰታል። ክርስቶስ ወደ ሕይወታቸው ይገባል፣ መንፈስ ቅዱስም ከውስጥ ወደ ውጭ ይለውጣቸዋል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "17 ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል" ብሏል (2 ቆሮ. 5፡17፣ ህዳግ)።

## የመንፈስ ጥምቀት

ሰዎችን ወደ አዲስ ልደት ከመምራት በተጨማሪ፣ እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፤ ክርስቶስን እንደ አዳኝ የተቀበሉ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ መጎትጎት አለብህ። ይህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ነበር። በኢየሩሳሌም ያሉ ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች እንደዳኑ በሰሙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ እንዲጸልዩ ጴጥሮስና ዮሐንስን ላኩላቸው (ሐዋ. 8፡14-17)። ከዓመታት በኋላ፣ ጳውሎስ ኤፌሶን በደረሰ ጊዜ፣ በዚያ ለነበሩት ደቀ መዛሙርት የጠየቃቸው የመጀመሪያ ጥያቄ፣ "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" የሚል ነበር። (19:2) ሐዋርያው መንፈስን እንዳልተቀበሉ ሲያውቅ ወዲያው እጁን ጫነባቸው እና "መንፈስ ቅዱስም ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ ትንቢትም ተናገሩ" (ቁ. 6)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፤ የሐዋርያትን ምሳሌ በመከተል እያንዳንዱ አዲስ ክርስቲያን ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቅ ጠንክረህ መሥራት አለብህ። በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስን የሚቀበል ሁሉ እግዚአብሔር አማኞችን በመንፈስ ቅዱስ ለምን እንደሚያጠምቃቸው ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አለብህ። መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት የክርስቶስ ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ ነው (ሐዋ. 1፡8)። ስለዚህ በመንፈስ የተጠመቁ አዳዲስ አማኞች ስለ ክርስቶስን ለቤተሰቦቻቸው እና ለጓደኞቻቸው እንዲመሰክሩ ማበረታታት ያስፈልጋል።

በእውነት በመንፈስ የታጠቀ ሚስዮናዊ ቤተ ክርስቲያን ለመፍጠር፣ እያንዳንዱ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንደሚያስፈልገው ብዙ ጊዜ መስበክ እና ማስተማር ያስፈልጋል። ስለ መንፈስ ጥምቀት የምታስተምረው ትምህርት ሦስት ጥያቄዎችን በግልፅ ሊመልስ ይገባል፡ (1) በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

ምንድን ነው? (2) አማኝ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ያለበት ለምንድን ነው? እና (3) ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዴት ሊቀበል ይችላል?[1]

በተጨማሪም፤ ለቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠሙ ወይም በተደጋጋሚ እንዲሞሉ እድሎችን መስጠት ያስፈልግሃል። ይህም ማለት አማኞች እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ እና መንፈስ ቅዱስን እንዲጠይቁት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ቦታ መስጠት ያስፈልግሃል (ሉቃስ 11፡13)። በተጨማሪም፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በነጻነት የሚያስተናግዱበትን ድባብ በጥንቃቄ ማዳበር ያስፈልግሃል። እንዲህ ያለው ድባብ የእግዚአብሔርን መገኘት እና በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ውስጥ የሚጠብቀውን እምነት ይጨምራል።[2]

## የዕለት ተዕለት ግንኙነት

በመጨረሻም፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ከክርስቶስ ጋር በዕለት ተዕለት ኅብረት እየኖሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብህ። ኢየሱስ ይህንን ልምምድ በክርስቶስ መኖር ወይም በእኔ መኖር ሲል ጠቅሷታል (ዮሐንስ 15፡4-7)። ጳውሎስ "በመንፈስ መመላለስ" ብሎ ጠርቶታል (ገላ. 5፡25)። ስለዚህ ዳግመኛ መወለድ ወይም በመንፈስ መሞላት ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ለሕዝቡ ማስተማር አለብህ። ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከክርስቶስ ጋር የማይቋረጥ ኅብረት ለመኖር ራሳቸውን መስጠት አለባቸው (ዮሐንስ 14፡16-18፣ 23፤ 1 ዮሐንስ 1፡3)።

በቃል እና በምሳሌ የእግዚአብሔርን ህዝብ እንዴት የሚከተሉትን ማድረግ እንደሚችሉ ማስተማር አለብህ፡-

- "በመንፈስ መመላለስ" (ገላ. 5፡25)።
- "እንደ መንፈስ ፈቃድ መኖር" (ሮሜ. 8፡5-6) "ልባቸውን በመንፈስ ፍላጎት ላይ" በማድረግ ነው።
- የእግዚአብሔር መንፈስ ጥበቃ፣ እርዳታ እና አጽናኝነት ከእነርሱ ጋር እንዲሆ መጋበዝ (ዮሐንስ 14፡16)።
- "በሁሉ ዐይነት ጸሎትና ልመና፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ" (ኤፌ. 6፡18፤ ሮሜ. 8፡26፤ ይሁዳ 20)።
- ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲያሰላስሉ አእምሮአቸውን እንዲያበራና ልባቸውን እንዲያነቃቃ በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ (ዮሐ. 16፡13)።
- በሕይወታቸው መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት (ገላ. 5፡22-23)

---

[1] በዚህ ርዕስ ላይ ለቀረበው የስብከት *ማብራሪያ፣ የጴንጤቆስጤን ማወጅ፡ 100 የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተመለከቱ የሥብከት ማውጫዎች* የሚለውን መጽሐፍ ተመልከት፤ የስብከት 2፡ "በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" የሚለውን መጽሐፍ ተመልከት። ይህ መጽሐፍ በኢ-መጽሐፍ ቅርጸት (PDF) በ www.DecadeofPentecost.org ይገኛል።

[2] አማኞች መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ስለማዘጋጀት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ለተልዕኮ ማደራጀት የሚለውን መጽሐፍ፣ ምዕራፍ 7 ይመልከቱ፡ "በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን እንዴት መስበክ እንደሚቻል" የሚለውን መጽሐፍ ተመልከት። በነጻ ለማውረድ በ www.DecadeofPentecost.org ይገኛል።

እነዚህን ግቦች ለማሳካት ከቅዱሳት መጻሕፍት መንፈስ ስለ ታጠቀ ሕይወት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትጋት ማስተማር ያስፈልጋል። እንዲሁም እነዚህን ልምዶች በራስህ ህይወት እና አገልግሎት ውስጥ ሞዴል ማድረግ ያስፈልጋል።

# የጴንጤቆስጤያዊ ተግባርን ያበረታታል

የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ ጴንጤቆስጤያዊ ልምምድ ከመምራት ጋር ተያይዞ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ወደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ተግባር ጉባኤውን መምራት አለብህ። ይህንን ለማድረግ፣ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ አስር ዋና የጴንጤቆስጤያዊ ተግባራትን ለማስተዋወቅ መትጋት አለብህ፡-

## በመንፈስ ቅዱስ የተመራ አዋጅ

በመጀመሪያ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የመንፈስ ቅዱስ የሚመራ የእግዚአብሔር ቃል አወጃን መለማድ አለብህ። ይህን በምታደርግበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ደቀ መዝሙር የእግዚአብሔር ህላዌ ይገናኛል፣ ይህ ደግሞ እርሱ ወይም እርሷ በላቀ ኃይል እና ውጤታማነት እንዲያገለግሉ ያስችላቸዋል። ቅብዓቱን ስትፈልግ የኢየሱስንና የሐዋርያትን ምሳሌ ትከተላለህ። ኢየሱስ ስለ ራሱ ስብከት ሲናገር፣ "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና" ብሏል (ሉቃስ 4፡18)። ሐዋርያትም በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ታግዘው ሰብከዋል (ሐዋ. 2፡14-18፤ 4፡8፤ 13፡8-12)።

የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ የመንፈስን ቅባት በአንተ ላይ እንደሚሆን እርግጠኛ መሆን ትችላለህ። ከዚያም እርሱ ሲመጣ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በድፍረት በማወጅ በእምነት ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል (ሐዋ. 4፡31)። ኢየሱስ የተቀባውን የቃሉን አዋጅ (የወንጌልን ሥብከት) በተአምራት እንደሚያረጋግጥ ቃል ገብቷል (ማር. 16፡15-18)።

## ለታመሙ መጸለይ

ሁለተኛ፤ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመለኮታዊ ፈውስ እግዚአብሔርን በማመን ለታመሙ እና ለተጎዱ ሰዎች ለመጸለይ እራስህን ማለማመድ አለብህ። ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ሲል ላካቸው:- "በሽተኞችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ" (ማቴ. 10:8) ያዕቆብ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን "ከእናንተ መካከል የታመመ ሰው አለ? የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ይጥራ፤ እነርሱም በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። 15 በእምነት የቀረበ ጸሎት የታመመውን ሰው ይፈውሰዋል፤ ጌታም ያስነሣዋል፤" (ያዕቆብ 5፡14-15)።[3]

## በተልእኮ መሳተፍ

ሦስተኛ፤ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የእግዚአብሔር ተልእኮ በቤተ ክርስቲያንህ ቋሚ አጀንዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ። ለእግዚአብሔር ተልእኮ መቅናት የእውነተኛ ጴንጤቆስጤያዊነት መሰረቱ ነው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱን "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ

[3] በዚህ ርዕስ ላይ የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት፣የአፍሪካ ተስፋ ተከታታይ የመማሪያ መጽሐፍን፣ የኃይል አገልግሎት፡ በመንፈስ ኃይል እንዴት ማገልገል እንደሚቻል ምዕራፍ 11፡ "የታመሙትን እንዴት መፈወስ እንደሚቻል" ተመልከት።

ትሆናላችሁ" ብሏል 1፡8)። ቤተ ክርስቲያን ተልእኮን እየሸሸች ራሷን ጴንጤቆስጤያዊ ብላ መጥራት አትችልም። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ንቁ የሚስዮን ፕሮግራም የማቋቋም ግዴታ አለብህ።

ይህንን ለማድረግ፣ የእግዚአብሔርን ተልእኮ አዘውትረህ መስበክ እና ማስተማር ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ተልእኮ በምድር ላይ ያሉትን ቋንቋዎች፣ ነገዶች እና ህዝቦች ሁሉ ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት መቤዠት እና መጥራት ነው (ማቴ. 24፡14፤ ራዕ. 5:9)። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የእግዚአብርን ተልእኮ በመፈጸም ላይ የመሳተፍ ግዴታውን መረዳቱን ማረጋገጥ አለብህ።

እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኑ አባላት በተልእኮዎ ውስጥ በግል እንዲሳተፉ እድሎችን መፍጠር ያስፈጋል። ይህንንም ህዝቡን ለአጭር ጊዜ በሚስዮን ተኮር ጉዞዎች፣ በኮንፈራንሶች፣ በጎዳና ላይ ወንጌልን ስብከት እና ሌሎች ተመሳሳይ መድረኮችን በማዘጋጀት ማከናወን ይችላሉ። በተጨማሪም፣ አባላት ለቤተ ክርስቲያኑ ተልእኮ መርሃ ግብር የገንዘብ ቃል ኪዳናቸውን እንዲያደርጉ የሚጠየቁበት ተደጋጋሚ የተልእኮ ግንዛቤ ዝግጅቶችን አቅዶ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን በገንዘባቸው እና በጸሎታቸውን የምትደግፋቸው ሚስዮናውያን ሊኖሩት ይገባል።[4]

## የእግዚአብሔር ጥሪ

አራተኛ፤ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፤ የእግዚአብሔርን የአገልግሎት ጥሪ አፅንዖት መስጠት አለብህ። የእግዚአብሔር ጥሪ ሰዎችን ወደ ራሱ እና ወደ ዓላማው መምረጡ እና መጥራቱ ነው። ኢየሱስ ራሱ ከእግዚአብሔር የተላከው ነው። እርሱ ዛሬም እየጠራ ወደ መከሩ ይልካል (ማቴ. 4፡19፤ ዮሐ. 20፡ 21)። ለደቀ መዛሙርቱ " እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ እንድትሄዱና ፍሬ እንድታፈሩ ፍሬያችሁም እንዲኖር ሾምኋችሁ" ብሏቸዋል (ዮሐ. 15፡16)።

የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን በቀጣይነት እንድትስፋፋ ከተፈለገ (እግዚአብሔር እንዲሠራ እንዳሰበ) በየጊዜው አዳዲስ የቤተ ክርስቲያን ተወካዮች፣ መጋቢያን፣ ሚስዮናውያን፣ ወንጌላውያን እና ሌሎች የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋዮች ሊኖራት ይገባል። እነዚህ ሰዎች ከጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያናችን መምጣት አለባቸው። ስለዚህ፣ የምታገለግለው ሕዝብ በሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ጥሪ እንዲሰሙ ማበረታታት አለብህ። እግዚአብሔር ሲናገርም እንደ ነቢዩ፣ "እነሆኝ፣ ላከኝ!" ብለው መመለስ አለባቸው (ኢሳ. 6:8)።[5]

## መንፈሳዊ ጦርነት

አምስተኛ፤ በአፍሪካ የምትገኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደመሆንህ ፣ በመንፈሳዊ ጦርነት ለመሳተፍ ዝግጁ መሆን አለብህ። የአጋንንት ኃይሎች እራሳቸውን በሚገለጡበት ጊዜ ለመጋፈጥ እና

---

[4] በዚህ ርዕስ ላይ የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 40፡ "የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዎችን ፕሮግራም" ማዳበር ተመልከት።

[5] ስለ መለኮታዊ የአገልግሎት ጥሪ ተጨማሪ ለማግኘት ምዕራፍ 1ን "ልምድ ያለው ሰው" የሚለውን ተመልከት። ክርስቶስን ለአሕዛብ ማወጅ፡ 100 የስብከት ዝርዝሮች በመንፈስ የታጠቀ ተልእኮዎ ክፍል 5፡ "የእግዚአብሔር ጥሪ" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔርን ጥሪ በተመለከተ አሥራ ሁለት የስብከት ዝርዝሮችን ይገኛሉ። እነዚህ ዝርዝሮች በኢ-ብክ ቅርጽ በwww.DecadeofPentecost.org ይገኛሉ።

ለማሸነፍ ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆን አለብህ። ኢየሱስና ሐዋርያቱ ያደረጉት ይህንኑ ነው (ማርቆስ 1፡21-28፤ የሐዋርያት ሥራ 16፡16-18)። ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ ጉባኤውን ማዘጋጀት አለብህ።[6]

## ደማቅ አምልኮ

ስድስተኛ፤ ቤተ ክርስቲያንህ ንቁ፣ በመንፈስ የሚራ አምልኮን ስለመለማዱዋ እርግጠኛ መሆን አለብህ። እንዲህ ዓይነቱ አምልኮ የጴንጤቆስጤያዊ መንፈሳዊነት መለያ ነው። ጴንጤቆስጤያዊያን በነጻ እና ለመንፈስ ቅዱስ ስፍራ በሚሰጥ የአምልኮ ይታወቃሉ። አገልግሎታቸው በጋለ ስሜት መዘመር፣ ማጨብጨብ፣ ማሸብሸብ እና እጅ ማንሳትን ያካታል። ሆኖም፣ የቤተ ክርስቲያንህ አምልኮ በጋለ ስሜት የተሞላ መሆኑ በቂ አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ መገኘት መሞላት አለበት። ደግሞም እውነተኛ መሆን አለበት። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት ይገባል" (ዮሐንስ 4፡24) በማለት አስተምሯል። ጳውሎስ አክሎም "የጌታ መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ" ብሏል(2ቆሮ. 3፡17)።

በአምልኮ ጊዜ፣ ሁሉም ሰው ትኩረቱን በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ እንዲያተኩር ማበረታታት አለብህ። ጉባኤው የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲንቀሳቀስ ልባቸውን እንዲከፍቱ ልታስተምራቸው ይገባል።[7]

## የግል ምስክርነት

ሰባተኛ፤ የቤተ ክርስቲያንህ አባላት ምስክርነታቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ማበረታታት አለብህ። የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ያደረገውን ነገር ለማካፈል በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ መሆን አለባቸው (1 ጴጥ. 3፡15)። መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር የተቤዣቸው፣ከጠላት እጅ የታደጋቸው ይህን ይበሉ፤" (መዝ. 107፡2) በማለት ይመክራል።

ምስክርነት መስጠት የክርስቶስ ምስክር የመሆን መገለጫ ነው። አማኞች ለጠፉት ወንጌልን የሚሰብኩበት ቀላል ግን ኃይለኛ መንገድ ነው። ስለዚህ ይህንን ተግባር በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ማበረታታት አለብህ። የእግዚአብሔር ሕዝብ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ውስጥ እንዴት እንደሰራ ምስክርነቶችን እንዲካፈሉ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ቦታ መስጠት አለብህ።

## ጸጋ ሥጦታዎች

ስምንተኛ፤ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ የመንፈስ መንቀሳቀስን ለመንፈሳዊ ስጦታዎች መገለጥ መትጋት አለብህ። ይህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ልማድ ነበር፣ ዛሬም ቢሆን የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስትያን ልምምድ መሆን አለበት (ለምሳሌ፣ ሐዋ. 11፡ 28-30፤ 13፡1-2፤ 21፡10-14)። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10፣ ጳውሎስ ስለ ዘጠኝ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተናግሯል።

8 ለአንዱ በመንፈስ የጥበብን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤9ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው በአንዱ

[6] በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ ግንዛቤ ለማግኘት ምዕራፍ 20ን ተመልከት:- "በመንፈሳዊ ጦርነት መካፈል። በተጨማሪም የአፍሪካ ተስፋተከታታይ መጽሐፍ፣ የኃይል አገልግሎት፡ በመንፈስ ኃይል እንዴት ማገልገል እንደሚቻል፣ ምዕራፍ 12፡ "አጋንንትን ማስወጣት" የሚለውን ተመልከት።

[7][7] በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 18 ፡ "ቤተ ክርስቲያንን በአምልኮ መምራት"ን ተመልከት።

መንፈስ የመፈወስ ስጦታዎች ይሰጠዋል፤10 ለአንዱ ታምራትን የማድረግ፣ ለሌላው ትንቢትን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ መናፍስትን የመለየት፣ ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጐም ስጦታ ይሰጠዋል።[8]

ህዝቡን በእነዚህ ስጦታዎች እንዲያገለግሉ ስታስተምር ቤተ ክርስቲያን ትታነጻለች፣እግዚአብሔር ይከብራል፣ መንግስቱም ይሰፋል።

ነገር ግን የመንፈሳዊ ስጦታዎች የግድ የሚከሰቱ እንዳልሆኑ ማወቅ አለብህ። ስጦታዎቹን መመኘት እና መበረታታት ይፈልጋሉ (1ቆሮ. 12፡31፤ 14፡1)። ስለዚህ በራስህ ህይወት ውስጥ የመንፈሳዊ ስጦታዎችን መገለጥ መመኘት አለብህ፣ በሌሎች ህይወት ውስጥም ማነሳሳት አለብህ። በጉዳዩ ላይ በማስተማር እና በመስበክ ይህንን ማድረግ ትችላለህ። እንዲሁም ትክክለኛውን የጸጋ ስጦታ አሠራር ምሳሌ መተው አለብህ። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ለጸጋ ስጦታዎች ቦታ በመስጠት (14፡26) እና አላግባብ አጠቃቀምን እርምት በመስጠት የመንፈሳዊ ስጦታዎችን መገለጥ ማበረታታት ይገባሃል (14፡39-40)።[9]

## የምልጃ ጸሎት

ዘጠነኛ፣ ቤተ ክርስቲያንህን ወደ ብርቱ ምልጃ ጸሎት መምራት አለብህ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንዳለችው ቤተ ክርስቲያን፣ ዛሬ በአፍሪካ የምትገኘው የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ቁርጠኛ መሆን አለባት (ሐዋ. 1፡14፤ 4፡23-32፤ 12፡5፤ 13፡2)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው እንዳስተማራቸው ሁሉ አንተም ለሕዝብህ ተመሳሳይ ነገር ማስተማር አለብህ (ሉቃስ 11፡1-13)። በጸሎት ላይ ብዙ ጊዜ በመስበክ እና በማስተማር እና በቤተ ክርስቲያኑ ፊት የጸሎትን የአኗኗር ዘይቤን በታማኝነት ተምሳሌት በመሆን ይህንን ማድረግ ትችላለህ። ህዝቡ ፓስተራቸውን ሲጸልይ ሲመለከቱ፣ እነርሱም እንዲጸልዩ መበረታታቸው ግልጽ ነው (ሉቃስ 11፡1፤ ዘጸ. 33፡10)።[10]

## ቅዱስ ኑሮ

በመጨረሻም፤ እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቅዱስ እና እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ህይወት እንዲኖሩ ማሳሰብ አለብህ (1ኛ ዮሐንስ 2፡6)። ቅዱስ ኑሮ የቅዱሳት መጻሕፍት ግዴታ እና የጴንጤቆስጤያዊ አማኞች ሁለንተናዊ ልምምድ ነው (1ጴጥ. 1፡16)። ክርስቲያን የሚለው መጠሪያ እንደሚያመለክተው፣ የክርስቶስ ተከታዮች እርሱን ለመምሰል መጣር አለባቸው። የሚወክሉት አምላክ ቅዱስ ነውና ቅዱሳን መሆን አለባቸው። ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖችን " በጠማማና በክፉ ትውልድ መካከል ንጹሓንና ያለ ነቀፋ፣ ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች ሆናችሁ፣ እንደ ከዋክብት በዓለም ሁሉ ታበሩ ዘንድ " ሲል አሳስቧቸዋል (ፊሊ. 2፡15)።

ስለዚህ ለሕዝቦቻችሁ ክርስቶስን መስለው እንዴት እንደሚኖሩ ማሳየት አለባችሁ። ይህንን ለማድረግ፣ ክርስቲያኖች ቅዱስ እና ንጹህ ህይወት እንዲኖሩ በሚያሳስብ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ብዙ ጊዜ ማስተማር እና መስበክ ያስፈልጋል። እንደዚህ አይነት ህይወት ምን እንደሚመስል ለሰዎች የበለጠ በተምሳሌነት ራስህን ማሳየት አለብህ። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ያሉ አማኞችን እንዲህ ሲል አሳስቧቸዋል፣ "በእናንተ በምታምኑት መካከል ሳለን እንዴት በቅድስና፣ በጽድቅ እንዲሁም ያለ ነቀፋ ሆነን እንደኖርን እናንተም እግዚአብሔርም ምስክሮች ናችሁ" (1 ተሰ. 2፡10)። በተጨማሪም

---

[8] አባሪ 2፡ "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት።

[9] በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 21 "በመንፈስ ኃይል ማገልገል"ን ተመልከት፡ ።

[10] በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 8 "የጸሎት ቀዳሚነት"ን ተመልከት።

አማኞችን “እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል እናንተም የእኔን ተከተሉ” በማለት መክሯቸዋል (፩ቆሮ. ፲፩፡፩)። ለቤተ ክርስቲያንህ አባላት ተመሳሳይ ቃላት መናገር መቻል አለብህ።

---

እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርት ወደ ሃይማኖታዊ ልማድ በፍጹም ሊወርድ አይገባም፣ ምንም እንኳን እምነቶች ምንም ያህል እውነት ቢኖራቸውም። ጴንጤቆስጤያዊነት በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍና በሐዋርያት ጹሑፎች ውስጥ እንደተገለጸው በመጀመሪያው መቶ ዘመን ከነበሩት አማኞች ልምድና አሠራር ምሳሌን ለመከተል የሚሻ የሕይወት መንገድ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የራሱን ወይም የእርሷን ቤተ ክርስትያን ወደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ልምምድ እና ተግባር ለመምራት አላማ ማድረግ አለበት።

# ~ ምዕራፍ 12 ~

# የጴንቆስጤ ትውፊቶችን ማክበር

ሌይላ ማኪኒ በአፍሪካ ውስጥ የመጀመሪያዋ የጴንጤቆስጤያዊ የልጆች ሚስዮናዊት ነበረች። ከ1906 እስከ 1908 በሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ፣ ዩኤስኤ በአዙሳ ጎዳና በነበረው የመንፈስ ቅዱስ ፍሰት መጀመሪያ ላይ በመንፈስ ከተሞሉት አንዷ ነበረች። መነቃቃቱ በሚሲዮናዊነት ቅንዐት የተሞላ ነበር ስለሆነም ሌይላ፣ ከአክስቷ ጁሊያ ሃቺንስ እና ሌሎች ጋር ወንጌልን ለመስበክ ወደ አፍሪካ ለመሄድ ተነሳሳች። ሌይላ በተልእኮው ሐዋርያዊ እምነት ጋዜጣ ላይ እንዲህ ስትል ጽፋለች፣ “ወደ አፍሪካ ሲመራኝ ለማመን ፈቃደኛ ነኝ። ጌታ ወደዚያ እንድሄድ እንደሚፈልግ አውቃለሁ። ለህዝቡ መመስከር እና ልጆችን ስለተባረከው ጌታ ማስተማር እና ለጌታ መስራት እፈልጋለሁ። ስለ እርሱ ስል የምወዳቸውን ሁሉ ለመተው ፈቃደኛ ነኝ። "የሌይላ ማኪኒ ታሪክ በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ መነቃቃት ዙሪያ ከሚሊዮኖች አንዱ ነው።

በአፍሪካ ያለ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የጴንጤቆስጤያዊ መልእክት ወደ አህጉሩ እንዴት እንደመጣ ሊረዳ እና ሊያደንቅ ያስፈልገዋል። አንድ አፍሪካዊ መጋቢ በአንድ ወቅት “ከየት እንደመጣን ካላወቅን ማን እንደሆንን ወይም ወዴት እንደምንሄድ አናውቅም” በማለት ተናግሯል። ያለፈው ካላወቅን ሽራ እንደሌለው ጀልባ እንሆናለን። ያለ ግልጽ አቅጣጫ ወይም ያለ ዓላማ የመንዳት አደጋን እንፈጥራለን። ነገር ግን፣ ከየት እንደመጣን እና ለምን እዚህ እንዳለን ካወቅን በልበ ሙሉነት ወደፊት መራመድ እንችላለን።

ይህ ምዕራፍ በአፍሪካ ስለ ጴንጤቆስጤያዊነት አጀማመር በርካታ ጠቃሚ ጥያቄዎችን ይመልሳል። የዘመናዊው የጴንጤቆስጤያዊ እንቅስቃሴ መነሻዎች ምንድን ናቸው? ወደ አፍሪካ መቼ እና እንዴት መጣ? ጴንጤቆስጤያዊ በአህጉሪቱ እንዴት ተስፋፋ? በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላይ ምን ፈተናዎች ሊጋጥሟታል? የአፍሪካ ጴንጤቆስጤያዊነት የወደፊት ዕጣ ፈንታስ ምን ይመስላል?

# እንቅስቃሴው ጅማሮ

በታኅሣሥ 1900 መገባደጃ ላይ ቻርለስ ፎክስ ፓርሃም በቶፔካ፣ ካንሳስ፣ ዩናይትድ ስቴትስ በሚገኝ አንድ ትንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎቹ የምርምር ጹሑፍ እንዲያቀርቡ ጠየቃቸው። የምርምር ሥራው የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት "የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ" ለማግኘት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲመረምሩ ነበር። ጥናቱ ከተጠናከረ በኋላ ተማሪዎቹ ውጤታቸውን ለፓርሃም አቀረቡ። የደረሱበት ድምዳሜ የመንፈስ ጥምቀት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ በልሳኖች መናገር ነው የሚል ነበር።

ከዚያም ለብዙ ቀናት ተከታታይ የጸሎት ስብሰባ ጀመሩ። ብዙም ሳይቆይ ጥር 1 ቀን 1901 ከእኩለ ሌሊት በኋላ መንፈስ ቅዱስ አግነስ ኦዝማን በተባለች ሴት ላይ በኃይል መጣ። መንፈስ ቅዱስ እንደሰጣት በተአምራት በልሳኖች መናገር ጀመረች። በቀናት ውስጥ፣ ፓርሃምን ጨምሮ ሌሎች ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፣ ይህም በልሳኖች በመናገር የተረጋገጠ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላታቸው የተነሣ፣ ፓርሃምና ተማሪዎቹ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንዳሉት አማኞች በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ወንጌልን መስበክ ጀመሩ። ልባቸው በታላቅ ሚስዮናዊ ቅንዓት ተሞላ። ፓርሃም እግዚአብሔር መንፈሱን የሚያፈስሰው በቅርቡ ከመመለሱ በፊት ስለ ክርስቶስ ምሥራች ለአሕዛብ እንድትደርስ ለቤተ ክርስቲያን ኃይል ለመስጠት እንደሆነ ያምን ነበር።

እ.ኤ.አ. በ1905 ፓርሃም ትምህርት ቤቱን ወደ ሂዩስተን፣ ቴክሳስ፣ ዩኤስኤ አዛወረው፣ በዚያም ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማስተማር ቀጠለ። ብዙም ሳይቆይ ሉሲ ፋሮው እንቅስቃሴውን ተቀላቀለች። ከዚያም ፓርሃምን ከዊልያም ጄ. ሲሞር አፍሪካዊ አሜሪካዊ የቅድስና ሰባኪ ጋር አስተዋወቀችው። ሲይሞር የፓርሃምን ትምህርት ካደመጠ በኃላ፣ እርሱም ደግሞ የጴንጤቆስጤያዊ መልእክትን ተቀበለ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሲይሞር በሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ ካለች ትንሽ የቅድስና ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዲሆን ግብዣ ቀረበለት። ሲይሞር ግብዣውን ተቀብሎ ወደ ሎስ አንጀለስ ተጓዘ። በቤተ ክርስቲያን ባደረገው የመጀመርያ ስብከቱ በልሳን የመናገር ማስረጃ ስለ ሚረጋገጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነበር። የቤተክርስቲያቱ መጋቢ ጁሊያ ሃቺንስ መልእክቱን ውድቅ አድርጋ ሲይሞርን ከተልእኮው ውጭ አደረገችው።

ከዚያም ሴይሞር በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቤት የጴንጤቆስጤያዊ መልእክት መስበክ ጀመረ። ሲሰብክ እና ህዝቡ ሲጸልይ ብዙዎች በመንፈስ ተሞሉ። ህዝቡ በጣም በመብዛቱ በአዙዛ ጎዳና ላይ ያለ አሮጌ የቤተ ክርስቲያን ህንፃ ለመግዛት ተገደዱ። እግዚአብሔር መንፈሱን ማፍሰሱን ቀጠለ እና በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከ1906 እስከ 1908 በሺዎች የሚቆጠሩ ከዓለም ዙሪያ መጥተው በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። በዓለ ሃምሳ መጣ የሚለውን መልእክት ይዘው ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

የጴንጤቆስጤያዊ ሚስዮናውያን ከአዙሳ ጎዳና ወደ ቻይና፣ ህንድ፣ ጃፓን፣ ግብፅ፣ ላይቤሪያ፣ አንጎላ እና ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ ከ25 በላይ አገሮችን በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ወጡ። ኃያሉ የአዙሳ ጎዳና መነቃቃት ጴንጤቆስጤያዊያን ከማንም በላይ በዓለም ዙሪያ እንዲስፋፉ አድርጓል። ዛሬ ጉባኤ

እግዚአብሔርን ጨምሮ ቢያንስ 26 የተለያዩ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ እምነቶች መነሻቸውን በአዙሳ ጎዳና ላይ ያደርጋሉ።[1]

በእነዚያ ዓመታት እግዚአብሔር መንፈሱን በዓለም ዙሪያ ባሉ ሌሎች ቦታዎች ያፈሰሰ ነበር። ሌሎች የጴንጤቆስጤያዊ መፍሰስ ማዕከላት ዌልስ (1904)፣ ሕንድ (1905)፣ እንግሊዝ (1907)፣ ኮሪያ (1907)፣ ቺሊ (1909) እና ሌሎች ቦታዎች ነበሩ። እግዚአብሔር ለነቢዩ ኢዩኤል የገባውን ቃል እየፈፀመ ነበር፡- "በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር፡— መንፈሴን በሰው ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ ይላል" (ሐዋ. 2፡17፤ ኢዩኤል 2፡28)።

# ጴንጤቆስጤ ወደ አፍሪካ ደረሰ

አሁን የጴንጤቆስጤያዊ መልእክት ወደ አፍሪካ እንዴት እንደመጣ እና በአህጉሪቱ እንዴት እንደተስፋፋ እንመልከት

## ጴንጤቆስጤ ወደ አፍሪካ መምጣት

የመጀመሪያዎቹ የጴንጤቆስጤያዊ ሚስዮናውያን ከአሜሪካ ወደ አፍሪካ የመጡት በቀጥታ ከአዙሳ ጎዳና ተልከው ነው። በ1907 ላይቤሪያ ደረሱ። ቡድናቸው ሉሲ ፋሮው፣ ጄ ደብሊው እና ጁሊያ ሃቺንስ፣ የእህታቸው ልጃቸው ሌይላ ማኪኒ እና በኋላ በዚያው ዓመት የመጣው ኤድዋርድ ማኩሌይን ያጠቃልላል። በአጠቃላይ ወደ ደርዘን የሚጠጉ አፍሪካውያን አሜሪካውያን ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት በዚያ ዓመት በሁለት ቡድን ከአዙዛ ወደ ላይቤሪያ ተጓዙ። በሳምንታት ውስጥ ሰባቱ በወባ ወይም በጥቁር ውሃ ትኩሳት ሞቱ። ቢሆንም ብዙ ላይቤሪያውያን ወደ ጌታ መጥተው በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ አይተዋል። በአፍሪካ የመጀመሪያው ቋሚ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን በ1907 በሞንሮቪያ ተተከለ። ከአዙሳ የመጡ ሚስዮናውያንም ወደ ደቡብ አፍሪካ እና አንጎላም ተጉዘዋል።

የጴንጤቆስጤያዊ መልእክት ለማሰራጨት እግዚአብሔር አፍሪካውያን አሜሪካዊያንን ተጠቅሟል። ከእነዚህም የደቡብ አፍሪካው ኤልያስ ሌዋባ እና የላይቤሪያው ዊልያም ዋዴ ሃሪስ ሁለት ደስ የሚሉ ታሪኮች ናቸው። እነዚህ ሰዎች በደቡብ እና በምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ባሉ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ላይ ተጽእኖ ያሳደረ እንቅስቃሴዎች በመጀመር በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ረድተዋል።

ኤልያስ ሌትዋባ (1870-1959) በደቡብ አፍሪካ ታሪክ ውስጥ በጣም ተደማጭነት ያለው አፍሪካዊ የጴንጤቆስጤያዊ ሰባኪ ተብሎ ይጠራል። በ1870 አካባቢ፣ ኤልያስ ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ እናቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ራዕይ አየች። መንፈስ ቅዱስ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል እግዚአብሔር አንድ ቀን ልጇን እንደ ዕቃው እንደሚጠይቀው ነገራት። ሌትዋባ እግዚአብሔርን ለማወቅ እና እርሱ እንዲጠቀምበት በመራብ አደገ።

በ1908፣ ወደ ደቡብ አፍሪካ ከመምጣቱ በፊት በቻርለስ ፓርሃም አገልግሎት መንፈስ ቅዱስን የተቀበለውን አሜሪካዊ ሚስዮናዊ ጆን ጂ ሌክን አገኘ። ሌክ በሎስ አንጀለስ በሚገኘው የአዙሳ ጎዳና

---

[1] የአዙሳ ጎዳና መነቃቃት አፍሪካን እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳረፈ ለበለጠ መረጃ፣ ከአዙሳ እስከ አፍሪካ እስከ መንግስታት፣ ሁለተኛ እትም፣ የዴንዚል አር. ሚለር፣ በ www.DecadeofPentecost.org ላይ በነጻ የሚገኘውን መጽሐፍ ይመልከቱ።

መነቃቃት ላይም ተሳትፏል። ሌትዋባ እና ሌክ በአገልግሎት እስከ 1913 ድረስ ማለትም ሌክ ወደ አሜሪካ እስኪመለስ አብረው ተጉዘዋል።

እግዚአብሔር ሌትዋባ እናት እንደገለፀላት፣ ብዙዎችን ወደ መዳን እና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን በመምራት ኃይለኛ የጴንጤቆስጤያዊ ሰባኪ እና አስተማሪ ሆነ። በደቡብ አፍሪካ እና በሮዴዢያ (ዚምባብዌ) በአገልግሎቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ሲፈወሱ እና በሺዎች የሚቆጠሩ ሲድኑ አይቷል። ሌትዋባ በደቡብ አፍሪካ ከሚገኘው ሐዋርያዊ እምነት ተልዕኮ ጋር ግንኙነት ነበረው። በደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ጥቁር የሚመራ ሴሚናሪ የሆነውን የፍጥሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትን አቋቋመ። ሌትዋባ በ1959 እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሳይታክት ሰብኳል።

ዊልያም ዋዴ ሃሪስ (1860-1929 ገደማ) ወንጌልን በመላው ምዕራብ አፍሪካ ለማዳረስ እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። ሃሪስ "የአፍሪካ ስኬታማ ወንጌላዊ" ተብሎ ተጠርቷል። ገና በጉልምስና ዘመኑ፣ በላይቤሪያ ከሚገኙ የሜቶዲስት እና ኤጲስቆጶሳት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት ነበረው። ሃሪስ የአዙሳ ጎዳና ሚስዮናውያን በሞንሮቪያ በነበሩበት ወቅት ሞንሮቪያ ኖሯል። አንዳንዶች እነዚህ የአፍሪካ አሜሪካውያን ሚስዮናውያን የሃሪስ የጴንጤቆስጤያዊ ሥነ-መለኮት ምንጭ እንደነበሩ ያምናሉ።

ሃሪስ መልአኩ ገብርኤል በራእይ ተገልጦለት ብዙዎች በትንቢታዊ አገልግሎቱ ወደ ክርስቶስ እንደሚመጡ ይነግረዋል። ያንን ራዕይ ተከትሎ ሃሪስ ሰዎች ኃጢአታቸውን ትተው ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ በመንገር በመላው ላይቤሪያ፣ ኮትዲቭዋር፣ ጋና እና ሴራሊዮን ተዘዋወረ። በመንፈስ ኃይል አገለገለ፣ አጋንንትን እያወጣ፣ ድውያንን እየፈወሰ፣ እና በልሳኖች ይናገር ነበር። በተጨማሪም ሰዎች ጥንቆላን ትተው በኢየሱስ እንዲያምኑ እና ነጮች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ይዘው የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር እስኪመጡ እንዲጠብቁ አጥብቆ ተናገረ። በአገልግሎቱ ከመቶ ሺህ የሚበልጡ ሰዎች ወደ ክርስትና እንደተመለሱ ይገመታል።

ሌትዋባ እና ሃሪስ በአፍሪካ ውስጥ ኢየሱስ ያድናል፣ ይፈውሳል፣ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃል እና በቅርቡ እንደሚመጣ በማለት ሙሉ ወንጌልን የሰበኩ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የአፍሪካ መጋቢያን፣ ወንጌላውያን፣ አስተማሪዎች እና ሚስዮናውያን ምሳሌዎች ናቸው።

## የጴንጤቆስጤ በመላው አፍሪካ መስፋፋት

ጴንጤቆስጤ በመላው አፍሪካ በጉባኤ እግዚአብሔር (AG) የመስፋፋት ታሪክ መንፈስ ቅዱስ በአፍሪካ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል በምዕራባውያን ሚስዮናውያን እና በአፍሪካውያን አገልጋዮች አማካይነት ሲሠራ የሚያሳይ ታሪክ ነው። ጉባኤ እግዚአብሔር በአህጉሪቱ ካሉ በርካታ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ሲሆን እግዚአብሔር  የክርስቶስን መልእክት ለማዳረስ የተጠቀምበት ቤተክርስትያን ነው። እስቲ እነዚህን ሁለት ታሪኮች እንመልከት፡-

**በላይቤሪያ ፡፡** በ1908፤ ጃስፐር ከላቢዮ ቶ "ፈጣሪ አምላክ ካለህ እንዳገኝህ እርዳኝ" ሲል ጸለየ። እግዚአብሔር ቶን "ወደ ውቅያኖስ እንዲሄድ" ነገረው። በተመሳሳይ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ለአሜሪካዊው ሚስዮናዊ ከጆን ሙር ፐርኪንስ ጋር ምሪት እየሰጠው ነበር። ፐርኪንስ በቶሮንቶ ካናዳ በጴንጤቆስጤያዊ መነቃቃት ላይ በመገኘት በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ነበር። በኋላ እግዚአብሔር የክርስቶስን መልእክት ወደ ላይቤሪያ እንዲወስድ አዘዘው።

ፐርኪንስ በላይቤሪያ የባህር ዳርቻ በመርከብ ሲጓዝ መንፈስ ቅዱስ ወደ አንድ የተወሰነ ቦታ እንዲሄድ ሲነግረው ሰማ። የመርከቡ አለቃ ግን "ይህ ቦታ አስተማማኝ አይደለም" ሲል አስጠነቀቀው። ፐርኪንስ ግን አቁሞ ለመውረድ ጠየቀ። እርሱ እና ቡድኑ የወረዱበት ስፍራ ቶ የነበረበት ሥፍራ ነበር።

ወቅቱ የገና ቀን ነበር 1908፤ ፐርኪንስ ለቶ ወንጌልን አካፈው ቶም ወዲያውኑ ክርስቶስን ተቀበለ። ዛሬ ላይ የላይቤሪያ የጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክረስትያን ቶ እና ፐርኪንስ በጀመሩት ሥራ ላይ የተገነባ ቤተ ክርስቲያን ነው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሀገሪቱ ውስጥ ትልቁ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተዕምነት ነው።

**በናይጄሪያ ፡፡** በ1930ዎቹ መጀመሪያ ላይ በፖርት ሃርኮርት ናይጄሪያ የሚኖረው አውጉስቲን ኢሁሪኢዌ ዎጉ የጴንጤቆስጤያዊ ኢቫንጀል የተባለውን በጉባኤ እግዚአብሔር ዩ.ኤስ.ኤ የሚታተም መጽሔት ቅጂ አገኘ። ዎጉ በመጽሔቱ ላይ ስለ መለኮታዊ ፈውስ እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ባነበበው ነገር ስለተሳበ ለታመሙ መጸለይ እና ሰዎችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት ጀመረ። ይሄድበት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የጴንጤቆስጤያዊ ትምህርቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኗ፣ ዎጉ እና ሌሎች ጥቂት ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ብለው የሰየሙትን ገለልተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን መሰረቱ።

ከበርካታ አመታት በኋላ በ1939 ዎጉ በፖርት ሃርኮርት አንዳንድ አሜሪካዊ የAG ሚስዮናውያንን አገኘ። ሚስዮናዊያኑ ወደ ናይጄሪያ የመጡት እዚያ ሥራ ለመጀምር የሚችልበትን ሁኔታ ለመመርመር ነበር። ዎጉ እንዲረዱት ሚስዮናውያን እንዲልኩ ጠየቃቸው። ተልዕኮው ተስማምቶ በደብልዩ ሎይድ ሺረር የሚመራ ቡድን ከዎጉ ጋር እንዲሰራ ተላከ። ቤተ ክርስቲያንን የናይጄሪያ ጉባኤ እግዚአብሔር ብለው ለመጥራት ተስማሙ። ዛሬ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አባላትና ተከታዮች ያሉት በአፍሪካ ትልቁ የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ነው።

እነዚህ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ታሪኮች ውስጥ ሁለቱ ብቻ ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአፍሪካውያን እና ወደ አፍሪካ በላካቸው ሰዎች ትብብር አፍሪካን እንዴት እንደወረሰ ለማሳየት ይረዳሉ። የጴንጤቆስጤ ነበልባል በአህጉሪቱ ውስጥ ባሉ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ኅብረት እንደ ጋና የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን እና የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንደ ተቀጣጠለ ሌሎች ታሪኮችን መናገር ይቻላል።

**የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር ፡፡** በ1906 የጴንጤቆስጤያዊ መልእክት መጀመሪያ ወደ ላይቤሪያ ሲመጣ በአፍሪካ ውስጥ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ወይም አማኞች አልነበሩም። እግዚአብሔር ግን መንፈሱን በአህጉሩ ማፍሰስ ጀመረ። የጉባኤ እግዚአብሔር እድገት እግዚአብሔር አህጉሩን እንዴት እንደባረከ የሚያሳይ ብሩህ ምሳሌ ነው። በ1948 በተሰራው ቆጠራ የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር በ11 የአፍሪካ አገሮች ውስጥ፣ 700 ገደማ አብያተ ክርስቲያናት እና 40,000 አማኞች እንደነበሩ ያሳያል።

እ.ኤ.አ. በ1989 በአህጉሪቱ የሚገኙ የጉባኤ እግዚአብሔር ቤተዕምነተችን ያቀፈ የአፍሪካ የጉባኤ እግዚአብሔር ሕብረት(AAGA) ተቋቋመ። AAGA ከ1991 እስከ 2000 ያሉትን አስር ዓመታት "አሥርት የመኸር ዓመት" በሚል አጽንዖት ሲሰራ ነበር። አጽንዖቱ በመንፈስ የታጠቀ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ተልእኮ ላይ ነበር። በእነዚህ አሥር ዓመታት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በ31 አገሮች ፣ 11,688 አብያተ ክርስቲያናት፣ 2.1 ሚሊዮን ምእመናን ያደገ ሲሆን በአጠቃላይ በ39 አገሮች ወደ 24,019 አብያተ ክርስቲያናት እና 6.3 ሚሊዮን የሚሆን የምእመናን ቁጥር አድጎል። በ"አሥርት የመኸር ዓመት " የተገኘው ፈጣን ውጤት በሚቀጥሉት አሥርት ዓመታት ውስጥም ቀጥሏል። በ2010 የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተክርስትያን በ67,827 አብያተ ክርስቲያናት እና 16.6 ሚሊዮን ተከታዮች አድጎል።

እ.ኤ.አ. በጥር 2010፣ AAGA ""አሥርት ጴንጤቆስጤያዊ ዓመታት " (2010-2020) የተባለ ሁለተኛው አሥርት ንቅናቄን ጀምሯል። ልክ እንደ "አሥርት መኸር ዓመት " የ"አሥርት ጴንጤቆስጤያዊ ዓመታት " የቤተ ክርስቲያንን ተከላ እና ተልእኮዎች ላይ አፅንዖት ያደረገ ነው። ግቡ 10 ሚሊዮን

የቤተክርስቲያኑ አባላት በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው በመንፈስ የታጠቁ ምስክሮች ሆነው ሲንቀሳቀሱ ማየት ነው። እ.ኤ.አ. በ2019 መገባደጃ ላይ የአፍሪካ ጉባኤ እግዚአብሔር ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ እና የህንድ ውቅያኖስ ተፋሰስ ውስጥ ባሉ 87,741 አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ወደ 18.7 ሚሊዮን ተከታዮች አድጎል።

በጃንዋሪ 2021፣ AAGA "አሥርት የሪቫይቫል አመታት" የተባለውን ሦስተኛውን የአስርዮሽን አጽንዖት ጀምሯል። በዚህ አስርት ዓመታት ውስጥ፣ ቤተ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌል፣ በመንፈስ ጥምቀት፣ በቤተ ክርስቲያን ተከላ እና በተልዕኮዎች ላይ ትኩረት በመስጠት ትቀጥላለች። የ"አሥርት የሪቫይቫል አመታት" የአፍሪካ አሴምብሊስ ኦፍ ጎድ ልዩ ትኩረት በሰሜን አፍሪካ ላይ በማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ አላማውም ከዚህ ቀደም ችላ በተባለው አካባቢ በመንፈስ የታጠቀ የቤተ ክርስትያን ተከላ እንቅስቃሴዎችን ለመጀመር ነው።

# የጴንጤቆስጤ ተጽእኖ

ጴንጤቆስጤያዊነት የአፍሪካን ቤተ ክርስቲያን ገጽታ በብዙ መልኩ ቀይሯል። የንቅናቄው እድገት አስደናቂ ነው። እ.ኤ.አ. በ2015 የኦክስፎርድ ሪሰርች ኢንሳይክሎፔዲያ በአፍሪካ 202 ሚሊዮን ጴንጤቆስጤያዊያን (ተሐድሶዎች) እንዳሉ ዘግቧል ፣ ይህም ከአህጉሪቱ የክርስቲያን ህዝብ 35% እና ከጠቅላላው ህዝቧ 17% ነው። በተለያየ ደረጃ፣ በሁሉም የአፍሪካ ቤተ እምነቶች ጴንጤቆስጤያዊ ተጽእኖ አለባቸው ማለት ይቻላል። ብዙ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት የጴንጤቆስጤያዊ መገለጫዎች እንደ አምልኮ፣ እና የብርቱ ጸሎት የራሳቸው አድርገው ተቀብለዋል። በርካቶች እንደ ዳግመኛ መወለድ፣ ልሳን መናገር እና የሃይል አገልግሎት ያሉ አንዳንድ የጴንጤቆስጤያዊ መሰረታዊ ልማዶችን ተቀብለዋል።

የጴንጤቆስጤያዊ ክርስትናም የአፍሪካን ባህልም የቀየረ ነው። ይህን ካደረጉበት አንዱ መንገድ "ድሕነት እና ለውጡ" በመባል የሚታወቀው ክስተት ነው። ሰዎች ቁርጠኛ ክርስቲያኖች ሲሆኑ፣ ሕይወታቸው ይለወጣል፣ እናም ከኃጢአታቸውና ከተዋረደ ሕይወት "ይነሳሉ"። በዚህም የተሻሉ ሰዎች እና የበለጠ አምራች ዜጋ ይሆናሉ። ቤተሰቦቻቸውን በፍቅር እና በአክብሮት መያዝ ይጀምራሉ፣ በዚህም የበለጠ ስኬታማ ልጆችን ያፈራሉ። ከዚህም በላይ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ጠንካራ ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ ከፍተኛ ትምህርት መግባት፣ ጠንክረው በመስራት፣ የተሻለ ሥራ ያገኛሉ። እንዲሁም ከሙስና የጸዱ በመሆንም ይታወቃሉ። ይልቁንም በኑሮ የሚታገሉትን ለመንከባከብ በርኅራኄ ይዘረጋሉ። በተጨማሪም አንዳንድ የጴንጤቆስጤያዊ ክርስቲያኖች እሴቶቻቸውን ወደ ፖለቲካው መድረክ እየወሰዱ እዚያም ለውጥ እያመጡ ነው። እነዚህ ተግባራት እና ሌሎችም ለተሻለ ማኅበረሰብ መፈጠር አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛል። ሁሉም የጴንጤቆስጤያዊ ክርስቲያኖች በኅብረተሰቡ ውስጥ የክርስቶስን እሳቤዎች ጠብቀው የሚኖሩ ባይሆኑም፣ ይህን ለማድረግ የሚጥሩት አማኞች በጎ ተጽዕኖ እያሳደሩ ነው።

# ነገን መጋፈጥ

የዛሬዋ በአፍሪካ ያለች የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆማለች። ያለፈውን ጊዜ ስትመለከት በዚህ ምዕራፍ እንደተነጋገርነው በብዙ ስኬቶች ልትመካ ትችላለች። ሆኖም ግን ወደ ፊት ስትመለከት ብዙ ፈተናዎች እንደሚገጥሙአት ይታሰባል። ወደ ፊት ከሚገጥሙአት ተግዳሮቶች ውስጥ ሦስቱ የአስተምህሮ መዛባት፣ የመንፈሳዊ ግለት መቀዛቀዝ እና ራስ ወዳድነት ዋንኛ ስጋቶች ናቸው።

በምላሹ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እራስዎን ሶስት አጓጊ ጥያቄዎችን ብትጠይቁ ጥሩ ነው።

- ለቅዱሳት መጻሕፍት ታማኝ ሆኜ እኖራለሁ ወይስ ቤተ ክርስቲያኔን ወደ ስህተት አስተምህሮ እመራለሁ?
- ቤተክርስቲያኔን ወደ እውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ መነቃቃት እመራታለሁ ወይንስ “ሃይማኖታዊ መልክ አላቸው፤ ኀይሉን ግን ክደዋል” ወደ ተባለው መንፈሳዊ ውድቀት እንድትገባ እፈቅዳለሁ? (2 ጢሞ. 3:5)
- ምእመናቼን እና የጠፉትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲደርሱ ወደ እውነት እየመራሁ ነው ወይስ ወደ ከንቱ፣ ወደ ራስ ወዳድነት የግል ብልጽግና እና በረከት እየመራ[ቸ]ው ነው?

በአፍሪካ ውስጥ የምትኖረው የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስትያን የወደፊት እጣ ፈንታ በአብዛኛው የሚወሰነው አንተ እና በሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እነዚህን ጥያቄዎች በሚመልሱበት አግባብ  ላይ ነው።

በአህጉሪቱ ያሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ለጴንጤቆስጤያዊ ትውፊቶቻቸው ታማኝ ለመሆን በሙሉ ልብ ራሳቸውን ከሰጡ እና በእውነት በጴንጤቆስጤያዊ ትምህርት፣ ልምምድ እና ተግባርን ካስቀጠሉ፣ መጪው ጊዜ ብሩህ ነው። ነገር ግን፣ ትውፊቶቻቸው ትተው በዙሪያቸው እንዳሉት ለመሆን ከወሰኑ፣ በአፍሪካ ውስጥ ያለው የጴንጤቆስጤያዊ እምነት የወደፊት ዕጣ ፈንታ አደጋ ላይ ነው። ስለዚህ በመላው አፍሪካ ያሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የአባቶቻቸውን ቅዱስ ምሳሌዎች በጥብቅ መከተላቸው በጣም አስፈላጊ ነው።

ይህ የጴንጤቆስጤያዊ ትውፊት የተቀደሰ አደራ ነው። እውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ ታህድሶ የዓለም የመጨረሻው ታላቅ ተስፋ ነው። የጴንጤቆስጤያዊ ስጦታ ከተከበረ እና ወደ ነበልባል ከተቀጣጠለ፣ ከአፍሪካ ወደ ዓለም ሀገሮች በመስፋፋት ወደሚነድድ እሳትነት ሊያድግ ይችላል።  ችላ ከተባለ ወይም አላግባብ ወደ መጠቀም ካመራን ግን ሊዳፈን እና ሊጠፋ ይችላል። ስለዚህ በመላው አፍሪካ የሚገኙ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ጳውሎስ ለወጣቱ የጴንጤቆስጤ የሥራ ባልደረባውና የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ለሆነው ለጢሞቴዎስ የተናገረውን ቃል ማዳመጥ አለባቸው፡- “በእጆቼ መጫን የተቀበልኸውን በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታቀጣጥል አሳስብሃለሁ ” (2ጢሞ. 1:5)። ጳውሎስ አክሎም “የተሰጠህን መልካሙን ዐደራ፣ በእኛ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ”  ይላል (ቁ. 14)።

በአፍሪካ እንደሚገኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን፣ እኛም በጴንጤቆስጤያዊ አርበኞቻችን የተሰጠንን የእግዚአብሔርን ስጦታ ልንንከባከበው እና ልናቀጣጥል ይገባል። እንደነሱ  በእኛ ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የተሰጠንን በታማኝነት መጠበቅ አለብን።

# ~ ክፍል 4 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ
# የግል ሕይወት

# ~ ምዕራፍ 13 ~

# በመልካም ስርዓት የሚተዳደር ሕይወት

ወጣቱ መጋቢ ጭንቅላቱን በእጁ ቀብሮ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጧል። የገጠሙት የመጋቢነት ጥያቄዎች ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሆኖአል። አገልግሎቱን ትቶ ወደ ሥራው ለመመለስ እያሰበ ነው። ይህ ወጣት መጋቢ ያልተገነዘበው ነገር በጭንቀቱ ውስጥ ብቻውን እንዳልነበር ነው። በመላው አፍሪካ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። ብዙ የአገልግሎት ጫናዎችን መቋቋም እንደማይችሉ ይሰማቸዋል።

እነዚህ መጋቢያን በጣም የሚጨነቁበት አንዱ ምክንያት ህይወታቸውን በጥሩ ሁኔታ መምራትን አለመማራቸው ነው። በጣም በስርዓት ያልተያዘ ህይወት ስለሚመሩ እያንዳንዱ አዲስ ፈተና ሚዛናቸውን እንዲስቱ ያደርጋቸዋል።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከህይወት እና የአገልግሎት ጫናዎች ሁሉ ሊያመልጥ ይችላል ብሎ ማሰቡ ከእውነታው የራቀ ነገር ቢሆንም፤ እነዚህን ተግዳሮቶች በብቃት መቋቋም እንደሚችሉ ማመን ተገቢ ነው። ይህ ምዕራፍ አንተ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በጥሩ ሥርዓት የሚተዳደር ሕይወት እንዴት መምራት እንደምትችል ምክር የሚሰጥ ክፍል ነው።

## ሕይወትን በሥርዓት የማስተዳደር አስፈላጊነት

ለመጋቢ መመሪያውና የበላይ አስተዳዳሪው መጽሐፍ ቅዱስ ነው (1ጢሞ. 3፡1-2)። ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች "ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ኤጲስቆጶሳት አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ" (ሐዋ. 20፡28) በማለት መመሪያ ሰጥቷል። እንደ የበላይ ተመልካች፣ መጋቢው "የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ያስተዳድራል" (ቲቶ 1፡7)። በዚህ ምክንያት የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የአጥቢያ

ቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮች በብቃት የመምራት ኃላፊነት አለበት። ሆኖም መጋቢያን ቤተ ክርስቲያንን በተሳካ ሁኔታ ከማስተዳደር በፊት በመጀመሪያ የራሳቸውን ህይወት በመልካም ሁኔታ መምራት መቻል አለባቸው።

## በሥርዓት የሚተዳደር ሕይወት

በመልካም ሁኔታ የሚመራ ህይወት ከጭንቀት፣ ወይም አላስፈላጊ ከሆነ እክል እና ግራ መጋባት ነጻ ነው ማለት አይደለም። ሆኖም በአገልግሎት ለመቀጠል የሚያስፈልግህን መተማመን ይሰጥሃል። የበለጠ ውጤታማ እንድትሆን ያደርግሃል። በትንሽ ጥረት የበለጠ ለመስራት ትችላለህ። ደግሞም የህይወት ድንገተኛ ገጠመኞችን በአግባብ ለመቋቋም ይረዳል። በመልካም ሁኔታ የሚመራ ህይወት አራት ገጽታዎችን እንመልከት፡-

**1. ዓላማ።** በመልካም ሁኔታ የሚመራ ህይወት ማለት ግልጽ ዓላማ ያለው ሕይወት ነው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ዓላማ "መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነ" ሲል ገልጿታል (ሮሜ. 12፡2)። እግዚአብሔር ለህይወትህ ያለውን አላማ በግልፅ በተረዳህ መጠን ፣በዚህ አላማ ዙሪያ ህይወትህን በማስተካከል የበለጠ ውጤታማ ትሆናለህ።

በሰፊው ለመናገር ያህል  አንተ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ - እንደሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ እግዚአብሔርን ለማክበር እና ፈቃዱን ለማድረግ መኖር አለብህ። ይህንን እውነት እንደ መነሻ ብትቀበልም፣ እዚህ ማቆም ግን የለብህም። ለሕይወትህ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍጹም ወይም ሙሉ ፈቃድ ለማወቅ መጣር አለብህ። እግዚአብሔር ለምን በዚህ ልዩ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን እንዳስቀመጠህ ለመረዳት መጣር አለብህ። "ጌታ ሆይ፣ ለምን ወደዚህ ቦታ አመጣኸኝ?" "ለአንተ ክብር እዚህ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?"ብለህ በጸሎት የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ አለብህ።

**2. ቅድሚያ።** በዚህ ጊዜ፣ በዚህች ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ለመኖርህ የእግዚአብሔርን አላማ በግልፅ ከተረዳህ፣የግል እና የአገልግሎት ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ነገሮች መለየት ትችላለህ። ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች በጣም አስፈላጊ ናቸው ብለህ የምታምናቸው ነገሮች ናቸው። አብዛኛውን ጊዜህን እና ጉልበትህን የምታተኩርባቸው ጉዳዮች ናቸው። ክርስቶስ ስለ ህይወቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ሲናገር፡- ከሰማይ የወረድሁት የራሴን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ነው" ብሏል (ዮሐንስ 6፡38)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳትህን የአገልግሎት እና የህይወት ውሳኔዎች እንዲመራህ መጠቀም ትችላለህ። "ይህ ድርጊት ጌታ በሕይወቴ ያለውን ዓላማ ለመፈጸም የሚረዳኝ እንዴት ነው?" የሚልን ጥያቄ መጠየቅ ትችላለህ። የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚያራምድ የትኛውንም ተግባር መቀበል አለብህ። የእግዚአብሔርን ዓላማ የማያራምድ ማንኛውም ተግባር ደግሞ ማስወገድ ወይም ማቋረጥ አለብህ።[1]

**3. ሚዛን።** በተጨማሪም በመልካም ሁኔታ የሚመራ ሕይወት ሚዛናዊ ሕይወት ነው። ሚዛናዊ ህይወት ለእያንዳንዱ የህይወት አስፈላጊ ተግባራት ተገቢውን ጊዜ እና ጉልበት የሚበጅት ነው። በወደቀ ዛፍ ግንድ ላይ ወንዝ ለማቋረጥ የሚሞክር ሰው ሚዛኑን መጠበቅ አለበት። ወደ ግራ ወይም ቀኝ ካጋደለ ወደ ውሃው ውስጥ ይወድቃል። ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢም ተመሳሳይ ነው። እርሱ ወይም እርሷ

[1] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር በግል እና በአገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች፣ ምዕራፍ 4ን "የግል ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች" እና ምዕራፍ 5፡ "የአገልግሎት ቅድሚያዎች" ተመልከት።

ሁሉንም ትኩረታቸውን በአንድ ወይም በሁለት የሕይወት ዘርፎች ወይም በአገልግሎት ላይ ብቻ ካተኮሩ፣ ሚዛናቸውን ሊስቱ እና በሌላ ወሳኝ ቦታ ላይ ውድቀት ሊገጥማቸው ይችላል።

ለምሳሌ፣ መጋቢ እንደመሆንህ መጠን የቤተ ክርስትያን አባላትን በመንከባከብ ብዙ ጊዜ ልታጠፋ ትችላለህ። በዚህም ምክንያት የራስህን ቤተሰብ ችላ ማለት ይመጣል። ወይም ለስብከት ዝግጅት ብዙ ሰዓት በመውሰድ ጸሎትን ወይም የጠፉትን መድረስን ችላ ልትል ትችላለህ። እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በተለያዩ የህይወት ዘርፎች ሚዛንህ ለመጠበቅ መጣር አለብህ፣ ለምሳሌ

- በማድረግ እና በመሆን መካከል ያለው ሚዛን፣
- በስራ እና በእረፍት መካከል ያለው ሚዛን፣
- በአገልግሎት እና በቤተሰብ መካከል ያለው ሚዛን፣፣
- ሌሎችን በመንከባከብ እና ራስን በመንከባከብ መካከል ያለው ሚዛን።

ኢየሱስ ለፈሪሳውያን የተናገረው ቃል እዚህ ላይ ይሠራል። ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ሌሎች ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ ተግባራትን ቸል እያሉ በአሥራት ላይ ያላቸውን ከልክ ያለፈ ትኩረት በሚመለከት ሞግቷቸዋል። “የፊተኛውን ሳትተዉ የኋለኛውን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር” (ሉቃስ 11፡42) ብሏል።

**4. አቅጣጫ**። በመጨረሻም፣ ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሥርዓት የሚተዳደር ሕይወት ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ሕይወት ነው። የመንፈስ ቅዱስን መመሪያ በቅርበት በተከተልክ ቁጥር ህይወትህ የበለጠ ስርአት ያለው ይሆናል።

ጳውሎስ በገላትያ ያሉትን አማኞች “በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አታድርጉ” ሲል አበረታቷቸዋል (ገላ. 5፡16)። ከዚያም በርካታ “የሥጋ ሥራዎችን” ዘርዝሯል። እነዚህ ድርጊቶች እያንዳንዳቸው በደካማ ወይም ስነ-ስርዓት የሌለው የህይወት ፍሬ ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው: - " ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣20 ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኝነት፤21ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እንዲሁም እነዚህን የመሰለው ነው” (ገላ. 5፡19-21)።

በሌላ በኩል በመንፈስ ቅዱስ መመራት ለእግዚአብሔር መገዛት ማለት ነው። እንዲህ ያለው ሕይወት “የመንፈስን ፍሬ” ለማፍራት ያስፈልጋል። ጳውሎስ ይህንን ፍሬ “ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ የውሃነት እና ራስን መግዛት” (ገላ. 5፡22-23) ሲል ገልጿል። እያንዳንዳቸው እነዚህ በጎነቶች በመልካም ሁኔታ የሚመራ የህይወት ውጤት ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ። ፍሬዎቹ የተፈጠሩት በክርስቶስ በመኖር (ዮሐ. 15፡5) እና በመንፈስ በመመላለስ ነው (ገላ. 5፡24-25)።

## በመልካም ሁኔታ የሚተዳደር ሕይወት ምሳሌ

ኢየሱስ በመልካም ሁኔታ የተመራ ሕይወትን በመለማመድ ረገድ ፍጹም ምሳሌያችን ነው። ኢየሱስ ህይወቱን በአባቱ አጀንዳ ዙሪያ በማድረግ ከአባቱ እቅድ ጋር ተራመደ። በዚህ ምክንያት፣ በተልዕኮው ላይ ማተኮር ችሏል። የኢየሱስ ሕይወት ከላይ የተገለጹትን ሕይወትን በመልካም የመመራት ባሕሪን እንዴት እንደሚያሳይ ተመልከት።

- **ዓላማ**። ኢየሱስ የመምጣቱን አላማ ያውቅ ነበር እናም ለህይወቱ ተልእኮ ጽኑ ነበር። ለዚህም ነው አገልግሎቱ ወደ ፍጻሜው በደረሰ ጊዜ “የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርሁህ ” ብሎ ወደ አባቱ መጸለይ የቻለው (ዮሐ. 17፡4)።

- **ቅድሚያ**። ኢየሱስ የነገሮችን ቅደም ተከተል ይጠብቃል። ለምሳሌ፣ ከአባቱ ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ቅድሚያ ሰጥቶ ነበር። ማርቆስ ስለ እርሱ ሲጽፍ፡- “ማለዳም ገና ጎሕ ሳይቀድ፣ ኢየሱስ ተነሥቶ ከቤት ወጣ፤ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራም ሄዶ ይጸልይ ጀመር” (ማር. 1፡35)።
- **ሚዛን**። ኢየሱስ ፍጹም ሚዛናዊ ሕይወት ኖሮአል። መሆንን ከማድረግ፤ ሥራን ከእረፍት ጋር ሚዛኑን በማስጠበቅ ኖረ (ማር 6፡31-32)። ሚዛኑን የጠበቀ ሕይወት ስለኖረ አልዘገየም ወይም አይቸኲልም። ትክክለኛውን ነገር ሲያደርግ ሁል ጊዜ በትክክለኛው ቦታ ላይ ነበር።
- **አቅጣጫ**። ኢየሱስ ህይወቱን የኖረው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው። በመንፈስ ተሞልቶ ነበር (ሉቃ. 4፡18-19)፣ እናም መንፈስ እንደሚመራው ሁልጊዜ ያደርግ ነበር (ማቴ. 4፡1፤ ሉቃ. 4፡ 1)። ስለ ራሱ እንዲህ አለ፡- ““እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና” (ዮሐንስ 5፡19)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የኢየሱስን ምሳሌ ለመከተል መወሰን አለብህ (1 ዮሐንስ 2፡6)።

### በሥርዓት የሚተዳደር ሕይወት ጥቅሞች

በሥርዓት የሚተዳደር ሕይወትን ማሳካት ጥረትን የሚጠይቅ ቢሆንም ለጴንጤቆስጤ መጋቢ፣ የሚጠቅም ጥረት ነው። ህይወቱን በጥሩ ሁኔታ የሚመራ መጋቢ በአገልግሎት የበለጠ ውጤታማ ይሆናል። ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ የሚይዝ ስለሆነ በትንሽ ጥረት ብዙ መሥራት ይችላል።

በተጨማሪም በመልካም ሁኔታ የሚመራ ሕይወት ከፍተኛ የአእምሮ ሰላም አለው። ውጤታማ የሕይወት አያያዝ  ሥርዓት ያለው ነው፤ ሥርዓት ደግሞ  ሰላምን ይፈጥራል። ኢየሱስ በህይወቱ በሙሉ የአእምሮ ሰላም ነበረው። ሌሎች ሲደነግጡ እርሱ የተረጋጋ ነበር። ለምሳሌ፣ ደቀ መዛሙርቱ በማዕበሉ ሲደናገጡ፣ በጀልባዋ በስተኋላ በሰላም ተኝቷ ነበር (ማቴ. 8፡23-27)። ጳውሎስ ወደ ሮም ባደረገው ጉዞ ላይም ተመሳሳይ ነገር ነበር የሆነው (ሐዋ. 27፡27-38)።

በጥሩ ሁኔታ የተመራ ሕይወት በአገልግሎት ውስጥ ረጅም ዕድሜ ይቆያል። በአግባቡ ያልተደራጀ ህይወት ውጥረትን ያስከትላል። ጭንቀት ደግሞ መከሰምን ያስከትላል። ይሁን እንጂ በጥሩ ሁኔታ የሚመራ ሕይወት ሰላም ያስገኛል፣ ይህም በአገልግሎት ላይ የበለጠ ለመጽናት አስተዋጽኦ አለው።

## በጥሩ ሁኔታ የሚተዳደር ህይወት ሶስት ገፅታዎች

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ሶስት የህይወት እና የአገልግሎት ዘርፎችን በሚከተለው መልኩ በተሳካ ሁኔታ ማስተዳደር መቻል አለብህ።

### የፋይናንስ አስተዳደር

በመጀመሪያ የግል ፋይናንስህን በሚገባ ማስተዳደር መማር አለብህ። ይህን ሂደት መጀመሪያው ያለህን ነገር ሁሉ ዞሮ ዞሮ የእግዚአብሔር መሆኑን ማስተዋል ነው (መዝ. 24፡1፤ 1ቆሮ. 4፡7)። አንተ የእግዚአብሔር ንብረት አስተዳዳሪ እንደሆንህ ማወቅ አለብህ፣ እናም አንድ ቀን ገንዘብህን እንዴት እንደያዝክ እግዚአብሔር መልስ ትሰጣለህ (ሉቃስ 16፡2)።

ጥሩ የገንዘብ አያያዝ እቅድ ገቢያችንን በሦስት ሰፊ ምድቦች መከፋፈል ይጠይቃል፡: የመጀመሪያ ለእግዚአብሔር መስጠት ፤ በሁለተኛ ደረጃ  መቆጠብ ፤ በመጨረሻም፣ በብልሃት ወጪን ማቀድ ነው። ይህንን ባለ ሶስት ክፍል ለመልካም የፋይናንስ አስተዳደር እቅድ በጥልቀት እንመልከተው።

1. ***መጀመሪያ ለእግዚአብሔር ትሰጣለህ።*** እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የገንዘብ ዋስትናን ለማግኘት በለጋስነት መስጠትን የመጀመሪያ እርምጃ ልታደርግ ይገባል። ቅዱሳት መጻሕፍት ደጋግመው እንደሚነግረን፣ የምንቀበለው ነገር ሁሉ የመጀመሪያው ፍሬ የእግዚአብሔር ነው (ዘጸ. 13፡1፤ 34፡26፤ ዘሌ. 2፡14፤ ምሳ. 3፡9)። ስለዚህ ፋይናንስህን የመምራት መነሻው አሥራትህን እና መባህን በታማኝነት ለእግዚአብሔር በመስጠት ነው። ቀጥሎ ለቤተ ክርስቲያን የገባህው እንደ ተልእኮ ወይም የግንባታ መዋጮ ቃል ኪዳኖች ያሉ ሌሎች የገንዘብ ግዴታዎችን መወጣት አለብህ። እግዚአብሔር ለእርሱ የሚለግሱትን አብዝቶ እንደሚባርክ ቃል ገብቷል (ሚል 3፡10-11፤ ሉቃስ 6፡38)።

2. **በመቀጠል፣ ለወደፊቱ ትቆጥባለህ**። ለእግዚአብሔር ከሰጠህ በኋላ ለወደፊት እና ለድንገተኛ ፍላጎቶች መቆጠብ አለብህ። በየሳምንቱ የተወሰነ የገንዘብ መጠን ወደ ቁጠባ ሂሳብ በማስቀመጥ ይህንን ማሳካት ትችላለህ። ይህ አካውንት እያደገ ሲሄድ ለአደጋ ጊዜ እንደ ሴፍቲኔት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣ በተጨማሪ ለትልቅ ግዢ የገንዘብ ምንጭ ሊሆን ይችላል።

3. ***በመጨረሻም ወጪህን በጥበብ ታቅዳለህ።*** ለእግዚአብሔር ከሰጠ እና የቁጠባህን ገንዘብ ከለየህ በኋላ የሚቀረው ለቤተሰብ ፍላጎቶች ማለትም እንደ ምግብ፣ የመኖሪያ ቤት ኪራይ እና ሌሎች ፍላጎቶች ለማሟላት ሊያገለግል ይችላል። ይህም ገንዘብ የእግዚአብሔር ስለሆነ በጥበብ ሊወጣ ይገባል። ይህንን ለማድረግ በጣም ጥሩው መንገድ የበጀት ወይም የፋይናንስ እቅድ ማዘጋጀት ነው። ይህ እቅድ የወጪ መመሪያ ሆኖ ያገለግላል፣ የግዢዎችህን ቅደም ተከተል ለመለየት ይረዳል። በአግባቡ የሚተዳደር ፋይናንስ ለቤት ሰላም እና መረጋጋት የራሱ አስተዋጾ አለው። የግል እና ቤተሰብ ግቦችህን ለማሳካትም ይረዳል።

## ጊዜን ማስተዳደር

በአግባህ የሚተዳደር ሕይወት በሁለተኛነት ጊዜህን በአግባቡ መቆጣጠርን መማር ይጠይቃል። በባህላዊ ተጽእኖ ምክንያት፣ ብዙ አፍሪካውያን መጋቢያን የጊዜ አያያዝን ፈታኝ አድርገው ያዩታል። ጊዜ ግን የአንድ ሰው በጣም ጠቃሚ ሀብት ነው። የጠፋውን ገንዘብ መተካት ብንችልም፣ የጠፋውን ጊዜ መመለስ አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም አጋጣሚዎች በአግባቡ በመጠቀም ጊዜን እንድንዋጅ ይመክረናል (ኤፌ. 5፡15-16፤ ቆላ. 4፡5)።

እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ገንዘብህን መበጀትን መማር እንዳለብህ ሁሉ፣ ጊዜህንም መበጀትን መማር አለብህ። ለቤተሰብ፣ ለስራ፣ ለመዝናኛ፣ ለጥናት፣ ለጸሎት፣ ለጉብኝት እና ለሌሎች አስፈላጊ ተግባራት ጊዜ መመደብን መማር ያስፈልጋል። ይህ ተግባር የዕለት ተዕለት የተግባር ዝርዝሮችን መፍጠር፣ የስራ ቦታዎን ማስተካከል፣ ዕለታዊ እና ሳምንታዊ ልማድን ማዳበር ይጠይቃል፤ ለይደር ማቆየትን ደግሞ ማስወገድን ይጠይቃል።

## ራስን መንከባከብ መለማመድ

በአግባህ የሚተዳደር ሕይወት በሦስተኛነት እራስን መንከባከብ መለማመድ ይጠይቃል። እራስን መንከባከብ የራሳችንን መንፈሳዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ ፍላጎቶችን የመጠበቅ ልምምድ ነው። ይህን የምናደርገው በራስ ወዳድነት ሳይሆን መንፈሳዊ ምክንያቶችን ይዘን ነው። እግዚአብሔርን እና ሌሎችን በተሻለ ሁኔታ እንድናገለግል ለራሳችን መጠንቀቅ አለብን።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር መንፈስ፣ ነፍስና ሥጋ አድርጎ ፈጠረው (1ኛ ተሰ. 5፡23)። መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝ የሰው ባህሪ ነው። ነፍስ የሚያስብ፣ ስሜት እና ፈቃድ ያለው የሰው ባህሪ ነው። ሥጋ ደግሞ የሰው ግዙፉ ባህሪ ነው። ራስን መንከባከብ ሦስቱንም መንከባከብን ያካትታል።

በቃሉ፣ በአምልኮ፣ በጾም እና በጸሎት በማሰላሰል መንፈሳዊ ሕይወትህን መንከባከብ ትችላለህ። በተጨማሪም ሀሳብ፣ ስሜት፣ እና ፈቃድህን ያለማቋረጥ ለክርስቶስ ጌትነት ማስገዛት አለብህ።[2] መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፡- "መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" (ሮሜ. 12፡2)። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ የአስተሳሰባችንን እንዴት መቆጣጠር እንዳለብን ያስተምረናል፡-

"እውነት የሆነውን ሁሉ፣ ክቡር የሆነውን ሁሉ፣ ትክክል የሆነውን ሁሉ፣ ንጹሕ የሆነውን ሁሉ፣ ተወዳጅ የሆነውን ሁሉ፣ መልካም የሆነውን ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ወይም ምስጋና፣ እንደ እነዚህ ስላሉት ነገሮች አስቡ" (ፊሊ. 4፡8)

ሰውነታችንን መንከባከብ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን በሥጋችን ልናከብረው ይገባል (1ቆሮ. 6፡19-20)። ጤናማ ሰውነት ካለን በሕይወታችን ላይ የእግዚአብሔርን ጥሪ በተሻለ መንገድ እንድንፈጽም አቅም ይኖረናል። ሕይወትን በሙላት እንድንኖር ያስችለናል (ዮሐ. 10፡10)። ስለዚህ ሰውነታችንን በደንብ በመመገብ፣ቋሚ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ፣በቂ እንቅልፍ በመተኛት እና መደበኛ የህክምና ክትትል በማድረግ እንክብካቤ ማድረግ አለብን።

# በአግባብ የሚተዳደር ህይወትን መከታተል

ምናልባት፣ "እኔ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በደንብ የሚተዳደር ኑሮ ለመከተል እንዴት እሄዳለሁ?" ብለህ ትጠይቅ ይሆናል።

## ውሳኔ አድርግ

በአግባብ የሚተዳደር ህይወት የመኖር ፍለጋህን በውሳኔ ልትጀምር ያስፈልጋል። ኢየሱስ ስለ አባካኙ ልጅ ታሪክ ተናግሯል። በዚህ ታሪክ ውስጥ አመጸኛው ልጅ ከአባቱ ርስቱን ጠይቆ ከቤት ወጣ። ብዙም ሳይቆይ በሚያሳዝን የአኗኗር ዘይቤ ምክንያት እራሱን በሜዳ ያሉ አሳማዎች ሲመግብ አገኘው። በዚህ ጊዜ ግን ወደ ልቡ ተመለሰና "ተነሥቼ ወደ አባቴ ልሂድና እንዲህ ልበለው "አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በአንተ ፊት በድያለሁ፤19 ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም፤ ከተቀጠሩት አገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቍጠረኝ" እለዋለሁ ብሎ በልቡ አሰበ(ሉቃስ 15፡18-19)። ወስኖም ተነሳና ወደ ቤቱ ጉዞውን ጀመረ።

በአግባብ የሚተዳደር ህይወት መፈለግ ረገድም የታሪኩ ሂደት ተመሳሳይ ነው። ውጤታማ የአኗኗር ዘይቤ ጉዞ በቆራጥ ውሳኔ መጀመር አለበት። አሁን ያለህበትን ሁኔታ ተመልክተህ ለመኖር እና ለማገልገል የተሻለው መንገድ እንዳለ መወሰን አለብህ። ከዚያ ለራስህ "ተነሥቼ የበለጠ ውጤታማ የአኗኗር ዘይቤን እከተላለሁ" ማለት አለብህ።

[2] ይህ ርዕስ በምዕራፍ 15 "ጠንካራ የአምልኮ ልማድ"ላይ ተብራርቷል።

# አቅድ

በአግባብ የሚተዳደር ህይወት ለመምራት መወሰን አስፈላጊ ቢሆንም፣ በቂ አይደለም። ውሳኔው ሊሰራ በሚችል እቅድ መደገፍ አለበት። ይህ እቅድ ሶስት ደረጃዎችን ያካትታል፡፡ እነሱም፡-

1. ***ራስን መገምገም***፡፡ በአግባብ የሚተዳደር ህይወት ጉዞህን ራስህን በመገምገም ትጀምራለህ። በዚህ ግለ-ግምገማ ውስጥ የት ላይ መሻሻል እንደሚያስፈልግህ ለማወቅ አሁን ያለህን የአኗኗር ዘይቤ ትመረምራለህ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሐቀኝነት በመመለስ ይህንን ማድረግ ትችላለህ-

- ገንዘቤን በማስተዳደር ረገድ ምን ያህል ጥሩ እየሰራሁ ነው?
- ጊዜዬን በማስተዳደር ረገድ ምን ያህል ጥሩ እየሰራሁ ነው?
- መንፈሴን፣ ነፍሴን እና አካሌን በመንከባከብ ረገድ ምን ያህል ጥሩ እየሰራሁ ነው?
- በእያንዳንዳቸው በእነዚህ ዘርፎች እንዴት የተሻለ መስራት እችላለሁ?

እነዚህን ጥያቄዎች በጥንቃቄ መልስና እና መልሶችህን በማስታወሻ ደብተር ውስጥ ፃፍ።

2. ***ግቦችን ማዘጋጀት።*** ማሻሻያ የሚያስፈልግህን ቦታዎች ለይተህ ካወቅህ በኋላ፣ የአንተን ግላዊ የእድገት ግቦች አዘጋጅ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ እና በጥንቃቄ በመመለስ ይህንን ማድረግ ትችላለህ።

- የፋይናንስ አስተዳደር ክህሎቶቼን በምን መንገዶች ማሻሻል እፈልጋለሁ?
- የጊዜ አጠቃቀም ክህሎቶቼን በምን መንገዶች ማሻሻል እፈልጋለሁ?
- መንፈሴን፤ ነፍሴን እና አካሌን በመንከባከብ ክህሎቴን በምን መንገዶች ማሻሻል እፈልጋለሁ?

እንደገና መልሶችህን በማስታወሻ ደብተር ውስጥ በዝርዝር ጻፍ።

3. **እቅድ ማዘጋጀት።** አንዴ ግቦችህን ካወጣህ በኋላ እነዚህን ግቦች ለመድረስ እቅድ ማውጣት አለብህ። በአንድ ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ጉዳዮች ላይ ብቻ አተኩር ከዚያም እያንዳንዱን ግብ ለማሳካት እቅድ አውጣ። በእቅድህ ውስጥ፣ ግቦችዎን ለማሳካት ልትወስዳቸው የምትችላቸውን የተወሰኑ እርምጃዎችን መለየት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፣ የቤተሰብ በጀት በማዘጋጀት እና በመከተል የፋይናንስ ችሎታህን ማሻሻል ትፈልግ ይሆናል። ወይም በየማለዳው የዕለት ተግባር ዝርዝር በመስራት እና ከዚያ ይህንን ዝርዝር በመጠቀም የቀን እንቅስቃሴዎችን በመምራት የጊዜ አያያዝ ችሎታህ ማሻሻል ያስፈልግህ ይሆናል።

# መተግበር

አንዴ እቅድህን ካዘጋጀህ በኋላ ወደ ተግባር መሄድ አለብህ። እቅድህን ለመፈጸም እርምጃ መውሰድ አለብህ። ከእቅድህ ጋር በመጣበቅ ቆራጥ ሁን። ከዚያ ከሶስት እስከ ስድስት ወራት መጨረሻ ላይ እድገትህን ገምግም። ጥሩ ስራ የሰራህበትን እና ጥሩ ያልሰራህበትን ቦታ ለይ። ከዚያ እቅዱን አስተካክል እና ሂደቱን ድገመው። በተመሳሳዩ ግቦችን መከለስ ያስፈልግ ይሆናል ፣ ወይም በሌሎች ግቦች መተካት ያስፈልግ ይሆናል።

# ምዕራፍ 13 በመልካም ስርዓት የሚተዳደር ሕይወት

---

በአግባቡ የሚተዳደር ህይወት ማግኘት ረጅም የህይወት ሂደት ነው። ልንከተለው የሚገባ ግብ ነው፣ ደግሞ በጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ህይወት ውስጥ ብዙ በረከቶችን ያመጣል።

# ~ ምዕራፍ 14 ~

# ጤናማ ግንኙነቶች

የሙሴ ሕግ አዋቂ የሆነ አንድ ጥያቄ ወደ ኢየሱስ ቀረበ። “መምህር ሆይ፤ ከሕግ ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ትእዛዝ ነው?” ሲል ጠየቀ። ኢየሱስ ምንም ሳያቅማማ እንዲህ ሲል መለሰለት:- ““ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤38 ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፤39ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም፣ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ የሚለው ነው፤ 40ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው” (ማቴ. 22፡36-39)። ስለዚህ፣ እንደ ኢየሱስ ከሆነ፣ ግንኙነቶች እግዚአብሔርን የማገልገል ትርጎሜ ማዕከላዊ ቦታ ይይዛሉ።

ክርስትና ከሃይማኖት በላይ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግላዊ ግንኙነት ነው። ክርስትና አንዳንድ እምነቶችን ብቻ መከተል ወይም አንዳንድ የአምልኮ ሥርዓቶችን መፈጸም አይደለም። ከዚህ ይልቅ አምላክንና ሌሎችን የመውደድ ጉዳይ ነው።ክርስትናን ከሌሎች ሃይማኖቶች የሚለየው ይሄው ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር የፍቅር ግንኙነት ነው።

የመጋቢያዊ አገልግሎት በቅርበት መከናወን አለበት። እረኛ በጎቹን ከሩቅ ሊጠብቅ እንደማይችል ሁሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢም ከሩቅ ህዝቡን መንከባከብ አይችልም። በአገልግሎት ስኬታማ ለመሆን፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጠንካራ እና ጤናማ ግንኙነቶችን የመገንባትን አስፈላጊነት መረዳት አለበት። እና እነዚህ ግንኙነቶች እንዴት እንደሚዳብሩ እና እንደሚጠበቁ ማወቅ አለበት።

## ግንኙነቶችን መረዳት

ግንኙነቶች እርስ በእርሳችን የምንሰራቸው ትስስሮች ናቸው። እርስ በርሳችን የምንገናኝባቸው መንገዶች ናቸው። ግንኙነቶች የቅርብ ወይም የሩቅ፣ ጠንካራ ወይም ደካማ፣ እውነተኛ ወይም ጤናማ ያልሆኑ ወይም አጥፊ ሊሆኑ ይችላሉ። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከቤተሰብ አባላት፣ ከቤተ ክርስቲያን

አባላት፣ ከጓደኞች እና ከሌሎች መጋቢያን ጋር ጤናማ ግንኙነቶችን እንዴት መፍጠር እንደምትችል ማወቅ አለብህ። ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ማስተማር መቻል አለብህ።

ስለዚህ ጳውሎስ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ጤናማ ግንኙነት እንዲፈጥሩ አሳስቧቸዋል። በኤፌሶን ላሉ ክርስቲያኖች "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" ሲል ጽፏል (ኤፌ. 4፡ 3)። በሮም ላሉት አማኞች "እርስ በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ። ዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ካሉ ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ እንጂ አትኩራሩ፤ በራሳችሁም አትመኩ" (ሮሜ. 12፡16)። ውጤታማ አገልግሎት ለማገልገል በጉባኤ ውስጥም ሆነ ከጉባኤ ውጭ ጤናማ ግንኙነቶች መመስረት ወሳኝ መሆኑን ጳውሎስ ተረድቷ ነበር።

# የግንኙነቶች ዓይነቶች

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙህን የግንኙነቶች አይነቶችን ወይም ደረጃዎችን ማወቅህ አስፈላጊ ነው። ይህ ግንዛቤ በየትኞቹ ግንኙነቶች ላይ የበለጠ ዋጋ መክፈል እንዳለብህ እና የበለጠ ቅድሚያ መስጠት እንዳለብህ ያመላክትሀል ።

## ቀዳሚው ግንኙነት

በህይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊው ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት ነው። ሌሎች ሁሉም ግንኙነቶች በዚህ ዋና ግንኙነት ላይ መገንባት አለባቸው። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ቅድሚያ መስጠት አለብህ። ይህንን ግንኙነት በትክክል ካገኝህ፣ ሁሉም ሌሎች ግንኙነቶች ወደ ቦታ ይይዛሉ። በተቃራኒው ይህን ግንኙነት ከተቋረጠ፣ ሌሎች ሁሉም ግንኙነቶች አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል።

ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት ጥልቅ ፍቅር ያለው መሆን አለበት (ማቴ. 2፡37)። ይህ ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር ለትእዛዛቱ ሙሉ በሙሉ በመታዘዝ (ዮሐ. 14፡15፣21) እና ለሌሎች ባለህ ከፍቅር የመነጨ አሳቢነት ይገለጻል (ዮሐንስ 15፡12)።

## የቤተሰብ ግንኙነቶች

ሁለተኛ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ቀጥሎ የሚቀመጠው ከትዳር ጓደኛህ ጋር ያለህ ግንኙነት ብቻ ነው። እግዚአብሔር ባልና ሚስት አንድ ሥጋ እንዳደረጋቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘፍ. 2፡24)። ክርስቶስም ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ባል የራሱን ሥጋ እንደሚወድ እንዲሁ ሚስቱን መውደድ አለበት። ሚስትም ባሏን ታክብር በቤት ውስጥ ላለው ሥልጣኑ መገዛት አለባት (ኤፌ. 5፡21-33)። አንተ እና ባለቤትህ ይህን ግንኙነት ከሌሎች ሰብዓዊ ግንኙነቶች ሁሉ በላይ ከፍ አድርጋችሁ ልትመለከቱ ይገባል። እና ይህን ግንኙነት ለማጠናከር ብዙ ጊዜ እና ጥረት ማድረግ አለብህ።

ሦስተኛው፤ በጣም አስፈላጊ ግንኙነትህ ከልጆችህ ጋር ነው። ልጆችህን በጥልቅ መውደድ አለብህ፤ እና ከልብ ልትንከባከቢቸው ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆች ልጆቻቸውን በጌታ ምክር ማሳደግ እንዳለባቸው ይናገራል (ኤፌ. 6፡4)። ስለዚህ የመጋቢ ተግባራህን በመከታተል ተጠምደህ ልጆችህን በፍፁም ቸል አትበል። ከዚህ ይልቅ ከእያንዳንዳቸው ጋር ወዳጅነት ለመመሥረት ጊዜ መመደብ አለብህ። ይህ በቤት ውስጥ የፍቅር ጓደኝነትን ይፈጥራል። ይህ ድባብ ስራህን በሰላም እንድትቀጥል ያስችልሃል፤ በአገልግሎት ላይ ውጤታማነት ይጨምራል። ለቤተ ክርስቲያን እና ለህብረተሰቡ ምስክር ሆኖ ያገለግላል። ከሁሉም በላይ፣ ልጆችህን ከክርስቶስ ጋር ወደ ግላዊ ግንኙነት መምራት አለብህ። እያንዳንዱ ልጅ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱን ማረጋገጥ አለብህ።

በተጨማሪም፣ ከቤተሰብህ ጋር የፍቅር ግንኙነት መመሥረት አለብህ። ለወላጆችህ፣ ለወንድሞችህና ለእህቶቻችሁ፣ ለአክስቶችህ እና ለሌሎች የቤተሰብ አባላት ተገቢውን ክርስቲያናዊ ፍቅርና አክብሮት ማሳየት አለብህ። ሆኖም ሁሉንም ነገሮች በተገቢው ቅደም ተከተል ማድረግ ተገቢ ነው። ከትዳር ጓደኛህ እና ከልጆችህ የበለጠ የቤተሰብ አባላትህን በጭራሽ መምረጥ የለብህም። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- "አንድ ሰው ዘመዶቹን፣ በተለይም የቅርብ ቤተሰቡን የማይረዳ ከሆነ ሃይማኖቱን የካደ፣ ከማያምንም ሰው ይልቅ የባሰ ክፉ ነው" (1 ጢሞ. 5:8)።። [1]

## የአገልግሎት ግንኙነት

ከእግዚአብሔር እና ከቤተሰብ አባላት ጋር ካለህ ግንኙነት በተጨማሪ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የአገልግሎት ግንኙነቶችህን በጥንቃቄ መከታተል አለብህ። እነዚህ ግንኙነቶች ከምታገለግላቸው እና ከአብሮ ሰራተኞች ጋር ያለን ግንኙነቶ ያካትታል ይሄውም የቤተ ክርስቲያን አባላት፣ ማህበረሰብ እና ቤተ እምነቱን ወይም ዋና ቢሮን ያካትታል። እያንዳንዳቸው ግንኙነቶች ልዩ ናቸው። በመሆኑም እያንዳንዳቸው በተለየ መንገድ መያዝ አለባቸው። በአገልግሎት ውስጥ ያለህ ስኬት ወይም ውድቀት እነዚህን ግንኙነቶች በምትይዝበት አያያዝ በከፍተኛ ደረጃ ይወሰናል።

በተጨማሪም፣ የቤተክርስቲያናችሁ መንፈሳዊ አገልግሎት እና ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ጠንካራ ግላዊ እና ሙያዊ ግንኙነት መገንባት ያስፈልግሃል። ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ሲመርጥ እንዲሰብኩና አጋንንትን እንዲያወጡ ላካቸው። ሆኖም በመጀመሪያ የጠራቸው ከእርሱ ጋር ጊዜ እንዲያሳልፉ ነበር(ማር. 3፡13-15)። ጌታ ከእርሱ ጋር አብረው በነበሩበት ጊዜ የሚገነባው ትስስር ሲለያዩ ለአገልግሎታቸው መሠረት እንደሚሆን ያውቅ ነበር። አንተ ለምትመራው ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው። ከአገልጋዮች እና ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ያለህ ትስስር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ አገልግሎቶች ሁሉ መሠረት ሆኖ ያገለግላል።[2]

## ሦስት አደገኛ ግንኙነቶች

አንዳንድ ግንኙነቶች አደጋ ያመጣሉ። ከእነዚህ ግንኙነቶች መካከል ሦስቱ ከዓለም ጋር ያለህ ግንኙነት፣ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለህ ግንኙነት እና የቅርብ ጓደኛ ምርጫ ጋር ያለህ ግንኙነቶች ናቸው። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እነዚህን ግንኙነቶች እንደሚከተለው በጥንቃቄ ማሰስ አለብህ።

**1. ከዓለም ጋር ያለ ግንኙነት።** ከዓለም ጋር ባለህ ግንኙነት ንቁ መሆን አለብህ። ዓለም በሰይጣን ቁጥጥር ስር ካሉት እና እርሱን በሚያገለግሉት ምድራዊ ስርዓቶች የተዋቀረ ነው (1ኛ ዮሐንስ 5፡19)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ "ከዓለም ለይቼ ስለ መረጥኋችሁ የዓለም አይደላችሁም፤" (ዮሐንስ 15፡19) ብሏቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ የክርስቶስ ተከታዮች በዓለም ውስጥ ቢኖሩም፣ እርሱ ወይም እርሷ በዓለም ነገሮች መጠመድ እንደሌለባቸው ያስረዳል (1ቆሮ. 7፡31)። ፍቅራቸውን በዓለማዊ ነገሮች ላይ ማድረግ የለባቸውም (1ኛ ዮሐንስ 2፡15)። ሕይወታቸውም የዓለም መንገድ መከተል የለበትም (ሮሜ. 12፡2)።

**2. ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለህ ግንኙነት።** በተጨማሪም፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለህን ግንኙነት በቅርበት መከታተል አለብህ። አንዳንድ መጋቢያን በዚህ ግንኙነት ውስጥ ድንበር መጠበቅ ስላቃታቸው በውርደት ውስጥ ወድቀዋል፤ የእግዚአብሔርንም ሥራ አሳፍረዋል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *"22 ከወጣትነት ክፉ ምኞት ሽሽ፤ በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋርም ጽድቅን፣ እምነትን፣*

---

[1] በዚህ ርዕስ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 7ን "በቤተሰብ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ተመልከት።

[2] በዚህ ርዕስ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 5ን "በአገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ተመልከት።

*ፍቅርንና ተከተል*" (2 ጢሞ. 2፡22) በማለት አስጠንቅቆታል። በተጨማሪም ልጁን በእምነት "አሮጊቶችን እንደ እናቶች፣ ወጣት ሴቶችን ደግሞ እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና አስተናግዳቸው" (1 ጢሞ. 5፡2) በማለት አስተምሮታል።

ከተቃራኒ ጾታ ጋር መገናኘት ያለብህ በፍፁም ተገቢነት ባለው ሁኔታ ነው። ከትዳር ጓደኛህ ሌላ ተቃራኒ ጾታ ጋር ብቻህን ማግኘት የለብህም። እንዲሁም የአስተሳሰብህን መጠበቅ አለብህ። አመንዝራነት የሚጀምረው በሰው ሃሳብ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ሃሳብህ ከትዳር ጓደኛህ ወደ ሌላ ሰው እንዲዞር ፈጽሞ መፍቀድ የለብህም (ማቴ. 5፡28)። መጽሐፍ ቅዱስ "ከሁሉም በላይ ልብህን ጠብቅ፤የሕይወት ምንጭ ነውና" (ምሳ. 4፡23) በማለት ይመክራል።

**3. የጓደኞች ምርጫ።** የአንድ ሰው የጓደኛ ምርጫ በህይወቱ ላይ ትልቅ በረከት ወይም ትልቅ ጉዳት ሊያመጣ ይችላል። ስለዚህ ጓደኞችን ለመምረጥ ጥበብን ሊኖርህ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ "ጻድቅ ሰው ለወዳጁ መልካም ምክር ይሰጣል፤ የክፉዎች መንገድ ግን ወደ ስሕተት ይመራቸዋል" (ምሳ. 12፡26) ይለናል። ጳውሎስ አክሎ፣ "አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል" ይላል(1ቆሮ. 15፡33)። ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደመሆንህ፣ ወደ እግዚአብሔር እንድትቀርብ እና እርሱን የሚያስደስት ሕይወት እንድትመራ ከሚያበረታቱህ ጋር ብቻ ጠንካራ ጓደኝነት መመሥረት አለብህ።

# ጤናማ ግንኙነቶች ባህሪያት

አፍሪካውያን የአንድ ሰው የህይወት ጥራት በአብዛኛው የሚወሰነው በእርሱ ወይም በእርሷ ግንኙነቶች ጥራት እንደሆነ ይታሰባል። ታዲያ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በቤቱ፣ በአጥቢያ እና በማኅበረሰብ ዘንድ ጤናማ ግንኙነቶችን በመገንባት እና በመጠበቅ ረገድ ራሱን ለመምራት ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው አንዳንድ መመዘኛዎች ምን ምን ናቸው? እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ግንኙነቶችህ አምስት ባህሪያትን ማሳየት አለባቸው፡-

## ፍቅር

ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት መግለፅ ያለበት የመጀመሪያው ባህሪ የመስዋዕትነት ፍቅር ነው። የትዳር ጓደኛህን፣ ልጆችህን እና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ክርስቶስ በወደደህ ፍቅር መውደድ አለብህ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "እኔ እንደ ወደድኳችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ" (ዮሐንስ 13፡34) በማለት አዘዛቸው። አንዳቸው ከሌላው ጋር ያላቸውን ግንኙነት መግለጽ ያለባቸው ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ፍቅር መሆኑን እየነገራቸው ነበር። ኢየሱስ ስለ እነርሱ ነፍሱን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር። አሁን፣ አንዳቸው ለሌላው ህይወታቸውን አሳልፈው ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለባቸው (ዮሐንስ 15፡12-13)። በዚህ መንገድ ጴጥሮስ "እርስ በርሳችሁም አጥብቃችሁ ከልብ ተዋደዱ" በማለት አሳስቦናል (1 ጴጥ. 1:22)።

## ግልጽ ግንኙነት

ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት ሊገልጽ የሚገባው ሁለተኛው ባህሪ ግልጽ፣ ታማኝ ግንኙነት ነው። ጳውሎስ በኤፌሶን የሚኖሩ ክርስቲያኖች እውነትን በፍቅር እንዲናገሩ መክሯቸዋል። ይህን ቢያደርጉ እንደ ክርስቶስ አካል እንደሚያድጉና በሳል እንደሚሆኑ ይናገራል (ኤፌ. 4፡15)። ሐዋርያው በመቀጠል የቆላስይስ አማኞችን እንዲህ ሲል መክሯቸዋል፡- "ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ በጨው እንደ ተቀመመ ሁል ጊዜ በጸጋ የተሞላ ይሁን" (ቆላ. 4፡6)።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደመሆንህ፣ ከመናገርህ በፊት ቃላቶችህን በጥንቃቄ መመዘን አለብህ፣ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል አስታውስ፣ "አንደበቱን የሚጠብቅ ሕይወቱን ይጠብቃል፤አፉ እንዳመጣለት የሚናገር ግን ይጠፋል" (ምሳ. 13፡3)። ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት በባልንጀራነት፣ በራስ መተማመን እና በቅንነት መታወቅ አለበት። ቃላቶችህ ግልጽ እንጂ ዘርጣጭ፤ ሐቀኛ እንጂ ነውረኛ መሆን የለባቸውም። ሌሎች ሲናገሩ በጥሞና ማዳመጥ መማር አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ " ከማዳመጡ አስቀድሞ የሚመልስ፣ቂልነትና ዕፍረት ይሆንበታል" (ምሳ. 18፡13) በማለት ይመከራል።

## *የጋራ መተማመን*

ከቤተሰብህ እና ከቤተ ክርስትያን አባላት ጋር ያለህ ግንኙነት የሚገልጽ ሶስተኛው ባህሪ እርስ በርስ መተማመን ነው። ይህ ማለት ሰዎች እርስ በርስ ያላቸው መተማመን ነው። የጋራ መተማመን በግንኙነት ውስጥ ያሉ ሁሉም አካላት እውነተኛ እንደሚሆኑ እና ለግንኙነቱ ቁርጠኝነት እንደሚኖራቸው የጋራ እምነት መፍጠር ነው። የጋራ መተማመን እንዲኖር፣ በግንኙነት ውስጥ ያሉ ሁሉም ወገኖች አንዳቸው ለሌላው ያላቸውን ታማኝነት ማሳየት አለባቸው። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለሰዎች አመኔታ ብቁ መሆንህን ማረጋገጥ አለብህ። ሰዎች ፓስተራቸው በዙሪያቸው ሲሆን ደህንነት ሊሰማቸው ይገባል። ጥልቅ ሚስጥራቸውን ለእርሱ ወይም ለእርሷ ለመንገር መተማመን እና ድፍረት ሊሰማቸው ይገባል። ፓስተራቸው ምስጢሮቻቸውን ለማንም እንደማይናገር እርግጠኞች መሆን አለባቸው።

## ክብር

ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት መግለፅ ያለበት አራተኛው ባህሪ እርስ በርስ መከባበር ነው። አክብሮት ለሌሎች ስሜት፣ መብት እና ክብር ያለ ከፍ ያለ ግምት ነው። ጴጥሮስ ክርስቲያኖችን "ለሰው ሁሉ ተገቢውን አክብሮት ስጡ" ሲል አጥብቆ አሳስቧቸዋል፣ (1 ጴጥ. 2፡17)። ሚስቶች ባሎቻቸውን ማክበር አለባቸው ፣ ባሎችም ሚስቶቻቸውን ማክበር አለባቸው። ልጆች ወላጆቻቸውን ማክበር አለባቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን ማክበር አለባቸው። የቤተክርስቲያኑ አባላት ፓስተራቸውን ማክበር አለባቸው፣ ፓስተራቸው ሊያከብራቸው ይገባል።

ሰዎች ሁሉ የፈጣሪያቸውን መልክ ስለያዙ ዘራቸው፣ ነገዳቸው ወይም ማኅበራዊ አቋማቸው ምንም ይሁን ምን እያንዳንዱን ሰው ከፍ አድርጋችሁ ልትመለከቱት ይገባል። ጳውሎስ የሮም ክርስቲያኖችን "እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ" እና "እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ።" (ሮሜ.12፡10) በማለት አሳስቧቸዋል። አክሎም " እርስ በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ። ዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ካሉ ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ እንጂ አትኩራሩ፤ በራሳችሁም አትመኩ" (ቁ. 16) በማለት መክሮአቸዋል፡፡

## ትህትና

በመጨረሻም፣ ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት በትህትና መታወቅ አለበት። ትህትና ከግትርነት እና ራስን ከፍ ከፍ የማድረግ ተቃራኒ ነው፤ ከትዕቢት እና ከትምክህት ነፃ መሆን ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ትሁት ነው ስንል ይህ ሰው ራሱን እግዚአብሔር እንደሚያየው የማየት ብቃት አለው ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ትሑት ሰው ራሱን በትክክል ማየት ይችላል። ትህትና የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ነው። ጳውሎስ "4 ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ደግሞም ቸር ነው። ፍቅር አይመቀኝም፤ አይመካም፤ አይታበይም፤5 ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም፤ ራስ ወዳድ አይደለም፤ አይበሳጭም፣ በደልን አይቈጥርም" ይላል (1ቆሮ. 13፡4-5)።

ትዕቢት የጥልቅ እና ዘላቂ ግንኙነት መንገድን ይዘጋል። ትሕትና ግን ጥሩ የግንኙነት በር ይከፍትልናል (ሮሜ. 12፡16)። እንደ ትሁት መጋቢ፣ ከህዝቡ እንድትመሳሰል ይጠበቅብሃል። ቅርብ መሆን አለብህ። በራስህ እና በሰዎች መካከል ግድግዳ ከመሥራት ይልቅ ድልድይ ልትሰራ ይገባል።

# ጤናማ ግንኙነቶችን መጠበቅ

ጤናማ እና እግዚአብሔርን የሚያከብር ግንኙነት ከሌሎች ጋር ለመገንባት እና ለማቆየት የሚረዱህ ሶስት ልምዶች ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

## የአላማ ሰው ሁን

በመጀመሪያ፣ ከቤተሰብህ አባላት፣ ከቤተ ክርስትያን አባላት እና ከአገልግሎት አጋሮችህ ጋር ጤናማ ግንኙነትን ስለመገንባት እና ስለማቆየት ዓላማ ያለው ሰው መሆን አለብህ። ይህ እንዲሆን መነሳሳቱን በራስ መውሰድ እና እነዚህን ግንኙነቶች በንቃት መከታተል አለብህ። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። በሰዎች መካከል መኖርን መረጠ። ጊዜ ወስዶ አደመጣቸው እና ጭንቀታቸው ሰማ። ጠላቶቹም ይህንን ስላስተዋሉ "የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ" ብለው ከሰሱት (ማቴ. 11፡19)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እንደ ኢየሱስ ለመሆን መጣር እና ከሌሎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር አለብህ።

## ግንኙነቶችን አሳድግ

በተጨማሪም ጤናማ ግንኙነቶችን ለመንከባከብ ጠንክረህ መሥራት አለብህ። ከቤተሰብህ፣ ከቤተ ክርስቲያን አባላት፣ እና ከአገልግሎት አጋሮችህ ጋር ጠንካራ እና ዘላቂ ትስስር ለመፍጠር የሚያስፈልገውን ጊዜ እና ጥረት ለማዋል ፈቃደኛ መሆን አለብህ። ይህንን ለማድረግ ከእነርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ፣ ታሪኮቻቸውን በማዳመጥ፣ በቀልዳቸው እየሳቁ፣ ስለ ልባቸውና ስለ ውድቀታቸው ማልቀስ ያስፈልጋል (ሮሜ. 12፡15)። ይህን ካደረግክ ከጊዜ በኋላ በአንተና በሕዝብህ መካከል ጠንካራ የፍቅር ትስስር ይፈጠራል።

## ይቅርታን ተለማመድ

በመጨረሻም፣ ከሌሎች ጋር ጠንካራና ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ለመመስረት እና ለመጠበቅ ከፈለግክ ይቅርታ መጠየቅን መማር አለብህ። ሰዎች ያሰናክላሉ ደግሞም ይሰናከላሉም ይህ የማይቀር ነው። አለመግባባቶች ይከሰታሉ፣ ስሜቶች ይጎዳሉ። ግንኙነቶች እንዲጠበቁ ከተፈለገ ይቅርታ መኖር አለበት።

ይቅርታ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች አሉት። አንደኛው ገጽታ የጥፋተኛው ወገን ይቅርታ መጠየቅ ሲሆን ሌላኛው ገጽታ የተበደለው ወገን ይቅርታ መስጠት ነው። ሁለቱንም ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለብህ (ማቴ. 5፡22-26)። ቅር ከተሰኘህ ይቅርታ ለመጠየቅ ፈጣን መሆን አለብህ። አንድ ሰው ይቅርታ ሲጠይቅ ይቅርታህን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለብህ። ይቅርታ ጥፋተኛውንም ሆነ የተበደለውን ነጻ ያወጣል። ለእርቅ በር ይከፍታል፣ የተበላሹ ግንኙነቶች እንዲሻሻሉ መንገድ ይሆናል።

---

ውጤታማ አገልግሎት በጠንካራ ጤናማ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው። ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እነዚህን ግንኙነቶች ለመገንባት ብዙ ዋጋ ይከፍላል።

# ~ ምዕራፍ 15 ~

# ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ

ከዚህም በላይ ለእርሱ ብዬ ሁሉን ነገር የተውሁለትን፣ ወደር የሌለውን ጌታዬን ክርስቶስ ኢየሱስን ከማወቅ ታላቅነት ጋር ሳነጻጽር፣ ሁሉንም ነገር እንደ ጉድለት እቈጥረዋለሁ፤ ለእርሱ ስል ሁሉን አጥቻለሁ፤ ክርስቶስን አገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤" (ፊልጵ. 3፡8)። እነዚህ ቃላት የሐዋርያው ጳውሎስ ናቸው። ጳውሎስ እስከ ዛሬ ከኖሩት ሁሉ ከኢየሱስ በመቀጠል በሁለተኛነት ታላቅ ሚስዮናዊ እንደሆነ ይታመናል። ጳውሎስ በኃይል ሰብኳል፣ ተአምራትን አድርጓል፤ በሮም ግዛት ውስጥ አብያተ ክርስቲያናትን ተክሏል። እግዚአብሔር ለአሕዛብ የመዳንን በር ለመክፈት ተጠቅሞበታል (ሐዋ. 14፡27)። ሆኖም በዚህ ሁሉ ውስጥ በሕይወቱ ውስጥ ትልቁ ስኬት ኢየሱስን ማወቁ ብቻ እንደሆነ በጽኑ ያምን ነበር። የዘወትር ጸሎቱ "ክርስቶስን ማወቅ እፈልጋለሁ" (ፊልጵ. 3፡10) የሚል ነበር።

እንደ ጳውሎስ፣ አንተም ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መሪ ነህ። ስለዚህ ብዙ ኃላፊነቶች አሉብህ። አማኞችን ወደ ደቀ መዛሙርት እንድታሳድግ እና የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር እንድታሰፋ ተጠርተሃል። እነዚህ ትላልቅ ስራዎች ናቸው ። እነዚህን ተግባራት በታማኝነት ማከናወን አለብህ። ሆኖም በአገልግሎት ሩቅ መሄድ ከፈለግክ፣ ልክ እንደ ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ያለህን ግንኙነት ማስቀደም አለብህ። ክርስቶስን ለማወቅ እና ከእርሱ ጋር ዘላቂ ህብረት እንዲኖርህ እራስህን መስጠት አለብህ።

ይህንን ለማድረግ፣ ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ማዳበር ያስፈልጋል። ምንም ያህል ጠንካራ ሰራተኛ ብትሆንም ፣ ምንም ያህል ታታሪ ወይም ውጤታማ ብትሆንም፣ ከጌታ ጋር ያለህን ሕብረት ልትተካው አትችልም። ይህ ምዕራፍ ስለ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ይመለከታል።

# የግል መንፈሳዊ ልምምድ

የግል መንፈሳዊ ልምምድ ምንነትን በመበየን ምርመራችንን እንጀምር።

## ሃሳብን መረዳት

ልማድ አንድ ሰው በየጊዜው የሚያደርገው ነገር ነው። ልማድ ከመደጋገሙ የተነሳ የተፈጥሮ አካል ይሆናል። በየማለዳው ጥርስን በመቦረሽ ልማድ እንዳዳበርን፤ ልማዶች የሚዳብሩት በመደጋገም ነው። መጀመሪ አንድ ሰው ልማዱን የማዳበር አስፈላጊነት እራሱን ማሳመን ይኖርበታል። አንዳንድ ጊዜ ይህን ለማድረግ ሥርዓት ውስጥ መግባት አለብን። ይሁን እንጂ ሥርዓት ውስጥ ከገባን በኋላ ነገሩ የተለመደ ይሆናል።

ታዲያ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ምንድን ነው? የግል መንፈሳዊ ልምምድ በየቀኑ ከክርስቶስ ጋር ሕብረት የማድረግ ክርስቲያናዊ ሥነ ስርዓት ነው። ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳደግ በየቀኑ የሚለየው ጊዜ አለው። ይህ ልማድ ነው። ምክንያቱም በጊዜ ሂደት፣ መደበኛ ይሆናል። ዓላማው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ለመንከባከብ እና ለእርሱ እና ለተልእኮው ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማሳደግ ስለሆነ መንፈሳዊ ነው።

## የአምልኮ ልማድ ጥቅሞች

ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ካዳበርክ እና በታማኝነት ከያዝክ ብዙ ጥቅሞች ወደ ህይወትህ እና አገልግሎትህ ይመጣሉ። ከእነዚህ ጥቅሞች ውስጥ አራቱን እንመልከት፡-

**1. ክርስቶስን ማወቅ።** የጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ማዳበር የመጀመሪያው ጥቅም ከክርስቶስ ጋር ባለህ ግንኙነት እንድታድግ ያደርግሃል። የዕብራውያን ጸሐፊ “በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ” (ዕብ. 10፡22) በማለት ያሳስበናል። ያዕቆብ ይህን ትዕዛዝ ለሚያከብሩ የተገባውን ቃል አክሎ፦ “ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተም ይቀርባል” ይለናል (ያዕቆብ 4:8)። ስትጸልይና ቅዱሳት መጻሕፍትን ስታሰላስል ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ትገባለህ (ዕብ. 10፡19)። በዚያ “ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር እግዚአብሔር*(ያህዌ)* ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት ይነጋገር ነበር፤” (ዘጸ. 33፡ 11) ለሙሴ እንደተባለለት፤ ራስህን ከእግዚአብሔር ጋር ስትነጋገር ታገኘዋለህ።

**2. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስተዋል**። ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ማዳበር ሁለተኛው ጥቅም እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ፈቃድ በደንብ መረዳት መቻል ነው። ስትጸልይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስታነብ እና ትምህርቱን በህይወትህ ላይ ስትተገብር አእምሮህ ይለወጣል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ “መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ” ፈትነህ ታውቃለህ (ሮሜ 12፡2)።

**3. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የዓለም እይታን ማዳበር።** ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ማዳበር ሦስተኛው ጥቅም ልምምዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታን ለማዳበር ይረዳሃል። ቅዱሳት መጻሕፍትን በጸሎት ስትመረምር፣ እግዚአብሔር እንደሚያየው ዓለምን ማየት ትጀምራለህ። ለሰው ልጅ ያለውን እቅድ መረዳት ትጀምራለህ። ያንን እቅድ ለመፈጸም ያለ ድርሻህን ትገነዘባለህ።

**4. ከመንፈስ ጋር ተስማምቶ መኖር።** ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ የመጠበቅ አራተኛው ጥቅም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በቅርበት መኖርን መማር ነው (2ቆሮ. 13፡14)። ጳውሎስ ክርስቲያኖችን “በመንፈስ እንዲራመዱ” አሳስቧል (ገላ. 5:25)። በመቀጠልም “ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ” በማለት መክሯቸዋል (የጥሬ ትርጉም ኤፌሶን 5፡18)። በአምልኮ ድባብ ውስጥ፣ ከኃይል ምንጭ ወደ አምፖል

ሃይል እንደሚፈስስ፣ መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን እና መገኘቱን ይለቃል። ሶኬቱ እስከተሰካ ድረስ፣ አምፖሉ ያበራል። ነገር ግን፣ መሰኪያው ከተነቀለ፣ ኃይሉ ይቋረጣል፣ አምፖሉ ይጠፋል። በታማኝ የግል መንፈሳዊ ልምምድ አማካኝነት ከኃይል ምንጩ ጋር እንደተሰካ መቆየት ትችላለህ። በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልተህ መቆየት ትችላለህ።

# ቅድሚያ የሚሰጣቸው መንፈሳዊ ልማዶች እና ተግባራት

ከዚህ ሀሳብ ጋር በተገናኘ ሁለት ጥያቄዎች የሚነሱ ሲሆን አንደኛው " እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ለማዳበር የምትችለው እንዴት ነው?" የሚል ሲሆን ሁለተኛው "ከልምምዱ የበለጠ ለመጠቀም ምን ማድረግ አለብኝ?" የሚሉ ጥያቄ ነው፡፡

## ሶስት ጠቃሚ ጉዳዮች

ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ለመመስረት ሶስት ተዛማጅ ጉዳዮችን ማንሳት ያስፈልጋል።

1. **ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች።** የግል መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ለመግባት የመጀመሪያ እርምጃ ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ነገሮች መወሰን ነው። ሰው ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር በጣም አስፈላጊ እና መጀመሪያ ለሚያደርገው ነገር ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ መወሰን አለብህ። የግል መንፈሳዊ ልምምድህን ይህን ግንኙነት ለማጠናከር እንደ አንድ ዘዴ አድርገህ ልትመለከተው ትችላለህ። ይህንን ለማድረግ "በአጣዳፊ ጉዳዩ መገዛት " ተብሎ ከሚጠራው ነገር መጠበቅ ያስፈልጋል። ማለትም ብዙ አስቸኳይ የህይወት እንቅስቃሴዎች እነዚህን በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ልማዶች እንዲያጨናንቁብህ መፍቀድ የለብህም።

በስራ እንደ ተጠመደ መጋቢ፣ በየቀኑ ብዙ አስቸኳይ ጉዳዮች ይገጥሙሃል። ጊዜህን የሚጠይቁ የማያቋርጡ አንገብጋቢ ጉዳዩች ያጋጥሙሃል። እነዚህን ፍላጎቶች ችላ ማለት ባትችልም፣ በተገቢው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ መማር ግን አለብህ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት መጠበቅ አለብህ። ያንን ግንኙነት ከቅድሚያ ዝርዝርህ በአንደኝነት ማስቀመጥ አለብህ። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። ከሰማይ አባቱ ጋር እንዳይገናኝ የሚያደርጉ ብዙ ኃላፊነቶች እንዲያጨናንቁት አልፈቀደም። መጽሐፍ ቅዱስ "ብዙ ጊዜ ወደ ገለልተኛ ስፍራ ወጥቶ ይጸልይ ነበር" (ሉቃስ 5፡16) ይለናል። አገልግሎቱን ለመደገፍ ከአባቱ ጋር ብቻውን የሚያሳልፍበት ጊዜ እንደሚያስፈልገው ያውቅ ነበር።

የማርያምና የማርታ ታሪክም ይህንን ነጥብ የበለጠ ያሳያል። ማርያም በኢየሱስ እግር ስር ተቀምጣ፣ ሲያስተምር ለማዳመጥ ቅድሚያ ሰጥታ ነበር። ይሁን እንጂ ማርታ መሥራት በሚያስፈልጋቸው ሥራዎች ሁሉ ትኩረቷ ተከፋፍሎባት ነበር። ኢየሱስ ለማርታ እንዲህ አላት፡- "ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፤ ትዋከቢአለሽም፤42 የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ማርያም እኮ የሚሻለውን ድርሻ መርጣለች፤ ይህም ከእርሷ አይወሰድም" (ሉቃስ 10፡41-42)። ማርታ በአጣዳፊው ጉዳዩች ትኩረቷ ተወስዶባት ነበር። ይሁን እንጂ ማርያም ከሁሉ የተሻለውን ነገር ማለትም ከጌታ ጋር ኅብረትን ለማድረግ ቀድሚያ ሰጥታ ነበር። እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንዲሁ ማድረግን መማር አለበት።

"ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ አንብቤ መጸለይ አልቻልም። በጣም ብዙ አስቸኳይ ነገሮች አሉኝ" ለማለት ትፈተን ይሆናል። ነገር ግን፣ በተደጋጋሚ ይህን ሰበብ የምትሰጥ ከሆነ ፣ ለማምለጥ አስቸጋሪ በሆነ የሕይወት ሥርዓት ውስጥ ትወድቃለህ። ነገር ግን የእለት ተእለት የግል ጊዜህን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳለህ ቀጠሮ የምትመለከተው ከሆነ እና ይህን ቀጠሮ በታማኝነት የምትጠብቅ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን መገኘት ረሃብ ታዳብራለህ። የግል ጊዜህን በደስታ ማከናወን ትጀምራለህ።

**2. የጊዜ አጠቃቀም።** የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ለማዳበር ሊያነሳው የሚገባው ሁለተኛው ጉዳይ የጊዜ አያያዝ ነው። የጊዜ አያያዝ ለእያንዳንዱ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ተገቢውን የጊዜ መጠን መመደብን ለማረጋገጥ የዕለት ተዕለት መርሃ ግብሩን የመስራት ልምምድ ነው። ውጤታማ መጋቢያን ጊዜ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ይገነዘባሉ። ስለሆነም በአግባብ ሊቆጣጠሩት ይገባል። ቀንህን በምታቅድበት ጊዜ፣ ለግል የጸሎት ጊዜ የሚሆን በቂ ጊዜ መያዙን ማረጋገጥ አለብህ።[1]

አንድ መጋቢ የአምልኮ ጊዜውን እንዴት እንደሚያከናውን ሲናገር "በየቀኑ ጠዋት ለጸሎት እና መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት ጊዜ መደብኩ" ይላል። "ለማገለግለው ሕዝብ ምን አይነት ፕሮግራም እንዳለኝ አሳውቃለሁ። ከዚያም በዚያን ጊዜ አንድ ሰው ደውሎ 'ላገኝህ እፈልጋለሁ' ቢለኝ ጸሎቴን እስከጨርስ ድረስ እንዲጠብቁ እነግራቸዋለሁ። ስጨርስ ወጥቼ ከእነርሱ ጋር እገናኛለሁ። በእርግጥ ምላሽ መስጠት ያለብኝ ድንገተኛ ሁኔታዎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ናቸው። በመደበኛው አካሄዴ ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ጊዜ ቅድሚያ እሰጣለሁ" ብሏል።

**3. ራስን በስርዓት መምራት**። ጠንካራ የግል መንፈሳዊ ልምምድ ለማዳበር ሦስተኛው ጉዳይ ራስን መግዛት ነው። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ቢያስቀምጥ እና ጊዜውን ቢያደራጅ ሆኖም እቅዱን ለመከተል የሚያስፈልገው ራስን በስርዓት መምራት ባይችል ምን ይጠቅመዋል? ስለዚህ በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ቀጠሮ ለማክበር ራስን በስርዓት መምራት አለብህ። እንደ መጋቢ፣ አሁን "የመጸለያ ጊዜ ነው ፤ አሁን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የማንበብያ ጊዜ ነው" በማለት የሚነግርህ ሰው የለም። ስለዚህ እራስህን በስርዓት መምራት አለብህ። ጳውሎስ አንድ መጋቢ ራሱን መግዛት እንዳለበት ለጢሞቴዎስ ነገረው (1 ጢሞ. 3:2)። በተጨማሪም ራስን መግዛት ወይም ራስን በሥርዓት መምራት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንደሆነ አስተምሯል (ገላ. 5፡23)።

## ሁለት የግል መንፈሳዊ ልምምድ

በዚህ ምእራፍ ላይ አስቀድመን እንደገለጽነው የግል ጊዜ ሁለቱ ተቀዳሚ ተግባራት ጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት ናቸው። እያንዳንዳቸውን እነዚህን የግል መንፈሳዊ ልምምዶች በጥልቀት እንመልከታቸው:-

**1. የግል ጸሎት።** የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የግል ጸሎትን በግል ጊዜ ውስጥ ማካተት አለበት። የግል ጸሎት ከልመና ጸሎት ወይም ከአማላጅ ጸሎት የተለየ ነው። በልመና ጸሎት ውስጥ፣ ጠያቂው በህይወቱ ወይም በእርሷ ውስጥ ያለውን ፍላጎት እንዲያሟላ ጌታን ይጠይቃል። በምልጃ ጸሎት እርሱ ወይም እርሷ ስለሌሎች ፍላጎት ይጸልያል። ነገር ግን፣ በግል ጸሎት ውስጥ፣ ጸላዩ ወደ እግዚብሔርም ይቀርባል፤ መንገዱን ለእግዚአብሔር ያስረካባል። ዳዊት "እግዚአብሔር ሆይ፤ አካሄድህን እንዳውቅ አድርገኝ፤ መንገድህንም አስተምረኝ" ብሎ በጠየቀ ጊዜ ይህን አይነት የግል የጸሎት እየጸለየ ነበር።

የግል ጸሎት በተጨማሪ የመዝሙር፣ የአምልኮ እና ለእግዚአብሔር የምስጋና ጊዜዎችን ይጨምራል። አንዳንዴ ዳዊት እንደጸለየው- "አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፉ አደረግሁ።...በሂሶጵም እንጻኝ፥ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ" (መዝ. 51:4፣7) ይህ ንስሃ መግባትን ይጨምራል። የእግዚአብሔር ቃል "ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው" (1ኛ ዮሐንስ 1፡9) በማለት ተስፋ ይሰጣል።

[1] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር እና የጊዜ አያያዝ ለበለጠ፣ ምዕራፍ 13 "በመልካም ስርዓት የሚተዳደር ሕይወትን" ተመልከት ።

በግል የጸሎት ጊዜ፣ ለቤተሰብ ጥሩ አካላዊ እና መንፈሳዊ ጤንነት መጸለይ ያስፈልጋል። እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን መጸለይ ያስፈልጋል ማለትም መንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲሰጣት እና ጉዳዮቿን እንዲመራ ደግሞም የቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑ ሁሉ በመንፈስ እንዲሞሉ መጸለይ ያስፈልጋል ማለት ነው። በተጨማሪም፣ ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ጤንነት ላይ እንድትሆን እና የመንፈስ ስጦታዎች እና ፍሬዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲገለጡ መጸለይ ያስፈልጋል።

**2. የግል መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት።** የግል መንፈሳዊ ልምምድ የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ይጨምራል። ነገር ግን በግል እና በሙያዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መካከል ያለውን ልዩነት መረዳቱ አስፈላጊ ነው። ሙያዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጋቢ ለመጋቢያዊ አገልግሎት ለመዘጋጀት የሚያደርገው ጥናት ነው። እንዲህ ዓይነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከናወነው እርሱ ወይም እርሷ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያጠና ስብከት ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲያዘጋጅ ነው። ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ሙያዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አስፈላጊ ነው። ሆኖም፣ በግል የጸሎት ጊዜ ማድረግ ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓይነት አይደለም።

በግል ጸሎት ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የምታካሄደው ለግል መንፈሳዊ እድገት ነው። አላማህ ስብከትን ማዘጋጀት ሳይሆን የእግዚአብሄርን ቃል በደንብ መረዳት እና የእግዚአብሔር ቃል ህይወትህን እንዲቀርጽ ለመፍቀድ ነው። የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓላማ እግዚአብሔርን በቃሉ መገናኘት ነው። አላማው እግዚአብሔርን የበለጠ ማወቅ፣ ወደ ክርስቶስ መቅረብ እና እርሱን በፍፁም ማገልገል ነው። ኢዮብ ለቅዱሳት መጻሕፍት የሰጠውን መሰጠት ሲናገር "ከአፉ ከወጣው ትእዛዝ አልራቅሁም፤የአንደበቱን ቃል ከዕለት እንጀራዬ አብልጬ ይዣለሁ" (ኢዮ 23፡12) ብሏል።

አንዳንዶች የግል መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አራት ደረጃዎች እንዳሉት ይጠቁማሉ። የመጀመሪያው እርምጃ ምንባቡን በዝግታ እና በጥንቃቄ ማንበብ ነው። ሁለተኛው እርምጃ በጽሑፉ ላይ ማሰላሰል ነው፣ "እግዚአብሔር በዚህ ክፍል ውስጥ ምን እየነገረኝ ነው?' እና "በዚህ ክፍል ውስጥ ላለው የእግዚአብሔር መልእክት እንዴት ምላሽ መስጠት አለብኝ?" የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ነው። ሦስተኛው እርምጃ "ጌታ ሆይ፣ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?" ብሎ መጸለይ ነው። የመጨረሻው እርምጃ ደግሞ እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የተናገረውን መታዘዝ እና መርሆቹን በተግባር ላይ ማዋል ነው።

# ስለ ግል መንፈሳዊ ልምምድ ተጨማሪ ግንዛቤዎች

በመዝጊያ ላይ፣ የግል መንፈሳዊ ልማድን ለማሳደግ እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ለማጠናከር ሶስት ተጨማሪ ግንዛቤዎችን እንመልከት።

## የጌታን ጸሎት በመጠቀም

አልፎ አልፎም ቢሆን፣ የጌታን ጸሎት በግል ጊዜህ እንደ መመሪያ መጠቀም ያስፈልግሃል። ይህ ጸሎት በማቴዎስ 6፡9-3 ላይ ይገኛል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አርአያ ወይም ምሳሌ ሆኖ የሰጣቸው ውጤታማ ጸሎት ነው። ይህንን ጸሎት እንደ መመሪያ በመጠቀም የግል የጸሎት ጊዜህን በሚከተለው መንገድ መምራት ትችላለህ።

1. **በውዳሴ ጀምር፡** "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ" (ቁ. 9)። ለእግዚአብሔር በመዘመር እና በማምለክ ጥቂት ጊዜ አሳልፍ። ስለ ማንነቱ አመስግነው እና ስላደረገው ሁሉ አመስግነው።

2. **የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ጸልይ፡**- *"መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን"* (ቁ. 10)። የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ሰዎች ሕይወት እንድትመጣ ጸልይ። ሰዎች ዳግም ተወልደው ክርስቶስን መከተል እንዲጀምሩ ጸልይ (ዮሐ. 3፡3-8)። እንዲፈወሱ እና ከአጋንንት እስራት እንዲድኑ ጸልይ(ማቴ. 12፡28፤ ሉቃ. 11፡20)። በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ጸልይ (ማር. 9፡1፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡3-8) ጌታ በቅርቡ እንደሚመጣ እያሰብክ ጸልይ (ሉቃስ 22:18፤ ራእ. 12:10፤ 22:20) ።

3. **እግዚአብሔርን ለምን፡**- "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" (ቁ. 11)። "እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት በክርስቶስ ኢየሱስ" የሚያስፈልህን ሁሉ እንዲያሟላልህ እግዚአብሔርን ለምን (ፊልጵ. 4፡19)። ስለሌሎች ፍላጎቶችህም ማልድ።

4. **ይቅርታን ጠይቅ ደግሞም ይቅር በል፡**- "እኛ ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን" (ቁ. 12)። ይቅርታን በመጠየቅ እና ለሌሎች ይቅርታ በመስጠት እራስህን በእግዚአብሔር ፊት አዋርድ።

5. **የእግዚአብሔርን መመሪያ እና ጥበቃን ጠይቅ:** "ወደ ፈተናም አታግባን፣ ነገር ግን ከክፉ አድነን" (ቁ. 13) በህይወትህ እና በአገልግሎትህ እና ከዲያብሎስ እና ከአጋንንቱ ኃይላት ጥበቃውን እንዲበዛልህ እግዚአብሔርን ለምን።

## ቀጣይነት ያለው ጸሎት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የዕለት ተዕለት የግል የጸሎት ጊዜውን ከመጠበቅ በተጨማሪ "ያለማቋረጥ መጸለይን" መማር አለበት (1 ተሰ. 5፡17)። ይህ ማለት ግን ቀኑን ሙሉ በጸሎቱ ክፍል ውስጥ መቆየት አለበት ማለት አይደለም። ይልቁንም መጸለይን ፈጽሞ ማቆም የለበትም ማለት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ቀጣይነት ባለው ኅብረት ውስጥ መኖርን መማር አለበት ማለት ነው። የእለት ተእለት እንቅስቃሴህን ስትሰራ ጸሎት ያለማቋረጥ በአንደበትህ አይታጣ (መዝ. 34፡1፤ ዕብ. 13፡15)። ዕለቱን ከላይ እንደተገለፀው በግል የጸሎት ጊዜ የምትጀምር ከሆነ ይህ ልምምድ ይሻሻላል። ያለማቋረጥ ጸሎት ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ለመራመድ አስፈላጊ ነው (ገላ. 5፡25)።

## ማስታወሻ መውሰድ

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእለት እለት ጸሎትን በማስታወሻ መያዝ ጥሩ ልምምድ ነው። የጸሎት ማስታወሻ መጋቢው የግል የጸሎት ጊዜውን የሚዘግብበት ማስታወሻ ደብተር ነው። በዚህ ማስታወሻ ውስጥ፣ እግዚአብሔርን የጠየቅካቸውን ጥያቄዎች፣ እግዚአብሔር ለጥያቄዎቹ ከሰጠው መልስ ጋር በማያያዝ መመዝገብ ያስፈልጋል። በጸሎትህ መልስ ውስጥ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ስትመለከት እምነትህ ይጠነክራል።

እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ የምትቀበለውን ማንኛውንም ቃል ወይም መረዳት መመዝገብ ያስፈልጋል። እነዚህ መረዳቶች ከጊዜ በኋላ መመሪያ ሆነው ሊያገለግሉህ ይችላሉ። ጌታ ለሕይወትህና ለአገልግሎት የሚሰጠውን መመሪያ እንድታስተውል የሚረዱህ መመሪያዎች። በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በምታነብበት ጊዜ የምታገኘውን ማንኛውንም ግንዛቤ መጻፍ ይጠቅማል። ከእነዚህ ግንዛቤዎች መካከል አንዳንዶቹ ለጉባኤ መልእክት ሊሆኑ ይችላሉ። እግዚአብሔር እንድታስታውሏቸው የሚፈልጋቸውን ነገሮች በልብህ እንዲያስቀምጠው እየጠየቀህ አልፎ አልፎ በማስታወሻህ ላይ የጻፍከውን መከለስ ያስፈልጋል።

---

ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእለት ተእለት የግል መንፈሳዊ ልምምድ አማራጭ አይደለም ፤ የግድ ነው። እንዲህ ያለው ልማድ ሕይወትንና አገልግሎትን በብዙ መንገድ ይጠቅማል። በሕይወትህ ላይ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመፈጸም የሚያስፈልግህን መመሪያ እና መንፈሳዊ ጥንካሬን ይሰጣል።

# ~ ክፍል 5 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የአደባባይ አገልግሎት

# ~ ምዕራፍ 16 ~
# በመንፈስ የተቀባ ጸሎት

አንድ የጴንጤቆስጤያዊ እምነት ተከታይ ያልሆነ መጋቢ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አያምንም ነበር። በተሞክሮው ላይ ብዙ ጊዜ ጥርጣሬውን ነበረው። ከዚያም አንድ ቀን፣ የሐዋርያት ሥራ 2ን በማንበብ እና በጴንጤቆስጤያዊ ቀን የተከናወኑትን ነገሮች እያሰላሰለ፣ የጴንጤቆስጤያዊ ልምድን በጸሎቱ ጠየቀ እናም ሥጦታውን ተቀበለ። ይህ ሰው "መንፈስ ቅዱስን ከተቀበልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስብከቴ ካለፉት የስብከት ዓመታትዎቼ የበለጠ ውጤት አስገኝቷል!" በማለት መስክሯል።

በታሪክ ኃይለኛ በመንፈስ የተቀባ ስብከት የጴንጤቆስጤያዊ አገልግሎት መለያ ምልክት ነው። ከሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ የጴንጤቆስጤያዊ እንቅስቃሴ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታጠቁ ለአሕዛብም የድኅነትን መልእክት በቅንዓት የሚያውጁ እጅግ በጣም ብዙ የሰባኪያን ሠራዊት አፍርቷል።

ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ ስብከት ርዕሰ ጉዳዮችን ይመለከታል። መንፈስ ቅዱስ ሰባኪውን የመቀባት ሚናው ላይ ያተኩራል። እንዲሁም የስብከት ዝግጅት እና አቀራረብ ላይ ምክርነቶችን ይሰጣል።

## የጴንጤቆስጤያዊ ስብከት

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር 16፡15) ብሎ አዘዛቸው። ስብከት ሰዎች ክርስቶስን እንዲከተሉ እና ፈቃዱን እንዲያደርጉ ለማሳመን በማሰብ የእግዚአብሔር ቃል ማወጅ ነው። ስብከት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ጭብጥ ነው። መስበክ ወይም ማወጅ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ወደ 150 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። ውጤታማ፣ በመንፈስ የተቀባ መልእክቶችን የመስበክ ችሎታ የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ዋና ኃላፊነት ነው።

### የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አብነት

ጴንጤቆስጤያዊያን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙት የሐዋርያትና የሌሎች ሰዎች ስብከት በዛሬው ጊዜ ላሉ ሰባኪዎች አርአያ እንዲሆን ተመዝግቧል ብለው ያምናሉ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሉቃስ በሐዋርያት እና በሌሎች ሰባኪዎች የተሰበኩትን የበርካታ ስብከቶች ይዘቶች መዝግቧል (ለምሳሌ፦ ጴጥሮስ ሐዋርያት ሥራ 2፡14-40፤ 3፡ 12-26፤ 10፡ 28-47፤ እስጢፋኖስ ሐዋርያት ሥራ 7፡1-53፤ ጳውሎስ የሐዋርያት ሥራ 13፡16-41፤ 17፡22-31)። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሉቃስ ለእነዚህ ስብከቶች የሰጣቸው ሰፊ ቦታ ጸሐፊው ለጭብጡ የሰጠውን አስፈላጊነት ያሳያል። አንባቢዎቹም ሐዋርያት እንዴት እንደሰበኩ እንዲያውቁ የፈለገው እነርሱም ተመሳሳይ እንዲያደርጉ አስቦ መሆኑ ግልጽ ነው።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉትን ስብከቶች በጥንቃቄ መመርመራችን ቢያንስ አምስት ጠቃሚ የሐዋርያት ስብከት ገጽታዎችን ያሳያል፦

1. **ኢየሱስን ያማከለ።** በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙ የስብከት መልእክት ማዕከል የክርስቶስ ማንነት እና ሥራ ነው። የአዲስ ኪዳን ሰባኪዎች ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን፣ እና ብቸኛው የመዳኛ መንገድ እርሱ እንደሆነ አዘውትረው አውጀዋል (ሐዋ. 2፡22-24፣ 30-32፤ 3፡13-20፤ 4፡10-12 5፡30-31፣ 8፡5፣ እና ሌሎች)።

2. **ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ማምራት።** በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉ ሰባኪዎች ማስረጃዎቻቸውን ለመደገፍ ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠቅሰዋል- (ሐዋ. 2፡17-21፤ 3፡22-23፤ 4፡11፣ 25-26፤ እና ሌሎች)።

3. **በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ።** በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉት ሰባኪዎች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ነበሩ (ሐዋ. 2:4፣ 14፤ 4:8፣ እና ሌሎች)።

4. **ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ማረጋገጫ።** በሐዋርያት ሥራ፣ የወንጌል ስብከት ብዙ ጊዜ በሚያረጋግጡ ምልክቶች እና ድንቅ ነገሮች ይታጀብ ነበር። (ሐዋ. 3፡1-8፤ 8፡4-7፤ 14፡8-10፤ እና ሌሎች)።

5. **የንስሐና የእምነት ጥሪ።** በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉ ሰባኪዎች በመደበኛነት ስብከታቸውን የሚጨርሱት ወደ ንስሐ እና እምነት በመጥራት ነው (ሐዋ. 2፡38፤ 3፡19፤ 8፡22 እና ሌሎች)።

ዛሬ በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ ስብከት እነዚሁ ባህርያት ማዕከላዊ መሆን አለባቸው። ይህን ዝርዝር በማስታወስ የራስህን የስብከት አገልግሎት ለመገምገም እንደ መመዘኛ ብትጠቀምበት ጥሩ ነው።

## የመንፈስ ቅዱስ ቅባት

በብሉይ ኪዳን፣ ነቢያት፣ ካህናት እና ነገሥታት ሲሾሙ በዘይት ይቀቡ ነበር (ዘጸ. 28:41፤ 1 ሳሙ. 9:16፤ 16:11-13፤ 1 ነገ. 1:34፤ 19:16) ይህ ቅባት የመጠራታቸው ምልክት ሆኖ ያገለግል ነበር። በያዙት ሃላፊነት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥልጣንም ያመለክታል። በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንፈስ በእነርሱ ላይ መገኘቱን የሚያመለክት ሲሆን ይህም የአገልግሎት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ያስችላቸዋል (ኢሳ. 61፡1-2)።

ከላይ እንደተገለጸው፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለው የስብከት አንዱ ገጽታ ሰባኪዎቹ በመንፈስ ቅዱስ የተቀቡ መሆናቸው ነው። እስቲ ይህን ሃሳብ ጠለቅ ብለን እንመልከተው።

## የኢየሱስ የተቀባ አገልግሎት

ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና" (ሉቃስ 4፡18) በማለት ማወጅ ነው። ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ማለት መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ መሆኑን ማለቱ እንደሆነ ገልጿል። ይህንን ቃል የተጠቀመው መንፈስ ቅዱስን በእርሱ በኩል የሚያደርገውን ኃያል አሰራር ለመግለጽ ሲሆን ይህም መሲሃዊ አገልግሎቱን እንዲፈጽም አስችሎታል።

## የሐዋርያት የተቀባ አገልግሎት

በጴንጤቆስጤ ቀን በ120ዎቹ ደቀ መዛሙርት ላይም ተመሳሳይ ነገር ደርሶባቸዋል። በመጀመሪያ፣ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ (ሐዋ. 2፡3)። ከዚያም ሞላባቸው። በመጨረሻም፣ በእነርሱ በኩል ይናገር ጀመር (ቁ. 4፣14)። ይህ ሁሉ የሆነው ኢየሱስ በሐዋርያት ሥራ 1፡8 "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ያለው ተስፋ ፍጻሜ ነው።

ስለዚህም መቀባት ማለት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እና በኃይል መታጠቅ ማለት ነው። መንፈስ በኢየሱስና በደቀ መዛሙርት ላይ ለአገልግሎት እንዲቀባቸው እንደወረደ፣ ዛሬም መንፈስ በተቀበለው ደቀ መዝሙር ላይ እርሱን ወይም እርሷን ለአገልግሎት እንዲቀባው ይመጣል።

## ቅብዐት ሲገለጽ

ቅባት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር በሰጡ ግለሰቦች አማካኝነት የሚሆን የመንፈስ ቅዱስ ኃያል ሥራ ነው። በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ደቀ መዝሙር ላይ የሚያርፈው የእግዚአብሔር የተገለጠ መገኘት ነው፣ ይህም መጋቢያን በላቀ ኃይል እና ውጤታማነት እንዲያገለግሉ ያስችላቸዋል።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ በመንፈስ ቅዱስ "የተሞላ/fill " እና "ምሉዕ/full" የሚሉት ቃላት አንዳንድ ጊዜ የመንፈስን ቅባት ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላሉ። "በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ/fill" የሚለው ቃል የመንፈስ መምጣትን፣ መሞላትን ሲያሳይ አንድን ሰው በኃይል እና በስልጣን እንዲሰራ እና እንዲናገር መቀባቱን የሚገልጽ ነው (ሐዋ. 4፡8፣ 31፤ 13፡9-12)። "በመንፈስ ቅዱስ ምሉዕ/full" የሚለው ቃል በመንፈስ ቅዱስ የመቀባትን ቋሚ/ቀጣይ ሁኔታ ይገልጻል (ሐዋ. 6፡3፣ 5፤ 7፡55)። ይህ በዮሐንስ "የተቀበላችሁት ቅባት" ያለው ሊሆን ይችላል (1 ዮሐንስ 2፡27)። በክርስቶስ እስከኖርን ድረስ ቅባቱ በእኛ ላይ ይኖራል (ዮሐ. 15፡4-7)። ከኃጢአት መለየት ቅባቱ ከእኛ ጋር እንዲዘልቅ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው (ዮሐንስ 14፡15-16)። ይህ ቅባት በእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሕይወት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆን አለበት።

## የተቀባ ስብከት

በመንፈስ የተቀቡ ስብከት ከአንደበተ ርቱዕነት፣ ከተፈጥሯዊ የመናገር ችሎታ ወይም ብዙዎችን በስሜት ከማንቀሳቀስ ችሎታ ጋር መምታታት የለበትም። እንዲሁም በጋለ ስሜት ከቀረበ የስብከት አቀራረብ ጋር መምታታት የለበትም። በመንፈስ የተቀባ ስብከት እነዚህን ባሕርያት ቢያሳዩም፣ ከዚህ የላቀ ነው። በመንፈስ የተቀባ ስብከት በመንፈስ የተመራ ስብከት ነው። በኢየሱስና በሐዋርያቱ በምሳሌነት የታየው የስብከት ዓይነት ነው።

ሉቃስ ይህንን እውነት በአጵሎስ ታሪክ እንዲህ ሲል ያስረዳል፣ "አጵሎስ…የተማረና ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር። 25 ይህ ሰው፣ የጌታን መንገድ የተማረ፣ ስለ ኢየሱስም በትክክል የሚናገርና በመንፈስ እየተቃጠለ የሚያስተምር ነበር" (የሐዋርያት ሥራ 18፡24-25) ስለዚህ አጵሎስ አንደበተ ርቱዕ እና አእምሮዊ ብቃት ያለው ሰባኪ ነበር። ነገር ግን "የሚያውቀው የዮሐንስን

ጥምቀት ብቻ ነበር" (ቁ. 25)። የጴንጤቆስጤያዊ ልምድ አልነበረውም። ይሁን እንጂ ጵርስቅላና አቂላ "የእግዚአብሔርን መንገድ ይበልጥ አስተካክለው አስረዱት።" በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደነበር ግልጽ ነው። ከዚያም ወደ አካይያ ሄደ በዚያም "ከጸጋው የተነሣ አምነው ለነበሩት ትልቅ ረዳት ሆናቸው" (ቁ. 27)።

ኢየሱስ ስለ ራሱ የተቀባ ስብከትና ትምህርት ሲናገር፣ "እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስም ሕይወትም ነው" (ዮሐንስ 6፡63) ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያትን ስብከት ሲገልጽ ሐዋርያትም ስለ ጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ በታላቅ ኀይል መመስከራቸውን ቀጠሉ፤ በሁላቸውም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበር" (ሐዋ. 4፡33)። በሁላቸውም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበር" የሚለው ሐረግ የመንፈስ ቅዱስን ቅባት በትክክል ይገልጻል። በሐዋርያት ሥራ፣ በሰባኪ ላይ ያለው የመንፈስ ቅባት የሚሰሙ ሰዎችን ልብ ይነካ ነበር (ሐዋ. 2፡4፣ 14 ከ1ቆሮ. 2፡4፣ የሐዋርያት ሥራ 2፡37 ከ1ቆሮ. 2፡5 ጋር)።

ጳውሎስ በመልእክቶቹ ውስጥ ስለ ራሱ መንፈስ ስለተቀባ ስብከት ተናግሯል። በመጀመሪያ ወንጌልን እንዴት እንደሰበከላቸው ለቆሮንቶስ አማኞች አስታወሳቸው "ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኀይል በመግለጥ እንጂ፣ በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም፤" (1ቆሮ. 2፡4-5) ሲል ጽፏል። በሮሜ ላሉ አማኞች አገልግሎቱን ሲገልጽ፡- "ይህም የሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፣ በምልክቶችና በታምራት ነበር። በዚህም ሁኔታ... የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ" (ሮሜ. 15፡19)። በተሰሎንቄ ላሉ አማኞች "ወንጌላችን ወደ እናንተ የመጣው በኀይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙም መረዳት እንጂ በቃል ብቻ አይደለም" (1ኛ ተሰ. 1፡5) በማለት አሳስቧቸዋል።

መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ኢየሱስንና ሐዋርያትን እንደቀባው ሁሉ ዛሬም ስብከታችንን ሊቀባ ተዘጋጅቷል። ይሁን እንጂ የቅብዓቱ ምንጭ ምንድን ነው? እንዴት ልናገኘው እንችላለን ?

# የቅባቱ ምንጭ

በመንፈስ ቅባት ለመስበክ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ምንጩን መረዳት አለበት። የቅብዓቱ ምንጭ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እና በኃይል መገኘት ነው። በሰባኪውም ላይ እና በውስጡ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ. 14፡17፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡8)። ይህን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የምንቀበለው አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ እና ሲሞላ ነው (ሐዋ. 2፡4)። አንድ ሰው "ከመንፈስ ጋር ሲèዝ" ቅባቱ በዘላቂነት በእርሱ ላይ ይኖራል (ገላ. 5፡25)። ይህ እውነት በኢየሱስና በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ ተገልጧል።

## የኢየሱስ ቅባት ምንጭ

ኢየሱስ የቅባቱ ምንጭ የጌታ መንፈስ መሆኑን አረጋግጧል (ሉቃስ 4፡18)። ምንም እንኳን እርሱ በእውነት በሥጋ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፣ ከመለኮታዊ ኃይሉ እና መብቶች እራሱን ባዶ ማድረግ እና አገልግሎቱን በመንፈስ ኃይል ማከናወንን መረጠ (ፊልጵ. 2፡5-8)። ስለዚህ የኢየሱስ በመንፈስ የተቀባ አገልግሎት እርሱን ለሚከተሉ ሁሉ አርዓያ ይሆናል።

ኢየሱስ በመንፈስ እስኪቀባ ድረስ አገልግሎቱን አልጀመረም። የመንፈሱ ጥምቀት የተከናወነው ዮሐንስ በውኃ ካጠመቀው በኋላ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ "[ኢየሱስ] እየጸለየ ሳለ መንፈስ ቅዱስም በአካላዊ ቅርጽ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ " (ሉቃስ 3፡21-22) ይላል። ከዚያም ኢየሱስ "አገልግሎቱን ጀመረ" (ቁ. 23)። በመንፈስ ኃይል መንቀሳቀስ እና ማገልገል ጀመረ (ሉቃስ 4፡1፣ 14)።

"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች ወንጌልን እንድሰብክ ቀብቶኛልና" (ሉቃስ 4፡18) በማለት አስታወቀ። በኋላ፣ ሰዎቹ የኢየሱስን ንግግር ሲሰሙ፣ "ከአንደበቱ በሚወጣው ከጸጋው ቃል ተገረሙ" (ቁ. 22)። "የሚናገረው በሥልጣን ስለ ነበር በትምህርቱ ተደነቁ" (ቁ. 32፤ ማቴ. 7፡28-29)።

## የሐዋርያት ቅባት ምንጭ

መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ የተቀባ አገልግሎት ምንጭ እንደሆነ ሁሉ ለሐዋርያትም የቅባት አገልግሎት ምንጭ ነበር። ልክ እንደ ኢየሱስ፣ ሐዋርያትም በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ። ከዚያም በኃይል መስበክ ጀመሩ።

ጴጥሮስ ለዚህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ከሁሉ የተሻለው ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ከጴንጤቆስጤ በፊት፣ ጴጥሮስ ኢየሱስን በአንዲት ሴት አገልጋይ ፊት ከእየሱስ ጋር ነኝ ብሎ ለመመስከር ፈርቶ ነበር (ማቴ. 26፡ 69-72)። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ በኃላ በኃይል ሰበከ፣ ስብከቱ የሰሚዎቹን ልብ ነካ (ሐዋ. 2፡37)። በውጤቱም፣ ሦስት ሺህ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መጡ። ይህ ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ (4፡8፣ 31-33) ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደግሟል።

ኢየሱስና ሐዋርያቱ በኃይል እንዲሰብኩ ያስቻላቸው ያው ቅባት ዛሬ ለእኛ ተሰጥቶል።

# ቅባቱን መለማመድ

ከቅባት ጋር በተገናኘ መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች፡- "አንድ ሰው ዛሬ የመንፈስ ቅዱስን ቅባት እንዴት በእውነት ሊለማመድ ይችላል? ቅባቱ እንዴት ሊቀበል ይችላል? በአገልግሎት እንዴት ይገለጣል? እንዴትስ ማቆየት ይቻላል? የሚሉት ናቸው፡፡

## ቅባቱን መቀበል

ቅባቱን የምንቀበለው ኢየሱስና የቀደምት ደቀ መዛሙርት በተቀበሉት መንገድ ነው። መጀመሪያ ላይ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ ቅባቱን ይቀበላል። ከላይ እንደተገለጸው፣ ኢየሱስ በጥምቀቱ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል። ከዚያም በስልጣን ማገልገል ጀመረ። ለደቀመዛሙርቱም ሁኔታው ተመሳሳይ ነበር። በመጀመሪያ መንፈስን የተቀበሉት በጴንጤቆስጤ ቀን ነው። ቀጥሎ እንደ ኢየሱስ እነርሱም በኃይል ማገልገል ጀመሩ።

ኢየሱስ አንድ ሰው መንፈስን እንዴት እንደሚቀበል ግልጽ መመሪያ ሰጥቷል። ለደቀ መዛሙርቱ "የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ!" አላቸው (ሉቃስ 11:13)። ሲያስረዳም "ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤10 ምክንያቱም የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ በር ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል" ብሏል(ቁ. 9-10)። መንፈስ ቅዱስን የምንቀበለው በእምነት በመጠየቅ (ቁ. 9)፣ በእምነት በመቀበል (ቁ. 10 ከማርቆስ 11፡24) እና በእምነት በመናገር ነው (ሐዋ. 2፡4)።[1]

[1] በምዕራፍ 20 "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" ላይ መንፈስ ቅዱስን ስለመቀበል የበለጠ ተብራርቶል፡

## ቅባቱን መግለጥ

በመንፈስ ጥምቀት የተቀበልከው ቅባት በአገልግሎት የሚገለጠው በዋናነት በመንፈሳዊ ስጦታዎች ነው። በመንፈስ የተቀባ ስብከት እንደ የትንቢት ስጦታ ሊገለጥ ይችላል። የተቀባ ስብከት መንፈስ የተነሳሳ፣ በመንፈስ የተቃኘ ንግግር ነው። በመንፈስ የተቀባ ስብከት እንደ የእውቀት ቃላት እና የጥበብ ቃላት ያሉ የመገለጥ ስጦታዎችንም ሊያካትት ይችላል። በተጨማሪም በልስጥራ በጳውሎስ እንደሆነው በመንፈስ የተቀባ ስብከት ብዙውን ጊዜ ከኃይል ስጦታ መገለጥ ጋር አብሮ ይመጣል (ሐዋ. 14፡8-10)።[2]

መንፈስ ቅዱስን በመጠየቅ እና በእምነት ምላሽ በመስጠት ቅባቱን ማግኘት ይቻላል። ለስብከት ወደ መድረኩ ስትቀርብ፣ "መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ አሁን መጥተህ ቃልህን እንዳገለግል ቀባኝ" ብለህ መጸለይ አለብህ። እግዚአብሔር ጸሎትህን እንደ ሰማ በማመን በእምነት መንቀሳቀስ አለብህ። አንዴ የመንፈስን መገኘት ከተረዳህ፣ በእምነት ምላሽ ስጥ፣ ለእርሱ አመራር በመገዛት እና በስብከትህ እንዲደግፍህ እና ኃይል እንዲሰጥ በእርሱ ታመን።

## ቅባቱን መጠበቅ

ቅባቱ የሚጠበቀው በመንፈስ በመኖር እና በመመላለስ ነው (ገላ. 5፡25)። በመንፈስ የተመራ ጉዞ ለእግዚአብሔር እና ለተልእኮው የመገዛት ሕይወት ነው። ጸሎት፣ በልሳን አዘውትሮ መጸለይን ጨምሮ፣ ቅባትን ለመጠበቅ ቁልፍ ሚና አለው (ሮሜ. 8፡26-27፤ 1 ተሰ. 5፡17)።

# የተቀቡ ዝግጅት እና ማድረስ

ውጤታማ ፣ በመንፈስ የተቀባ ሰባኪ ለመሆን ያሚፈልግ ማንኛውም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለስብከት ዝግጅት እና ለስብከት አቀራረብ መጠንቀቅ አለበት። እርሱ ወይም እርሷ ለመንፈስ ቅዱስ መገኘት እና መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን ተግባር እየቀባ እና እየመራ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

## የስብከት ዝግጅት

የሐዋርያት ሥራን በጥልቀት መመርመራችን ሁለት ጉልህ እውነቶችን ያሳያል። የሐዋርያት መልእክት በቅዱሳት መጻሕፍት የተሞሉና በመንፈስ ቅዱስ የተቀቡ ናቸው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉ ሰባኪዎች ሰፊ የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት ነበሩዋቸው። በመልእክታቸው ውስጥ ብዙ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይጠቅሳሉ። ለምሳሌ፦ የጴጥሮስ የጴንጤቆስጤያዊ ስብከት አራት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ይዟል (ሐዋ. 2፡16-21፣ 25-28፣ 31፣ 34-35)። በተመሳሳይ፣ እስጢፋኖስ ለአይሁድ ሳንሄድሪን የላከው መልእክት ስምንት ጥቅሶችን ይዟል (ሐዋ. 7፡3፣ 6-7፣ 28፣ 32-35፣ 37፣ 40፣ 42-43፣ 49)። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉ ሌሎች ስብከቶችም ተመሳሳይ አካሄድ ነበራቸው። እነዚህ ቀደምት ሰባኪዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ተረድተው መልእክቶቻቸውን በዚያ መረዳት ላይ መስርተዋል።

ዛሬ በአፍሪካ ያሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያንም እንዲሁ ማድረግ አለባቸው። ልክ እንደ ሐዋሪያት ስብከታችንን በጸና ቅዱሳት መጻሕፍት መሰረት ላይ መጣል አለብን። ይህን ለማድረግ ራሳችንን ሥርዓት ላለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማስገዛት አለብን። ለመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ስብከት ዝግጅት በየሳምንቱ በቂ ጊዜ ልንሰጥ ይገባል። በምንዘጋጅበት ጊዜ፣ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ዝግጅትን እንደማይከለክል

---

[2] አባሪ 2፡ "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት።

ይልቁንም ውጤታማ እደሚያደርግ በመገንዘብ ሃሳባችንን እንዲቀባ እና እንዲመራ መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ አለብን።

በተጨማሪም፣ በሐዋርያት ሥራ ላይ ያሉ ሰባኪዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና መቀባትን እየተጠባበቁ ይጸልዩ ነበር። የሐዋርያት ሥራ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ከጸሎት ጋር ያገናኛል። ለምሳሌ፣ መንፈስ በጴንጤቆስጤ ዕለት ከመፍሰሱ በፊት ደቀ መዛሙርቱ ይጸልዩ ነበር (ሥራ 1:14፤ 2:1-4)። ከሁለተኛው የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በፊት የኢየሩሳሌም አማኞች በከተማይቱ ውስጥ ይጸልዩ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 4: 23-31) ፤ ጳውሎስ በመንፈስ ከመሙላቱ በፊት ጳውሎስና ሐናንያ ይጸልዩ ነበር (ሐዋ. 9፡5፣ 10-15)። ተጨማሪ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል።

መንፈስ ቅዱስ ስብከታችንን እንዲቀባ የምንፈልግ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ራሳችንን ለጸሎት መሰጠት አለብን። እንዲህ ዓይነቱ ቁርጠኛ ጸሎት የመንፈስን ቅባት ያመጣል፣ የስብከታችንን ጭብጥ እና አቀራረብ በእጅጉ ይለውጣል።

## የስብከት አቅርቦት

የስብከት አቀራረብ ዓላማ አድማጮችን ለማስደሰት ሳይሆን ሰዎች የመልእክቱን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው። የተነገረው ወይም የሚደረገው ነገር ሁሉ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኙ ለመምራት ያለመ መሆን አለበት። ለዚህ ግብ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ማናቸውም ቴክኒኮች ወይም ስልቶች መጎልበት አለባቸው። ከዓላማው የሚያዘናጋ ማንኛውም አካሄድ መወገድ አለበት።

ስለዚህ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ ሰባኪዎች፣ አካሄዳችን ትክክለኛ መሆን አለበት። ከመጮህ፣ ዓላማ የለሽ እንቅስቃሴ ከማድረግ መቆጠብ አለብን። ይልቁንም እንቅስቃሴዎቻችን ተፈጥሮዊ መሆን አለባቸው። እንቅስቃሴዎቻችን ከመንፈስ አሠራር እና ከመልእክቱ ይዘት በተፈጥሮ የሚመነጩ መሆን አለባቸው። በአእምሯዊ እና በስሜታዊነት ከመልእክቱ ጋር ከተዋሃደ፣ ተገቢ የሆኑ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ይህን ተከትለው ይመጣሉ።

በዚህ ሂደት ውስጥ የድህነት ጥሪ አስፈላጊ ነው። በዚህ ወሳኝ የስብከት ደረጃ፣ ሰባኪው በመንፈስ ቅዱስ ሊመራ ይገባዋል። የድህነት ጥሪ አዳዲስ ሀሳቦችን ወደ መልእክቱ የምንጨምርበት ጊዜ አይደለም። ሰባኪው ትኩረቱን ሊጠብቅ ይገባል ወደ ሌላ ጉዳዬች መሄድ የለበትም። ከዚህ ይልቅ እርሱ ወይም እርሷ ሕዝቡ እንዲያደርጉ የፈለጉት ላይ ግልጽ የሆነ መመሪያ መስጠት አለባቸው።

---

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በስብከታችን ላይ የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ዋጋ ስለምንሰጥ እና ስለምንፈልግ በሰባኪዎች ዘንድ ለየት ያደርገናል። ይህን በማድረግ፣ የኢየሱስን እና የአዲስ ኪዳን ሰባኪዎችን ምሳሌ እየተከተለን እንደሆነ እናምናለን። “ጌታ ሆይ ለአገልግሎት ሙላና ቀባኝ” የሚለው የሁልጊዜ ጸሎታችን መሆን አለበት።

# ~ ምዕራፍ 17 ~

# ውጤታማ ትምህርት

ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል" (ሆሴዕ. 4፡6)። ይህ በነቢዩ ሆሴዕ በኩል ለእስራኤል ካህናት የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእስራኤል መንፈሳዊ መሪዎች ለሕዝቡ እውነትን ማስተማር ባለመቻላቸው ሕዝቡ ውሸትን አምነው ነበር። በውጤቱም፣ ወደ ኃጢአት ጠልቀው በመግባት ተቅበዘበዙ። ነቢዩ ሁኔታውን ሲገልጽ "ታማኝነት የለም፤ ፍቅርም የለም፤እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድሪቱ የለም። በዚያ ያለው ርግማን፣ መዋሸት፣ መግደል፣መስረቅና ማመንዘር ብቻ ነው፤ቃል ኪዳንን ሁሉ ያፈርሳሉ፤ደም ማፍሰስና ግድያ ይበዛል" (ቁ. 1-2)።

በሚያሳዝን ሁኔታ፣ በአፍሪካ የሚገኙ በርካታ የጴንጤቆስጤያዊ ክርስቲያኖችም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። ስለ እግዚአብሔር ቃል ግልጽ የሆነ ግንዛቤ የላቸውም። ስለዚህ፣ መንፈሳዊ እድገታቸው ተዘግቷል። በዚህም ምክንያት ለሐሰት አስተማሪዎች በቀላሉ ሰለባ ሆነዋል። እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለመጋቢ በተጠራህበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደዚህ ያለ ሁኔታ አለመኖሩን ማረጋገጥ አለብህ።

## የመጋቢ ሀላፊነት

እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን መንጋ የመመገብን ታላቅ ሀላፊነት ይሸከማል። ጳውሎስ በኤፌሶን ካሉት የቤተ ክርስቲያን መጋቢያን ጋር ባደረገው የመጨረሻ ስብሰባ፣ "ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ኤጲስቆጶሳት አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ" (የሐዋርያት ሥራ 20፡28) በማለት አሳስቧቸዋል። ከዚያም እነዚህን መጋቢያን "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ" ሲል አዘዛቸው። ጳውሎስ የኤፌሶን መጋቢያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የእግዚአብሔር ቃል ቢያስተምሩዋቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደሚጠነክሩ ተረድቶ ነበር። ይህም

በቅርቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡትን፣ እውነትን የሚያጣምሙ እና ህዝቡን ከክርስቶስ ለመሳብ የሚሞክሩትን "ነጣቂ ተኩላዎችን" እንዲቃወሙ ያዘጋጃቸዋል (ቁ. 29-30)።

ማስተማር የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የመሆን አበይት መገለጫ ነው። ጳውሎስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ስለ ሰጣቸው አምስት የአገልግሎት ስጦታዎች ሲጽፍ፦ “አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞች አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ነው” (ኤፌ. 4፡ 11-12) በማለት ተናግሮአል፡፡

በዚህ ምንባብ፣ ጳውሎስ የመጨረሻዎቹን ሁለት የአገልግሎት ስጦታዎች ወደ አንድ እንዴት እንደቀላቀለ አስተውል። ጳውሎስ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ስጦታዎች እንዳደረገው “እረኞች እና አስተማሪዎች” ከማለት ይልቅ “እረኛ አስተማሪዎች” ብሏል (ይህን በደንብ የሚያሳየው የግሪኩ ቅጂ ነው)። በዚህ ምክንያት አንዳንድ ሊቃውንት ይህንን ስጦታ “መጋቢ-መምህር” ብለውታል። ነጥቡ ይህ ነው፡ አንድ ወንድ ወይም ሴት መጋቢ ከሆኑ እርሱ ወይም እርሷ አስተማሪም መሆን አለባቸው። እግዚአብሔር ወደ መጋቢ የጠራውን ሰው ፣ የማስተማር ስጦታም ሰጥቶታል።

በጎቹን በአግባቡ ለመንከባከብ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቃሉን በብቃት ለመመገብ መቻል አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ዳቦ (ማቴ. 4፡4)፣ ወተት (1 ጴጥ. 2፡2) እና ጠንካራ ምግብ ካሉ ምግቦች ጋር ያመሳስለዋል (ዕብ. 5፡12-14)። ህዝቡን የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ ያልቻለ መጋቢ ታማኝ ያልሆነ እረኛ ነው፣ እናም ለዚህ ውድቀት እግዚአብሔር ተጠያቂ ያደርገዋል (ያዕቆብ 3፡1፤ ሕዝ. 34፡1-6)።

ነገር ግን፣ የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ለሕዝቡ የምታስተምር ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ የክብር አክሊል አለህ (ማቴ. 24፡45-47)። ከሁሉም በላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ ብርቱዎች ይሆናሉ። ጳውሎስ “ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም። ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው” እንዳለው ነው (ኤፌ. 4፡14-15)።

## ደቀ መዛሙርት ማድረግ

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን “ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” (ማቴ. 28፡19) በማለት አዟል። እርሱ በእነርሱ ያደረገውን ደቀ መዛሙርትም እንዲያደርጉ እየነገራቸው ነበር። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሄዶ እውነትን አስተምሯቸዋል እንዲሁም እንዴት መኖር እንዳለባቸው አሳይቷቸዋል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን፣ በቤተክርስቲያናችን አባላትም እንዲሁ ማድረግ አለብን። ወደ እምነት ማምጣት ብቻ በቂ አይደለም ደቀ መዛሙርት ማድረግ አለብን። ደቀ መዝሙር የክርስቶስ ታማኝ ተከታይ ነው። እርሱ ወይም እርሷ በኢየሱስ እግር ስር ተቀምጠው ከእርሱ የሚማሩ ናቸው። ሰዎችን ክርስቶስን እንዲከተሉ መጥራት ብቻ ሳይሆን፣ ሁሉንም ትእዛዛቱን እንዲታዘዙ ማስተማር አለብን (ቁ. 20)።

## ስብከት እና ማስተማር

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ብዙ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እራሳቸውን እንደ ሰባኪ ይመለከታሉ ነገር ግን እራሳቸውን አስተማሪ አድርገው አይመለከቱም። እንደ መጋቢ እግዚአብሔር ሁለቱንም እንድትሆን ጠርቶኃል። በተመሳሳይ ጊዜ የተዋጣለት ሰባኪ እና ውጤታማ አስተማሪ መሆን አለብህ። የእግዚአብሔር

ሕዝብን የማስተማር ሥራህን በግልጽ ለመረዳት በስብከቱና በማስተማር መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ አለብህ።

መጽሐፍ ቅዱስ በእነዚህ ሁለት ሥራዎች መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ ያሳያል። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ "በምኵራቦቻቸው እያስተማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ቃል እየሰበከ፣ ...በመላው ገሊላ ይዘዋወር ነበር" ይላል (ማቴ. 4:23፣ አጽንዖት ተጨምሯል)። ስለ ጳውሎስና ስለ በርናባስ ሲናገር "ከሌሎች ብዙ ሰዎች ጋር ሆነው የጌታን ቃል እያስተማሩና እየሰበኩ በአንጾኪያ ተቀመጡ" ይላል (የሐዋርያት ሥራ 15:35፣ አጽንዖት ተጨምሯል)። ጳውሎስ በኤፌሶን የሚገኘውን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ጢሞቴዎስን "እኔ እስክመጣ ድረስ ለማንበብ፣ ለመምከርና ለማስተማር ትጋ" ሲል መክሯል (1 ጢሞ. 4:13፣ አጽንዖት ተጨምሯል)። እንግዲህ በስብከትና በማስተማር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ስብከት በዋነኝነት ሰዎችን በክርስቶስ ወደ እምነት የመጥራት ዓላማ ያለው የወንጌል አዋጅ ነው። ማስተማር ለክርስቶስ መኖር ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት ነው። ስብከት ማወጅ ነው ፤ ማስተማር ማብራራት ነው። ስብከት መግለጫን ማስተዋወቅ ነው ፤ ማስተማር መመሪያ መስጠት ነው። ሰባኪው ኃጥን በክርስቶስ ወዳለ እምነት ይጠራል ፤ መምህር የጌታን መንገድ ያስረዳቸዋል። የአስተማሪው አላማ የእግዚአብሔርን ህዝብ እንዴት በፍፁምነት እግዚአብሔርን ማገልገል እንዳለበት ማሳየት ነው። እንደ መጋቢ መምህር፣ ቅዱሳን መጻሕፍትን ለእግዚአብሔር ሕዝብ በጥንቃቄ ማስረዳት አለብህ። የሰሙትን ቃል በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስፈልጋቸውን መረጃ እና ግንዛቤ መስጠት አለብህ።

## የኢየሱስን ምሳሌ መከተል

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከሁሉ የሚበልጠውን አስተማሪ የኢየሱስን ምሳሌ ለመከተል መጣር አለብህ። ኢየሱስ ራሱን ብዙ ጊዜ "መምህር" ሲል ጠርቷል (ማቴ. 26፡18፤ ዮሐንስ 13፡13-14)። ሌሎችም እንዲሁ (ለምሳሌ፡ ማቴ. 8፡19፤ 12፡38፤ ሉቃ. 10፡25፤ ዮሐ. 11፡28)። ወንጌላት ብዙ ጊዜ ስለ ኢየሱስ የማስተማር አገልግሎት ዘግበዋል። (ለምሳሌ፡ ማርቆስ 1፡21-22፤ ሉቃስ 4፡31-32)። የኢየሱስ ትምህርት በረጅም የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች ተዘግበዋል። እነዚህ ክፍሎች የተራራው ስብከት (ማቴ. 5-7)፣ የደብረ ዘይት ንግግሩ (ማቴ. 24-25) እና የመጨረሻው ክፍል ንግግር (ዮሐ. 14-16) ያካትታሉ። ኢየሱስ የማስተማር አገልግሎቱን በቁም ነገር ከወሰደው እኛም ዛሬም እንዲሁ ማድረግ አለብን።

ኢየሱስ የማስተማር አገልግሎቱን እንዴት እንደፈፀመ ብዙ ማለት ይቻላል። ስለ እርሱ የማስተማር ዘዴዎች መጻሕፍት ተጽፈዋል። የእርሱ የማስተማር ዘዴ ሦስት ገጽታዎች ሊጠቀሱ ይገባል፦

**1. በሥልጣን አስተምሯል፡፡** መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር "እንደ ጸሓፍት ሳይሆን፣ እንደ ባለ ሥልጣን በማስተማሩ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ" (ማር. 1፡22) ይላል። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ስለተላከ እና እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል በመናገሩ ምክንያት በስልጣን አስተማረ። አብ ያስተማረኝን እንደምናገር፣ በራሴም ፈቃድ ምንም እንደማላደርግ ታውቃላችሁ" (ዮሐ. 8፡28) በማለት መስክሯል። በሥልጣን ለማስተማር ልክ እንደ ኢየሱስ አንተም የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ማስተማር አለብህ።

**2. በፍቅር አስተምሯል።** ኢየሱስ ያስተማራቸውን እጅጉን ይወዳቸው ነበር። ትምህርቱ፣ ለሰዎች ካለው ፍቅር የመነጨ ነበር። በአንድ ወቅት ኢየሱስ የደከሙና የተራቡ ብዙ ሰዎች አገኘ። "ባያቸው ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ስለ ነበሩም አዘነላቸው" ከዚያም ለእነርሱ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሣ "ብዙ ነገር ያስተምራቸው ጀመር" (ማርቆስ 6፡34)። በኋላ ምግብ መግቧቸዋል (ቁ. 35-44)። ነገር ግን በመጀመሪያ ትልቁ ፍላጎታቸው የሆኖውን የእግዚአብሔርን ቃል ነበር የመገባቸው።

በሌላ ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በአንድ ሰገነት ውስጥ ተገኘ። መጽሐፍ ቅዱስ “ኢየሱስም ይህን ዓለም ትቶ ወደ አብ የሚሄድበት ጊዜ እንደ ደረሰ ዐወቀ። በዓለም የነበሩትን፣ የራሱ የሆኑትን ወደዳቸው፤ በፍጹም ፍቅሩም ወደዳቸው” ይላል (ዮሐንስ 13:1)። ለእነርሱ ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሣ፣ እና እነርሱ ራሳቸው በቅርቡ የመሪነትን ኃላፊነት ስለሚቀበሉ፣ ስለ አገልጋይ አመራር ትምህርት አስተማራቸው (ቁ. 2-17)።

ከላይ በተነሱት በሁለቱም አጋጣሚዎች ኢየሱስ ሀዋሪያት ለሰዎች ያላቸውን ፍቅር እንዲያሳዩ አነሳስቶታል። በተመሳሳይ መልኩ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንድትመራ የተሰጠህን ሕዝብ መውደድ አለብህ። ይህ ፍቅር የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት እንድታስተምራቸው ሊያነሳሳህ ይገባል። ለሕዝብህ ፍቅር ከሌለህ፣ ቃላቶችህ “እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል” (1 ቆሮ. 13:1) ሊሆኑ ይችላል።

**3. በመንፈስ ኃይል አስተምሯል።** ኢየሱስ በአንድ ወቅት የማስተማር አገልግሎትን ምንነት ለደቀ መዛሙርቱ ገልጿል። “እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስም ሕይወትም ነው” ብሏል (ዮሐ. 6:63)። የኢየሱስ ቃላቶች በመንፈስ እና በህይወት የተሞሉ ነበሩ ምክንያቱም እርሱ ራሱ መንፈስ እና ህይወትን የተሞላ ነው። አገልግሎቱን የጀመረው በመንፈስ ቅዱስ በመቀባት ነው (ሉቃስ 3:21-22፤ 4:18-19)። ከዚያም የማስተማር አገልግሎቱን በመንፈስ ኃይል ያከናውን ነበር (ሉቃስ 4:14-15)።

ኢየሱስ ያስተማረው በቃላት ብቻ ሳይሆን የመንፈስን ኃይል በመግለጥ ጭምር ነው (ሉቃስ 5:17)። ቃሉ በመንፈስ ኃይል ስለተሞላ፤ ሲያስተምር አጋንንት ይጮኹ ነበር “የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፤ ከኛ ምን ትሻለህ? ልታጠፋን መጣህን? እኔ ማን እንደሆንህ ዐውቃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ!” (የማርቆስ ወንጌል 1:24) ኢየሱስ ጋኔኑን ከሰውዬው ውስጥ ሲያወጣ፣ ሕዝብ “ይህ ነገር ምንድን ነው? ሥልጣን ያለው አዲስ ትምህርት መሆኑ ነው! ርኩሳን መናፍስትን እንኳ ያዛል፤ እነርሱም ይታዘዙለታል!” ይሉ ነበር (ቁ. 27)።

ኢየሱስ የማስተማር አገልግሎቱን ለደቀ መዛሙርቱ አስተላልፏል (ማቴ. 28:19-20)። እርሱን በመመልከት ሌሎችን እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ ተምረዋል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን። የኢየሱስን የማስተማር አገልግሎት ለመለማመድ ጥረት ማድረግ አለብን።

# መጋቢ እንደ ዋና መምህር

እንደ መጋቢ እንድትመሩ በተጠራችሁበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የ“ዋና መምህር” ኃላፊነትን መወጣት አለብህ። በሌላ አነጋገር፣ አንተ ራስህ የተካነ የቃሉ አስተማሪ መሆን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዲያደርጉ በትጋት ማሰልጠን አለብህ። ኢየሱስና ሐዋርያቱ ያደረጉት ይህንኑ ነው። እንደ ዋና መምህርነት ሶስት ዋና ዋና ኃላፊነቶች አሉህ:- (1) የራስህ የማስተማር አገልግሎት ማዳበር አለብህ። (2) የሌሎችን የማስተማር ችሎታ ማዳበር አለብህ እና (3) የቤተ ክርስቲያንን የማስተማር አገልግሎት ማደራጀት አለብህ። እያንዳንዳቸውን እነዚህን ኃላፊነቶች እንመልከት:-

## እራስን ማዳበር

በመጀመሪያ፤ የቤተ ክርስቲያን ዋና መምህር እንደመሆንህ የራስህን የማስተማር አገልግሎት ለማሻሻል መጣር አለብህ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ አንድ መጋቢ "ማስተማር የሚችል” መሆን አለበት ይላል (1 ጢሞ. 3:2)። ወይም በሌላ ትርጉም እንተገለጸው አንድ መጋቢ “በማስተማር የተካነ”

መሆን አለበት። ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች በጻፈው ደብዳቤ ላይ የማስተማር ተሰጥኦ ያላቸው ሁሉ ይህንን ስጦታ በታማኝነት ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ተናግሯል (ሮሜ. 12፡6-8)። ይህ ማለት እንደ መምህ ችሎታቸውን ለማዳበር በትጋት መጣር አለባቸው። የማስተማር ችሎታ እንደ መንፈሳዊ ስጦታ ቢሰጥም በትምህርት ክህሎት መዳበር አለበት። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የዕድሜ ልክ የእግዚአብሔር ቃል ተማሪ መሆን አለብህ። የማስተማር ችሎታህን ለማዳበር ጠንክረህ መሥራት አለብህ (2ጢሞ. 2፡15)።

አንድ ሰው ማስተማር ከመናገር፤ ከመማር ደግሞ ከመስማት በላይ ነው ሲል በትክክል አስቀምጦታል። የማስተማር የመጨረሻ አላማ በተማሪዎች ህይወት ላይ ለውጥ ማምጣት ነው። ስለዚህ ውጤታማ የሆነ የማስተማር ሂደት የተማርናቸውን እውነቶች መተግበርን ይጨምራል። በዚህ ምክንያት የምናገለግለውን ሕዝብ ቃላችንን ብቻ ስለሰሙ መርካት የለብንም። ልንረካ የሚገባው ህይወታቸው ሲለወጥ ስናይ ብቻ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት ብቻ ሳይሆን አማኞች የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት በሕይወታቸው ላይ እንዲተገብሩ መርዳት አለብን።

በተጨማሪም፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ከንግግራችን ይልቅ ብዙ ጊዜ በድርጊታችን እንደምናስተምር መረዳት አለብን። ጳውሎስ ይህንን እውነት ተረድቷል። ስለዚህም የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን “እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል እናንተም የእኔን ተከተሉ” ሲል ጥሪውን አስተላልፎአል (1 ቆሮ. 11፡1)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ "በሚገባ የተማረ ሰው ሁሉ እንደ መምህሩ ይሆናል” (ሉቃስ 6:40) ሲል ይህንኑ መሠረታዊ መርህ እያነሳ ነበር። ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን ምሳሌ በመሆን ለሌሎች የምናስተምራቸውን ነገሮች በተግባር ልናውል ይገባናል።

### ሌሎችን ማዳበር

ሁለተኛ የቤተ ክርስቲያን ዋና መምህር እንደመሆንህ የሌሎችን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የማስተማር ችሎታ ለማዳበር መሥራት አለብህ። ቤተ ክርስቲያን ስታድግ እና ስትበስል የሚፈጠሩ አገልግሎቶችን እንዲመሩ መሪዎች ያስፈልጋሉ። ጥሩ ለመምራት እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ መሠረታዊ የማስተማር ችሎታዎችን ማዳበር ይኖርበታል። እያንዳንዱ አዲስ መሪ በጥሩ ሁኔታ ለመምራት የሚያስፈልገውን ስልጠና ማግኘቱን ማረጋገጥ አለብህ።

ይህንን ሲያደርጉ መሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደሚያጠኑና በትክክል እንደሚተረጉሙ ማስተማር አለብህ። የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች እንዴት ማዘጋጀት እና ማስተማር እንደሚችሉ ልታሳያቸው ይገባል። እነዚህን ነገሮች ካደረግህ፣ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ብቁ አስተማሪዎች ይኖራታል። መሪዎች እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው ማስተማር ካልቻልክ፣ የቤተ ክርስቲያን የደቀ መዝሙርነት አገልግሎት ይዳከማል፤ መንፈሳዊ እድገቷም ይጎዳል።

## ቤተ ክርስቲያንን ለትምህርት አገልግሎት ማደራጀት

በመጨረሻም፤ ዋና አስተማሪ እንደመሆንህ መጠን ለክርስቲያናዊ ትምህርት የጉባኤው ዋና ተሟጋች መሆን አለብህ። በጥንቃቄ ማደራጀት እና የቤተ ክርስቲያንን የማስተማር አገልግሎት ማስተዋወቅ አለብህ። በተጨማሪም በጉባኤው ውስጥ ያለ እያንዳንዱን ሰው በቤተ ክርስቲያን የማስተማር አገልግሎት እንደሚያሳትፍ ማረጋገጥ አለብህ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥልጠና መርሃ ግብሮች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው።

## የጎልማሶች የሰንበት ትምህርት ቤት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከየጎልማሶች የሰንበት ትምህርት የበለጠ የሥልጠና ፕሮግራም የለም። ሰንበት ትምህርት ቤት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጉባኤው ውስጥ ላሉ በሁሉም የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሰዎች የሚደርስ ብቸኛው አገልግሎት ነው። ስለዚህ የምትመራው ቤተ ክርስቲያን በሚገባ የተደራጀ በበጀት የተደገፈ የጎልማሳ ሰንበት ትምህርት መርኃግብር እንዲኖራት መሥራት አለብህ። በተጨማሪም የጎልማሳ ሰንበት ትምህርት መምሪያው በብቁ ሰው መመራቱን ማረጋገጥ አለብህ። የዚህ አገልግሎት ትልቅ ጠቀሜታ ስላለው፣ በትምህርት መርኃግብሩ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለብህ። እእንቅስቃሴዎቹን መከታተል እና ውጤታማነቱን ለማሻሻል መጣርም አለብህ።[1]

## ከቤት ሕብረት ቡድኖች

በትክክል ከተሰራ የቤት ሕብረት ቡድኖች ሌላ ውጤታማ የደቀ መዝሙርነት ስልጠና መንገዶች ናቸው። እነዚህ ቡድኖች ለሕብረት፣ ለጸሎት እና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በየሳምንቱ ቤተ ክርስቲያን አባላት ቤት ይሰበሰባሉ። እንደ ዋና መምህር፣ እያንዳንዱ የቤት ሕብረት ቡድን በታማኝ እና በአግባቡ በሰለጠነ መሪ መመራቱን ማረጋገጥ አለብህ። በተመረጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርዕስ ላይ ግልጽ ውይይት ለማድረግ በእያንዳንዱ የቤት ሕብረት ቡድን የስብሰባ ጊዜ መመደብ አለብህ። አንተ ወይም የወከልከው ሰው በእያንዳንዱ የቤት ሕብረት ውስጥ ያለውን የትምህርት ሂደት በቅርበት መከታተል አለብህ። ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።[2]

## የአገልግሎት ዘርፎች

የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዘርፎች የደቀ መዝሙርነት ማሰልጠኛ እንደሆኑ ሊታዩ ይገባል። እነዚህ የአገልግሎት ዘርፎች የወንዶች አገልግሎት፣ የእህቶች አገልግሎት፣ የወጣቶች አገልግሎት፣ የልጆች አገልግሎት እና ሌሎችም ናቸው። ይህ የአገልግሎ ዘርፍ በሚሰበሰብበት ጊዜ ተግባራዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መማር ይኖርባቸዋል።

## የአገልግሎት ትምህርት ቤት

እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሚያገለግልበት አጥቢያ የአገልግሎት ትምህርት ቤት ስለ መስጠት ሊያስብ ይገባል። የአገልግሎት ትምህርት ቤት አላማ "ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ነው" (ኤፌ 4:12)። አላማው ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎ ሰራተኞችን ማሰልጠን ነው። በዚህ ትምህርት ቤት መጋቢው ተግባራዊ የሆኑ ትምህርቶችን ለምሳሌ መስበክ፣ ማስተማር፣ ጸሎት፣ ምስክርነት፣ ቤተ ክርስቲያን ተከላ፣ መሪነት ወዘተ ያስተምራል። እንዲ አይነት ስልጠና ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ በቂ የሰለጠኑ ሰራተኞች እንዲኖራት ያደርጋል።

ቤተ ክርስቲያን ስታድግ እና ስትሰፋ ይህን የመሰለውን ኃላፊነትህን ምናልባት ለሌላ ሰው ማጋራት ያስፈልግህ ይሆናል። ሆኖም እንደ ቤተ ክርስቲያን ዋና መምህር የቤተ ክርስቲያንን የትምህርት እና የደቀ መዝሙር አገልግሎ ጋር ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብሃል።

---

[1] የአፍሪካ ተስፋ በእውነት መኖር ተከታታይ በሰባት ዓመታት ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት ተማሪዎችን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያጠኑ ታስቦ የተዘጋጀ የጎልማሳ ሰንበት ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት ነው። በ https://africaats.org/resources/ ላይ በነፃ ማውረድ ይገኛል።

[2] የአፍሪካ ተስፋ የእምነት ሥር ተከታታይ ወቅታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሥርዓተ ትምህርት ነው https://africaatts.org/resources/ ላይ በነፃ ማውረድ ይችላል።

---

ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ጴጥሮስን፣ “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን?” ብሎ ጠየቀው። ጴጥሮስም ሦስት ጊዜ፣ “አዎን ጌታ ሆይ፣ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ” ሲል መለሰ። ኢየሱስም “ጠቦቶቼን ጠብቅ” ወይም “በጎቼን ጠብቅ” ሲል መለሰ (ዮሐንስ 21:15-18)። ጴጥሮስ በእውነት ኢየሱስን የሚወድ ከሆነ፣ ጌታው ያዘዘውን ያደርጋል፤ የእግዚአብሔርን መንጋ በታማኝነት ይመግባል።

ዛሬም፣ ኢየሱስ በመላው አፍሪካ የሚገኙ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን “ትወዱኛላችሁ?” የሚል ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠይቃቸዋ። ጴጥሮስን “በጎቼን ጠብቅ” ሲል የሰጣቸውን ትእዛዝ ይሰጣቸዋል። ለፍቅራቸው ማረጋገጫ፣ ኢየሱስ እነዚህን መጋቢያን ኃላፊነታቸውን በቁም ነገር እንዲወስዱ አዟል። በመሆኑም የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት በማስተማር ህዝቡን መንከባከብ አለባቸው።

# ~ ምዕራፍ 18 ~

# ቤተ ክርስቲያንን በአምልኮ መምራት

በማዕከላዊ አፍሪካ ሃገር፣ አንድ ወጣት አገልጋይ በእድሜ ከገፋ መጋቢ ስር አገልግሎት እንዲሰጥ ተመደበ። በመጀመሪያው እሁድ መጋቢው ወጣቱን አምልኮ እንዲመራ ጠየቀው። ወጣቱ ግን አልተደሰተም። ስብከት መስበክ ነበር ፍላጎቱ። አምልኮን መምራት እንደ መጋቢነቱ የሚመጥነው አልመሰለውም። በተጨማሪም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ስለነበር፣ መጸለይ ወይም ሌላ ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልገው አልተረዳም ነበር።

እንደሚጠበቀው፣ በእሁድ ጠዋት ወጣቱ የመራው የአምልኮ ሥርዓት ጥሩ አልነበረም። የቀድሞው መጋቢ ጥበብ የተሞላበት ጣልቃ ገብነት ባይሆን ኖሮ አገልግሎቱ ይበላሽ ነበር። የቀድሞው መጋቢም ቢሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአምልኮ መሪ በጥንቃቄ መምረጥ እንዳለበት ተረዳ። አሁን በሳል የሆኑ በአግባብ የሰለጠኑ የአምልኮ መሪዎች ብቻ ማገልገል እንዳለባቸው ያምናል።

ቤተ ክርስቲያንን ወደ እውነተኛው አምልኮ መምራት ጥልቅ መንፈሳዊ ተግባር ነው። ክህሎትን፣ ዝግጅትን እና መንፈሳዊ ብስለትን ይጠይቃል። ንጉሥ ዳዊት ይህን ተረድቶ ነበር። ስለዚህም ሕዝቡን በምስጋናና በአምልኮ የሚመሩ ከሌዋውያን መካከል ብቻ እንዲመረጡ አደረገ (1 ዜና 15፡16)። አንድ መጋቢ ሰዎችን አምልኮ እንዲመሩ ሰዎችን ሊመርጥ ቢችልም፣ የተመረጡት ሰዎች በቃሉ እና በመንፈስ በመመራት አምልኮውን የመምራት ኃላፊነታቸውን ፈጽሞ ቸል ሊሉ አይገባም።

## የእውነተኛ አምልኮ ይዘት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዕብራይስጥ እና የግሪክ ቃላት አምልኮ ማለት ለእግዚአብሔር መስገድ እና እጅ መንሳት ማለት ነው። ቃላቶቹ አንድ ሰው ለእርሱ ያለውን ምስጋና በትህትና የመግለጽ እና እርሱን ለቅድስናው፣ ለክብሩ እና ለኃይሉ ከፍ የማድረግን ሃሳብ ያስተላልፋሉ (ኢሳ. 6፡1-3፤ ራዕ. 7፡11-12)።

## በመንፈስ እና በእውነት የሆነ አምልኮ

ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት የእውነተኛን አምልኮ ምንነት ገልጿል፡- “በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤ አብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን ይፈልጋል። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል” (ዮሐ. 4፡23-4)። በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ኢየሱስ ስለ እውነተኛው አምልኮ አራት ጥልቅ እውነቶችን ገልጿል፡-

1. **እግዚአብሔር መንፈስ ነው።** እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ በጊዜ ወይም በቦታ አይገደብም። ስለዚህም በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊመለክ ይችላል።
2. **እግዚአብሔር እውነተኛ አምላኪዎችን ይፈልጋል።** እርሱን የሚፈልገው ውጫዊ መልክና ሥርዓት ሳይሆን ከልባቸው በጥልቅ የሚያመልኩትን ሰዎች ነው (ማር. 12፡33)።
3. **እውነተኛ አምልኮ በመንፈስና በእውነት መከናወን አለበት።** እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ የሚያመልኩት በመንፈስ ሊሰግዱለት ይገባል። እርሱ ፍፁም እውነት ስለሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት በተገለጠው መሠረት እርሱን ማምለክ አለባቸው።
4. **ጊዜው አሁን ነው።** እግዚአብሔርን በመንፈስ እና በእውነት የምናመልክበት ጊዜ አሁን ነው።

አምልኮ በራዕይ 4 ላይ እንደ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች ለእግዚአብሔር መገኘት ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ቅዱስ ተግባር ነው። አራቱ ሽማግሌዎች በክርስቶስ መገኘት ተገርመው "በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ሰገዱለት" (ቁ. 10)። የእግዚአብሔር ሰዎች እርሱን በሚያመልኩበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር እርሱን የበለጠ ያመልኩት ዘንድ በመካከላቸው መገኘቱን የበለጠ ይገልጣል።

## የጴንጤቆስጤያዊያን ተስፋዎች

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የጴንጤቆስጤያዊ አምልኮን ልዩ ባህሪ መረዳትህ በጣም አስፈላጊ ነው። የጴንጤቆስጤያዊ አምልኮ ልዩ የሚያደርገው ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ቅዱስ መገናኘትን አጽንዖት ስለሚሰጥ ነው። ስለዚህ ጴንጤቆስጤያዊያን ከብዙ ጴንጤቆስጤያዊ ካልሆኑት በተለየ መጠባበቅ ወደ አምልኮ ይመጣሉ። ብዙ ጴንጤቆስጤያዊ ያልሆኑ ሰዎች ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ወይም ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ለመፈጸም ዓላማ ይዘው ወደ አምልኮ ሊገብ ይችላሉ። እውነተኛው ጴንጤቆስጤያዊ ግን ወደ አምልኮ የሚገባው የተለየ አላማ አለው። የእርሱ ወይም የእርሷ አላማ ሕያው የሆነውን ክርስቶስን መገናኘት ነው፣ እናም በአምልኮ ባገኘው ክርስቶስ ፣ በመንፈሱ መለወጥ ይችላል (2ቆሮ. 3፡17-18)።

ይህ ለውጥ ትንሽ ወይም ትልቅ፣ ረቂቅ ወይም የገዘፈ ሊሆን ይችላል። ስውር ለውጥ፣ አማኙ ክርስቶስን በአምልኮ ሲያገኘው፣ እርሱን ለማገልገል የታደሰ ብርታት እና ደስታን በማግኘቱ የመከሰት ነው። የበለጠ አስገራሚ ለውጥ ሚሆነው አምላኪው ከሞት ከተነሳው ክርስቶስ ጋር ሲገናኝ እና በተአምራዊ ሁኔታ መፈወስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ሊሆን ይችላል።

እንዲህ ያለው ለውጥ የሚመጣው በሁለት መንገዶች ነው፡፡ በመንፈስ እና በእውነት (ዮሐ. 4፡23)። አምላኪዎች ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ እርሱ መገኘቱን ይገልጣል። ለእግዚአብሔርን መገለጥና መገኘት (በመንፈስ አምልኮ) በእምነት ምላሽ ሲሰጡ ወደ ክርስቶስ መልክ ይለወጣሉ (2ቆሮ. 3፡17-18)። በተጨማሪም፣ ለተሰበከው ቃል (በእውነት አምልኮ) በእምነት ምላሽ ሲሰጡ፣ የበለጠ ይለወጣሉ።

# ቤተ ክርስቲያንን ለአምልኮ ማዘጋጀት

እንደ መጋቢ፣ እግዚአብሔርን በእውነት እንድታመልክ ቤተ ክርስቲያንን የማዘጋጀት ኃላፊነት ያንተ ነው። ህዝቡ በመንፈስ እና በእውነት የማምለክን ምንነት ማወቁን ማረጋገጥ አለብህ። በተጨማሪም ሕዝቡ እንዲህ ዓይነቱን አምልኮ እየተለማመዱ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ። ይህንን በሦስት መንገዶች ማከናወን ትችላለህ-

## ስለ አምልኮ በማስተማር

በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አምልኮ የሚናገረውን ለቤተ ክርስቲያን ማስተማር አለብህ። ይህንንም በስብከቶች፣ በምክሮች እና በተከታታይ ትምህርቶች አማካኝነት ማድረግ ትችላህ። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ህዝቡን እንዴት በመንፈስ እና በእውነት ማምለክ እንዳለበት ማስተማር ከሚችልባቸው ምርጥ መንገዶች አንዱ በተግባር ማሳየት ነው። ህዝቡ እረኛው እግዚአብሔርን አጥብቆ ሲያመልክ መመልከት አለበት። አንድ መጋቢ በአንድ ወቅት ለሌሎች ወጣት መጋቢያን "እግዚአብሔርን በቅንነት የምታመልከው ከሆነ ሰዎችህ ይከተሉሃል እና እነርሱም በተመሳሳይ ያመልኩት ይጀምራሉ" ብሏል።

በተጨማሪም፣ ለሰዎች በአኗኗራቸው እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚችሉ በምሳሌነት ማሳየት አለብህ። ይህንን በቅድስና ሕይወት በመምራት እና ለሌሎች የመንፈስ ቅዱስ በረከቶች መተላለፊያ በመሆን ማድረግ ትችላለህ።

## የአምልኮ አገልግሎቶችን በመከታተል

ሁለተኛ፣ የበላይ ተመልካች በመሆንህ የአምልኮ ሥርዓቶችን በጸሎት መከታተል አለብህ። ይህ ህዝቡ በእውነት እግዚአብሔርን በመንፈስ እና በእውነት እንዲያመልኩ መመራታቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ያሉት ነገሮች ሁሉ "በተገቢው እና በሥርዓት" እንዲከናወኑ መጠበቅ አለብህ (1 ቆሮ. 14፡40)። በሌላ አነጋገር፣ አምልኮ እግዚአብሔርን በእውነት በሚያስከብር እና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በሚያቀርብ መንገድ መተግበር አለብህ (1ቆሮ. 10፡31)።

## የአምልኮ ቡድኑን በመምራት

ሦስተኛው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በመንፈስ እና በእውነት ማምለኳን የምታረጋግጥበት መንገድ የአምልኮ ቡድንህን በፍቅር በመምከር ነው። የእነርሱ ድርሻ ጉባኤውን በእውነት በመንፈስ ወደ ሚመራ ውዳሴና አምልኮ መምራት መሆኑን ልታስተምራቸው ይገባል። ስለዚህ እግዚአብሔርን በእውነት እንዴት ማምለክ እንዳለባቸው በማስተማር እና ሌሎችን ወደ እውነተኛው አምልኮ እንዴት መምራት እንደሚችሉ በማሳየት ከእነርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ አለብህ።

በተጨማሪም፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን እና የመንፈስን ምሪት እንዴት መከተል እንደሚችሉ ያውቁ ዘንድ፣ ከአምልኮ ቡድን አባላት ጋር ብዙ ጊዜ መጸለይ አለብህ። እንዲሁም ቡድኑ መንፈሳዊ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መዝሙሮችን መምረጡን ማረጋገጥ አለብህ። እንደ መጋቢ፣ ሁሉንም አዳዲስ መዝሙሮች በአምልኮ አገልግሎት ውስጥ ከመጠቀም በፊት አስቀድመው የማየት እና የመከታተል መብትህን አስጠብቅ።

በተጨማሪም፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስ ቀጥሎ፣ የቤተ ክርስቲያን ዋና የአምልኮ መሪ እንደሆንክ ሁል ጊዜ ልብ ማለት ይገባሃል። ይህ ማለት ግን ሕዝቡን በምስጋናና በአምልኮ ሁል ጊዜ ትመራላህ ማለት አይደለም። ይልቁንም አገልግሎቱ ሁል ጊዜ በአንተ ኃላፊነት ስር ነው ማለት

ነው። የአምልኮ ቡድኑ አንተ እንደ መጋቢ፣ በማንኛውም ጊዜ አገልግሎቱን መቀበል እና መምራት እንደምትችል መረዳት አለባቸው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የአምልኮ ቡድኑ ወዲያውኑ አገልግሎቱን ለአንተ መተው መልመድ አለበት።

በመንፈስ እና በእውነት ውስጥ እውነተኛ አምልኮ ሲከሰት፣ ኃይለኛ በረከቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ፣ እግዚአብሔር ይከበራል፣ የመንፈስ መገኘት ይገለጣል፣ እና የክርስቶስ አካልም ይበረታል።

# ቤተ ክርስቲያንን በአምልኮ መምራት

እነዚህን እውነቶች የተረዳው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተክርስቲያኑን በመንፈስ ወደተመራ አምልኮ ለመምራት ይጓጓል። ይህ ማለት በአምልኮ ጊዜ ውስጥ የመንፈስን ድምጽ በትኩረት ለመስማት መከታተል እና ምሪቱን ለመከተል ፈጣን መሆን አለብህ። ሙሴ በምድረ በዳ እንዳደረገው፣ ደመናው ሲንቀሳቀስ ቤተ ክርስቲያን እንድትንቀሳቀስ፣ ደመናውም በቆመ ጊዜ እንድታቆም ለመምራት ዝግጁ መሆን አለብህ (ዘጸ. 40፡34-38)።

## አበረታች ተሳትፎ

የቤተ ክርስቲያኑ መንፈሳዊ መሪ እንደመሆንህ፣ በጉባኤ ያሉ ሁሉም ሰዎች በአምልኮ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት አለብህ። እጆቻቸውን ወደ ላይ በማንሳት፣ በመዘመር፣ በዕልልታ፣ በማጨብጨብ፣ በማሸብሸብ፣ በመንበርከክ፣ በመመስከር፣ ወይም በማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስ የአምልኮ መግለጫ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ አበረታታ። ሕዝቡም አሥራታቸውንና መባቸውን ሲሰጡ እግዚአብሔርን እያመለኩ እንደሆነ ልታስተምራቸው ይገባል። ይህንንም በማድረግ በሀብታቸውና በበኩራታቸው እግዚአብሔርን ያከብራሉ (ምሳ. 3፡9)።

## መዘምራንን ማደራጀት

በተጨማሪም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የመዘምራን እና የሙዚቃ ተጫዋቾችን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች እና በስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲያገለግሉ ማበረታታት አለበት። እያንዳንዱ ቡድን ወይም መዘምራን በማንኛውም ጊዜ ለመጋቢ ወይም አምልኮ ከሚመራው አካል ጋር በመናበብ መቆየት አለባቸው። ስለዚህ ከአምልኮ ቡድኑ ጋር እንደሆነው ከዘማሪዎች እና ከሙዚቃ ተጫዋቾች ጋር በተመሳሳይ መልኩ አብረው መስራት አለብህ። ሙዚቃ በመጫወትና እና በመንፈስ ለሆነው አገልግሎት በመስራት መካከል ያለውን ልዩነት ልታስተምራቸው ይገባል።

## መንፈሳዊ ስጦታዎችን መንከባከብ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪ በአምልኮ አገልግሎቶች ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድን ማበረታታት አለበት። ይህ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የተለመደ ክስተት ነበር፣ እናም ዛሬ በአምልኮ አገልግሎቶች የተለመደ ክስተት መሆን አለበት (ሐዋ. 11፡27-28፤ 13፡2)።

ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን "መንፈሳዊ ስጦታዎችን፣ ...ስጦታ በብርቱ ፈልጉ" (1ቆሮ. 14፡1) በማለት አሳስቧቸዋል። በተጨማሪም በምትሰበሰቡበት ጊዜ እያንዳንዱ መዝሙር አለው፤ ትምህርት አለው፤ መግለጥ አለው፤ በልሳን መናገር አለው" (1ቆሮ. 14፡26) ብሏል። ስለዚህ፣ እንደ መጋቢ፣ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያንን ማስተማር አለብህ። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም

እንዲገለጡ ቦታ መስጠት አለብህ። በተመሳሳይም መንፈሳዊ ስጦታዎችን አላግባብ ከመጠቀም መጠንቀቅ አለብህ (1ቆሮ. 14፡26-33)።[1]

## የሙዚቃ ሚና

ሙዚቃ እና መዝሙር በአምልኮ ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ሕዝብ፣ "ጻድቃን ሆይ፤ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፤ ቅኖች ሊወድሱት ይገባቸዋል። እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት፤ዐሥር አውታር ባለውም በገና ዘምሩለት። አዲስ መዝሙር ዘምሩለት፤በገናውን ባማረ ቅኝት ደርድሩ፤ እልልም በሉ" (መዝ. 33፡1-3)።

እንደ ጳውሎስ አባባል፣ ሙዚቃ እና መዝሙር በአምልኮ ውስጥ ቢያንስ አራት ተግባራት አላቸው፡፡ እግዚአብሔርን ለማክበር፣ ለእርሱ ምስጋናን ለመግለጽ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ለማስተማር እና አማኞች ለእርሱ እንዲኖሩ መምከር ናቸው ። ሐዋርያው ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በጻፈው ደብዳቤ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን አጽንዖት ሰጥቷቸዋል፡- " በመዝሙርና በውዳሴ፣ በመንፈሳዊም ዝማሬ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ በልባችሁ ለጌታ ተቀኙ፤ አዚሙም። በዚህም እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉ ነገር ሁል ጊዜ አመስግኑ" (ኤፌ. 5፡19-20)። ለቆላስይስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ላይ ቀጥሎ ያሉትን አበክሮ ገልጿል። " ክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤ በመዝሙርና በማሕሌት፣ በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ" (ቆላ. 3፡16)።

## ወቅታዊ ማስጠንቀቂያ

ወቅታዊ ማስጠንቀቂያ! ሰዎች በቅንዓት ዝማሬ ስለሚወዱ ብዙውን ጊዜ ወደ ጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ይሳባሉ። ይህ ጥሩ ነው እና ይህን ልምምድ ማበረታታት አለብህ። በተመሳሳይ ጊዜ ግን፣ ቤተ ክርስቲያን ለጌታ "እንግዳ እሳት" እንድታቀርብ ፈጽሞ መፍቀድ የለብህም (ዘሌ. 10፡1)። በሌላ አነጋገር፣ ዝማሬው እና ውዝዋዜው የተቀደሱ ልቦች ለእግዚአብሔር መንፈስ እንዲሰጡ ከማድረግ ይልቅ የሥጋ ማሳያ እንዳይሆኑ ማረጋገጥ አለብህ። ስለዚህ፣ እንደ መጋቢ፣ ሙዚቃው ከልክ እንዲያልፍ በፍጹም መፍቀድ የለብህም። ይህ ከሆነ እውነተኛውን ከልብ የመነጨ አምልኮ ያጠፋል። የጳውሎስን ማሳሰቢያ አስታውስ፡- "ሥጋ በእግዚአብሔር ፊት አይመካ" (1 ቆሮ. 1፡29፣ ቀጥተኛ ትርጉም)። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንህ "የዝማሬህን ጩኸት ከእኔ አርቅ፤የበገናህንም ዜማ አልሰማም" ከማለት ተጠንቀቅ (አሞጽ 5፡23)።

# ሁለት የአምልኮ ፈተናዎች

አፍሪካ ከ2,100 በላይ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ከ3,000 በላይ ብሔረሰቦችን ያቀፈች ሰፊ አህጉር ናት። ስለዚህ በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ ጉባኤ ከተለያዩ ነገዶች የመጡ ግለሰቦችን መካተት ያልተለመደ ነገር አይደለም። በተጨማሪም እያንዳንዱ ጉባኤ በተለያዩ የዕድሜ ቡድኖች የተዋቀረ ነው። ይህ ልዩነት ለሙዚቃ እና ለአምልኮ ዘይቤዎች የተለያዩ ምርጫዎች ይፈጥራል። በጥበብ ካልተያዙ በጉባኤ ውስጥ አለመግባባት መንስኤ ሊሆን ይችላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትን ከማበረታታት ይልቅ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት የመከፋፈል ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ.

[1] አባሪ 2፡ "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት።

ከዚህ ልዩነት የሚመነጩ ሁለት ተግዳሮቶች በአምልኮ ዘይቤዎች ላይ አለመግባባቶች እና ለአምልኮ አገልግሎቶች ውስጥ ብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎችን የመቅጠር ፈተና ናቸው። እንደ መጋቢ፣ እነዚህን ፈተናዎች በጥበብ መወጣ አለብህ።

## ሙዚቃ እና የአምልኮ ዘይቤዎች

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ብዙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት አባላት በሙዚቃ እና በአምልኮ ዘይቤዎች እርስ በርስ ይጋጫሉ። ለምሳሌ፣ የቤተክርስቲያኑ ወጣቶች ጮክ ያለ፣ ኃይለኛ የአምልኮ ዘይቤን ሊመርጡ ይችላሉ፣ አረጋውያን አባላት ደግሞ ጸጥ እና፣ የተቆጠበን ዘይቤን ይመርጣሉ። አንደኛው የዘመኑ መዝሙሮችን ይመርጣል፣ ሌላው ደግሞ ቀደምት መዝሙሮችን ይመርጣል። እንደ መጋቢ፣ ይህንን ሚዛናዊነት ለመጠበቅ ታላቅ ጥበብን መጠቀም አለብህ። እና በአምልኮ ውስጥ ያለውን ዘይቤ እና ይዘት መለየት መቻል አለብህ።

ዘይቤ ስለ ውጫዊ የአምልኮ ዓይነቶች ያለን ግለሰባዊ ምርጫዎች ይናገራል ፤ ጭብጡ ደግሞ ስለ ውስጣዊ እውነታዎች ይናገራል። አምልኮ በሙሉ ልብ እግዚአብሔርን ማድነቅ ነው (ማር. 7፡6-7)። እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ክርስቲያን የተለያዩ ዘይቤዎችን በመጠቀም እግዚአብሔርን በእውነት ማምለክ ይችላል። አንድ ሰው ምንም አይነት ዘይቤ ቢጠቀም በመንፈስ እና በእውነት ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አለው። በመንፈስና በእውነት ካልሆነ ይጣላል። ስለዚህ ህዝቡ በአምልኮው ውስጥ አንዱ የሌላውን ምርጫ እንዲያከብር ማስተማር አለባችሁ። "ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንተናነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ" (ሮሜ. 14፡19)።

ብልህ መጋቢ አረጋውያን አባላት ወጣቶቹ እግዚአብሔርን በሚያመልኩበት መንገድ ልባቸውን ወደ እግዚአብሔር በመክፈቱ እና ወደ እርሱ ቀርበው ሲያዩ ደስ እንዲላቸው ያስተምራቸዋል። ለወጣቶች ካላቸው ፍቅር የተነሳ ከእነርሱ ጋር በመሆን አምላካቸውን ለማምለክ ፈቃደኞች መሆን አለባቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ወጣቶቹ የሽማግሌዎችን ፍላጎትና ምርጫ እንዲያከብሩ እና በሙሉ ልብ በአምልኮታቸው እንዲተባበሩ ማስተማር አለብህ። እንዲሁም ወጣቶቹ ቀደምት መዝሙሮች እንዲወዱ እና እንዲያደንቁ ማስተማር ያስፈልጋል።

ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የቤተክርስቲያኑ የአምልኮ አገልግሎቶች አዳዲስ እና ቀደምት፣ ወቅታዊ እና ነባር መዝሙሮች ቅይጥ ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል። ዋናው ነገር እያንዳንዱ አማኝ በአምልኮ ውስጥ የእግዚአብሔርን መንፈስ ማግኘቱ እና ለክርስቶስ ያላቸውን ልባዊ ታማኝነት መግለጻቸው እንደሆነ ማሰብ ተገቢ ነው።

## በርካታ ቋንቋዎች

ከላይ እንደተገለፀው በአፍሪካ የሚገኙ በርካታ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች ይሳተፋሉ። ይህ ጉዳይ ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አንዳንድ ጉልህ ፈተናዎችን ይፈጥራል። ቤተ ክርስቲያኒቷ የአምልኮ አገልግሎቱን በሃገሩ ዋና ቋንቋ ብቻ ለመምራት ከመረጠ - ሁሉንም ሌሎችን ቋንቋዎች ችላ ስትል ሰዎችን ከሌሎች የቋንቋ ቡድኖች የመለየት አደጋ ይገጥማታል። ነገር ግን ደግሞ፣ በአምልኮ ውስጥ ብዙ ቋንቋዎችን የምትጠቀም ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው አማኞች መካከል ቅሬታ የመፍጠር አደጋ ላይ ነች። ስለዚህ ይህንን ሁኔታ በጥበብ መቆጣጠር አለብህ። የቤተክርስቲያኑ የአምልኮ አገልግሎቶች ለአካባቢው ሰው የሚስብ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ ሌሎችን የመቀበል መንገድ መክፈት ያስፈልጋል።

ይህንን ችግር ለመፍታት የእግዚአብሔርን ጥበብ መፈለግ ይገባል። አንተና የአመራር ቡድንህ የሚከተሉትን ጉዳዮች በጸሎት መፍታት ይኖርባችኋል፡-

- ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ አገልግሎት የምትጠቀምበት ዋና ቋንቋ የትኛው ነው?
- የትኞቹ ሌሎች ቋንቋዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ? እነዚህ ቋንቋዎች መቼ እና በምን ሁኔታ ውስጥ ጥቅም ላይ ይዋሉ?
- ማስታወቂያዎች፣ የአደባባይ ጸሎቶች እና ስብከቱ በየትኛው ቋንቋ ይተረጎሙ?
- በመዝሙር ውስጥ የትኞቹ ቋንቋዎች ጥቅም ላይ ይዋሉ? እነዚህ ቋንቋዎች መቼ እና እንዴት ጥቅም ላይ ይዋሉ?
- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የትኞቹ የቋንቋ ቡድኖች በአሁኑ ጊዜ ችላ እየተባሉ ነው? እየተካተቱ እንደሆኑ እንዲሰማቸው ልንረዳቸው የምንችለው እንዴት ነው?

እያንዳንዱ ጉባኤ ይህን ችግር ለመፍታት የራሱን መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፤ ሆኖም አንዳንድ ሰፋ ያሉ መሠረታዊ መርሆች ግን ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን። ለምሳሌ፣ አምልኮ ሲታቀድ፣ በአገልግሎቱ ላይ የሚሳተፉትን ሁሉ የሚቀበል እና የሚያካትት መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ። ሌላው አላማ ሁሉም ተሰብሳቢዎች መታነጻቸውን ምረጋገጥ ነው። በተጨማሪም የአምልኮ ሥርዓቱ ምእመናንን ከመከፋፈል ይልቅ ወደ አንድነት ማምጣት አለበት። እነዚህን መርሆዎች ማክበር ትክክለኛ ውሳኔዎች ለመወሰን ይረዳል።

አንዳንድ የከተማ አብያተ ክርስቲያናት፣ ልክ እንደ ዓለም አቀፍ አብያተ ክርስቲያናት፣ አገልግሎቶቻቸውን በሀገሪቱ የጋራ የአውሮፓ ቋንቋ መምራት ይፈልጋሉ። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ክልላዊ አፍሪካዊ ቋንቋ መጠቀም ይፈልጋሉ። አንዳንዶች ሙሉውን አገልግሎት ለመተርጎም ይፈልጋሉ። ሌሎች ደግሞ ስብከቱን ብቻ ይተረጉማሉ። ሌሎች እያንዳንዱ አገልግሎት በተለየ ቋንቋ ማካሄድ ይፈልጉ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያንህ የምትከተለው የትኛውንም ስልት ቢሆን፣ ግብህ መሆን ያለበት በአምልኮው ላይ የሚሳተፍ ሁሉ የተከበረ እና የተካተተ እንዲሆን ማድረግ ነው።

---

የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ዋና ሃላፊነት ቤተክርስቲያኑን ወደ እውነተኛ፣ በመንፈስ ወደተቀባ አምልኮ መምራት ነው። እርሱ ወይም እርሷ እግዚአብሔርን በመንፈስ እና በእውነት ማምለክ ምን ማለት እንደሆነ ለሰዎች በማስተማር እና በራሱ ህይወት ውስጥ ትክክለኛ የአምልኮ አኗኗር ምን እንደሚመስል በተግባር ማሳየት ይችላል።

# ~ ምዕራፍ 19 ~

# ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጴንጤቆስጤያዊ ሪቫይቫል መምራት

አንድ ሰው በበዓለ ሃምሳ ቀን የነበረው የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ መነቃቃት እንደሆነ ገልጿል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ መንፈሱን በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ያፈሰሰበት፣ ህይወትን በመሙላት በምድር ላይ ያለውን ተልእኮዋን እንድትፈጽም ስልጣን የሰጣት በዚያ ቀን ነበር። የዘመናችን የጴንጤቆስጤያዊ ንቅናቄ ስሙንና ማንነቱን ያገኘው በዚያ ቀን ከተፈጠረው ኹነት ነው።

ጴንጤቆስጤያዊ መሆን ማለት የጴንጤቆስጤ ልምድ እና አላማ መቀበል ማለት ነው። የጴንጤቆስጤ ልምምድ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ሲል የሚገልጸውን ኃይለኛ መንፈሳዊ ልምምድ ነው (ሉቃስ 3፡16፤ የሐዋርያት *ሥራ* 1፡5)። የጴንጤቆስጤ አላማ ከአካባቢ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ለመመስከር በመንፈስ ቅዱስ መታጠቅ ነው (ሐዋ. 1፡8)።

ጴንጤቆስጤያዊ ካልሆኑ አብያተ ክርስቲያናት በተለየ፣ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ፍሰት በተደጋጋሚ ካልተለማመዱ የጴንጤቆስጤያዊን እውነተኛ ዓላማና ጥሪ ይዘው መቀጠል አይችሉም። ሰው አየር መተንፈሱን ካቆመ እንደሚሞት ሁሉ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያንም በእግዚአብሔር መንፈስ መንቀሳቀስ ካቆመች ትሞታለች። በሌላ አነጋገር፣ ቤተ ክርስቲያን በእውነት ጴንጤቆስጤያዊ ለመሆን የጴንጤቆስጤያዊ ታህድሶ መለማመድ አለባት። ኢየሱስም "መንፈስ ሕይወትን ይሰጣል፤ *ሥጋ ግን ምንም አይጠቅምም*" (ዮሐ. 6፡63)። ይህ ምዕራፍ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያንህ ወደዚህ ተሃድሶ እንዴት እንደምትመራ ያብራራል።

# ታህድሶን መረዳት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ሪቫይቫል ከመምራቱ በፊት፣ በአእምሮው የአዲስ ኪዳን መነቃቃት ምን እንደሚመስል ግልጽ የሆነ ምስል ሊኖረው ይገባል። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ብዙዎች የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የተዛባ የመነቃቃት እሳቤ አላቸው። የመነቃቃት ሀሳባቸውን ያገኙት ከቅዱሳት መጻሕፍት ሳይሆን ከዕውቅ የቤተ ክርስቲያን ባህል ነው። በዚህም ምክንያት፣ ሪቫይቫልን የሚያዩት በቤተ ክርስቲያን በደስታ መዘመር፣ መጨፈር እና እግዚአብሔርን ማመስገን አድርገው ነው። ወይም ደግሞ እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ቁሳዊ በረከቶችን እና ብልጽግናን ሲያወርድ ታህድሶ እንደሆነ ያስባሉ። ከእነዚህ ገጽታዎች መካከል አንዳንዶቹ ታህድሶን የሚያጅቡ ክስተቶች ቢሆኑም፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደተገለጸው ያለውን እውነተኛ ታህድሶን አይገልጹም።

ሪቫይቫል የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባይገኝም፣ የመንፈሳዊ መታደስ ጽንሰ-ሐሳብ ግን አለ(ሐዋ. 3፡19)። ሪቫይቫል የሕይወትን መታደስ ያመለክታል። ቃሉ የንቃተ ህሊና፣ ጉልበት እና ጥንካሬ መመለስን ያሳያል። ብሉይ ኪዳን ሪቫይቫል ብሎ የሚጠራውን (መዝ. 85፡6፤ ዕንባ. 3፡2)፣ አዲስ ኪዳን የመንፈስ መፍሰስ እንደሆነ ይገልፃል (ሐዋ. 2፡17-18)። በሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች፣ ለአዲስ ኪዳን መነቃቃት ሦስት አስፈላጊ ነገሮችን ይገኛሉ፡-

- በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የተጠመቁት እና በኃይል የታጠቁት በመንፈስ ቅዱስ ነው (ሐዋ. 1፡8፤ 2፡1-4)።
- በመቀጠል፣ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለጠፉት ክርስቶስን በድፍረት ማወጅ ጀመሩ (ሐዋ. 2፡14-40፤ 4፡31)።
- በመጨረሻ፣ የጠፉ ሰዎች ንስሐ ገብተዋል፣ በክርስቶስ አምነው ድነዋል (ሐዋ. 2፡41፣ 47፤ 5፡ 12-16)።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደተገለጸው የእውነተኛ መንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ሌሎች መገለጫዎች ተአምራዊ ፈውሶች፣ ምልክቶች እና ድንቆች ናቸው (ሐዋ. 2፡43፤ 5፡12-16)። እነዚህ ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ አስደናቂ ነገሮች ብዙ ጊዜ ታላቅ ደስታን፣ ሕያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎችን እና የቤተ ክርስቲያንን እድገት ያመጣሉ። ቢሆንም፣በእውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ ታህድሶ ሶስት አስፈላጊ ነገሮች ማዕከላዊነት መያዝ ይገባቸዋል፡- መንፈሳዊ ኃይል መታጠቅ፣ ብርቱ ምስክር መሆን እና ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ። ከነዚህ ሶስት መለያዎች አንዱ ከጠፋ፣ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ሪቫይቫል ነው ለማለት ይቸግራል።

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ

በጴንጤቆስጤ ቀን የተፈፀመውን በጥልቀት በመመልከት የእኛን የታህድሶን ፍቺ ትንሽ እናስፋ። የሐዋርያት ሥራ 2ን በቅርበት ስንመረምር የእውነተኛው የአዲስ ኪዳን ታህድሶ ሰባት ቁልፍ ነገሮችን ያሳያል፡-

### እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሰዎች

የእውነተኛው የአዲስ ኪዳን መነቃቃት የመጀመሪያው ቁልፍ አካል የእግዚአብሔር ህዝብ በጸሎት የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በጴንጤቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ከመጀመሩ በፊት 120 ደቀ መዛሙርት" እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ዘወትር በቤተ መቅደስ" እንደ ነበሩ

ይነግረናል(ሉቃስ 24፡53)። ደግሞም “በአንድ ልብ ሆነው ያለ ማቋረጥ ተግተው ይጸልዩ ነበር” (የሐዋርያት ሥራ 1፡14) ይላል። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጸሎትን ከመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጋር ያለማቋረጥ ያገናኛል። እንድምታው ግልጽ ነው፡፡ አንድ ቤተ ክርስቲያን የጴንጤቆስጤያዊ ሪቫይቫልን ማግኘት ከፈለገች ምእመናን እግዚአብሔርን በጸሎት አጥብቀው መፈለግ አለባቸው።

## እግዚአብሔር መንፈሱን ያፈሳል

ሁለተኛው የአዲስ ኪዳን መነቃቃት የእግዚአብሔር መንፈስ መፍሰስ ነው። በጴንጤቆስጤ ዕለት፣ ለህዝቡ ጸሎት ምላሽ፣ እግዚአብሔር በቸርነቱ መንፈሱን በቤተ ክርስቲያን ላይ አፈሰሰ። እንዲህ ሆነ።

"1 የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ነበር፤ 2 ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው። 3 የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ። 4 ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር"(የሐዋርያት ሥራ 2፡1-4)።

## አማኞች መንፈስን ይቀበላሉ

ሦስተኛው የአዲስ ኪዳን መነቃቃት አካል አማኞች በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው ነው። እግዚአብሔር መንፈሱን ማፍሰስ አንድ ነገር ነው ፤ ሕዝቡ መንፈስን መቀበሉ ሌላ ነው። በጴንጤቆስጤ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን “ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር” (ሐዋ. 2፡4)። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ በገባው ቃል መሠረት በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ (ሐዋ. 1፡4-5)። በዚያን ጊዜ፣ ከአካባቢያቸው እና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ የክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ ኃይልን ተቀበሉ (ሐዋ. 1፡8)። የእግዚአብሔር ሰዎች መንፈስን መቀበላቸው የእውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ ታህድሶ መጀመሪያ ነው።

## የውጭ ሰዎች ይመለከታሉ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው አራተኛው የታህድሶ አካል የውጭ ሰዎች እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚያደርገውን ማስተዋላቸው ነው። በጴንጤቆስጤ ዕለት፣ በደቀ መዛሙርቱ ላይ የመንፈስን መምጣት የተመለከቱ እና ባልተማሩ ቋንቋዎች ሲናገሩ ያዳምጡ የነበሩት በሆነው “ተደነቁ”። እርስ በርሳቸውም “ይህ እንዴት ቢሆን ነው?” ብለው ይጠይቁ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 2፡12)።

## ወንጌል ይሰበካል

የእውነተኛው የአዲስ ኪዳን ታህድሶ አምስተኛው አካል ደፋር፣ በመንፈስ መሪነት የታጀበ የወንጌል አዋጅ ነው። በበዓለ ሃምሳ የሆነውም ይኸው ነው። ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ በኋላ ድፍረት ቆሞ ለተሰበሰበው ሕዝብ ወንጌልን ሰበከ። ስለ ኢየሱስ ነግሮአቸው ወደ ንስሐና እና ወደ እምነት ጠራቸው (ሐዋ. 2፡14-40)። በመንፈስ የተሞሉት ሁሉ ስለ ክርስቶስ ለመመስከር ከጴጥሮስ ጋር ተባበሩ (ቁ. 47)።

## ብዙዎች ይድናሉ

የአዲስ ኪዳን ታህድሶ ስድስተኛው አካል ብዙዎች ምላሽ መስጠታቸው እና በወንጌል አምነው መዳናቸው ነው። በጴንጤቆስጤ ዕለት፣ በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ እና በጴጥሮስ የተቀባ የወንጌል አዋጅ፣ ብዙዎች ንስሐ ገብተው ወደ ጌታ መጡ። መጽሐፍ ቅዱስ አድማጮቹ “ልባቸው በጣም ተነካ” በማለት ይገልጣ። ቀጥሎም ጴጥሮስን “ምን እናድርግ?” ብለው እንደጠየቁ ይናገራል። ጴጥሮስም፣ “ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ” (ሐዋ. 2፡37-38)። በዚህ ጥሪ፣ 3,000 ድነው በውኃ ተጠመው እና ወደ ቤተ

ክርስቲያን ተጨምረዋል (ቁ. 41)። በቀጣዮቹ ቀናትም፣ "ጌታ የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" (ቁ. 47)።

## ቤተ ክርስቲያን ትሰፋለች

የአዲስ ኪዳን ታህድሶ ሰባተኛው መገለጫ የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ነው። ከበዓለ ሃምሳ እና ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በኋላ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ቤተ ክርስቲያን በቁጥር ማደግ እና በመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ መስፋፋቷን ቀጠለች (ሐዋ. 2፡47፤ 4፡31-35፤ 5፡12-16፤ 9፡31)።

በሐዋርያት ሥራ 2 ውስጥ የተገለጹት ሌሎች ጉልህ የታህድሶ ገጽታዎች ለቅዱሳት መጻሕፍት፣ ለጸሎት እና እርስ በርስ መዋደድ ያሉ መሰጠቶች ናቸው። እግዚአብሔር በመካከላቸው ተአምራትን ሲያደርግ ህዝቡም በቅዱስ ፍርሃት ይኖሩ ነበር። በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት በልባቸው ውስጥ የልግስና መንፈስን ፈጠረ። እነዚህ ሁሉ ነገሮች የቤተ ክርስቲያንን እድገት አጠናክረዋል (ሐዋ. 2፡ 41፣ 47፤ 4፡4፤ 5፡14)።

በማጠቃለል፣ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ያለውን መልእክት ሲያምኑ፣ በመንፈስ ሲሞሉ እና ከዚያም ምሥራቹን ለሌሎች ለማካፈል ሲወጡ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ታህድሶ ይከሰታል። ወንጌልን የተቀበሉት ይድናሉ ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ ይሞላሉ። እነርሱ ራሳቸው ከዚያም ታማኝ የወንጌል አዋጅ ነጋሪዎች ይሆናሉ። ይህ ሂደት በተደጋጋሚ ሲደጋገም፣ ታህድሶው ወደ ሩቅ እና ሰፊ ዳርቻ ይዳረሳል።

# የመጋቢ ሚና

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢነትህ፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስትያን ውስጥ የታህድሶ ቁልፍ ነህ። የመንፈስን ፍሰት ማበረታታት ወይም ፍሰቱን መገደብ ትችላለህ። የምታደርገው ወይም የማታደርገው ነገር ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ የመንፈስ እንቅስቃሴን ውስጥ መግባት ወይም አለመግባቷን ሊወስን ይችላል። በተጨማሪም፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪ፣ መንፈስ ሲመጣ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ምላሽ እንደምትሰጥ ትወስናለህ። ይህን ታላቅ ኃላፊነት በቁም ነገር ልትመለከተው ይገባል።

የጴንጤቆስጤያዊ ታህድሶ የሚጀምረው በመጋቢው ልብ ውስጥ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ መንቀሳቀስ ፍላጎት እርሱ ወይም እርሷ በቤተ ክርስቲያን ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዲፈስ እግዚአብሔርን አጥብቆ እንዲፈልግ ያነሳሳዋል። ፓስተሩ ይህንን የመነቃቃት ፍላጎት በእግዚአብሔር ህዝብ ልብ ውስጥ ማስተላለፍ አለበት። በርዕሱ ላይ ብዙ ጊዜ በመስበክ እና በማስተማር ይህንን ማድረግ ይችላል።

ለተሀድሶ በመጸለይ በህዝብ ልብ የበለጠ የተሃድሶ ጥማት መፍጠር ትችላለህ። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ "እላችኋለሁ፡- ለምኑ ይሰጣችሁማል። ፈልጉ ታገኙማላችሁ ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል" ብሏል (ሉቃስ 11፡9፤ ቁ. 13) የኢየሱስ ቃላት ቀጥተኛ ትርጉም እንዲህ ይነበባል፣ "እላችኋለሁ፡- ለምኑ ይሰጣችኋል። ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ። ማንኳኳቱን ቀጥሉ፣ በሩም ይከፈትላችኋል። አንድምታው ግልጽ ነው፡፡ መንፈስን መለመናችንን እስከቀጠልን ድረስ ከእግዚአብሔር መቀበላችንን እንቀጥላለን። ነገር ግን መጠየቅ ስናቆም መቀበል እናቆማለን። ስለዚህ የጴንጤቆስጤያዊ ታህድሶ እሳቶች በዘላቂ ጸሎት መቀጣጠል አለበት።

በተጨማሪም፣ እንደ መጋቢ ለሕዝብህ በእምነት እንዴት መጸለይ እንዳለብህ ማሳየት አለብህ። እግዚአብሔርን በታማኝነት የሚፈልጉ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ታህድሶን ለመላክ የገባውን ቃል እንደሚፈጽም እንዲያምኑ ልታበረታታቸው ይገባል (ማር. 11፡24)። የጴጥሮስን ትንቢታዊ መልዕክትን

ያለማቋረጥ ማስታወስ ያስፈልጋል "በመጨረሻው ቀን እግዚአብሔር ይላል፣ መንፈሴን በሥጋ ለበሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ" (የሐዋርያት ሥራ 2:17፣ አጽንዖት ተጨምሯል)። የቤተ ክርስቲያን አባላት ይህንን የተስፋ ቃል ሲቀበሉ፣ የሰማይ አባት "ለሚጠይቁት መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጥ" ኢየሱስን የሰጠውን ተስፋ እንዲያምኑ ይበረታታሉ (ሉቃስ 11:13)።

ቤተ ክርስቲያን የጴንጤቆስጤያዊ ተሀድሶ እንደምትሻ፣ በተመሳሳይ ጊዜ፣ የጴንጤቆስጤያዊ ተልእኮ ተኮር መሆን አለባት። በሐዋርያት ሥራ 1:8 ላይ የኢየሱስ ግልጽ መመሪያ ይህ ነበር። በመጀመሪያ፣ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" በማለት ታህድሶ እንደሚሰጥ ቃል ገባ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ ተልዕኮን አዘዘ፡- "እናንተም እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ..."።

ስለዚህ፣ እንደ መጋቢ፣ በመንፈስ ኃይል ለሆነ ምስክርነት ለመዘጋጀት አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት የመምራት ተግባር ከዋና ጉዳዮችህ ውስጥ አንዱ መሆን አለበት። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያስቀመጠህ አንዱ ዋና ምክንያት እርሱ መንግሥቱን ለመገንባት የሚጠቀምባቸውን በመንፈስ የታጠቁ ደቀ መዛሙርት እንድታስነሣ ነው (ኤፌ. 4፡11-12)።

# የጴንጤቆስጤያዊ ተሀድሶን ማበረታታት

በጴንጤቆስጤ ቀን በኢየሩሳሌም መንፈስ ከፈሰሰ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፣ ሉቃስ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን 50 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው በሰማርያ ሌላ የመንፈስ ቅዱስ ፍሰት እንደሆነ ይናገራል (ሥራ 8:1-25)። ይህ ተሀድሶ በወንጌላዊው ፊሊጶስ ሲመራ ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ አግዘውት ነበር። የእነዚህን ሰዎች ድርጊት በመመልከት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሀድሶን ስለ ማበረታታት ሰባት ተግባራዊ ትምህርቶችን እናገኛለን፡-

### በመንፈስ ተሞላ

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ተሀድሶን የምታበረታታበት የመጀመሪያው መንገድ በግልህ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ወይም ደጋግሞ እንዲሞላ ከልብ በመፈለግ ነው። ፊልጶስ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈስ ከተሞሉ ሰባት "ዲያቆናት" አንዱ ነበር (ሐዋ. 6፡3-5)። በጴንጠቆስጤ ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በመንፈስ ተሞልቶ ሊሆን ይችላል። በስደት ከከተማዋ ሲወጣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር። ሰማርያ በደረሰ ጊዜ፣ በመንፈስ ኃይል አገለገለ፣ ይህም በቦታው ላይ ታላቅ ተሀድሶን አመጣ።

እርሱን ለመርዳት ከኢየሩሳሌም ከሐዋርያቱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ እርሱ ወረዱ (8፡14-17)። ሐዋሪያቱ በሰማርያ መነቃቃትን ማነሳሳት የቻሉት እነርሱ ራሳቸው በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ስለነበሩ ነው። የጴንጤቆስጤያዊ ተሀድሶ የሚጀምረው በአንተ፣ በመጋቢው እና በሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ወይም ደጋግሞ መሞላት ነው።[1]

### ደፋር እምነትን መለማመድ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሀድሶን የምታበረታታበት ሁለተኛው መንገድ ደፋር እምነትን ማሳየት ነው። ፊልጶስ ሰማርያ ሲደርስ በእምነት ተራመደ። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር የሰበከውን መልእክት የሚያረጋግጥ ተአምራትን ሰጠው ብዙዎችም ወደ ጌታ መጡ (ሐዋ. 8፡5-8)።

---

[1] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር ከመንፈስ ጋር ስላለው ልምድ፣ ምዕራፍ 1ን ተመልከት፡ "የተሞከሮ ሰው"

እንደ ፊልጶስ ተሀድሶ እንደሚመጣ ማመን ያስፈልግሃል። እግዚአብሔር የገባውን ቃል ማድረግ እንደሚችል ሙሉ በሙሉ ልታምን ይገባል (ሮሜ. 4፡18-21)። እናም ተሀድሶ እንደሚመጣ ሙሉ ድፍረት በመያዝዝ በእግዚአብሔርን ቃል ተስፋ ላይ በድርጊት መገለጥ ያስፈልጋል። ይህን ካደረግክ እምነትህ ወደ ሌሎችም ይተላለፋል። ጉባኤው መጋቢው በድፍረት ሲሰራ ሲያዩ፣ እነርሱም እግዚአብሔርን ተሀድሶ እንደሚልክ ያምናሉ።

## ክርስቶስን መስበክ

ቤተ ክርስቲያንህን ወደ ጴንጤቆስጤያዊ ታሀድሶ የምትወስድበት ሶስተኛው መንገድ የክርስቶስን ወንጌል በታማኝነት መስበክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ፊልጶስ በሰማርያ ወዳለች ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው" ይለናል (ሐዋ. 8፡5)። ይህ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የክርስቲያኖች ልማድ ነበር። በሄዱበት ሁሉ፣ ስለ ኢየሱስ ለሰዎች ይነግሩ ነበር (ሐዋ. 2:22፤ 3:13፤ 4:2፣ 33፤ 9:22፤ 16:31)። በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ እውነተኛውን የአዲስ ኪዳን ታሀድሶ ለመለማመድ ከፈለክ እንደ ፊልጶስ እና ሐዋርያት ማድረግ አለብህ። ክርስቶስን ለሁሉም በታማኝነት መስበክ አለብህ። ህዝብህም እንዲሁ እንዲያደርግ ማስተማር አለብህ።[2]

## ለታመሙ መጸለይ

አራተኛ፣ እግዚአብሔር በሚከተለው ተአምራዊ ምልክቶች ቃሉን ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ እንዲያረጋግጥ በመጠበቅ ለታመሙ እና ለተቸገሩት በታማኝነት በመጸለይ ቤተ ክርስቲያንህ ወደ እውነተኛ አዲስ ኪዳን ተሀድሶ መምራት ትችላለህ። በሰማርያ፣ "ብዙ ሕዝብም ፊልጶስ የተናገረውን ሲሰሙና ያደረገውንም ታምራዊ ምልክቶች ሲያዩ፣ አንድ ልብ ሆነው ያዳምጡት ነበር" (ሐዋ. 8፡ 6)። እነዚህ ተአምራዊ ምልክቶች ኃይለኛ መዳንን እና ተአምራዊ ፈውሶችን ያካትታሉ። በውጤቱም፣ ታላቅ ደስታ ወደ ህዝቡ መጣ፣ ብዙዎች ዳኑ። መነቃቃትም ወደ ከተማዋ መጣ።[3]

## የመንፈስ ጥምቀትን አጽንዖት ስጥ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጴንጤቆስጤያዊ ተሀድሶን የምታበረታቱበት አምስተኛው መንገድ አባላት በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ አስፈላጊነትን ደጋግሞ ማጉላት ነው። በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት ሳምራውያን ወንጌል መቀበላቸውን በሰሙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ከእነርሱ ጋር እንዲጸልዩ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላኩ (ሐዋ. 8፡14-17)። ማንኛውም መጋቢ ቤተ ክርስቲያን የጴንጤቆስጤያዊ መነቃቃትን እንድታገኝ የሚፈልግ ከሆነ እንዲሁ ማድረግ አለበት። በመንፈስ ጥምቀት ላይ ብዙ ጊዜ ማስተማር እና መስበክ አለበት። መንፈስን ለመቀበልም ከህዝብ ጋር መጸለይ አለበት። ይህም ቤተ ክርስቲያን በተሐድሶው ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንድትሳተፍ እና ወንጌልን ለጠፉት ለማዳረስ ለማዘጋጀት ይረዳል።[4]

---

[2] በስብከቱ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 16:- "በመንፈስ የተቀቡ ስብከት" የሚለውን ተመልከት።

[3] ከተፈጥሮ በላይ በሆነው አገልግሎት ላይ፣ ከአፍሪካ ቲኦሎጂካል ማሰልጠኛ አገልግሎት (ATTS) https://africaats.org/ የሚገኘውን በዴንዚል አር ሚለር የተዘጋጀውን የኃይል አገልግሎት፡ በመንፈስ ኃይል እንዴት እንደሚያገለግል የተሰኘውን ዲስከቨሪ ተከታታይ መጽሐፍ ተመልከት።

[4] መንፈስን ለመቀበል ከአማኞች ጋር መጸለይን በተመለከተ፣ ምዕራፍ 11ን ተመልከት፡ "የጴንጤቆስጤ ልምድ እና ልምምድ ያበረታታል" እና ምዕራፍ 20፡ "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት"

## በህይወት ምስክርነት ከፊት መምራት

ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ ተሀድሶን የምታበረታታበት ስድስተኛው መንገድ እንደ ቤተ ክርስቲያን ለጠፉት በመመስከር ነው። ፊልጶስ የሰማርያን መነቃቃት የጀመረው በመንፈስ ኃይል በድፍረት ለጠፋው የሰማርያ ሕዝብ የክርስቶስ ምስክር በመሆን ነው። ይህንንም በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ሆነ። በሰማርያ የነበሩት አዲሶቹ ክርስቲያኖች ምሳሌውን እንደተከተሉ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፤ ምክንያቱም በአጭር ጊዜ ውስጥ "በዚህ ጊዜ በይሁዳ፣ በገሊላና በሰማርያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በሰላም መኖር ጀመረች፤ ተጠናከረችም። ደግሞም እግዚአብሔርን በመፍራት እየተመላለሰችና በመንፈስ ቅዱስ እየተጽናናች በቊጥር እየበዛች ሄደች፡" ይላል (ሐዋ. 9፡31)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እውነተኛ መንፈሳዊ መነቃቃትን የምትፈልግ ከሆነ፣ የፊልጶስን ምሳሌ መከተል አለብህ። ሕዝቡ እንዲመሰክር መናገር ብቻ ሳይሆን አንተ ራስህ ምስክር በመሆን የጴንጤቆስጤያዊ ታሀድሶ ዓላማ ምሳሌ መሆን አለብህ።[5]

## በጸሎት ጽና

በመጨረሻም፣ በዚህ ምዕራፍ ቀደም ሲል እንደተብራራው፣ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ለምእመናን በማሳየት ቤተ ክርስቲያንህን ወደ ጴንጤቆስጤያዊ ተሀድሶ መምራት ትችላለህ። ሐዋርያቱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሰማርያ ሲደርሱ "መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ በዚያ ስላሉት አዲስ አማኞች ጸለዩ" (ሐዋ. 8፡15)። ትክክለኛ የጴንጤቆስጤያዊ ተሀድሶ ወደ ቤተክርስትያናችሁ እንዲመጣ ማየት ከፈለግህ አንተም ህዝቡን ወደ ጸሎት መምራት አለብህ። "መልካም ለማድረግ አንታክት፤ ተስፋ ባንቆርጥ በጊዜው እናጭዳለንና" የሚለውን የጳውሎስን ቃል በማስታወስ (ገላ. 6:9) መልሱ እስኪመጣ ድረስ በጸሎት ጽና።[6]

---

በአካባቢ ማህበረሰቡ ሆነ በዓለም ላይ የክርስቶስ ምስክር ለመሆን እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስትያን ደጋግሞ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስን መለማመድ አለባት። በዚህ ተግባር የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ግንባር ቀደም መሆን አለበት። እርሱ ወይም እርሷ ተሀድሶን በቅንነት በመከተል አርአያ መሆን አለባቸው እና ህዝቡም እንዲሁ እንዲያደርጉ ማስተማር አለባቸው። ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን እግዚአብሔር ለኢዩኤል ከሰጠው ተስፋ እንደ መበረታቻ መውሰድ ይችላሉ።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው ቀን፣መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ጒልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ።18በዚያ ጊዜ በወንዶችና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ፣መንፈሴን አፈሳለሁ፤ እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ (ሐዋ 2፡17-18)።

---

[5] ቤተ ክርስቲያንን በመንፈስ ኃይል ወደ ተሰጠ የወንጌል አገልግሎት ስለመምራት፣ ምዕራፍ 36ን "የአዲስ ኪዳንን ስትራቴጂ መረዳት" እና ምዕራፍ 37፡ "የጠፉትን ወንጌላዊነት" የሚለውን ተመልከት።

[6] ቤተ ክርስቲያንን በጸሎት ስለመምራት፣ ምዕራፍ 8ን ፡ "የጸሎት ቅድሚያ" የሚለውን ተመልከት።

# ~ ምዕራፍ 20 ~

# አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት የጀመረውን ሥራ ለቤተ ክርስቲያኑ ሰጥቷል። ከመለየቱ በፊት፣ ደቀ መዛሙርቱን ከኢየሩሳሌም ውጭ ባለ በተራራ ጫፍ ላይ ሰበሰባቸው። በዚያም የመጨረሻ ትእዛዝ እና የመጨረሻ ቃል ኪዳን ሰጣቸው።

ትእዛዙም ""ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤ 5 ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" " (ሐዋ. 1፡4-5) የሚል ነበር። የገባው ቃል ደግሞ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" የሚል ነበር (ቁ. 8)። እነዚህን መመሪያዎች ሲሰጥ፣ የሰጣቸውን ተልእኮ ለመፈጸም ቤተ ክርስቲያኑን እያደራጀ ነበር።

በተመሳሳይ መልኩ፣ በአፍሪካ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተክርስቲያኑ በክርስቶስ የማዳን ተልዕኮ ውስጥ እንዲሳተፍ ማሰባሰብ አለበት። ልክ እንደ ኢየሱስ፣ ህዝብ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ እና ለጠፉት የክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ በኃይል የታጠቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብህ። የትኛውም ቤተ ክርስቲያን መሪዎቿ እና አባሎቿ ይህን የተስፋ ቃል ከላይ እስካልተቀበሉ ድረስ በእግዚአብሔር ተልእኮ በብቃት ለመሳተፍ ዝግጁ አይደለም (ሉቃስ 24፡49)። ይህ ምዕራፍ ይህንን አስፈላጊ ጉዳይ ያብራራል። ምዕራፉ አባላትህን ወደ መንፈስ ጥምቀት ለመምራት እራስህን እንድታዘጋጅ ይረዳሃል።

# የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምንድን ነው?

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት (አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ ጥምቀት ተብሎ የሚጠራው) ህይወትን የሚቀይር ሃይለኛ ልምድ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ግንኙነት ሲሆን መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ተከታይ ላይ የሚወርድበት፣ የሚያለብስበት እና በእርሱ ህልውና እና ሃይል የሚሞላበት ሂደት ነው። በጴንጤቆስጤ ቀን በ120ዎቹ ደቀ መዛሙርት ላይ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ልምዳቸውን እንዲህ ሲል ይገልፃል።

1 የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ነበር፤ 2 ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው። 3 የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ። 4 ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር (ሐዋ 2፡-14)።

በዚያ ወቅት ደቀ መዛሙርቱ ያጋጠማቸውን ሁኔታ ተመልከት። በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ቃል እንደገባው መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ። በመቀጠልም መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይሉና በመገኘቱ ሞላባቸው። ከዚህም የተነሣ መንፈስ እንደፈቀደላቸው በልሳኖች መናገር ጀመሩ። በመጨረሻም፣ በሚያስገርም ኃይል እና ውጤታማነት መመስከር ጀመሩ (ሐዋ. 2፡14-41)። ይህ ሥርዓት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሁሉ ቀጥሏል። እና ዛሬም እንደሚቀጥል መጠበቅ እንችላለን።

እነዚህን ነገሮች በአዕምሮአችን ይዘን፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሦስት ነገሮችን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን።

**1. ኃይለኛ ተሞክሮ ነው።** ኢየሱስ የመንፈስ ጥምቀትን “ከላይ ኃይልን መልበስ” ሲል ገልጿታል (ሉቃስ 24፡49)። “መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ” ሐዋ 1፡8 በማለት ቃል ገባ። ሰው በመንፈስ ሲሞላ የኃያሉ የእግዚአብሔርን ኃይል ይገናኘዋል።

**2. ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ ቃል ኪዳን ነው።** ኢየሱስ የሰማይ አባት በእምነት ለሚለምን ለማንኛውም ልጁ መንፈስ ቅዱስን በነጻ እንደሚሰጥ ተናግሯል (ሉቃስ 11፡13፤ ማር. 11፡24)። በጴንጤቆስጤ ስብከቱ ላይ፣ ጴጥሮስ ስለተሞክሮ ሲናገር፣ “የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፣ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና” ” (ሐዋ. 2፡39) ብሏል።

**3. የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።** ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ” (ሐዋ. 1፡4) በማለት አዘዛቸው። በተመሳሳይ መልኩ፣ ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞች “በመንፈስ ተሞሉ” ሲል አዟቸዋል (ኤፌ. 5፡18)። እያንዳንዱ ክርስቲያን የክርስቶስ ምስክር ለመሆን ስለተሾመ፣ በመንፈስ ቅዱስ መታጠቅ አለበት (ሉቃስ 24፡48-49፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡8፤ 5፡32)።

የመንፈስ ጥምቀት ክርስቲያን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንዲመራ የበለጠ ያስታጥቀዋል (ገላ. 5፡16)። የመጸለይ ችሎታውን ያሳድጋል (ሮሜ. 8፡26-27)። በመንፈስ ጥምቀት የተቀበለ ሰው መንፈሳዊ ስጦታዎች በሕይወቱ የመገለጥ እድሉ ከፍተኛ ነው (1ቆሮ. 12፡7-10)። በተጨማሪም፣ ልምምዱ ለእግዚአብሔር ነገር የበለጠ ንቁ እንድንሆን ያደርገናል (ዮሐ. 16:8፤ 1 ቆሮ 2:12)፣ የበለጠ መንፈሳዊ መረዳት የሚያስችል አቅም (ዮሐ. 3:8፤ 1 ቆሮ. 2:14) እግዚአብሔርን መውደድ

(ሮሜ 5፡5)፣ እና ለሥራው የበለጠ መቀደስን ያስከትላል (ሐዋ. 4፡20፤ 5፡29)። በመሆኑም ሁሉም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ያስፈልገዋል።

# የመንፈስ ጥምቀትን ማበረታታት

እነዚህ ነገሮች እውነት ስለሆኑ፣ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አባላቱን ለመንፈስ ጥምቀት ለማነሳሳት እና ለመምራት ጠንክሮ ይሰራል። ሰዎችህ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ ለማበረታታት እና ለመርዳት የምትጠቀምባቸው አምስት ስልቶች አሉ።

**1. እንዲገነዘቡ መርዳት።** በመጀመሪያ፣ ሰዎች የልምምዱን ተፈጥሮ፣ ዓላማ እና አስፈላጊነት እንዲረዱ በመርዳት በመንፈስ እንዲሞሉ ማበረታታት አለብህ። በጉዳዩ ላይ ብዙ ጊዜ በመስበክ እና በማስተማር ይህን ማድረግ ትችላለህ። አማኞች ስለ መንፈስ የበለጠ እውቀት ሲያገኙ፣ ለእርሱ ምላሽ ለመስጠት እና ለመሞላት በተሻለ ሁኔታ ዝግጁ ይሆናሉ።[1] 72‹

**2. ፍላጎትን ማነሳሳት።** ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፣ "የተጠማ ሁሉ ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ" (ዮሐንስ 7፡37) ብሏል። በሌላ አጋጣሚ "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና" (ማቴ. 5፡6) ሲል ቃል ገብቷል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል የእግዚአብሔር ረሃብ እና ጥማት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው።

ይህንን በመረዳት በእግዚአብሔር መንፈስ የመሞላትን ፍላጎት በሕዝቦቻችሁ ውስጥ መከተት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ የምትችልበት አንዱ መንገድ በመንፈስ መሞላት ሕይወትን እንዴት እንደሚባርክ እንዲገነዘቡ በመርዳት ነው። እነዚህ በረከቶች የመመስከር ሃይል፣ ወደ ከክርስቶስ የመቅረብ እድል፣ የጸሎት አቅም ማግኘት፣ በፈተና ላይ ድል መቀዳጀትና እና ሌሎችንም ያካትታሉ።

በፊታቸው በመንፈስ የተሞላ የሕይወት ጉዞ በማድረግ በሰዎች ልብ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ፍላጎት መፍጠር ትችላለህ። አማኞች በመጋቢው ሕይወት ውስጥ የሚታዩትን የመንፈስ ስጦታዎች እና ፍሬዎች ሲመለከቱ በመንፈስ የመሞላት ፍላጎት በልባቸው ውስጥ ይፈጠራል።

**3. እምነትን ማነሳሳት።** ዳግመኛም ስለ መንፈሱ ሲናገር፣ "በእኔ የሚያምን፣ መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል" (ዮሐንስ 7፡38) ብሏል። ጳውሎስ "በእምነት የመንፈስን ተስፋ እንድንቀበል ነው" (ገላ. 3፡14) ይላል። መንፈሱን የሚቀበሉት በእምነት ስለሆነ፣ አማኞች በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ተስፋዎች ላይ እምነታቸውን እንዲገነቡና መንፈሱን እንዲቀበሉ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡- በሉቃስ 11 ላይ ያለውን የክርስቶስን ቃል ልታስታውሳቸው ትችላለህ። በዚያ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ቃል ገብቷል፡- "እላችኋለሁ፡- ለምኑ ይሰጣችኋል።... የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና..." (ቁ. 9-10፤ ዝከ. ቁ. 13፣ አጽንዖቶች ተጨምረዋል)። በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው ማለት እነርሱንም ጨምሮ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ማለት እንደሆነ አጽንዖት ስጥ። በተጨማሪ ልታካፍላቸው የምትችላቸው ሌሎች ተስፋዎች በማርቆስ 11፡24 እና በሐዋርያት ሥራ 2፡39 ላይ ይገኛሉ። ከዚህም በላይ

[1] የጴንጤቆስጤ አዋጅ፡ 100 የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መግለጫዎች፣ኢ-መጽሐፍ፣ ከ Dec adeofPentecost.org ድህረ ገጽ በነጻ ማውረድ ይገኛል። በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል።

እግዚአብሔር በመንፈስ የሞላቸው እና ለክብሩ የተጠቀመባቸውን ሰዎች ምስክርነት በማካፈል የህዝቡን እምነት መገንባት ትችላለህ።

**4. ተገቢውን ድባብ በማዳበር ።** ምእመኖቻችሁ በመንፈስ እንዲሞሉ የምትረዱበት ሌላው ጠቃሚ መንገድ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተገቢውን ድባብ በማዳበር ነው። የመንፈስ ጥምቀት በተሻለ ሁኔታ የምንለማመደው እምነት ከፍ ባለበት እና የመንፈስ መገኘት ጠንካራ በሆነበት ድባብ ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች የመንፈስን እንቅስቃሴ በትጋት ሲጠብቁ እምነታቸው ከፍ ይላል ምክንያቱም እግዚአብሔር የገባውን ቃል ወዲያውኑ ይፈጽማል ብለው ይጠብቃሉ። ሰዎች አስደናቂ የሆነውን የእግዚአብሔርን አብሮነት ሲገነዘቡ የመንፈስ መገኘት መኖሩን ማረጋገጥ እንችላለን። እንደ ያዕቆብ፣ “በእርግጥ እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ አለ” (ዘፍ. 28፡16) በማለት መመስከር ይችላሉ።

አስታውስ፣ በጴንጤቆስጤያዊ ቀን፣ መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ ስፍራውን ሞላ ፤ ከዚያም ሕዝቡን ሞላ (ሐዋ. 2፡3-4)። እንዲሁ በመጀመሪያ፣ መገኘቱ ይሰማሃል ፤ ከዚያም መንፈሱ ትቀበላለህ። የመንፈስ መገኘት አስቻይ ምክንያቶች ከልብ በሆነ ጸሎት፣ ለቃሉ መታዘዝ፣ በተቀባ አምልኮ እና ለመንፈስ ክፍት መሆን ናቸው።

**5. እድሎችን አመቻች።**. በመጨረሻም፣ ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ ለማየት የምትጠብቅ ከሆነ፣ ለመቀበል ተደጋጋሚ እድሎችን ልታቀርብላቸው ይገባል። የመንፈስ ጸሎት (በልሳን መጸለይ) በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ስብሰባዎች ውስጥ መደበኛ ክስተት መሆን አለበት። በተጨማሪም፣ በመንፈስ የመሞላት ግብዣን የሚያካትቱ መደበኛ የመሠዊያ ጥሪዎችን ማቅረብ አለብህ።

የቤተ ክርስቲያንን የአምልኮ አገልግሎቶች ስታቅድ፣ መጨረሻ ላይ ለጸሎት አገልግሎት በቂ ጊዜ መስጠት አለብህ። ይህ ማለት የአምልኮና የስብከት ጊዜን ማሳጠር ያስፈልግሃል ማለት ነው። በተጨማሪም፣ የምስባክ አገልጋዬች እንዴት ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት እንደሚችሉ ማሠልጠን ያስፈልጋል። በተጨማሪም፣ አማኞች በመንፈስ የሚነቃቁበት የተለየ የጸሎት ጉባኤዎችን እና የቤት ህብረቶችን መለየት ያስፈልግ ይሆናል።

# የመንፈስ ጥምቀትን ለመቀበል ከአማኞች ጋር መጸለይ

ስብከትህን ካቀረብክ በኃላ አማኞች በመንፈስ ለመሞላት ጥሪህን ተከትለው ሲመጡ ቀጥሎ ምን ማድረግ አለብህ? እነዚህን ሰዎች ወደ መንፈስ ጥምቀት ልምድ እንዴት መምራት ትችላለህ?

በመጀመሪያ፣ በእነዚህ አማኞች በመንፈስ ሲሞሉ በሕይወታቸው ስለሚፈጠረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ማወቅህ አስፈላጊ ነው። እንደ በበዓለ ሃምሳ ቀን፣ መንፈስ አስቀድሞ በእነርሱ ላይ ይመጣል (ሐዋ. 2፡3)። ከዚያም በኃይሉና በመገኘቱ በመሙላት በውስጣቸው ይንቀሳቀሳል (ቁ. 4ሀ)። በመጨረሻም፣ መንፈስ ቅዱስ በመንፈስ አነሳሽነት የሆነ ንግግር ከውስጣቸው ሞልቶ 4ለ) ይፈሳል። በአማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁ እነዚህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲከሰቱ መጠበቅ አለብህ።

በሂደቱ፣ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉት ሰዎች በእምነት እና በድፍረት መንቀሳቀስ እንደሚኖርባቸው ልብ ልትል ይገባል። አስታውስ፣ መንፈስን ለመቀበል ልባቸውን የሚያዘጋጀው እምነት ነው፤ የእርሱን መገኘት የሚያመጣው እምነት ነው ፤ እና በመንፈስ አነሳሽነት የሆነ ንግግር ሲናገሩ የመንፈስን ኃይል የሚለቀቀው በእምነት ነው። እነዚህን ነገሮች በልብህ ይዘህ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የመንፈስ ጥምቀት ፈላጊዎችን ወደ መንፈስ ጥምቀት እንዴት መምራት እንዳለብህ እንመልከት።

## ሶስት የእምነት ደረጃዎች

በሉቃስ 11፡9-13፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን እንዴት እንደሚጠይቁ እና እንደሚቀበሉ አስተምሯቸዋል። ይህ ምንባብ፣ በጴንጤቆስጤ ቀን በ120ዎቹ ላይ ከደረሰው ጋር (የሐዋርያት ሥራ 2፡1-4) መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል የሶስት እርከን ሂደትን ይጠቁማል። እነዚህ ሦስት እርምጃዎች በእምነት መጠየቅ፣ በእምነት መቀበል እና በእምነት መናገር ናቸው። በእነዚህ ሶስት የእምነት ደረጃዎች ውስጥ የመንፈስ ጥምቀት ፈላጊዎችን እንዴት መምራት እንደሚችሉ እነሆ፡-

**ደረጃ 1፡ በእምነት መጠየቅ።** በመጀመሪያ፣ መንፈሱን ለመጠየቅ የመንፈስ ጥምቀት ፈላጊዎችን ምራ። "ለምኑ ይሰጣችሁማል" (ሉቃስ 11:9፣ አጽንዖት የተጨመረበት) ኢየሱስ የገባውን ቃል አስታውስ። በንስኃ ጸሎት ውስጥ ንስኃ ገቢን እንደምትመራው ሁሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ በሚጠይቅ ጸሎት የመንፈስ ጥምቀት ፈላጊዎችን መምራት ትችላለህ። ሲጸልዩ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደሚሰማ እና ጸሎታቸውን እንደሚመልስላቸው እያወቁ እንዲያምኑ አስተምሯቸው። የመንፈስ ጥምቀት ፈላጊዎችን እያንዳንዱን መስመር በመድገም ጸሎቱ እንደሚከተለው ልትመራው ትችላለህ፡-

"ጌታ ሆይ፣ በመንፈስ ቅዱስ ልሞላ መጣሁ… መንፈስ በእኔ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን እንደምቀበል ቃል ገብተሃል… ምስክርህ ለመሆን ያን ኃይል እፈልጋለሁ… የሚለምን ሁሉ እንደሚቀበል ቃል ገብተሃል… ስለዚህ፣ ለመቀበል እጠብቃለሁ… በተቀበልኩ ጊዜ፣ በእምነት እናገራለሁ… አልፈራም… መንፈስህ እንደሚነግረኝ በልሳኖች መናገር እጀምራለሁ… መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ አሁን በእኔ ላይ ና።

አብርሃቸው ከጸለይክ በኃላ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደ ሰማ እና አሁን በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላቸው ዝግጁ መሆኑን አረጋግጥላቸው። መንፈስ በእነርሱ ላይ በሚመጣበት ጊዜ ንቁ እንዲሆኑ አበረታታቸው። እርሱን መገኘቱን በንቃት ሊከታተሉት ይገባል። ለመንፈስ መምጣት ምላሽ በመስጠት አብረውህ ጌታን እንዲያመልኩ ጥቂት ጊዜ ልትወስድ ትችላለህ።

**ደረጃ 2፡ በእምነት መቀበል።** አሁን የመንፈስ ጥምቀት ፈላጊዎችን በእምነታቸው ወደ ቀጣይ ደረጃ ምራ። ኢየሱስ "የሚለምን ሁሉ ይቀበላል" (ሉቃስ 11:10፣ አጽንዖት ተጨምሯል) ብሏል። ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ንቁ መቀበል ሳይሆን ንቁ መሆን ነው። "የሚለምን ሁሉ መቀበል አለበት" እያለ ነው። ኢየሱስ ይህ እንዴት እንደሚሆን ነግሮናል። የሚከናወነው በእምነት ተግባር ነው። "ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" ብሏል (ማርቆስ 11፡24፣ አጽንዖት የተጨመረ)።

ጸሎት ፈላጊዎቹን በእምነታቸው ደረጃ ለመምራት፣ እጃቸውን ወደ ሰማይ እንዲያነሱ ጠይቅ፣ እና በእምነት ይህን ቀላል ጸሎት ጸልዩ፡- "ጌታ ሆይ፣ አሁን፣ በኢየሱስ ስም፣ መንፈስ ቅዱስን ተቀብያለሁ። ይህ ጸሎት መንፈስን ለመቀበል እምነታቸውን ያነሳሳላቸዋል። በዚያን ጊዜ፣ "እንደተቀበሉ ማመን!" አለባቸው። ባመኑበት ቅጽበት፣ መንፈሱ በውስጣቸው ይሰማቸዋል እና ይሞላቸዋል። የመንፈስን መገኘት በውስጣቸው እንዲመረምሩ ንገራቸው።

**ደረጃ 3፡ በእምነት መናገር።** አሁን፣ ጸሎት ፈላጊዎቹን በእምነት እንዲራመዱ እና በድፍረት መናገር እንዲጀምሩ አበረታታቸው- ከአእምሮአቸው ሳይሆን ከውስጥ፣ የእግዚአብሔርን መገኘት እንዳለ እያሰቡ እንዲናገሩ አበረታታቸው(ዮሐንስ 7፡38) ። በውስጣቸው ላለው መንፈስ ራሳቸውን ሲያስገዙ ፣ በማያውቁት ቋንቋ መናገር ይጀምራሉ (ሐዋ. 2፡4፤ 10፡46፤ 19፡6)። ንግግራቸው ጴጥሮስ ኢየሱስ የሰጠውን ትእዛዝ በመታዘዝ ከጀልባው ላይ ወጥቶ በውኃ ላይ ሲራመድ ከወሰደው የእምነት እርምጃ ጋር ሊመሳሰል ይችላል። ድፍረት የተሞላበት የእምነት እርምጃው ተአምር አስገኝቷል (ማርቆስ 14፡28-29)።

የእነርሱም እንዲሁ ይሆናል! በእምነት መናገሩን በመቀጠል ከመንፈስ ጋር ሙሉ በሙሉ እንዲተባበሩ እንጂ እንዳይፈሩ አበረታታቸው።

### በልሳን መናገር

በልሳን ስለመናገር ትንሽ ማለት እዚህ ላይ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ይህ ብዙ ጊዜ ከዚህ ቀደም ላልተለማመደው ሰው አዲስ እና ምናልባትም እንግዳ ክስተት ነው። በመንፈስ የተሞላ አማኝ በልሳን ሲናገር በተፈጥሮ ንግግር እንደሚደረገው የሚናገረው ቃል ከአእምሮው እንደማይወጣ መረዳት ያስፈልጋል። ቃላቱ የሚመነጩት ከውስጥ ከመንፈስ ነው። ኢየሱስ፤ “በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፣ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከውስጡ ይፈልቃል” እንዳለ (ዮሐንስ 7፡38፣ ቀጥተኛ ትርጉም)። ጳውሎስ “በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና፤ ምስጢር የሆነውን በመንፈስ ስለ ሚናገር የሚረዳው የለም” (1ኛ ቆሮ. 14፡2)። ደግሞም የግድ መናገር እንደሌለባቸው ጸሎት ለምታደርግላቸው ወገኖች አሳስባቸው። ሂደቱ ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ አሰራር በራሱ ፍሰት የሚመጣ ነው። በቀላሉ እንዲከሰት ግን መፍቀድ እና በእምነት በድፍረት በመናገር ከመንፈስ ጋር መተባበር አለባቸው።

### ከጸሎት በኋላ ምክር መስጠት

ከጸሎት በኋላ ምክር መሰጠቱ አስፈላጊ ነው። በመንፈስ ከተሞሉ የምንሰጠው ምክር ደግሞ ካልተሞሉ የምንሰጠው ምክር የተለያ ነው።

በመንፈስ ለተሞሉ እና በልሳኖች ለሚናገሩት ስትመክር መንፈስን መቀበል በራሱ ፍጻሜ እንዳልሆነ ንገራቸው። ይልቁንም መንፈስ ቅዱስን መቀበል ወደ ታላቅ ዓላማ የሚያደርስ መንገድ ነው። መንፈሱን የተቀበሉበት አላማ ለእግዚአብሔር ለመኖር እና ለክርስቶስ በመንፈስ ሃይል ምስክሮች እንዲሆኑ ብርታት እንዲያገኙ ነው። እንዲሁም በየእለቱ በመንፈስ በመጸለይ ማለትም በልሳኖች በመጸለይ ጊዜ እንዲያሳልፉ ልታበረታታቸው ያስፈልጋል። ይህ ልምምድ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያጠናክራቸዋል፣ እናም የመንፈስን ህልውና ያሳስባቸዋል (1 ቆሮ. 14፡4)።

በመንፈስ ላልተሞሉ ሰዎች ደግሞ ተስፋ እንዳይቆርጡ ንገራቸው። “ለምኑ ይሰጣችሁማል” የሚለው (ሉቃስ 11፡9፣ አጽንዖት ተጨምሯል) የኢየሱስ የተስፋ ቃል አሁንም እውነት መሆኑን አረጋግጥላቸው። ኢየሱስ እንዳስተማረው እንዲለምኑ፣ እንዲፈልጉ እና እንዲያንኳኩ ንገራቸው። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ፣ “የሚለምን ሁሉ ይቀበላል” (ቁ. 10፣ አጽንዖት የተጨመረበት) ኢየሱስ የገባውን ቃል ማስታወስ ይኖርባቸዋል። እንደገና መጸለይ ይፈልጉ እንደሆነ ልትጠይቃቸው ትችላለህ። ፈቃደኛ ከሆኑ፣ በድፍረት እምነት እንዲያደርጉት በማበረታታት ከላይ ያለውን ሂደት እንዲደግሙት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የሚቀበሉትን ማንቀሳቀስ

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ኢየሱስ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅበትን ዋና ምክንያት መርሳት የለብህም። እርሱ የሚያጠምቀው በመንፈስ ቅዱስ ደቀ መዛሙርት ምስክሮቹ እንዲሆኑ ኃይል እንዲያገኙ ነው (ሐዋ. 1፡8)። ስለዚህ በመንፈስ የተሞሉትን ወዲያውኑ ለቤተሰቦቻቸው እና ለጓደኞቻቸው መመስከር እንዲጀምሩ ማበረታታት አለብህ። የወንጌል ስርጭት፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ

እና የተልእኮ አገልግሎት እንዲገቡ ልትመራቸው ይገባል። በወንጌልም ሆነ በሐዋርያት ሥራ ኢየሱስና ሐዋርያት ያደረጉት ይህንኑ ነው።[2]

ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደተቀባ (እንደተጠመቀ) በኃይል ማገልገል ጀመረ (ሉቃስ 3:22-23፤ 4:8፤ 14፣ 18-19፤ 5:17)። ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈሱን ሲቀበል ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆሞ ሦስት ሺህ ሰዎች ወደ ጌታ እስኪመጡ ድረስ በኃይል ሰበከ (ሐዋ. 2፡14-41)። ወደ ክርስቶስ የመጡትም በኃይል መሰከረዋል። ከምሥክራቸው የተነሣ፣ "ጌታ የሚድኑትን ዕለት ዕለት በቍጥራቸው ላይ ይጨምርላቸው ነበር" (ቁ. 47)። ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ እግዚአብሔር በድጋሚ መንፈሱን በኢየሩሳሌም ደቀ መዛሙርት ላይ ባፈሰሰ ጊዜ፣ "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ" (4፡ 31)። ይህ አብነት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሁሉ የቀጠለ ሲሆን ዛሬም በጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሊቀጥል ይገባል።

[2] በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ለማግኘት ምዕራፍ 37: "የጠፉትን ወንጌላዊነት" እና ምዕራፍ 39ን ተመልከት፡- "አዲሶችን አብያተ ክርስቲያናት መትከል" የሚለውን ተመልከት።

# ~ ምዕራፍ 21 ~

# በመንፈስ ኃይል ማገልገል

ሄንሪ እና ሚስቱ ሩት በደቡብ ምሥራቅ ላይቤሪያ በግሎፋከን መንደር ለሚገኙ ጣዖት አምላኪዎችን ሚስዮናውያን ሆነው እያገለገሉ ነበር። ለረጅም ጊዜ ሄንሪ ህዝቡ ጣዖቶቻቸውን ትተው ወደ ኢየሱስ እንዲመለሱ ያሳስብ ነበር፣ ነገር ግን ምላሹ አጥጋቢ አልነበረም።

አንድ ቀን የመንደሩ አለቃ እና ሽማግሌዎቹ ሄንሪን ጎበኙ። አለቃው ሄንሪን እንዲህ አለው፡- “የአባቶቻችንን ጣዖታት ትተን ወደ አምላክህ እንድንመለስ ስትጠይቅ ነበር። ከጣዖቶቻችን ይልቅ አምላካችሁ ኃያል ነው ትላላችሁ ነገር ግን የምትመኩበትን የእግዚአብሔርን ኃይል አላየንም። ኃይሉን ብታሳየን እርሱን ለማገልገል ጣዖቶቻችንን መተውን እናስባለን።

ሄንሪ የመንደሩ አለቃ እርሱን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም እየተገዳደረ እንደሆነ ተረዳ! ስለዚህ “ጌታ ሆይ፣ ኃይልህን ለግሎፋከን ሰዎች አሳይ” ሲል ጸለየ። እግዚአብሔር የሄንሪን ጸሎት መለሰ፣ እና ብዙም ሳይቆይ በሄንሪ አገልግሎት ኃይሉን ማሳየት ጀመረ።

አንድ ቀን ጠዋት የአለቃው ልጅ ዓይኑን የሸፈነውን የዓይን ሞራ ግርዶሹን እንዲያስወግድለትና በግልጽ እንዲያይ እንዲጸልይ ሄንሪን ጠየቀው። ሄንሪ እጁን በሰውየው ላይ ጭኖ ጸለየ፣ እግዚአብሔርን ተአምር ጠየቀ። እግዚአብሔር ወዲያውኑ ጸሎቱን ተቀበለ እናም የልጁ የዓይን ሞራ ግርዶሽ ጠፋ!

ከዚያ በኋላ ጌታ በግሎፋከን ሰዎች መካከል ተአምራትን ማድረጉን ቀጠለ። በአንድ ወቅት ልትቀበር በቀረበች በሞተች ሴት ላይ እጁን እንዲጭን ጌታ ተናገረው። ሁሉን በሚገርም ሁኔታ፣ የሴቲቱ ዓይኖች ተከፈቱ፣ እና ህይወቷ ተመለሰ። በእነዚህና በሌሎች ተአምራት ምክንያት፣ አለቆቹና ሽማግሌዎቹ ከሌሎች የግሎፋከን መንደር ሰዎች ጋር በመሆን ወደ እግዚአብሔር ዘወር ብለው በኢየሱስ አመኑ። በመጨረሻም በመንፈስ ቅዱስ የምታምን ጠንካራ ቤተ ክርስቲያንም ተቋቋመ።

በታላቁ ተልእኮው፣ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤16 ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ሲል አዞል። በዚህ ትእዛዝ ላይ ጨምሮ፣ “የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ፤ 18 እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፤ የሚገድል መርዝ ቢጠጡ እንኳ አይጐዳቸውም፤ እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወሳሉ” (ማር. 16፡15-18)። በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ውስጥ፣ ሰዎች ምሥራቹን ሲሰሙ እና የመንፈስን ኃይል ሲያሳዩ እምነታቸውን በኢየሱስ ላይ ያደርጋሉ።

ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በመንፈስ ኃይል የማገልገልን አስፈላጊነት ያብራራል። ይህን በማድረግ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 የተዘረዘሩትን ስጦታዎች መገለጫ ከአገልግሎት ዓላማቸው ጋር እንመለከታለን። በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች አሠራር አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችን ይሰጣል።

# በመንፈስ ኃይል ማገልገል

እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሚከተሉት ምልክቶች በመንፈስ ኃይል እንዴት ማገልገል እንዳለበት ማወቅ አለበት። እንዲህ ያለው አገልግሎት በአዲስ ኪዳን መደበኛ ሥርዓት ነበር፣ ዛሬም መደበኛ የአገልግሎት መሆን አለበት።

የኃይል አገልግሎት መነሻው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ስለዚህ በመንፈስ ኃይል ለማገልገል የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለበት። ኢየሱስ ይህን ተረድቷል። ለዚህም ነው ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን “ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤ 5 ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ” ” (ሐዋ. 1፡4-5)። ኢየሱስም ቀጥሎ “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” (ቁ. 8) ሲል ተስፋ ቃልን ሰጣቸው።

በሚያሳዝን ሁኔታ ዛሬ በአፍሪካ ያሉ ብዙ መጋቢያን የመንፈስን ኃይል አልታጠቁም። እነዚህን መጋቢ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ስላልሆኑ፣ በአገልግሎታቸው ውስጥ የመንፈስን ኃይል መገለጥ አይለማመዱም። ይህ አሳዛኝ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞላህ “ከላይ ኃይልን እስክትለብስ” (ሉቃስ 24፡49) እግዚአብሔርን መፈለግ አለብህ። በበዓለ ሃምሳ ቀን የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት እንደሆነው (የሐዋርያት ሥራ 2፡1-4) እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ይሞላሃል ለአገልግሎትም ኃይል ይሰጥሃል።[1]

በተጨማሪም ምንም እንኳን በመንፈስ የተሞሉ ቢሆኑም በአገልግሎታቸው ውስጥ የመንፈስን ኃይል እምብዛም የማይለማመዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን አሉ። ከእነዚህ መጋቢያን ውስጥ ብዙዎቹ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ዋና ዓላማ በልሳን መናገር ብቻ እንደሆነ ያስባሉ። እነዚህን ሰዎች ጠዋት ጠዋት ሸጉጡን እንደሚያጸዳ፣ ጥቂት በአየር ላይ ተኩሶ፣ ሸጉጡን አስቀምጦ እና ሚስቱን ጥሩ ስጋ ጥብስ

[1] በዚህ ርዕስ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 2ን “የመንፈስ አካል” እና ምዕራፍ 20፡ “አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት ተመልከት።

እንድታበስል እንደሚጠብቅ የመንደር አዳኝ ናቸው። ብዙ ጫጫታ ያሰማሉ፣ ነገር ግን ምንም ውጤት የላቸውም።

በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አስፈላጊ መገለጫ ቢሆንም በመንፈስ የመሞላት ዋና ዓላማ ግን አይደለም። በመንፈስ የመሞላት ዋና ዓላማ ለአገልግሎት መብቃት ነው (ሐዋ. 1፡8)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በልሳን ከመናገር መንፈስ ኃይል ወደ ታጠቀ አገልግሎት መሄድ አለብን። በምልክቶች ታጅበን በመንፈስ ኃይል ማገልገልን መማር አለብን። እንዲህ ያለው አገልግሎት ለእግዚአብሔር ሕዝብ በረከትን ያመጣል እና ኃጢአተኞችን ወደ ኢየሱስ ይስባል።

# በመንፈስ ኃይል የታጠቀ አገልግሎት ምሳሌ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የኢየሱስን እና የደቀ መዛሙርት አገልግሎት በወንጌሎች እና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለውን በማጥናት እና በመምሰል በመንፈስ ኃይል እንዴት ማገልገል እንደሚቻል በተሻለ መንገድ መማር ይችላል።

## የኢየሱስ አገልግሎት

ኢየሱስ በእውነት በሥጋ የተገለጠ አምላክ ቢሆንም መንፈስ ቅዱስን የሞላበት ሰው ሆኖ አገልግሎቱን ለመፈጸም መረጠ። መጽሐፍ ቅዱስ “የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ” (ፊልጵ. 2፡7) ይላል። በዚህ መንገድ ኢየሱስ በመንፈስ ኃይል የታጠቀ አገልግሎት ዋነኛ ምሳሌያችን ሆነ።

ከክርስቶስ መምጣት ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ኢሳይያስ መሲሑ ጥሪውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚፈጽም ተንብዮአል (ኢሳ. 61፡1-2)። የኢሳይያስ ትንቢት ሲፈጸም ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን የጀመረው “እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል ቀባው እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያብሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ” (ሐ.ሥ 10፡ 38)። እነዚህ እና ሌሎች የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ኢየሱስ አገልግሎቱን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዳከናወነ ያሳያሉ (ሉቃስ 4፡1፣ 14፤ 5፡17 ይመልከቱ)። ከኢየሱስ አገልግሎት ጋር የነበሩት ተአምራት ምልክቶች እና ድንቆች ሰዎች እርሱን እንዲከተሉ ለማሳመን ረድተዋል (ማቴ. 4፡23-25፤ 9፡35-36፤ ዮሐ. 2፡11)።

ጌታችን በአገልግሎቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ላይ በፈቃደኝነት መደገፉ ትልቅ ምሳሌ ይተውልናል። እንደ ኢየሱስ እኛም በመንፈስ ቅዱስ መታጠቅ አለብን። እንደ እርሱ እኛም ምሥራቹን በድፍረት ለሁሉም ማወጅ አለብን። በተመሳሳይ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተደረጉ ምልክቶችና ድንቆች የምናውጀውን ቃል እንዲያጸናው በእግዚአብሔር ልንታመን ይገባል።

## የሐዋርያት አገልግሎት

ከኢየሱስ አገልግሎት በተጨማሪ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉት የሐዋርያት እና የሌሎች ደቀ መዛሙርት ያገለገሉት አገልግሎት በመንፈስ ኃይል ስለ ማገልገል ግሩም ምሳሌ ናቸው ። እነዚህ ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ኃይል ማገልገልን የኢየሱስን በመንፈስ ኃይል መታጠቅ በመመልከት እና ይህንኑ አካሄድ በመከተል ተምረዋል። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ደቀ መዛሙርቱ ያከናወኗቸው ተአምራት ሁሉ በመሠረቱ ኢየሱስ በወንጌል ያደረገው ተአምራት አይነት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው።

ሐዋርያት በመንፈስ ስለ መሞላት የኢየሱስን ምሳሌ ተከትለዋል። እርሱ እንዳገለገለው ከማገልገላቸው በፊት፣ በመንፈስ መታጠቅ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቁ ነበር። እና ልክ እንደ ኢየሱስ፣ እነርሱን ተከትሎ ወደ ክርስቶስ የሚመጡት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መታጠቃቸውን እና በመንፈስ ኃይል ለአገልግሎት መነሳሳታቸውን ያረጋግጡ ነበር (ሐዋ. 2፡38-39፤ 8፡14-17፤ 9፡17፤ 19፡1-7 ይመልከቱ)።

እነዚህ ምሳሌዎች እውነተኛ የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ከተፈጥሮ እውቀት፣ ክህሎት እና ችሎታ በላይ እንደሆነ ያስተምሩናል። የአዲስ ኪዳን አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እና መንፈሳዊ ኃይልን መታጠቅ ይጠይቃል። በመንፈስ ቅዱስ ቅባት፣ ኢየሱስ እና ሐዋርያት የመዳንን መልእክት በምልክቶች ታጅበው አውጀዋል።

# የምልክቶች እና ድንቆች ሚና

ዛሬ የወንጌል አገልግሎት ምልክቶች እና ድንቆች ሚና ምንድን ነው? ምልክቶች፣ ድንቆች እና ተአምራት እግዚአብሔር ለወደቀው የሰው ልጅ ያለውን ፍቅራዊ ርህራሄ ያሳያሉ። ወንጌል ሕይወትን የመለወጥ ኃይል እንዳለው ያሳያሉ። እንደ መንገድ ምልክቶች፣ ኢየሱስን ፈዋሽ፣ አዳኝ እና ነጻ አውጪ አድርገው ይጠቁማሉ። ዮሐንስ እንዲህ ሲል ይነግረናል፣ "ብዙ ሰዎችም በሽተኞችን በመፈወስ ያደረጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች ስላዩ ተከተሉት" (ዮሐ. 6:2፣ 20:30-31፣ ሐዋ 3:1-10ን) ተመልከት። እግዚአብሔር ዛሬም በአገልግሎታችን ተመሳሳይ ነገር እንዲከሰት ይፈልጋል።

ኢየሱስ በተጨማሪ በአጋንንት ሃይሎች የተያዙት የገሃነም ደጆች፣ ቤተ ክርስቲያንን መስፋት እደማይገቱ ተናግሯል (ማቴ. 16፡18)። ኢየሱስ የተጨቆኑትን ነጻ ለማውጣት እና በዲያብሎስ መንግሥት ላይ ግዛት ለማሳየት አጋንንትን አወጣ (ማቴ. 12፡28-29፤ ሉቃ. 11፡20-22)። ኢየሱስ መንፈሱን ለሚቀበሉ እና ለሥልጣኑ ራሳቸውን ለሚያስገዙ ሁሉ ይህንኑ ኃይልና ሥልጣን ሰጥቷቸዋል (ማቴ. 10፡1፤ ማር. 3፡14-15፤ ሉቃስ 9፡1-2፤ ሐዋ. 1፡8)።

የጴንጤቆስጤው መጋቢ የመንፈስ ኃይል ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያኑ አባል የተሰጠ መሆኑን ማወቅ አለበት (ሐዋ. 2፡39)። እግዚአብሔር እያንዳንዳቸውን በቅዱስ መንፈሱ ሊሞላቸው፣ ለምስክርነት ስልጣን ሊሰጣቸው እና የተለያዩ የመንፈስ ስጦታዎችን ሊሰጣቸው ይፈልጋል። ይህንን የሚያደርገው ለቤተ ክርስቲያን "የጋራ ጥቅም" (1ቆሮ. 12፡7) እና በምድር ላይ ለመንግሥቱ እድገት ነው(ማርቆስ 16፡20 ተመልከት)።[2]

# መንፈሳዊ ስጦታዎች

በመንፈስ ጥምቀት የተቀበልነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአገልግሎት የሚገለጠው በዋነኛነት በመንፈሳዊ ስጦታዎች ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10፣ ጳውሎስ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰሩ ስለሚገባቸው ዘጠኝ የመንፈስ ስጦታዎች ተናግሯል። እነዚህ ዘጠኙ ስጦታዎች አንዳንድ ጊዜ የተገለጡ ስጦታዎች ተብለው ይጠራሉ፤ ምክንያቱም፣ በቁጥር 7 ላይ ጳውሎስ እነርሱን "የመንፈስ መገለጥ" በማለት

---

[2] በምዕራፍ 20፡ "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" በሚለው የቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈስ እንዲሞሉ ስለመምራት የበለጠ ማወቅ ትችላለህ።

ጠርቷቸዋል። እነዚህ ስጦታዎች የአብን ፈቃድ ለመፈጸም በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ደቀ መዛሙርት አማካኝነት የተሰጡ ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ቅባቶች ተብለው ተገልጸዋል። ዘጠኙ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሶስት ምድቦች ሊከፋፈሉ ይችላሉ። የመጀመሪያው ምድብ የመገለጥ ስጦታዎች ሲሆኑ የእውቀት ቃል፣ የጥበብ ቃል እና መናፍስትን መለየትን ያጠቃልላል። ሁለተኛው ምድብ ትንቢታዊ ሥጦታ ሲሆን ትንቢትን፣ የተለያዩ ዓይነት ልሳኖችን እና የልሳኖችን ትርጓሜ ያካትታል። ሦስተኛው ምድብ የኃይል ስጦታዎች ናቸው፣ እርሱም የፈውስ ስጦታዎችን፣ እምነትን እና ተአምራዊ ኃይሎችን ያካትታል፡፡ ምልክቶችና ድንቆች የሚገለጡት በዋናነት በኃይል ሥጦታ ነው።[3]

## የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ

መንፈስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚሰጡት በሦስት ምክንያቶች ነው፡- በመጀመሪያ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ይሰጣሉ (1ቆሮ. 12፡7፤ 14፡12፣ 26)። በመንፈሳዊ ስጦታዎችን በመጠናከር ፣ ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን ለአገልግሎት በብቃት ማዘጋጀት ትችላለች (ኤፌ. 4፡11-12)።

ሁለተኛ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚሰጡት ቤተ ክርስቲያን ለጠፉት ወንጌልን በብቃት እንድታሰራጭ ለማስቻል ነው። ይህ የመንፈሳዊ ስጦታዎች ተግባር በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በዋነኝነት የሚታይ ነው። ሥጦታዎቹ በግንባር ቀደምት የስብከተ ወንጌል እና በተልእኮዎች ጋር በተያያዘ ተገልጠዋል።

በመጨረሻም፤ መንፈስ ቅዱስ ሌሎች በመንፈስ ኃይል የታጠቁ አጥቢያዎችን እንዲተከሉ እና እንዲስፋፉ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል። የቤተ ክርስቲያን ተከላ የተሳካ የሚሆነው በእግዚአብሔር ኃይል የታጀበ ምልክቶች ወንጌል በሚሰበክበት ጊዜ ነው። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተነገሩት የሄንሪ እና የሩት ታሪክ ይህንን እውነት ያሳያል።

## የመንፈሳዊ ስጦታዎች አሠራር

ለቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ አሠራር መንፈሳዊ ኃይል አስፈላጊ ነው። ሰዎች ግን መንፈሳዊ ኃይልን አላግባብ ሊጠቀሙ ይችላሉ። የመንግሥት ባለሥልጣን የፖለቲካ ሥልጣኑን አላግባብ እንደሚጠቀም ሁሉ የጴንጤቆስጤያዊ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ኃይሉን አላግባብ መጠቀም ይችላል። ይህንን ለመከላከል፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12-14 ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በአግባቡ ለመስራት የተወሰኑ መመሪያዎችን አስቀምጧል።

በምዕራፍ 13 ላይ፣ ሐዋርያው መንፈሳዊ ስጦታዎች የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫዎች እንደሆኑ መረዳት አለባቸው ብሏል። ስለዚህ ሌሎችን መውደድ እና ለሌሎች ግድ መሰኘት የእያንዳንዱን የመንፈስ መገለጥ የመገለጣቸው መርህ መሆን አለበት።

በምዕራፍ 14 ላይ ጳውሎስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በአጥቢያ ጉባኤ፣ በተለይም የትንቢትን፣ የልሳኖችን እና ልሳኖችን የመተርጎም ስጦታዎች በትክክል እንዲገለጡ የተወሰኑ ህጎችን አውጥቷል። ትንቢታዊ ንግግሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውዥንብር መፍጠር የለባቸውም ይላል። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማበረታታት እና ለማጽናናት ማገልገል አለባቸው (ቁ. 3)። በተጨማሪም፣ የትንቢት ስጦታዎች ሁል ጊዜ በሥርዓት መቅረብ አለባቸው (ቁ. 27-32)። በመጨረሻም፣ የትንቢታዊ

[3] የእነዚህን ስጦታዎች ሙሉ ዝርዝር ከትርጉማቸውና ከዓላማዎቻቸው ጋር፣ አባሪ 2ን ተመልከት፡- “የ1 ቆሮንቶስ 12:8-10 መገለጥ ስጦታዎች።

ንግግሮች መንፈስ እና ይዘት ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከመቀበላቸው በፊት "በጥንቃቄ መመዘን" አለባቸው (ቁ. 29)።

ዛሬ በመላው አፍሪካ የትንቢት ስጦታዎች አላግባብ ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፤ የኃይል ስጦታዎችም እንዲሁ። ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት ፈውስና ተአምራትን ወደ ንግድ ለውጠውታል። እነዚህ ሙሰኛ ሰዎች ያለምንም ሀፍረት የውሸት ምልክቶቻቸውን እና ድንቆችን ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለሚሹ ሰዎች ያቀርባሉ። ነገር ግን፣ በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣ ተአምራት የተሸጠበት ምንም ዓይነት ምሳሌ አናገኝም።

እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያንህ ከእንደዚህ አይነት ፈሪሃ እግዚአብሔር ከሌላቸውን ድርጊቶች እንድትታቀብ መስራት አለብህ። ይልቁንስ በአገልግሎትህ ምልክቶችን እና ተአምራትን እንዲገለጡ እግዚአብሔርን በትህትና ታመን። ይህን የእግዚአብሔርን የሚያደርገውን ተአምራት ለገበያ ለማቅረብ ለሚደረገው ፈተና እጅ መስጠት የለብህም። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "ሕሙማንን ፈውሱ፣ ሙታንን አስነሡ፣ ለምጻሞችን አንጹ፣ አጋንንትን አውጡ" ብሎ አዘዛቸው። ከዚያም "በነጻ ተቀበላችሁ ፤ በነጻ ስጡ" (ማቴ. 10:8) እውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መንፈሳዊ ስጦታዎች እንደፈለገው ላለመጠቀም ስጦታው ከእርሱ እንዳልሆነ ሁልጊዜ ያስተውላል። ይልቁንም፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በመሆናቸው ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው እርሱ "እንደ ፈቀደ" ብቻ ነው የሚል ግንዛቤ መያዝ አለብን (1ቆሮ. 12፡11)።

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የመንፈሳዊ ስጦታ መገለጫ መገምገም ትችላለህ።

**1. መገለጡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ ነውን?** ከቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ ትምህርቶች ጋር የማይጣጣም ከሆነ ውድቅ መደረግ አለበት። የእግዚአብሔር መንፈስ ከእግዚአብሄር ቃል ጋር ፈጽሞ አይቃረንም።

**2. የስጦታው መገለጥ እግዚአብሔርን ያከብራል?** መንፈሳዊ ስጦታዎች አገልጋዩን ከፍ ለማድረግ አልተሰጡም ፤ የተሰጡት እግዚአብሔርን ለማክበር እና ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ለመጠቆም ነው (ማቴ. 15፡31፤ ማር. 2፡12)። የመንፈሳዊ ሥጦታ መገለጥ ከእግዚአብሔር ሌላ ማንንም ከፍ ከፍ ለማድረግ የሚፈልግ ከሆነ ሊጠየቅ ይገባል (ዮሐ. 16፡13-15፤ 1ቆሮ. 1፡29)።

**3. መገለጡ ቤተ ክርስቲያንን ያንጻልን?** ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተሰጥተዋል። አንድ መገለጫ ግራ መጋባትን ከፈጠረ ወይም ሰዎች በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት የሚያዳክም ከሆነ ውድቅ መሆን አለበት።

**4. መገለጡ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለማራመድ ያገለግላል?** ስለዚህ በጸጋ ስጦታዎች የሚሠሩ የክርስቶስ ምስክሮች መሆን አለባቸው። የመንፈስ መገለጥ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ተልዕኮ ለማዘናጋት ወይም ወደ ኋላ ለመመለስ የሚሞክር ከሆነ መፈቀድ የለበትም።

## መንፈሳዊ ስጦታዎች ማበረታታት

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን መንፈሳዊ ስጦታዎች አላግባብ ከመጠቀም መጠንቀቅ ቢኖርብህም፣ ይህ የአንተ ዋና ጉዳይ ሊሆን አይገባም። የአንተ ዋና ትኩረት የስጦታዎችን መገለጥ ማበረታታት መሆን አለበት። ስለ ምልክቶች እና ድንቆች በማውራት በጭራሽ መርካት የለብህም። ይልቁንም፣ በቤተ ክርስቲያን እና በገበያ ቦታ እንዲገለጡ ማስተማር አለብህ። ይህንን በአራት መንገዶች ማድረግ ትችላለህ፡-

በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ስላለው ከፍቅር የመነጨ አሳቢነት፣ እና እንዴት ሰውን ለማዳን፣ ለመባረክ እና ለመፈወስ የጸጋውን እጁን ሊዘረጋ እንደሚፈልግ ለምእመናን ማስተማር አለብህ። በተጨማሪም እግዚአብሔር በመንፈስ በተሞላ አገልግሎት እንዴት ሊጠቀምባቸው እንደሚፈልግ እና በእነርሱ ሕይወት መንፈሳዊ ስጦታዎችን ሊገለጥባቸው እንደሚችል ማስተማር ያስፈልጋል።

ሁለተኛ፣ በመንፈስ የተሞላ አገልግሎትን በሰዎች ፊት በአርአያነት ማሳየት አለባችሁ። አባላት መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንዲለማመዱ ለማበረታታት ከሁሉ የተሻለው መንገድ እንዴት እንደሚደረግ ማሳየት ነው። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያደረገው ይህንኑ ነው። አጋንንት ያደረባቸውን ሰው በማዳን (ሉቃስ 8፡26-39) እና የታመመች ሴትን በመፈወስ የሞተችውን ሴት ልጅ በማስነሳት በመንፈስ ኃይል እንዴት እንደሚያገለግሉ አሳያቸው (ቁ. 40-56)። ከዚያም "የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩና ድውያንን እንዲፈውሱ ላካቸው" (9፡2)። ስለዚህ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላህ እና ደግሞም እንዲሞላህ መፍቀድ አለብህ። ከዚያም፣ በራስህ ህይወት እና አገልግሎት መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመግለጥ እንዲጠቀምብህ እርሱ ላይ መደገፍ አለብህ።

ሦስተኛ፣ አባሎት ለመንፈስ ቅዱስ መነሳሳት ምላሽ እንዲሰጡ እና መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመግለጥ በእምነት እንዲሠሩ ማበረታታት አለብህ። በአምልኮ እና በስብከተ ወንጌል ጊዜ ህዝቡ ስጦታዎችን እንዲለማመዱ እድሎችን መስጠት አለብህ።

በመጨረሻም፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ተገቢውን ድባብ ለማዳበር የመንፈሳዊ ስጦታዎችን መገለጥ በቤተ ክርስቲያን ማበረታታት አለብህ። እንዲህ ያለው ድባብ መገለጫው የእግዚአብሔር መገኘት በእምነት መናፈቅ ነው። እግዚአብሔር ህዝቦቹ በእውነተኛ ውዳሴ እና አምልኮ ልባቸውን ሲከፍቱለት መገኘቱን ይገልፃል። እግዚአብሔር አንዳች ነገር እንዲሰራ የሚጠባበቅ እምነት የሚፈጠረው የእግዚአብሔር ሕዝብ እጁን እንዲዘረጋ እና መገኘቱን እንዲጠባበቅ ሲበረታታ ነው " እግዚአብሔርም በምልክት፣ በድንቅና በልዩ ልዩ ታምራት እንዲሁም እንደ ፈቃዱ በታደሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ስለዚሁ ነገር መስክሮአል" (ዕብ. 2፡4)።

---

እውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የመንፈስ ቅዱስ ሰው ለመሆን ይጥራል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በምልክቶች እና ድንቆች ማገልገልን ዓላማቸው ያደርጋል፣ ሕዝቡም እንዲሁ እንዲያደርግ ያስተምራል።

# ~ ምዕራፍ 22 ~

# በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ መሳተፍ

ኢየሱስ ከሰይጣንና ጭፍሮቹ ጋር ታላቅ መንፈሳዊ ትግል ውስጥ እንደገባ ተረድቶ ነበር። አንድ ጊዜ ከዓይነ ስውር እና ዲዳ ከነበረው ሰው ጋኔን አስወጣ። ሰውየው ማየትና መናገር ሲጀምር ሰዎቹ በመገረም ተመለከቱ። አንዳንዶች፣ "ይህ የዳዊት ልጅ ሊሆን ይችላል?" ብለው ጠየቁ። ሌሎች በሹክሹክታ፣ "ይህ አጋንንትን የሚያወጣ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ነው" (ማቴ. 12፡22-24) አሉ።

ኢየሱስም የሚያስቡትን አውቆ፣ "እርስ በርሱ የሚለያይ መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች፣ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም" አላቸው። ከዚያም "እኔ አጋንንትን የማወጣ በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች" ሲል ፈውሱ እንዴት እንደተከናወነ ገለጸላቸው። ከዚያም "ወይስ አንድ ሰው ወደ ኀይለኛ ሰው ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣ አስቀድሞ ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር እንዴት አድርጎ ይሳካለታል? ኋላም ቤቱን መበዝበዝ ይችላል" አለ (ማቴ. 12፡25-29)።

ዛሬም ተመሳሳይ ነው ፤ እኛም ከክፉ ኃይሎች ጋር ታላቅ ግጭት ውስጥ አለን። ሰዎችን ከኃጢአትና ከሰይጣን መዳፍ ነፃ ለማውጣት መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ መግባት አለብን። መጀመሪያ ጠንካራውን መንፈስ ማሰር አለብን። ያኔ ቤቱን መዝረፍ እንችላለን። ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የአጋንንት በመዋጋት እና በማሸነፍ ብቃት ያለው መሆን እንዳለበት ያብራራል።

## መንፈሳዊ ጦርነትን መረዳት

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከመመለሱ በፊት፣ ለቤተክርስቲያኑ ታላቅ ተልእኮ ሰጠ። ተከታዮቹን "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. 28፡19-20) በማለት አዘዛቸው።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተልእኮውን መወጣት የጀመሩበት ታሪክ ነው።

ታላቁ ተልእኮ ዛሬም በስራ ላይ ነው። “እስከ ዓለም ፍጻሜ” ድረምስ በሥራ ላይ ይውላል (ቁ. 20)። ይህንን ተልእኮ በብቃት ለመወጣት፣ ቤተ ክርስቲያኑ እና አመራሯ ሰይጣንንና አጋንንቱን እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው።

## የመንፈሳዊ ጦርነት እውነታ

መንፈሳዊ ጦርነት እውን ነው። እውነተኛ ጠላት አለ፣ እናም እኛ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ልንዋጋው እና ማሸነፍ ያለብን እውነተኛ መንፈሳዊ ጦርነቶች አሉ። ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በጻፈው ደብዳቤ ላይ ስለዚህ መንፈሳዊ ጦርነት እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- “ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኀይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው” (ኤፌ. 6:12)።

ሐዋርያው በመቀጠል የክርስቶስ አገልጋዮች ከክፋት ጋር በሚደረገው ጦርነት የሚጠቀሙበት ኃይለኛ መንፈሳዊ መሣሪያዎች የተሰጣቸው እንዴት እንደሆነ ገልጿል፡- “ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኀይል ያለው ነው” (2ቆሮ. 10:4)።

በመላው አፍሪካ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በቂ የወንጌል ምስክር አላገኙም። እነዚህ ሰዎች የሚኖሩት የክርስትናን መስፋፋት በሚቃወሙ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች የተያዙ ሰዎች ባሉበት ቦታዎች ነው። እነዚህ  ቦታዎችና ሀይማኖታዊ ሥርአቶች በኃያላን የአጋንንት አለቃዎች ቁጥጥር ስር ናቸው። ስርዓቱ በጠቅላላ በሰይጣን፣ “በአጋንንት አለቃ” ቁጥጥር ስር ነው (ማር. 3:22፤ 1 ዮሐንስ 5:19)። እነዚህን ሰዎች ለማዳን "ብርቱው መንፈስ" ታስሮ መባረር ይኖርበታል (ማቴ. 12:28-29)። ስለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ተልእኮ በተሳካ ሁኔታ መወጣት ካለባት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መንቀሳቀስን መማር አለባት። በተጨማሪም የአጋንንት ሃይሎችን እንዴት መግጠም እና ማሸነፍ እንዳለበት ማወቅ አለበት።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን” በማለት እንዲጸልዩ አስተምሯቸዋል (ማቴ. 6:10)። በአንድ ወቅት እንዲህ አላቸው፡- “እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔር መንግሥት በኀይል ስትመጣ እስከሚያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ” (ማር.9:1)። ኢየሱስ የጴንጤቆስጤያዊ ቀንን እየተናገረ ነበር። በጴንጤቆስጤያዊ ቀን ደቀ መዛሙርቱ “ከላይ ኃይልን ይለብሳሉ” (ሉቃስ 24:49፤ ሥራ 2:4)።

ዛሬ፤ አንድ ሰው በዳነ፣ በተፈወሰ፣ አርነት በወጣ ወይም በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ቁጥር የእግዚአብሔር መንግስት በኃይል ትመጣለች። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል እንድትመጣ አማኞችን ደጋግሞ እንዲጸልዩ መምራት አለበት።

## የመንፈሳዊ ጦርነት ተፈጥሮ

መንፈሳዊ ጦርነት በክፉ እና በበጎ ፣ በቅዱስ እና በእርኩስ ኃይላት መካከል የሚደረግ ግጭት ነው። በዚህ ዘመን፣ በሰይጣንና በአጋንንቱ እና በእውነተኛይቱ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ቀጣይ ትግል ነው። ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን የማዳን ተልእኮ ለአሕዛብ እንዳይደርስ አቅሙን ሁሉ ሰብስቧል። እርሱ ነፍሰ ገዳይ እና ውሸታም ነው እናም “ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ” ይፈልጋል (ዮሐንስ

8፡44፤ 10፡10)። እርሱና አጋንንቱ የሰዎች አእምሮ የወንጌልን እውነት ለማሳወር ይሠራሉ (2ቆሮ. 4፡3-4)። ዲያብሎስ እግዚአብሔርን ስለሚጠላ የእግዚአብሔር የሆኑትን ሊጎዳ ይፈልጋል። ሆኖም እግዚአብሔርን ሊያሸንፈው እንደማይችል ያውቃል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሚወዳቸውን የሰውን ዘር ማሰቃየትና ማጥፋት ምርጫው አድርጎ እየሰራ ይገኛል።

ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ መጣች አበሰረ (ማርቆስ 1፡14-15፤ ሉቃስ 8፡1፣ 9፡11)። የሰይጣንን መንግሥት ለመገልበጥና የእግዚአብሔርን አገዛዝ በምድር ላይ ለመመሥረት እንደመጣ በድፍረት ተናግሯል። የእግዚአብሔር መንግሥት መልእክት የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ስብከት ማዕከላዊ ሀሳብ ነበር (ሐዋ. 8፡12፤ 19፡8)። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩና "በጠላት ኃይል ሁሉ" ላይ የመንግስቱን ኃይል እንዲገልጡ ላካቸው (ሉቃስ 10:19፤ ማቴ. 10:7፤ ሉቃስ 9:1-2፤ 10:8-9)። [1]

# ለመንፈሳዊ ጦርነት መዘጋጀት

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የአጋንንትን መናፍስት ለመቃወም እና ለማሸነፍ በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ መሆን አለብህ። አንተ ሆነ የቤተ ክርስቲያን አባላት ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ማስተማር አለብህ። ለመንፈሳዊ ጦርነት እራስህን ለማዘጋጀት የሚረዱ አንዳንድ መንገዶችን እንመልከት ፡-

## በመንፈስ ቅዱስ መሞላት

በመጀመሪያ፣ በመንፈስ ቅዱስ ደጋግመህ መሞላትህን አረጋግጥ (ሐዋ. 2፡4፤ 4፡31) ይሄም ብቻ ሳይሆን አሁን ላይ በመንፈስ ቅዱስ እየተመላለስክ እና "ከመንፈስ ጋር እየተራመድክ" መሆኑን አረጋግጥ(ገላ. 5፡25)። ኢየሱስ ራሱ በመንፈስ የተሞላ ነበር (ሉቃስ 3፡21-22)፣ በመንፈስ ኃይል ኖሮ አገለገለ (ሉቃስ 4፡18-19፤ ሐዋ. 10፡38)። ኢየሱስ አጋንንትን ያወጣው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሆነ መስክሯል (ማቴ. 12፡28)። በመንፈሳዊ ጦርነት በተሳካ ሁኔታ መካፈል ከፈለግህ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለበህ።

## ክርስቶስ የፈጸመውን መገንዘብ

በመቀጠል፣ ለመንፈሳዊ ጦርነት ስትዘጋጅ ክርስቶስ በቀራንዮ ያደረጋቸውን ነገሮች በሙሉ መገንዘብ አለብህ። ኢየሱስ ለሰው ልጆች ቤዛነት ዋጋ ከፍሏል (ኢሳ. 53፡6፤ 1 ዮሐ. 2፡2)። በዓለም ላይ የዲያብሎስን አገዛዝ አሸንፏል (ዮሐንስ 12፡31)። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ "የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ" (ቆላ. 2፡15) በማለት ይነግረናል።

አሁን ላይ፣ ክርስቶስ በቀራንዮ ባደረገው ታላቅ ስራ፣ ሰይጣን እና አጋንንቱ የተሸነፉ ጠላቶች ሆነዋል (ዕብ. 2፡14-15)። በመንፈስ የምንመላለስ ከሆነ እና እራሳችንን በሙላት ለክርስቶስ እና ለፈቃዱ ካስገዛን፣ ሰይጣንንና አጋንንቱን ለማሸነፍ የሚያስፈልገንን ኃይል እና ስልጣን ይሰጠናል።

[1] ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ለበለጠ፣ በአፍሪካ ቲዎሎጂካል ማሰልጠኛ አገልግሎት (https://africaats.org/) የታተመውን የአፍሪካ ተስፋ ግኝት ተከታታይ የመማሪያ መጽሐፍን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የጴንጤቆስጤ ትርጓሜ በዴንዚል አር.ሚለር የተጻፈውን ተመልከት።

## በክርስቶስ ማን እንደሆንክ እወቅ

በተጨማሪም፣ ለመንፈሳዊ ጦርነት በመዘጋጀት ላይ፣ በክርስቶስ ማን እንደሆንክ እራስህን ማወቅ አለብህ። ምንም እንኳን በዚህ ምድር ላይ ብትኖርም፣ እንደ እግዚአብሔር ልጅ፣ የሰማይ ዜጋ ነህ (ፊልጵ. 3፡20)። ይህንን እውነት ካስታወስክ እና እንደ እውነተኛ የሰማይ ልጅ ለመኖር ከመረጥክ፣ ጌታ የዚያን ግዛት ሃብት፣ ስልጣን እና ሃይል ሁሉ ይሰጥሃል። እንደ እግዚአብሔር መንግስት ዜጋ ማሰብና መስራትን በተማርክ ቁጥር የመንግስቱን ወንጌል ለጠፋው የሰው ልጅ ለማወጅ የበለጠ ዝግጁ ትሆናለህ እና በመንፈሳዊው ዓለም ጦርነት ለማድረግ የበለጠ አቅም ይኖርሃል።

## የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ትጥቅ ልበስ

በመጨረሻም፣ ጳውሎስ መንፈሳዊ ተዋጊዎችን "በጌታና በኃይሉ ብርቱዎች ሁኑ" (ኤፌ. 6፡10) በማለት አሳስቧቸዋል። ይህን ማድረግ የምንችልበት አንዱ መንገድ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ትጥቅ በመልበስ ነው። ያኔ ክፉው ቀን ሲመጣ ከጠላት ጋር መቋቋም እንችላለን (ቁ. 11፣13)።

ጳውሎስ ክርስቶስ ለአገልጋዮቹ የሰጣቸውን ሰባት ኃይለኛ መንፈሳዊ መሣሪያዎችን ጠቅሷል። እንዲሁም በእያንዳንዱ መሳሪያ መንፈሳዊ ጦርነትን እንዴት መፈጸም እንደሚቻል አንዳንድ ግንዛቤዎችን ሰጥቶአል (ኤፌ. 6፡13-18)። እነዚህን ሰባት መንፈሳዊ ትጥቆችን በጥልቀት እንመልከታቸው፡-

1. **የእውነት ቀበቶ።** በመጀመሪያ፣ "በእውነት መታጠቂያ" (ኤፌ. 6፡14) ራሳችንን ማስታጠቅ አለብን። የእውነትን መታጠቂያ መልበስ ሁለት ነገሮችን ይወክላል። አንድም በእግዚአብሔር ቃል እውነት እራሳችንን ማስታጠቅ እንደለብን የሚያሳስብ ሲሆን (ዮሐ. 17፡17)፤ በተጨማሪም እራሳችንን በእውነተኛነት ማለትም በፍፁም ታማኝነት መኖር እንዳለበን የሚያመለክት ነው። በዚህ መሳሪያ የዲያብሎስን ውሸቶች መቋቋም እንችላለን (ዮሐ. 8፡44)።

2. **የጽድቅ ጥሩር።** በመቀጠል፣ "የጽድቅን ጥሩር" (ኤፌ. 6፡14) በመልበስ ራሳችንን ለመንፈሳዊ ውጊያ ማዘጋጀት አለብን። ይህንን የምናደርገው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ላይ መሆናችንን እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በማይቋረጥ ህብረት ውስጥ መኖራችንን በማረጋገጥ ነው (ዮሐ. 15፡5)። ከዚህ ግንኙነት የተነሳ ንጹህ እና የተቀደሰ ህይወት እንድንኖር እንችላለን (ቲቶ 2፡11-12)።

3. **በዝግጅት የቆሙ እግሮች።** ሦስተኛ፣ "በዝግጁነት" (ኤፌ. 6፡15) ራሳችንን ማስታጠቅ አለብን። በሌላ አነጋገር፣ ከጠላት ጥቃት ዘወትር ልንጠነቀቅ ይገባናል (1ጴጥ. 5፡8)። ይህ ዝግጁነት የሚመነጨው ወንጌልን በመስማትና በመታዘዝ ነው። ደግሞም፣ እንደ እግዚአብሔር መንጋ ታማኝ እረኞች፣ ጳውሎስ ከኤፌሶን ሽማግሌዎች ጋር እንዳደረገው፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የጠላት ጥቃትን እንዲፋለም ማዘጋጀት አለብን።

4. **የእምነት ጋሻ።** አራተኛ፣ "የእምነትን ጋሻ" ልንይዝ ይገባናል (ኤፌ. 6፡16)። ይህንን መንፈሳዊ መሳሪያ "የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ" (ቁ. 16) ለመከላከል ልንጠቀምበት እንችላለን። እነዚህ የሚንበለበሉት ፍላጻዎች የተለያዩ የዲያብሎስ ፈተናዎች ሲሆኑ ያልተቀደሱ አስተሳሰቦች፤ ፍላጎቶች እና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አለመታዘዝን ያካትታሉ። እምነታችን የሚገነባው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት እና በማንበብ ነው (ሮሜ. 10፡17) ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ (ይሁዳ 20)።

5. **የመዳን የራስ ቁር።** በእጃችን ያለው አምስተኛው መሣሪያ "የመዳን ራስ ቁር" ነው (ኤፌ. 6፡17)። ይህ መዳን ከኃጢአት እና ከገሃነም መዳን ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የሚመጣውን ማንኛውንም መዳን ወይም አርነት መውጣት ያካትታል ለምሳሌ ከአጋንንት መዳንን፣ አደጋን፣ በሽታንና ሞትን ያካትታል።

**6. የእግዚአብሔር ቃል።** ስድስተኛ፣ "የመንፈስን ሰይፍ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል " (ኤፌ. 6፡ 17)ማንሳት አለብን። የእግዚአብሔር ቃል ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እጅግ ኃይለኛ መንፈሳዊ መሳሪያ ነው። በትጋት በማጥናት እና ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሰላሰል ራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል ማስታጠቅ እንችላለን (መዝ. 119፡11)። በተጨማሪም፣ ለሚሰሙት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ማወጅ አለብን (2ጢሞ. 4፡2)።[2]

የእግዚአብሔር ቃል ለጥቃትም ሆነ ለመከላከያ ውጊያ ሊያገለግል ይችላል። ቃሉ በጸሎት ሲገለጽ፣ እንዲሁም በመንፈስ ቅብአት መስበክ እና ማስተማር እንደ ማጥቂያ መሣሪያ ሊያገለግል ይችላል። እናም ኢየሱስ በምድረ በዳ እንዳደረገው የሰይጣንን ጥቃት ለመከላከል እንደ መከላከያ መሳሪያ መጠቀም ይቻላል (ሉቃስ 4፡1-13)።

በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሰው "የእግዚአብሔር ቃል" የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ከመንፈስ የሚቀበለው ግላዊ ቃል ሊሆን ይችላል። ይህ ጌታ በአንድ ሰው ልብ ውስጥ የሚያስቀምጠው የተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሊሆን ይችላል። ወይም የተለየ ፍላጎትን የተመለከተ ከእግዚአብሔር የተገኘ መገለጥ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ የእውቀት ቃል ወይም የጥበብ ቃል ሊሆን ይችላል(1ቆሮ. 12፡8)።

**7. በመንፈስ ጸሎት።** በመጨረሻም፣ በመንፈስ ጸሎት ማድረግን እንደ መሳሪያ መውሰድ አለብን። እንዲህ ያለው ጸሎት ኃይለኛ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው። ስለዚህም ጳውሎስ አማኞችን "በሁሉ ዓይነት ጸሎትና ልመና በመንፈስ ጸልዩ" (ኤፌ. 6፡18) በማለት ያሳስቧቸዋል። ይህ ማለት ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ጸሎታችንን እንዲቀባ እና እንዲመራን መፍቀድ አለብን ማለት ነው። የዚህ አይነት ጸሎት በልሳኖች የምልጃ ጸሎትን ማድረግን ያጠቃልላል (1ቆሮ. 14፡14፤ ሮሜ. 8፡26)።

## ሰባት ሌሎች መንፈሳዊ መሣሪያዎች

መጽሐፍ ቅዱስ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጠላትን ለማሸነፍ ስለሚጠቀምባቸው ሰባት ተጨማሪ ኃይለኛ መንፈሳዊ መሳሪያዎች ይናገራል፡-

**1. የጾም መሣሪያ።** ከጸሎት ጎን ለጎን ጥቅም ላይ ስናውለው ጾም ለኛ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው (ማር 9፡29)

**2. የምስጋና መሳሪያ።** በመንፈስ ከተቀባ ምስጋና ታላቅ መንፈሳዊ ኃይል ይመነጫል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲያመሰግን ቅጥር ፈርሷል (ኢያሱ 6፡16-20)፣ ሠራዊት ተሸንፏል (2ዜና. 20፡1-26) የእስር ቤት በሮች ተከፍቷል(ሐዋ. 16፡25-26)።

**3. ፍቅርን እንደ መሣሪያ መጠቀም።** እውነተኛ ፍቅር ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመምራት አስደናቂ ኃይል አለው (ሮሜ 5፡5)። አንዳንዶች፣ በምክንያታዊ ክርክሮች፣ ወይም በመንፈስ ኃይል መገለጦች ጭምር መሸነፍ ያልቻሉ፣ በክርስቲያናዊ ፍቅር በቀላሉ ለክርስቶስ መሸነፍ ይችላሉ(12፡20-21) ።

**4. የመንፈስ ጥምቀትን እንደ መሣሪያ።** ኢየሱስ ለተከታዮቹ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን እንደሚቀበሉ ቃል ገባላቸው (ሐዋ. 1፡8)። ይሄውም መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው (ሉቃስ 3፡ 16፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡5፤ 2፡4)።[3]

---

[2] የጴንጤቆስጤ ፓስተር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ስላለው ግንኙነት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 9ን "መጽሐፍ ቅዱስን ያምናል" ተመልከት፡ ፡

[3] ስለ መንፈስ ጥምቀት፣ ምዕራፍ 20ን ተመልከት፡ "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት።

**5. የመንፈስ ስጦታዎች እንደ መሳሪያ።** የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥበት አንዱ ምክንያት አማኞች ለመንፈሳዊ ጦርነት እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው (1ቆሮ. 12፡8-10)።[4]

**6. የኢየሱስ ስም እንደ መሳሪያ።** የኢየሱስ ስም በሰማይ ያለ ሁሉ ሥልጣን ቁልፍ ነው (ፊልጵ. 2፡ 9-11)። እርሱ እንዳዘዘው ስሙን ስንጠቀም፣ የገሃነም ኃይላት እጅ ይሰጣሉ (ዮሐንስ 14፡13-14፤ ሐዋ. 3፡ 6፤ 9፡27፤ 16፡18)።

**7. የወንጌል ስርጭትን እንደ መሣሪያ።** ጳውሎስ ወንጌልን "የሚያምኑትን ሁሉ ለማዳን የእግዚአብሔር ኃይል" ሲል ጠርቶታል (ሮሜ. 1፡16)። ወንጌል በክርስቶስ የመዳን መልእክት ነው። የወንጌል መልእክት ሲሰበክ በሚሰሙት ልብ ውስጥ እምነትን የመፍጠር ኃይል አለው (ሮሜ. 10፡17)። ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ወንጌልን በታማኝነት ከመስበክ ቸል ማለት የለብንም (1ቆሮ. 9፡16)።

# በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ መሳተፍ

ጥያቄው ፣ "የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ (ወይም፣ ለነገሩ፣ ማንኛውም በመንፈስ የተሞላ ደቀ መዝሙር) በአጋንንት እስራት ውስጥ ላለ ሰው በመጸለይ እና ርኩሳን መናፍስትን ማስወጣት የሚችለው እንዴት ነው?" በአጋንንት ለታሰሩትን ነጻ ለማውጣት ልትከተል የምትችለው ባለ ሶስት እርምጃ ሂደት እንመልከት።[5]

## መጠይቅ

የታሰሩትን ነፃ ለማውጣት የመጀመሪያው እርምጃ የሚቻል ከሆነ ጸሎት የሚፈልገውን ሰው ጥያቄ መጠየቅ ነው። በዚህ ደረጃ መዳን ከሚያስፈልገው ግለሰብ ጋር ትነጋገራለህ። ግቡ ስለ ሰውዬው ሁኔታ የበለጠ ግንዛቤ ማግኘት ነው። በዚህ ጊዜ፣ መናፍስትን በመለየት ስጦታ፣ ስለ መንፈሱ አሰራር መረዳት ልታገኝ ትችላለህ። ወይም አጋንንቶች ከእግዚአብሔር መገኘት የተነሳ ራሳቸውን ሊገልጡ ይችላሉ (ማር. 1፡23፤ 5፡6-7)።

ከተቻለ በእስራት ያለውን ሰው በንስሐ ጸሎት እና በኃጢአት ኑዛዜ ጸሎት መምራት ያስፈልጋል። ይህ በተለይ የሰውዬው የኃጢአት ልምምድ ከመንፈሳዊ እስራት ጋር በቅርበት ሊገናኝ ስለሚችል በጣም አስፈላጊ ያደርገዋል። በዚህ ጸሎት ውስጥ፣ በእስራት ያለው ሰው በሕይወቱ ውስጥ የአጋንንትን ፍላጎት እና ከእዛ ጋር የተያያዙ የሥጋ ሥራዎችን መተው ይኖርበታል።

## ሚኒስቴር ተሳትፎ

ሁለተኛው ነጻ የማውጣ ሂደት ጸሎት ማድረግ ነው። ይህ ከአጋንንት ሃይሎች ጋር የሚደረግ የሃይል ግብግብ ነው። የኢየሱስን ስም በመጥራት እና መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ እና ህልውና እና ኃይሉን እንዲገልጥ በመጋበዝ ጸሎቱን መጀመር አለብህ። አንዴ የእግዚአብሔርን መገኘት ከተረዳህ፣ አጋንንትን እንዲወጡ (ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ማባረርን) ማዘዝ ትችላለህ።መንፈስ እንደሚመራህ፣ ከሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሂደቶች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ መጠቀም ትችላለህ፡-

---

[4] አባሪ 2፡ "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት።

[5] አጋንንት እስራት ነጻ ስለማውጣት እና ስለማሸነፍ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣የአፍሪካ ተስፋ ግኝት ተከታታይ የመማሪያ መጽሐፍን፣ የኃይል አገልግሎት፡ በመንፈስ ኃይል እንዴት ማገልገል እንደሚቻል፣ ምዕራፍ 11፡ "አጋንንትን ማስወጣት" እና ምዕራፍ 12፡ "የአካባቢ ገዢዎችን ድል መንሳት" የሚለውን ተመልከት።

- አጋንንትን በኢየሱስ ስም ማሰር ትችላላችሁ (ማቴ. 16፡17-19፤ 18፡18)።
- አጋንቶች እንዲወጡ፣ እንዲሄዱ፣ ወይም እንዲለቁ ልታዝዛቸው ትችላለህ (ሉቃስ 4፡35)።
- አጋንቶች ወደ ሰውዬው ዳግመኛ እንዳይገቡ ልታዝዛቸው ትችላለህ (ማርቆስ 9፡25)።

አንዳንድ ጊዜ አጋንንት ይገዳደራሉ፣ እናም ትግል ይመጣል (ሉቃስ 8:29፤ 11:14)። እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች ድሉ እስኪመጣ ድረስ በእምነት መጽናት አለብህ። አርነት መውጣት ብዙ ጊዜ ከሥጋዊ መገለጫዎች ጋር አብሮ ይመጣል (ማር. 7፡30፤ ሉቃ. 4፡33-35፤ 9፡42)። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ መፍራት ወይም ሃሳብን መበተን የለብህም። ይልቁንም፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መመራት በመቀጠል አጋንንት ጸጥ እንዲሉ እዘዝ (ማር.1፡25)። በኢየሱስ ስም ሥልጣን፣ እንዲወጡና እንዳይመለሱ እዘዛቸው (ማርቆስ 9፡ 25)።

## ከጸሎት በኂላ የምክር አገልግሎት መስጠት

ነጻ በማውጣት ሂደት ውስጥ የመጨረሻው ደረጃ ከጸሎት በኋላ ማማከር ነው። ይህ እርምጃ በአጋንንት ቁጥጥር ስር ለነበረው ሰው በጣም አስፈላጊ ነው። እርሱ ወይም እርሷ አርነት ከወጡ በኋላ ጸሎት እና የስሜት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ዳግመኛ ካልተወለዱ እንደሆነ ወዲያውኑ ወደ በክርስቶስ እንዲያምኑ ልትመራቸው ይገባል። በተጨማሪም፣ ወዲያውኑ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መምራት አለብህ። ኢየሱስ እነዚህን አስፈላጊ ጉዳዮች ችላ ስለማለት አስጠንቅቋል (ማቴ. 12፡43-45)። ግለሰብ ሙሉ በሙሉ ከባርነት ነፃ እስኪወጡ ድረስ ከግለሰቡ ጋር የቅርብ ግንኙነት ማድረግ ወይም ይህን የሚያደርግ ሰው መመደብ አለብህ።

---

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በመንፈሳዊ ጦርነት እንድታደርግ ክርስቶስ አደራ ጥሎብሃል (ማርቆስ 16፡15-16)። በእናንተ ውስጥ የሚኖረው በዓለም ካለው እጅግ እንደሚበልጥ አውቀህ ዲያብሎስን እና አጋንንቱን በታላቅ እምነት ድል ልትነሳው ትችላለህ (1ዮሐ. 4፡4)።

# ~ ክፍል 6 ~

# ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ እረኛ

# ~ ምዕራፍ 23 ~

# የመጋቢያዊ አገልግሎትን መረዳት

አንድ ሰው በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርግ እና ለዚያ ተግባር ቁርጠኛ ሲሆን ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ምን እየሰራ እንደሆነ ወይም ለምን እንደሚሰራ በአግባቡ ላይረዳ ይችላል። መንፈስ በአንድ ወቅት ፊልጶስን ወደ ቅን እና ጥልቅ ትጉህ ወደ ሆነ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ መራው። ጃንደረባ በትጋት ቅዱሳት መጻሕፍትን ያነብ ነበር። ነገር ግን የሚያነበው አልገባውም ነበር (ሐዋ. 8፡29-31)። በሌላ ጊዜ ደግሞ ጳውሎስ በአቴንስ ተመሳሳይ ቅን እና ትጉህ የሆኑ አንዳንድ ሰዎችን አገኘ። እነዚህ ሰዎች “የማይታወቅ አምላክ” ያመልኩ ነበር። ሆኖም ማንን እንደሚያመልኩ ወይም ለምን እንደሚያመልኩ አልተረዱም ነበር(ሐዋ. 17፡22-23)። ማብራሪያ ያስፈልጋቸው ነበር።

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ብዙ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። በእረኝነት አገልግሎት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣ እና እንደ መጋቢነት ሚናቸውን ለመወጣት የቆረጡ ናቸው። ሆኖም፣ በእውነቱ፣ ስለሚያደርጉት ወይም ለምን እንደሚሄዱ ብዙም አይረዱም። እንደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ “ሰው ካልነገረኝ እንዴት አውቃለሁ?” የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። ይህ ምዕራፍ የተፃፈው ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። ይህ ምእራፍ የእረኝነት አገልግሎትን ለመረዳት መሠረት ይጥላል። አላማው የጠንካራ አገልግሎት መሠረት መገንባት ነው።

## የመጋቢያዊ አገልግሎት አውድ

የመጋቢያዊ አገልግሎት የሚከናወነው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አውድ ውስጥ ነው። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል ኤክሌሲያ ሲሆን ትርጉሙም የተጠሩትና የተለዩ ማለት ነው። ስለዚህም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን እንዲያገለግሉትና እንዲያመልኩ የተለዩ የሰዎች ስብስብ ነው። ከእግዚአብሔር መንፈስ ተወልደው በኢየሱስ ደም የታጠቡት ሰዎች ስብስብ ነው (ዮሐንስ 3፡3-7፤ የሐዋርያት ሥራ 20፡28)።

ስለ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ነገሮች ማለት ይቻላል። አንደኛ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ናት። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን "ቤተ ክርስቲያኔ" በማለት ጠርቶታል (ማቴ. 16፡18)። ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ቤተሰብ... የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን" ብሎ ጠርቶታል (1 ጢሞ. 3፡15)። ሁለተኛ፣ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደሪያ ናት። ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር "እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርባት ማደሪያ"(ኤፌ. 2፡22) "ቅዱስ ቤተ መቅደስ" ብሎ ጠርቶታል። በመጨረሻም፣ ቤተ ክርስቲያን "የእውነት ዓምድና መሠረት ናት" (1ጢሞ. 3፡15)። በሌላ አነጋገር እውነትን የምትደግፍ መንፈሳዊ መዋቅር ናት። የቤተ ክርስቲያን አንዱ ተቀዳሚ ተልእኮ እውነትን መጠበቅ እና ማወጅ ነው (ማቴ. 28፡19፤ 2ቆሮ. 2፡14)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በዚህ አውድ ውስጥ አገልግሎትህን እንደምታከናውን በሚገባ ማወቅ አለብህ።

# የአገልግሎቱ ጽንሰ-ሐሳብ

እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱሳዊውን የአገልግሎት ጽንሰ-ሐሳብ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር የሰጣትን ተልእኮ እንድትወጣ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን እንደሚሾም ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ። የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ክርስቶስ በቅርቡ ከመምጣቱ በፊት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለሰው ሁሉ ምሥራቹን መስበክ ነው (ማር. 16፡15-16፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡8)። ከዚያም ያመኑትን ወስዶ ታዛዥ ደቀ መዛሙርት አድርጎ የጌታቸውን መልክ እንዲመስል መቅረጽ ነው (ማቴ. 28፡19፤ ቆላ. 3፡10)።

አገልግሎት የሚለው ቃል የማገልገል እና የተግባር ጽንሰ-ሀሳቦችን ይይዛል። ጳውሎስ የአገልግሎትን ሃሳብ በስፋት ገልጿል። በኤፌሶን 4፣ ስለ ሶስት የአገልግሎት ዓይነቶች ተናግሯል፡-

## የኢየሱስ አገልግሎት

በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ፣ ስለ መሲሑ አገልግሎት ተናግሯል (ኤፌ. 4፡8-0)። በመስቀል ላይ ባደረገው የማዳን ሥራ (ሞቱን፣ መቀበሩን፣ ትንሣኤውን እና ወደ አብ ዕርገቱን ጨምሮ) ኢየሱስ አዲስ ኪዳንን መረቀ። ክርስቶስ በምድር ሳለ በሐዋርያነት (ዕብ. 3፡1)፣ ነቢይ (ሉቃስ 24፡19)፣ ወንጌላዊ (ሉቃስ 19፡10)፣ መጋቢ (ዮሐ. 10፡11-16) እና አስተማሪ ሆኖ አገልግሏል (ዮሐ. 3፡2) 13፡13)። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን መረጋጋት እና ጽናት የተረጋገጠበት "ዋና የማዕዘን ድንጋይ" ሆነ (ኤፌ. 2፡20)።

## የአማኞች አገልግሎት

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ ስለ አማኞች አገልግሎት ተናግሯል (ኤፌ. 4፡11-16)። ኢየሱስ አገልግሎቱን ለቤተ ክርስቲያን አደራ ሰጥቷል። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ማንኛውም የኢየሱስ አገልግሎት የአገልግሎቱ ቅጥያ ነው። የአገልግሎት ግብ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል "በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ" እንዲደርስ (ኤፌ. 4፡13) እንዲበስል ነው። በእምነት የጎለመሱትም ዞር ብለው ሌሎችን በማበርታት መላው ቤተ ክርስቲያን እንድታድግና እንድትበለጽግ ማድረግ አለባቸው።

## የአመራር ቢሮዎች

ሦስተኛ፣ ጳውሎስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸውን የአመራር አገልግሎቶች ገልጿል። "አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤" በማለት ጽፏል (ኤፌ. 4፡11)። ብዙዎች እንደሚያደርጉት እነዚህ የአገልግሎት ሚናዎች በዋናነት እንደ ማዕረግ መታየት የለባቸውም። እንደ አገልግሎት ተግባራት መታሰብ አለባቸው። መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን የሚገዙባቸው ቢሮዎች አይደሉም።

ይልቁንም፣ ለአገልጋይ መሪዎች "[የእግዚአብሔርን] ሕዝብ ለአገልግሎት ሥራ እንዲያስታጥቁ" (ኤፌ. 4፡ 12) እንደሚከተለው ተሰጥቷቸዋል።

- **ሐዋርያዊ ተግባር**:- ሐዋርያው የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ማይደረስባቸው ቦታዎች እና ወንጌል ባልተደረሳቸው ሕዝቦች መካከል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በማራመድ እና ሌሎችም በተመሳሳይ ቤተ ክርስቲያን እንዲተክሉ በማስታጠቅ ቤተ ክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን ዓላማዎች ያገለግላል።
- **ትንቢታዊ ተግባር**:- ነቢዩ የእግዚአብሔርን መልእክት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመናገር እና ሌሎችም እንዲያደርጉ በማስታጠቅ ቤተ ክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን አላማዎች ያገለግላል።
- **የወንጌል አገልግሎት**: ወንጌላዊው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለጠፉት በማወጅ እና ሌሎችም በተመሳሳይ እንዲያውጁ በማስታጠቅ ቤተ ክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን አላማዎች ያገለግላል።
- **የመጋቢነት ተግባር**: ፓስተሩ የእግዚአብሔርን ህዝብ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል በማገልገል እና ሌሎችም እንዲመግብ በማስታጠቅ ቤተ ክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን አላማዎች ያገለግላል።
- **የማስተማር ተግባር**:- መምህሩ የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በማስተማር እና ሌሎችም እንዲያስተምሩ በማስታጠቅ ቤተ ክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን ዓላማዎች ያገለግላል።

እነዚህ አገልግሎቶች እና ተግባራት ብዙ ጊዜ ይደራረባሉ፣ አንድ ግለሰብ በተለያዩ ሚናዎች ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ፣ አንድ ግለሰብ እንደ ሐዋርያ እና ነቢይነት በተመሳሳይ ጊዜ ሊሠራ ይችላል። ሌላው እንደ አስተማሪና ወንጌላዊ ወዘተ ሆኖ ሊሠራ ይችላል። ከላይ እንደተጠቀሰው ኢየሱስ እና ሐዋርያው ጳውሎስ ያሉ በአምስቱም ሚናዎች አገልግለዋል። በቁጥር 11 ላይ ባለው ቃል መሰረት፣ ጳውሎስ የመጋቢን እና የአስተማሪን ሚና ወደ አንድ መጋቢ-መምህር ተግባር የተቀላቀለ ይመስላል።

በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ፣ ጳውሎስ ራሱን እንደ "ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ" በማለት አስተዋውቋል (ሮሜ 1:1፤ ቲቶ 1:1)። በተመሳሳይ፣ ጴጥሮስ ራሱን እንደ "የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ" (2ጴጥ. 1:1) በማለት ራሱን አስተዋውቋል። ሁለቱም ሰዎች መጀመሪያ አገልጋይነታቸውን እንዴት እንዳስቀደሙ ልብ በል። የእውነተኛ ሐዋርያት ምልክቱ ይሄ ነው። በአምስቱ የአመራር አገልግሎቶች የሚያገለግል ማንኛውም ሰው ዛሬም ተመሳሳይ መሆን አለበት። ከምንም በላይ፣ ራሱን እንደ እግዚአብሔር እና የሕዝቡ አገልጋይ አድርጎ መቁጠር አለበት (ዮሐ. 21፡15-17፤ 1 ጴጥ. 5፡2-4)።

እነዚህ አምስት "የክርስቶስ ዕርገት ስጦታዎች" በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስ ሥልጣን መግለጫዎች ሆነው ያገለግላሉ። አላማቸው ቤተ ክርስቲያንን ወደ መለኮታዊ አላማ መምራት ነው። ጳውሎስ እነዚህ አገልግሎቶች ሁለት ተግባራት እንዳላቸው አስተምሯል፣ መትከል እና ማጠጣት (1 ቆሮ. 3: 6)። የመትከል አገልግሎት ሐዋርያትን እና ወንጌላውያንን ሊያካትት ይችላል። የማጠጣት አገልግሎት ነቢያትን፣ መጋቢያን እና አስተማሪዎች ሊያካትት ይችላል። በተካዮች እና በአጠጪዎች መካከል ያለው ትብብር የእግዚአብሔርን ሥራ እድገት ያመጣል።

## ተጨማሪ አገልግሎት

ከአመራር አገልግሎቶች ጋር፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተወሰኑ ተጨማሪ አገልግሎቶችን አስቀምጧል። እነዚህ አገልግሎቶች ሽማግሌዎችን እና ዲያቆናትን ያካትታሉ (ሐዋ. 6፡1-6፤ 14፡23፤ 1 ጢሞ. 3፡1-10)። የዕብራይስጥ ቃል ሽማግሌ ዘኬን በማለት ይገልጸዋል፣ እርሱም የሚያመለክተው ልምድ እና ስልጣን ያለውን ሰው ነው (ዘኍ. 11፡16)። ሽማግሌ የሚለው የግሪክ ቃል ፕሬስባይቴሮስ ሲሆን ትርጉሙም ተመሳሳይ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ሽማግሌ የበላይ ተመልካች ሆኖ የማገልገል ሥልጣን ያለላቸው ናቸው (በግሪክ ኤጲስቆጶስ) (ሐዋ. 20፡17፣ 28)። ስለዚህ፣ መጋቢ ሽማግሌም እና የበላይ ተመልካችም ነው (ሐዋ. 20፡17፣28፤ 1ጢሞ. 3፡1-2፤ ቲቶ 1፡5-7)። ቤተ ክርስቲያንን በብቃት ለመምራት፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በመንፈሳዊ ነገር የበሰለ መሆን አለበት፣ እና እርሱ ወይም እርሷ የእግዚአብሔርን ቃል ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው (1 ጢሞ. 3፡6፤ 2 ጢሞ. 4፡2)።

ዲያቆን ተብሎ የተተረጎመው የግሪክኛ ቃል ዲያቆኖስ ሲሆን ትርጉሙም "የሚያገለግል" ማለት ነው። በሐዋርያት ሥራ 6 ላይ፣ ሐዋርያት "ለጸሎትና ለቃሉ አገልግሎት" ቸል እንዳይሉ ሰባት በመንፈስ የተመሉ ሰዎችን መረጡ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ሁለቱ እስጢፋኖስና ፊልጶስ የክርስቶስ ብርቱ ምስክሮች ሆነዋል። በሮሜ 16፡1 ጳውሎስ ፌቤን የሮም ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ሲል አስተዋውቋታል።

# የመጋቢው ሥራ

"መጋቢ" የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የመጣው ፖይሜን ከሚለው የግሪክኛ ቃል ነው፣ ቀጥተኛ ፍችውም "እረኛ" ማለት ነው። እንደ መጋቢ፣ የአንተ ድርሻ የእግዚአብሔርን መንጋ መጠበቅ ነው (ሐዋ. 20፡28)። እንደ እረኛ፣ እንደ እግዚአብሔር ህዝብ መሪ፣ አማካሪ እና ጠባቂ ማገልገል አለብህ (1ጴጥ. 5፡1-4)።

## የመጋቢ ኃላፊነቶች

ከእረኝነት ኃላፊነቶችህ መካከል መንጋውን መንከባከብ (ዮሐ. 21:15-17፤ 1 ጴጥ. 5:2-3)፣ አካልን ማጠናከር (ኤፌ. 4:11-12)፣ የእግዚአብሔር ህዝብን መምከር (1 ጢሞ. 5:14) በጎቹን መጠበቅ (ሐዋ. 20፡28) ይገኙበታል። ሌሎች ኃላፊነቶች ደግሞ መስበክ (2 ጢሞ. 4:2)፣ ማስተማር (1 ጢሞ. 3:2፤ ቲቶ 2:1)፣ መምራት (ዕብ. 13:17)፣ ማስተዳደር (ሥራ 20:28)፣ ደቀ መዛሙርት ማድረግ (ማቴ.28፡19)፣ ለጠፉት ወንጌልን መስበክ (2ጢሞ. 4፡5) እና ቤተ ክርስቲያንን ለተልእኮ ማደራጀት ናቸው (ሐዋ. 13፡1-4)።[1]

በቤተክርስቲያኑ የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት፣ ከጴንጤቆስጤያዊ ቀን በኋላ ብዙም ሳይቆይ፣ ሐዋርያት የመጋቢነትን ሚና ያዙ። እርሱ አጽንዖት የሰጠውን በማጉላት ኢየሱስ እንደመራቸው ቤተ ክርስቲያንን መርተዋል። በሐዋርያት ሥራ 2፡38-47 ውስጥ ሉቃስ ስለ ቤተ ክርስቲያን በሰጠው መግለጫ ላይ ብዙዎቹ አጽንዖቶቻቸው ተገልጸዋል።

ይህ አስደናቂ ክፍል፣ ከሱ በፊት ካሉት ቁጥሮች ጀምሮ የሐዋርያትን አሥር መጋቢያዊ አጽንዖት ያሳያል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እነዚህ አስር አጽንዖቶች ዛሬ ለራስህ አገልግሎት አብነት ሆነው እንዲያገለግሉ በመፍቀድ የሐዋርያትን ምሳሌ ብትከተል ብልህነት ነው።

---

[1] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር ሀላፊነቶች ለበለጠ፣ ከምዕራፍ 23-27 ተመልከት።

**1. የወንጌል አዋጅ።** በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ ጴጥሮስ ቆሞ በድፍረት ወንጌልን ሰበከ። ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤያዊ ቀን ስብከቱ ላይ የክርስቶስን ሞት እና ትንሳኤ አጽንዖት ሰጥቷል (ሐዋ. 2፡23-24፣ 32፤ 1 ቆሮ. 15፡1-4)። ከዚያም ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡና በወንጌል እንዲያምኑ በመጥራት መልእክቱን ቋጭቷል (ሐዋ. 2፡36-40)። ይህ አጽንዖት በሐዋርያት ሥራ ሁሉ ቀጥሏል (ዝከ. 3:19፤ 20:21፤ 26:20)። በተመሳሳይ መልኩ የወንጌል ማወጅ ዛሬ የመጋቢ አገልገሎት ማዕከላዊ መሆን አለበት።[2]

**2. በመንፈስ ቅዱስ መታጠቅ።** ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመታጠቅ አስፈላጊነት አጽንዖት ሰጥቷል (ሐዋ. 2፡38-39፤ ዝከ. 2፡17-18)። ክርስቶስን የተቀበሉ ሰዎች ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ እድል ሊሰጣቸው ይገባል። ልክ እንደ ወንጌል አዋጅ፣ ይህ አጽንዖት በሐዋርያት ሥራ (8፡14-17፤ 9፡17-18፤ 10፡44-46፤ 19፡1-7) ቀጥሏል። በአፍሪካ ውስጥ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተም እንዲሁ ማድረግ አለብህ። እያንዳንዱ አባል ለጠፉት ምስክር እንዲሆን ስልጣን እንዲያገኝ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ላይ ብዙ ጊዜ መስበክ እና ማስተማር አለብህ።[3]

**3. የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር።** በተጨማሪም፣ ሉቃስ የኢየሩሳሌም አማኞች "ለሐዋርያት ትምህርት ራሳቸውን እንደሰጡ" (ሐዋ. 2፡42) ነግሮናል። በዚህ መንገድ ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማርን አጽንዖት ሰጥተዋል። ከአመታት በኋላ ጳውሎስ፣ "በአደባባይም ሆነ ከቤት ቤት በመዘዋወር እናንተን ከማስተማርና ይጠቅማችኋል ብዬ ያሰብሁትን ከመስበክ ወደ ኋላ አላልሁም" ብሏል(20፡20)። ይህ የጳውሎስ የአሠራር ዘዴ በሄደበት ይከተለው ሁሉ ነበር (ዝከ. 11፡26-26፤ 15፡35፤ 28፡31)። አንተም እግዚአብሔር እንድትመራው በጠራህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል በትክክል፣ ግልጽ እና በስፋት ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ።[4]

**4. የውሃ ጥምቀት እና የጌታ እራትን ማክበር።** የኢየሱስን ትእዛዛት በመጠበቅ (ማቴ. 28፡19-20፤ ሉቃ.22፡19) ሐዋርያት የውሃ ጥምቀትንና የጌታ እራትን አጽንዖት ሰጥተዋል (ሐዋ. 2፡38-41)። የውሃ ጥምቀት የአማኙን አዲስ ልደት ልምድ ይመሰክራል። የጌታ እራት ደግሞ ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ቀጣይ ግንኙነት ይመሰክራል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እነዚህ ሁለት ቅዱሳት ሥርዓቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በታማኝነት መከበራቸውን ማረጋገጥ አለብህ።[5]

**5. በጸሎት መምራት።** ሐዋርያት ለጸሎት የበለጠ አጽንዖት ሰጥተዋል። ሉቃስ ሕዝቡ "ለጸሎት ይተጉ ነበር" (የሐዋርያት ሥራ 2፡42) ይለናል። በጸሎት መትጋት ለአማኙ የግል መንፈሳዊ ልምምድ እና ምስክርነት ኃይል መሰረትን ይፈጥራል። በቤተ ክርስቲያን እና በአማኞች ሕይወት ውስጥ የመንፈስን መገኘት እና ኃይል ያረጋግጣል (ዝከ. 4፡31)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተም በማስተማር እና በግል ምሳሌ በመሆን ህዝቡን በጸሎት መምራት አለብህ።[6]

**6. ምልክቶችን እና ድንቆችን መጠበቅ።** ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን መገኘት እና ኃይል ለማሳየት የበለጠ ተግተዋል። ሉቃስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- "በሐዋርያት እጅ ብዙ ድንቅና

---

[2] ስለ የጴንጠቆስጤ ፓስተር የስብከት አገልግሎት ተጨማሪ ለማግኘት ምዕራፍ 16ን "በመንፈስ የተቀቡ ስብከት" የሚለውን ተመልከት:-

[3] ለበለጠ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ ምዕራፍ 20 "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት"ን ተመልከት፡

[4] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር የማስተማር አገልግሎት፣ ምዕራፍ 17ን "ውጤታማ ትምህርት" የሚለውን ተመልከት።

[5] የጌታ ዕራትን ስለ መምራትለበለጠ፣ ምዕራፍ 42ን "የጌታ ዕራትን፣ ልጆችን ማስረከብ እና ሹመትን መምራት"የሚለውን ተመልከት።

[6] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር እና ጸሎት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 8 "የጸሎት ቅድሚያ" የሚለውን ተመልከት፡

ታምራት ይደረግ ስለ ነበር፣ ሰው ሁሉ ፍርሀት አደረበት" (ሐዋ. 2፡43)። የእግዚአብሔር መገኘት እና ሃይል ማሳያዎች ዛሬ የአንተ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አገልግሎት ማሳያ ሊሆን ይገባል።[7]

**7. አንድነትን ማሳደግ**። በተጨማሪም ሐዋርያት በአካሉ ውስጥ አንድነት እንዲኖር አድርገዋል። ሉቃስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- "ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ አደረጉ" (ሐዋ. 2፡ 44)። እዚህ የተነገረው የሰዎች አንድነት ከአካላዊ ቅርርብ በላይ ነበር። ቤተ ክርስቲያንን በተልዕኮዋ ወደፊት የሚያራምድ የልብ እና የዓላማ አንድነት ነበራቸው።

**8. ልግስና ማበረታታት**። በተጨማሪም ሐዋርያቱ ልግስና አሳይተዋል። በውጤቱም፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት "ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ያህል ይሰጡት ነበር" (ሐዋ. 2፡45)። እንዲህ ዓይነቱ ልግስና የተወለደው እርስ በርስ እና ከጌታቸው ጋር ካለ የፍቅር ግንኙነት ነው። እንደ ሐዋርያት አንተም ለእግዚአብሔር ሥራ በልግስና በመስጠት ሕዝብህን መምራት አለብህ።

**9. ለአምልኮ መደራጀት**። ሉቃስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- "በየዕለቱ በቤተ መቅደስ በአንድነት እየተገናኙ፣ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በቀና ልብ ይመገቡ ነበር፤እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፤ ጌታም የሚድኑትን በቍጥራቸው ላይ ዕለት በዕለት ይጨምር ነበር" (ሐዋ. 2፡46-47)። ሐዋርያቱ ሕዝቡ ለአምልኮ፣ ለሥልጠና እና ለማበረታታት መሰባሰብ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያውቁ ነበር።[8]

**10. ለምስክርነት ማሰባሰብ**። በመጨረሻም ሐዋርያት ስለ ክርስቶስ ምሥክርነት አጽንዖት ሰጥተዋል። የክርስቶስን መልእክት ለሌሎች እንዲያካፍሉ በማበረታታት ህዝቡን ለተልእኮ አነቃቁ። በውጤቱም፣ "ጌታ የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ጨመረ" (ሐዋ. 2፡47)።[9]

በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት እነዚህ አሥር የሐዋርያዊ አጽንዖቶች ዛሬ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አብነት ሊሆኑልህ ይችላሉ። አገልግሎትህን ከኢየሱስና ከሐዋርያቱ አገልግሎቶች ጋር ለማስማማት ይረዱሃል። እና የምትመግባት ቤተ ክርስቲያን በማህበረሰብህ እና በዓለም ውስጥ መንፈሳዊ ኃያል መሆኗን ለማረጋገጥ ይረዳሉ።

## የመጋቢ ተነሳሽነት እና ተጠያቂነት

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የምታደርገውን ነገር አስፈላጊ ሲሆንም ለምን እንደምታደርገው መረዳት ደግሞ የበለጠ አስፈላጊ ነው። ጴጥሮስ ስለ መጋቢ ሥራ ትክክለኛ መነሳሻ ሃሳብን ጽፏል (1 ጴጥ. 5፡2-3)። መጋቢያን ሥራቸውን የሚሠሩት በግዴታ ስሜት፣ ወይም በገንዘብ ጥቅም፣ ወይም በሰዎች ላይ የመግዛት ፍላጎትን መነሻ ሃሰብ አድርገው አይደለም። ከዚህ ይልቅ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከልባቸው መንከባከብና በፍቅር ማገልገል አለባቸው። በመልካም ዓላማ የሚያገለግሉ መጋቢያን ይሸለማሉ። ጴጥሮስ ታማኝ መጋቢያንን "የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን አክሊል ትቀበላላችሁ" (ቁ. 4) ሲል በተስፋ አበረታቷቸዋል።

[7] ከተፈጥሮ በላይ በሆነው አገልግሎት ላይ፣ ምዕራፍ 21"በመንፈስ ኃይል ማገልገል"የሚለውን ተመልከት።

[8] ቤተ ክርስቲያንን በአምልኮ ስለመምራት ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 18ን "አምልኮን መምራት" የሚለውን ተመልከት።

[9] ቤተ ክርስቲያንን ለምሥክርነት ስለማንቀሳቀስ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 37ን "የጠፉትን ወንጌላዊ" የሚለውን ተመልከት።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንድ ቀን ጥሪህን እንዴት እንደፈፀምክ መልስ ለመስጠት በክርስቶስ ፊት እንደምትቆም መዘንጋት የለብህም። ጳውሎስ እንዲህ ይለናል፡ “ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል” (2ቆሮ. 5፡10)። ታማኝ መጋቢ ይሸለማል (ማቴ. 25:23) ፤ ታማኝ ያልሆነው መጋቢ ተጠያቂ ይሆናል (ቁ. 26)።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣የእግዚአብሔርን ሕዝብ መንከባከብ ያልቻሉ እረኞች ተፈርዶባቸዋል። ለምሳሌ እግዚአብሔር በኤርምያስ በኩል እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- “በማሰማሪያ ቦታዬ ያሉትን በጎቼን ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው!... ነገር ግን መንጋውን አትንከባከቡትም። 4 ደካማውን አላበረታችሁትም፤ በሽተኛውን አልፈወሳችሁትም፤ የተጐዳውንም አልጠገናችሁትም። የባዘኑትን አልመለሳችሁም፤ የጠፉትንም አልፈለጋችሁም፤ በግፍና በጭካኔ ገዛችኋቸው” (ኤር. 23፡1-2፤ ሕዝ. 34፡ 1-10)።

# ለአገልግሎት ማስቻል

የእረኝነት አገልግሎት ጥልቅ መንፈሳዊ ሥራ ነው። የጠፉትን ወንጌልን በብቃት ለመስበክ እና ቅዱሳንን ለማስታጠቅ፣ የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ በመለኮታዊ አቅራቦቶች መታመንን መማር አለበት። የመጋቢ አገልግሎት መንፈሳዊ ጦርነትን ጨምሮ በመንፈሳዊ መሳሪያዎች መካሄድ አለበት (ኤፌ. 6፡12፤ 2ቆሮ. 10፡4-5)።[10]

ከእነዚህ መንፈሳዊ መሳሪያዎች አንዱ በመንፈስ ቅዱስ ስትጠመቅ የተቀበልከው ኃይል ነው። ወደ ሰማይ ከመመለሱ በፊት፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመቀበል በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው (ሐዋ. 1፡4-8)። “ከላይ ኃይልን እስኪለብሱ ድረስ” (ሉቃስ 24፡49) አገልግሎታቸውን መጀመር አልነበረባቸውም። ያንን ኃይል የተቀበሉት በበዓለ ሃምሳ ቀን ነበር። በዚያን ቀን "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር” (ሐዋ. 2፡4)። እንደ ሐዋርያት ሁሉ ያለ መለኮታዊ ኃይል የመጋቢነት ሚናህን በአግባቡ መወጣት አትችልም። ልክ እንደነሱ፣ ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቅ እና የክርስቶስ ምስክር እንዲሆን ማድረግ አለብህ።[11]

---

[10] ስለ መንፈሳዊ ጦርነት፣ ምዕራፍ 22ን “በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ መሳተፍ" የሚለውን ተመልከት፡

[11] አዲስ አማኞችን ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ስለመምራት፣ ምዕራፍ 20ን “አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" የሚለውን ተመልከት፡።

# ~ ምዕራፍ 24 ~

# በጎችን መንከባከብ

በአንድ ወቅት ፈሪሳውያን ኢየሱስን "ከኃጢአተኛ" ሰዎች ጋር በመገናኘቱ ይነቅፉት ነበር። “ይህ ሰው ኃጢአተኞችን ይቀበላል” "ከነሱ ጋር አብሮ ይበላል!" በማለት ያጉረመርማሉ። ኢየሱስ ንግግራቸውን ሰምቶ፣ “ከእናንተ መካከል አንዱ መቶ በጎች ቢኖሩትና ከእነርሱ አንዱ ቢጠፉበት?” ሲል ጠየቃቸው። ከዚያም ከበጎቹ አንዷ እንደጠፋች ያወቀውን የእረኛውን ታሪክ ነገራቸው። ታማኝ እረኛ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ትቶ አንዱን የጠፋውን በግ ለመፈለግ ተነሳ። ባገኘውም ጊዜ በትከሻው ላይ አስቀምጦ ወደ ቤቱ ወሰደው። ወደ መንደሩ ሲገባ ጓደኞቹንና ጎረቤቶቹን “የጠፋውን በግ አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ!” ብሎ ጠራ (ሉቃስ 15፡4-6)።

ዳዊት ንጉሥና ዘማሪ ከመሆኑ በፊት የአባቱን በጎች የሚጠብቅ እረኛ ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ መንጋውን መውደድን ተማረ። ዳዊት በጎቹን እንደሚንከባከበው ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚወደውና እንደሚንከባከበው ተረዳ። እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ አንዳች አይጐድልብኝም። 2 በለመለመ መስክ ያሳርፈኛል፤በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል።” (መዝ. 23፡1-2)።

ኢየሱስ ለራሱ የእረኛነት ማዕረግ ወሰደ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" አለ። ቀጥሎም "በጎቼን አውቃለሁ በጎቼም ያውቁኛል ... ነፍሴንም ስለበጎቼ አኖራለሁ" (ዮሐንስ 10: 14-15)አለ። የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስን “የበጎች ታላቅ እረኛ” ብሎ ይጠራዋል (ዕብ. 13፡20)። በጎቹ እርሱን ለመከተል የመረጡት ናቸው። ኢየሱስ የበጎቹ ባለቤት እርሱ እንደሆነም ተናግሯል። ቅጥረኛው በጎቹን አውሬ በሚመጣበት ጊዜ ይሮጣል ፣ እውነተኛው እረኛ ግን በጎቹን ለመከላከል በአቋሙ ይጸናል። ነፍሱን እንኳን ለእነርሱ ሲል አሳልፎ ለመስጠት ተዘጋጅቷል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ኢየሱስን እንደ አርአያህ መውሰድ አለብህ። ኢየሱስ በአካል ቢኖር እንደሚያደርገው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ልትጠብቅ ይገባል። ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን መንጋ የመንከባከብ ሃላፊነት ያብራራል።

# የእረኛ ልብ

እንደ እግዚአብሔር መንጋ እረኞች፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ሩህሩህ፣ ታማኝ እና እምነት የሚጣልበት መሆን አለባቸው፣

## ሩህሩህ

ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር፣ "መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፤ ጠቦቶቹን በክንዱ ይሰበስባል፤በዕቅፉም ይይዛቸዋል" (ኢሳ. 40፡11) በማለት ጽፏል። ልክ እንደ ጌታቸው፣ ትክክለኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ሩህሩህ ናቸው። ሰዎችን በእውነት ይወዳሉ። ይህ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና ውጭ ያሉትን ያጠቃልላል። ኢየሱስ ለሰዎች ያለውን ፍቅር አሳይቷል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ ሲናገር፡- " ሕዝቡም እረኛ እንደሌለው በግ ተጨንቀውና ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ጊዜ አዘነላቸው" (ማቴ. 9፡36)። በተመሳሳይ፣ እንድታገለግሉ እግዚአብሔር የጠራችሁን ሰዎች በእውነት መውደድ አለባችሁ።

## ታማኝ

በተጨማሪም፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ታማኝ መሆንህን ማረጋገጥ አለብህ። ሁሉንም ትተህ ጌታህን ሙሉ በሙሉ ለመከተል ፈቃደኛ መሆን አለብህ (ማቴ. 19፡21፤ ማር. 8፡34-35)። ክርስቶስ ህዝቡን እንደ ቅዱስ አደራ በእጅህ አስቀምጧል። ስለዚህ የራስህን የግል መብቶች በነጻነት መተው አለብህ። እናም ክርስቶስ በአንተ እንክብካቤ ስር ያሰቀመጣቸውን በታማኝነት ማገልገል አለብህ። ጳውሎስ ስለ ወንጌል አገልጋዮች ሲጽፍ "ባለ ዐደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት አለባቸው" ይላል (1ቆሮ. 4፡ 2)።

## እምነት የሚጣልብህ

በመጨረሻም፣ የእግዚአብሔርን መንጋ በታማኝነት ለመጠበቅ እምነት የሚጣልብህ መሆን አለብህ። መከራ ሲመጣ በጎቹን ትቶ እንደሚሸሽ እንደ ምንደኛ አትሁን (ዮሐ. 10፡12-13)። ይልቁንም ጽኑ እና አስተማማኝ መሆን አለብህ። የጠራህ አምላክም ሆነ የምታገለግላቸው ሰዎች በአንተ ሊደገፉ መቻል አለባቸው። ምንም ቢመጣ፣ ቆመህ ኃላፊነቶን መወጣት እንደምትችል መታወቅ አለበት።

# የእረኛው ሥራ

እንደ እግዚአብሔር እረኛ፣ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሁለት ከባድ ኃላፊነቶችን ይሸከማል፡- በጎችን መንከባከብ እና ቤተ ክርስቲያንን እንደ ለሌሎች ግድ የሚሰኝ ማህበረሰብ ማደራጀት። እነዚህን ሁለት ኃላፊነቶች እንመልከት፡-

## በጎቹን መንከባከብ

በመጀመሪያ በጎቹን መንከባከብ አለብህ። ይህንን ለማድረግ ቢያንስ ስድስት ኃላፊነቶችን መወጣት ያስፈልግሃል፡-

1. **በጎቹን መመገብ።** የኢየሱስ ለጴጥሮስ የሰጠው መልእክት ፣ "[ብትወደኝ]...በጎቼን ጠብቅ" (ዮሐንስ 21፡17) የሚል ነበር። እግዚአብሔር ለእስራኤል፣ "እንደ ልቤም የሆኑ፣ በዕውቀትና በማስተዋል የሚመሯችሁን እረኞች እሰጣችኋለሁ" (ኤር. 3፡15)። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሰዎች መመገብ አለብህ። የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ልታስተምራቸው ይገባል። ይህ አሰራር ምእመናን በእምነት እንዲያድግ

እና እንዲጠነክር ያደርጋል። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ እና በክርስቶስ እንድትበስል ያደርጋል (ኤፌ. 4፡11-16)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን 'ቃሉን እንዲሰብክ' ያበረታታበት አንዱ ምክንያት ይህ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም። "ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም" (2 ጢሞ. 4:2)።

አንተ ራስህ የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት መስበክ እና ማስተማር ብቻ ሳይሆን ሁሉን አቀፍ የማስተማር መርሃ ግብር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መመስረት አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ላሉ ልጆች፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች እየተማሩ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ።[1]

**2. መንጋውን መጠበቅ።** ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎች "ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ኤጲስቆጶሳት አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ" (ሐዋ. 20፡28) በማለት አሳስቧቸዋል። ከዚያም "እኔ ከሄድሁ በኋላ፣ ነጣቂ ተኵላዎች መጥተው በመካከላችሁ ሰርገው እንደሚገቡና ለመንጋውም እንደማይራሩ ዐውቃለሁ። 30 ከእናንተው መካከል እንኳ የራሳቸውን ደቀ መዛሙርት ለማፍራት እውነትን የሚያጣምሙ ይነሣሉ። ስለዚህ ተጠንቀቁ!" (ቁ.29-31) ብሏል።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥመድ ከሚፈልጉ ከሐሰተኛ ነቢያትና ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ተጠንቀቅ። እነዚህን "የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች" ለይተህ በድፍረት ልትጋፈጣቸው ይገባል። ካስፈለገም ከቤተ ክርስቲያኑ አመራር ጋር ከጉባኤው ማገድ አለብህ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየትን በሚፈጥሩ ችግርፈጣሪዎች ላይም እንዲሁ አድርግ (ሮሜ 16፡17)።

በተጨማሪም ለእግዚአብሔር ሕዝብ እውነትን በማሳየት ከሐሰት ትምህርትና ከሐሰት አስተማሪዎች መጠበቅ አለብህ። ያን ጊዜ " ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም። 15 ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው" እንዳለው ይሆናሉ(ኤፌ. 4፡14-15)።[2]

**3. ለተጎዱት መድረስ።** ኢየሱስ ለተጎዱ ሰዎች እጁ የተዘረጋ ነበር (ማቴ. 9፡36፤ 15፡32-38)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተም እንዲሁ ማድረግ አለብህ። በቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰብ ውስጥ ላሉ ደካሞችና በመከራ ላሉ በፍቅር መቅረብ አለብህ። ይህ መበለቶችን እና ወላጅ አልባ ልጆችን ይጨምራል (ያዕቆብ 1፡27)። እንዲሁም በሽተኞችን፣ ድሆችን፣ በእስር ቤት ያሉትን እና ሌሎች የተቸገሩትን ሊያካትት ይችላል (ማቴ. 25፡38)። ኢየሱስ እንዲህ ሲል አበረታቶናል፣ "እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው" (ቁ. 40)።

እንዲሁም በኢጋንንት የተያዙ፣ ተስፋ የቆረጡ፣ ወደ ኋላ የተመለሱትን ወይም የሚንከራተቱትን ቤት መጎብኘት ያስፈልግሃል። እንደፍላጎታቸው አገልግል። እንዲሁም ሆስፒታል የገቡትን ወይም የታሰሩትን የቤተ ክርስቲያን አባላትን መጎብኘት አለብህ። ከእነርሱ ጋር ለመጸለይ ጊዜ ወስደህ ማበረታታት አለብህ። እንዲሁም ችግር ያለባቸውን ወይም የምክር ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች የሚያስተናግዱ የተወሰኑ የቢሮ

---

[1] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ስላለው ሃላፊነት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 17ን "ውጤታማ ትምህርት" የሚለውን ተመልከት።

[2] ቤተ ክርስቲያንን ስለመጠበቅ የበለጠ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 27ን "መንጋውን መጠበቅ" የሚለውን ተመልከት።

ሰዓቶችን መርሐግብር ያስፈልግ ይሆናል። ችግሮቻቸውን በትኩረት አድምጥ፣ ከእነርሱ ጋር ጸልይ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መፍትሔ እንዲያገኙ እርዳቸው።[3]

**4. ደካማዎችን ማበርታት።** በየጉባኤው ውስጥ በመንፈሳዊ ነገር ደካማ የሆኑ ሰዎች አሉ። በዚህ ምክንያት ከጌታ ጋር የሚያደርጉት ጉዞ የተረጋጋ አይደለም። አንዳንዶች፣ በመንፈሳዊ ብስለት የጎደላቸው ወይም በሌላ ምክንያት፣ ከጌታ የመራቅ አደጋ ላይ ናቸው። በዚህ አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በየጊዜው መከታተል አለብህ። እነርሱን ለማበረታታት እና ከጌታ ጋር በሚያደርጉት ጉዞ ለማጠናከር መንገዶችን መፈለግ አለብህ። ይህን ለማድረግ አንዱ መንገድ አንድ ጠንካራ ክርስቲያን እንዲከታተላቸው እና እንዲያበረታታቸው መመደብ ነው። ሌላው መንገድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ነው። መንፈስ ቅዱስ ረዳት፣ አጽናኝ እና መሪ ይሆንላቸዋል።[4]

**5. የጠፉትን መፈለግ።** ኢየሱስ "የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን" እንደመጣ መስክሯል (ሉቃስ 19፡ 10)። ደቀ መዛሙርቱንም እንዲሁ እንዲያደርጉ አዘዛቸው (ማርቆስ 16፡15-16፤ ሉቃስ 14፡23)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የጌታን ምሳሌ መከተል አለብህ። ለጠፋው መመስከር አለብህ፣ አንተም ህዝብንም ተመሳሳይ እንዲያደርጉ መምራት አለብህ። በተጨማሪም፣ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ለተሞላ የስብከተ ወንጌል፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ተልዕኮ ማደራጀት አለብህ።

ይህንን ለማድረግ ሰዎች ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ የማወቅ ፍላጎት ላይ ብዙ ጊዜ መስበክ እና ማስተማር ያስፈልጋል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በወንጌል የጠፉትን ለማድረስ ያላቸውን ሃላፊነት ደጋግመህ ማሳሰብ አለብህ። እንዲሁም ህዝቡን ለምስክርነት ለማነሳሳት እና ለማስታጠቅ ፕሮግራሞችን እና ተነሳሽነትዎችን መውሰድ አለብህ። አንድ ሰው "መጋቢ ህዝቡን ለመመስከር ጥሩው መንገድ እራሱ ምስክር መሆን ነው። ሰዎች ፓስተራቸውን ለክርስቶስ የጠፉትን ሲያሸንፉ እና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲያመጣቸው፣ እነርሱም እንዲሁ ለማድረግ ይነሳሳሉ። ሲል በትክክል ተናግሯል።[5]

**6. አመጸኞችን መገሰጽ።** ተግሣጽ በጎችን የመንከባከብ አስፈላጊ አካል ነው። የባዘኑትን ወደ መንጋው የምንጠራበት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ነው። አመጸኛ ሰዎች ግልጽ የሆነ ኃጢአት ሲሠሩ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ይገባል። ንስሐ ከገቡ፣ ወንድም ወይም እህት ሆነው ወደ ክርስቶስ አካል ይመለሳሉ። ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ካልሆኑ ተግሣጽ ማግኘት አለባቸው (ማቴ. 18፡15-17)። ይህ ልምምድ ሁለት ነገሮችን ያሳካል። አንድም ወደ ኋላ የሚመለሰውን ለማንቃት የሚያገለግል ሲሆን ሌላም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ለማስጠንቀቅ ያገለግላል።

አስታውስ፣ የዲሲፕሊን ግብ ሁል ጊዜ ሰውየውን ገንዘብ ማድረግ ነው። በመሆኑም በትህትና እና በፍቅር መንፈስ ማከናወን አለብህ። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል:- "አንድ ሰው በኀጢአት ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት ይገባል። ነገር ግን አንተም እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ" (ገላ. 6፡1)።

---

[3] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር የምክር አገልግሎት ተጨማሪ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 26ን "የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምከር" የሚለውን ተመልከት።

[4] የቤተክርስቲያን አባላትን ወደ መንፈስ ሙላት ስለመምራት፣ ምዕራፍ 20ን "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት የመለውን ተመልከት።

[5] የጠፉትን ስለማግኘት፣ ምዕራፍ 37ን "የጠፉትን ወንጌላውያን" እና ምዕራፍ 39፡ "አዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል" የሚለውን ተመልከት።

### ለሌሎች ግድ የሚሰኝ ማህበረሰብ መፍጠር

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተ በግል ለሰዎች ማሰብ ብቻ ሳይሆን ከላይ እንደተገለጸው፣ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ እንድታደርግ ማነሳሳት አለብህ። ቤተ ክርስቲያን በእውነት ተቆርቋሪ ማህበረሰብ ለማድረግ መጣር አለብህ። ለሌሎች ግድ የሚሰኝ ማህበረሰብ መሆን ማለት የቅዱሳን ልብ ለተጎዳው በርኅራኄ ይሞላል ማለት ነው። በእግዚአብሔር ፍቅር ስለተሞሉ፣ በተፈጥሯቸው እጃቸውን ይዘረጋሉ። የተጎዳ ወንድም ወይም እህት ሲያዩ ወዲያውኑ በአዘኔታ ምላሽ ይሰጣሉ። ኢየሱስ የሥጋ ደዌ ያለበትን ሰው ባገኘው ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነበር። ሰውየው ኢየሱስን “ብትፈቅድ ልታነጻኝ ትችላለህ” አለው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፡- “ኢየሱስም ለሰውየው በመራራት እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣“እፈቅዳለሁ፣ ንጻ” አለው” (ማርቆስ 1:40-42፣ ጎዳግ)።

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለሌሎች ግድ የሚሰኝ ማህበረሰብ ለመቅረጽ አንዱ መንገድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን እና መንፈስ በሕይወታቸው ውስጥ በኃይል እየሰራ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡22)። በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ፈሰሰ ይላል መጽሐፍ ቅዱስ (ሮሜ. 5፡5)። እንዲሁም፣ ሰዎች በመጋቢው ሕይወት ውስጥ የሚታየውን ርኅራኄ ሲመለከቱ፣ እራሳቸው አዛኝ ይሆናሉ። ሁኔታው እንደሚፈልግ፣ እና መንፈስ እንደሚመራ፣ ርህራሄ የተሞላበት ፕሮግራሞችን በማቋቋም ረገድ ቤተ ክርስቲያንን መምራት ያስፈልጋል። ይህ የመመገብ፣ መኖሪያ ቤት ዕድሳት እና ሌሎች ፕሮግራሞችን ሊያካትት ይችላል።

## የእረኛው ተጠያቂነት

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ራሳቸውን እንደ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፣ ወይም ተንከባካቢዎች አድርገው መመልከት አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን የእነርሱ እንዳልሆነች ፈጽሞ መርሳት የለባቸውም ፤ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ናት። ይልቁንም እንደ ቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪዎች ተጠያቂዎች ናቸው። በመሆኑም ሥራቸውን በታማኝነት መወጣት አለባቸው ምክንያቱም አንድ ቀን ክርስቶስ ሲመለስ ንብረቱን እንዴት እንዳስተዳድሩ መልስ ይሰጣሉ (ሉቃስ 12፡42-43፤ 1ቆሮ. 4፡2)።

ለራሳቸው የሚጨነቁ እና መንጋውን ችላ የሚሉ መጋቢያን ከባድ ፍርድ ይደርስባቸዋል። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን እረኞች አጥብቆ ያወግዛል። ለምሳሌ ያህል፣ ሕዝቅኤል በበጎች ጉዳት ራሳቸውን የሚያደልቡ እረኞች ላይ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሯል፡- “ ደካማውን አላበረታችሁትም፤ በሽተኛውን አልፈወሳችሁትም፤ የተጐዳውንም አልጠገናችሁትም። የባዘኑትን አልመለሳችሁም፤ የጠፉትንም አልፈለጋችሁም፤ በግፍና በጭካኔ ገዛችኋቸው” (ቁ. 10) ብሏል። በሌላ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር የእስራኤልን እረኞች ““መንጋዬን ስለ በተናችሁ፣ ስላባረራችሁና ተገቢውን ጥንቃቄ ስላላደረጋችሁላቸው፣ ለክፋታችሁ ተገቢውን ቅጣት አመጣባችኋለሁ” (ኤር. 23፡2) ይላል።

በአዲስ ኪዳን ያዕቆብ እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል፡- “ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፤ ምክንያቱም እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ እንደምንቀበል ታውቃላችሁ” (ያዕቆብ 3፡1)። ጴጥሮስ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች ሲጽፍ፣ “እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው ጥፋት የሚያስከትል የስሕተት ትምህርት በስውር ያስገባሉ፤ በዚህም በራሳቸው ላይ ድንገተኛ ጥፋት ያመጣሉ” (2ጴጥ. 2፡1)።

እግዚአብሔር ታማኝ ባልሆኑ መጋቢያን ላይ ሲፈርድ፣ በጎቹን በታማኝነት የሚንከባከቡትን ደግሞ በልግስና ይከፍላቸዋል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "በተገቢው ጊዜ ምግባቸውን እንዲሰጣቸው ባለቤቱ በቤተ ሰዎቹ ላይ የሾመው ታማኝና ብልኅ አገልጋይ እንግዲህ ማነው? 46 ባለቤቱ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ የተጣለበትን ዐደራ እየፈጸመ የሚያገኘው ያ አገልጋይ የተባረከ ነው፤47 እውነት እላችኋለሁ፤ በንብረቱ ሁሉ ላይ ይሾመዋል" (ማቴ. 24፡45-47)።

ጴጥሮስ ለአብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ሲጽፍ እንዲህ ሲል መክሯቸዋል፡- "2 በእናንተ ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብሔር እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን፤3 እንዲሁም በዐደራ ለተሰጣችሁ መንጋ መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በላያቸው በመሠልጠን አይሁን" (1ጴጥ. 5፡ 2-3)። ከዚያም "የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ" ብሎ አበረታታቸው (ቁ. 4)።

---

ለክርስቶስን እንደ መንጋው እረኛ ሆኖ ማገልገል ክብር እና የተቀደሰ ተግባር ነው። ኃላፊነታቸውን በታማኝነት የሚወጡ መጋቢያን በታላቅ ደስታ እና በመጠባበቅ የወደፊቱን መመልከት ይችላሉ። አንድ ቀን የጌታቸውን "ደግ አድርገሃል፤ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' ሲል ይሰማሉ (ማቴ. 25:21)።

# ~ ምዕራፍ 25 ~

# አካሉን ማጠናከር

አንድ የተከበረ ሰባኪ በመካከለኛው አፍሪካ አገር ትልቅ የስብከተ ወንጌል ኮንፈረንስ አካሄደ። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ በኮንፈረንሱ ተገኙ፣ እና በሺዎች የሚቆጠሩ ክርስቶስን እንደ አዳኝነት ለመቀበል ለቀረበላቸው ግብዣ ምላሽ ሰጡ። ኮንፈረንሱ በተካሄደበት ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።

ከሶስት አመታት በኋላ፣ የክትትል ጥናት ሲካሄድ በኮንፈረንስ ውስጥ ጌታን ካገኙ በሺዎች ከሚቆጠሩት መካከል ጥቂቶች ብቻ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንደቀሩ ታወቀ። ይህንን የሰማ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲህ ሲል መለሰ፦ "በሪፖርቱ በጣም ተረበሽኩ። በአፍሪካ ያለች ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስን የደቀ መዝሙርነት ዘዴዎች እንደገና መከለስ እንዳለባት በውስጤ ተሰማኝ። በአፍሪካ የምትገኘው የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን መስበክ ደቀ መዝሙርነትን የማድረግን ተግባር እንደሚጨምር መረዳት አለባት"

በአፍሪካ ያለችው የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌል ስኬቶች ትታወቃለች። ይህ በጎ ሆኖ ሳለ በደቀ መዝሙርነት ስኬቶችም በደንብ መታወቅ አለባት። ወንጌላዊነት እና ደቀ መዝሙርነት አብረው ይሄዳሉ። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እራሱን ወይም ራሷን ቤተክርስቲያኗን ለማሳደግ ብቻ ሳይሆን አካልን ለማጠናከር መትጋት አለባቸው። ይህ ምዕራፍ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የክርስቶስን አካል ማጠናከር ስለምትችልበት መንገዶች ያብራራል።

## የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሀላፊነት

የእያንዳንዱ መጋቢ ዋና ተግባር የሚመራውን ቤተ ክርስቲያን ማነጽ እና ማጠናከር ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተክርስቲያኗን ካገኘበት ጊዜ ይልቅ በበለጠ አጠናክሮ ለማስረከብ ማቀድ አለበት። አንድ መጋቢ ይህንን ግብ ማሳካት የሚችልበት ዋና መንገድ የደቀ መዝሙርነት ስልጠና

ነው። ይህ ተግባር ኢየሱስ ተከታዮቹን "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጉ" (ማቴ. 28፡19) ብሎ ባዘዛቸው የታላቁ ተልዕኮ ማዕከል ነው። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርት ጋር ያደረገውን ከሌሎች ጋር እንዲያደርጉ እየነገራቸው ነበር። እንደ እርሱ፣ ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን አሕዛብ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ትውልድ በመገንባት ላይ ማተኮር ነበረባቸው። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ይህንን የኢየሱስን ስልት ጎላ አድርጎ ገልጿል፡- "በብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ" (2 ጢሞ. 2:2)።

## ቤተ ክርስቲያንን ማጠናከር

ጳውሎስ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ የሰጠውን ትእዛዝ በቁም ነገር ተመልክቷል። በሐዋርያዊ አገልግሎቱ ጉልህ ድርሻ ያለው የተከልካቸውን አብያተ ክርስቲያናት ለማጠናከር ነበር። ለዚህም ነበር በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መጋቢያንን የሾመው (ሐዋ. 14፡23)፣ የተከላቸውን አብያተ ክርስቲያናት የተመለከተ (15፡41) እና የጌታን መንገድ የሚያስተምር ቀጣይ ደብዳቤ ጻፈላቸው። ጳውሎስ በተጨማሪ ጌታ አብያተ ክርስቲያናትን ለማነጽ ሐዋርያዊ ሥልጣኑን እንደሰጠው መስክሯል (2ቆሮ. 10፡ 8፤ 13፡10)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አገልግሎትህን በተመሳሳይ መንገድ መመልከት አለብህ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቶስ እንድትመሩ እንደሰጣችሁ ዋና ደቀ መዛሙርት ሰሪ እራስህን ማየት አለብህ።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በጻፈው ደብዳቤ ላይ ክርስቶስ የክርስቶስን አካል ለማጠናከር መጋቢዎችን (ከሌሎቹ አራቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ጋር) እንደ ሰጣቸው ተናግሯል (ኤፌ. 4፡11-16)። በዚህ ምንባብ ሐዋርያው የነዚህ አገልጋዮች ተቀዳሚ ኃላፊነት "[የክርስቶስን] ሕዝብ ለአገልግሎት ሥራ ማስታጠቅ" እንደሆነ ተናግሯል (ቁ. 12)። ይህን ማድረግ ያለባቸው "ሁላችንም እስክንበስል ድረስ የክርስቶስ አካል እንታነጽ ዘንድ ነው" (ቁ. 12-13)። ከዚያም፣ ጳውሎስ እንዳስረዳው፣ ቤተ ክርስቲያን "በነገር ሁሉ እርሱ ራስ የሆነው የበሰለ አካል ትሆናለች፣ እርሱም ክርስቶስ" ትሆናለች (ቁ. 15)።

ስለዚህ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ለማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ጤንነት ወሳኝ ነው። የቤተ ክርስቲያን አመራር ደቀ መዛሙርት ማፍራት ካቃተው በስብከተ ወንጌል እና በቤተ ክርስቲያን ተከላ አብዛኛው ጥረት ከንቱ ይሆናል።

## ቃላቶቹን መረዳት

ደቀ መዛሙርት የማድረጉን ሂደት የበለጠ ለመረዳት፣ ጥቅም ላይ የዋሉትን ቃላት መረዳታችን አስፈላጊ ነው። ከእነዚህ ቃላት ውስጥ ሦስቱን እንመልከት፡

**1. ደቀ መዝሙር።** ደቀመዝሙር ቁርጠኛ ተማሪ ነው። እርሱ ወይም እርሷ ከመምህር እግር ስር በትኩረት ተቀምጠው ቃላቸውን የሚሰሙ ናቸው። እንደ አንድ የእጅ ሙያ ለማጅ፣ አንድ ደቀ መዝሙር ከተዋጣለት የእጅ ጥበብ ባለሙያን ይማራል። የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ህይወቱን ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠ እና በየቀኑ እርሱን እየተከተለ፣ ከእርሱ እየተማረ ተልእኮውን የሚከታተል ሰው ነው።

**2. ደቀ መዝሙርነት።** ደቀ መዝሙርነት ኢየሱስን የመምሰል የዕድሜ ልክ ሂደት ነው። የሚጀምረው አንድ ሰው ህይወቱን ለክርስቶስ ሲሰጥ ሲሆን ማብቂያው እስከ ዕለተ ሞት ድረስ ባለው ጊዜ ነው። የደቀ መዝሙርነት ጽንሰ-ሀሳብ የአዲስ ኪዳን ዋና ጭብጥ ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል። አማኝ የሚለው ቃል በወንጌልና በሐዋርያት ሥራ 35 ጊዜ ተጠቅሶል። ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል በወንጌል 289 ጊዜ በሐዋርያት ሥራ ደግሞ 13 ጊዜ ተጠቅሷል።

ደቀ መዝሙርነት ለክርስቶስ እና ለተልእኮው መስጠትን ይጠይቃል። ኢየሱስ ተከታዮቹን “መስቀሉን ተሸክሞ የማይከተለኝ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም” ሲል አስጠንቅቋል (ሉቃስ 14፡27)። ይህን በማለቱ ደቀ መዛሙርቱ ከመሆናቸው በፊት ዋጋቸውን መተመን እንዳለባቸው ማሳሰቢያ ነው፡፡ “ከእናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም” ሲል አስጠንቅቋል (ቁ. 33)።

**3. ደቀ መዝሙር አድራጊ።** ደቀ መዝሙር አድራጊ ማለት “አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጉ” (ማቴ. 28፡19) የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ ለመታዘዝ ቁርጥ ውሳኔ የሚያደርግ ሰው ማለት ነው። እርሱ ወይም እርሷ ጌታቸውን ሙሉ በሙሉ ለመከተል እና ሌሎችንም ደቀመዛሙርት ለማድረግ የሚተጉ በሳል የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ናቸው። ውጤታማ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ሰዎችን ወደ ጌታ ማምጣት በቂ እንዳልሆነ ይገነዘባሉ። ሥራቸው ግብን የሚመታው አማኞች ወደ ሙሉ ወደ ሆነ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሲያሳድጉ ነው።

# ቤተ ክርስቲያንን የማጠናከሪያ መንገዶች

ክርስቶስ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ በሙያ ሥልጠና ብቻ እንዲሠራ አላሰበም። ይልቁንስ አምስቱን የአገልግሎት ስጦታዎች ለቤተክርስቲያኑ ሰጠ። ዓላማው መደበኛ ክርስቲያኖችን በመንግሥቱ ኑሮ እና አገልግሎት ማሰልጠን ነው። የሐዋርያት፣ የነቢያት፣ የወንጌል ሰባኪዎች፣ መጋቢያን እና አስተማሪዎች ዓላማ ክርስቲያኖችን ሰዎችን ወደ ጌታ እንዲመጡ ማሳደግ ነው፣ ከዚያም እርስ በርሳቸው መተሳሰብንና እርስ በርሳቸውም ውጤታማ የክርስቶስ አገልጋዮች እንዲሆኑ ማስተማር ነው (ኤፌ. 4፡11-16)። .

ስለዚህ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ እንደተጠራ እና የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለማራመድ ስልጣን እንደተሰጠው ማስተማር አለብህ። ጥቂቶች ለሐዋርያነት ሲጠሩ፣ ሁሉም በታላቁ ተልዕኮ እንዲሳተፉ ተጠርተዋል። ጥቂቶች ለነቢይነት ሲጠሩ፣ ሁሉም ለትክክለኛና ለበጎ ነገር ለመቆም ተጠርተዋል። ጥቂቶች ለወንጌል ሰባኪዎች ሲጠሩ፣ ሁሉም ግን እምነታቸውን ለሌሎች ለማካፈል ተጠርተዋል። ጥቂቶች አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሲጠሩ፣ ሁሉም ክርስቶስን እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው ሌሎችን እንዲያስተምሩ ተጠርተዋል። ጥቂቶች መጋቢ ለመሆን ሲጠሩ፣ ሁሉም ሌሎችን በፍቅር እንዲንከባከቡ ተጠርተዋል። እንደ መጋቢ፣ የአንተ ስራ እነዚህን ነገሮች ለእግዚአብሔር ህዝብ ማስተማር እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠንካራ የደቀ መዝሙርነት ስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት ነው።

ቤተ ክርስቲያንህን ለማጠናከር ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ስድስት ስልቶችን እንመልከት፡

## ደቀ መዝሙርነትን በዐርዓያነት ማሳየት

በመጀመሪያ፣ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በዐርዓያነት በማሳየት ቤተ ክርስቲያንን ማጠናከር ትችላለህ። እውነተኛ ደቀ መዝሙር ምን እንደሚመስል በራስህ ህይወት ማሳየት አለብህ። የቤተ ክርስቲያን አባላት የፓስተራቸውን ቅዱስ አኗኗር ሲመለከቱ፣ በተመሳሳይ መንገድ እንዲኖሩ ይበረታታሉ። እነርሱም የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ይፈልጋሉ። በውጤቱም፣ ቤተክርስቲያኑ ታድጋለች እና ፍሬያማ ትሆናለች፣ እናም የእግዚአብሔር መንግስት ይሰፋል።

ይህ የደቀ መዝሙርነት ስልት በተለይ በወንጌል ባልተደረሱ ቦታዎች አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለማቋቋም አስፈላጊ ነው። በወንጌል ባልተደረሱ ቦታዎች ያሉ አዲስ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ መኖር ምን

ማለት እንደሆነ ግንዛቤ የላቸውም። የክርስትና ሕይወት ብቸኛ ምሳሌያቸው መጋቢው እና የቤተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ነው። በመሆኑም ልክ እንደ ጳውሎስ ለሕዝቡ፡- "እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል እናንተም የእኔን ተከተሉ" (1ቆሮ. 11፡1) ለማለት ዝግጁ መሆን አለብህ።

## ስብከት እና ማስተማር

ሁለተኛ፣ ስልታዊ በሆነ ስብከት እና ስልታዊ በሆነ የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት የክርስቶስ አካልን ማጠናከር ትችላለህ። ስልታዊ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ግልጽ ዓላማን ይዘን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክቶችን ማዘጋጀት እና መስበክ ነው። ይህንን ለማድረግ በመጀመሪያ በጸሎት እና በቃሉ ላይ በማሰላሰል መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራበትን አቅጣጫ መወሰን አለብህ። በጸሎት ስትጠባበቁ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ "መንገዱ ይህ ነው፤ በእርሱ ሂድ" በማለት ለልባችሁ ይናገራል (ኢሳ. 30፡ 21)።[1]

አንዴ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን መመሪያ ከተገነዘብክ፣ ቤተክርስቲያኗን ወደዛ አቅጣጫ ለማንቀሳቀስ ያተኮሩ ስብከቶችን ማዘጋጀት እና መስበክ መጀመር አለብህ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን "ሙሉውን የእግዚአብሔር ምክር" ማለትም መላው የእግዚአብሔር ቃል እየተማረች መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ (ሐዋ. 20፡27)። እነዚህ ልምምዶች የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል እና ለሕይወታቸው ያለውን ፈቃድ እንዲገነዘቡ ይረዳል።[2]

በተጨማሪም፣ በትምህርት እና ስብከትህ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ተልዕኮ ተደጋጋሚ መልዕክቶችን ማስተላለፍ አለብህ። በዚህ ተልዕኮ ውስጥ መሳተፍ የቤተ ክርስቲያንን ሃላፊነትንም ማካተት አለበት። አንዳንድ ጊዜ ሚሲዮ ዴኢ ተብሎ የሚጠራው የእግዚአብሔር ተልእኮ፣ በምድር ላይ ካሉ ነገዶች፣ ቋንቋ እና ህዝቦች ሁሉ ሰዎችን ለመቤዠት እና ለመጥራት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ነው (ራእ. 5:9፤ 7:9)። ኢየሱስ በታላቁ ተልእኮው ንግግሩ ውስጥ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም የቤተ ክርስቲያንን ሃላፊነት አፅንዖት ሰጥቷል (ማቴ. 28፡18-20፤ ማር. 16፡15-18፤ ሉቃስ 24፡46-49፤ ዮሐንስ 20፡21-22፤ ሐዋ. 1፡8)።

## ህዝብን በመንፈስ ቅዱስ ማስታጠቅ

ሦስተኛ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለአገልግሎት መብቃታቸውን በማረጋገጥ አካልን ማጠናከር ትችላለህ። ይህ ለአገልግሎት ማብቃት መንፈሳዊ እና ስነ ልቦናዊ ማበረታታትን ያካትታል።

መንፈሳዊ ማበረታታት። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተልዕኮ እንደተሰጠው ማየት አለብህ። ይህ የኢየሱስ ለቤተ ክርስትያን የሰጠው የመጨረሻ ትእዛዝ ነበር። ወደ ሰማይ ከማረጉ ጥቂት ቀደም ብሎ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፡- " "ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤5 ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" አለ (ሐዋ. 1፡4-5)። ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤

---

[1] በዚህ ርዕስ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 15ን "ጠንካራ የማደር ልማድ" የሚለውን ተመልከት።

[2] በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 16:- "በመንፈስ የተቀቡ ስብከት" እና ምዕራፍ 17:- "ውጤታማ ትምህርት" የሚለውን ተመልከት። "እውነትን መኖር" እና "የእምነት ሥር" የደቀመዝሙርነት ሥርዓተ ትምህርት በነጻ www.africaatts.org/resources ላይ ማውረድ ይቻላል።

በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" አላቸው (ቁ. 8)፡፡ ምዕራፍ ሁለት እንደሚያሳየን ደቀ መዛሙርቱ የክርስቶስን ሲታዘዙ ኢየሱስ የገባውን ቃል ፈጸመ።

የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ነበር፤ 2 ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው። 3 የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ። 4 ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር። ሐዋ 2፡1-4

ይህ መለኮታዊ ኃይል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውጤታማ የሆነ የወንጌል አገልግሎት ለማገልገልና እና ተልዕኮን ለመወጣት ቁልፍ ጉዳይ ነው። ስለዚህ በርዕሱ ላይ ብዙ ጊዜ መስበክ እና ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከምእመናን ጋር መጸለይ አለብህ።[3] በመንፈስ ኃይል እንዴት እንደሚኖሩ እና እንደሚራመዱ የበለጠ ማስተማር አለብህ። የመንፈስን ፍሬ እንዲያፈሩ እና የመንፈስን ስጦታዎች በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው እንዲገልጡ ልታበረታታቸው ይገባል (ገላ. 5፡22-23፤ 1ቆሮ. 12፡8-10)።[4]

ስነ-ልቦናን ማጎልበት። እንደ መጋቢ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለአገልግሎት የስነ ልቦና ብቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ መስራት አለብህ። አባላት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፉ በሩ ክፍት እንደሆነ ሲያዩ የሥነ ልቦና ጥንካሬ ያገኛሉ። በር መከፈቱ በመረጡት አገልግሎት ውጤታማ እንዲሆኑ የበለጠ ያደርጋል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በምእመናን ላይ እንዲህ ያለ እምነትን ማፍራት የአንተ ድርሻ ነው።

ይህን ስታደርግ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለአገልግሎት ፈቃደኛ እንዲሆኑ ይበረታታሉ። ነገር ግን፣ ይህን ማድረግ ካልቻል በአገልግሎት ለመሳተፍ ፈቃደኞች አይሆኑም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአገልግሎት ብቁ የሆንከው አንተ ብቻ እንደሆንክ ከመናገር መቆጠብ አለብህ። ይልቁንም ለሁሉም ሰው የሚሆን የአገልግሎት ቦታ እንዳለ አፅንዖት መስጠት አለብህ። ክርስቶስን በብቃት ማገልገል እንደሚችሉ መተማመንን በሰዎች ልብ ውስጥ ልትፈጥር ይገባል።

## ሠራተኞችን ለሥራ ማንቀሳቀስ

ህዝቡ ከያዘ በኃይል ከታጠቀ በኋላ ለአገልግሎት መቀስቀስ አለበት። ቤተ ክርስቲያንን የምታጠናክርበት አራተኛው መንገድ ይህ ነው። ሰራተኞችን ለሥራ ማንቀሳቀስ ሂደት የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል:

**አስፈላጊነትን መለየት።** ልትሞላ የምትፈልገውን ክፍተት በመለየት ለሥራ ማንቀሳቀስ ሂደቱን ጀምር። ቤተ ክርስቲያን አዲስ የሕፃናት አገልግሎት መጀመር ነው? አዲስ ቤተ ክርስቲያን መትከል ነው? የቤተ ክርስቲያንን የአምልኮ አገልግሎት ማሻሻል ወይም ሌላ ተግባር ማከናወን ትፈልጋለህ? ማየት የምትፈልገውን በግልፅ በማስቀመጥ ለሥራ ማንቀሳቀስ ሂደቱን መጀመር አለብህ።

---

[3] የጴንጤቆስጤ ዕለት አዋጅ፡ 100 የስብከት መግለጫዎች በፒዲኤፍ ኢ-መጽሐፍ ከ www.DecadeofPentecost.org ድህረ ገጽ ላይ በነፃ ማውረድ ይችላሉ። መንፈስን ለመቀበል ከአማኞች ጋር እንዴት መጸለይ እንዳለብን ለተጨማሪ ማብራሪያ፣ ምዕራፍ 20ን "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" የሚለውን ተመልከት፡ ።

[4] ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ትርጓሜ፣ አባሪ 2ን "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 መገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት፡።

***የስራ እድሎችን መፍጠር።*** ከዚያም ምን አይነት የስራ መደብ ወይም ዘርፍ መፈጠር እንደሚያስፈልግህ መወሰን አለብህ። ለእያንዳንዱ አዲስ የዘርፍ አገልግሎት የሥራ መግለጫ ማዘጋጀት አለብህ። የሥራ መግለጫው ለሥራው መመዘኛዎችን እና ቦታውን የያዘውን ሰው ተግባራት ማካተት አለበት፡፡

***መጸለይ።*** በሂደቱ ሁሉ የመከሩን ጌታ የሚፈለጉትን ሠራተኞች እንዲያስነሳ በመለመን ወደ መከሩ ጌታ መጸለይ አለብህ (ሉቃስ 10፡2)።

***ራዕይን ማጋራት።*** በትክክለኛው ጊዜ ራዕዩን ለቤተ ክርስቲያን ማካፈል አለብህ። ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እንደሚባርክ እየገለጽክ ስለ አዲሱ የአገልግሎት ዘርፍ ለምእመናን መንገር አለብህ።

***ሠራተኞች መቅጠር።*** ከዚያ በጎ ፈቃደኞችን መጠየቅ አለብህ። ስራው ምን እንደሚያካትት በትክክል መናገር ያስፈልጋል። ሥራውን በጥሩ ሁኔታ ሊሠሩ ይችላሉ ብለህ የምታስባቸውን የተወሰኑ ግለሰቦችን መለየት እና ስለ በጎ ፈቃደኝነት እንዲጸልዩበት መጠየቅ ይገባል። የግለሰቡን ስጦታዎች ከሥራ መስፈርቶች ጋር ማዛመድ አለብህ።

**ስልጠና።** በፈቃደኝነት ለሚሰሩ ሰዎች የስልጠና መርሃ ግብር ማዘጋጀት አለብህ።

***በማስማራት።*** አዲሶቹን አገልጋዬች ከመረጥክ በኋላ እና በትክክል ካሠለጠንካቸው በኋላ ወደ ቦታቸው ማስማራት አለብህ። ከዚያም ከአዲሶቹ አገልጋዬች ጋር መገናኘ እና እድገታቸውን መከታተል እና በስራው ውስጥ ማበረታታት ቤተ ክርስቲያኒቱም ለእነዚህ ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች ልታሟላላቸው ይገባል።

## የአገልግሎ ሥልጠና

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ለአገልግሎት አባላትን ስናጭ በበጎ ፈቃደኝነት ምላሽ ለሰጡ ሰዎች ስልጠና ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለብህ። ሰዎች ለሥራው እንደሚሰለጥኑ ካወቁ በፈቃደኝነት የመሥራት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ስልጠናም የስኬት እድላቸውን በእጅጉ ያሳድጋል። ይህ ስልጠና በልዩ ሴሚናሮች ወይም በስራ ላይ ስልጠና ሊከናወን ይችላል። ስልጠናው ስራውን ለምን እና እንዴት እንደሚሰራ ሊሸፍን ይገባል። አዲሶቹ ሰራተኞች አገልግሎቱ ለምን እንደተቋቋመ እና ምን ለማከናወን እንደሚፈልግ ማወቅ አለባቸው። እንዲሁም ሥራውን እንዴት በተሻለ መንገድ እንደሚሠሩ መማር አለባቸው። ፓስተሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት ትምህርትን መጀመር ሊያስፈልገው ይችላል።[5]

## የተሰጡትን መቅረጽ

አካልን ማጠናከር የምትችልበት የመጨረሻ መንገድ ለአገልግሎ ፍላጎት የሚያሳዩትን በመለየት እና በጥንቃቄ በመምከር ነው። እንደ መጋቢ፣ ለእግዚአብሔር ሥራ ልዩ ቅንዓት እንዳላቸው የሚያሳዩትን አባላት ልብ በል። በእነዚህ ግለሰቦች ላይ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለ ልትገነዘብ ይገባል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንዳደረገው ከእነርሱ ጋር የመማከር ግንኙነት መመሥረት ያስፈልግሀል። ከዚያም ከእነዚህ ግለሰቦች ጋር ጊዜ አሳልፍ።፣ ከእነርሱ ጋር በመጸለይ እና በአንዳንድ የአገልግሎት ተግባራት ውስጥ አብረውህ እንዲቀላቀሉ ጋብዛቸው።

አንዳንዶች የኢየሱስ ደቀ መዝሙርነት ስልት ሦስት ሂደቶችን ያካትታል ይላሉ፡- በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ሌሎችን ሲያገለግል ደቀ መዛሙርቱ ይመለከቱ ነበር። አንዳንዴ ወደ ጎን ወስዶ ያደረገውን እና

[5] ይህ አገልግሎት በምዕራፍ 17 ላይ “ውጤታማ ትምህርት” ተብራርቷል።

ለምን እንዳደረገው ያብራራላቸው ነበር። ሁለተኛ፣ ኢየሱስ እየተመለከታቸው ደቀ መዛሙርቱ አገልግለዋል። ከዚያም ሥራቸውን ይገመግም ነበር። በመጨረሻም፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በራሳቸው እንዲያገለግሉና ሌሎችን ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ ልኳቸዋል። ጌታ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው እና መንፈስ ቅዱስም በአገልግሎት እንደሚረዳቸው ቃል ገብቷል።

በመማከር ግንኙነት ያቀረብካቸው አንዳንዶች የአገልግሎት ጥሪ ሊሰማቸው ይችላል። ይህ ሲሆን ጥሪውን መመርመር ያስፈልጋል። ጥሪን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ልታግዛቸው ያስፈልጋል።

---

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን "እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል" በማለት ያስተምራል። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተ ክርስቲያንን ለማጠናከር ከሁሉ የተሻለው መንገድ ጠንካራ የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም ማዘጋጀት ነው። ይህ ፕሮግራም አማኞችን ወደ ደቀ መዛሙርት፤ ደቀ መዛሙርትን ደግሞ ወደ ውጤታማ የወንጌል አገልጋዮች ለመቀየር ያለመ መሆን አለበት።

# ~ ምዕራፍ 26 ~

# የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማማከር

የቤተ ክርስቲያንህ አባላት ከብዙ አመታት ከዘለለ የትዳር ግንኙነት በኃላ ለመፋታት ያስባሉ። ባለቤቱን በሞት የተነጠቀ ወንድም ከኃዘን እና ብቸኝነት ጋር ይታገላል። አንዲት ያለ አባት ልጆችን የምታሳድግ እናት የካንሰር ምርመራን አድርጋ ካንሰር እንዳለባት ትሰማለች። ወላጆ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኘውን እንግዳ ባህሪ ያመጣውን ልጃቸውን ለመቆጣጠር ይታገላሉ። በመላው አፍሪካ የሚገኙ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተክርስቲያናችን አባላት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ጉዳዮች መካከል እነዚህ የመሳሰሉት ይገጥሟቸዋል። ከአጋንንት እስራት፣ ሥር የሰደደ ድህነት፣ ሥራ አጥነት፣ ሱስ አስያዥ ልማዶች እና ሌሎችም ጋር የሚታገሉትን ወደ ዝርዝሩ ሊጨመሩ ይችላሉ።

እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶችን በራሱ አምሳል ፈጠረ። አዳምንና ሔዋንን በአካላቸው፣ በአእምሮና በመንፈስ ፈጥሯቸዋል። ከእርሱ ጋር ፍጹም ተስማምተው የሚኖሩ "የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች" ነበሩ። ነገር ግን፣ በኃጢአት ሲተላለፉ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እና እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት ተናጋ (ዘፍ. 3፡6-24፤ ሮሜ. 5፡12)። ስብራት እና ስቃይ የሰው ልጅ የኑሮ አካል ሆነ።

መጋቢያዊ ምክር የመጋቢ አገልግሎት ማዕከል ነው። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን አፍቃሪ፣ ተቆርቋሪ ማህበረሰብ እንድትሆን ጠርቷታል። የእግዚአብሔር ህዝብ ከጌታ ጋር እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመሆን ለተሰበሩ ሰዎች ፈውስ እና ሙሉነትን እንዲያመጡ ይፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን የጠፉ ሰዎች ለውጥ፣ እርቅ እና ተስፋ የሚያገኙበት መሆን አለበት (2ቆሮ. 5፡18-19)። እግዚአብሔር ይህ ተግባር መፈጸሙን እንዲያረጋግጥ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢን ሾሞታል።

ይህ ምዕራፍ በአፍሪካ የጴጤቆስጣዊ መጋቢ የምክር አገልግሎትን ይዳስሳል። የመጋቢውን የምክር ልዩ ባህሪያት ያብራራል  በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይጥላል። በምክር ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሚና የበለጠ ይመረምራል። በመጨረሻም፣ ስለ መጋቢ ምክር ዓይነቶች፣ መርሆች እና ሥነ-ምግባር በአጭሩ ያወያያል።

# እንደ አማካሪ ይመግባል

ክርስቶስ እያንዳንዱን የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ እንዲወጣ ጠርቶታል። አማኞችን ውጤታማ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ መጋቢውን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል (ኤፌ. 4፡11-12)። ከመስበክ፣ ከማስተማር እና ከመምራት በተጨማሪ ክርስቶስን ሙሉ በሙሉ የሚከተሉ አባላት መንፈሳዊ ምክር እና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት ለፓስተሩ ተሰጥቶል።

## የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ

የአገልግሎቱ ማብቂያ እየቀረበ ሲመጣ፣ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ "በጎቼን ጠብቅ" ብሎ አዘዘው (ዮሐንስ 21፡16)። ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ባደረገው የስንብት ንግግር፣ መጋቢያን ነቅተው መጠበቅ እንዳለባቸው ገልጿል። በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እረኞች ይሆኑ ዘንድ ይገባቸዋል (ሐዋ. 20፡28)። በተመሳሳይ፣ ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች "የእግዚአብሔርን መንጋ እረኞች እንዲሆኑ" አሳስቦል(1 ጴጥ. 5፡2)። የተጎዱትን፣ የሚታገሉትን እና የቆሰሉትን በጎች መንከባከብ ነበረባቸው።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የማማከር ጥሪ የሙያ ጉዳይ ብቻ አይደለም ፤ መለኮታዊ ሹመት ነው። የቤተ ክርስቲያን አባላት (እና በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ አባል ያልሆኑ) ከስሜታዊ፣ ማህበራዊ እና መንፈሳዊ ጉዳዮች ጋር ሲታገሉ፣ እርዳታ ለማግኘት ወደ ፓስተራቸው መዞር መቻል አለባቸው። እረኛ በጎቹን እንደሚመግብ፣ እንደሚመራ እና እንደሚከላከል ሁሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያንም ክርስቶስ በእነርሱ ሥር ያስቀመጣቸውን መንከባከብ አለባቸው።

## ልዩ ግንኙነት

ከሌሎች የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች ጋር ሲወዳደር፣ የመጋቢው የምክር አገልግሎት ልዩ ነው። ሰዎች ብዙውን ጊዜ መጋቢያንን እንደ እግዚአብሔር ተወካዮች አድርገው ይመለከቷቸዋል። በፈውስ ሂደት ውስጥ እንደ በእግዚብሔር የተቀቡ እና እደ ታጠቁ ያዩዋቸዋል። ከሌሎች የአዕምሮ ጤና ባለሙያዎች በተለየ የፓስተሩ አላማ የእግዚአብሔርን ህዝብ "በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት ሲያድጉ"(2ጴጥ. 3፡18) ማየት ነው።

በተጨማሪም፣ መጋቢያን ከአባሎቻቸው ጋር የመተማመን ግንኙነት አላቸው። ችግሮቻቸውን፣ የሕይወት ምዕራፎቻቸውን እና ስኬቶቻቸውን ጨምሮ በተለያየ የአባሎቻቸው ህይወት ጉዳይ ውስጥ ይሳተፋሉ። የጋብቻ ሥነ-ሥርዓቶችን፣ የልጅ መሰጠትን እና የቀብር ሥነ ሥርዓቶችን እንዲያካሂዱ ይጠራሉ። በዚህ ልዩ ግንኙነት ምክንያት አባላት በቀላሉ ምን ይሉኝን ሳይፈሩ ከመጋቢያቸው ጋር ሚስጥራቸውን ማጋራት ይችላሉ።

በተጨማሪም መጋቢያን ከሌሎች የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች የበለጠ ተደራሽ ናቸው። ብዙ ማህበረሰቦች ባለሙያ አማካሪዎች የላቸውም። በሚገኙበት ጊዜም እንኳ አገልግሎታቸው ብዙ ጊዜ ውድ ነው። የብዙሃኑ ብቸኛ ተስፋ መጋቢ ነው። በተጨማሪም፣ ልክ እንደ ጌታ፣ መጋቢያን "ለተጨቆኑ እና ረዳት ለሌላቸው" (ማቴ. 9፡36) በርኅራኄ መድረስ ይችላሉ። ምክር መስጠት የእግዚአብሔርን ፍቅር ከተጎዱት ጋር ለመካፈል እንደ አጋጣሚ አድርገው ይመለከቱታል።

## ጋቢያዊ የምክር አገልግሎት

ዛሬ በመላው አፍሪካ፣ በርካታ የምክር ሞዴሎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። እያንዳንዳቸው የሰውን ሁኔታ ውስብስብ ተፈጥሮ ለመፍታት ያለሙ ናቸው። ሁሉም ደግሞ በተወሰነ የዓለም እይታ እና እምነት

ስርዓት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል፡- ዓለማዊ እይታ፣ የአፍሪካ ባህላዊ እይታ እና የክርስቲያን አተያይ ያካትታሉ።

ዓለማዊ የስነ-ልቦና ምክር በዓለም አተያይ እና አቀራረብ ሳይንሳዊ ነው፣ ብዙ ጊዜ የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት ይክዳል። ይህ አካሄድ የአዕምሮ፣ የስሜታዊ እና የጠባይ መታወክ በሽታዎችን ለማከም የተለያዩ ቴክኒኮችን እና ህክምናዎችን ይጠቀማል። በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች፣ አገር በቀል አፍሪካዊ የፈውስ ዘዴዎች እውቅና ተሰጥቷቸው ከምዕራባውያን የሕክምና ዓይነቶች ጎን ለጎን እንዲሠሩ ተፈቅዶላቸዋል። እነዚህ ባህላዊ አካሄዶች ህይወትን እና ደህንነትን የማይታዩ መንፈሳዊ ሀይሎችን ጋር በሚያገናኘው የአፍሪካ እይታ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የምክር አቀራረብ ከዓለማዊ ወይም ባህላዊ አቀራረብ የተለየ ነው። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አካሄድ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረተ፣ ክርስቶስን ያማከለ እና በመንፈስ የሚመራ ነው። የእረኝነት ምክር በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ላይ የተመሠረተ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እና "ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል" (2ጢሞ. 3፡16) ያምናል። የእግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ መጠን መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወት ውስጥ ለሚፈጠሩ ችግሮች ሁሉ መልስ ይዟል።

# ለመጋቢነት ምክር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያምናል። ስለሆነም፣ ለምክር አገልግሎት ትክክለኛ መመሪያ ነው። ከሌላው የመመርመሪያ መሣሪያ በተለየ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ልብ ጥልቅ ምሥጢር ያሳያል (ዕብ. 4፡12)። የሰው ልጆችን ስብራት ከሥር መሰረት ያነሳል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ችግሮች ሁሉ መፍትሔ እንደሆነም ያሳያል።

ይህ ማለት የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደመሆንህ መጠን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሚገኙ እውነቶች ራስህን መሙላት አለብህ ማለት ነው። በተጨማሪም እነዚህ እውነቶች በምክር አገልግሎትህ ልትጠቀማቸው ይገባል። የማማከር ችሎታህን ለማሳደግ ከዓለማዊ ንድፈ ሐሳቦች ለመዋስ ከመረጥክ፣ እነዚህ ንድፈ ሐሳቦች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እና ከክርስቲያናዊ እሴቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብህ።[1]

### የብሉይ ኪዳን መሪዎች

ብሉይ ኪዳን አምላካዊ ምክርን የሚያቀርቡ የመሪዎችን ምሳሌዎችን በብዛት ይዟል። ለምሳሌ፣ ሙሴ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሲፈርድና ሲመክር ብዙ ሰዓታት ያሳልፍ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በቡድን ሆነው ይመክራቸው ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ወይም ሁለት ብቻ ሆነው ይመክር ነበር (ዘጸ. 18፡13-27)። ይሁን እንጂ ሙሴ ራሱ ምክር የሚያስፈልገው ጊዜ ደረሰ። አማቹ ዮቶር በሥራው እንደደከመ ስላአስተዋለ ሙሴን ለመርዳት ብቃት ያላቸውን ሰዎች እንዲመርጥ መከረው። ሙሴ የዮቶርን ምክር በመከተል ሥራው ተሳካለት።

---

[1] የጴንጤቆስጤ ፓስተር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ስላለው ግንኙነት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 9ን "መጽሐፍ ቅዱስን ያምናል" የሚለውን ተመልከት።

ዳዊት አምላካዊ አማካሪ የሆነ ሌላ ምሳሌ ነው። በመዝሙሩም ሕዝቡን መከሯል። የህይወት ጉዳዮችን ለመፍታት ብዙ መልካም ስልቶችን አቅርቧል። በምሳሌም መጽሐፍ ስለ ሰሎሞን፤ ነቢያት በጽሑፎቻቸው ስላሰፈሩት ምክር ተመሳሳይ ነገር ሊባል ይችላል።

## የኢየሱስ አገልግሎት

ኢየሱስ ራሱ አማካሪ ነበር። ኢሳይያስ “ድንቅ መካር” ብሎ ጠርቶታል (ኢሳ. 9፡6)። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ከመንፈሳዊ ጉዳዮች ጋር ለሚታገሉ ሰዎች ምክር ሰጥቷል። ሦስቱ የሚታወቁ ምሳሌዎች ኒቆዲሞስ (ዮሐንስ 3፡1-21)፣ ዘኬዎስ (ሉቃስ 19፡1-9) እና በዝሙት የተያዘችው ሴት (ዮሐንስ 8፡1-11) ናቸው። ኢየሱስ “እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ” (ዮሐንስ 10፡10) ብሏል።

አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ በስሜት የተጨነቁትን ያገለግል ነበር። ማርያምና ማርታ ወንድማቸውን አልዓዛርን ባጡ ጊዜ ኢየሱስ ወደ እነርሱ መጣ። ርኅራኄ አሳያቸው እናም በሐዘናቸው አብሯቸው ሆነ (ዮሐ. 11፡17-44)። ከመሰቀሉ በፊት በነበረው ምሽት፣ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለሚመጣው መከራ ሲያዘጋጃቸው ብዙ ጊዜ አሳልፏል (ዮሐንስ 14-16)።

የኢየሱስ የምክር አገልግሎት ከተለያዩ የሕይወት ዘርፎች የተውጣጡ ሰዎችን የነካ ነበር። የተማሩትን እና ያልተማሩትን፣ የከበሩትን እና ተራውን፣ ሀብታምና ድሆችን፣ ወንዶችን፣ ሴቶችን እና ህፃናትን ሁሉ የነካ ነበር። ኢየሱስ ለሰዎች ያለው ፍቅር ሁሉንም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መሰናክሎች ተሻግሮ የጠፉትን የመፈለግ እና የማዳን ተልእኮውን ለመፈጸም ገፋፍቶታል (ሉቃስ 19፡10)።

## የጳውሎስ የምክር አገልግሎት

የጳውሎስ ደብዳቤዎች እንደ ምክር ሊነበቡ ይችላሉ። ሐዋርያው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ያለውን አሳቢነት መጋቢያዊ ልብ ያሳያሉ። በእነርሱ ውስጥ ከሕይወትን ጉዳዮች ጋር የሚታገሉትን ይመክራል። ለምሳሌ በፊልጵስዩስ ላሉት አማኞች “ስለ ምንም ነገር አትጨነቁ” በማለት ጽፎላቸዋል። ቢጸልዩ የእግዚአብሔርን ሰላም ያገኛሉ (ፊልጵ. 4፡6-7)። ሌላው የጳውሎስ የምክር አገልግሎት ምሳሌ ከሆነው ከጢሞቴዎስ ጋር አብሮ የመጣበት መንገድ ነው። ጳውሎስ የድፍረትን እና በራስ የመተማመን ስሜትን ችግርን በመፍታት ረድቶታል (2ጢሞ. 1:3-14፤ 2:15)።

ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው ደብዳቤ ላይ አንዳንድ አሉታዊ አስተሳሰቦችን እና ምግባሮችን ቤተ ክርስቲያንን ሊያፈርሱ እንደሚችሉ ተናግሯል። ሐዋርያው ለፊልሞና በጻፈው ደብዳቤ ላይ በፊልሞና እና ከአሳዳሪው ጠፍቶ አምልጦ የነበረው ነገር ግን አሁን ክርስቲያን ወንድም በሆነው በባሪያው አናሲሞስ መካከል የተፈጠረውን ግንኙነት ለማስተካከል ያለመ ነበር። የጳውሎስን ደብዳቤዎች በጥልቀት ስንመረምር የምክር ዘዴው ክርስቶስን ያማከለ፣ በመንፈስ የሚመራ፣ የሚያስተምር፣ የሚደግፍ፣ የሚያስማማ እና አንዳንዴም የሚጋጭ እንደነበር እናያለን።

# በምክር አገልግሎት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሚና

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በምክር አገልግሎትህ ውስጥ ጠንካራ አጋር አለህ። ያ አጋር መንፈስ ቅዱስ ነው። በእርሱ ላይ መታመንን መተው የለብህም። አንድ ወታደር መሳሪያውን ሳይዝ ወደ ጦርነት ሲሄድ አስቡት። ይህ ወታደር ሁሉንም የደንቦችን እና የጦርነት ስልቶችን ሊያውቅ ይችላል፣ ነገር ግን ያለ መሳሪያው መጨረሻው አስከፊ ነው። የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ መንፈሳዊ ጦርነት መግባትም እንዲሁ ሞኝነት ነው።

## *ረዳት*

ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን አራት ጊዜ ጰራቅሊጦስ ሲል ጠርቶታል፣ ፍችውም በግሪክ "ረዳት" ወይም "መካሪ" ማለት ነው (ዮሐ. 14፡16፣ 26፤ 15፡26፤ 16፡7)። እንደ ሰማያዊ መካሪያችን፣ መንፈስ ቅዱስ በምክር አገልግሎት ጉዞ ሁሉ ሊረዳን ዝግጁ ነው። ከተጋበዘ አማካሪውን ይመራል፣ ያጠናክራል እና ይደግፋል። እናም አገልግሎት ተቀባዩን ደግሞ ህመሙን እና ትግሉን እንዲቋቋም ይረዳዋል (ዮሐ. 14፡1፤ 16፡8)። መምከር ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ ጦርነትን ያስከትላል (ኤፌ. 6፡12)። በእውነት "ልባቸው የተሰበረውን ይጠግን" እና "ለታሰሩት ነጻነትን ለማወጅ የሚያስችል ብርቱ የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው" (ኢሳ. 61፡1፤ ሉቃ. 4፡17-18)። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ "በጌታና በታላቅ ኃይሉ የበረታችሁ ሁኑ" (ኤፌ. 6፡10) ሲል ያበረታታናል።

በቅንነት እና በእምነት የተሞላ ጸሎት የምክር ሂደቱ አስፈላጊ አካል ነው። ይህ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ይረዳል። መጽሐፍ ቅዱስ "እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል" (ሮሜ. 8፡26)። ኢየሱስ የሰማይ አባት ለሚለምን ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጥ ተናግሯል (ሉቃስ 11፡9-10፣13)።[2]

ኢየሱስ ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አማካሪ ፍጹም አርአያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ "በዲያብሎስ ሥር ያሉትን ሁሉ [ለመፈወስ]" (ሐዋ. 10፡38) በመንፈስ ቅዱስ እንደተቀባ ይናገራል። በዚህ ቅባት ለድሆች የምስራች አበሰረ፣ ለታሰሩትም ነፃነትን አውጇል፣ የተጨቆኑትን ነጻ አወጣ (ሉቃ. 4፡18)። ጳውሎስ ለጴንጤቆስጤያዊ አማካሪ የሚሆን ሌላ ጥሩ አርአያ ነው። ምንም እንኳን ጳውሎስ ታላቅ ትምህርት እና ስኬት ቢኖረውም፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ላይ ተደገፈ (1ቆሮ. 2፡4-5)። በተመሳሳይ መልኩ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ውጤታማ አማካሪ ለመሆን የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያስፈልገዋል።

## የእውነትን የሚገልጥ

ኢየሱስ በተጨማሪ መንፈስ ቅዱስ የእውነት ሁሉ ገላጭ እንደሆነ አስተምሯል (ዮሐ. 16፡13)። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንድንረዳ እና እንድንተረጉም ይረዳናል። ደግሞም የእግዚአብሔርን አሳብ እና ስለ ምንመክራቸውን ሰዎች አሳብ ግንዛቤዎችን ይሰጠናል (1 ቆሮ. 2፡11-12)። ይህ አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የአንድ ሰው ባህሪ የሚወሰነው በእርሱ ሃሳቦች እና በህይወት ክስተቶች ላይ በሚያስቀምጠው ትርጓሜዎች ነው። በህይወቱ ዙሪያ የተከሰቱት ስህተቶች በክፉ ኃይሎች እና ቅድመ አያቶች አምልኮ የተከሰቱ ናቸው ብሎ የሚያምን ሰው ይኖራል። መንፈስ ቅዱስ ነጻ የሚያወጣቸውን እውነት እንዲያውቁ ይረዳቸዋል (ዮሐ. 8፡32)።

## ስጦታ ሰጪ

የአእምሮ ጤና ችግሮች የተለያዩ፣ ውስብስብ እና ከባህል ጋር የተገናኙ ናቸው። ተፈጥሮዊ እና መንፈሳዊ ጉዳዮችን ያካትታሉ። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለምክር ሂደቱ አስፈላጊ ነው (1ቆሮ. 12፡ 8-10)። በራዕይ ስጦታ፣ መንፈስ ቅዱስ ለጴንጤቆስጤ አማካሪው ስለ ሚያማክረው ግለሰብ ፍላጎቶች ግንዛቤን ሊሰጥ ይችላል። መናፍስትን በመለየት ስጦታ አማካኝነት፣ የአጋንንት መናፍስትን መኖር እና

---

[2] አማኞች መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ስለመርዳት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 20 ተመልከት፡ "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" የሚለውን ተመልከት፡።

እንቅስቃሴ ሊገልጥለት ይችላል። በትንቢታዊ ስጦታ፣ አማካሪው በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተስፋ እና የፈውስ መልዕክትን ሊያመጣ ይችላል። ስለዚህ የጴንጤቆስጤው መጋቢ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እና በእያንዳንዱ የምክር ሂደት ውስጥ ለሚሰራው ስራ ንቁ መሆን አለበት።[3]

# የመጋቢ ምክር ዓይነቶች

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የሚከተሉትን የምክር ዓይነቶች ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለበት፡-

## መንፈሳዊ ምክር

መንፈሳዊ ምክር ተመካሪው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት እና ለህይወቱ ያለውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ያተኩራል። መንፈሳዊ ምክር ሲሰጥ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ዋና ትኩረት አማካሪው ከክርስቶስ ጋር ወደ ህያው ግንኙነት እንዲመጣ ነው። ሌላው አሳሳቢ ነገር ይሄ መንፈሳዊ ግንኙነት ጤናማ እና እያደገ መምጣቱ ነው። ሌሎች ተዛማጅ የምክር ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ሰውዬው እግዚአብሔርን እንደ ወዳጅ፣ አሳቢ አባት ያለው ግንዛቤ
- ሰውዬው ስለ ድነት እውነተኛ ትርጉም እና ተፈጥሮ ያለው ግንዛቤ
- የሰውዬው ከክርስቶስ ጋር ቀጣይነት ያለው ጉዞ
- ከእስራት መዳን እና የውስጥ ፈውስ አስፈላጊነት
- ክርስቲያናዊ እሴቶችን ከዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ማስታረቅ።

በአፍሪካ አውድ ውስጥ፣ አማካሪው የቀድሞ እስላማዊ ወይም የባዕድ አምልኮ ልምዶችን ከክርስቲያናዊ የሕይወት ጉዞ ጋር ለማዋሃድ የሚያደርገውን ሙከራ መቃወም ያስፈልገዋል። እነዚህ ልማዶች ከክፉ ኃይሎች እና እርግማኖች ጥበቃን ለማግኘት ድግምቶችን ወይም ክታቦችን መጠቀምን ሊያካትቱ ይችላሉ።

## ጋብቻ እና የቤተሰብ ምክር

ጋብቻ እና የቤተሰብ ምክር ክርስቲያናዊ እሴቶችን እና በአባላት እና ቤተሰቦች ውስጥ ቅዱስ ኑሮን ለማበረታታት ያለመ ነው። የዚህ አይነት ምክር የግለሰብ ወይም የቡድን ሴሚናሮችን ማዘጋጀት ሊጠይቅ ይችላል። የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ለመጋባት ለሚያስቡ ጥንዶች ከጋብቻ በፊት ምክር መስጠት
- ለባለትዳሮች እርስ በርስ ግንኙነታቸውን ማጠናከር ለሚፈልጉ ትዳርን የማበልፀግ ምክር መስጠት
- በትዳራቸው ውስጥ ፈተና ላጋጠማቸው ጥንዶች የጋብቻ ምክር
- ለክርስቲያን ወላጆች ምክር

---

[3] ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ 2ን "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 መገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት፡።

- ከግለሰባዊ ግንኙነቶች ጋር የሚታገሉ የቤተሰብ አባላትን ለመርዳት የቤተሰብ ቡድን ምክር
- እንደ ጋብቻ፣ ልጅ መውለድ፣ ሞት እና የቀብር ሥነ ሥርዓቶች ያሉ የቤተሰብ ሥርዓቶችን በተመለከተ የሚሰጥ ምክር።

## የድጋፍ እና የቀውስ ጊዜ ምክር

የድጋፍ እና የቀውስ ምክር ሰዎችን በአሰቃቂ የህይወት ክስተቶች ውስጥ ለመርዳት ያለመ ነው። እነዚህ ክስተቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ወደ ሞት የሚወስድ ህመም ወይም የሚወዱት ሰው በሞት ማጣት
- ድርቅ፣ ረሃብ፣ ወረርሽኞች እና የተፈጥሮ አደጋዎች
- የወንጀል ወይም የጥቃት ሰለባ መሆን
- ሥራ አጥነት እና ድህነት።

በነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት አባላት ህመማቸውን ሲታገሉ የሚያዳምጣቸው ሰው ሊያስፈልጋቸው ይችላል። አንድ መጋቢ ለሕይወት አስጊ የሆኑ ሁኔታዎችን እንደ ራስን ማጥፋት እና ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት ለመቋቋም ካልታጠቀ፣ እርሱ ወይም እርሷ በሽተኛውን ወደ ሙያዊ አማካሪ መላክ አለበት።

## የእድገት ምክር

የዕድገት ምክር ሰዎች በሕይወታቸው እንዲሳካላቸው ለማበረታታት ያለመ ነው። ግቡ ወደፊት የተሻለውን መንገድ እንዲወስኑ መርዳት ነው። መዝሙረ ዳዊት እና ምሳሌ ብዙ የጥበብ እና ምክር ይሰጣሉ (ለምሳሌ መዝ. 32፡8፤ ምሳ. 15፡22)።

# የማማከር መርሆዎች

በዮሐንስ 4 ላይ ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር የተገናኘበትን በጥንቃቄ መመርመር የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሊጠቀምባቸው የሚፈልጋቸውን አራት ጠቃሚ ምክሮችን ያሳያል።

## መተማመን መፍጠር

ኢየሱስ የምክር ሂደቱን የጀመረው በራሱና በሴቲቱ መካከል መተማመን በመፍጠር ነው። ጌታ አልኮነናትም ይልቁንም አክብሮት አሳይቷታል። ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፍቅሩን እና ማቅረብን አሳይቷል። በወቅቱ ከነበረው የባህል እንቅፋት በመውጣት ወደ ከእርሷ ጋር ብቻውን ተቀምጦ ተነጋገረ (ዮሐንስ 4፡ 7-9፣ 17-18)።

## በጥሞና ማዳመጥ

ኢየሱስ ሴትየዋ ስላለችበት ሁኔታ በጥናት ላይ ያሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለማወቅ ስለፈለገ የምትናገረውን በጥሞና አዳምጦ ተገቢውን ምላሽ ሰጠ። ምላሹ ሴቲቱ የነበራትን መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንደተረዳ በግልፅ አሳይቷል። ሴቲቱ እውነትን እንዳትቀበል እና ነፃነት እንዳታገኝ የሚከለክሏትን እነዚያን የእውሮች አስተሳሰቧች ሞግቷቸዋል (ዮሐንስ 4:9-16፣ 21-24)።

## እውነትን በፍቅር መናገር

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ኢየሱስ የደበቀችውን በፍቅር ገልጦ በእውነትን ረቷታል (ዮሐ. 4፡16-18፤ ኤፌ. 4፡15)።

## ዋናው ትኩረት

በሂደቱ ሁሉ፣ ኢየሱስ ሴቲቱ ትክክለኛ የመኖሯን አላማ እንድታውቅ በመርዳት ግቡን መትቷል። በመጨረሻም ሴቲቱ ኃጢአቷን አምና እርሱን መሲሕ መሆኑን አወቀች። ከዚያም ስለ እርሱ ለሌሎች ለመንገር ሮጠች (ዮሐንስ 4፡28-29)።

# የምክር ሥነ ምግባር

እንደ ክርስቶስ ተወካዮች እና እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ ባለ አደራዎች፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ታማኝነት ያላቸው ወንዶች እና ሴቶች መሆን አለባቸው። በምክር ውስጥ የሚከተሉትን የስነምግባር ጉዳዮች ግምት ውስጥ ማስገባት አለብህ። እነዚህን መርሆዎች ማክበር አንተንም ሆነ አገልግሎት ፈላጊውን ይጠብቃል፡-

## ውስንነትን መረዳት

በምክር ውስጥ ስለ ችሎታዎችህ እና ውስንነትን ሐቀኛ መሆን አለብህ እና ከእነዚህ ውስንነቶች በላይ ለመሄድ መሞከር የለብህም። በተወሰኑ አገሮች ሙያዊ አማካሪዎች ሰርተፊኬት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

## በማጣቀስ ላይ

ከአቅምህ በላይ የሆነን ነገር ማወቅ አለብህ። በተለያዩ አካባቢዎች ምክር ለመስጠት የሰለጠኑ ወይም ብቁ ካልሆንክ፣ አገልግሎት ፈላጊውን ወደተመሰከረላቸው ክርስቲያን አማካሪዎች ለማመልከት ዝግጁ መሆን አለብህ። እንዲሁም በአንተ እና በአገልግሎት ፈላጊውን መካከል አላስፈላጊ የጥገኝነት ግንኙነት ሲፈጠር ወይም አገልግሎት ፈላጊውን በምክሩ የማያስፈልገው ደረጃ ሲደርስ ለማሰናበት ወይም ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ ለመላክ ዝግጁ መሆን አለብህ።

## የጾታ ግንኙነት ጥንቃቄ

መጋቢ እንደመሆንህ መጠን ከተቃራኒ ጾታ ጋር ስትመክር ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ። በአንተ እና አገልግሎት ፈላጊው መካከል ስሜታዊ መስህብ መፈጠር ከጀመረ፣ የምክር ክፍለ ጊዜው አብቅቶ ወደ ሌላ አማካሪ መላክ ይኖርብሃል።

## ሚስጥር ጠባቂነት

አገልግሎት ፈላጊው ያጋራሁን መረጃ ማክበር እና ከሌሎች ጋር ፈጽሞ መወያየት የለብህም።

---

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለእግዚአብሔር ህዝብ አማካሪ በመሆን ከማገልገል ሀላፊነትህ በፍፁም መራቅ የለብህም። ይልቁንም፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ምሳሌህ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ረዳትነት በመያዝ፣ ይህን አስፈላጊ አገልግሎት በጉጉት መፈጸም አለብህ።

# ~ ምዕራፍ 27 ~

# መንጋውን መጠበቅ

በታሪክ ውስጥ ክፉ መሪዎች በሰው ልጆች ላይ ተነግሮ የማያልቅ ወንጀሎችን ፈጽመዋል። ከእነዚህ ወንጀሎች መካከል ጅምላ ፍጅት፣ የዘር ማጽዳት እና ኢፍትሃዊ ጦርነቶች ይገኙበታል። አንዳንዶች እነዚህን የጭካኔ ድርጊቶች በቀጥተኝነት መፈጸማቸው ጥፋተኛ ሲሆኑ ፤ ሌሎች ክፉዎችን ለማቆም ምንም ነገር ባለማድረጋቸው ጥፋተኛ ናቸው። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ አፍሪካም የዚህ አይነት የግፍ ታሪክ የራሷን ድርሻ አላት። ዓለም አቀፋዊ የመልካም አስተዳደር መርህ እያንዳንዱ መንግስት ህዝቡን ከክፉ አድራጊዎች የመጠበቅ ሃላፊነት መሸከም ነው። ለቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔርን ሕዝህ ከዲያብሎስና ከአጋንንት ጭፍሮች ጥቃት የመጠበቅ ኃላፊነት አለብን።

ኢየሱስ "በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት የሚያሸምቁ" ስላላቸው ስለ ሐሰተኛ ነቢያት አስጠንቅቋል። "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" (ማቴ.7፡15-16) ሲል መክሯል። ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎችም ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል። እንዲህም አላቸው፡- "እኔ ከሄድሁ በኋላ፣ ነጣቂ ተኵላዎች መጥተው በመካከላችሁ ሰርገው እንደሚገቡና ለመንጋውም እንደማይራሩ ዐውቃለሁ። 30ከእናንተው መካከል እንኳ የራሳቸውን ደቀ መዛሙርት ለማፍራት እውነትን የሚያጣምሙ ይነሣሉ። 31ስለዚህ ተጠንቀቁ" ((የሐዋርያት ሥራ 20:29-31)።

ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔርን መንጋ ከእነዚህ የሰይጣን ወኪሎች ስላለው የመጠበቅ ኃላፊነት ያብራራል። "መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መንጋውን የመጠበቅ ኃላፊነት ስላለው ምን ይላል?" እና "እርሱ ወይም እርሷ ይህን ሃላፊነት ለመወጣት እንዴት ይጓዛሉ?" ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡

# የመንጋው ተፈጥሮ እና ዋጋ

መጽሐፍ ቅዱስ በመጋቢ እና በአማኞች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ የእረኛ እና የበግ ምስል ይጠቀማል። የጴንጤቆስጤ መጋቢ ለጉባኤው ያለውን ሃላፊነት የበለጠ ለመረዳት የበጎቹን ምንነት እና ዋጋ መረዳት ያስፈልገዋል።

## የበጎች ተፈጥሮ

አንድ መጋቢ በአንድ ወቅት "ይህን ህዝብ መምራት የድመትን መንጋ እንደ መምራት ነው!" በማለት በምሬት ተናግሯል። ድመቶችን መምራት የማይቻል ነው። ግትር ናቸው። ወደሚፈለገው አቅጣጫ ለመሄድ ፈቃደኛ አይደሉም። በጎችም ግን እንዲህ አይደሉም። በጎች ታዛዥ ናቸው። እረኛው በሚመራበት ቦታ ሁሉ ለመከተል ዝግጁ ናቸው። ይሄ ጥሩ ሆኖ ሳለ ይህ ባህርይ ለበጎቹ አደገኛ ነው። አንዳንድ ጊዜ በሞኝነት የተሳሳተ ሰው ይከተላሉ። ስለዚህ እንክብካቤ እና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል።

እውነተኛ ክርስቲያኖች ራሳቸውን በፈቃደኝነት ለመልካሙ እረኛ ያገዙ ናቸው። እርሱ በሚመራበት ቦታ ሁሉ ለመከተል ዝግጁ ናቸው (ዮሐንስ 10፡27)። ሆኖም፣ አንዳንድ ክርስቲያኖች ያልበሰሉ ናቸው፣ እና እንደ በጎች አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ተኩላዎችን ከእውነተኛ እረኞች ጋር ይምታታባቸዋል። እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ያይደሉትን በጭፍን ይከተላሉ።

በተጨማሪም በጎች ተፈጥሯዊ መከላከያ የላቸውም። በዚህ ምክንያት ለጥቃት የተጋለጡ ናቸው። ስለሆነም የሚጠብቃቸው እረኛ ያስፈልጋቸዋል። ከመንጋው እና ከእረኛው እንክብካቤ ይርቃሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ለአዳኞች ቀላል አደን ይሆናሉ። የብዙ ክርስቲያኖችም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። ከፓስተራቸው እንክብካቤ እና ከቤተክርስቲያኑ ደኅንነት ይርቃሉ። በመሆኑም የእውነተኛ እረኛ እንክብካቤ እና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል።

## የበጎች ዋጋ

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን፣ በጎች ለእረኛው ትልቅ ዋጋ ይሰጡ ነበር። ብዙውን ጊዜ የቤተሰቡ ዋነኛ መተዳደሪያ ምንጭ ነበሩ። በጎች ሥጋቸው ለምግብ፣ ወተታቸው ለመጠጥ ፣ ሱፋቸው ለልብስ፣ ቆዳቸው ለመጠለያና ለሌሎች ዓላማዎች ይውላሉ። ክርስቲያኖች ለመልካሙ እረኛ የበለጠ ዋጋ አላቸው። ይህ ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች እውነት ነው፡-

በመጀመሪያ፣ ክርስቲያኖች ለቤዛነታቸው ከከፈለው ከፍተኛ ዋጋ የተነሳ ለክርስቶስ ዋጋ አላቸው። ኢየሱስ ስለ ራሱ እንዲህ አለ፡- "መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል" (ዮሐ. 10፡11)። ጴጥሮስ ለክርስቶስ ያለንን ዋጋ ያስታውሰናል፡- "የተዋጃችሁት በሚጠፉ ነገር፣ በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፤" (1ጴጥ. 1፡18-19)።

በተጨማሪም ክርስቲያኖች ከእርሱ ጋር ባላቸው ልዩ ግንኙነት ምክንያት ለክርስቶስ ዋጋ አላቸው። ጳውሎስ "በዚያን ዘመን ከክርስቶስ ተለይታችሁ፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቃችሁ፣ ለኪዳኑም ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ፣ በዓለም ላይ ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር እንደ ነበራችሁ አስታውሱ አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባችኋል" ይላል (ኤፌ. 2፡12-13)። ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ሕዝብ "የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ" ሲል ያሳስበናል (1 ጴጥ. 2፡9)። እንደ እግዚአብሔር የተመረጠ መንጋ ሕዝቡ ልዩ እንክብካቤ ይገባዋል።

# የመንጋው ስጋቶች

እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ህዝቦቻችሁን ከሐሰተኛ ነቢያትና ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ለመጠበቅ ምንጊዜም ንቁ መሆን አለብህ።

## ሐሰተኛ ነቢያትን እና ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ማወቅ

ሐሰተኛ ነቢይ ማለት ለእግዚአብሔር እናገራለሁ የሚል ነገር ግን በእውነቱ ከሆነ እርሱ ወይም እርሷ በራሳቸው ስም ወይም በሐሰት ወይም በአጋንንት መንፈስ የሚናገሩ ናቸው (ኤር. 23፡16)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደነዚህ ባሉት ሐሰተኛ ነቢያት ላይ እንደሚነሳ ያስጠነቅቃል። በሕዝብም መካከል እንዲኖሩ አይፈቀድላቸውም (ሕዝ. 13: 9)። ኢየሱስ ሐሰተኛ ነቢያት አንዳንድ ጊዜ "ታላላቅ ምልክትና ተአምራት እንደሚያደርጉ" እና "ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እንደሚያስቱ" ምልክት እንደሚያደርጉ አስጠንቅቋል (ማቴ. 24፡24)። ጳውሎስ "ደቀ መዛሙርትን ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ እውነትን የሚያጣምሙ ጨካኞች ተኩላዎች" ብሏቸዋል (ሐዋ. 20፡29-30)። ተረት እንደሚያስተምሩና ሰዎች መስማት የሚፈልጉትን እንደሚናገሩም ጽፏል (2ጢሞ. 4፡3-4)።

የሐሰት አስተማሪዎች ከሐሰተኛ ነቢያት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ሐሰተኛ ነቢይ ለእግዚአብሔር እናገራለሁ ብሎ ሲያስት፣ ሐሰተኛ አስተማሪ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ከትክክለኛ ትርጉም ውጭ ለመናገር እንደወደደ ያጣምማል። ብዙ ጊዜ ይህንን የሚያደርገው ደግሞ ለግል ጥቅሙ ነው (ቲቶ 1፡11)። መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ሰዎች አላዋቂዎች እና የማይረጋጉ ናቸው እናም ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ጥፋታቸው እንደሚያጣምሙ ይናገራል (2ጴጥ. 3፡16)።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐሰተኛ ነቢያትንና ሐሰተኛ አስተማሪዎችን የምንለይባቸው ሁለት መንገዶች አሉ።

**1. ሕይወታቸውን በመመልከት።** ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን " "በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ። 16ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" (ማቴ. 7፡15-16)። ሐሰተኞች ያልሆኑትን ያስመስላሉ። እንደ ቅዱሳን ይለብሳሉ እና ይመራሉ ፤ ሃይማኖታዊ ቃላት ይጠቀማሉ፣ እና አስደናቂ ጸሎቶችን ይጸልያሉ። አንዳንዶች ድንቅ ተአምራትን ሊያደርጉ ይችላሉ። በውጫዊ መልኩ፣ የተቀደሱ እና የተቀቡ ይመስላሉ። ነገር ግን በውስጣቸው ቀማኞች፣ ውሸታሞች እና አመንዝሮች ናቸው። የግል ሕይወታቸው ፍሬ ግብዝነታቸውን ያሳያል። ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው ሕይወት የሚኖር ወንድ ወይም ሴት እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ አይደለም።

ኢየሱስ በዘመኑ የነበሩትን የሐሰት አስተማሪዎች ""እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ውጫቸው በኖራ ተለስነው የሚያምሩ፣ ውስጣቸው ግን በሙታን ዐፅምና በብዙ ርኵሰት የተሞላ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ! 28እናንተም በውጭ ለሰዎች ጻድቃን ትመስላላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በግብዝነትና በክፋት የተሞላ ነው" (ማቴ. 23፡27-28) ብሎቸዋል። እነዚህ ዓመፀኛ ወንዶች እና ሴቶች እራሳቸውን ለእግዚአብሔር እና ለቤተ ክርስቲያን ስልጣን ለማስገዛት ፈቃደኞች አይደሉም።

**2. ዓላማቸውን እና ዘዴዎቻቸውን መጥቀስ።** በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሐሰተኛ ነቢያትንና ሐሰተኛ አስተማሪዎችን የምንለይበት ሁለተኛው መንገድ መነሳሳታቸውን እና አሠራራቸውን በመመልከት ነው። የሐሰተኛው ነቢይ ዋነኛ ዓላማ የራሱን ወይም የራሷን የራስ ወዳድነት ፍላጎት ማሳካት ነው። ይህንን

ለማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል ያዛባሉ። ብዙውን ጊዜ ጽሑፎችን ከዐውደ-ምንባብ ያወጡታል። ከራሳቸው አጀንዳ ጋር እንዲስማሙ ይተረጉሟቸዋል። ዓላማቸው ደቀ መዛሙርትን ወደ እነርሱ መሳብ ነው" (የሐዋርያት ሥራ 20፡30)። ስለ ተከታዮቻቸው መዳን ወይም በክርስቶስ ማደግ ብዙም አይጨነቁም። ለግል ጥቅማቸው እና ክብራቸው ግን የበለጠ ያሳስባቸዋል።

## የሐሰት ትምህርቶች በአፍሪካ

በሚያሳዝን ሁኔታ፣ በአፍሪካ በሚገኙ በብዙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፣ የሐሰት ትምህርቶች እና የሐሰት ትንቢቶች የተለመዱ እየሆነ ነው። እነዚህ ትምህርቶች እምነት እና ከኃጢአት ንስሐ የመግባትን አስፈላጊነት ችላ በማለት ምድራዊ በረከትን እንደሚሰጡ  ቃል ይገባሉ። በአብዛኛው በሰዎች ጊዜያዊ ፍላጎቶች ላይ በማተኮር መንፈሳዊ እድገታቸውን እና ክርስቶስን የመምሰልን እድገት ችላ ይላሉ። ይህን ሲያደርጉ የጠፉትን ወደ ክርስቶስ አያመጡም እና ቅዱሳንን ለዘለአለም  ሕይወት አያዘጋጁም (ማር. 8፡36)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ካሉ ትምህርቶች እንድንርቅ አጥብቆ ያስጠነቅቃል (1 ጢሞ. 4፡1)።

በተለይ በአፍሪካ ውስጥ ሁለት የሐሰት ትምህርቶች ተስፋፍተዋል፡-

1. **የብልጽግና ወንጌል።** የመጀመሪያው ኑፋቄ "የብልጽግና ወንጌል" ተብሎ የሚጠራው ነው። የብልጽግና ወንጌል ሁሉም አማኞች ለጤና፣ ለሀብት እና ብልጽግና በረከቶች የቃል ኪዳን መብት እንዳላቸው የሚያስተምር ትምህርት ነው። ኑፋቄ መምህራኑ እነዚህን በረከቶች በእምነት፣ በአዎንታዊ ኑዛዜ እና "የእምነትን ዘር" በመዝራት ማግኘት ይቻላል ይላሉ።

እግዚአብሔር በታማኝነት የሚከተሉትን እንደሚባርክ እውነት ቢሆንም፣ የብልጽግና ወንጌል የሚባለው ኢየሱስና ሐዋርያት የሰበኩት ወንጌል አይደለም። ኢየሱስ ሕዝቡን "ንስሐ ግቡ ምሥራቹን እመኑ" ሲል አዘዛቸው። ((የማርቆስ ወንጌል 1:15) ጴጥሮስ "ከጌታም የመጽናናት ጊዜ እንዲመጣላችሁ ንስሐ ግቡ… ኃጢአታችሁም ይደመሰስ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ" (ሐዋ. 3፡19) በማለት ተናግሯል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል አስጠንቅቋል፣ " እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን አለማወቅ በትዕግሥት ዐልፎአል፤ አሁን ግን በየቦታው ያሉ ሰዎች ሁሉ ንስሓ እንዲገቡ ያዛል፤" (ሐዋ. 17፡30)።

እውነተኛዋ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን የብልጽግናን ወንጌል መቃወም አለባት ምክንያቱም ክርስቶስን ያላማከለ በተቃራኒው ራስ ወዳድ ትምህርት ስለሆነ ነው። በእግዚአብሔር የማዳን ተልዕኮ ላይ ሳይሆን በሰዎች ቁሳዊ ፍላጎት ላይ የሚያተኩር ኑፋቄ ነው። የብልጽግና ወንጌል አጽንዖት ከአገልግሎት ይልቅ በረከት ላይ ነው። ኑፋቄው በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ ጉዳት እያደረሰ ያለ የተዛባ ወንጌል ነው። ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች የሰጠው ማስጠንቀቂያ ትክክል ነው:- " በክርስቶስ ጸጋ የጠራችሁን እርሱን ትታችሁ፣ ወደ ተለየ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ መዞራችሁ ደንቆኛል፤ 7እንደ እውነቱ ከሆነ ሌላ ወንጌል የለም። የሚያደነጋግሯችሁና የክርስቶስን ወንጌል ለማጣመም ጥረት የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። 8ነገር ግን እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን" ((ገላ. 1፡6-8)።

2. **ቀያጭነት**። በአፍሪካ ውስጥ በጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያለው ሌላው አጥፊ ተግባር ቀያጭነት ነው። ቀያጭነት የክርስትና እምነት ከአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖቶች አካላት ጋር መቀላቀል ነው። ሐሰተኛ ነቢያት እና ሐሰተኛ አስተማሪዎች ብዙ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያናቸው ለመሳብ ሲሉ አንዳንድ ጊዜ ይህንን ዘዴ ይጠቀማሉ። በአፍሪካ ውስጥ ብዙ የቀያጭነት ምሳሌዎች ይገኛሉ። በምዕራብ አፍሪካ፣ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

- የነቢዩ መባ
- የቤዛነት መስዋዕት
- የመሥዋዕት መባ
- የተቀባ ዘይት መሸጥ እና ዘይትን ቅዱስ ጽሑፋዊ ባልሆነ መንገድ መጠቀም
- የተቀደሰ ውሃ መሸጥ እና መጠቀም
- ማርና ወተት መሸጥና መጠቀም
- "የእግዚአብሔር ሰው" ምስሎችን መሸጥ
- የቅዱስ መጥረጊያ የሚሉትን መጠቀም(ጠላቶችን ለማጥፋት)
- ከሙት ባሕር የሚገኘውን ጭቃ መጠቀም
- ከዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ አምጥቶ መጠቀም
- የተከፈለ ትንቢታዊ አገልግሎ (የገስት ሃውስ አገልግሎት)።

እነዚህ ልማዶች ባህላዊ ሃይማኖታዊ ልማዶችን "ክርስቲያን" ለማድረግ የሚደረጉ ሙከራ ናቸው። የሚሸከረከሩት በገንዘብ እና ለሚቀበሏቸው የበረከት እና የጥበቃ ተስፋ በመስጠት ነው። "እውነተኛውን የወንጌልን መልእክት" (ቆላ. 1፡5-6) በመደገፍ ውድቅ ሊደረጉና ሊወገዙ ይገባል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የምታገለግሏቸውን ሰዎች ዘላለማዊ እጣ ፈንታ በእጃችህ እንደያዝክ መርሳት የለብህም። ስለዚህ፣ የምታደርገውን በጥንቃቄ መመርመር እና ማስተማር አለብህ። እውነትን ማስተማር ተስኖህ ለሐሰት ትምህርት እጅ ከሰጠህ ሕዝቡ ወደ መረን ይወጣል፣ ቤተ ክርስቲያን ይጎዳል፣ በእግዚአብሔር ፊት ይፈረድብሃል።

## የሐሰት ትምህርቶች እና ትንቢቶች ውጤቶች

የሐሰት ትምህርት ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዱበት አምስት መንገዶች።

**1. የሐሰት ትምህርት እግዚአብሔርን አለመፍራትን ያበረታታል።** እውነት ክርስቲያኖችን ትቀድሳለች እና እግዚአብሔርን ለመምሰል ታነሳሳለች (ዮሐንስ 17፡17)። በሌላ በኩል፣ የሐሰት ትምህርቶች አእምሮንና ልብን ያበላሻሉ፣ ሥነ ምግባር ጥሰትን ያበረታታሉ (1ቆሮ. 15፡33)።

**2. የሐሰት ትምህርት እግዚአብሔርን የማይፈሩ *መሪዎችን ያፈራል።*** እውነት አገልጋይ መሪዎችን ታፈራለች ፤ ይሁን እንጂ የሐሰት ትምህርት እግዚአብሔርን የማይፈሩ፣ አምባገነን መሪዎችን ያፈራል። እውነተኛው የክርስቲያን መሪ "ሌሎችን ትክክል በሆነው ትምህርት እንዲያበረታታና ይህንኑ ትምህርት የሚቃወሙትን ይወቅስ ዘንድ እንደ ተማረው በታመነ ቃል የሚጸና መሆን አለበት" (ቲቶ 1፡9)።

**3. የውሸት ትምህርት ሰዎችን ባሪያ ያደርጋል።** እውነት ሰዎችን ነጻ ያወጣል (ዮሐንስ 8፡32)። ኑፋቄ መምህራን ግን ሰዎችን ባሪያ ያደርጋሉ (ገላ. 4፡9)። ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንዲህ ሲል አሳስቧቸዋል፣ "ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድንኖር ነው። ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ ዳግመኛም በባርነት ቀንበር አትጠመዱ" (ገላ. 5፡1)

**4. የውሸት ትምህርት ደካማ ክርስቲያኖችን ያፈራል።** የሐሰት ትምህርትና ኑፋቄ የተማሩ ክርስቲያኖች በጸጋ አያድጉም። መንፈሳዊ ሕጻናት ሆነው ይቆያሉ። ሕብረታቸው በቁጥር ቢያድግ እንኳን ደካማ እና ውጤታማ ሳይሆን ይቀራል።

**5. የውሸት ትምህርት ወደ ፍርድና ወደ ጥፋት ይመራል።** መጽሐፍ ቅዱስ ስለ "ዕውቀት የጐደላቸውና ጽናት የሌላቸው ሰዎች ሌሎችን ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ፣ እነዚህንም ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ" (2ጴጥ. 3፡16) ይናገራል።

# መንጋውን መጠበቅ

የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ እንደመሆንህ መጠን በጎቹን ሁል ጊዜ መጠበቅ አለብህ። ነፍስህንም ስለ እነርሱ አሳልፈህ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለብህ (ዮሐንስ 10፡11፤ 1 ሳሙ. 17፡34-35)። እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለእግዚአብሔር ህዝብ ዘብ ለመቆም የሚከተሉትን አምስት መንገዶች መከተል ትችላለህ፡-

## ለበጎቹ በመጸለይ

መጀመሪያ ብዙ ጊዜ ጉባኤው ይዘህ በአብ ፊት ተንበርከክ። ይህን በማድረግ መንጋውን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ የሚያስፈልግህን ጥንካሬ እና ጥበብ ከእርሱ ታገኛለህ። በተጨማሪም፣ ጸሎትህን የእግዚአብሔር ጥበቃ እጅ በሕዝቡ ላይ እንዲሆን ያደርጋል።

## መንፈሳዊ ማስተዋልን በማሳየት

ሁለተኛ፣ መንፈሳዊ ማስተዋልን መጠቀም አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ "አታላይ መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት እንደሚከተሉት ያስጠነቅቃል (1 ጢሞ. 4፡1)። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ያልሆነን ማንኛውንም ትምህርት ወይም መንፈሳዊ መገለጥ ለማወቅ እንዲረዳህ መናፍስትን የመለየት ስጦታ እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን ጠይቅ። ይህ መንፈሳዊ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ወይም በአጋንንት መንፈስ እየተመራ መሆኑን እንድታውቅ ያስችልሃል።[1]

## እውነተኛ ዶክትሪን በማስተማር

ሦስተኛ፣ ትክክለኛ ትምህርትን በታማኝነት መስበክና ማስተማር አለብህ (2ጢሞ. 4፡2፤ ቲቶ 1፡9)። ይህ ልማድ በጎቹን ያጠናክራል እንዲሁም ከሐሰት ትምህርቶች ይፈውሳቸዋል። በንጽሕና መንገድ ላይ እንዲቆዩ ይረዳቸዋል (መዝ. 119፡9-11)።

ሐሰተኛ ነቢያትንና ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በመለየት

አራተኛ፣ ቤተ ክርስቲያንን ከሐሰተኛ ነቢያትና ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ማስጠንቀቅ አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችን ለመለየት ሦስት መንገዶችን ይናገራል፡-

**1. ትንቢታቸው አይፈጸምም።** ትንቢታቸው ካልተፈጸመ ከእግዚአብሔር ዘንድ አልሰሙም። ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው (ኤር. 28፡9)።

**2. ሰዎችን ከእውነት ያርቃሉ።** ትንቢታቸው ተፈጽሞ ሰዎችን ከእውነተኛው የወንጌል መልእክት ቢያርቁ ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው (ዘዳ. 13፡1-3፤ ገላ. 1፡6-9)።

---

[1] ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ 2ን "የ1 ቆሮንቶስ 12፡8-10 መገለጥ ስጦታዎች" የሚለውን ተመልከት።

**3. ያልተቀደሰ ሕይወት ይኖራሉ።** ትንቢታቸው ተፈጽሞ ድንቅ ምልክትም ቢያደርጉ በኃጢአተኛ ሕይወት ዘይቤ ቢኖሩ ሐሰተኞች ነቢያት ናቸው (2ጴጥ. 2፡10-15)። ኢየሱስ፣ “ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ” በማለት አስጠንቅቋል (ማቴ. 7፡15-16፤ ቁ. 22-23)።

እንደ ታማኝ እረኛ በጎቹን ከአዳኞች መጠበቅ አለብህ፣ እና ጌታ ከአንተ ጋር እንደሚያደርግ፣ አንተም በቀና መንገድ ልትመራቸው ይገባሀል (መዝ. 23፡3)።

## የሐሰት ትምህርቶችን በማጋለጥ

በመጨረሻም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የሐሰት ትምህርቶችንና የሐሰት ትንቢቶችን በመለየት እና በማረም የእግዚአብሔርን መንጋ መጠበቅ አለብህ። ጳውሎስ “ትንቢቶችን አትናቁ” ሲል ጽፏል። ይሁን እንጂ አክሎም “ነገር ግን ሁሉንም ፈትኑ ፤ መልካም የሆነውን ያዙ፤ ከማናቸውም ዐይነት ክፉ ነገር ራቁ” (1ኛ ተሰ. 5፡20-22)። ስለዚህ፣ የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ እንደመሆንህ መጠን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት ማወቅ ይኖርብሃል።

ይህን ማድረግ የምትችልባቸው ሦስት መንገዶች አሉ፡-

**1. የሚማሩትን በመከታተል።** የሐሰት ትምህርቶች በትናንሽ ቡድኖች ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ ይችላሉ። የቡድን መሪው የሰማውን ወይም ያነበበውን ነገር ማስተማር ይጀምራል። ይሄን ተከትሎ ኑፋቄው በአጭር ጊዜ ውስጥ በመላው ቤተ ክርስቲያን ሊስፋፋ ይችላል። ስለዚህ ጉባኤው እውነት እየተማረ መሆኑን ለማረጋገጥ በሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ በደህንነት እና በደቀ መዝሙር ትምህርት ክፍሎች፣ በቤት ሕብረቶች፣ እና በሌሎች ቡድኖች የሚሰጠውን ትምህርት በቅርበት መከታተል አለብህ።

**2. ሰዎች የሚያዳምጡትን በማወቅ**። ዛሬ በቴክኖሎጂ አማካኝነት ሁሉም ዓይነት ትምህርት እና ስብከት ተጥለቅልቀዋል። ህዝባችን እነዚህን የኑፋቄ መምህራን እያዳመጠ ነው። ብዙ የሚዲያ ሰባኪዎች ምሥራቹን በታማኝነት ሲያሰራጩ አንዳንዶች ስህተትን እያስተማሩ ነው። ወደ ቃሉ እውነት እንድትጠቁማቸው ሕዝቡ የሚሰሙትን ነገር ማወቅ አለብህ።

**3. “የበሩ ጠባቂ” በመሆን።** መጋቢ እንደመሆንህ መጠን የቤተ ክርስቲያን በር ጠባቂ ሆነህ መቆም አለብህ። በሌላ አነጋገር፣ ማን ለጉባኤው እንዲናገር እንደምትፈቅድ በጥንቃቄ መከታተል አለብህ። ሰባኪ የቱንም ያህል ዝነኛ ወይም ካሪዝማቲክ ቢሆን፣ እርሱ ወይም እርሷ ሥነ ምግባር ከሌለው፣ ወይም ከእውነት የራቀ ከሆነ፣ በመድረክህ ላይ እንዲወጡ አትፍቀድላቸው።

---

የእግዚአብሔርን መንጋ በታማኝነት የሚጠብቅ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለራሱ በረከትን ያመጣል። በጎቹ በእረኛቸው ጥበቃ ሥር ይለመልማሉ፣ እናም የጎለመሱ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ይሆናሉ። እረኛውም ይባረካል። እርሱ ወይም እርሷ ጥሩ እና ታማኝ አገልጋዮች በመሆን ይሸለማሉ።

ጴጥሮስ ስለ ታማኝ እረኛ ሽልማት ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- “ በእናንተ ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብሔር እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን፤ 3እንዲሁም በዐደራ ለተሰጣችሁ መንጋ መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በላያቸው በመሠልጠን አይሁን። 4የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን አክሊል ትቀበላላችሁ” (1ጴጥ. 5፡2-4)።

~ ክፍል 7 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ መሪ

# ~ ምዕራፍ 28 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ አመራር

ጳውሎስና የሚስዮናውያን ቡድኑ ከገላትያ ተነስተው ወደ ምዕራብ ወደ እስያ ግዛት አመሩ። ነገር ግን፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በዚያ አቅጣጫ እንዳይቀጥሉ ከለከላቸው። ስለዚህ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ወደ ቢታንያ ግዛት ለመጓዝ ወሰኑ። ዳግመኛም መንፈስ ከለከላቸው። እናም እንደገና ወደ ምዕራብ ዞሩ። በመጨረሻም በኤጂያን ባሕር በስተሰሜን ምዕራብ ዳርቻ ላይ ወደምትገኘው ጥሮአስ የተባለች ከተማ ደረሱ። እዚያም አንድ ያልተለመደ ነገር ተከሰተ።

በሌሊትም መንፈስ ቅዱስ ለጳውሎስ ራእይ ሰጠው። ሐዋርያው በራዕዩ አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ "ወደ መቄዶንያ ተሻግረህ እርዳን" እያለ ሲለምነው አየ (ሐዋ. 16፡6)። ጳውሎስ ራእዩን ለወዳጆቹ ሲያካፍል፣ ሁሉም ከጌታ እንደሆነ ተስማሙ። ሉቃስ እንዲህ ሲል ገልጿል፦ "ጳውሎስ ይህን ራእይ ካየ በኋላ፣ እግዚአብሔር ወንጌልን እንድንሰብክላቸው ጠርቶናል ብለን በመወሰን ወዲያው ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ፈለግን" (ቁ. 10)። (የጳውሎስ በመንፈስ መመራት ሌሎች ምሳሌዎች በሐዋርያት ሥራ 13፡1-5፤ 15፡28 እና 20፡22 ውስጥ ይገኛሉ።)

ጳውሎስ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ጥሩ ምሳሌ ነው። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራው በመፍቀድ ሌሎችን መራ። ይህንንም ሲያደርግ እርሱ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ቅባትና መሪነት ያገለገለውን የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል ነበር (ሉቃስ 4፡1፤ ዮሐንስ 5፡19፤ የሐዋርያት ሥራ 10፡38)።

ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ አመራርን ያብራራል። በኢየሱስ እና በሐዋርያት ዘዴዎች ላይ የተመሰረተ የአመራር ሞዴል ያቀርባል። በመጀመሪያ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ይገልጻል። ከዚያም፣ ስለ ትክክለኛ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ አንዳንድ ባህሪያት እና ተግባራት ያብራራል።

# የጴንጤቆስጤያዊ አመራርን መግለጽ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የሆኑም ያልሆኑም ብዙ የአመራር ዘዴዎችን በጋራ እንደሚጠቀሙ እውነት ቢሆንም፣ አንዳንድ አስፈላጊ ልዩነቶች ግን አሉ። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የአመራር አቀራረብ ጉልህ በሆነ መልኩ የተቀረፀው በመንፈስ ባለው ልምድ ነው። መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው እና በሌሎች ህይወት ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ያላቸው ልዩ ግንዛቤ የአመራር ልምምዳቸው ላይ በጥልቅ ተጽኖ ያሳድርበታል።

የጴንጤቆስጤያዊ መሪ በእግዚአብሔር የተጠራ ወንድ ወይም ሴት ሲሆን በመንፈስ የተሞላ እና የመንፈስ ቅዱስን ጥበብ እና ምሪት የሚፈልግ ነው። የእርሱ ወይም የእርሷ አላማ በሥራቸው ያሉትን የእግዚአብሔር ሕዝብ በታማኝነት እና በብቃት ተልእኳቸውን በምድር ላይ በማራመድ ረገድ ያለውን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሚና እንዲወጡ ተጽዕኖ ማሳደር ነው። ይህንን ፍቺ ወደ አራት ክፍሎች እንከፋፍለን።

### በእግዚአብሔር የተጠራ

በመጀመሪያ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ህዝቡን እንዲመራ በእግዚአብሔር ተጠርቷል። በዚህ ምክንያት፣ እርሱ ወይም እርሷ እራሱን “የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ፣ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራና ለእግዚአብሔር ወንጌል የተለየ” ብሎ ከገለጸው ከጳውሎስ ጋር በቅርበት ይመሳሰላል።

### በመንፈስ የተሞላ

በመቀጠል፣ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ በመንፈስ የተመላ ነው እናም ህይወቱን “ከመንፈስ ጋር በመነዝ” ለመኖር ይፈልጋል (ገላ. 5፡25)። " ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ" (ሉቃስ 24:49) የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ እና የጳውሎስን "መንፈስ ተሞሉ" (ኤፌ. 5:18) የሚለውን መመሪያ በቁም ነገር ይወስዳል።

### የእግዚአብሔርን መመሪያ ይፈልጋል

ሦስተኛ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ በሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ የመንፈስን መመሪያ በንቃት ይፈልጋል። ዋናው ተግባሩ በቅዱሳት መጻሕፍት እና በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንደሆነ ይገነዘባል። ስለዚህ ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና በጸሎት ብዙ ጊዜ ያሳልፋል።

### በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ ተጽእኖ ያደርጋል

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በምድር ላይ ለማራመድ በእግዚአብሔር የተሾመበትን ሚና በታማኝነት እና በብቃት ለመወጣት የተወሰነ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስብስብ (አንድ ተለየ ሕዝብ ወይም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል) ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ይተጋል።

# የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ባህሪያት

አንድ ወንድ ወይም ሴት የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ለመሆን ብቁ የሚያደርገው ምንድን ነው? በመሰረታዊነት፣ ትክክለኛው የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ዳግም መወለድ፣ በመንፈስ መሞላት እና ሌሎችን ወደ መንፈስ-ወደ ታጠቀ ጉዞ መምራት መቻል አለበት። የመንፈስን ድምጽ ማወቅ እና በመንፈሳዊ

ስጦታዎች አገልግሎት ብቁ መሆን መቻል አለበት። የእግዚአብሔርን ተልእኮ ተረድቶ ቁርጠኛ መሆን አለበት። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመስዋዕትነት ሕይወቱን ለክርስቶስ አሳልፈው ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለበት።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ ህይወትህ እና አገልግሎትህ በስድስት አስፈላጊ ባህሪያት መታወቅ አለበት።

## *ታማኝነት*

ከምንም በላይ፣ ቅዱስ እና ክርስቶስን የሚያከብር ሕይወት ለመኖር መጣር አለብህ። በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ፣ ምንም አስፈላጊ ነገር የለም። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን፣ እጅግ በጣም ብዙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት እና ድርጅቶች በጠንካራ ስብዕናቸው እውቅናን ያተረፉ ግን ሙሰኛ በሆኑ ወንዶች እና ሴቶች ተሞልቷል። እነዚህ "የበግ ለምድ የለበሱ ተኲላዎች" በቤተ ክርስቲያን ላይ እፍረትን እያመጡ ነው (ማቴ. 7፡15)።

መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ ስለሌላቸው ሰዎች ይናገራል። ለምሳሌ፣ ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎች ገብተው የእግዚአብሔርን መንጋ ስለሚያበላሹ "ጨካኞች ተኲላዎች" አስጠንቅቋቸው ነበር። በዚሁ መልእክት ላይ እርሱ ግን እንዴት በታማኝነት እንደመራቸው አስታውሷቸዋል። "የማንንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም" (ሐዋ. 20፡33) ብሏል። በተመሳሳይም ለተሰሎንቄ ሰዎች በመካከላቸው እንዴት እንደተመላለሰ አስታውሷቸዋል፡- "በእናንተ በምታምኑት መካከል ሳለን እንዴት በቅድስና፣ በጽድቅ እንዲሁም ያለ ነቀፋ ሆነን እንደኖርን እናንተም እግዚአብሔርም ምስክሮች ናችሁ" (1ኛ ተሰ. 2፡10)። ጳውሎስ በሥልጣን መምራትና በኃይል ማገልገሉ ብቻ ሳይሆን በታማኝነት ኖሯል። ዛሬም እንዲሁ ማድረግ አለብን።

## *መረዳት*

ሁለተኛ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እግዚአብሔር የሰጠህን ሀላፊነቶች በግልፅ መረዳት አለብህ። የእግዚአብሔርን ህዝብ በመምራት በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ተልእኮውን እንዲያሰፋ ክርስቶስንና ቤተክርስቲያኑን በታማኝነት ማገልገል አለብህ። ይህንን መረዳት ከሁለት ምንጮች ማግኘት ትችላለህ- ከእግዚአብሔር ቃል እና ከእግዚአብሔር መንፈስ። ቅዱሳት መጻሕፍትን በታማኝነት በማጥናት፣ የእግዚአብሔርን አሕዛብን የመቤዠትን ተልእኮ ትረዳለህ። በመጸለይ እና የእግዚአብሔርን ድምጽ በትኩረት በመከታተል፣ ያንን ተልዕኮ ለመፈጸም ያለህን ልዩ ሚና ትገነዘባለህ።

ኢየሱስ በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ውስጥ ያለውን ቦታ በግልፅ ተረድቶ ነበር። ብዙ ጊዜ ስለ ተልእኮው ተናግሯል (ማርቆስ 10፡45፤ ዮሐንስ 6፡38፤ 18፡37)። "የሰው ልጅ የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" በማለት ተናግሯል (ሉቃስ 19፡10)። በተመሳሳይም ጳውሎስ በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ያለውን ልዩ ሚና ተረድቷል። እንዲህ ሲል ጽፏል፣ " እኔም ለዚህ ነገር የምሥራች አብሣሪና ሐዋርያ እንዲሁም ለአሕዛብ የእውነተኛ እምነት አስተማሪ ሆኜ ተሾምሁ" (1 ጢሞ. 2፡7)።

በዕለት ተዕለት ጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማድረግ፣ እንደ ኢየሱስ እና ጳውሎስ፣ የእግዚአብሔርን ተልእኮ መረዳት ያለህን ሚና የበለጠ መፈጸም ትችላለህ።[1]

## ቁርጠኝነት

ሦስተኛ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ የእግዚአብሔርን ተልእኮ መረዳት ብቻ ሳይሆን፣ ተልዕኮውን ለመፈጸም የበኩልህን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ቁርጠኛ መሆን አለብህ። የእግዚአብሔር ተልእኮ፣ አንዳንድ ጊዜ ሚሲዮ ዴኢ ተብሎ የሚጠራው፣ እግዚአብሔር ከወደቀው የሰው ልጅ ጋር በተያያዘ በዓለም ላይ ያለው ዓላማ እና ስራ ነው። በምድር ላይ ካሉ ነገዶች፣ ቋንቋ እና አሕዛብ ሁሉ ሰዎችን ለመጥራት በቤተክርስቲያኑ በኩል ይሰራል (ራዕ. 5፡9፤ 7፡9)።

የሰዎች ሀሳብ ከተልእኮው ሊርቅ ቢችልም፣ ትኩረትህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ላይ መሆን አለበት። ሁሉም ሀሳቦችህ እና ድርጊቶችህ በእግዚአብሔር ተልዕኮ አቅጣጫ መንቀሳቀስ አለባቸው። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ የእግዚአብሔርን ለአሕዛብ ያለውን የማዳን እቅድ፣ ትልቁን ምስል መረዳት አለብህ። ቤተ ክርስትያንህ ለዚያ ታላቅ እቅድ ለማስፈጸም ያላትን ቦታ መረዳት አለብህ። ከዚያም ቤተ ክርስቲያንን ወደዚያ አቅጣጫ ማንቀሳቀስ አለብህ።[2]

## ቅባት

አራተኛ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ የመንፈስን ቅባት ተንከባከብ፣ እናም በቁርጠኝነት፣ በቅዱስ ኑሮ እና ትሁት በሆነ አገልግሎት የመንፈስን መገኘት በህይወትህ ለመጠበቅ መጣር አለብህ። አንተን እንዲቀባህ፣ እንዲያነቃህ እና በአገልግሎት እንዲመራህ በመንፈስ ቅዱስ ላይ በብርቱ መታመን አለብህ። እናም ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሳይቀበሉ አገልግሎታቸውን እንዳይጀምሩ ሲል ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውን ትዕዛዝ በቁም ነገር ልትወስደው ይገባል (ሐዋ. 1፡4-5፤ ሉቃ. 24፡49)።

## ትህትና

አምስተኛ፣ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ እራስህን እንደ እግዚአብሔር እና እንደ ህዝቡ አገልጋይ ማየት አለብህ። ራሱን አዋርዶ በመስቀል ላይ እስከ ሞት ድረስ አገልጋይ የሆነውን የጌታችሁን ምሳሌ ተከተል (ፊልጵ. 2፡7-8)። እንዲሁም " በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ 44 ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤45 የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና" " (ማር.10፡ 43-45)።

ይህ አይነቱ አመራር የሚከተል መሪ አገልጋይ መሪ በመባል ይታወቃል። በተቃራኒው፣ ራሳቸውን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ እና የእግዚአብሔርን ህዝብ ለመበዝበዝ የሚፈልጉ መሪዎች በፍጹም እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ሊባሉ አይችሉም። እነርሱ "የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች" ናቸው (ማቴ. 7፡15-16፤ ሐዋ. 20፡29-30)። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፡- " ከእነዚህ ራቅ" (2ጢሞ. 3፡5)።[3]

---

[1] ስለእግዚአብሔር ተልእኮ ለበለጠ፣የአፍሪካ ተስፋ ግኝቶች ተከታታይ መጽሐፍ፣የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሚሲዮን ስነ መለኮት፣በፖል ዮርክ ይመልከቱ።

[2] ቤተ ክርስቲያንን ወደ እግዚአብሔር ተልእኮ ስለመምራት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 31ን "ሚሲዮናዊ አመራር" የሚለውን ተመልከት።

[3] በአገልጋይ አመራር ላይ ለበለጠ ግንዛቤ፣ ምዕራፍ 29ን "የአገልጋይ አመራር" የሚለውን ይመልከቱ ።

### ብቃት

በመጨረሻም፣ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ ለብቃት መጣር አለብህ። ጥሩ ሰው መሆን አስፈላጊ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ መረዳት አለብህ። አፍሪካውያን ጥሩ፣ ትሁት እና እንግዳ ተቀባይ በመሆን ይታወቃሉ። ጥሩ መሪ ለመሆን ግን የተወሰኑ ክህሎቶችን ማዳበር ይጠይቃል። እነዚህ ችሎታዎች የማስተማር ችሎታን፣ ራዕይን የመስጠት፣ ሌሎችን ለማነሳሳት እና ስራውን የማደራጀት ችሎታ ያካትታሉ።

በተጨማሪም፣ በመጨረሻ የመሪነት ችሎታ ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ መረዳት አለብህ። ጳውሎስ ይህን ጠንቅቆ ያውቃል። ለቆሮንቶስ ሰዎችም እንዲህ ሲል ገልጿል፣ “ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፣ በራሳችን ብቃት ከእኛ ነው የምንለው አንዳች ነገር የለንም።6 እርሱም በፊደል ላይ ሳይሆን በመንፈስ ላይ የተመሠረተውን የአዲሱ ኪዳን አገልጋዮች እንድንሆን ብቁዎች አደረገን፤” (2ቆሮ. 3፡5-6)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ ለእንደዚህ አይነት ብቃት ያለማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር መመልከት አለብህ።

## የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ተግባራት

የጴንጤቆስጤያዊው መጋቢ በሩጫ ውድድር ወቅት ከጉባኤው ኃላ እየሮጠ “ቆዩኝ እኔ መሪያችሁ ነኝ!” እያለ የሚጮህ መሆን የለበትም። በተቃራኒው እርሱ ወይም እርሷ ህዝቡን እንዲከተሉት እየጠየቀ ከሕዝብ ቀድመው መሄድ አለበት። ደቀ መዛሙርቱን “ኑ ተከተሉኝ፣ ሰዎችንም እንድታጠምዱ እልካችኋለሁ” ብሎ እንደ ተናገረ እንደ ኢየሱስ መሆን አለብህ። መጽሐፍ ቅዱስ “ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት” ይለናል (ማር. 1፡17-18)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈስ መሪነት ፕሮግራሞችን እና ስልቶችን እንድትዘረጋ ክርስቶስ ሾሞሃል። ከዚያም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በስራው እንዲከተሉህ ማነሳሳት አለብህ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ እንደ መንፈሳዊ መሪ፣ ታማኝ ተከታይ መሆን አለብህ። የእግዚአብሔርን መንፈስ በታማኝነት መከተል አለብህ። መንፈስ ቅዱስ ከበላይህ ላስቀመጠው አካል በትሕትና ተገዛ። የእግዚአብሔርን ተልእኮ በሦስት ዋና መንገዶች እንድትፈጽም ቤተ ክርስቲያንህን መምራት አለብህ፡-

### ራዕይ አጋራ

በመጀመሪያ፣ ለቤተ ክርስቲያን የወደፊትን የምትሄድበትን ራዕይ በማንሳት ሕዝብህን መምራት አለብህ። በሌላ አነጋገር፣ ጌታ ወደፊት ስላቀደላቸው አስደናቂ ነገር እንዲመለከቱ ልትረዳቸው ይገባል። ከዚያ ወደዚያ አቅጣጫ እንዲሄዱ ተጽዕኖ ማድረግ አለብህ። ይህን የምትሰራው በቃልህ፣በድርጊትህ እና በአመለካከትህ ማለትም በምትናገረው፣በምታደርገው ነገር እና እራስህን ለህዝብ በምታቀርብበት መንገድ ነው።

በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት ራእይህ ከተቀበልክ መላ ነገርህን ስለሚይዝ ሊተወው አይችልም። በውጤቱም፣ ስለ ራእዩ ያለማቋረጥ ትናገራለህ። የመነሳሳትህ ፍላጎትህ ከህይወትህ ስለሚቀዳ ህዝቡን ይነካል፣ ራእዩን እንዲጋሩ ያደርጋቸዋል። ትክክለኛ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ እንደመሆንህ፣የራስህን የወደፊት ራዕይ በፍፁም ማስተዋወቅ የለብህም። ይልቁንም በቃሉ እና በመንፈሱ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ራዕይ ማስተዋወቅ አለብህ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፡- “ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል” (ምሳ. 29፡18)። ወይም፣ አንድ ትርጉም “ትንቢታዊ ራዕይ በሌለበት ሕዝቡ ተስፋ ይቆርጧል” ይላል። እንዲህ ዓይነቱ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ብዙውን ጊዜ በራስን መሳብን፣ ማሽቆልቆልን እና በመጨረሻም መጥፋት ያስከትላል። ነገር ግን በአግባቡ የተብራራ ራዕይ ምእመናን አምስት ነገሮችን እንዲረዱ ያደርጋል፡-

1. **እነማን ናቸው?** በእግዚአብሔር መንፈስ የተደገፈ ሚስዮናውያን ናቸው፣ በክርስቶስ የታዘዘውን በምድር ላይ እንዲያደርጉ ተልእኮ ተሰጥቶአቸዋል።

2. **የት መሄድ አለባቸው?** የጠፉትን ለክርስቶስ በመማረክ፣ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል እና ሚስዮናውያንን ወደ አሕዛብ በመላክ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም አብረው መንቀሳቀስ አለባቸው።

3. **ምን ማድረግ እንዳለባቸው?** በእግዚአብሔር መንፈስ ታጥቀው እና ተልእኮውን ለመፈጸም የበኩላቸውን ለመወጣት ቁርጠኛ መሆን አለባቸው።

4. **እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው?** ፓስተሩ ስራውን እንዴት ማከናወን እንዳለበት የተወሰነ እቅድ ወይም ፕሮግራም ማውጣት አለበት። ከዚያም እርሱ ወይም እርሷ ለህዝቡ እንዴት በስራው ውስጥ መሳተፍ እንደሚችሉ ማሳየት ይጠበቅበታል።

5. **እንዴት መጀመር እንዳለባቸው?** ውጤታማ የሆነው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ህዝቡ በጥሩ ሁኔታ እንዲጀምር ለመርዳት ስራዎችን ለየግለሰብ ይመድባል።

በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ብዙ ከእግዚአብሔር የሆኑ ህልሞች በመጋቢው ልብ ውስጥ ይሞታሉ። አንተ ግን ይህ እንዲሆን መፍቀድ የለብህም። ለቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የሆነውን ራዕይ በታማኝነት ማግኘት እና ማሳየት አለብህ። በሕዝብህ ፊት ቆመህ በልበ ሙሉነት “መንገዱ ይህ ነው በዚህ እንሂድ” ማለት አለብህ(ኢሳ. 30፡21)።[4]

## ክትትል

ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያየላትን መዳረሻ መለየት እና እዚያ መድረሻ ላይ በመድረስ መካከል መሄድ ያለብህ መንገድ አለ። እንደ እግዚአብሔር ተወካይ፣ በዚያ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን መምራት አለብህ። እግዚአብሔር ያየውን ራዕይ ማሳየት ብቻ ሳይሆን የራዕዩን አፈጻጸም መከታተል አለብህ።

ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። ራእዩን አሳየ፣ ከዚያም ራእዩን ለማሳካት ስትራተጂውን ተግባራዊ አደረገ። የእርሱ ስልት ወንዶችንና ሴቶችን መጥራት፣ ማሰልጠን፣ ማሰልጠን፣ ማብቃት እና ከዚያም ወደ ስራው ማሰማራት ነበር። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ አንተም እንዲሁ ማድረግ አለብህ። ይህንን በመንፈስ የተመራ እቅድ በማቀድ ፣ በቅስቀሳ እና በክትትል ማድረግ ትችላለህ።

ስለዚህ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተ ህዝብህን ለማነሳሳት ብቻ ሳይሆን ስራውን በበላይነት እንድትቆጣጠር ተጠርተሃል (1ጢሞ. 3፡1-2፤ ቲቶ 1፡7)። የበላይ ተመልካች እንደመሆንህ፣ ቤተ ክርስቲያንን በመንፈስ ለተመራ ተልዕኮ ማደራጀት አለብህ። እቅዱን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ዘዴዎች እና እንቅስቃሴዎች ማድረግ አለብህ እነዚህ ተግባራት ሠራተኞችን መቅጠር፣ ማቀድ፣ ማሰልጠን እና ወደ

[4] ስለ ራዕይ ቀረጻ ለበለጠ፣ ምዕራፍ 30ን “የራዕይ አመራር” የሚለውን ተመልከት።

መስከ መላክን ያካትታሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ፣ ማስተዋልና መመሪያ ለማግኘት ወደ መንፈስ ቅዱስ መመልከት አለብህ።

## ዘላቂነት

በመጨረሻም፣ እንደ እግዚአብሔር ህዝብ መሪ፣ የቤተክርስቲያኗን ሚስዮናዊ ራዕይ የማስፋት እና የማስቀጠል ሀላፊነት ትወጣለህ። ይህን ማድረግ የምትችለው አንዱ መንገድ ሌሎች ባለራዕይ የሆኑ የጴንጤቆስጤያዊ መሪዎችን በማስነሳት ነው። ይህ ካላደረግህ ራእዩ ከአንተ ጋር ይሞታል፣ ተልዕኮው ይከሽፋል። ባለራዕይ መሪዎቻቸው ራዕያቸውን ማጋራት ባለመቻላቸው በርካታ ወንዶችና ሴቶች ተከታይ የጴንጤቆስጤያዊ መሪዎችን ጋር አብረው መሞታቸው እንዴት ያሳዝናል።

ኢየሱስ ግን ራእዩን ለሌሎች አስተላለፈ። አገልግሎቱን ከጀመረ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ደቀ መዛሙርትን መጥራት ጀመረ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- “ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ አሥራ ሁለቱን ሾመ” (ማር. 3፡14፤ 1፡16-17፤ 2፡13-14፤ 3፡13-19)። እነዚህ ደቀ መዛሙርት እርሱ ከሄደ በኋላ ሥራውን ቀጠሉ። ኢየሱስ ይህ እንዲሳካ አሠልጥኗቸዋል፣ ኃይል ሰጥቶቸዋል፣ እና “ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ” ብሎ ልኮቸዋ (ማቴ. 28፡19)። በሌላ አነጋገር፣ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ከሌሎች ጋር እንዲያደርጉ ይጠብቅ ነበር።

ጳውሎስ የኢየሱስን ምሳሌ ተከትሏል። የሚስዮናዊነት አገልግሎቱን ብቻውን አላከናወነም፣ ነገር ግን ሌሎች እንዲቀላቀሉት ጋበዘ። ከዚያም ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንዳደረገው አሠለጠናቸው። የጳውሎስ ደቀ መዛሙርት ዮሐንስ ማርቆስ፣ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ፣ ሉቃስ እና ሌሎችም ይገኙበታል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከእርሱ ጋር እንዳደረገው ለሌሎች እንዲያሰለጥን አዘዘው። በእምነት ልጁን “ በብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ” (2 ጢሞ. 2:2) ሲል ጽፏል። ራእዩን በሌሎች ላይ ለማስቀጠል ከፈለግን የኢየሱስንና የጳውሎስን ፈለግ መከተል አለብን።

ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች “የእኛን ምሳሌ እንዴት መከተል እንደሚገባችሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁና” ሲል መክሯቸዋል፣ ምክንያቱም “ይህን ያደረግነው ምሳሌነታችንን እንድትከተሉ ብለን ነው” (2 ተሰ. 3:7፣ 9) ብሏል። ዛሬም የጴንጤቆስጤያዊ ተልእኮ ራዕይ ለማስቀጠል ከፈለግን፣ ልክ እንደ ጳውሎስ፣ ሌሎች ሊመስሉአቸው የሚፈልጓቸው ዓይነት ሰዎች መሆን አለብን። ማለትም ክብር፣ ታማኝነት እና ራዕይ ያለን ሰዎች መሆን አለብን።

---

እግዚአብሔር የሾመው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደመሆንህ፣ መሆን የሚትችለውን ምርጥ መሪ መሆን አለብህ። እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ይህንን ሚና ለመወጣት አስፈላጊውን የአመራር ችሎታ ለማዳበር ጠንክረህ መስራት አለብህ።

# ~ ምዕራፍ 29 ~

# የአገልጋይ መሪነት

አንድ ቀን የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አንድ ጥያቄ ይዘው ወደ እርሱ ቀረቡ። “በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?” ብለው ጠየቁት። (ማቴ. 18፡1) እነዚህ ደቀ መዛሙርት በዚህ ጉዳይ እርስ በርሳቸው ሲከራከሩ ነበር (ማቴ. 20፡20-28፤ ማር. 9፡33-37፤ 10፡35-45፤ ሉቃ. 22፡24-27)። አንዳንዶቹ ከፍተኛ ሥልጣን እንዲኖራቸው እና በደቀ መዛሙርት መካከል መሪዎች ለመሆን ይፈልጉ ነበር።

ኢየሱስ ልባቸውን አውቆ አንድ ትንሽ ልጅ መጥቶ በመካከላቸው እንዲቆም አደረገ። ከዚያም ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፡- “እውነት እላችኋለሁ፣ ካልተለወጣችሁ እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ፈጽሞ ወደ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም።4 ስለዚህ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው” (ማቴ. 18፡3-4)። በሌላ ጊዜ ደግሞ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ገልጿል፡- “የአሕዛብ ገዢዎች በሕዝባቸው ላይ ጌቶች እንደሚሆኑ፣ ባለ ሥልጣኖቻቸውም በኀይል እንደሚገዟቸው ታውቃላችሁ፤26 በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም። ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤27 የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን” (ማቴ. 20:25-27)።

ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ስለሚፈልገው አመራር እየተናገረ ነበር። በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያሉ መሪዎች ከዓለም መሪዎች በተለየ መንገድ እንዲመሩ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ አዳዲስ መሪዎች ከመገለገል ይልቅ ሌሎችን ማገልገል ይኖርባቸዋል። ሕዝብን ከመግዛት ይልቅ የሚመሩት በፍቅር መንከባከብ አለባቸው። ይህ አይነቱ አመራር አገልጋይ አመራር በመባል ይታወቃል። ዛሬም በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እግዚአብሔር የሚፈልገው ዓይነት አመራር ይሄ ነው።

# የአገልጋይ አመራር ገለጻ

መሪነት ሰዎች በተወሰነ መንገድ እንዲሠሩ ወይም ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲሄዱ ተጽዕኖ የማድረግ ችሎታ ነው። ለጴንጤቆስጤ መጋቢ መሪነት የእግዚአብሔርን ህዝብ በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲፈልጉ ተጽዕኖ ለማድረግ በእግዚአብሔር የተሰጠ ችሎታ ነው (ማቴ. 6፡33)። የእግዚአብሔርን ህዝብ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በማራመድ ረገድ እግዚአብሔር የሾመውን ሚና እንዲወጡ ማነሳሳት መቻል ነው።

እንደ ሁሉም አይነት መሪዎች፣ አገልጋይ መሪዎች ተልዕኮ ተኮር ናቸው። ይሁን እንጂ አገልጋይ መሪዎች ለሚመሩት ሕዝብ ዕድገትና ደህንነት ያሳስባቸዋል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትሕትና እና በርኅራኄ ያገለግላሉ፤ ከማስገደድ ይልቅ በፍቅር ተጽዕኖ ለማድረግ ይጥራሉ።

የአገልጋይ መሪ አስተሳሰብ በአፍሪካ ውስጥ ብዙ ጊዜ ከሚታየው "የአለቃ አስተሳሰብ" ተቃራኒ ነው። ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌላቸው አለቆች በማስፈራራት ይገዛሉ ፤ አገልጋይ መሪ ግን በፍቅር እና በርህራሄ ይመራል። አለቃ መሪ መታዘዝን ይጠይቃል ፤ አገልጋይ መሪ በራስ መተማመንን ያሳድጋል። አለቃ መሪ ህዝቡን ይበዘብዛል ፤ አገልጋይ መሪ ግን ሊባርካቸው ይፈልጋል።

ኢየሱስ እንደ አለቃ መሪ ሊገዛ ይችል ነበር ፤ እርሱ ግን አገልጋይ መሪ ሆኖ መምራትን መረጠ (ማቴ. 20፡28)። በማንኛውም ጊዜ፣ ኢየሱስ ፈቃዱን እንዲፈጽሙ የመላእክት ጭፍሮችን ማዘዝ ይችል ነበር (26፡53)። ሆኖም ራሱን ዝቅ ለማድረግ እና ለአባቱ ፈቃድ ራሱን ለማስገዛት መረጠ (26፡39፣42)። በመስቀል ላይ የከፈለው መስዋዕትነት የአገልጋይ መሪ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የመጨረሻ ምሳሌ ነው። ልክ እንደ ጌታቸው፣ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን አገልጋይ መሪዎች ናቸው። ተከታዮቻቸውን ከመበዝበዝ ይልቅ በደስታ እና በፍቅር ያገለግላሉ።

የእግዚአብሔር መንግሥት “ከታች ወደ ላይ የሚዘወር መንግሥት” ተብሎ ተገልጿል። ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለው አመራር በዓለም ሥርዓት ውስጥ ካለው አመራር በተለየ መንገድ ስለሚሠራ ነው። በዓለማዊ ድርጅቶች ውስጥ መሪው የበላይ እንደሚሆን ይጠበቃል። እርሱ ወይም እርሷ ሌሎችን ይቆጣጠራሉ እና አብዛኛውን ክብር እና ጥቅሞችን ያገኛሉ። ነገር ግን፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መሪው ከታች ነው ያለው። እርሱ ወይም እርሷ ሌሎችን ለማገልገል እና ለመባረክ ይተጋሉ።

# የአገልጋይ መሪ ባህሪያት

አገልጋይ መሪ መሆን የሚፈልግ ማንኛውም የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ውስጥ ስድስት ባህሪያት መገኘት አለባቸው:-

## ትህትና

በመጀመሪያ፣ እንደ አገልጋይ መሪ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በትህትና መምራት አለበት። እርሱ ወይም እርሷ የግል እውቅና ወይም ስልጣንን በመፈለግ ጊዜ ማባከን የለባቸውም። ይልቁንም የመጥምቁ ዮሐንስን ምሳሌ በመከተል “ እርሱ ሊልቅ፣ እኔ ግን ላንስ ይገባል” ማለት ይገባዋል (ዮሐንስ 3፡30)። የጌታን ቃልም ማስታወስ አለባቸው:- “ከመካከላችሁ ከሁላችሁ የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል፤12 ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል፣ ራሱን የሚያዋርድ ግን ይከበራል” (ማቴ. 23፡11-12)።

በአንዳንድ የአፍሪካ ቦታዎች፣ መጋቢያን ለራሳቸው ከፍ ያለ የማዕረግ ስሞችን የመጠየቅ አዝማሚያ አለ። ኢየሱስ ይህን ልማድ አስጠንቅቋል። ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፡- “እናንተ ግን ‘መምህር’ ተብላችሁ አትጠሩ፤ አስተማሪያችሁ አንድ ብቻ ነው፣ እናንተ ሁላችሁም ወንድማማቾች ናችሁና።9 በሰማይ ያለ አንድ አባት ስላላችሁ፣ በምድር ማንንም ‘አባት’ ብላችሁ አትጥሩ። 10 መምህራችሁ አንዱ ክርስቶስ ስለ ሆነ፣ ‘መምህር’ ተብላችሁ አትጠሩ። ከመካከላችሁ ከሁላችሁ የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል፤” (ማቴ. 23፡8-11)። ትንሽ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ትልቅ ማዕረግ ይፈልጋሉ። ታላላቅ መሪዎች ግን እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች መታየታቸው ያረካቸዋል።

ኢየሱስ ከመስቀሉ በፊት በነበረው ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በኢየሩሳሌም ደርብ ላይ ባለው ክፍል ውስጥ ጊዜ አሳልፎ ነበር። በዚያም ስለ አገልጋይ አመራር ትምህርት አስተማራቸው። የፋሲካን ምግብ ከጨረሰ በኋላ፣ ተነሳ፣ ውጫዊ ልብሱን አውልቆ፣ ፎጣ በወገቡ ላይ ጠመጠመ። ከዚያም ገንዳውን በውኃ ሞላና የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብ ጀመረ። ሲጨርስ፣ “ያደረግሁላችሁን ታሰተውላላችሁን?” ሲል ጠየቃቸው።

ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ ሲል ገለጸላቸው፡- “እናንተ፣ ‘መምህርና፣ ጌታ’ ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝ እንዲሁ ነኝና።14 እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተም እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል።15 እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ” (ዮሐ. 13፡13-15)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያስተማራቸው በመንግሥቱ ውስጥ ታላቅ መሪ የሚባለው ትንሹን የአገልጋይ ቦታ የሚይዙት ናቸው።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የኃይል እና የትዕቢትን መንፈስ አጥብቀህ መቃወም አለብህ። እንደ እውነተኛ አገልጋይ መሪ የእግዚአብሔርን ህዝብ መበዝበዝ በፍጹም የለብህም። ይልቁንም ለማገልገል እና የበረከት ምክንያት ለመሆን መፈለግ አለብህ።

## ርህራሄ

ሁለተኛ፣ እንደ እውነተኛ አገልጋይ መሪ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንድትመራ ለተጠራህበት ቤተክርስትያን አማኞች ልትራራላቸው ይገባል። ለአማኞች ማዘን ማለት ከእነርሱ ጋር በቅርበት መሆን እና ስሜታቸውን፣ ጉዳታቸው እና ደስታቸውን መካፈል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ "በድካማችን ሊራራልን" የሚችል ታላቅ ሊቀ ካህናችን እንደሆነ ይናገራል (ዕብ. 4: 15)። ኢየሱስ በአልዓዛር መቃብር ከማርያምንና ማርታን በማልቀስ ሃዘኑን ተጋራቸው (ዮሐንስ 11፡35)። እንደ ኢየሱስ፣ እንድ አገልጋይ መሪ፣ “ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ” እና “ከሚያዝኑ ጋር እዘኑ” (ሮሜ. 12፡15) የሚለውን መማር አለበት።

## ግልጽነት

ሦስተኛ፣ እንደ አገልጋይ መሪ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ግልጽ ለመሆን መጣር አለበት። ይህ ማለት እውነተኛ ማንነትህን ከሌሎች ለመደበቅ አትሞክርም ማለት ነው። ያልሆንከውን አስመስለህ ለመታየት አትሞክርም። ጳውሎስ የራሱን ግልጽነት ለቆሮንቶስ ሰዎች አሳስቧቸዋል። “ከእናንተ ጋር ባለን ግንኙነት፣ ከእግዚአብሔር በሆነ ቅድስናና ቅንነት እንደኖርን ኅሊናችን ይመሰክራል፤” (2ቆሮ. 1፡12) ሲል ጽፏል። በኋላም “የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፤ ሁሉን በግልጽ ነግረናችኋል፤ ልባችንንም ወለል አድርገን ከፍተንላችኋል” (2ቆሮ. 6፡11) አክሎ ተናግሯል።

እንዲህ ዓይነቱ ግልጽነት በአንተ እና በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ያለውን የግንኙነት መስመር የተሻለ ያደርገዋል። ህዝቡ አንተን እንደ ታማኝ፣ሰው ማየት ይጀምራል። በውጤቱም፣ በአንተ እንዲያምኑ እና እርግጠኛ እንዲሆኑ ያበረታታል። የአንተን አመራር በመከተል ደስተኞች ይሆናሉ።

## እምነት

አራተኛ፣ እንደ አገልጋይ መሪ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የእግዚአብሔር ህዝብን ያምናል። በእርሱ ወይም እርሷ የሚያድረው፣ ስልጣን የሚሰጠው እና የሚመራው የእግዚአብሔር መንፈስ፣ በአባሎቻቸውን የሚመራው ያው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያምናሉ። በዚህ ምክንያት፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በእግዚአብሔር ህዝብ ማመን ይችላል፣ እና እርሱ ወይም እርሷ አገልግሎትን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለባቸው። ኢየሱስ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር ያደረገው ይህንኑ ነው (ዮሐንስ 20፡21)። ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ ጋር ያደረገው ይህንኑ ነው (2ጢሞ. 2፡2)። አሥር ሥራዎችን ለመሥራት ከመሞከር ይልቅ፣ ውጤታማው መጋቢ አሥር አባላትን እነዚህን አሥር ሥራዎች እንዲሠሩ ያስታጥቃቸዋል።

ስለዚህ፣ እንደ ታማኝ አገልጋይ መሪ፣ የእግዚአብሔርን ስጦታዎች በሌሎች ላይ ልብ በል። እና እነርሱን በማንቃት እና ስራውን እንዲሰሩ በማሰልጠን ከእነርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ አለብህ። እነዚህ ታዳጊ መሪዎች በመረዳታቸው እና በችሎታቸው እያደጉ ሲሄዱ፣ የበለጠ ሀላፊነት ለእነርሱ መስጠት አለብህ። ደግሞም አዲሱን ሚናቸውን በብቃት ለመወጣት የሚያስፈልጋቸውን ስልጣን መስጠት አለብህ።

ታላቅ መሪ በሌሎች ስኬት አይሰጋም። በተቃራኒው፣ የእርሱ ወይም የእርሷ ታላቅ ደስታ ሌሎች ተልዕኮውን ለመፈፀም እንዲሳተፉ በማነሳሳት ነው።

## ተግባቦት

አምስተኛ፣ እንደ አገልጋይ መሪ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ከሚመራው በአግባብ መነጋገርን መማር አለበት። ይሄ ጥሩ የሐሳብ ልውውጥ ማድረግ በጥበብ መናገርና በማስተዋል ማዳመጥን ይጨምራል። መጽሐፍ ቅዱስ “አካሄዳችሁ ሁልጊዜ በጸጋ የተሞላ፣ በጨው የተቀመመ ይሁን” በማለት ይመክራል (ቆላ. 4፡6)። እንዲሁም “ለመስማት ፈጣን (ወይም ዝግጁ) እንድንሆን” (ያዕቆብ 1፡19) ያስተምረናል። ስለዚህ፣ እንደ ውጤታማ አገልጋይ መሪ፣ ውጤታማ ተግባቦት እንዲኖርህ ብዙ ጊዜ እና ጉልበት ማፍሰስ አለብህ።

## ቅባት

በመጨረሻም፣ እንደ አገልጋይ መሪ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የመንፈስ ቅዱስን ቅባት መፈለግ አለበት። እርሱ ወይም እርሷ በስር ያሉ ሌሎች መሪዎች ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ማነሳሳት አለባቸው። በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርት እንደ ተቀበሉት አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ ቅባቱ ይቀበላል (ሐዋ. 2፡4)። የመንፈስ ቅዱስ ቅባት የሚጠበቀው በመንፈስ በመመላለስ ነው (ገላ. 5፡25)።

ኢየሱስ በመንፈስ የተቀባ አገልጋይ አመራር ምን እንደሚመስል ዋና ምሳሌ ነው። ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር፣ የሚያስፈልጋቸውን በማገልገል ሌሎችን እንዲያገለግል መንፈስ ቅዱስ እንደቀባው አበሰረ (ሉቃስ 4፡18-19)። ጴጥሮስ የኢየሱስን አገልጋይ አገልግሎት እንዲህ ሲል ገልጾታል፡- “እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል ቀባው፤ እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያብሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ” (የሐዋርያት ሥራ 10 : 38)

ልክ እንደ ኢየሱስ የአምላክን ሥራ በራሳችን ኃይል ወይም ችሎታ ለመሥራት ፈጽሞ መሞከር የለብንም። ይልቁንም በመንፈስ ኃይልና ቅባት መታመን አለብን (ሉቃስ 24፡49፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡8)።

# የአገልጋይ መሪነት ምሳሌዎች

መጽሐፍ ቅዱስ የአገልጋይ አመራር ምሳሌዎችን ይዟል። ከእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ አራቱን እንመልከት። ሁለቱ በብሉይ ኪዳን ይገኛሉ፣ ሁለቱ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ።

## ሙሴ፡- የተወከለ አገልግሎት

ሙሴ አገልግሎቱን ለመወከል የፈቀደ ትሁት አገልጋይ መሪ ጥሩ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ለሙሴ ሕዝቡን እንዲመራ በመምረጥ ታላቅ ሥልጣንን ሰጠው (ዘጸ. 3፡1-10)። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር" ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት ይነጋገር ነበር" (33፡11)። እግዚአብሔርም ሙሴን ተጠቅሞ በሕዝቡ መካከል ድንቅን ተአምራትን አደረገ (4፡21፤ ሐዋ. 7፡36)። ይሁን እንጂ ሙሴ አልታበይም። ይልቁንም፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትሕትና ለመምራት መረጠ (ዘኍ. 12፡3)።

መጽሐፍ ቅዱስ የሙሴ አማች ሙሴን ሥራውን እንዲፈጽም እንዴት እንደመከረው ይናገራል (ዘጸ. 18፡13-27)። ዮቶርም ሙሴን ሥራውን ሁሉ ሲሠራ ባየው ጊዜ "የምትሠራው መልካም አይደለም።18 አንተና ወደ አንተ የሚመጡት እነዚህ ሰዎች የምታደርጉት ነገር ቢኖር ራሳችሁን ማድከም ነው፤ ሥራው ለአንተ ከባድ ሸክም ነው፤ ብቻህን ልትወጣው አትችልም" (ቁ. 17-18)። ሙሴ የዮቶርን ምክር በመከተል አብዛኛውን ሥራውን ለታማኝ ሰዎች ሰጠ። በውጤቱም፣ ሙሴ እፎይታ አገኘ፣ ሥራው ተሳካለት፣ እናም ህዝቡም ተባረከ።

## ዳዊት፡- ሌሎችን የሚያሳድግ መሪ

የአገልጋይ መሪ ሌላው ጥሩ ምሳሌ ንጉሥ ዳዊት ነው። እግዚአብሔር እርሱን "እንደ ልቤ የሆነ ሰው" ብሎ ጠርቶታል (ሐዋ. 13፡22፤ 1 ሳሙ. 13፡14)። ዳዊት በንጉሥነቱና በእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋይነት ቦታው ላይ አስተማማኝ ስለነበር ሌሎችን ለማነጽ ጊዜና ጉልበት ማዋል ችሏል።

ዳዊት ትሑት አገልጋይ መሪ እንደመሆኑ መጠን እንደ ቀድሞው መሪ እንደ ሳኦል የሌሎችን ሰዎች ስኬት አልፈራም። ዳዊት በልበ ሙሉነት የራሱን ከማይስማሙት ጋር እንኳን አብሮ ሰራ (1ዜና. 11፡10-47)። ከእርሱ በታች ያገለገሉትንም አከበራቸው፣ እንዲሳካላቸው አበረታታቸው (ቁ. 17-19፣25)። እግዚአብሔር ዳዊት ሌሎችን ለማሳደግ መፍቀዱን ለዳዊት ለስኬታማነት እና በእርሱ ሥር የሚያገለግሉትን ለመባረክ ተጠቅሞበታል።

## ጳውሎስ፡ አሰልጣኝ መሪ

ሦስተኛው የትሑት አገልጋይ መሪ ምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። እግዚአብሔር ጳውሎስ ሐዋርያ እንዲሆን የመረጠው ቢሆንም ራሱን እንደ የክርስቶስ አገልጋይ አድርጎ ይቆጥር ነበር (ሮሜ 1፡1፣ ቲቶ 1፡1)። ጳውሎስ በአንድ ወቅት ራሱን "ከሐዋርያት ሁሉ የሚያንስ" ሲል ገልጿል (1 ቆሮ. 15፡9)። እርሱ ራሱ በበርናባስ ስር ሰልጥኖ ነበር (ሐዋ. 9፡26-27፤ 11፡25-26)። በተራው ደግሞ ሌሎችን በትጋት አሰልጥኗል። ደብዳቤዎቹ ሌሎችን ለማነጽ ያለማቋረጥ የሚጥርበትን መንገድ ያሳያሉ።

ከጳውሎስ ታላላቅ ስኬቶች መካከል ሁለቱ ጢሞቴዎስ እና ቲቶ ነበሩ። ጢሞቴዎስን አሰልጥኖታል (የሐዋርያት ሥራ 16፡1-5) እና ከጊዜ በኋላ "በእምነት ልጄን" ሲል መጥራት ብቻ ሳይሆን የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እንዲመራ አምኖ ሹሞታል (1 ጢሞ. 1፡2-3)። ቲቶንም መክሮ በቀርጤስ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት እንዲመራ ሾመው (ቲቶ 1፡5)። ሐዋርያው ጢሞቴዎስን፣ ቲቶንና ሌሎችን ለማሰልጠን ጥረት ባያደርግ ኖሮ ተጽዕኖውም ሆነ ሥራው በእጅጉ ይቀንስ ነበር።

### ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሁሉ የላቀ ምሳሌያችን

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአገልጋይ አመራር ዋና ምሳሌ ነው። ጌታ እውነተኛ የእግዚአብሔር መንግሥት መሪዎች ከራስ ወዳድነት ነፃ ሆነው ሌሎችን እንዲያገለግሉ አስተምሯል (ሉቃስ 22፡24-27)። ይህንን ጽንሰ ሐሳብ በራሱ ሕይወትና አገልግሎት አሳይቷል። ኢየሱስ ስለራሱ ሲናገር፡- "የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም" (ማር.10፡45) ብሏል። ጳውሎስ የኢየሱስን አገልጋይ የአመራር ዘይቤ እንደሚከተለው ገልጾታል፡-

በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤6 እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤7ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ራሱን ባዶ አደረገ፤8ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ራሱን ዝቅ አደረገ፤እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ። ፊሊ 2፡5-8

በመሆኑም ጳውሎስ ክርስቲያን መሪዎችን ጨምሮ ሁሉንም ክርስቲያኖች "ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና ቊጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ። 4እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ" ሲል ይመክራል (ፊሊ 2፡3-4)።

# የአገልጋይ መሪነት የትኩረት ዘርፎች

የአገልጋይ አመራር አመለካከት በጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሕይወት እና አገልግሎት በሦስት ዘርፎች ማለትም በቤት፣ በቤተ ክርስቲያን እና በማህበረሰቡ መገለጥ አለበት።

### አገልጋይ መሪ በቤት ውስጥ

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የመጀመሪያው የአገልጋይ አመራር ቦታ ቤት ነው። ጉባኤህን ከማገልገልህ በፊት የትዳር ጓደኛህንና ልጆችህን በታማኝነት ማገልገል አለብህ። ጳውሎስ ስለ የበላይ ተመልካች ወይም መጋቢ ሲናገር፣ "ልጆቹን ታዛዥና አክባሪ አድርጎ በማሳደግ የገዛ ቤተ ሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳድር ሊሆን ይገባል" (1 ጢሞ. 3፡4)። ጳውሎስ በመቀጠል፣ "አንድ ሰው የራሱን ቤት ማስተዳደር ካላወቀበት፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊጠብቅ ይችላል?" ብሏል (ቁ. 5)።

ስለዚህ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የመጀመሪያው የአገልጋይ አመራር ትኩረት ቤተሰብ መሆኑን ማወቅ አለብህ። እራስዎን ዝቅ ለማድረግ እና የትዳር ጓደኛዎን እና ልጆችዎን በጥሩ ሁኔታ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆን አለብህ። በአንድ በኩል፣ ቤተሰብህ "የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያንህ ነው፣ ቀጥሎ የምትመራው ቤተ ክርስቲያን "ተባባሪ ቤተ ክርስቲያን" ነው። ቤተሰብህን የምታገለግልበት አመለካከት ቤተ ክርስቲያንህን የምታገለግልበት አመለካከት መሆኑ የማይቀር ነው። ለሁለቱም አገልጋይ መሪ መሆን አለብህ።

### አገልጋይ መሪ በቤተ ክርስቲያን

ሁለተኛው የአገልጋይ አመራር ቦታህ ቤተ ክርስቲያን ነው። እራስህን ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሰጠህ ስጦታ አድርገህ መመልከት አለብህ (ኤፌ. 4፡11-12)። በተጨማሪም፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንድትጠብቅ ክርስቶስ እንደጠራህ ማወቅ አለብህ። ጴጥሮስ ለሽማግሌዎች እንዲህ ሲል ጽፏል፡- " በእናንተ ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብሔር

እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን፤3 እንዲሁም በዐደራ ለተሰጣችሁ መንጋ መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በላያቸው በመሠልጠን አይሁን" (1ጴጥ. 5፡2-3)።

እንደ እውነተኛ አገልጋይ መሪ የእግዚአብሔርን ቃል በመመገብ፣ደካሞችን በማበርታት እና ለታመሙ እና ለተቸገሩት በመጸለይ የእግዚአብሔርን መንጋ መጠበቅ አለብህ። በጎቹንም ከአዳኞች መጠበቅ አለብህ(ሐዋ. 20፡28-31)። በተጨማሪም፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እርስ በርስ እንዴት እንደሚተሳሰቡ በማሳየትና በተግባር እንዴት እንደሚያደርጉ በማሳየት የአገልግሎት ምሳሌ መሆን አለብህ።[1]

## የአገልጋይ መሪ በማህበረሰብ ውስጥ

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ሶስተኛው የአገልጋይ አመራር ቦታህ ማህበረሰብህ ነው። ስለዚህ እራስህን እንደ ቤተሰብህ እረኛ እና የቤተ ክርስትያን መጋቢ ብቻ ሳይሆን የምትኖርበት መንደር ወይም ማህበረሰብ እረኛ አድርገህ ማየት አለብህ። ኢየሱስ "የምድር ጨው" እና "የዓለም ብርሃን" እንድንሆን አስተምሯል (ማቴ. 5፡13-16)። ስለዚህ፣ ከአካባቢህ ሰዎች ጋር በቅርበት መተዋወቅ፣ ለእነርሱ መጸለይ፣ ማገልገል እና የክርስቶስን ፍቅር በታማኝነት ከእነርሱ ጋር ማካፈል አለብህ።[2]

---

ኢየሱስ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ለአገልጋይ አመራር መስፈርት አውጥቷል። ለደቀ መዛሙርቱ "የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና" ብሏቸዋል። (ማር. 10፡45)። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የጌታውን ፈለግ መከተል አለበት። እናም "መጀመሪያ ለመሆን የሚፈልግ፣ ከሁሉ መጨረሻና የሁሉም አገልጋይ ይሁን" (9፡35) የሚለውን ቃሉን ማስታወስ አለብህ።

---

[1] የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለመጠበቅ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 24:- "መንጋውን መንከባከብ" እና ምዕራፍ 27ን "መንጋውን መጠበቅ" የሚለውን ተመልከት።

[2] ስለ አንድ ማህበረሰብ ስለ መንከባከብ፣ ምዕራፍ 38ን "ማህበረሰብን ማገልገል" የሚለውን ይመልከቱ።

# ~ ምዕራፍ 30 ~

# ባለ ራዕይ መሪ

ከብዙ ጸሎት እና ውስጥን ከመስማት በኋላ፣ መጋቢ ኢማኑኤል በዋና ከተማው የሚገኘውን ምቹ ቤተ ክርስትያን ትቶ ቤተሰቡን ይዞ ወደ ሀገሪቱ ጥቅጥቅ ደን በሆነ ስፍራ እንዲገባ እግዚአብሔር እንደጠራው ተረዳ። በስፍራው የቤተ ክርስቲያን ተከላ እንቅስቃሴ ሊጀምር ነው። መጋቢው "በሃገሬ በወንጌል ከሁሉ በታች ያልደረሰበት አውራጃ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እኔና ቤተሰቤ እንድንሄድ የሚፈልገው በዚያ ነበር" በማለት ያስታውሳል። እግዚአብሔር ራእዩን በልቡ እንዳስቀመጠው እርግጠኛ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ መጋቢ ኢማኑኤልን ወደ እዚህ መንደር ሲመራው ቦታው ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚገኝ ቢሆንም በጥንቆላ የተዘፈቀ ነበር። ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ፓስተሩ እና ባለቤቱ ከአካባቢው ጠንቋዮች ዛቻ ይደርስባቸው ነበር። ሆኖም ጥንዶቹ በትዕግስት ለሚያዳምጡዋቸው ሁሉ ወንጌልን በመስበክ ጸኑ። ይሄን ተከትሎ ሰዎች ዳኑ እናም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፣ እና ቤተ ክርስቲያን ማደግ እና መጎልመስ ጀመረች።

መጋቢ ኢማኑኤል በመንፈስ ስለሚመራ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እንቅስቃሴ የመጀመር ራዕዩን ብዙ ጊዜ ለአባላቱ አካፍሏል። ብዙም ሳይቆይ ሌሎች ራእዩን መያዝ ጀመሩ፣ እና ከጊዜ በኋላ መጋቢ ኢማኑኤል ለአገልግሎት ያሰለጠናቸው መሪዎች መውጣት ጀመሩ። መጋቢ ኢማኑኤል በየአቢያተ ክርስቲያናቱ ለመስበክ እና በዙሪያው ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ለመትከል ብዙ ጊዜ እነዚህን ታዳጊ መሪዎች ከእርሱ ጋር ይወስድ ነበር። እነርሱም ባለፉት ዓመታት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል። ሌላው ቀርቶ ሚስዮናውያንን አሰልጥነው በሰሜን በወንጌል ባልተደረሱ ጎሳዎች መካከል አብያተ ክርስቲያናትን እንዲተክሉ ልከዋል።

ዛሬ የመጋቢ ኢማኑኤል ቤተ ክርስቲያን እያደገ ነው። ህዝቡም የፓስተራቸውን ራዕይ በመለየት በክልሉ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል ቀጥሏል። መጋቢ ኢማኑኤል ባለራዕይ መሪ መሆን ምን ማለት እንደሆነ በተግባር አሳይቷል።

ቤተ ክርስቲያንን ወደ ውጤታማ ተልእኮ ለመምራት፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እግዚአብሔርን ለቤተ ክርስትያን ያለውን አላማ በግልፅ መረዳት አለበት። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መሳተፍ እንዳለባት ግልጽ የሆነ ራዕይ ሊኖረው ይገባል። ፓስተሩ ቤተ ክርስቲያን ወዴት መሄድ እንዳለባት ግልጽ የሆነ ራዕይ ሲሰጥ ህዝቡ እንዲከተል ይነሳሳል። እርሱ ወይም እርሷ እንደዚህ ያለ ራዕይ ማሳየት ሲሳናቸው፣ ቤተ ክርስቲያን ትታወራለች (ምሳ. 29፡18)። ይህ ምዕራፍ አጥቢያ ለመምራት የራዕይን አስፈላጊነትን ያብራራል።

# ባለ ራዕይ መሪነት ገለጻ

ባለራዕይ እረኛ መሪ የእግዚአብሔርን ህዝብ ካለበት ቦታ እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ቦታ የሚመራ ወንድ ወይም ሴት ነው። እንዲህ አይነት በመንፈስ የሚመራ መሪ ዛሬን አሻግሮ መጪውን ማየት ይችላል። አሁን ያለችበትን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በትክክል መገምገም እና ጥንካሬዋንና ድክመቷን ይረዳል። ቤተ ክርስቲያን ምን መሆን እንደምትችል እና ምን መሆን እንዳለባት ለማየት ይችላል። ቤተ ክርስቲያኒቱ እግዚአብሔር ያየላትን ግብ የምታሳካበትን መንገድ ለመንደፍ ይችላሉ። በመጨረሻም፣ ባለራዕይ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ግቦች ለማሳካት በድፍረት ወደፊት እንድትራመድ ማነሳሳት ይችላል።

# የባለራዕይ መሪዎች ባህሪያት

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጸው የባለራዕይ መሪዎችን ስምንት ባህሪያትን እንመልከት፡-

### በመንፈስ የሚመራ

በመጀመሪያ፣ እውነተኛ ባለራዕይ መሪ በመንፈስ የሚመራ ነው። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተክርስቲያኑን ወደ እግዚአብሔር አላማ ከመምራቱ በፊት፣ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ እና የመንፈስ ቅዱስን አመራር መከተል መቻል አለበት (ገላ. 5፡25)። የእግዚአብሔርን እቅድ ቢጋለ ስሜት ለመከታተል የራሱን እቅድ ለመተው ፈቃደኛ መሆን አለበት።

### በእምነት የተሞላ

ሁለተኛ፣ ባለራዕይ መሪ በእምነት የተሞላ ነው። በችግርና በአሉታዊ ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔርን የማመን እና በእርሱ የመታመን ችሎታ አለው (ዕብ. 11፡1-37)።

### ትክክለኛ

ሦስተኛ፣ ባለራዕይ መሪ ቤተ ክርስቲያን እንድትከተለው ትክክለኛ አርአያ ያኖራል (ፊልጵ. 3፡17)። ቤተ ክርስቲያንን መምራት እንደሚችል የተመሰከረለት የአገልግሎት ታሪክ አለው። እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን የሚጠብቀውን ምላሽ በሕይወቱ ያሳያል።

### ወደፊት ላይ ያተኮረ

አራተኛ፣ ባለራዕይ መሪ ወደፊት ላይ ያተኮረ ነው። አእምሮው የተመሰረተው በትላንትናው ስኬቶች ላይ ሳይሆን በነገው እድሎች ላይ ነው። ጳውሎስ ይህንን የባህርይ ሲመሰክር፣ “አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ” (ፊልጵ. 3፡13) በማለት መስክሯል።

### ትንቢታዊ እና ተግባራዊ

አምስተኛ፣ ባለራዕይ መሪ፣ በተመሳሳይ ጊዜ፣ ትንቢታዊ እና ተግባራዊ ነው። ሊሆን የሚችለውን መመልከቱ ትንቢታዊ ያደርገዋል። ግቡ ላይ ለመድረስ ምን መደረግ እንዳለበት ስለሚገነዘብ ተግባራዊ ነው። ባለራዕይ መሪ የወደፊቱን እያሰበ ቤተ ክርስቲያንን አሁን ባለችበት ፈተና በተግባራዊ በሆነ መንገድ መምራት መቻል አለበት።

### የሚታመን

ስድስተኛ፣ ባለራዕይ መሪ ታማኝ ነው። የታማኝነት ታሪክ አለው። በዚህ ምክንያት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊከተሉት ፈቃደኞች ናቸው።

### ተፅዕኖ ፈጣሪ

ሰባተኛ፣ ባለራዕይ መሪ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው። ሌሎችን እንዲሠሩ ለማነሳሳት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ችሎታ አለው። የሌሎችን አመለካከት፣ ምርጫ እና ድርጊት ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማሳደር የሚያስፈልጉትን ስጦታዎች እና ክህሎቶች አሉት።

### ደፋር

በመጨረሻም ባለራዕይ መሪ ደፋር ነው። እርግጠኛ ባይሆንም ወደፊት ለመሄድ ደፋር ነው። መጋቢ ኢማኑኤል ከዋና ከተማው ምቾት ሲወጣ በፊቱ ያለውን አያውቅም ነበር። ሆኖም፣ ፍላጎቶቹን እንደሚያሟላ እግዚአብሔርን በማመን ቤተሰቡን በድፍረት ወደማይታወቅ መርቷል።

## የባለራዕይ መሪዎች ምሳሌዎች

በብዙ መንገድ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ያስነሣቸው እና ባለራዕይ መሪ እንዲሆኑ የቀባቸው የወንዶችና የሴቶች ታሪክ ነው። እነዚህ መሪዎች ከላይ የተጠቀሱትን የአመራር ባህሪያት በምሳሌነት ያሳያሉ። የሚከተሉት ስድስት ሰዎች የእነዚያ መሪዎች ምሳሌዎቻችን ናቸው።

### አብርሃም፡ በእምነት የተሞላ ራእይ

አብርሃም በእምነት የተሞላ ባለ ራዕይ መሪ ነበር። በእምነት ወደ ፊት ተመለከተ እና " መሠረት ያላትን፣ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ነበር" (ዕብ. 11:10). ከዚያም እግዚአብሔር የገባውን ቃል እንደሚፈጽም በማመን ቤተሰቡን በእምነት ወደማይታወቅ አገር መራ (ዕብ. 11፡8)። ይህንንም በማድረግ “ለሚያምኑ ሁሉ አባት” ሆነ (ሮሜ. 4፡11)።

### ዮሴፍ፡ ትንቢታዊ ማስተዋል

ዮሴፍ በትንቢታዊ ማስተዋል የሚመራ ሰው ነበር። እግዚአብሔር የፈርዖንን ሕልም ፍቺን ሰጠው (ዘፍ. 41፡15-24)። ከዚያም ዮሴፍ ለዚህ ትንቢታዊ መልዕክት እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለበት ለንጉሡ ተግባራዊ ምክር ሰጠው (ቁ. 25-36)። በዚህ ምክንያት ብዙዎች ከረሃብ መዳን ችለዋል። ፈርዖን በዮሴፍ

ውስጥ የእግዚአብሔርን መንፈስ አይቶ ስለነበር ወደ ከፍተኛ የመሪነት ቦታ ከፍ ከፍ አደረገው። ከራሱ ከፈርዖን ቀጥሎ ሁለተኛ ሆነ(ቁ. 37-44)።

### ኢያሱና ካሌብ፡ ደፋር ራእይ

የኢያሱ እና የካሌብ ድፍረት የተሞላበት ራዕይ ሌሎች በፍርሃት ሲያፈገፍጉ በእምነት እንዲራመዱ አስችሏቸዋል (ዘኍ. 14፡6-9)። ኢያሱና ካሌብ ለፍርሃት ከመሸነፍ ይልቅ በአምላካቸው ላይ ማመንን መረጡ። ህዝቡ የነሱን መሪነት ለመከተል ፈቃደኛ ባይሆኑም ቃላቸውን አክብረው ለአርባ አመታት ራእዩን ጠብቀው ቀጣዩን ትውልድ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገቡ አዘጋጁ።

### ነህምያ፡ የዓላማ አንድነት

ነህምያ በአንድ ዓላማ የእግዚአብሔር ሕዝብ የኢየሩሳሌምን ግንብ እንደገና እንዲገነቡ መርቷል። ይህን ያደረገው ከፍተኛ ተቃውሞ እየገጠመው ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ በሰጣቸው ተልእኮ ላይ ማተኮር ቢችሉ ምን ሊሆን እንደሚችል ባለው ራእይ ተደግፎ ሥራውን ይሰራ ነበር።

### ሃጌ፡ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ አመለካከት

የሃጌ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከራስ ወዳድነት እንዲመለሱና የአምላክን ቤት ሥራ እንዲያስቀድሙ አነሳስቷቸዋል። ሀብታቸውን ሁሉ በማፍሰስ የራሳቸውን ቤት እንዳይገነቡ ጠይቀዋል። ይልቁንም፣ የእግዚአብሔርን ቤት በመገንባት ላይ ያላቸውን መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ነበረባቸው። ነቢዩ የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ ዓላማ ቢንቀሳቀሱ ሥራው እንደሚጠናቀቅ ይነግራቸው ነበር።

### ኢየሱስ፡ ዋንኛ ምሳሌያችን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባለራዕይ መሪ ዋንኛ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ ለምን እንደመጣ፣ ወዴት እንደሚሄድ እና እዚያ ለመድረስ ምን ማድረግ እንዳለበት በግልፅ ተረድቷል። እርሱ ወደፊት የሚሄደውን መንገድ አይቶ ያንን መንገድን ለመከተል ሙሉ በሙሉ ራሱን የመስጠት ፍጹም ምሳሌ ነው (ዕብ. 12፡ 2)። ከዚያም ሌሎችን ወደራሱ ጠርቷል፣ አሰልጥኗል፣ እና በስራው እንዲቀላቀሉት አነሳስቷል።

### ጳውሎስ፡ ሚስዮናዊ ራእይ

ከኢየሱስ ቀጥሎ፣ ጳውሎስ ታላቅ የሚስዮን መሪ ነበር። ጳውሎስ ወንጌልን ወደ አሕዛብ ለማድረስ ሰማያዊ ራእይ የተጠራ ሰው ነበር። ጳውሎስ ራዕዩን ለሌሎች አስተላልፏል። ለስብከተ ወንጌል፣ ለቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ለተልእኮ ሊሆን የሚችል ምሳሌ ትቶአል። በአገልግሎቱ መገባደጃ አካባቢ፣ ጳውሎስ፣ “ከሰማይ ለታየኝ ራእይ አልታዘዝ አላልሁም” (ሐዋ. 26፡19) በማለት መመስከር ችሏል።

# መሪነት ኃይል

እውነተኛ ባለራዕይ መሪ ለመሆን ስለ አመራር ኃይል መሰረታዊ ግንዛቤ ያስፈልግሃል። እናም ባለራዕይ አመራር በተግባር ምን እንደሚመስል በግልፅ መረዳት ያስፈልጋል።

### ተልዕኮ እና ራዕይ

መጀመሪያ፣ በተልእኮ እና በራዕይ መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት አለብህ። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፣ ራዕይ የሚያድገው ከተልእኮ እንጂ በተቃራኒው አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ተወስኗል። የእግዚአብሔር ተልእኮ፣ አንዳንድ ጊዜ ሚሲዮ ዴኢ ተብሎ የሚጠራው፣ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት በምድር ላይ ካሉ ነገዶች፣ ቋንቋ እና ህዝቦች ሁሉ ሰዎችን

መዋጀት እና ለራሱ መጥራት ነው። ኢየሱስ በታላቁ ተልእኮው ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ ተናግሯል፦ "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. 28፡18-20፤ ማር. 16፡15-18፤ ሉቃስ 24፡49፤ ዮሐንስ 20፡21፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡8)። ቤተ ክርስቲያን ያለችው የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም ነው።[1]

ክርስቶስ እያንዳንዱን የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እና ቤተ ክርስትያን በተልእኮው ሙሉ በሙሉ እንዲፈጽሙ አዟል። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን ወስኗል። በመሆኑም፣ ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ስርጭት፣ በደቀ መዝሙርነት እና በቤተ ክርስቲያን ተከላ ላይ በንቃት መሳተፍ አለባት። በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያንን እና ሌሎች ክርስቲያን ሠራተኞችን ለማስነሳት እና ለመላክ ራዕይን መሰነቅ አለባት። እነዚህን ሰራተኞች በጸሎት እና በገንዘብ ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆን አለባት።[2]

ራዕይ ጉባኤው የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም ስላላቸው ሚና ያላቸውን ግንዛቤ ይናገራል። በተፈጥሮው የወደ ፊትን ይመለከታል። በዛሬ ተግባራት ላይ ብቻ ሳይሆን በነገ እድሎች ላይም ያተኩራል። ራዕይ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በሆነችው እና እግዚአብሔር ነገ እንድትሆን በሚፈልገው መካከል ያለውን ልዩነት ያጠባል። ራዕይ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር እርዳታ ምን ልትሆን እንደምትችል በመንፈስ የተቃኘ የአዕምሮ ምስል ነው።

አንተ እና የምትመራው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተልእኮ መቀበል ስትጀምር፣ እግዚአብሔር እንድትፈፅም የሚፈልገውን ራዕይ ይሰጥሃል። ይህ በእግዚአብሔር አነሳሽነት የተገለጠ ራዕይ ከላይ እንደተገለፀው ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ተልዕኮ ጋር ይጣጣማል። የእግዚአብሔርን ተልእኮ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናዊ ዓላማ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግልጽ የሆነ መረዳት እንዲኖርህ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለዚህ ነው። ከተልእኮው ውስጥ ራዕይ ይወጣል። ከራዕይ ግቦች ይወለዳሉ። እና ግቦች ወደ ተግባር ይለወጣሉ።

## ራዕይን ማዳበር

ጥሩ ምርት ለማግኘት እርሻ መልማት እንዳለበት ሁሉ በመለኮታዊ መንፈስ የተነደፉ ስትራቴጂዎችን ለመፍጠር ራዕይን ማዳበር ያስፈልጋል። በሚከተሉትን ሶስት ስልቶችን በመተግበር ራዕይን በራስህ ልብ እና በቤተ ክርስትያን ውስጥ ማዳበር ትችላለህ።

**1. የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ።** በመጀመሪያ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ አማካኝነት ራዕይን በልብህ ማዳበር ትችላለህ። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማራመድ የተጠቀመባቸውን የታላላቅ መሪዎች ታሪኮችን በጸሎት ማንበብ ጠቃሚ ነው። ስታነብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ፦

---

[1] ስለ ሚስዮናዊ ራዕይ፣ ምዕራፍ 31ን "ሚሲዮናዊ አመራር" የሚለውን ተመልከት።

[2] ቤተ ክርስቲያናችሁን ለተልእኮ ስለማንቀሳቀስ ለበለጠ፣ ምዕራፍ 40ን "የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዎችን ፕሮግራም ማዳበር" የሚለውን ተመልከት፡

- እግዚአብሔር በዚህ መሪ ልብ ውስጥ ምን ራእይ አስቀመጠ?
- ይህ መሪ ራዕዩን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?
- ራእዩን ለመፈጸም እርሱ ወይም እርሷ እንዴት እርምጃ ወሰዱ?
- በዚህ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ምን እያለኝ ነው?

መልሶችህን በማስታወሻ ደብተር ውስጥ ፃፍ እና በጸሎት በልብህ አሰላስል። ከጊዜ በኋላ ከእነዚህ ሐሳቦች ውስጥ ስብከቶችን ማዘጋጀትና ለጉባኤ ማካፈል ያስፈልግ ይሆናል። በዚህ መንገድ፣ አንተ እና ጉባኤው የእግዚአብሔርን ተልእኮ እና ያን ተልእኮ ለመፈጸም ያላችሁን ሚና በመረዳትህ ውስጥ አንድ ዓይነት አመለካከት ይኖራችሁል።

**2. እግዚአብሔርን መጠበቅ።** ሁለተኛ፣ እግዚአብሔርን በጸሎት በመጠባበቅ በልብህ ውስጥ ራዕይን ማዳበር ትችላለህ። ከልብ የሆነ በምስጋና ወደ እርሱ በመቅረብ ጀምር (ያዕቆብ 4፡8)። አንዴ የእግዚአብሔርን መገኘት ከተረዳህ፣ "ጌታ ሆይ፣ ፈቃድህን አሳየኝ፣ የልብህን ሃሳብ እንዳገኘው ፍቀድልኝ ብለህ መጸለይ አለብህ። ከዚያም በመንፈስ መጸለይ እና ድምፁን በመስማት በእግዚአብሔር ፊት መቆየት አለብህ (ሮሜ 8፡26-27፤ ኤፌ. 6፡18)።

በዚህ መንገድ ስትጸልይ፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ልብህ ወይም አእምሮህ የሚያኖራቸውን ተደጋጋሚ ሀሳቦችን ወይም ግንዛቤዎችን ልብ በል። በጊዜ ሂደት፣ ከእነዚህ ግንዛቤዎች ውስጥ አንዳንዶቹ የበለጠ እና የበለጠ ግልጽ እየሆኑ ይሄዳሉ። በመጨረሻ ወደ ሸክም ያድጋሉ። ከሸክሙ ጋር እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በተወሰነ አቅጣጫ እየመራ እንደሆነ ጥልቅ መረዳት ይመጣል (ኢሳ. 30፡21)። በተጨማሪም ጉባኤውን ጌታን ምሪት ወደ መፈለግ መምራት ያስፈልግህ ይሆናል።

**3. ፍላጎትን መመልከት።** በመጨረሻም፣ በአካባቢህ ወይም በሌላ ቦታ ያሉ የሰዎችን ፍላጎት በመመልከት ራዕይን ማዳበር ትችላላችሁ (ዮሐ. 4፡35)። ስትመለከት፣ እግዚአብሔርን ማስተዋልን ለምን፣ "ጌታ ሆይ፣ የሰዎችን ጥልቅ ውስጣዊ ፍላጎት እንዳላይ እርዳኝ" (2ቆሮ. 4፡18)። በተጨማሪም፣ "ጌታ ሆይ፣ ከእነዚህ ፍላጎቶች ውስጥ የትኛውን ቤተ ክርስቲያናችን እንድታሟላ ትፈልጋለህ?" ብለህ መጸለይ አለብህ። ከጸለይክ በኋላ በጸጥታ የእግዚአብሔርን ምላሽ አድምጥ።

## የመንፈስ ቅዱስ ሚና

የምንኖረው እግዚአብሔር መንፈሱን በሰዎች ሁሉ ላይ ባፈሰሰበት በመጨረሻው ዘመን ነው (ሐዋ. 2፡17-18)። እግዚአብሔር መንፈሱን የሰጠን ኃይል እንዲሰጠን እና በሥራው እንዲመራን ነው። እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መሪ፣ በማንኛውም ጊዜ በመንፈስ አመራር ላይ ጥገኛ መሆን አለብህ። የወቅቱ የአመራር ቴክኒኮች እና የቤተ ክርስቲያን የዕድገት ስልቶች የራሳቸው ቦታ ቢኖራቸውም፣ በነዚህ በሰው የተዘየዱ አካሄዶች ላይ በፍጹም መታመን የለብህም። ባለራዕይ መንፈሣዊ መሪ እንደመሆኑ፣ የዘካሪያስን ቃል በማስታወስ ሁል ጊዜ የመንፈስን ምሪት መፈለግ እና ምሪቱን መከተል አለብህ፣ "'በመንፈሴ እንጂ በኀይልና በብርታት አይደለም' ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" (ዘካ. 4፡ 6)።

## ራዕይ መውሰድ

በግልህ ራዕይ መኖሩ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ራዕዩን ለራስህ መያዝህ ግን በቂ አይደለም። ያንን ራዕይ ለቤተ ክርስቲያን ማስተላለፍ መቻል አለብህ። እና የእግዚአብሔርን ህዝብ እንዲከተሉ በሚያነሳሳ መንገድ ልታደርገው ይገባል። ይህ ሂደት ራዕይ ማጋራት በመባል ይታወቃል። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፈፀመው አብዛኛው ሥራ ራዕይን ማጋራትን ያካትታል። ያለማቋረጥ ራዕዩን ለእነርሱ እያካፈለ

እንዲከተሉት ያደርግ ነበር። በተመሳሳይ፣ ራእይህን ለቤተ ክርስቲያን ማሳወቅ እና አባላትን "እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል እናንተም የእኔን ተከተሉ" ብሎ መጥራት አስፈላጊ ነው (1ቆሮ.11፡1)።

ይህ እንዲሆን ራዕዩ የህዝቡን ምናብ ማስፋት አለበት። ራዕዩ ፈታኝ እና ሊደረስበት የሚችል መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር ራዕዩ ከልክ በላይ ሰፊ መሆን የለበትም። ይህ ከሆነ ሕዝብን ያስጨንቃል። በተቃራኒው የሕዝብን መነሳሳታቸውን እስኪያወርድ ድረስ በጣም ጠባብ መሆን የለበትም። ራዕዩ ህዝቡ ለመተግበር በጣም ሰፊ ከሆነ፣ ፓስተሩ ለሥራ አመቺ ወደሆኑ ክፍሎች መከፋፈል አለበት። ይሄውም ሊደረስባቸው የሚችሉ የአጭር ጊዜ እና የረዥም ጊዜ ግቦች መቅረጽን ይጠይቃል።

አንዳንድ ጊዜ ራዕዩን በደረጃ ማስተዋወቅ ብልህነት ነው። በመጀመሪያ፣ ራእዩን ከትዳር ጓደኛህ ወይም ከጓደኞችህ እና ከታመኑ መሪዎች ጋር መጋራት ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ መወያየት፣ መጸለይ እና መቀጠል እንዳለብህ ከመንፈስ ምስክር ማግኘት ትችላለህ። በመቀጠል፣ ራእዩን ከቤተክርስቲያኑ ቦርድ እና ሰራተኞች ጋር በማካፈል ራዕዩን እንዲገዙት ማድረግ ያስፈልጋል። ራዕይን ለመተግበር ቡድን መመስረት ይጠይቃል። ስለዚህ ሁሉም ወሳኝ አባላት በቡድኑ ውስጥ መሆናቸው አስፈላጊ ነው።

ራዕዩን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ለመካፈል ጊዜው ሲደርስ፣ "የራዕይ ለማከፈል አንድ ሰንበት መለየት ያስፈልጋል። ይህ ክስተት ራዕዩን ለህዝቡ በግልፅ ለማስረዳት መድረክ ይፈጥራል። ከዚያም ስለ ራእዩ ማውራት እና በየጊዜው መስበክ አለብህ። ይህ አቀራረብ በሰዎች ልብ ውስጥ ራዕይን ለመትከል ይረዳል።

በተጨማሪም መላው ቤተ ክርስቲያን ራዕዩን ለማሳካት በአንድነት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ። ራእዩ ተፈጽሞ ለማየት ሁሉም ሰው እንዲሰጥ፣ እንዲሄድ፣ እንዲሰራ፣ እንዲያገለግል እና እንዲሰዋ ማበረታታት አለብህ። በጉዞው ላይ፣ ራእዩ እንዴት እየተፈፀመ እንዳለ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲያካፍሉ የተወሰኑ ግለሰቦችን መጥራት ያስፈልጋል። እነዚህ ምስክርነቶች ህዝቡን ለማነሳሳት እና ቤተ ክርስቲያንን በመንገዱ ላይ ለማቆየት ይረዳሉ።

## እንቅፋቶችን ማሸነፍ

የራዕዩ አተገባበር ሲፈተሽ ልትደነቅ አይገባም። የእግዚአብሔርን ራዕይ ለመከታተል የምትፈልግ ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን እንቅፋት እና የአጋንንት ተቃውሞ ያጋጥማታል። ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ሲጽፍ "ወደ እናንተ ለመምጣት ፈልጌ ነበር፤ … ነገር ግን ሰይጣን አዘገየኝ" (1 ተሰ. 2፡18)። እንዲህ ያለው ተቃውሞ የቤተ ክርስቲያንን እድገት ለዘለቄታው ሊያቆመው አይችልም። ለአንተ እና ለቤተ ክርስቲያን ራእዩን አጥብቀህ እንድትይዝ ግን አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር በሰጠህ ራእይ ላይ አተኩረህ ከቀጠልክ፣ እርሱ ወደ ተግባር ያደርሰዋል። ኢየሱስ፣ "ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም" (ማቴ. 16፡18) ሲል ቃል ገብቶል።

---

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ በተነገረው ታሪክ ውስጥ፣ መጋቢ ኢማኑኤል እግዚአብሔር ለሰጠው ራዕይ ታማኝ ነበር። በታዛዥነት እና በእምነት ራእዩ እስኪፈጸም ድረስ ጸንቷል። ለአንተም ተመሳሳይ ነገር ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔርን ራዕይ ለቤተ ክርስቲያንህ ምን እንደሆን ካወቅህ እና በአስቸጋሪ ወቅቶች ውስጥ የምትገፉ ከሆነ፣ የራእይህን ፍፃሜ ማየት ትችላለህ። አምላክ ለዕንባቆም የገባውን ተስፋ በልበ ሙሉነት መናገር ትችላለህ፦ "ራእዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና…የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤ በርግጥ ይመጣል፤ ከቶም አይዘገይም" (ዕብ. 2:3)።

# ~ ምዕራፍ 31 ~

# ተልዕኮ መር አመራር

አንድ ቀን ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ እየተራመደ ነበር። በዚያም ጴጥሮስና እንድርያስ መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አገኛቸው። “ተከተሉኝ፤ ሰው አጥማጆች አደርጋችኋለሁ” አላቸው። መጽሐፍ ቅዱስ “ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት” (ማር. 1፡16-18) ይላል። ሰዎች በተፈጥሯቸው ጠንካራ የተልእኮ ስሜት ባላቸው መሪዎች ይሳባሉ። ጴጥሮስና እንድርያስ ኢየሱስን ለመከተል እንደተነሳሱ ሁሉ ብዙ ሰው ጠንካራ የተልእኮ ስሜት ያውን መሪ ለመከተል ይነሳሳል ነበር።

ይህ ምዕራፍ በጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሚሲዮናዊ መሪነት ሚናው ላይ ያተኩራል። የእግዚአብሔርን ተልእኮ በምድር ላይ እንዲያገለግሉ ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ሃላፊነቱን ይወያያል። በዚህ ታላቅ አላማ ውስጥ ሌሎች እንዲከተሏቸው እንዴት ማነሳሳት እንደሚችሉ ይወያያል።

## ሚሲዮናዊው መጋቢ

ኢየሱስ ራሱ የሚስዮናውያን መሪ ስለ ነበረ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ተመሳሳይ የሚስዮናውያን መሪ እንዲሆን ጠርቶል። ኢየሱስ ህዝቡን በተልእኮ ለመምራት የሚያስፈልገው የመንፈስ ቁርጠኝነት እና እምነት የተሞሉ ወንዶችንና ሴቶችን ይፈልጋል (2ዜና. 16፡9)።

### አስፈላጊ ባህሪያት

የሚስዮን መሪዎች ወዴት እንደሚሄዱ ያውቃሉ፣ ደግሞም እንዴት እዚያ መድረስ እንዳለባቸው ያውቃሉ። በመሆኑም፣ ሌሎች በጉዞው ላይ እንዲቀላቀሉአቸው ማነሳሳት ይችላሉ። ሚስዮናዊ መጋቢያን ሦስት አስፈላጊ ባሕርያት አሏቸው፡-

1. ***መረዳት።*** ሚስዮናዊ መጋቢያን የእግዚአብሔርን ተልእኮ የተረዱ ናቸው። እግዚአብሔር ሚስዮናዊ አምላክ እንደሆነ እና በምድር ላይ ካሉት ህዝቦች ሁሉ ሰዎችን ለመቤዠትና ለመጥራት ተልእኮ ላይ እንዳለ ይገነዘባሉ (ማቴ. 24፡14፤ ራዕ. 5፡9፤ 7፡9)። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ሚሲዮ ዴኢ በመባል ይታወቃል፣ እርሱም በላቲን "የእግዚአብሔር ተልዕኮ" ነው። ሚስዮናዊው መጋቢ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተልዕኮ በምድር ላይ ለመፈጸም እንዳለች ተረድቷል። እርሱ ወይም እርሷ እንደ መጋቢነት ከተቀዳሚ ተግባራቸው አንዱ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም ቤተ ክርስቲያንን ማነሳሳት እንደሆነ ይረዳሉ።[1]

2. **ቁርጠኝነት።** የእግዚአብሔርን ተልእኮ ከመረዳት ባለፈ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተክርስቲያኑን በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ተልእኮውን ለመፈጸም በሙላት ለመሳተፍ ቁርጠኛ መሆን አለበት። ይህን ታላቅ ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለበት።

3. **ብቃት።** በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተ ክርስቲያንን የእግዚአብሔርን ተልእኮ እንድትከተል ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉትን አስተሳሰቦች እና ክህሎቶች ለማዳበር ቁርጠኛ መሆን አለበት። እውነተኛው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በመጨረሻ፣ የአገልግሎት ብቃቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ ይገነዘባል (ሐዋ. 1፡8፤ 2ቆሮ. 3፡5-6)።

## የኢየሱስ ምሳሌ

ኢየሱስ ትክክለኛ የሚስዮን መሪ ነበር። ለምን ወደ ምድር እንደመጣ በግልፅ ተረድቷል። ስለመጣበት ምክንያት "የሰው ልጅ የጠፋትን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና" (ሉቃስ 19፡10) በማለት ተናገረ። በሌላ ቦታ ደግሞ "ፈቃዴን ለማድረግ ሳይሆን የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁ" (ዮሐ. 6፡38) በማለት ተናግሯል። ኢየሱስ በአንድ ወቅት ተልእኮውን "ምግብ" ሲል ጠርቶታል (ዮሐንስ 4፡34)። ምግብ ሰውነትን እንደሚያበረታ እና እንደሚያጠነክር ሁሉ፣ ኢየሱስም የአባቱን ፈቃድ በማድረግ ሃይል እና ብርታት ያገኝ ነበር። ይህ ቁርጠኝነት በመጨረሻ ወደ መስቀል አመራው (ማቴ. 20፡28)።

ወደ ሰማይ ከመመለሱ በፊት፣ ኢየሱስ ተልዕኮውን እና አገልግሎቱን ለቤተክርስቲያኑ አስረከበ። ለደቀ መዛሙርቱም "አብ እንደ ላከኝ እኔ እልካችኋለሁ" (ዮሐ. 20፡21) አላቸው። ልክ ኢየሱስ ተልእኮውን በአባቱ ፈቃድ እንደቀዳ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ተልእኮውን የሚቀዳው ከክርስቶስ ፈቃድ ነው። ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ያለው ቁርጠኝነት በተልእኮው እንዲዘልቅ እንደረዳው፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢም በተልእኮው እንዲዘልቅ ይደግፈዋል (ማቴ. 26፡36-44፤ ማቴ. 28፡19-20፤ ዮሐ. 14፡16)))።

## ከማድረግ በፊት መሆን

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የሚስዮናዊ አመራር ከማድረግ በላይ ሆኖ መገኘት መሆኑን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ ለጴጥሮስና ለእንድርያስ፣ "ተከተሉኝ፣ እኔም ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ" አላቸው (ማርቆስ 1፡17)። ኢየሱስን በመከተል እና በመንፈሱ በመሞላት፣ የደቀመዛሙርቱ ማንነት ተለወጠ። እንደ መምህራቸው ሆኑ (ሉቃስ 6:40፤ የሐዋርያት ሥራ 4:13)።

መንፈሱ በኃይል እንዲያገለግሉ ብቻ ሳይሆን፣ ክርስቶስን ለመከተል ያለውን ሸክም ያጋራቸው ነበር። መንፈስ ቅዱስ ምኞታቸው ብቃታቸው እና ችሎታቸው በክርስቶስ ጌትነት ስር እንዲገዛ ረዳቸው።

---

[1] ስለ እግዚአብሔር ተልእኮ ለበለጠ፣ የአፍሪካ ተስፋ ግኝቶች ተከታታይ መማሪያ መጽሀፍ፣ በፖል ዮርክ የተዘጋጀ፣ ከአፍሪካ ቲዎሎጂካል ማሰልጠኛ አገልግሎት (ATTS)፣ www.africaats.org ይመልከቱ።

በመሆኑም የእግዚአብሔርን የማዳን ተልእኮ በመፈጸም ከክርስቶስ ጋር ተባበሩ። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ኃይለኛ መንፈሳዊ ልምምድ ማግኘታቸው ለሚስዮናዊ መሪነታቸው መሰረት ሆነ (ሉቃስ 3፡16፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡4-5)።[2]

ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲሞላን እና በውስጣችን እንዲሰራ ከፈቀድን፣ ወደ ክርስቶስ መልክ ይለውጠናል (2ቆሮ. 3፡18)። መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ የነበረውን የመከሩን ፍቅር ይሰጠናል።

## ሚስዮናዊ መሆን

ጌታ ኢየሱስ ወንዶች እና ሴቶች እንዲከተሉት እና የጀመረውን ስራ እንዲቀጥሉ ጠራቸው። ከዚያም ጊዜውን እና ጉልበቱን በማሰልጠን እና የሚስዮናውያን መሪዎችን በመቅረጽ ላይ አድረገ። ኢየሱስ ይህን ያደረገበት አንዱ መንገድ ለአጭር ጊዜ የሚስዮን ጉዞ በመላክ ነው። አስተምሯቸዋል፣ አስታጠቀቸው፣ ከዚያም ላካቸው (ሉቃስ 9፡1-6፤ 10፡1-16)። ሲመለሱም ስለ ሥራቸው ገለጸላቸው (10፡17-20)።

አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አስቀድሞ መሪዎች አልነበሩም። በሕይወታቸውም ተልእኮ ያላቸው አልነበሩም። ተራ ሰዎች ነበሩ። ሆኖም፣ ሕይወታቸውን በኢየሱስ እጅ ለመቅረጽ ፈቃደኞች ነበሩ። ኢየሱስ በህይወቱ እና በትምህርቱ ዓለም አቀፋዊ ራእይን አሳያቸው። “ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” ብሎ አዘዛቸው (ማቴ. 28፡19)። ልክ እንደ እርሱ፣ እነርሱም በመንፈስ ቅዱስም እንዲታጠቁ አበክሮ ነገራቸው (ሉቃስ 4፡18-19፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡8)።

ጴጥሮስ ከጌታ ጋር በመጀመሪያ ሲገናኝ፣ እራሱን እንደ መሪ አልወሰደም ነበር። ኢየሱስን “ጌታ ሆይ ከእኔ ራቅ። እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ!" አለው (ሉቃስ 5:8) ጴጥሮስ በራሱ ብቁ ሰው እንዳልሆነ ተሰምቶት ነበር። ይሁን እንጂ ኢየሱስ የጴጥሮስን እንዴት አድርጎ ሊለውጠው እንደሚችል ያውቅ ነበር። ስለዚህ ጴጥሮስን መልሶ "ከእንግዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ” አለው (ቁ. 10) ጴጥሮስ ኢየሱስ ለመከተል በመወሰኑ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደምናየው ኃያል ሚስዮናዊ መሪ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- “ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለቱን ሾማቸው፤ ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው” (ማር 3፡14)።

ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሱስ ጋር ጊዜ በማሳለፍ፣ ትምህርቱን በማዳመጥ እና ድርጊቱን በመመልከት እንደ ጌታቸው ሆኑ። ኢየሱስ እያንዳንዳቸውን ልዩ በሆነ መንገድ ሚስዮናውያን መሪዎች አድርጎ ቀርጿቸዋል። ይህን ስላደረገ፣ የመሠረተው ቤተ ክርስቲያን እስከ ዛሬ ቀጥላለች። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ለመሆን የምንመኝ እንደመሆናችን መጠን ውጤታማ ከሆኑ ሚስዮናዊ መሪዎች ጋር ጊዜ ብናሳልፍ ጥሩ ነው። ወደ ኢየሱስ ስንቀርብ እና ተመሳሳይ ነገር ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር ስንውል እንለወጣለን።

የአመራር በትር ተላልፎልናል። እኛም እውነተኛ ሚስዮናዊ መሪዎች ለመሆን መጣር አለብን። እንደ ኢየሱስና ሐዋርያቱ እኛም ሌሎችን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ አለብን። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- “እንግዲህ ልጄ ሆይ፤ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። 2 በብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ” (2 ጢሞ. 2:2)።

---

[2] በመንፈስ ቅዱስ ስለመጠመቅ፣ ምዕራፍ 10፣ 11 እና 20ን ተመልከት።

# ተልእኮ ምኞት

የተልእኮ ተግባር የሚነሳው ከተልእኮ ምኞት ነው። ምኞት ትልቅ ነገርን ለማሳካት ያለ ከፍተኛ ፍላጎት ነው። መዝሙረኛው ስለ እግዚአብሔር ለልጁ እና ለአሕዛብ ያለውን ምኞት ተናግሯል። አብ ወልድን ለምነኝ "መንግሥታትን ርስት አድርጌ፣የምድርንም ዳርቻ ግዛት እንዲሆንህ እሰጥሃለሁ" (መዝ. 2:8)። እንደ እግዚአብሔር ልጆች በዚህ ሚስዮናዊ ጸሎት ከወልድ ጋር መቀላቀል እንችላለን። ይህንን ማድረጋችን ጓደኞቻችን እና ጎረቤቶቻችን ወደ ኢየሱስ ሲመጡ ለማየት ከፍተኛ ፍላጎት ይፈጥርብናል። ከዛም ባለፈ አሕዛብ በክርስቶስ የመዳን ምሥራች ሲደርሱ የማየት ምኞትን ይፈጥርብናል።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የእግዚአብሔርን ምኞት የራሳህ ማድረግ አለብህ። አብርሃምም ያደረገው ይህንኑ ነው። ምንም እንኳ አርጅቶ ልጅ ባይኖረውም እግዚአብሔር “ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት፤ እስቲ መቍጠር ከቻልህ፣ ከዋክብቱን ቍጠራቸው፤ ዘርህም እንዲሁ ይበዛል” (ዘፍ. 15:5) አለው። አብርሃም የእግዚአብሄርን ተስፋ አመነ እናም ፍላጎቱን ተካፈለ። ከመታዘዙ የተነሣ፣ ለሚያምኑ ሁሉ አባት ሆነ (ሮሜ. 4:11)። እግዚአብሔር ለአሕዛብ መዳን መሻት እንዲሰጥህ ለምነው። ከዚያም በዚኅ ስሜት ቤተ ክርስቲያንህን በእግዚአብሔር ተልእኮ ውስጥ እንድትሳተፍ እንድትበረታታ እንድትገፋፋ አድርግ።

# ተልዕኮዊ ተግባር

ለተልእኮ ምኞት አስፈላጊ ቢሆንም፣ ብቻውን በቂ አይደለም። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ምኞቱ ዕውን እንዲሆን መስራት አለብን። ጳውሎስ የዚህ እውነት ምሳሌ ነው። ጳውሎስ አሕዛብ ወደ ክርስቶስ ሲመለሱ የማየት ምኞት ነበረው (ሐዋ. 22:21፤ ሮሜ. 10:1)። ይህ ምኞቱ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ለወንጌል እንዲደክም አስገደደው። እንዲህ ሲል መስክሯል፣ “ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን የሆንሁትን ሆኛለሁ፤ ..ዳሩ ግን እኔ ሳልሆን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው” (1 ቆሮ. 15:10)። በተመሳሳይ መልኩ፣ አንተም ተልዕኮህን ወደ ተግባር መቀየር አለብህ። ቤተ ክርስቲያህን የእውነተኛ ሚስዮናዊት ቤተ ክርስቲያን ለማድረግ መጣር አለብህ።

## የተልእኮዎች እይታን መትከል

የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ዋና ሀላፊነት የጠፉትን በእግዚአብሄር ህዝብ ልብ ውስጥ ፍቅርን መትከል ነው። ሕዝቡ ከቤተ ክርስቲያናቸው ቅጥር ውጭ ያሉትን መጥፋታቸውን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። በአፍሪካ እና በዓለም ዙሪያ ወንጌል ባልተዳረሰባቸው ቦታዎች የሚኖሩትን ህዝቦች መጥፋታቸውን ሊገነዘቡ ይገባል። ይህ እንዲሆን በጉባኤህ ፊት መስበክ፣ ማስተማር እና ተልእኮዎን ሞዴል ማድረግ ይኖርብሃል። እናም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል በሚሲዮ ዲኢ ውስጥ የመሳተፍ ሃላፊነቱን እስኪረዳ ድረስ መጽናት ያስፈልጋል።

የተልእኮ ራዕይ በሁለት መንገድ በእግዚአብሔር ህዝብ ልብ ውስጥ መትከል ይቻላል። ይሄውም በእግዚአብሔር መንፈስ እና በእግዚአብሔር ቃል ነው። ጴጥሮስ ስለ አሕዛብ ያለውን አመለካከት የለወጠው ኃይለኛ የመንፈስ እንቅስቃሴ እና የጌታን ቃል ነበር (ሐዋ. 10:9-16፣ 19-20)። እንደ ሚስዮናዊ መሪ፣ ተመሳሳይ የለውጥ ኃይል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖሩን ማረጋገጥ አለብህ። በአገልግሎትህ ውስጥ መንፈስ በኃይል መንቀሳቀሱን ማረጋገጥ አለብህ፣ እና እያንዳንዱ አባል በመንፈስ መሞላቱን ለማየት መጣር አለብህ። የእግዚአብሔር መንፈስ ለምን እንደሚንቀሳቀስ ለሕዝቡ ማስረዳት አለብህ።

እግዚአብሔር መንፈስ ሚስዮን መር መንፈስ እንደመሆኑ፣ ህዝብን በእግዚአብሔር ተልዕኮ ውስጥ እንዲሳተፉ ያዘጋጃቸዋል።

በተመሳሳይ ጊዜ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ተልዕኮ የሚናገረውን ለሕዝቡ ማስተማር አለብህ። እናም ለመንፈስና ለቃሉ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ልታሳያቸው ይገባል። ለጠፉት ሰዎች በቅንዓት ለመጸለይ፣ ለተልእኮዎው በልግስና ለመስጠት እና ምሥራቹን በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች በታማኝነት ለመካፈል ራሳቸውን መስጠት አለባቸው። በመጨረሻም፣ ለእግዚአብሔር ተልእኮ ራሳቸውን እንዲሰጡ መጠየቅ አለብህ።

እንደ እውነተኛ ሚስዮናዊ መሪ፣ ቤተ ክርስቲያን ከራስ ወዳድነት ሌሎች ተኮር ወደ መሆን፣ ከራስ ፍላጎት በዙሪያቸው በጠፋው ዓለም ፍላጎቶች ላይ ወደ ማተኮር መምራት አለብህ። ይህ ሚስዮናዊ ጉዞ በአንተ በኩል ትኩረት ይጠይቃል። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ላይ ማስተካከያዎችን ማድረግ እና በስብሰባዎች ዓላማ እና ይዘት ላይ ለውጦችን ማድረግን ይጠይቃል።

## የሚስዮናውያን ታሪኮችን ማካፈል

ተልእኮ ያላትን ቤተ ክርስቲያን የምትፈጥርበት አንዱ መንገድ ሚስዮናዊ ታሪኮችን ለጉባኤው በማካፈል ነው። እነዚህን ታሪኮች በስብከትህ እና በአስተምሮህ ውስጥ በማካተት ይህንን ማድረግ ይቻላል። ከእነዚህ ታሪኮች ውስጥ ብዙዎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። የኢየሱስ ታሪክ እስካሁን ከተነገረው ሁሉ የሚበልጠው የሚስዮናውያን ታሪክ ነው። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም በሚስዮናውያን ታሪኮች የተሞላ ነው። እንዲሁም የሚስዮናውያን መጻሕፍትን በማንበብ እና የሚስዮናውያንን ንግግር በማዳመጥ ታሪኮችን መሰብሰብ ትችላለህ። በተጨማሪም፣ የራስህ ታሪክ ለጉባኤው ከመናገር ወደኋላ አትበል።

## የተልእኮ አገልግሎቶችን መርሐግብር ማስያዝ

እንዲሁም ሚስዮናውያን ቤተ ክርስትያንህ እንዲሰብኩ በየጊዜው መርሐግብር ማስያዝ ያስፈልጋል። ወይ ለተልእኮ አገልግሎት ወይም ለተልዕኮዎ ግንዛቤ እንዲሰጡ ቅዳሜና እሁድ እንዲመጡ ልትጋብዛቸው ትችላለህ። ሚስዮናውያን ሲመጡ፣ የጉዞ ወጪያቸውን መሸፈንን መርሳት የለብህም። ጉባኤው በሚስዮናውያን አገልግሎት በመስጠት እንዲካፈሉ እድል መስጠት ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያንም ሚስዮናዊውን ቀጣይነት ባለው መልኩ መደገፍን ማሰብ አለባት።

## "የስኬት ዑደቶች" መፍጠር

በሰዎች ልብ ውስጥ የተልእኮ ራዕይን ለመትከል ሌላው ውጤታማ መንገድ "የስኬት ዑደቶች" ነው። ይህ ሃሳብ የመጣው ከዳዊት ታሪክ ነው። በእስራኤል ላይ ከመንገሡ በፊት ጥቂት የተሳኩ ወታደራዊ ዘመቻዎችን መርቷል። ሕዝቡም "እስራኤልን በውትድርና የመራህ አንተ ነህ" ብለው ዳዊትን አከበሩት (2ሳሙ. 5፡2)። ወይም፣ ቃል በቃል፣ "እስራኤልን የምታወጣ እና የምታገባ አንተ ነህ አሉት። "ማውጣት እና ማስገባት" የሚለው ሐረግ ስለ ስኬት ዑደቶች ይናገራል፣ እና የአጭርና ሊደረስባቸው የሚችሉ የተልእኮ ሥራዎችን የመምራትን ሐሳብ ይጠቁማል። እያንዳንዱ ስኬት ህዝቡ በተከታታይ የበለጠ ግብ እንዲያቀምጥ ያበረታታል።

ለምሳሌ፣ መጀመሪያ ላይ "ለጎረቤቶች የመጸለይ" ዘመቻ ማቀድ ትችላለህ። ጉባኤው የጎረቤቶችን ስም አምጥተው በቤተ ክርስቲያን ይጸልይላቸው። ህዝቡ የጸሎት መልሱን ሲያይ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር አልፈው እንዲሄዱ ይበረታታሉ። ትናንሽ ስኬቶች የበለጠ ሚስዮናዊ ለመሆን ልባቸውን ይከፍታሉ። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በሚሄደው የስኬት ዑደቶች ከራሳቸው አልፈው ብዙዎችን እንዲደርሱ ይበረታታሉ።

እነዚህ ስኬቶች የተልእኮ የገንዘብ ድጋፍ እና ስልጠና እንዲጨምሩ ያደርጋል። ከጊዜ በኋላ፣ ቤተ ክርስቲያን የአጭር ጊዜ ተልእኮ ቡድኖችን ወደ ሌሎች ከተሞችና መንደሮች ለስብከተ ወንጌል እና ለቤተ ክርስቲያን ተከላ ዘመቻ ማሰማራት ትችላለች። አንዳንዶች ሚስዮናውያንን ለመርዳት ወይም አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል ወደ ሌሎች አገሮች ለመሄድ ፈቃደኞች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ቡድኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ እና ሪፖርት ሲያደርጉ፣ ህዝቡ ለተልእኮዎች ተሳትፎ የበለጠ ይነሳሳል።

# የአጥቢያ ተልእኮዎች ቡድን

“በፍጥነት መሄድ ከፈለግክ ብቻህን ሂድ” የሚለውን የድሮውን የአፍሪካ አባባል አስታውስ። ሩቅ መሄድ ከፈለክ ከሰው ጋር ሂድ። በስራው ውስጥ አንተን ለመርዳት የአጥቢያ የሚስዮን ኮሚቴ ወይም የተልእኮ ቡድን መፍጠር ያስፈልጋል። እነዚህ ባለራዕይ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች ቤተ ክርስቲያንን ለተልእኮ እንድታንቀሳቅስ ይረዱሃል።

ሚስዮናዊት ቤተ ክርስቲያን ከእግር ኳስ ቡድን ጋር ሊመሳሰል ይችላል። በዚህ ንጽጽር ውስጥ ፓስተሩ እንደ ኮከብ ተጨዋች ሳይሆን እንደ አሰልጣኝ ይቆጠራል። እና የሚስዮን ቡድን የሰልጣኝ ብድን አካል ነው። የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ደጋፊዎች ሳይሆኑ የሜዳ ላይ ተጫዋቾች ናቸው። የፓስተሩ እና ሚሲዮን ቡድኑ ስራ ተጫዋቾችን መቅጠር፣ ማሰልጠን፣ ማበረታታት እና ለድል መላክ ነው።

ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ከመምረጡ በፊት ሌሊቱን ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ (ሉቃስ 6፡ 12)። በተመሳሳይ መንገድ፣ የተልእኮ ቡድንዎን በጸሎት መምረጥ ያስፈልጋል። ሥራውን ለማሳካት በእምነት እና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎችን፣ ትክክለኛ አመለካከት እና ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መፈለግ አለብህ። ከዚያ ለመጸለይ እና ለማቀድ በየጊዜው ከሚስዮን ቡድን ጋር መገናኘት ይኖርብሃል። ከብድኑ ጋር፣ የቤተ ክርስቲያኗን የስብከተ ወንጌል፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እና የተልእኮ ፕሮግራሞችን ታዘጋጃላችሁ። ስልታዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች መለየት እና የቤተ ክርስቲያኑ ተልእኮ በጀት ታዘጋጃላችሁ።

---

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሊመለስ ሲል፣ በመጨረሻው ትእዛዝ እና የመጨረሻ ትዕዛዝ እና ቃል ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ። ትእዛዙም “ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤5 ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ” የሚል ነበር(ሐዋ. 1፡4-5)። የገባው ቃል “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” የሚል ነበር(ቁ. 8)።

በእነዚህ ቃላት፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በቅርቡ በጴንጤቆስጤ ቀን የሚያገኙት ልምድ አሕዛብን ከመቤዠት ካለው ተልእኮ ጋር በቅርበት እንደሚያያዝ እያሳሰባቸው ነበር። ስለዚህ፣ ጴንጠቆስጤ መሆን ማለት ሚስዮናዊ መሆን ማለት ነው። ስለዚህም እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለመሆን ቀናተኛ ሚስዮናዊ መሪ መሆን አለበት። እንደ ሚስዮናዊ መሪ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተ ክርስቲያኑን ከአካባቢ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ በመንፈስ በታገዘ ተልእኮ እንዲመራ በክርስቶስ ተሹሟል።

# ~ ክፍል 8 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ
# እንደ አስተዳዳሪ

# ~ ምዕራፍ 32 ~

# ሰነዶችን፣ ፋይናንስን እና ንብረትን ማስተዳደር

ኢየሱስ የንብረቱ አስተዳዳሪው ንብረቱን እንደሚያባክንበት ያወቀ አንድ ሀብታም ሰው ታሪክ ተናግሯል። ሃብታሙ ሰው ታማኝ ያልሆነውን ሥራ አስኪያጅ ጠርቶ ሥራውን እንዴት እንዳከናወነ እንዲገልጽ ጠየቀ (ሉቃስ 16፡1-2)።

መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ የእግዚአብሔር ንብረት አስተዳዳሪ እንደሆነ ያስተምራል። ምክንያቱ ደግሞ እርሱ ወይም እርሷ ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ስለሆነ ነው (መዝ. 24፡1፤ ያዕ 1፡17)። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ንብረት እንዴት እንደያዘ እንዲገልጽ አንድ ቀን በፍርድ እንደሚጠየቅ ያስተምራል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል፡- “ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል” (2ቆሮ. 5፡10)።

ይኸው መርህ ለጴንጤቆስጤ መጋቢ ይሠራል። እርሱ ወይም እርሷ የሚመሯት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መሆኗን ማስታወስ አለባቸው። የሚያስተዳድሩት የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ነው ፣ እና አንድ ቀን ንብረቱን እንዴት እንዳስተዳድሩ ለእርሱ መልስ ይሰጣሉ።

## የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደ አስተዳዳሪ

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለነበሩት ክርስቲያኖች “ባለ ዐደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት አለባቸው” ሲል ጽፏል (1 ቆሮ. 4፡2)። እግዚአብሔር የሾመህ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ተመልካች እንደመሆንህ፣ የእግዚአብሔርን ቤት በታማኝነት እና በብቃት ማስተዳደር አለብህ። ይህም የጉባኤውን መንፈሳዊ እና

ጊዜያዊ ጉዳዮችን ያጠቃልላል። ፓስተሩ የህዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት በጥንቃቄ መከታተል አለበት። በተመሳሳይ ጊዜ እርሱ ወይም እርሷ የቤተክርስቲያኑን አስተዳደራዊ ጉዳዮች በታማኝነት መምራት አለበት። ይህ የቤተክርስቲያኑ መዝገቦችን፣ ፋይናንስ እና ንብረቶችን ያጠቃልላል።

ከሐዋርያት፣ ከነቢያት፣ ከመምህራን፣ ከተአምራት እና ከሌሎችም ስጦታዎች ጋር፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የ"መምራት" ስጦታ ሰጥቷታል ወይም አንዳንድ ትርጉሞች እንደተረጎሙት፣ የክርስቶስ አካልን ለማነጽ የሚረዳ "የማስተዳደር" ስጦታ ይሉታል (1ኛ ቆሮ. 12፡28)። ጳውሎስ "ኤጲስቆጶስ የእግዚአብሔር ሥራ ባለ ዐደራ" ሲል ይጠራዋል (ቲቶ 1፡7)። የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በሚገባ ማስተዳደር የፓስተሩ ኃላፊነት ነው። ጳውሎስ ቲቶ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ የበላይ ተመልካች "ቅን፣ ቅዱስና ጠንቃቃ ሊሆን ይገባል" ሲል መጋቢ ምን መሆን እንዳለበት ነገረው (ቁ. 8)። እነዚህ ባህሪያት ሁሉም የአንድ ጥሩ አስተዳዳሪ ባህሪያት ናቸው።

በዚህ ምእራፍ ውስጥ የሚብራሩት አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለአንዳንዶች ተራ እና ከጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጥሪ ጋር የማይገናኙ ቢመስሉም፣ በጣም አስፈላጊ ናቸው። አንድ መጋቢ እነዚህን ጉዳዮች የሚይዝበት መንገድ የእረኝነት አገልግሎቱን በእጅጉ ይነካል። የቤተ ክርስቲያኗን አስተዳደራዊ ጉዳዮች በሚገባ መወጣት ያልቻሉ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን መንፈሳዊ ጉዳዮቿን መቆጣጠር አይችሉም። ጴጥሮስ፣ "እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል" (1 ጴጥ. 4፡10) በማለት አሳስቧል።

ቤተ ክርስቲያን ከድርጅት በላይ ብትሆንም፣ ድርጅት ደግሞ ናት ነው። በአብዛኛው፣ የማንኛውም ድርጅት ስኬት የሚወሰነው በአደረጃጀቱ እና በአስተዳደር ላይ ነው። አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያን አካል እንጂ ድርጅት ስላልሆነች ምንም ዓይነት ድርጅታዊ መዋቅር አያስፈልጋትም ብለው ይከራከራሉ። ይህ አባባል ግማሽ እውነት ነው። እውነት ነው ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካል ሕያው አካል ነች። ይሁን እንጂ ድርጅታዊ ባህሪ የላትም የሚለው ከእውነት የራቀ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እያንዳንዱ ህይወት ያለው ፍጡር በተፈጥሮው የተደራጀ ነው። ለምሳሌ፣ በሰው አካል ውስጥ፣ ጭንቅላት፣ እጆቹ፣ እግሮቹ እና ሌሎችም እንዲሁ ቦታ አላቸው።

ድርጅት ስነ ሥርዓትን ያሳያል፣ እና የተባበረ ጥረትን ያመለክታል። የቤት ዕቃ የጫነ መኪና ጠቃሚ ሀብት ይዞ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ከጭነት መኪናው ላይ ወርዶ በሥርዓት ቤት ውስጥ እስኪቀመጥ ድረስ ንብረቱ ብዙም ጠቃሚ አይሆንም። እንደዚሁም ሁሉ ቤተ ክርስቲያን አቅሟን እንድትጎናጸፍ በጥንቃቄ መደራጀት ይኖርባታል።

እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የአስተዳደር ክህሎቱን ለማዳበር መጣር አለበት። እናም እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የድርጅት ጉዳዮቹን የሚመራበት አሠራር ሊዘረጋ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ስትገነባ እና ስታድግ፣ ድርጅታዊ አወቃቀሯ ይበልጥ የተወሳሰበ እና የመዝገብ አጠባበቅ ስርዓቷ ይበልጥ የተጠናከረ ይሆናል። የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሶስት የአስተዳደር ኃላፊነቶች አሉት፦ (1) የቤተ ክርስቲያንን መዝገቦች መጠበቅ፣ (2) የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ አያያዝ እና (3) የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችን መጠበቅ ናቸው። የዚህ ምዕራፍ ቀሪው ክፍል የእነዚህን መጋቢ ሀላፊነቶች ይመለከታል።

# የቤተ ክርስቲያን መዝገቦችን መጠበቅ

ውጤታማ የሆነው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ትክክለኛ እና ወቅታዊ የሆኑ የቤተ ክርስትያን መዝገቦችን ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን ጊዜ እና ጉልበት ያጠፋል። እነዚህ የተፃፉ መዝገቦች ፓስተሩንና ቤተ ክርስቲያንን ቢያንስ በአራት ጠቃሚ መንገዶች ይጠቅማሉ፡-

በመጀመሪያ፣ በሚገባ የተደራጀ የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት ሲኖር ፓስተሩ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃ በቀላሉ እንዲያገኝ ያስችለዋል። መዝገቦቹ በደንብ የተያዙ ስለሆኑ መረጃው ታማኝ ይሆናል።

ሁለተኛ፣ በሚገባ የተያዙ መዝገቦች ፓስተሩ የቤተ ክርስቲያንን ንብረቶች እንዲያስተዳድር እና እንዲጠብቅ ሊረዳቸው ይችላል። የቤተ ክርስቲያኑ ይዞታ እና የገንዘብ ነክ ጉዳዮች እንደ ህጋዊ ማረጋገጫ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያኑ የመሬት ባለቤትነትን ጉዳይን በጥያቄ ካነሳ ፣ ፓስተሩ በፍጥነት ሰነድ በማቅረብ ጉዳዩን ማረጋገጥ ይችላል።

ሦስተኛ፣ ጥሩ መዝገቦች የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ስለ ቤተ ክርስቲያን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ጥበባዊ ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚያስፈልገውን መረጃ ይሰጣሉ። ለምሳሌ፣ ያለፉትን ዓመታት የነበረን መረጃ በመመስረት፣ ፓስተሩ ወደፊት የቤተክርስቲያኗን እድገት ማቀድ ይችላል። ይህ መረጃ አመራሩ በዕቅድ ዝግጅት እና የሰው ሃይል ፍላጎቶች ላይ ውሳኔዎችን እንዲሰጥ ሊረዳው ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ ባለፉት ዓመታት ምን ያህል ጋብቻዎች እንደነበሩ ከሰነዱ በመመልከት ፓስተሩ በሚቀጥለው ዓመት ምን ያህል ጋብቻ እንደሚፈጽም መገመት ይችላል። እርሱ ወይም እርሷ ስለወደፊቱ አዝማሚያዎችን ለመተንበይ ያለፈውን መረጃ መጠቀም ይችላሉ።

አራተኛ፣ ጥሩ መዝገብ አያያዝ ለፓስተሩ እና ለቤተ ክርስቲያኑ ካለፈው ዘመን ታሪክ ጋር ግንኙነት ይፈጥራል። ለፓስተሩ እና አባላቶቹ ከእነሱ በፊት የነበረውን ነገር ለማወቅ ያስችላል። የታሪክ መዛግብት የቀድሞ አባቶቻቸውን እንዲያደንቁ ይረዳቸዋል፤ እንዲሁም የባለቤትነት ስሜት እና ዘላቂነት እንዲሰማቸው ያደርጋል።

## የመልካም መዝገብ አያያዝ መርሆዎች

እያንዳንዱ መጋቢ የመሪነቱን ቦታ ለተተኪው እንዲያስረክብ የሚጠየቅበት ጊዜ ይመጣል። የታመነው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ለዚህ የማይቀር ክስተት ቤተ ክርስቲያንን ያዘጋጃል። እርሱ ወይም እርሷ ይህን ማድረግ የሚችሉበት አንዱ መንገድ ትክክለኛ የቤተ ክርስቲያን መዛግብትን በመያዝ ነው። ጥሩ የመዝገብ አያያዝ አምስት መርሆዎች አሉት፡-

1. **ትክክለኛ።** ሁሉም መዝገቦች እና ሰነዶች ትክክለኛ መሆን አለባቸው። ስለተፈጠረው ነገር እውነተኛ መረጃን መያዝ አለባቸው።

2. **የተደራጀ።** የቤተ ክርስቲያን መዛግብት በሚገባ የተደራጁ መሆን አለባቸው። በሎጂክ ምድቦች መደራጀት አለባቸው፣ ስለዚህ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለማግኘት ቀላል መሆን ይገባቸዋል።

3. **ወቅታዊ።** መዝገቦች ወቅታዊ መሆን አለባቸው። ሁሉም የገንዘብ ልውውጦች ወዲያውኑ በመዝገብ ላይ መከተብ አለባቸው። እንደ ሕፃን ማስረከብ፣ ጥምቀት እና ሰርግ ያሉ ሌሎች ዝግጅቶች በጊዜ መመዝገብ አለባቸው።

4. **ሙሉ።** የቤተ ክርስቲያን መዛግብት ሙሉ መሆን አለባቸው። ስለ አንድ ክስተት ወይም ግብይት ሁሉም አስፈላጊ እውነታዎች መመዝገብ አለባቸው።

5. **ደህንነቱ የተጠበቀ።** ሁሉም መዝገቦች ከሌቦች እና መጥፎ የአየር ሁኔታ.ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ መቀመጥ አለባቸው።

## ትክክለኛ ቃለ ጉባኤ

የጴንጤቆስጤ መጋቢ ሁሉም ኦፊሴላዊ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ትክክለኛ ቃለ ጉባኤ መያዙን ማረጋገጥ አለበት። ይህም ወርሃዊ የቦርድ ስብሰባዎችን፣ ዓመታዊ የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደራዊ ስብሰባዎችን እና ልዩ ስብሰባዎችን ያጠቃልላል። የእያንዳንዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በተሾመው ፀሐፊ ሊያዙ እና በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ እንዲፀድቁ መደረግ አለባቸው። ከፀደቁ በኋላ በጸሐፊው እና በመጋቢው ፊርማ ተፈርመው ለወደፊት ማጣቀሻ በቤተ ክርስቲያን ማህደር ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

## የክስተቶች ምዝገባ

እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ወቅታዊ የሆነ ክስተቶች መዝግቦ የሚይዝበት መዝገብ መያዝ አለበት። ይህ መዝገብ የቤተ ክርስቲያኑ አባላት፣ የውሃ ጥምቀቶች፣ ሰርግ፣ ሕፃን ለጌታ ማስረከብ እና የቤተ ክርስቲያን የአባላት መገኘትን መዝገብ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

**የቤተ ክርስቲያን አባልነት።** የቤተክርስቲያኑ ክስተቶች መመዝገቢያ የቤተክርስቲያኑ አባላት ዝርዝር ማካተት አለበት። የሁሉም አዲስ አባላት ሙሉ ስም በአባልነት በይፋ ሲቀላቀሉ ወደ ዝርዝሩ መታከል አለበት። ዝርዝሩ የተካተቱበትን ቀን እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ማካተት አለበት። ማንኛውም አባል ሲሞት ወይም ከቤተ ክርስቲያን ሲለቅ እነዚህ ክስተቶች መታወቅ አለባቸው። የአባልነት ሰርተፍኬት ወይም ካርድ ለአዲሶቹ አባላት የአቀባበል ስነ ስርአታቸው አካል አድርጎ መስጠት ጥሩ ነው። የሰርተፍኬቱ ኮፒ በቤተ ክርስቲያን ማህደሮች ውስጥ መቀመጥ አለባቸው.

**የውሃ ጥምቀቶች።** በውኃ የተጠመቁ ሰዎች ስም ዝርዝር ከተጠመቁበት ቀንና ከተጠመቁበት ዕድሜ ጋር የተያያዞ በቤተክርስቲያኑ ክስተቶች መመዝገቢያ መስፈር አለበት። የጥምቀት የምስክር ወረቀት ለእያንዳንዱ ተጠማቂ መሰጠት አለበት።

***ጋብቻ።*** በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተጋቡ ሁሉ በቤተክርስቲያኑ ክስተቶች መመዝገቢያ መዝገብ ማካተት አለባቸው። ይህ መዝገብ የሠርጉን ቀን እና የሙሽራውን እና የሙሽራውን ሙሉ ስም ማካተት አለበት። በዝግጅቱ ላይ በይፋ የተሳተፉትን ሌሎች ሰዎች ዝርዝር ጨምሮ ጋብቻውን ያስፈጸመውን አገልጋይ (ወይም አገልጋዮች) ስም ማካተት አለበት። ፓስተሩ ጥንዶቹ ከጉባኤው ጋር መቀላቀላቸውን በይፋ ያሳወቁበትን ቀን መመዝገብ ሊያስፈልግ ይችላል። ከሠርጉ ሥነ ሥርዓት በኋላ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ለባልና ሚስት መቅረብ አለበት። ፓስተሩ ጋብቻን በሚመለከት ሁሉንም የመንግስት ሕጎች ማክበር አለበት።

**የህጻን ለጌታ ማስረከብ።** የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉትን ሁሉንም የሕፃን ለጌታ ማስረከብ መመዝገብ አለበት። የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ሕፃናትን ባያጠምቁም፣ ሕፃን ለጌታ ማስረከብን ያምናሉ። ሐና ለልጇ ሳሙኤልን መሰጠቷ ለዚህ ተግባር ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል (1ሳሙ. 1:21-28)። ለጌታ ከማስረከብ ሥነ ሥርዓት በኋላ ፓስተሩ የሕፃኑን ሙሉ ስም በክስተቶች መመዝገቢያ ውስጥ፣ ከልጁ ከተወለደበት ቀን እና የክብረ በዓሉ ቀን ጋር መፃፍ አለበት። ዝርዝሩ የአባት እና የእናት ስም፣ የወላጆች አድራሻ እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን ማካተት አለበት። ፓስተሩ ለወላጆች የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት።

**የቤተ ክርስቲያን የአባላት መገኘት።** ፓስተሩ የቤተ ክርስቲያንን ሳምንታዊ የአባላት ክትትል ማድረግ አለበት። ይህ መዝገብ በእያንዳንዱ የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ የሚሳተፉትን ሰዎች ቀን እና ቁጥር፣ የእሁድ ጥዋት የአምልኮ አገልግሎትን፣ የእሁድ ምሽት አገልግሎትን፣ እንዲሁም ማንኛውንም የልጆች፣ የወጣቶች እና የሳምንቱ አጋማሽ አገልግሎቶች ማካተት አለበት። እነዚህ መዝገቦች በመጋቢ ወይም በቤተ ክርስቲያኑ ጸሐፊ ሊቀመጡ ይገባል።

## የስብከት መዝገብ

ከቤተ ክርስቲያን መዝገብ በተጨማሪ የምትሰብኩትን ስብከቶች የግል መዝገብ መያዝ ያስፈልጋል። ስብከት በቀረቡ ቁጥር፣ ትምህርት ስታስተምሩ ወይም በማንኛውም መድረክ በይፋ በተናገርክ ቁጥር ዝግጅቱን በስብከት መዝገብ ውስጥ መመዝገብ ጠቃሚ ነው። በዚህ መዝገብ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቀኑን፣ ዝግጅቱን እና መልእክቱ የቀረበበት ቦታ ማካተት አለበት። በተጨማሪም ስብከት ላይ የዋለውን የቅዱሳን መጻሕፍት ጥቅስ ከመልእክቱ ርዕስ ጋር ማካተት ይኖርበታል። እንዲሁም እንደ ሰዎች ለመልእክቱ የሰጡትን ምላሽ የመሳሰሉ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ማካተት ያስፈልጋል። ይህ መዝገብ መልእክቶችህን እንድትከታተል ይረዳሃል፤ እንዲሁም የስብከት ፕሮግራምህን እንድትገመግም ይረዳሃል። እንዲሁም ለወደፊት ማጣቀሻነት ይውል ዘንድ የስብከት ማስታወሻዎችዎን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

# የቤተ ክርስቲያንን ፋይናንስ ማስተዳደር

የጴንጤቆስጤ መጋቢ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የተያያዙ የገንዘብ ልውውጦች ሁሉ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መዛግብት መያዙን ማረጋገጥ አለበት። ይህ አሰራር የቤተክርስቲያኑ ፋይናንስ ሁል ጊዜ በትክክል መያዙን ያረጋግጣል። እንዲሁም ፓስተሩንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ አላግባብ በመጠቀም ከሚከሰሱት ክስ ለመጠበቅ ይረዳል።

## አቅርቦቶችን መቀበል እና ማስተናገድ

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት በዋነኛነት የሚከፈሉት በአሥራት እና በእሁድ ጠዋት የአምልኮ አገልግሎታቸው በሚቀበሉት መባ ነው። እነዚህ ስጦታዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልማዶች መሠረት ተሰብስበው ፣ ፓስተሩ እያንዳንዱ ገቢ በፍፁም ታማኝነት እና ግልጽነት መያዙን ማረጋገጥ አለበት።

ይህንን ለማድረግ እርሱ ወይም እርሷ መባዎች ሁል ጊዜ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ታማኝ በሆኑ የቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት እንደሚሰበሰቡ እና እንደሚቆጠሩ ማረጋገጥ አለባቸው። መባው ከቆጠሩ በኋላ፣ እነዚሁ ዲያቆናት የገቢ ቅጽ መሙላት አለባቸው። በስጦታ ቅጹ ላይ ቀኑን፣ ቦታውን፣ የተቀበሉት መባ(ዎች) ዓይነት (ወይም ዓይነቶች) እና ገንዘቡን የቆጠሩ ሰዎች ስም እና ፊርማዎች መመዝገብ አለበት። የገቢ ቅጹም የተቀበሉትን እያንዳንዱን አይነት ለመመዝገብ ስፍራ ሊኖሩት ይገባል። ለምሳሌ፣ አንዱ መስመር "አሥራት"፣ ሌላው "መባ"፣ ሌላ "የግንባታ ገንዘብ"፣ ሌላ "ተልእኮዎ" እና የመሳሰሉት ሊይዝ ይችላል። ዲያቆናት የተቀበሉት እያንዳንዱ መባ መጠን በተገቢው ምድብ ውስጥ መቀመጡን ማረጋገጥ አለባቸው።

እነዚህ መባ ፎርሞች በሁለት ቅጂዎች መቅረብ አለባቸው፤ አንዱ ቅጂ ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያዥ ሁለተኛው ደግሞ ለፓስተሩ የሚሆን ነው። ከዚያም ገንዘብ ያዥ ገንዘቡን እንደገና ይቆጥራል እና በቤተ ክርስቲያኑ መዝገብ ውስጥ የተቀበለውን እያንዳንዱን መጠን በተገቢው ምድብ ውስጥ ያስገባል። ከዚያም

እርሱ ወይም እርሷ ገንዘቡን ወደ ባንክ ያስቀምጣሉ (ከተቻለ እያንዳንዱ የገቢ አርዕስት ቤተ ክርስቲያን የባንክ ሒሳብ ሊኖረው ይገባል)። ይህ በማይቻልበት ጊዜ ገንዘቡ በማከማቻ ወይም በተዘጋ ካቢኔ ውስጥ መቀመጥ አለበት።

## የፋይናንስ መዝገቦችን መጠበቅ

የሂሳብ መዛግብት በወረቀት/ ደብተር ወይም በኮምፑተር ላይ ሊቀመጡ ይችላሉ። ኮምፒዩተር ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ ኮምፒውተሮች አንዳንድ ጊዜ ስለሚበላሹ በየሳምንቱ የወረቀት ሪፖርቶችን በፋይሉ ውስጥ ማስቀመጥ ብልህነት ነው። በማንኛውም ጊዜ ገንዘብ ወጪ ገቢ በሚደረግበት ጊዜ፣ ግብይቱ ደረሰኝ ላይ ይመዘገባል። ይህ ደረሰኝ የቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ያዥ በሰነድ መልክ መያዝ ይገባዋ።

እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ገቢ ወጪን ማንበብ እና መተንተን መማር አለበት። ይህ ክህሎት የቤተ ክርስቲያኑን የፋይናንስ ግንኙነት ለመከታተል እና በእያንዳንዱ አካውንት ውስጥ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚገኝ ለማወቅ ያስችለዋል። ይህ አሰራር ፓስተሩ እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥበብ ያለበት የገንዘብ ውሳኔ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። እናም የቤተ ክርስቲያኑ የፋይናንስ መዝገቦች በጥሩ ሁኔታ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል።

## የቤተ ክርስቲያን ገንዘቦችን አወጣጥ

ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ማንኛውም መባ ለተሰጠበት ዓላማ ብቻ መዋል አለበት። ለምሳሌ ለግንባታ ፈንድ የተሰጠውን ገንዘብ ወስዶ ለፓስተሩ መኪና መግዣ መጠቀም ሥነ ምግባር የጎደለው ነው። ገንዘቡ ከአንድ ሰው ወይም ፕሮግራም ወደ ሌላ ሲተላለፍ ደረሰኝ መቀበል አለበት፣ እና ደረሰኙ በትክክለኛው የሂሳብ አያያዝ ለገንዘብ ያዥ መሰጠት አለበት። ሁሉም ደረሰኞች በቤተ ክርስቲያኑ የሂሳብ ሰነዶች ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

## የፋይናንስ ሪፖርቶች

በየወሩ ሂሳብ ሲዘጋ የቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ያዥ ለፓስተሩ እና ለክርስቲያኒቱን አመራር የፋይናንስ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት። ይህ ሪፖርት የቤተ ክርስቲያኒቱን አመራር የወሩን የገቢና የወጪ ሒደት ትክክለኛ ሪከርድ ያቀርባል። ይህም የቤተ ክርስቲያንን ፋይናንስ በተመለከተ ጥበብ ያለበት ውሳኔ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል። ከወርሃዊ የሒሳብ ሪፖርት በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ያዥ ዓመታዊ የሒሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለፓስተሩና ለቤተ ክርስቲያኒቱን አመራር ማቅረብ ይኖርበታል። መጋቢውና የቤተ ክርስቲያኒቱን አመራር በተራው የዓመታዊውን የሒሳብ ሪፖርት ለቤተ ክርስቲያን አባላት በዓመታዊው የጠቅላላ ጉባኤ ጉባኤ ያቀርባሉ።

## በጀት ማውጣት

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ዓመታዊ የቤተ ክርስቲያንን በጀት እንዴት ማዘጋጀት እና መከተል እንዳለበት ማወቅ አስፈላጊ ነው። ይህ አሠራር የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በተሻለ መንገድ እንዲቆጣጠሩ ይረዳቸዋል። በጀት የፋይናንስ እቅድ ነው። ለመጪው አመት የቤተክርስቲያኑ ገቢ ግምት እና ገቢውን ለማከፋፈል እቅድ ማውጣት ያስፈልጋል። ጥሩ በጀት የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ያንፀባርቃል። ለምሳሌ:- አንድ ቤተ ክርስቲያን ለተልእኮዎ እና ለቤተ ክርስቲያን መትከል ቅድሚያ የምትሰጥ ከሆነ፣ በጀቱ ያንን ቅድሚያ የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት። በዚህ መንገድ በጀቱ እንደ ስልታዊ ሚስዮናዊ ሰነድ ሊታይ ይችላል።

የቤተ ክርስቲያንን በጀት ማዘጋጀት ፓስተሩ እና የክርስቲያኒቱን አመራር ባለፉት ዓመታት የቤተክርስቲያኗን የፋይናንስ ግንኙነት እንዲመረምሩ ይጠይቃል። ከዚያም ያንን መረጃ በመጠቀም፣ ቤተ

ክርስቲያኒቱ በሚቀጥለው ዓመት ገንዘቧን እንዴት እንደምታከፋፍል በሚመለከት ስልታዊ ውሳኔዎችን ማድረግ ይችላሉ። ይህ አሰራር የቤተክርስቲያኑ ገንዘቦች በጥቃቅን ነገሮች ላይ እንዳይባክኑ ይረዳል፣ በተቃራኒው በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ትኩረት ያገኛሉ።

በጀቱ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎችን ያቀፈ ነው። አንድ የታቀደው ገቢ እና ለቀጣዩ አመት የታቀዱ ወጪዎች። የታቀደው ገቢ አስራት፣ ልዩ ስጦታዎች እና ሌሎች ምንጮችን ይጨምራል። የታቀዱት ወጪዎች ቋሚ ወጪዎችን (እንደ ደሞዝ፣ የፕሮቪደንት ፈንድ እና የፍጆታ አገልግሎቶች) እና አላቂ ዕቃዎችን (እንደ የቢሮ እቃዎች፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ቁሳቁሶች፣ ማስተዋወቂያዎች እና የግንባታ ጥገና) ያካትታሉ። ቤተ ክርስቲያን ላልተጠበቁ እና ለአደጋ ጊዜ ወጪዎችም በጀት መመደብ አለባት። መጀመሪያ ላይ በጀቱን ማዘጋጀት አስቸጋሪ ይሆናል። ነገር ግን ከሁለት ወይም ሶስት አመታት በኋላ የቤተክርስቲያኑ ገቢ እና ወጪን በታማኝነት ከተከታተለ በኋላ የበጀት አወጣጥ ሂደቱ በጣም ቀላል ይሆናል። ያኔ ለቤተ ክርስቲያን ቀልጣፋ አገልግሎት ትልቅ ሀብት ይሆናል።

# የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችን መጠበቅ

የእግዚአብሔር ንብረቶች ባለአደራ እንደ ሆነ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የበለጠ የቤተክርስቲያኑ ንብረቶች በጥሩ ሁኔታ መያዛቸውን ማረጋገጥ አለብህ። እነዚህ ንብረቶች አስፈላጊ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሰነዶችን እንዲሁም የቤተክርስቲያኑ ሕንፃ፣ ግቢ እና ሌሎች ይዞታዎች ያካትታሉ።

## ህጋዊ ሰነዶችን መጠበቅ

ፓስተሩ የቤተክርስቲያኑ ህጋዊ ሰነዶች በሥርዓት መያዛቸውን እና በአስተማማኝ ቦታ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለበት። ከተቻለ እነዚህ ሰነዶች በካዝና ውስጥ ወይም በባንክ ውስጥ ባለው የደህንነት ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ መቀመጥ አለባቸው። በደህንነት ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ ያሉ እቃዎች ዝርዝር በቤተክርስቲያኑ ማህደሮች ውስጥ መቀመጥ አለበት።

## የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችን መንከባከብ

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ የቤተክርስቲያኑ ህንጻ እና ግቢ በጥሩ ሁኔታ የተጠበቀ መሆኑን የማየት ሃላፊነት አለበት። እርሱ ወይም እርሷ ይህንን ሃላፊነት የሚቆጣጠር የጥገና እና የግቢ ኮሚቴ መሾም ያስፈልጋቸው ይሆናል። ይህ ኮሚቴ የቤተክርስቲያኑ ንብረቶች ለእግዚአብሔር ቤት በሚመች መልኩ እንዲንከባከቡ ያደርጋል። ወለሎች እና ግቢዎች ተጠራርገው ከቆሻሻ የጸዱ መሆን አለባቸው። ግድግዳዎች ቀለም መቀባትና መታጠብ አለባቸው። በር መስኮት በንጽህና እና በጥሩ ሁኔታ መጠበቅ አለበት። የግንባታ እና የግቢ ጥገና ገንዘቦች የቤተክርስቲያኑ የበጀት ወጪዎች አካል መሆን አለባቸው.

የቤተክርስቲያኑ እቃዎች ላይም ተመሳሳይ ነው። የቤተ ክርስቲያን የቤት ዕቃዎች እንደ መድረክ፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ የቢሮ ዕቃዎች እና የድምፅ አውታሮች ንጽህና መጠበቅ እና መጠገን አለባቸው። ጥገና በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ በጊዜ መደረግ አለበት።

# ~ ምዕራፍ 33 ~

# አሳታፊ አመራርን መፍጠር

በአፍሪካ ሕፃናት እግር ኳስ ሜዳ ላይ ሲጫወቱ ማየት ያልተለመደ ነገር አይደለም። አንዳንዶች በእውነተኛ ኳስ ይጫወታሉ። ሌሎች፣ በገጠር አካባቢ፣ በቤት ውስጥ በተሰራ ኳስ አንዳንድ ጊዜ ፕላስቲክ ከረጢቶችን ተጠቅልለው ወደ ኳስ በመቀየር በገመድ ታስሮ ይጫወታሉ። ሲሮጡ፣ሲሳሳቁ እና ለቡድኖቻቸው የሚችሉትን ሲሰሩ ማየት እንዴት የሚያስደስት ነው።

አንዳንድ ልጆች በቡድን ውስጥ ታቅፈው ለመጫወት ዕድለኛ ናቸው። እዚያም የቡድን ስራ እና ፍትሃዊ ጨዋታ እሴቶችን ይማራሉ። የቡድን አባላት እያንዳንዱ ተጫዋች ለቡድኑ ጠቃሚ እንደሆነ ያውቃሉ። ቡድኑ ስኬታማ እንዲሆን እያንዳንዱ ተጫዋች የተቻለውን ማድረግ አለበት። ቢሸነፉም ሁሉም ሰው እርስ በርስ ለመበረታታት ይሰበሰባል። ልጆቹ የቡድኑ ስኬት በአብዛኛው የሚወሰነው በተጫዋቾች አመለካከት እንደሆነ ይማራሉ። ይህ በሜዳው ላይ ያሉትን እና ተቀያሪዎችን ያካትታል። ቤተ ክርስቲያን በአግባብ ከተደራጀ የእግር ኳስ ቡድን ብዙ መማር ትችላለች።

አንድ ሰው በአንድ ወቅት የፕሮፌሽናል የእግር ኳስ ግጥሚያን አስመልክቶ ሲናገር እጅግ እረፍት የሚያስፈልጋቸው ሃያ ሁለት ሰዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በሚያስፈልጋቸው በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የመመልከት ሂደት ነው ሲል ገልጿል። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ይህ ሁኔታ ዛሬ በአፍሪካ የሚገኙ ብዙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናትን ይገልጻል። ጥቂት አባላት የአገልግሎት ሸክሙን ተሸክመው ሲደክሙ አብዛኛው ጉባኤ ግን የሚያበረክተው በጣም ትንሽ ነው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ጥቂት ተጫዋቾች የሚለፉበት ብዙ ተመልካቾች የሚደሰቱበት “የእስቴዲየም ትርኢት” ሆነዋል። ይህ የማይሰራ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ከመሆኑ ባለፈ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በመፈጸም ረገድ የቤተ ክርስቲያንን ውጤታማነት እያሽመደመደ ነው። የትኛውም ቤተ ክርስቲያን እንድትጎለብት ፓስተሩ ምእመናንን ለመንግሥቱ አገልግሎት ማንቀሳቀስን መማር አለበት።

ይህ ምዕራፍ ይህንን ፈተና ያሳያል። በመጀመሪያ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ አሳታፊ አመራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይጥላል። ከዚያም እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ምእመናንን በብቃት በቤተ ክርስቲያን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ለአገልግሎት ማንቀሳቀስ የምትችልበትን ተግባራዊ ምክር ይሰጣል።

# መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል::

ከቤተ ክርስቲያን ጅማሮ ጀምሮ ሐዋርያት ሰውን ሁሉ በመንፈስ ኃይል ለአገልግሎት ማንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑን አይተዋል። ደግሞም ኢየሱስ፣ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ብሎም ነበር (ሐዋ. 1:8)። ይህ ተስፋ ለሐዋርያት ብቻ አልነበረም። ለሁሉም ክርስቲያን፣ አገልጋዬች እና ምዕመናን ነበር። ኢየሱስ ለቤተክርስቲያኑ ያለው እቅድ እያንዳንዱ አባል በመንፈስ እንዲሞላ እና እያንዳንዱም የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም እንዲሳተፍ ነበር።

## የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን

በጴንጤቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ከጀመረ በኋላ፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውጤታማ ለሆነ ስብከተ ወንጌልና ደቀ መዝሙርነት ሥልጠና መደራጀት ጀመረች። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- "ሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት፣ እንጀራውንም በመቍረስና በጸሎት ይተጉ ነበር" (ሐዋ. 2:42)። ከዚያም አክሎ፣ "በየዕለቱ በቤተ መቅደስ በአንድነት እየተገናኙ፣ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በቀና ልብ ይመገቡ ነበር፤47 እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፤ ጌታም የሚድኑትን በቍጥራቸው ላይ ዕለት በዕለት ይጨምር ነበር" (ቁ. 46-47)። እነዚህን በፍጥነት የሚያድጉ የቤት ቡድኖችን ለመንከባከብ መሪዎች ያስፈልጉ ነበር። ሐዋርያት ከእነዚህ አዳዲስ አማኞች መካከል አንዳንዶቹን ለአመራር እና ለአገልግሎት ማሰልጠን ጀመሩ።

ቤተክርስቲያኑ እያደገች እና እየበለጸገች ስትሄድ ሌሎች ወደ አመራር ቡድኑ መቀላቀል ጀመሩ። እነዚህ ወንዶችና ሴቶች በሐዋርያት ሥር ሆነው ያገለግሉና በሥራቸውም ይረዷቸው ነበር። ዛሬ እነዚህን ሰዎች ዲያቆናት እንላቸዋለን። ሐዋርያት እነዚህ ከምእመናን የወጡ መሪዎችን በመንፈስና በጥበብ የተሞሉ መሆን እንዳለባቸው ገልፀው ነበር። ሥራቸው ወደ ጌታ ለመጡ ግሪክኛ ተናጋሪ መበለቶች የምገባ ፕሮግራም ማደራጀት ነበር (ሐዋ. 6:1-7)። ሌሎች ፍላጎቶች ሲነሱ የእነዚህ ሰዎች ኃላፊነት እንደተቀየረ ምንም ጥርጥር የለውም። ከመካከላቸው ቢያንስ ሁለቱ እስጢፋኖስና ፊልጶስ የወንጌል ሰባኪዎች ሆነዋል።

ከዓመታት በኋላ፣ የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት ከዳበረ በኋላ፣ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያንን አመራር መዋቅር ለኤፌሶን ሰዎች አብራራላቸው። ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በሐዋርያት፣ በነቢያት፣ በወንጌላውያን፣ በመጋቢያን እና በአስተማሪዎች ነው (ኤፌ. 4:11)። ይሁን እንጂ እነዚህ መሪዎች ብቻቸውን አገልግሎት መስጠት አልነበረባቸውም። ሥራቸው "የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ሥራ ማስታጠቅ" ነበር (ቁ. 12)። ለሥራው እንዲረዷቸው ከምእመናን የወጡ መሪዎችን መመልመል ነበረባቸው። ይህን ቢያደርጉ፣ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ እና ውጤታማ እንደምትሆን እሙን ነው (ቁ. 11-16)።

## የሁሉም አማኞች ክህነት እና ነቢይነት

መጽሐፍ ቅዱስ "የአማኞችን ሁሉ ክህነት" ያስተምራል። ይህ ማለት እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ በእግዚአብሔር ፊት ካህን ነው ማለት ነው። እንደ ካህን፣ እርሱ ወይም እርሷ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ እና የመተርጎም እና የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሌሎች የመካፈል መብት አላቸው (1 ጴጥ. 2:5፣

9)። መጽሐፍ ቅዱስ "የአማኞችን ሁሉ ነብይነት" በተጨማሪ ያስተምራል። ይህ ማለት ዳግመኛ የተወለዱ እና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ቀን ትንቢታዊ ማህበረሰብ አካል ነው (ዘኁ. 11፡29፤ ኢዩኤል 2፡28-29፤ ሐዋ. 2፡17-18)። እግዚአብሔር መንፈሱን በመስጠት፣ "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳም ሁሉ፣ በሰማርያ፣ እስከ ምድር ዳርም ድረስ" (የሐዋርያት ሥራ 1፡8) የክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ ኃይል ሰጥቷቸዋል።

በጴንጤቆስጤ ዕለት፣ ጴጥሮስ ስብከቱን የጀመረው "ይህ [የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ] በነቢዩ ኢዩኤል የተናገረው ነው፡-"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው ቀን፣ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ጕልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ" (ሐዋ. 2፡16-17)። ጴጥሮስ ስብከቱን ሕዝቡን በማዘዝ ነበር የጨረሰው። "ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። ከዚያም ጴጥሮስ አስደናቂ የሆነ ተስፋ ሰጥቷል፡- "የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፣ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና" (ቁ. 38-39)። ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመንፈስ ኃይል ታጥቀው የሚያገለግሉበት ቀን ደርሷል እያለ ነበር።

የመንፈስ ኃይል መሰጠት ሁሉም ሰዎች ምንም ያህል ዝቅ ያሉ ወይም የተገለሉ ቢሆኑም፣ ክርስቶስን ለመናገር እና ለማገልገል ብቁ ያደርጋቸዋል። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ይህንን እውነታ ሊገነዘበው ይገባል፣ እና እርሱ ወይም እርሷ ህዝባቸውን በመንፈስ እንዲታጠቁ እና በቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታት አለበት።

# የተደራጁ መሪዎች ፍላጎት

ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ እንድታድግ እና እንድትጠነክር፣ ጠንካራ የመጋቢ አመራር እና ጠንካራ የምእመናን አመራርም ሊኖራት ይገባል።

ዛሬ በአፍሪካ ውስጥ ባሉ ብዙ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ፊት ለፊት ያለው ወሳኝ ፈተና አብዛኞቹ አባላት በበቂ ሁኔታ ደቀ መዝሙር አለመሆናቸው ነው። ይህም ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ አዳክሟል። ህዝቡ በአግባቡ ስላልሰለጠነ መጋቢያን በሌሎች ሊሰሩ የሚገባቸውን ተግባራት እያከናወኑ ነው። በዚህ ምክንያት መጋቢያን በትናንሽ ሥራዎች በጣም የተጠመዱ ስለሚሆኑ ትልልቅ ሥራዎችን በብቃት ለመወጣት ጊዜም ጉልበታቸውም የላቸውም።

የዮቶርና የሙሴ ታሪክ ይህንን ነጥብ ያሳያል (ዘጸ. 18፡13-16)። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት አውጥቶ ነበር። ከዛም ክርክራቸውን ለመፍታት ወደ እርሱ ይመጡ ነበር። ሙሴም ከማለዳ ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ እየፈረደላቸው ተቀመጠ። ይህ ከቀን ወደ ቀን ቀጠለ። ከጊዜ በኋላ ሙሴ ደከመ።

የሙሴ አማች ዮቶር የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ፣ ሙሴን እንዲህ ብሎ መከረው፣ "የምትሠራው መልካም አይደለም።18 አንተና ወደ አንተ የሚመጡት እነዚህ ሰዎች የምታደርጉት ነገር ቢኖር ራሳችሁን ማድከም ነው፤ ሥራው ለአንተ ከባድ ሸክም ነው፤ ብቻህን ልትወጣው አትችልም" (ቁ. 17-18)። ዮቶርም ሙሴን እንዲህ አለው፡- "ከሕዝቡ ሁሉ ብቁ ሰዎችን ምረጥ.... ያቀልሉሃልና" (ቁ. 21-22)። ሙሴ የዮቶርን ምክር ተከተለ። በውጤቱም፣ ህዝቡ በተሻለ ሁኔታ ተገለገለ እና ሙሴም እረፍት አገኘ።

እንደ ጥበበኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተም እንዲሁ ማድረግ አለብህ። ለሥራው እንዲረዱህ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውን ወንዶችና ሴቶች መምረጥ አለብህ። ከዚያም እነርሱን ማሰልጠን እና ስራቸውን እንዲያከናውኑ መሾም አለብህ። ይህን ካደረክ ከቤተ ክርስቲያን የዕለት ተዕለት ተግባራት ነፃ ትሆናለህ። አንተ ብቻ ልታደርገው በሚገቡት ተግባራት ላይ ማተኮር ትችላለህ፡፡ በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ታድጋለች እንዲሁም ትበለጽጋለች።

## የትኩረት ለውጥ

ይህንን ለማድረግ የትኩረት አቅጣጫ መቀየር ያስፈልጋል። እራስህን እንደ ኮከብ ተጫዋች ከማየት እንደ አሰልጣኝ ማየት መጀምር አለብህ። ስራህ ብዙ ግቦችን ማስቆጠር ሳይሆን ህዝቡን እንዴት ጎል ማስቆጠር እንዳለበት ማስተማር ነው። የአንተ ሥራ ሕዝቡን ሁሉ መምከር ሳይሆን ሕዝቡ ሁሉ ጥበብ ያለበት ምክር ሲቀበሉ ማየት ነው (ዘጸ. 18፡21-22)። የአንተ ሥራ ሁሉንም የግሪክ መበለቶችን መመገብ አይደለም፣ ነገር ግን ሁሉም የግሪክ መበለቶች በትክክል መመገባቸውን ማየት ነው (ሐዋ. 6፡1-3)። በሌላ አነጋገር፣ እንደ መጋቢ፣ የአንተ ሥራ "የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ሥራ ማስታጠቅ ነው" (ኤፌ. 4፡11-12)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎትህ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አባላትን ለአገልግሎት ማስታጠቅ መጀመር አለብህ። የቤተክርስቲያኑ የምእመናን አመራር ቡድን ደቀ መዛሙርት ከሚሆኑት ውስጥ ይወጣል።

## የምእመናን አመራር ቡድን ማንቀሳቀስ

እንደ መጋቢ፣ መሪዎችን ወደ አገልግሎት መለየት፣ ማሰልጠን እና መቀላቀል አለብህ። የቤተ ክርስቲያን አባላት ለእግዚአብሔር መንግስት አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የተለያዩ ስጦታዎች እና ክህሎት ያላቸው የቡድኖች ስብስብ አድርገህ ልታያቸው ይገባል። ቡድኑ ስኬታማ እንዲሆን እያንዳንዱ ተጫዋቾች የድርሻውን መወጣት አለበት። ምእመን መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የትኛውንም አገልግሎት የመሪነት ሚና የሚጫወት ሰው ነው። ይህ ዲያቆናት፣ ሽማግሌ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተባባሪ እና አስተማሪዎች፣ የሕዋስ ቡድን መሪዎች፣ የወንዶች እና የሴቶች አገልግሎት መሪዎች፣ የወጣቶች መሪዎች፣ የህጻናት አገልግሎት ዳይሬክተሮች፣ የመዘምራን ዳይሬክተሮች፣ የአምልኮ ቡድን መሪዎች፣ የተልእኮ ኮሚቴ አባላት እና ሌሎችንም ይጨምራል።

# ለምዕመናን መሪዎች መስፈርት

እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ለማገልገል ሲጠራ፣ በራሱ ብቁ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ሆኖ ለማገልገል፣ የአንድ ሰው ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከተቀመጠው መስፈርት ጋር መስማማት አለበት። ጳውሎስ ስለ ዲያቆናት ሲናገር፡- "እነርሱም አስቀድመው ይፈተኑ፤ ከዚያም፣ አንዳች ነቀፋ ካልተገኘባቸው በዲቁና ያገልግሉ" (1ጢሞ. 3፡10)።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሐዋርያት ለምእመናን መሪዎች ሁለት መሠረታዊ መመዘኛዎችን አስቀምጠዋል፡ "በመንፈስና በጥበብ የተሞሉ" (ሐዋ. 6፡3)። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3 እና ቲቶ 1፣ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች መመዘኛዎችን ዘርዝሯል። አብዛኛዎቹ እነዚህ መመዘኛዎች ከመጋቢያን እና ከሽማግሌዎች ጋር የተያያዙ ቢሆኑም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ማንኛውንም የመሪነት ሚና ለመመዘን አሁንም ጠቃሚ ናቸው።

ከእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎችን ስንሾም ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸውን አምስት ምድቦች ልንወስድ እንችላለን። እነዚህ አምስት ምድቦች (1) የእጩዎች ሥነ ምግባራዊ

ባህሪ፣ (2) መንፈሳዊ ልምዳቸው፣ (3) ባህሪያቸው፣ (4) የእለት ተእለት ባህሪያቸው እና (5) በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ምስክርነት ናቸው። ፓስተሩ አመራርን መሾም ያለበት በመንፈስ የተሞሉ፣ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ፣ ቁርጠኝነት ያላቸው፣ ሊማሩ የሚችሉ እና በመጋቢ መሪነት ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑትን ብቻ ነው።

# መሪዎችን ከሕዝብ መመልመል እና ማሰልጠን

የእግር ኳስ አሠልጣኝ ብቃት ያላቸውን ወንዶች ወይም ሴቶች በቡድኑ ውስጥ እንደሚፈልግ ሁሉ፣ እግዚአብሔር የሾመው የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደመሆንህ፣ አንተም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለመምራት ብቁ ግለሰቦችን መፈለግ አለብህ። ብቁ መሪዎች ከሌሉ እነርሱን ማሳደግ አለብህ። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ አብቅቷል ጳውሎስ ደግሞ ከጢሞቴዎስ፣ ከቲቶ እና ከሌሎችን አብቅቷል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምእመናን መሪዎችን ለማፍራት እነዚህን ሁለት ክፍሎች እንመልከት፡ ሠራተኞችን መመልመል እና መሪዎችን ማሰልጠን።

## ሠራተኞችን መመልመል

ምእመናንን የመመልመል ሂደት በቤተክርስቲያኒቱ ነባር መሪዎች መካከል ብዙ ውይይት ይጠይቃል። እንዲሁም እግዚአብሔርን ምሪት ለማግኘት ብዙ ጸሎትን ይጠይቃል። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። በአገልግሎቱ በሙሉ፣ ያለማቋረጥ የአባቱን መመሪያ ይፈልግ ነበር (ሉቃስ 5፡16)። ለምሳሌ፣ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ከመምረጡ በፊት “ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ፣ ሌሊቱንም ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ” (6፡12)።

አንዴ ከጌታ መመሪያ ከተቀበልክ፣ ስራውን ለማከናወን የትኞቹ ሰራተኞች እንደሚያስፈልጉ መወሰን አለብህ። ከዚያም ራእዩን ለጉባኤው ማካፈል እና ፈቃደኛ ሠራተኞችን መጠየቅ መጀመር አለብህ። በጎ ፈቃደኞችን በምትጠይቅበት ጊዜ ለሥራው ስልጠና ለመስጠት ቃል መግባቱ አስፈላጊ ነው። ይህ ብዙ ሰዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታታል። ብዙውን ጊዜ መሪዎች የሚገኙት ከበጎ ፈቃደኞች መካከል ነው። “በዚህ ቡድን ውስጥ የመሪነት አቅም ያለው ማን ነው?” በማለት እራሀን ሁል ጊዜ መጠየቅ አለብህ። የተወሰኑ ግለሰቦችን በግል ለመቅረብ እና የተወሰነ የመሪነት ሚና ስለመሟላት ከእነርሱ ጋር መነጋገርም ጠቃሚ ነው።

## የአመራርን ክህሎት መኀልበት

አቅም ያላቸው መሪዎች ከተለዩ በኋላ መኀልበት አለባቸው። ይህ የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሃላፊነት ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ ጳውሎስ የመጋቢው ሥራ “የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት” (ኤፌ. 4፡12) እንደሆነ አመልክቷል። ይህንን በሦስት መንገዶች ማድረግ ይችላሉ፡-

**1. በስራ ላይ ስልጠና።** የዚህ አይነት የአመራር ስልጠና የስራ ልምምድ ወይም በሥራ ላይ ስልጠና በመባልም ይታወቃል። ፓስተሩ አቅም ያለውን መሪ ልምድ ካለው መሪ ጋር ያጣምራል። ልምድ ያለው መሪ አዲሱን መሪ በእይታው ስር አድርጎ አንድን አገልግሎት እንዴት እንደሚመራ ያስተምረዋል።

**2. ሴሚናሮች።** አዳዲስ መሪዎችን ለማሰልጠን አልፎ አልፎ ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፖችን ወይም ወጣ ብሎ ልምድ መውሰድ ይጠይቃል።

**3. የስልጠና ግንኙነት።** የተለየ ተስፋ ያየህባቸውን ጥቂቶችን ምልምል መሪዎችን በግል መያዝ ያስፈልግህ ይሆናል። ይህንን ለማድረግ ከእነዚህ ተስፋ ሰጪ መሪዎች ጋር ስለ አገልግሎት በማስተማር ጊዜ ማሳለፍ ይገባል። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያደረገው ይህንኑ ነው (ዮሐንስ 3፡22)። ከእነርሱ ጋር ጥልቅ ግንኙነት መሠረተ፣ ጊዜና ሕይወቱን እነርሱን በመገንባት ላይ አዋለው ። እነርሱም ከጊዜ በኋላ እርሱን መምሰል ጀመሩ (ሐዋ. 4፡13)። ኢየሱስ " በሚገባ የተማረ ሰው ሁሉ እንደ መምህሩ ይሆናል" (ሉቃስ 6፡40) ሲል ገልጿል።

# የቡድን መንፈስን ማዳበር

ቤተ ክርስቲያን እንዲከናወንላት በሕዝቡ መካከል የአንድነትና የጋራ ዓላማ ሊኖር ይገባል። ህዝቡ ከራሱ በላይ ትልቅ ለትልቅ አላማ እንደተሰለፉ ሊሰማቸው ይገባል። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ታላቅ የማዳን ተልእኮ አካል እንደሆነች እና ተልእኮውን በመፈፀም ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚጫወቱ ማመን አለባቸው።

ይህ በተለይ ከምዕመናን ለሚፈሩ ምእመናን መሪዎች እውነት ነው። የአቅማቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ፣ የቡድኑ አካል እንደሆኑ ሊሰማቸው ይገባል። ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ባልደረቦቻቸው ጋር አብረው እንደሚንቀሳቀሱ ሲሰማቸው መልካም ፍጻሜ ላይ ይደርሳሉ። እንደ መጋቢ፣ በመሪዎች መካከል እንዲህ ያለውን የቡድን መንፈስ ለማዳበር መስራት አለብህ።

## *የጋራ ራዕይ ፍጠር*

እንደ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ አንተ የቤተ ክርስቲያን ራዕይ ጠባቂ እና ዋና አራማጅ ነህ። በቤተክርስቲያኑ የአመራር ቡድን ልብ ውስጥ የጋራ ራዕይን መፍጠር እና ማሳደግ የአንተ ውሳኔ ነው። ምእመኑ ራዕዩን እንዲከተል አሳማኝ መሆን አለበት። የኢየሱስ ራእይ በጣም አሳማኝ ከመሆኑ የተነሳ ጴጥሮስን፣ እንድርያስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን እንዲከተሉት አነሳስቷቸዋል (ማቴ. 4፡18-22)።

በተመሳሳይ መልኩ ራእዩን በግልፅ እና አሳማኝ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ መቻል አለብህ። ኢሳያስ እንዳለው "መንገዱ ይህ ነው፤ በእርሱ ሂድ" ማለት መቻል አለብህ (ኢሳ. 30፡21)። ይህ የጋራ ራዕይ፣ እንደ ኃያል ወንዝ ፍሰት፣ ሁሉንም ሰው ወደ አንድ አቅጣጫ ያንቀሳቅሳል።[1]

## *የወዳጅነት ስሜት ፍጠር*

በምእመናን መሪዎች መካከል የጋራ አመለካከት ከማዳበር በተጨማሪ በመካከላቸው የመተሳሰብ ስሜት መፍጠር አለብህ። ሰዎች በደንብ አብረው እንዲሰሩ እርስ በርሳቸው በእውነት መዋደድ እና አንዱ ከሌላው ጋር መሆንን መደሰት አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት የመረጠበት አንዱ ምክንያት "ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ" እንደሆነ ይነግረናል (ማርቆስ 3፡14)። ማለትም አንዱ ከሌላው ጋር እንዲሆኑ መረጣቸው። አሥራ ሁለቱ ከኢየሱስ ጋር ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ፣ እና እርስ በርስ እየተዋደዱ ኖሩ። አንድ ላይ ሆነው በምድር ላይ ተጽዕኖ ማምጣት ቻሉ።

በተመሳሳይ መልኩ፣ አንተ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በራስህ፣ በሰራተኞችህ እና በምእመናን መሪዎች መካከል ጠንካራ የወዳጅነት ስሜት ለመፍጠር መጣር አለብህ። ይህን ማድረግ የሚቻለው

---

[1] ለበለጠ የእይታ ቀረጻ፣ ምዕራፍ 28ን "የራዕይ አመራር" የሚለውን ይመልከቱ።።

ለመሰባሰብ ጥራት ያለው ጊዜ በማሳለፍ ብቻ ነው። ጊዜህን በሦስት ጉልህ መንገዶች በሕብረት ማሳለፍ ይቻላል፡-

**1. በጋራ መጸለይ።** በመጀመሪያ፣ አንተ እና ከምእመናን የተገኙት የአመራር ቡድን በጸሎት አብራችሁ ጊዜ ማሳለፍ አለባችሁ። ከምእመናን መሪዎች ጋር ለጸሎት አንድ ላይ የምትሰበሰቡበት ምቹ ጊዜ በየሳምንቱ ማዘጋጀት አለብህ። እነዚህ የጸሎት ጊዜያት በትኩረት መያዝ አለባቸው። በዚህ ጊዜ ለግል ጉዳዩች መጸለይ ቢቻልም፣ አብዛኛው ጊዜ ግን ለቤተ ክርስቲያን ራዕይ እና አገልግሎት መጸለይ አለበት።

**2. በጋራ ማገልገል።** በመቀጠል፣ ከምእመናን መሪዎች ጋር በአገልግሎት አብረህ ጊዜ ማሳለፍ አለብህ። እሁድ ጠዋት ከቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ፕሮግራም በፊት፣ የአመራር ቡድኑን አንድ ላይ ለጸሎት መጥራት እና በቡድን አብራችሁ እንደምትሰሩ ማስታወስ ተገቢ ነው። የምእመናን አመራር ቡድን አንድ ላይ የሚያገለግልበት ሌላው መንገድ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ቡድን መመስረት ነው። በየዓመቱ፣ በአስቸጋሪ ቦታ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል አብረው ጉዞ ማድረግ ይችላሉ።

**3. በጋራ ሕብረት ማድረግ።** ሦስተኛ፣ ከምእመናን መሪዎች ጋር በኅብረት አብረህ ጊዜ ማሳለፍ አለብህ። ከምእመናን መሪዎች አንዱ የሌላውን ቤት እንዲጎበኙ መበረታታት አለባቸው። በአመራር ቡድንህ ቤተሰቦች መካከል ወርሃዊ ማዕድ መቁረስ ፕሮግራም ካለ የቤተሰባዊነት ህብረቱን ለማጠናከር ጠቃሚ ነው። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ብዙ ጊዜ ካሳለፈ በኋላ፣ "ከእንግዲህ አገልጋዮች አልላችሁም...ወዳጆች ብያችኋለሁ" (ዮሐንስ 15፡15) አላቸው። በተመሳሳይ መልኩ እርስ በራስ ጓደኛዬ ተባብላችሁ መጠራራት መቻል ይኖርባችኃል።

---

አንድ ቤተ ክርስቲያን እንዲያድግ፣ የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ እና ራዕይ ወደ ፊት ለማራመድ የሚተጉ ጠንካራ ከምእመናን የተውጣጡ መሪዎች ሊኖሩት ይገባል። ስለዚህ ብልህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ጠንካራ የምእመናን አመራር ቡድን መገንባትን በአገልግሎት ውስጥ እንደ አንድ ዋና አላማ ያስቀምጣል። እርሱ ወይም እርሷ የእግዚአብሔርን መንግስት ለማራመድ ከእነርሱ ጋር ለማገልገል የሚችሉ የምእመናንን መሪዎች ለመለየት፣ ለመመልመል እና ለማጎልበት ጊዜ እና ጉልበት ያጠፋል።

# ~ ምዕራፍ 34 ~

# የቤተ ክርስቲያን ዘርፎችን መምራት

አንድ ሕፃን በእናቱ ማህፀን ውስጥ እያደገ ሲሄድ ሰውነቱ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ይሄዳል። ሲፀነስ፣ አንድ ሴል ብቻ ነበር። ነገር ግን ፣ በሚያስደንቅ ሁኔታ ፣ የዘረ-መል ቅንጅቱ ቀድሞውኑ ሙሉ ነው። በ 24 ሰዓታት ውስጥ እንቁላሉ በፍጥነት ወደ ብዙ ሴሎች መከፋፈል ይጀምራሉ። በሶስት ሳምንታት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ የነርቭ ሴሎች ይፈጠራሉ። በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት መጨረሻ፣ ምንም እንኳን ህጻኑ ወደ 10 ሴንቲሜትር (አራት ኢንች) ርዝመት ቢኖረውም፣ ሁሉም የአካል ክፍሎች እና እግሮች ይፈጠራሉ። ነገር ግን ህፃኑ ሙሉ ሰው እንዲሆን እና ከእናቱ ማህፀን ውጭ መኖር እንዲችል የአካል ክፍሎቹ ማደግ አለባቸው። ከስድስት ተጨማሪ ወራት በኋላ ህፃኑ ለመወለድ ዝግጁ ይሆናል። ሲወለድ እናትና አባት ልጃቸውን ይታቀፋሉ። ዳዊት “ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ” ብሎ መደሰቱ እውነቱን ነው (መዝ. 139:14)።

አዲስ ቤተ ክርስቲያን ከህጻን ውልደት ጋር ሊመሳሰል ይችላል። አስቀድሞ ቤተ ክርስቲያን የመሆን አቅም ይዞ ይጀምራል፤ ሆኖም፣ በተግባራዊ፣ ሙሉ በሙሉ የሚሰራ የአማኞች አካል ለመሆን የተወሰኑ ሥርዓቶችን ማዳበር ይኖርበታል። ከእነዚህ ሥርዓቶች መካከል አንዳንዶቹ የቤተ ክርስቲያን የዘርፍ አገልግሎቶች በመባል ይታወቃሉ። ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እነዚህን የአገልግሎት ክፍሎች በመተግበር፣ በማዳበር እና በማስተዳደር ውስጥ ስላለው ሚና ያብራራል።

## የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎ ክፍሎች ዓላማ እና ተግባር

የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች በክርስቶስ አካል ውስጥ ያሉ ልዩ ፍላጎቶችን ለመፍታት የሚደራጁ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ናቸው። ዓላማቸው ቤተ ክርስቲያን የጠፉትን የመድረስ ተልዕኮዋን በብቃት እንድትወጣ ማስቻል እና ክርስቶስን የሚመስሉ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ነው። የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉ ለሚሄደው የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት

መዋቅር ድጋፍ እንደሚያደርጉ ምሰሶዎች ሊታዩ ይችላሉ። አዳዲስ ክፍሎች ሲጨመሩ፣ የቤተክርስቲያኑ የማገልገል አቅም እየሰፋ ይሄዳል።

## የአገልግሎ ክፍሎቹ ዓላማ

የቤተ ክርስቲያንን የአገልግሎት ክፍሎች ዓላማ እና ተግባር በትክክል ለመረዳት የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ መጀመሪያ የቤተክርስቲያኒቱን ተልእኮ መረዳት አለበት። ቤተ ክርስቲያን የመኖር ዓላማ ታላቁን ተልዕኮ ለማሳካት እና ታላቁን የክርስቶስን ትዕዛዝ ለመፈጸም ነው። ታላቁ ተልእኮ "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጉ" (ማቴ. 28፡19) የሚለው የክርስቶስ ትእዛዝ ነው። ታላቁ ትእዛዝ ደግሞ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ" እና "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" (ማቴ. 22፡37-39) የሚል የጌታ ትእዛዝ ነው።

እነዚህ አስደናቂ ኃላፊነቶች በመጋቢ ወይም ቤተ ክርስቲያን አገሊጋዬች ብቻ ሊከናወኑ አይችሉም። ስራው ብዙ እጆችን ይፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ የማቋቋም ተልእኮዋን በብቃት እንድትወጣ ለማስቻል የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች ትልቅ ሚና አላቸው።

## የአገልሎት ክፍሎች ሰባት ተግባራት

የቤተ ክርስቲያን የአገልሎት ክፍሎች ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በተሻለ ሁኔታ ለማከናወን በሰባት መንገድ ያስችሏታል።

ዋና ዋና ተግባራት:

1. **የጠፉትን መድረስ።** በመጀመሪያ፣ ቤተ ክርስቲያን "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር 16፡15) የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ እንድትፈጽም የሚረዱ ክፍሎች አሉ። ለዚህ አስፈላጊ ተግባር ቤተ ክርስቲያንን ለማስተባበር ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ክፍል የበኩሉን ሊወጣ ይገባል። ሁሉም የአገልግሎት ክፍሎች ምዕመናን በግል ምሥራቹን ለሌሎች እንዲናገሩ ማበረታታት እና በቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል እና ተልእኮ መርሃ ግብሮች እንዲሳተፉ ማበረታታት አለባቸው።

2. **ደቀ መዛሙርት ማድረግ።** ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን "አሕዛብን ሁሉ ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. 28፡19-20) ሲል ጨምሮ አዟል። ደቀ መዛሙርት በማድረጉ ሂደት ውስጥ ማስተማር ዋና ድርሻውን ይወስዳል። ለእግዚአብሔር ሕዝብ መንፈሳዊ እድገት እና ለቤተ ክርስቲያን እድገት ሥርዓተ ትምህርት ማበጀት አስፈላጊ ነው። የአገልግሎት ክፍሎች ለዚህ ዓላማ ይረዳሉ።

3. **የሚያበረታታ አምልኮ።** ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሰዎች የሚሰበሰቡበት እና "በመንፈስ እና በእውነት" የሚያመልኩበት ሥፍራ ነው(ዮሐ 4፡23)። በሚገባ የተደራጀ የአምልኮና የሙዚቃ የአገልግሎት ክፍል እንዲህ ዓይነት አምልኮ እንዲሳካ ይረዳል።

4. **ጸሎትን ማሳደግ።** በተጨማሪም፣ የቤተ ክርስቲያን የመኖር አንዱ አላማ የእግዚአብሔርን ህዝብ እንዲጸልይ ማነሳሳት እና ማስተማር ነው (ሐዋ. 2፡42)። ኢየሱስ "ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል" (ማርቆስ 11፡17) በማለት ተናግሯል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች በአንድነት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ወደ እግዚአብሔር የሚጣሩበት ጸሎታቸውን እንዲመልስላቸው የሚጠብቁባት ስፍራ መሆን አለባት (ማቴ. 8፡19-20፤ ሐዋ. 4፡24)። የአገልግሎት ክፍሎች ቤተ ክርስቲያን ይህንን ተግባር እንድትፈጽም ይረዳሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ የአገልግሎት ክፍል በተሰበሰበ ቁጥር ጸሎትን ማጉላት አለበት።

**5. ህብረትን ማድረግ።** በተጨማሪም፣ የቤተ ክርስቲያን የመኖር አላማ በክርስቶስ የሆኑ ወንድሞች እና እህቶች ህብረትን እንዲያደርጉ ማበረታታት ነው። የአገልግሎት ክፍሎዎች ቤተ ክርስቲያን ይህንን ግብ እንድታሳካ ያግዛሉ። የእግዚአብሔር ሕዝብ በአገልግሎት ክፍል ስብሰባዎች ላይ ሲሰበሰቡ እርስ በርሳቸው በፍቅር ያድጋሉ። በውጤቱም፣ እርስ በርስ መደጋገፍ እና መተሳሰብ ይፈልጋሉ። ይህ ሕብረት አካልን አንድ ለማድረግ እና ለማጠናከር ያገለግላል። አዳዲስ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሳብም ይረዳል።

**6. ለተልዕኮ ማሰባሰብ።** ሌላው የቤተ ክርስቲያን የመኖር አላማ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም ነው። ይህ ማለት የክርስቶስን ምሥራች እርሱ ከሰማይ ከመመለሱ በፊት "ለነገድ፣ ለቋንቋ፣ ለወገንም ሁሉ" ማድረስ ነው። የአገልግሎት ክፍሎዎች ቤተ ክርስቲያን እራሷን ለስብከተ ወንጌል፣ ለቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ለተልእኮዎች እንድታንቀሳቅስ ይረዳሉ።

**7. መሪዎች ማሳደግ።** በመጨረሻም፣ ኢየሱስ መሪዎችን እንድታሰለጥን ቤተ ክርስቲያንን አዟል። ደቀ መዛሙርቱን ሌሎችን ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ አዘዛቸው (ማቴ. 28፡19)። ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ፣ "የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት" ለቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎችን ሰጠ (ኤፌ. 4፡11)። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎታል፡- "በብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ" (2ጢሞ. 2፡2)። የአገልግሎት ክፍሎች ቤተ ክርስቲያን ይህንን ተግባር በብቃት እንድትወጣ ይረዱአታል።

# መደራጀት ያለባቸው የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች

ቤተ ክርስቲያን ስታድግ እና ስትሰፋ፣ አንተ እና የአመራር ቡድንህ የአገልግሎት መዋቅሩን በጸሎት ማደራጀት ይኖርባችኋል። አንድ ወይም ሁለት የአገልግሎት ክፍሎችን በማቋቋም ልትጀምር ትችላላችሁ። ከዚያም፣ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራ፣ ሌሎች ክፍሎችን እና ፕሮግራሞችን ታደራጃላችሁ። መደራጀት ያለባቸው የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች የሚከተሉትን ያካትታሉ።

## ትምህርት ክፍል/ ዘርፍ

ትምህርት ክፍል የቤተ ክርስቲያን መሰረታዊ የሥልጠና ስፍራ ነው። ይህ ክፍል አማኞችን የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር እና መርሆቹን በሕይወታቸው ላይ ተግባራዊ በማድረግ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ማድረግን አልሞ የሚደራጅ ነው። በአብዛኛዎቹ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት የልጆች እና አዋቂ ሰንበት ትምህርት የክርስቲያን ትምህርት ክፍል ዋና አካል ነው። የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ ተግባር ደቀ መዛሙርት የማድረግ አገልግሎት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከትንንሽ ሕፃናት ጀምሮ እስከ አዛውንት ድረስ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን የሚያገለግል ብቸኛው የአገልግሎት ክፍል ነው።

ስለዚህ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ይህንን ክፍል ለማዳበር ቅድሚያ መስጠት አለበት። አዲስ ቤተ ክርስቲያን ከሚፈልጋቸው የመጀመሪያ የአገልግሎ ክፍሎች አንዱ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ደቀ መዛሙርት የሚያደርጉ እና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩባቸውን የቤት ለቤት ቡድኖች

ማደራጀት ያስፈልጋታል። በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ ክፍል በተወሰነ ደረጃ በትምህርት አገልግሎ መሳተፍ አለበት።[1]

## የሴቶች አገልግሎት

የሴቶች አገልግሎት ክፍል ብዙውን ጊዜ በጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ በጣም ኃይለኛ ዘርፎች አንዱ ነው። አላማው ሴቶችን በክርስቶስ መድረስ እና ህብረት እና የአገልግሎት እድሎችን መስጠት ነው። በዚህ አገልግሎት፣ ሴቶች ወደ ቤተሰባቸው አባላት፣ ጓደኞቻቸው እና ጎረቤቶቻቸው እንዲደርሱ እና ወደ ክርስቶስ እንዲያመጡ ይበረታታሉ። ሴቶች በደቀ መዝሙርነት፣ በቤተ ክርስቲያን ተከላ፣ በተልዕኮዎ እና በሌሎች አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

## የወንዶች አገልግሎት

የወንዶች አገልግሎት ክፍል ወንዶችን ለክርስቶስ ለመድረስ፣ ክርስቲያናዊ ኅብረትን ለማቅረብ እና በቤታቸው እና በማህበረሰባቸው ውስጥ መሪዎች እንዲሆኑ ለማስታጠቅ ያለመ ነው። ወንዶችን በመንፈስ ለታጠቀ አገልግሎት ለማዘጋጀት ዘርፉ ይሰራል። በዚህ አገልግሎት፣ ወንዶች በስብከተ ወንጌል፣ በቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ሌሎች የቤተክርስቲያኑ ዋና ተልእኮዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

## የወጣቶች አገልግሎት

የወጣቶች አገልግሎት ክፍል ዓላማ ወጣቶችን ለክርስቶስ ለመማረክ እና በመንፈስ የተሞሉ የበሰሉ ጎልማሶች እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ከዚህም በላይ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖሩ ለማስተማር እና ለሌሎች ወጣቶች ትርጉም ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማነሳሳት ነው።

## የልጆች አገልግሎት

የህፃናት አገልግሎት ክፍል ልጆችን በክርስቶስ ለመድረስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ወደ ተሞላ ህይወት መምራት እና በጌታ መንገድ ማሰልጠን አልሞ የሚደራጅ ዘርፍ ነው። የወላጆችን ጥረት ለመተካት ሳይሆን እነርሱን ለማገዝ ታስቦ አገልግሎቱ መደራጀት አለበት (ምሳ. 22: 6)። የዚህ አገልግሎት የልጆች ቤተ ክርስትያን እና የህጻናት ደቀ መዝሙርነት አገልግሎት እንደ የወንዶች እና ሴት ልጆች ክለቦችን ሊያካትት ይችላል።

## አምልኮ እና ሙዚቃ አገልግሎት

የአምልኮ እና ሙዚቃ ክፍል አላማ ሙዚቀኞችን፣ የአምልኮ መሪዎችን እና መዘምራን ጉባኤውን በመንፈስ ወደሚመራ አምልኮ እንዲመሩ መመልመል እና ማሳደግ ነው (ዮሐንስ 4፡23)። ዘርፉ ከተልእኮዎ ኮሚቴ ጋር በስብከተ ወንጌል እና በቤተ ክርስቲያን ተከላ ላይም ይሰራል። የአምልኮ ቡድኑ

[1] እውነትን መኖር ተከታታዮች መጽሐፍት፣ በሰባት ዓመታት ውስጥ ተማሪዎችን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን የሚማሩበት የጎልማሳ የሰንበት ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት። ሌላው ተከታታይ የእምነት መሰረት የትምህርት መጽሐፍት ናቸው። ይህ እንደ "የመጀመሪያ እርምጃዎች፡ በክርስቶስ ያለህ አዲስ ሕይወት፣" "የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች"፣ "በመንፈስ ውስጥ ያለ ሕይወት" እና ሌሎችን በሚመለከቱ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ይህ ወቅታዊ ሥርዓተ ትምህርት ነው። እነዚህ ተከታታይ ትምህርቶች በተለያዩ የአፍሪካ ቋንቋዎች ቀርበዋል። ስለእነዚህ ምንጮች https://afri caatts.org/resources/ ላይ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።

አባላት ብዙ ጊዜ አብረው መጸለይ አለባቸው፣ ለመንፈስ ቅዱስ ህልውና ምላሽ መስጠት እና በመገኘቱ ሁነው እንዴት እንደሚያገለግሉ መማር አለባቸው።[2]

## የጸሎት አገልግሎት

በሚገባ የተደራጀ የጸሎት አገልግሎት ክፍል የእያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ወሳኝ አካል ነው። ይህ አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን እረኞችና ምእመናን በመማለድ መንፈሳዊ ድጋፍ ያደርጋል። እንዲሁም ላልዳኑ ሰዎች ከአጥቢያ ጀምሮ፣ በመላው አፍሪካ እና በዓለም ዙሪያ ይማልዳል። ይህ አገልግሎት እንደ መደበኛ የጸሎት ስብሰባዎች፣ የጸሎት ጉዞ፣ የጸሎት ፕሮግራም እና የግለሰብ መር ጸሎት አገልግሎትን የመሳሰሉ በርካታ አቀራረቦችን ሊከተል ይችላል።[3]

## ተልዕኮ አገልግሎት

የሚስዮን አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን በየቦታው ወንጌልን በማዳረስ ላይ እንድታተኩር የማድረግ ሃላፊነት ተሰጥቷል። ኃላፊነቱም የስብከተ ወንጌል ዝግጅቶችን እና የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮዎችን ማቀድ እና ማከናወንን ያጠቃልላል። የወንጌል ክንውኖች፣ የመነቃቃት አገልግሎቶችን፣ በአደባባይ ላይ የሚደረጉ ኮንፈረንሶች፣ ከቤት ወደ ቤት የሚደረጉ የምሥክርነት ዘመቻዎች፣ የስነ ጽሑፍ ስርጭት እና ሌሎች የተለያዩ የወንጌል አገልግሎት ዘዴዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።[4]

ዘርፉ የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ መርሃ ግብር የማዘጋጀት እና የማስተዋወቅ ኃላፊነት አለበት። በዚህ ወሳኝ መርሃ ግብር፣ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያንን በጸሎታቸው እና በገንዘባቸው ለመደገፍ ያንቀሳቅሳል። አገልግሎቱ ይህን የሚያደርገው ሕዝቡን ስለ እግዚአብሔር ተልእኮ በማስተማር እና ለሚስዮናውያን በማስተዋወቅ ነው። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ወንጌል ስርጭትን፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ተልእኮን የተለያዩ ዘርፎች አድርገው ያደራጃሉ።[5]

## ርኅራኄ አገልግሎት

ኢየሱስ ስለ ሰዎችን አካላዊ ፍላጎት ያስብ ነበር። የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ማድረግ አለበት። ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "በእግዚአብሔር አብ ፊት ንጹሕና ነውር የሌለበት ሃይማኖት ይህ ነው፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው መርዳትና ከዓለም ርኵሰት ራስን መጠበቅ ነው" (ያዕቆብ 1፡27)። የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን በርኅራኄ አገልግሎቷ የክርስቶስን እጅ ለተቸገሩ እና ለተጎዱ ሰዎች ትዘረጋለች።[6]

## ነጠላ የአዋቂዎች አገልግሎት

በነጠላ የአዋቂዎች አገልግሎት፣ ክርስቲያን ያላገቡ ወንድሞች እና እኅቶች በእምነታቸው እንዲጠነክሩ እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ንቁ ሚና እንዲኖራቸው ይታጠቃሉ። ይህ አገልግሎት

---

[2] የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት በምዕራፍ 18፡ "ቤተ ክርስቲያንን በአምልኮ መምራት" በሰፊው ተብራርቷል።

[3] ስለ ቤተ ክርስቲያን የጸሎት አገልግሎት፣ ምዕራፍ 8ን "የጸሎት ቅድሚያ" የሚለውን ተመልከት።

[4] ቤተ ክርስቲያንን ለስብከተ ወንጌል ማስፋፋት በተመለከተ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 37ን ተመልከት፡ "የጠፉትን ወንጌላዊነት" የሚለውን ተመልከት።

[5] የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ፕሮግራም ስለማሳደግ፣ ምዕራፍ 40ን "የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዎች ፕሮግራም ማዳበር" የሚለውን ተመልከት።

[6] ስለ ርህራሄ አገልግሎት፣ ምዕራፍ 38ን "ማህበረሰብን ማገልገል" የሚለውን ተመልከት።

ቤተ ክርስቲያን ያላገቡ ጎልማሶች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ ያለውን ጥቅም እንዲገነዘብ ይረዳል። የዚህን ብዙ ጊዜ ችላ የተባለ ቡድን አቅም መጠቀም ያስፈልጋል።

### የኮሌጅ ተማሪዎች አገልግሎት

ቤተ ክርስቲያን በዩኒቨርሲቲ ወይም በኮሌጅ ግቢ አጠገብ የምትገኝ ከሆነ፣ የኮሌጅ ተማሪዎች አገልግሎት ለመጀመር ማሰብ አለብህ። የዚህ አገልግሎት አላማ ተማሪዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ኮሌጅን ወይም ዩኒቨርሲቲ ግቢውን መድረስ ነው። ይህ አገልግሎት እነዚህን ተማሪዎች በማሰልጠን እና በማሰባሰብ የዳኑ ተማሪዎች በወንጌል ሌሎች ተማሪዎችን እንዲደርሱ ያደርጋል። ቤተዕምነቱ የዩኒቨርሲቲ አገልግሎት ክፍል ካለው፣ ከዚያ አገልግሎጽ ዘርፍ ጋር ተቀራርበው መሥራት ያስፈልጋል።[7]

### ሚዲያ እና ቴክኖሎጂ አገልግሎት

የሚዲያ እና ቴክኖሎጂ አገልግሎት ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ይመለከተዋል። የቤተክርስቲያኑ የድምጽ እና የቪዲዮ መሳሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰራል እና ይጠብቃል። የቤተ ክርስቲያንን ድህረ ገጽ እና የማህበራዊ ድህረ ገጾች በኢንተርኔት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ያስተዳደራል እና ይከታተላል። ይህ ክፍል የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶችን እና ዝግጅቶችን እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን እና ኢንተርኔት ባሉ ሚዲያዎች የማሰራጨት ሃላፊነት አለበት።

### መስተንግዶ

መስተንግዶ አገልግሎት አላማ በቤተ ክርስቲያን የሚሳተፉትን መቀበል እና መርዳት ነው። ይህ አገልግሎት ለሁሉም ሰው በፍቅር የተሞላ እና ተቀባይነት ያለው አካባቢ ለመፍጠር ይጥራል። ተሰብሳቢዎችን ይቀበላል፣ እንግዶችን ወደ መቀመጫቸው ይመራል፣ ቁሳቁሶችን ያሰራጫል እና ስጦታዎችን ይሰበስባል። በተጨማሪም ደህንነትን ያበረታታል፣ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስርዓትን ያስጠብቃል።

### ግንባታ እና ግቢ አስተዳደር ጉዳይ የሚከታተል

የሕንፃና የመሬት አስተዳደር አገልግሎት የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችን የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት። ህንጻዎቹ እና ግቢው ንፁህ እና በጥሩ ጥገና ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

## ዘርፍ ማደራጀት

ጥያቄው ፣ "አንድ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አዳዲስ የአገልግሎት ክፍሎችን እና አገልግሎቶችን እንዴት ሊያደራጅ ይችላል?" የሚለው ነው። እርግጥ ነው፤ ከላይ ያሉትን ሁሉንም ክፍሎች በአንድ ጊዜ መጀመር አይቻልም። ይልቁንም አዳዲስ የአገልግሎት ክፍሎች በጸሎት እና በስልት መጀመር አለባቸው። አዳዲስ የአገልግሎት ክፍሎችን ማስጀመር ብዙ አመታትን የሚወስድ ደረጃ በደረጃ በሂደት መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

[7] ለኮሌጅ ተማሪዎች አገልግሎት ለማዳበር ግብዓቶች በበይነመረቡ https://chialpha.com/resources/ ላይ ይገኛሉ።

አዲስ የአገልግሎት ክፍሎችን መጀመር ብዙውን ጊዜ በመጋቢ እና በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በኩል የእምነት እርምጃን መውሰድን ያካትታል። ፍላጎቱን ካዩ፣ የመንፈስን አመራር ከተረዱ፣ አዲሱን አገልግሎት ለመጀመር በእምነት መንቀሳቀስ አለባቸው።

## የሂደቱ መጀመር

አንተ እና የቤተክርስቲያናችሁ አመራር አስቀድሞ እግዚአብሔርን በመፈለግ ሂደቱን መጀመር አለባችሁ። “ጌታ ሆይ፣ በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ምን አዲስ አገልግሎቶች ያስፈልጋል?” ብለህ ልትጠይቅ ይገባል። መንፈስ ቅዱስ እንድትጀምር የመራህ እንደሆነ ከተረዳህ የእነዚያን የአገልግሎ ዘርፍ እና አገልግሎቶች አጭር ዝርዝር መጻፍ ይገባል። ዝርዝሩን ከጻፍክ በኋላ ለአፈጻጸሙ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን፣ የትኛው በቀጣይነት እንደሚከተል መለየት ያስፈልጋል።

ከዚያ ትኩረትህን በቅድመ-ዝርዝሩ ላይ ባለው መሰረት ከአመራር ቡድንህ ጋር ተገናኝተህ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መወያየት አለብህ።

- ይህንን አዲስ ክፍል ለመጀመር ምን እርምጃዎች መውሰድ አለብን?
- ምን ዓይነት ግብዓቶች ያስፈልጋሉ?
- ፕሮግራሙን የሚመራው ማን ነው?
- መቼ ነው የሚጀምረው?

ውሳኔህን ጻፍ እና በእነርሱ ላይ መጸለይህን መቀጠል አለብህ። ከዚያ፣ ጊዜው ሲደርስ፣ ስልትህን ስልት ተግባራዊ ማድረግ መጀመር ትችላለህ። አቅምን መሰረት አድርጎ በትንሹ መጀመር ይመከራል። ለምሳሌ፣ አዲስ የሰንበት ትምህርት ክፍል ለመጀመር፣ ሦስቱን ክፍሎች በአንድነት አጣምሮ መጀመር ይቻላል፡ ጎልማሶች፣ ወጣቶች እና ልጆች። የሰንበት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኖ የሚያገለግለውን ሰው መሾም ፣ ወይም በዚህ ሚና ውስጥ እራስህን መምራት በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ እንደ አማራጭ ሊታይ ይችላል። አገልግሎቱ እያደገ ሲሄድ አዳዲስ ክፍሎችን መጀመር እና አዲስ መሪዎችን መሾም ይቻላል።

## መሪዎችን መምረጥ

ለማንኛውም አዲስ የትምህርት ክፍል ስኬት ቁልፉ በሚገባ የተመረጡ እና በትክክል የሰለጠኑ መሪዎች ናቸው። መሪዎችን በምትመርጥበት ጊዜ፣ የመሪነት አቅም ያላቸውን፣ ወደ መሪነት ልታሳድጋቸው የምትችላቸውን ግለሰቦች መፈለግ አለብህ። እነዚህ ሰዎች “በመንፈስና በጥበብ የተሞሉ” መሆን አለባቸው (ሐዋ. 6፡3)። በተጨማሪም፣ በእምነት የተሞሉ መሆን አለባቸው። የቤተ ክርስቲያንን ራዕይ ሙሉ በሙሉ መቀበል አለባቸው።

## ሰራተኞችን ማሰልጠን

ብዙ ጊዜ ብቁ መሪዎች አይገኙም። ስለዚህ፣ ውጤታማ መጋቢ በየጊዜው አዳዲስ መሪዎችን ያዘጋጃል። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። ሐዋርያት እንዲሆኑ የሚያሰለጥናቸውን አሥራ ሁለት ሰዎች በጸሎት መረጠ (ሉቃስ 6፡12-13)። ተራ ሰዎች ቢሆኑም ኢየሱስ የመሪነት ችሎታቸውን አይቶባቸው ነበር። “ኑ ተከተሉኝ… ሰዎችንም እንድታጠምዱ እልካችኋለሁ” (ማቴ. 4፡19) ብሎ አዘዛቸው። እርሱን ስለተከተሉት፣ ታላላቅ መሪዎች አደረጋቸው።

አዲስ የአገልግሎት ዘርፍ አመራሮችን እና ሰራተኞችን በሚቀጠሩበት ጊዜ ስልጠና እንደሚሰጣቸው ቃል መግባቱ አስፈላጊ ነው። ሰዎቹን "አብሬአችሁ አለሁ እና አገልግሎቱን እንዴት መፈጸም እንዳለባችሁ

አሳያችኃለሁ" በላቸው። ይህ የአገልግሎት ስልጠና በተለያዩ መንገዶች ሊከናወን ይችላል፡- በሴሚናሮች፣ አንድ ለአንድ የስልጠና ግንኙነት በመፍጠር እና ሌሎች ዘዴዎችም መጠቀም ይቻላል። ቤተ ክርስቲያን የማያቋርጥ የመሪዎች አቅርቦት ለማግኘት፣ ፓስተሩ ስለአመራር ሥልጠና ሁል ጊዜ ማቀድ አለበት።[8]

## የቡድን መንፈስ መፍጠር

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የዘርፍ አገልግሎቶች እንዲዳብሩ በመሪዎች እና በሠራተኞች መካከል የዓላማ እና የመተማመን ስሜት መፍጠር አለብህ። ይህ የቡድን መንፈስ አብረው እንዲሰሩ እና ስራቸውን በጥሩ ሁኔታ ለመስራት እንዲችሉ ያነሳሳቸዋል። የቤተ ክርስቲያንን ራዕይ በተደጋጋሚ በማስታወስ እና እያንዳንዱን ራዕዩን ለማሳካት የሚጫወቱትን ጠቃሚ ሚና በማሳየት ይህንን የቡድን መንፈስ ማሳደግ ትችላለህ።

ለማበረታታት እና ድሎችን እና ግቦችን ለመጋራት ከዘርፍ መሪዎች እና አገልጋዮች ጋር ብዙ ጊዜ መገናኘት አለብህ። እንዲሁም ታማኝ ሰራተኞችን በአደባባይ ለይተህ ልታበረታታቸው ይገባል (ሮሜ 13፡ 7)።

---

የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ታላቁን ተልዕኮ እና ታላቁን ትዕዛዙን በብቃት ለመፈጸም የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ስለዚህ ውጤታማ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ጠንካራ የአገልግሎት ክፍሎችን ለማዳበር ይሰራል።

---

[8] በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ሠራተኞችን ስለማሠልጠን፣ ምዕራፍ 33ን "ሰራተኞን ን ማንቀሳቀስ" የሚለውን ተመልከት።

# ~ ምዕራፍ 35 ~

# የቤተ ክርስቲያን አባልነትን መከታተል

ማን እየተማረ እንደሆነ እና ማን እንዳልሆነ ግልጽ የሆነ መረጃ የሌለውን ትምህርት ቤት አስቡ። ትምህርት ቤቱ የተማሪ ቅበላን ሆነ የተማሪ ስኬት በፍፁም መዝገብ አይይዝም። በግልጽ ለመገመት እንደሚቻለው፣ እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት ቤት የስኬት እድል አነስተኛ ነው። ስለ ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ነገር ሊባል ይችላል። ማን እንዳለ እና ማን እንደሌለ የጠራ መረጃ የሌላት ቤተ ክርስቲያን፣ የአማኞች መንፈሳዊ እድገትን መከታተል የሚችል ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን የመሆን ዕድሏ አናሳ ነው።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የምትመራው ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ የምትመራ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ። አንዱ አስፈላጊ የአስተዳዳሪ ትኩረት ጉዳይ የቤተክርስቲያኑ አባልነት ዝርዝር ነው። በደንብ የተያዘ የአባልነት ዝርዝር ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን በጎችን የመንከባከብ እና የጠፉትን በወንጌል አገልግሎት በተሻለ መንገድ ለመድረስ ይረዳታል። ይህ ምዕራፍ የቤተክርስቲያኗን የአባልነት የመከታተል ግዴታህን ያብራራል።

## የአባልነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን

መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እንደሚታወቀው ስለ መደበኛ የቤተ ክርስቲያን አባልነት በቀጥታ ባይናገርም፣ ይህንን ሀሳብ ይደግፋል።

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአባልነት መሠረት

የቤተ ክርስቲያን አባልነት ጽንሰ ሐሳብ መነሻው ከብሉይ ኪዳን ነው። በዚያም እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ልዩ የሆነ ግንኙነት መስርቶአል። ከእስራኤል የእርሱ ሕዝብ፣ እርሱም አምላካቸው ነበር። በምድረ በዳ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ህዝቡን የማደራጀት ስለፈለገ ሙሴን እንዲህ ሲል አዘዘው፡- "የወንዶቹን ስም አንድ በአንድ በመዘርዘር መላውን የእስራኤል ማኅበረሰብ በየጐሣቸውና

በየቤተሰባቸው ቍጠራቸው” (ዘኊ. 1፡2)። ከዚያም ሙሴና አሮን ከሕዝብ መካከል የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመሩ፣ የሚያገለግሉትን እና የሚወክሉትን ለመምረጥ ይህን የሕዝብ ቆጠራ ተጠቀሙ።

በአዲስ ኪዳን እስጢፋኖስ ስለ እስራኤል “በምድረ በዳ የተሰበሰበው ጉባኤ [ግሪክ፡ ኤክሌሲያ]” ሲል ተናግሯል። በአዲስ ኪዳን ኤክሌሲያ የሚለው ቃል “ቤተ ክርስቲያን” ተተርጉሟል። ክርስቶስን ለመከተል እና ተልዕኮውን በምድር ላይ ለማራመድ ከዓለም የተጠሩ ሰዎች ስብስብ ማለት ነው።

ኢየሱስ “ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ” (ማቴ. 16፡18) ብሏል። ቤተ ክርስቲያኑን የመስራት ሂደት የጀመረው ሰዎች እንዲከተሉት በመጋበዝ ነው (ማቴ. 4፡19)። ከእነዚህ ተከታዮች፣ ኢየሱስ አንዳንዶቹን ሐዋርያት እንዲሆኑ ሾሟል (ማርቆስ 3፡13-14)። ሐዋርያትም በተራቸው እነርሱ ሥር ሆነው እንዲያገለግሉ ዲያቆናትን ሾሙ። ቤተ ክርስቲያንን ለስኬት እያደራጁ ነበር። በውጤቱም፣ “በኢየሩሳሌም ያሉ የደቀ መዛሙርት ቍጥር በፍጥነት ጨመረ” (ሐዋ. 6፡1-7)።

አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን በሚገባ ለመስራት፣ ማን አባል እንደሆነ እና ማን እንዳልሆነ ሁሉም ሰው ማወቁ አስፈላጊ ነው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ተረድታለች። ለእነርሱ፣ የቤተ ክርስቲያን አባልነት የሆነ እና ያልሆነው ግልጽ ነበር። ለምሳሌ፣ በአንድ ወቅት፣ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን በኃጢያት የጸናን አባል ከቤተ ክርስቲያን መዝገብ እንድታስወግደው አዟል (1ቆሮ. 5፡5፣ 13)። በአግባቡ ክትትል የሚደረግበት የአባልነት መዝገብ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አማኞችን ለማጠናከር እና የቤተክርስቲያኗን ተልእኮ ለማሳደግ ይረዳል።

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአባልነት ጽንሰ-ሐሳብ

አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን አባልነት እንደ ዕድር ወይም እቁብ ማሰብ የለበትም። ክርስቲያን አባልነት ከዚያ የላቀ ጥልቀት ያለው ነው። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን “የክርስቶስ አካል” በማለት ጠርቷታል (1ቆሮ. 12፡27) ቤተ ክርስቲያንን ከሰው አካል ጋር አነጻጽሮታል። እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኑ አባል የክርስቶስ አካል ነው፣ እና “እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን” (ሮሜ. 12፡5)። ልክ የሰው አካል የተደራጀ እንደሆነ፣ እና እያንዳንዱ የአካል ክፍል የተለየ ተግባር እንዳለው፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው።

## የአባልነት መስፈርት

በብሉይ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲኖሩባቸው መመዘኛዎችን አዘጋጅቶ ነበር። እነዚህ መመዘኛዎች በአሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ተጠቃለዋል (ዘጸ. 20፡1-17)። በተመሳሳይም የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን እያደገችና ከኢየሩሳሌም ባሻገር ስትበተን፣ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው አህዛብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካተቱበትን መመዘኛዎችን አዘጋጅተዋል (ሐዋ. 15፡19-20፣ 28-29)። የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንደመሆንህ፣ ማንኛውም ሰው እንደ አባል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲቀላቀል የተወሰኑ መመዘኛዎችን ማሟላቱን ማረጋገጥ አለብህ፣ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

### አዲስ ልደት

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የዓለማቀፉ ቤተ ክርስቲያን ነጸብራቅ መሆን አለባት። ዓለም አቀፋዊው ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ታምነው የዳኑትን ሁሉንም ህዝቦች ያካትታል። ዓለም አቀፋዊው ቤተ ክርስቲያን የሚያጠቃልለው በእውነት ከመንፈስ ቅዱስ የተወለዱትን ብቻ ነው (1ቆሮ. 12፡13)። ስለዚህ፣ አንድ ሰው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ከመሆኑ በፊት እርሱ ወይም እርሷ መጀመሪያ የዩኒቨርሳል ቤተ

ክርስቲያን አባል መሆን አለባቸው። የዳኑትን ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚጨምረው ጌታ እራሱ ነው (ሐዋ. 2፡47)። ስለዚህም፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን አንድ ሰው በእውነት ዳግም መወለድ አለበት (ዮሐ. 3፡3-7)።

### የውሃ ጥምቀት

ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን አባልነት መስፈርት የውሃ ጥምቀት ነው። ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው" (ማቴ. 28፡19፤ የሐዋርያት ሥራ 2፡38) በማለት አዟል። የውሃ ጥምቀት አንድ ሰው ከሞት ወደ ሕይወት መሻገሩን የአደባባይ ምስክርነት የሚሰጥበት ነው (ሮሜ. 6፡4)።[1]

### የጋራ እምነት

የመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን አባልነት መመዘኛ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች እና መመሪያዎች ጋር ሙሉ ስምምነት ማድረግ ነው (1ቆሮ. 1፡10)። ይህ መስፈርት ቤተ ክርስቲያን አንድነቷን እንድትቀጥል እና እግዚአብሔር በሰጣት ተልዕኮ ላይ እንድታተኩር ያደርጋታል። እነዚህ ጉዳዮች በአዲስ አባላት ትምህርት ውስጥ መነሳት አለባቸው።

## የአዳዲስ አባላትን ቅበላ

እንደ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያን አባላትን ለመቀበል በሚገባ የተገለጸ አሰራር ማበጀት አለብህ። ይህ አሰራር ሶስት ክፍሎችን ማካተት አለበት.

### አባልነትን ማበረታታት

አዳዲስ አማኞች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀላቀሉ በየጊዜው ማበረታታት አለብህ። ይህንን ለማድረግ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ ወስደህ የቤተ ክርስቲያን አባልነት ጥቅሞችን ማስረዳት እና አዳዲስ ክርስቲያኖች እንዲቀላቀሉ መጋበዝ አለብህ። እንዲሁም ፈቃደኝነት ሚያሳዩትን በግል ማናገር ሊያስፈልግ ይችላል። እነዚህ ድርጊቶች አባላት በየጊዜው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲጨመሩ ያደርጋል። (ይህ በእርግጥ ወደ ክርስቶስ የሚመጡ አዳዲስ ሰዎች፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ የወንጌል አገልግሎት ምክንያት እንደሆነ በማሰብ ነው)። በተጨማሪም፣ የአባልነት ማመልከቻ ቅጾችን በቀላሉ መቅረብን ማረጋገጥ አለብህ።

### ለአባልነት በመዘጋጀት ላይ

ለቤተ ክርስቲያን አባልነት የምታዘጋጅበት ዘዴዎች መኖሩ አስፈላጊ ነው። ይህንን ለማድረግ አንዱ መንገድ የአዳዲስ አባላት ትምህርት በማዘጋጀት ነው። ይህ ተከታታይ ትምህርት መሆን አለበት። በአዋቂዎች የሰንበት ትምህርት ሰአታት ወይም በሌላ በማንኛውም ጊዜ በማለዳ ጠዋት ሊቀርብ ይችላል። በዚህ ክፍል ውስጥ፣ የእጩ አባላት ስለ ቤተ ክርስቲያን አባልነት ጥቅሞች እና ኃላፊነቶች ይማራሉ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተብራሩት አብዛኛው ሃሳብ በዚህ በክፍል ውስጥ ሊማሩ ይችላሉ።

---

[1] ስለ የውሃ ጥምቀት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 42ን "ቅዱስ ቁርባንን፣ መሰጠትን እና ጭነቶችን መምራት" የሚለውን ተመልከት።

## አባላትን መቀበል

በቤተክርስቲያኑ አመራር አባልነታቸው ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በአንድ እሁድ ጠዋት በአደባባይ ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀላቸውን በደስታ መገለጽ አለበት። በአባልነት የተቀላቀሉት ወደ መድረክ ፊት ማውጣት፣ ማመስገን እና መጸለይ ይገባል። ከዚያም ቤተ ክርስቲያን "የኅብረትን ቀኝ እጅ" ትዘረጋቸዋለች (ገላ. 2፡9)። በዚህ ጊዜ ለእያንዳንዱ አዲስ አባል አባልነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይገባል። ከዚያ ስማቸውን በቤተክርስቲያኑ አባልነት መዝገብ ላይ ይጨምራሉ።

በተጨማሪም፣ መጋቢው ወይም በቤተ ክርስቲያን የተወከለ አገልጋይ እነዚህን አዳዲስ አባላት በቤታቸው ቢጎበኝ ጥሩ ነው። ይህም ቤተ ክርስቲያን ለመቀላቀል ያደረጉትን ውሳኔ ምን ያህል እንደምታደንቅ ለማወቅ ይረዳቸዋል። በመጨረሻም አዲሶቹን አባላት ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማለትም ከቤት ለቤት ቡድኖች፣ ከሴቶች አገልግሎት፣ ከወንዶች አገልግሎት፣ ከወጣቶች ቡድን እና ከሌሎችም ጋር ማገናኘት አለብህ።

# የአባልነት ሀላፊነቶች

የቤተክርስቲያኑ መጋቢ እንደመሆንህ፣ አዲስ አባላት የአባልነት ሀላፊነቶችን እና ልዩ መብቶችን እንዲያውቁ ማድረግ አለብህ።

## የቤተክርስቲያኑ አባላት የአባላት ሀላፊነቶች

ከአባልነት ጋር ሃላፊነት ይመጣል። እነዚህ ኃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

1. **አዘውትሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ።** የዕብራውያን ጸሐፊ ክርስቲያኖች አንድ ላይ መሰብሰባቸውን ቸል እንዳይሉ አስጠንቅቋቸዋል። ይልቁንም በየጊዜው አንድ ላይ ሆነው እርስ በርስ መበረታታት ነበረባቸው። ይህ በተለይ ከኢየሱስ ምጽዓት አንጻር አስፈላጊ ነበር (ዕብ. 10፡25)። በተመሳሳይ መልኩ፣ የዛሬው የቤተክርስቲያኑ አባላት በቤተ ክርስቲያን ተሳትፎቻቸው ታማኝ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በሕብረት ይበረታታሉ፣ እግዚአብሔርን ያመልካሉ፣ አብረው ይጸልያሉ፣ ትምህርት ይቀበላሉ፣ ለእግዚአብሔር ሥራ ይሰጣሉ፣ እና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ዘላቂ ግንኙነት ያዳብራሉ።

2. **በመንፈስ የተሞላ የሕይወት ጉዞ።** እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን አባል በመንፈስ ለተሞላው የሕይወት ጉዞ መሰጠት አለበት (ገላ. 5፡25)። በመንፈስ ቅዱስ ገና ካልተጠመቁ፣ ልምምዱን በትጋት መፈለግ አለባቸው (ሐዋ. 1፡4-5፤ ኤፌ. 5፡18)። በመንፈስ ከተሞሉ፣ በመንፈስ በተሞላ አካሄድ ለመቀጠል ቁርጠኛ መሆን አለባቸው (ገላ. 5፡16፣ 25)።[2]

3. **የማያቋርጥ ምስክርነት።** እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የክርስቶስ ምስክር መሆን ይጠበቅበታል (ሐዋ. 1፡8)። ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከጎረቤቶቻቸው እና ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ክርስቶስን በታማኝነት ማካፈል አለባቸው። ኢየሱስ "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሌሎች ፊት ይብራ" (ማቴ. 5፡16) በማለት አዞናል።

4. **ቅዱስ ኑሮ።** የጴንጤቆስጤያዊ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ የሚመሰክሩት አንዱ መንገድ ቅዱስ ሕይወት በመምራት ነው (1ጴጥ. 1፡15፤ 2፡9)። ይህን ሲያደርጉ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ያሳያሉ።

[2] አማኞችን በመንፈስ ወደ ተሞላው የሕይወት ጉዞ ስለመምራት፣ ምዕራፍ 11ን "የጴንጤቆስጤ ልምድንና ልምምድን ያበረታታል" እና ምዕራፍ 20፡ "አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" ተመልከት።

በተመሳሳይ ጊዜ፣ ሕይወታቸው ለጠፋው ዓለም የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን ምን ማለት እንደሆነ ይመሰክራል (ፊልጵ. 2፡15)።

**5. በታማኝነት መስጠት።** ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አባል ቤተ ክርስቲያንን በገንዘብ መደገፍ ይጠበቅበታል (1ቆሮ. 16፡2)። አባላት አሥራታቸውን እና መስዋዕታቸውን በመስጠት አካሉን ያጠናክራሉ እናም የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ ለማራመድ ይረዳሉ። በተጨማሪም በደስታ መስጠት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል እናም በሕይወታቸው በረከት ለመቀበል በር ይከፍታል (2ቆሮ. 9፡7-8፤ ሉቃ. 6፡38)።

**6. ንቁ አገልግሎት።** በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ አባል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት ቦታውን ማግኘት ይጠበቅበታል። እያንዳንዱ አባል የድርሻውን ሲወጣ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ትሆናለች። እንደ መጋቢ፣ አባላት ልዩ ስጦታዎቻቸውን እንዲረዱ እና እነዚህን ስጦታዎች ክርስቶስን እና ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል እንዲያውሉ ለማድረግ መስራት አለብህ።

**7.፤ ጥብቅ ጸሎት።** የእውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ምልክት ልባዊ ጸሎት ነው። እያንዳንዱ አባል ለፓስተሩ፣ ለቤተክርስቲያኑ፣ ለማህበረሰቡ እና ለሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ዘወትር እንዲጸልይ ይጠበቃል። የተወሰኑትን በልዩ ሁኔታ የተቋቋመውን የምልጃ ጥሪ የጸሎት ቡድኖችን እንዲቀላቀሉ ማበረታታት ይፈልጋል።

**8. የትብብር አመለካከት።** በመጨረሻም አባላት የትብብር መንፈስን መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል። እንዲህ ያለው አመለካከት ለቤተ ክርስቲያን አንድነት አስተዋጽኦ ያደርጋል (ኤፌ. 4፡3)። ቤተ ክርስቲያን ትርጉም በሌለው ጭቅጭቅ እንዳትዘናጋ ከማድረጉም በላይ እግዚአብሔር የሰጣትን ተልእኮ ለመወጣት ትኩረት ሰጥታ እንድትቀጥል ያደርጋል።

## አባላት የተመለከቱ የቤተ ክርስቲያን ሀላፊነቶች

አዳዲስ አባላት ለቤተ ክርስቲያን የተወሰኑ ኃላፊነቶችን እንዳለባቸው ሁሉ፣ ፓስተሩ እና ቤተ ክርስቲያን ለአባላትም የተወሰኑ ኃላፊነቶችን ይሸከማሉ። እነዚህ ኃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ።

**1. የፍቅር አቀባበል።** በመጀመሪያ፣ አዲስ አባላት ሞቅ ያለ አቀባበል እንዲደረግላቸው እና ሙሉ በሙሉ ወደ ቤተክርስቲያኑ ህይወት እንዲቀላቀሉ ማድረግ አለብህ። አንዳንዶች የለመዱትን ሰዎች እና ፕሮግራሞች ፈልገው ጥለው ሊሄዱ ይችላሉ። ብዙም የማያውቁት አዲስ ዓለም ውስጥ ገብተው ይሆናል ወይም እንደገቡ ያስብ ይሆናል። እነዚህ አዳዲስ አባላት ከአካባቢያቸው ጋር እንዲላመዱ መርዳት አለብህ። በእውነት የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት እንደሆኑ እንዲሰማቸው ለማድረግ ሁሉንም ጥረት ማድረግ አለብህ።

**2. ጥራት ያለው የአምልኮ አገልግሎቶች።** ሁለተኛ፣ እንደ መጋቢ ለአዲሶች ሆነ ለነባርም የቤተ ክርስቲያን አባላት በእውነት የሚያንጽ የአምልኮ ፕሮግራም የማዘጋጀት ሃላፊነት አለብህ። በሌላ አነጋገር፣ የቤተክርስቲያኑ የአምልኮ አገልግሎቶች በሚገባ የታቀዱ እና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብህ። ይህንን ለማድረግ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ፣ ጤናማ እና አነቃቂ መልዕክቶችን ለማዘጋጀት እና ለመስበክ የተቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለብህ። በተጨማሪም እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል በጥራት እና በሙያዊ መንገድ መከናወኑን ማረጋገጥ አለብህ። ይህ አምልኮን ምራት፣ የመስጠት ጊዜ፣ ማስታወቂያዎችን ማድረግ ወይም ማንኛውንም የአገልግሎቱን ሂደት ያጠቃልላል።

በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ በኃይል መኖሩን ለማረጋገጥ አንተ እና የአመራር ቡድንህ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በጸሎት መታጠቅ ይኖርባችኃል።[3]

**3. የመጋቢ እንክብካቤ።** በተጨማሪም፣ የመንጋው እረኛ እንደመሆንህ መጠን እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ዋጋ እና እንክብካቤ ማግኘቱን መከታተል ግዴታ አለብህ። ኢየሱስን መምሰል አለብህ “መልካም እረኛ... ነፍሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል” (ዮሐንስ 10፡11)። ኑሮው ዝቅተኛ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን አባል በትኩረት ለማገልገል ዝግጁ መሆን አለብህ (ሉቃስ 15፡1-7)።[4]

**4. ልባዊ ጸሎት።** በመቀጠል፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለቤተ ክርስቲያን አባላት በታማኝነት መጸለይ አለብህ። ለጸሎት ለማስታወስ እንዲያገለግልህ የስማቸውን ዝርዝር መጻፍ ጥሩ ይሆናል። ከዚያ ዝርዝሩን በማየት በየቀኑ ለእያንዳንዱ አባል መጸለይ ትችላለህ። በተጨማሪም፣ በችግር ጊዜያቸው፣ አንተ እና የአመራር ቡድንህ ወደተጎዱ አባላት በመሄድ ማበረታታት እና ለመጸለይ ዝግጁ መሆን አለብህ።[5]

**5. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት።** በተጨማሪም፣ እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት መቀበላቸውን ማረጋገጥ አለብህ። ይህ ትምህርት ተግባራዊ እና ከሕይወታቸው ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። ትምህርት እንዲያድጉና የጎለመሱ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። እንዲሁም በአዋቂዎች የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍሎች እና ቤት ለቤት ቡድኖች ትምህርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጤናማ እና የሚያንጽ መሆኑን መከታተል አለብህ።[6]

**6. ከሐሰተኛ ነቢያት ጥበቃ።** የእግዚአብሔርን መንጋ እንደሚጠበብቅ መጋቢ፣ ሕዝብህን ከሐሰተኛ ነቢያት እና አስተማሪዎች የመጠበቅ ግዴታ አለብህ (ሐዋ. 20፡28-29)። ይህን ማድረግ የምትችልበት አንዱ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ያለማቋረጥ በማስተማር ነው። ሌላው መንገድ የተወሰኑ ሐሰተኛ ነቢያትንና አስተማሪዎች የመንገዳቸውን ስህተት በመጥቀስ ነው። በተጨማሪም፣ እነዚህን "የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች" በቤተ ክርስቲያን በስውር እንዳይገቡ መድረክ እንዳይረግጡ በማድረግ አባሎቻችሁን ከሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች መጠበቅ ትችላላችሁ (ማቴ. 7፡15)።[7]

**7. የአገልግሎት እድሎች።** እንዲሁም ለአዳዲስ አባላት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት እድሎችን መስጠት አለብህ። ለሆነ ቀላል የአገልግሎ ኃላፊነት ወዲያውኑ መጋበዝ አለብህ። ይህም ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲተሳሰሩ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም እግዚአብሔርን ማገልገል በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ላይ ከመገኘት ያለፈ ነገር መሆኑን ከመጀመሪያው እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። ተሳትፎ ንቁ አገልግሎትንም ያካትታል።

**8. ሰርግ እና የቀብር ሥነ ሥርዓቶችን ማከናወን።** በመጨረሻም፣ እንደ ፓስተራቸው፣ ከአባላት በህይወት ታላላቅ ክስተቶች ውስጥ የመሳተፍ ግዴታ አለብህ። የጋብቻ ምክር መስጠት እና የሠርግ ሥነ

---

[3] የአምልኮ አገልግሎቶችን ማቀድን በተመለከተ ተጨማሪ ግንዛቤን ለማግኘት ምዕራፍ 18ን “መምራት አምልኮ” ተመልከት።

[4] “በጎቹን መንከባከብ” የሚለውን ምዕራፍ 24 ተመልከት።

[5] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር እና ጸሎት ለበለጠ፣ ምዕራፍ 8 “የጸሎት ቅድሚያ” የሚለውን ተመልከት።

[6] ስለ ጴንጤቆስጤ ፓስተር እንደ መምህር ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 17ን “ውጤታማ ትምህርት” የሚለውን ተመልከት። እውነትን መኖር እና የእምነት ሥር ሥርዓት ትምህርት እጅግ በጣም ጥሩ የጴንጤቆስጤ ደቀመዝሙርነት ግብዓቶች ናቸው። ከአፍሪካ ቲዎሎጂካል ማሰልጠኛ አገልግሎት (ATTS) https://africaats.org/resources/ በነጻ ይገኛሉ።

[7] ቤተ ክርስቲያንን ከሐሰተኛ ነቢያት ስለመጠበቅ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 27ን “መንጋውን መጠበቅ” የሚለውን ተመልከት።

ሥርዓቶችን መፈጸም አለብህ. እንዲሁም ቀብር ሥርዓቶችን መምራት እና ለሐዘንተኛ የቤተሰብ አባላት ድጋፍ እና ማበረታቻ መስጠት አለብህ።[8]

# የአባላት ስብሰባዎች

የአባላት ስብሰባዎች የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ አካል ናቸው። በእነዚህ ስብሰባዎች፣ አባላት በአንድነት ይሰበሰባሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ይወያያሉ። ፓስተሩ እና ሌሎች መሪዎች የቤተክርስቲያኗን እድገት፣ ተግዳሮቶች እና ፍላጎቶች በተመለከተ ሪፖርቶችን ይጋራሉ። የአባላት ስብሰባዎች በየዓመቱ መከናወን አለባቸው። በተጨማሪም እንደ አስፈላጊነቱ በልዩ ሁኔታ የሚጠሩ ስብሰባዎች ሊዘጋጁ ይችላሉ። የአባላት ስብሰባዎች ስለሚመጡት ክስተቶች ለመወያየት እና ራዕይን ከቤተክርስቲያኑ ጋር ለመጋራት ጥሩ ጊዜ ነው። እነዚህ ስብሰባዎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለ ጉባኤው ያላቸውን ተስፋ እና ህልም እንዲወያዩበት እድል ይሰጣቸዋል። ከእነዚህ ስብሰባዎች በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ ስብሰባውን በደንብ ማዘጋጀት ይገባል። በጥንቃቄ የተዘጋጀ አጀንዳ እና ትክክለኛ ዘገባ ይዘህ ወደ እነዚህ ስብሰባዎች ሁሌም መምጣት አለብህ።

ከአባላት ስብሰባዎች በተጨማሪ፣ ከቤተ ክርስትያን ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ከአመራር ቡድንህ (ምእመናን ሽማግሌዎች እና ዲያቆናት) ጋር መገናኘት ያስፈልጋል። በእነዚህ ስብሰባዎች ወቅት፣ ከአመራር ቡድንህ ጋር ትጸልያለህ። አንድ ላይ ስብሰባ ማካሄድ፣ ራዕይን ማጋራት እና ለቤተ ክርስቲያን እድገት ስልቶችን ማዳበር ትችላለህ።

በተጨማሪም፣ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘርፍ መሪዎች፣ ለምሳሌ የሰንበት ትምህርት ዘርፍ ከሚመሩት፣ የቤት ለቤት ቡድኖች ከሚመሩት፣ የወንዶችና የሴቶች አገልግሎት መሪዎች፣ የወጣቶች አገልግሎት፣ የተልእኮ ኮሚቴ፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ፣ የወንጌል ሥርጭት፣ የአማላጅ የጸሎት ቡድኖች፣ እና ሌሎችም።[9]

# አፈንጋጭ አባላትን ሥርዓት ሥለማስያዝ

አመጸኛ የሆነን የቤተ ክርስቲያን አባል መቅጣት የሚያስፈልግበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱን ተግሣጽ ማድረግ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን ነው (ማቴ. 18:15-20፤ ሉቃ. 17:3፤ ዮሐ. 20:23፤ 1 ቆሮ. 5:1-5፤ ኤፌ. 5:11፤ 1 ጢሞ. 5፡19-20)። እንደ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ከዚህ ኃላፊነት መሸሽ የለብህም። ይልቁንም አጋጣሚው ሲፈጠር የተግሣጽ ዓላማ ሁለት መሆኑን አውቀህ ድፍረትንና ርኅራኄን በተሞላበት ቤተ ክርስቲያንን ለማንጻት (ሐዋ. 5፡9-11) እና ጥፋተኛውን ለመመለስ መስራት ይገባል (ገላ. 6፡1) .

አንተ እና የቤተክርስቲያኑ አመራር ተግሣጽ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ስትወስኑ፣ ኢየሱስ በማቴዎስ 18፡15-20 ያለውን ሥርዓት መከተል አለባችሁ። ይህ አሰራር ሶስት ደረጃዎችን ያካትታል። በመጀመሪያ፣ ፓስተሩ ወይም የተሾመው የቤተ ክርስቲያን መሪ ወደ ጥፋተኛው አባል በመሄድ ክሱን መወያየት እና

[8] ስለ ሰርግ እና የቀብር ሥነ ሥርዓቶች ተጨማሪ ለማወቅ ምዕራፍ 41ን "ሠርግና የቀብር ሥነ ሥርዓቶችን በመፈጸም" የሚለውን ተመልከት።

[9] ከአገልግሎት መሪዎች ጋር በመሥራት ላይ የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ምዕራፍ 33፡ "የምእመናን መሪዎችን ማሰባሰብ" እና ምዕራፍ 34፡ "የቤተ ክርስቲያን መምሪያዎችን መምራት" የሚለውን ተመልከት።

ንስሐ እንዲገቡ መጠየቅ ያስፈልጋል። ይህ ሙከራ ጉዳዩን ካልፈታው፣ አባሉ ከፓስተሩ እና ከቤተ ክርስቲያን አመራር ጋር እንዲገናኝ መጥራት ይገባል። ተግሣጽ ተቀባዩ አባል አሁንም ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ጉዳዩ በጉባኤው አባላት ፊት በተለየ የሥራ ስብሰባ ላይ ማቅረብ ያስፈልጋል። በዚህ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ የሚፈቀድላቸው ቋሚ የቤተ ክርስቲያን አባላት ብቻ ናቸው። የዚህ ጉባኤ ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል። ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ አጥፊው አባል ከቤተ ክርስቲያን አባልነቱ ሊባረር ይችላል(ማቴ. 18፡17)። ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ አነስተኛ የዲሲፕሊን እርምጃዎች ሊተገበሩ ይችላሉ።

# ~ ክፍል 9 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ተልዕኮ

# ~ ምዕራፍ 36 ~

# የአዲስ ኪዳን ስትራቴጂን መረዳት

መጽሐፍ ቅዱስ የጠፋውን የሰው ልጅ ስለ መቤዠት የእግዚአብሔር አስደሳች የተልዕኮ ሂደት ታሪክ ይነግረናል። እግዚአብሔርን የሚከተሉ ሁሉ በተልዕኮው እንዲተባበሩት እንዴት እንዳዘዛቸውም ይገልፃል። ስለዚህ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እራሱን ወይም እራሷን ለዚህ እጅግ አስፈላጊ ተግባር መተግበር እና መተባበር አለበት። እያንዳንዳችን ራሳችንን፣ "ቤተ ክርስቲያኔን በአገር ውስጥ፣ በአፍሪካ እና በዓለም ዙሪያ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ለመፈጸም የበኩሏን እንድትወጣ እንዴት በተሻለ መንገድ መምራት እችላለሁ?" ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። መልሱ በኢየሱስና በሐዋርያቱ በአብነት የታየውን የተልእኮ ስልት መከተል ነው።

ኢየሱስ በህይወቱ እና በአገልግሎቱ ቤተ ክርስቲያን እንዴት የእግዚአብሔርን ተልእኮ መወጣት እንዳለባት የሚያሳይ ትክክለኛ ዘዴ አሳይቷል። ሐዋርያቱ ይህን ተረድተው የኢየሱስን አርዓያ ተከትለዋል። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን፣ እና የክርስቶስ ተልእኮ ወራሾች፣ እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን። ይህ ሞዴል አንዳንድ ጊዜ "የአዲስ ኪዳን የመንፈስ ስትራቴጂ" ተብሎ ይጠራል። ይህ ምዕራፍ ይህንን ስልት በጥንቃቄ ይመረምራል። እንዲሁም በአፍሪካ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደመሆንህ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስልቱን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደምትችል ምክሮችን ይሰጣል።

## የሐዋሪያት ሥራ ሚሲዮናዊ አላማ

ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን የጻፈው በሚስዮን ዓላማ ነው። ሉቃስ ዘመን ላለችው ቤተ ክርስቲያን - ደግሞም በሁሉም ዘመን ለምትኖረው ቤተ ክርስቲያን - ወደ ጴንጤቆስጤያዊ እና ሚስዮናዊ ሥራዎቿ እንድታተኩር ጻፈ። ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ ተጀመረች ለአንባቢዎቹ በመንገር፣ እና እንዴት በከባድ ስደት ውስጥ፣ በመንፈስ ሀይል ድል እንዳደረገች በመዘገብ፣ አንባቢዎቹ ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ

ለማበረታታት ጻፈ። ስለዚህም ሉቃስ ኢየሱስ እስኪመለስ ድረስ በሁሉም ባህል እና በሁሉም ዘመን የሚሰራ የሚስዮናዊ ስልት ለማቅረብ የሐዋርያት ሥራን ጽፏል።

የሉቃስ የጽሑፍ ዋና ዓላማ በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ውስጥ ተገልጧል፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ *"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* እነዚህ የኢየሱስ ቃላት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የቀረቡትን የተልእኮዎች ዘዴ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው። በመጽሐፉ ውስጥ የተደጋገመ ንድፍ ያስተዋውቃሉ።

**የመንፈስ ቅዱስ መሞላት**

**—ሁልጊዜም ውጤቱ —**

**በመንፈስ የታጠቀ ምስክር መሆን ነው።**

ይህ ንድፍ የሉቃስ "የታጠቀ-ምሥክር ትኩረት" ተብሎ ይጠራል። ትኩረት ስንል በመፅሃፍ ውስጥ የተደጋገሙ የቃላት፣ ጽንሰ-ሀሳቦች ወይም ክስተቶች ንድፍ ማለት ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ይህ ንድፍ ተደጋግሟል። መንፈሱ በፈሰሰ ቁጥር ውጤቱ በመንፈስ የታጠቀ ምስክር መሆን ነው። ሁሉም የመንፈስ መፍሰስ ታሪኮች ያለ ልዩነት የሚያሳዩን ይሄንን ነው።[1]

የሐዋርያት ሥራ 1፡8 ተስፋ ዛሬም በእኛ ላይ ይሠራል። እንደ መጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ በወረደ ጊዜ እኛም ኃይልን መቀበል እንችላለን። እንደነሱ፣ በአካባቢያችን ጀምረን እና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መንፈስ ኃይል የክርስቶስ ምስክሮች መሆን እንችላለን።

# አዲሱ ኪዳን ስልት

ጳውሎስ ይህንን የሐዋርያት ሥራ 1፡8 ስልት በሮማዊያኑ ከተማ በኤፌሶን እንዴት እንደተገበረ እንመልከት (ሐዋ. 19፡1-11)። ይህን ስናጠና፣ የጳውሎስ ስልት ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ለማንቀሳቀስ የተጠቀመበት ስልት ቅጂ መሆኑን እንገነዘባለን። እኛም እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተክርስቲያኖቻችንን ለስብከተ ወንጌል ለቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ተልዕኮዎችን ለማንቀሳቀስ ልንጠቀምበት የሚገባ ስልት ነው።

## የኤፌሶን ተምሳሌታዊ አገልግሎት

ሉቃስ በኤፌሶን የነበረውን የጳውሎስን አገልግሎት የዘገበው፣ ጳውሎስ በሚስዮናዊነት ሥራው የተጠቀመበትን ስልት እንደ ምሳሌ ለማቅረብ ነው፡ ለቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ተልዕኮ ዘላቂ ስልት እንዲሆን ለማቅረብ አልሞ ነበር። ጳውሎስ በኤፌሶን ብቻ ሳይሆን በትንሿ እስያ (የዛሬዋ ምዕራብ ቱርክ)ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል ይህንን የመንፈስ ስልት እንዴት እንደተጠቀመ እንመልከት።

[1] በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ በዴንዚል አር. ሚለር የተዘጋጀውን *የሐዋርያት ሥራ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሚስዮን* በሚል የተዘጋጀውን የአፍሪካ ተስፋ ግኝት ተከታታይ መጽሐፍ ተመልከት።

## በኤፌሶን የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ (የሐዋርያት ሥራ 19:1-7)

ጳውሎስ ኤፌሶን የደረሰው ግልጽ የሆነ ግብ ይዞ ነበር። ዓላማው በቁጥር 10 ላይ ተገልጿል፤ ሉቃስ ከሁለት ዓመት በኋላ "በእስያ አውራጃ ይኖሩ የነበሩት የአይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት ቻሉ" ሲል ይነግረናል። የጳውሎስ ዓላማ ኤፌሶን እና ትንሿ እስያን ሁሉ በክርስቶስ መልእክት መድረስ ነበር። ጳውሎስ ግቡን ለማሳካት ግልጽ የሆነ ስልት በአእምሮው ይዞ ነበር። ይህ ስልት በሐዋርያት ሥራ 19፡1-11 በኤፌሶን የነበረውን አገልግሎት በጥንቃቄ በመመርመር የምናገኘው ነው። ይህን በአእምሯችን ይዘን፣ ጳውሎስ በኤፌሶን ያደረገውን እንመልከት።

ጳውሎስ ወደ ከተማዋ በደረሰ ጊዜ አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት አገኘ። እነዚህ ሰዎች የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የወደፊት መሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም (ሐዋ. 18፡24-27)። ወዲያው ጳውሎስ፣ "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" ሲል ጠየቃቸው(19:2)። ሐዋርያው ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እነዚህ ሰዎች በወንጌል ወደ ኤፌሶን እና እስያ የመድረስ ተልዕኮ ለመሳተፍ በመንፈሳዊ የታጠቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነበር። ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 1፡4-8 የኢየሱስን ትምህርት ተግባራዊ እያደረገ ነበር (ሉቃስ 24፡49)።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ጳውሎስ በአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ላይ እጁን ጫነባቸው እና "መንፈስ ቅዱስም ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ" (ሐዋ. 19፡6)። "መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ" የሚለው ሐረግ ኢየሱስ በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ...ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (አጽንዖት ተጨምሯል)" ያለውን የተስፋ ቃል ያስታውሰናል። ይህ ግንዛቤ በዚህ ምንባብ ውስጥ እየሆነ ያለውን ነገር እንድንረዳ ይረዳናል። መንፈስ ቅዱስ በጴንጤቆስጤያዊ ዕለት በደቀ መዛሙርቱ ላይ "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳም ሁሉ፣ በሰማርያ፣ እስከ ምድር ዳርም ድረስ" ምሥክር እንዲሆኑ እንደወረደ ሁሉ በእነዚህ ሰዎች ላይ ወረደ።

መንፈስ ቅዱስ በኤፌሶን አሥራ ሁለቱን እንደሞላ፣ "በልሳኖች ተናገሩ፣ ትንቢትም ተናገሩ፣" ይህም ክርስቶስ ስለ እርሱ እንዲናገሩ ኃይል እንደሰጣቸው ያሳያል።

## የኤፌሶን ዘመቻ (የሐዋርያት ሥራ 19:8-11)

እነዚህ አሥራ ሁለቱ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከተቀበሉ በኃላ፣ጳውሎስ የስብከተ ወንጌል እና የቤተ ክርስቲያን ተከላ ዘመቻውን ጀመረ። ይህ ዘመቻ ለሁለት ዓመታት የቀጠለ ሲሆን "በእስያ አውራጃ የሚኖሩ አይሁዶችና ግሪካውያን ሁሉ" የክርስቶስን ምሥራች እንዲሰሙ ሆኖል (ቁ. 10)። እንዴት ያለ አስደናቂ ስኬት ነው! በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በእስያ የሚኖሩ ሁሉ የተለያዩ ሁሉም ባሕሎችን የሚከተሉና የተለያዩ ጎሣዎችም ጭምር ወንጌሉን ሰሙ። በተጨማሪም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተተከሉ። ይህ ቁጥር በራዕይ 2-3 ላይ የተጠቀሱትን ሰባት የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ሳይጨምር አልቀረም።

## የመንፈስ ስልት

ሉቃስ በኤፌሶን የነበረውን የጳውሎስን አገልግሎት ታሪክ ሲጽፍ የሐዋርያው የሚስዮናዊነት ስልት ፍጹም ምሳሌ በማድረግ ነው። ወደ ኃላም በመመለስ በመጀመርያውና በሁለተኛው ሚስዮናዊ ጉዞው ያሳየው የሚስዮናዊ ስልቱን ያስረዳል። ዛሬ እኛ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን በራሳችን የስብከተ ወንጌል እና የቤተ ክርስቲያን ተከላ ጥረት ልንጠቀምበት የሚገባ ስልት ነው። ይህንን የመንፈስ ስልት በጥልቀት ስንመለከተው ሦስት ቁልፍ "ምሰሶዎች"ን ያካትታል፡-

**1. ምሰሶ አንድ፡ ማብቃት።** የጳውሎስ ሚስዮናዊ ስልት የመጀመሪያው ምሰሶ በመንፈስ ቅዱስ ማስታጠቅ ነበር። የመንፈስ ቅዱስ ማስታጠቅ ሁለት አተገባበር አለው። በመጀመሪያ፣ ሚስዮናዊውን ራሱ ማበረታታትን ያካትታል። ከዚያም ቤተ ክርስቲያንን ወይም አብያተ ክርስቲያናትን መተከልን ይጨምራል። እነዚህን አስፈላጊ ጉዳዮችን እያንዳንዳቸውን እንይ፡-

ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ኤፌሶን ገባ። ይሄን ሲያደርግ በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ በኢየሱስ ትዕዛዝ መሰረት በመንፈስ የታጠቀ ምስክር ሆኖ እያገለገለ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ በአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ላይ እጁን መጫን መቻሉ ራሱ በመንፈስ መሞላቱን ያሳያል። በተጨማሪም፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ሉቃስ የጳውሎስን በመንፈስ ኃይል ስላደረገው አገልግሎት ብዙ ምሳሌዎችን ይሰጣል (ለምሳሌ፣ የሐዋርያት ሥራ 9፡17-20፤ 13፡4-5፣ 9-11፤ 14፡8-10፤ 15፡12)።

ጳውሎስ ግን የእርሱ በመንፈስ መሞላት ብቻውን በቂ እንዳልሆነ የተረዳ ነበር። ሥራው እንዲበለጽግ ከተፈለገ በኤፌሶን ያለችው ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስም መታጠቅ እንዳለባት ተረድቷል። ስለዚህ፣ ወደ ከተማዋ እንደደረሰ፣ የጳውሎስ የመጀመሪያ ስራ በዛ ከተማ ያሉ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃቸውን ማረጋገጥ ነበር። ስለዚህም ነው አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት “ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?” ብሎ የጠየቃቸው። ለዚህም ነው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ከእነርሱ ጋር የጸለየው። ስለዚህ፣ የጳውሎስ ሚስዮናዊ ስትራቴጂ የመጀመሪያ አምድ ሁለቱ አስፈላጊ ክፍሎች የሚስዮናውያንን በመንፈስ ቅዱስ መታጠቅ እና የቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መታጠቅ ናቸው።

በዚህ መንገድ በኤፌሶን የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን በሁሉም የግዛቱ ማዕዘናት የምትደርስ ኃይለኛ የሚስዮናውያን ማዕከል ልትሆን ችላለች። እነዚሁ ሁለት አካላት፣ ሚሲዮናዊያንን በመንፈስ ቅዱስ ማስታጠቅ እና ቤተ ክርስቲያንን ማስታጠቅ የተልዕኮአችን ስትራቴጂ አካል መሆን አለበት። የጳውሎስ የመንፈስ ስልት ከዚህ በታች ቀርቧል፡

---

**አዲሱ ኪዳን “የመንፈስ ስልት”**

(የሐዋርያት ሥራ 19:1-11)

| **አምድ 1፡ ማስታጠቅ** | **አምድ 2፡ መመስከር** | **አምድ 3፡ በማስተባበር** |
|---|---|---|
| ● ሚስዮናዊያንን | ● ማወጅ | ● ማሰልጠን |
| ● ቤተ ክርስቲያንን | ● ማሳየት | ● መላክ |

---

**2. ሁለተኛው አምድ፡ መመስከር።** ሁለተኛው የጳውሎስ ሚስዮናዊ ስልት ምስክር መሆን ነው። በድፍረት መመስከር በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ውጤት ነው (ሐዋ. 1፡8፤ 4፡31)። እንደ ማስታጠቅ ሁሉ ምስክር መሆን ደግሞ ሁለት ክፍሎች አሉት፡ ማወጅ እና ማሳየት (ምስል 1 ይመልከቱ)።

በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ በብርቱ የወንጌል አዋጅ ስለ ክርስቶስ መስክሯል። ይህ አዋጅ የተጀመረው አሥራ ሁለቱ “በልሳኖችና ትንቢት ሲናገሩ” ነው። የሐዋርያት ሥራ 1፡8ን እንደ የትርጓሜ ቁልፍ በመጠቀም፣ ልክ ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን (2፡14) እንደ ተናገረው ትንቢታዊ አዋጅ፣ የአስራ ሁለቱ ትንቢት በመንፈስ ኃይል ለጠፉት የወንጌል ማወጅ መሆኑን መረዳት እንችላለን።

ከዚያም ሉቃስ “ጳውሎስም ወደ ምኵራብ እየገባ፣ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያሳመናቸው ሦስት ወር ሙሉ ምንም ሳይፈራ ፊት ለፊት ይናገር ነበር” (ሐዋ. 19፡8) በማለት ይነግረናል። በሐዋርያት ሥራ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማወጅ የክርስቶስን ምሥራች ከመስበክ ጋር እኩል ነው (8፡12፤ 28፡23፣ 31)። ጳውሎስ በምኩራብ ውስጥ ክርስቶስን ከማወጁ በተጨማሪ “በአደባባይም ሆነ ከቤት ቤት በመዘዋወር፣ እናንተን ከማስተማርና ይጠቅማችኋል ብዬ ያሰብሁትን ከመስበክ ወደ ኋላ አላልሁም። 21 በንስሓ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና በጌታችን በኢየሱስ እንዲያምኑ፣ ለአይሁድም ለግሪክ ሰዎችም አጥብቄ መስክሬላቸዋለሁ” ይለናል(20፡20-21)። በኤፌሶን የነበረው የጳውሎስ ምስክርነት የመንግሥቱን ሥልጣን በሚያሳዩ ምልክቶች የተደገፈ ነበር (19፡11-20)።

ስለዚህ፣ ልክ እንደ መጀመሪያው፣ ይህ ሁለተኛው የጳውሎስ የመንፈስ ስልት ሁለት ክፍሎች አሉት፡ - ወንጌልን በድፍረት ማወጅ እና በሚከተሉ ምልክቶች የመንግሥቱን ኃይል ማሳየት ናቸው። ምንም ጥርጥር የለውም፣ በኤፌሶን በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት ሰዎች ምስክርነታቸው ተመሳሳይ ሁለት ሂደትን፣ አዋጅን እና ምልክቶችን፣ ያካተተ ነበር። እነዚህ ሁለት ሂደቶች ዛሬ በአፍሪካ ውስጥ ባለችው የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ሊታዩ ይገባል።

**3. ሦስተኛው አዕማድ ፡ በማስተባበር።** ሦስተኛው የጳውሎስ ሚስዮናዊ የመንፈስ ስትራቴጂ ማስተባበር ነበር። ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ኃይል ከታጠቀች እና ወንጌል እየታወጀ እና በምልክቶች እየተረጋገጠ ስለ ነበር ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ለክልላዊ ተልእኮዎ ማንቀሳቀስ ጀመረ። ይህ ቅስቀሳ በሐዋርያት ሥራ 19፡10 ላይ ተገልጿል፡- “ይህን ማድረጉንም ሁለት ዓመት ስለ ቀጠለ፣ በእስያ አውራጃ ይኖሩ የነበሩት የአይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት ቻሉ” ጳውሎስ ከኤፌሶን ሳይወጣ በሁለት አጭር ዓመታት ውስጥ በወንጌል ወደ እስያ አውራጃ ሁሉ ደረሰ። ይህ ሊሳካ የቻለው በኤፌሶን ያሉትን ደቀ መዛሙርት በብቃት በማስተባበር በመቻሉ ነው።

ጽሑፉ የሚያመለክተው ጳውሎስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንን በሁለት መንገዶች ማለትም በማሰልጠን እና በመላክ እንዳስተባበረ ነው (ምስል 1 ይመልከቱ)። በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ በጢራኖስ ትምህርት ቤት ሰራተኞችን እና የቤተ ክርስቲያን ተካዮችን አሰልጥኗል (ሐዋ. 19፡9)። እንደ ዘገባው ከሆነ በጳውሎስ አመራር ስልጠና እና በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በእስያ የሚኖሩ ሁሉ የጌታን ቃል በመስማታቸው መካከል የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት እንዳለ ይጠቁማል። የትምህርት ቤቱ ሥርዓተ ትምህርት በስብከተ ወንጌል እና በቤተ ክርስቲያን መትከል ላይ ጠንካራ ተግባራዊ አጽንዖትን ያካተተ ይመስላል። በተጨማሪም፣ የትምህርት ቤቱ ድባብ በመንፈስ መገኘት የተሞላ መሆን አለበት።

የጳውሎስ የሥልጠና ሂደትም በሥራ ላይ የማሰልጠንን ዘዴ ያካተተ ይመስላል። ጳውሎስ በወንጌል አገልግሎቱ በመንፈስ የተሞሉትን አዲስ ደቀ መዛሙርት ስለማካተቱ በሐዋርያት ሥራ 19፡8-9 ላይ ፍንጭ እናገኛለን። በኤፌሶን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በቅርበት መቆየቱ ይህ የስልጠና ግንኙነት ስለመኖሩ ተጨማሪ ማስረጃ ነው (ቁ. 9፤ 20፡1፣17-18)። ጳውሎስ በሚስዮናዊነት ዘዴው ተማሪዎቹን መክሯቸዋል። በኋላም በኤፌሶን ለሚገኘው ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ “በብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ” (2 ጢሞ. 2:2) ብሎ አዞታል።

አንዴ ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ከተሞሉ እና ከሠለጠኑ ወይም ምናልባትም፣ ገና በስልጠና ላይ እያሉ ጳውሎስ ወንጌልን እንዲሰብኩ እና በመንፈስ ኃይል የተሰጣቸውን የሚስዮናውያን አብያተ ክርስቲያናትን እንዲተክሉ ወደ አውራጃው ክፍል ሁሉ ላካቸው። ምንም ጥርጥር የለውም፣ ልክ የአማካሪያቸውን የሚስዮናውያን ስልት ተጠቅመዋል። የዚህ ስልት መተግበር በመላው አውራጃ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በፍጥነት መብዛትን አስከትሏል (ሐዋ. 19፡10)። በተጨማሪም የጳውሎስ ስልት

ከተለያዩ ሕዝብ የተውጣጡ ሰዎችን ማነጋገርን እንደሚጨምር ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም ሉቃስ “አይሁድም ሆኑ ግሪካውያን” ወንጌልን እንደሰሙ ተናግሯል።

### የኢየሱስ ምሳሌ

ጳውሎስ ለኤፌሶን እና በትንሿ እስያ የተጠቀመበት ስልት የመጀመሪያው እንዳልነበረ ልብ ማለት ያስፈልጋል። የዚህ ስልት ምንጩ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ዓለም የላከበትን ምሳሌ መከተል ነበር።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በማሰልጠንና በመላክ ሚሲዮናዊያንን ማስተባበርን ምሳሌ ትቷል (ማር 3፡13-15)። ደቀ መዛሙርቱን ሲሄዱ ወንጌልን ይሰብኩና በሚከተላቸው ምልክት የመንግስቱን ኃይል ያሳዩ ነበር (ማር. 16፡15-18)። ይህን ከማድረጋቸው በፊት ግን፣ኢየሱስ ራሱ የመንፈስ ኃይል እንደተሰጠው (ሉቃስ 4፡18- 19፤ የሐዋርያት ሥራ 10:38)፣ ደቀመዛሙርት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ለማግኘት በኢየሩሳሌም መጠበቅ ነበረባቸው (ሉቃስ 24፡49፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡4-8)። የደቀ መዛሙርት በጴንጤቆስጤ ቀን እና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተዘገቡ በሌሎች በርካታ አጋጣሚዎች በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ለሥራው ታጥቀው ነበር። ጳውሎስ፣ በኤፌሶን ዘመቻው፣ ቤተክርስቲያኑን ወደ አካባቢው ሲልክ የኢየሱስን ምሳሌ እየተከተለ ነበር።

# ለእኛ ያለው ትምህርት

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን፣ ጳውሎስ በኤፌሶን በመንፈስ ኃይል ስለተሰጠው አገልግሎት ካደረግነው ምርመራ አንዳንድ ጠቃሚ ትምህርቶችን ልንማር እንችላለን። ከእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ሦስቱን እንመልከት፡-

### በመንፈስ መታጠቅ

በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ በራሳችን ሰብዓዊ ኃይል ወይም ችሎታ ለመሥራት ፈጽሞ ማሰብ እንደሌለብን እንማራለን። በተቃራኒው፣ እንደ ኢየሱስ እና ጳውሎስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና ቅባት ማገልገል አለብን። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አብነት መሠረት፣ ይህ መለኮታዊ ኃይል የሚመጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ስንጠመቅ እና ስንታጠቅ ነው። በየቀኑ በመንፈስ ስንመላለስ መንፈሱ በእኛ ይኖራል።

በተጨማሪም፣ ቤተ ክርስቲያኖቻችን የውጤታማ ወንጌል ሥርጭት፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እና የተልእኮ ማዕከላት እንዲሆኑ ከተፈለገ ግቡን ከዳር ለማድረስ አስፈላጊ የሆነ መንፈሳዊ ኃይል ሊኖራቸው እንደሚገባ እንማራለን። ስለዚህ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን የመጀመሪያ ስራችን መሆን ያለበት በቤተክርስቲያኖቻችን መንፈስ ቅዱስ ስልጣን መያዙ ነው። ወደ ክርስቶስ የሚመጡት ወዲያውኑ ወደ መንፈስ ጥምቀት እንዲያመሩ እና በመንፈስ የተሞላ ሕይወት እንዲመሩ በማስተማር ይህንን ዓላማ ማሳካት እንችላለን። በተጨማሪም፣ እነዚሁ ሰዎችን ወደ መንፈስ የታጠቀ ምስክርነት መምራት አለብን።[2]

---

[2] ቤተክርስቲያን መንፈስን እንድትፈልግ ስለማበረታታት፣ ምዕራፍ 19ን “ቤተክርስቲያንን ወደ ጴንጤቆስጤ ሪቫይቫል መምራት" የሚለውን ተመልከት። አማኞችን ወደ መንፈስ ኃይል ስለመምራት፣ ምዕራፍ 20ን ተመልከት፡ “አማኞችን ወደ መንፈስ ጥምቀት መምራት" የሚለውን ተመልከት።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስልት ተጠቀም

ሁለተኛ፣ የስብከተ ወንጌል ሥራን፣ የቤተ ክርስቲያንን ተከላ እና ተልእኮዎችን ለማከናወን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው፣ በመንፈስ የሚመራ ስልት መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን እንማራለን። በኤፌሶን ጳውሎስ በዚህ ዓይነት ዘዴ ተመርቶ ነበር። ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያስቀድም ስልት ነበር። ጳውሎስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ለዓለም አቀፋዊ ተልእኮዎች ለማነሳሳት የተጠቀመውን ስልት ይከተል ነበር።

በተጨማሪ፣ የጳውሎስ ዓላማ በመንፈስ ኃይል የታጠቀ የሚስዮናውያን ጉባኤዎችን በትንሿ እስያ በሙሉ ለመበተን ነበር። እነዚህ ጉባኤዎች እያንዳንዳቸው ሚስዮናውያን አብያተ ክርስቲያናትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመትከል የሚያስፈልጋቸውን ራዕይ እና መንፈሳዊ አቅም ያጎለበቱ ናቸው። በዚህ መንገድ፣ አብያተ ክርስቲያናት በመላው እስያ በዝተዋል፣ እናም ወንጌሉ በዚያ ለሚኖሩት ሁሉ - ለአይሁድም ለአሕዛብም በኃይል ተሰብኮል።

ዛሬም እኛ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ተመሳሳይ ነገር ማድረግ አለብን። በእርግጠኝነት፣ ሰዎችን እንዲድኑ መጣር አለብን። ሆኖም፣ ወንጌል ስርጭት፣ አስፈላጊ ቢሆንም፣ በራሱ በቂ እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባናል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚስዮናውያን አብያተ ክርስቲያናትን መትከል እና ማዳበር አለብን። በመንፈስ የሚስዮናውያን አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ የተሞሉ፣ የክርስቶስን መንገድ የተማሩ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በብቃት ለማራመድ የሰለጠኑ እና ከዚያም በቅርብ እና በሩቅ ስፍራዎች ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ የተነሳሱ እና የተላኩ አማኞች ናቸው።

## ሆን ተብሎ መንቀሳቀስ

በመጨረሻም፣ በምናደርገው ነገር ሁሉ፣ ሆን ብለን መንቀሳቀስ አለብን። ብዙ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ያለ ግልጽ ዓላማ ይከናወናል። በጣም ብዙ ጊዜ በግምት የምናደርጋቸው ነገሮች ይበዛሉ። ነገር ግን በእሁድ በሮችን ስለከፈትን ብቻ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያናችን ይመጣሉ ብለን ማሰብ አንችልም። ‘በንስኃ ጸሎት’ ስለመራናቸው ብቻ ሰዎች ዳግመኛ ተወልደዋል ብለን ማሰብ አንችልም። አንዳንድ ውጫዊ መገለጦችን ስላሳዩ አማኞች በእውነት በመንፈስ ኃይል እንደተጠመቁ መገመት አንችልም። አጥቢያ ቤተክርስቲያናችን የጴንጤቆስጤያዊ ወይም የካሪዝማቲክ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በመሆኗ ብቻ በመንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ አለ ብለን ልንገምት አንችልም። ቤተ እምነት በእነዚህ ነገሮች ስላመነ ብቻ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን የሚስዮናዊ ራዕይ እና ቅንዓት ታዳብራለች ብለን መገመት አንችልም። በተቃራኒው፣ ልናሳካው የምንፈልገውን ነገር ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል፣ እናም አላማችንን ለማሳካት እንዴት እንደምንሄድ ማወቅ አለብን።

እያንዳንዱን ውሳኔ እና እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ሆን ተብሎ መደረግ አለበት። በመንፈስ ቅዱስ በእውነት ለመሞላት (ወይም ደጋግሞ ለመሞላ) በማሰብ በግል የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ አለብን። የጠፋውን ንስሐ ገብቶ በእውነት ዳግም ሲወለድ ለማየት በፈለግን ወንጌልን መስበክ አለብን። በእውነት በእግዚአብሔር መንፈስ እንዲጣጠቁ በማሰብ ከአማኞች ጋር መጸለይ አለብን። አብያተ ክርስቲያናትን ስንተክል በመንፈስ የታጠቁ የሚስዮናውያን አብያተ ክርስቲያናት እንዲሆኑ በማሰብ መሆን አለበት።

ይህ ሁሉ ሲሆን ራዕያችንን እና ስልታችንን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያስነሣቸው መሪዎች አቅደን ማስተላለፍ አለብን። ከዚያም ወደ ከተማችን፣ አገራችን፣ ክልላችን፣ እና አሕዛብን በወንጌል ለመድረስ በማሰብ ቤተ ክርስቲያንን ማንቀሳቀስ አለብን። ኢየሱስ ያደረገው ይህንን ነበር። ጳውሎስም በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ  በእስያ ሁሉ ወንጌልን ያዳረሰው በዚህ መንገድ ነበር። ዛሬም ማድረግ ያለብን ይህ ነው።

# ~ ምዕራፍ 37 ~

# የጠፋትን በወንጌልን መድረስ

አንድን ሰው ብቻ ወደ ክርስቶስ መምራት ምን ያህል አስፈላጊ ነው? እርግጥ ነው፣ ለአንድ ሰው ዘላለማዊ ሕይወት አስፈላጊ ነው። ሆኖም፣ የሚከተለው ታሪክ እንደሚያሳየው ይህ አንዱ የክርስቲያናዊ ፍቅር ተግባር ለብዙ ሌሎችም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ኤድዋርድ ኪምባል በዲትሮይት፣ ሚቺጋን፣ አሜሪካ ውስጥ ትንሽ የሱቅ ሰራተኛ ነበር። በቤተክርስቲያኑ ደግሞ የሰንበት ትምህርት ቤት መምህርም ነበር። በ1854 ኪምባል ድዋይት የተባለ የአስራ ሰባት አመት ልጅ አገኘውና ጌታን መሰከረለት። ይህ ልጅ አድጎ ታዋቂው ወንጌላዊ ዲ.ኤል. ሙዲ ሆነ። ሙዲ በታሪክ ብዙዎችን ወደ ጌታ ካመጡ ሰዎች አንዱ ነው። ሙዲ በተጨማሪ ኤፍ ቢ ሜየርን ወደ ወንጌል እና ተልእኮ ሥራ እንዲገባ ተጽዕኖ አሳደረበት፣ እርሱም በተራው በጄ.ዊልበር ቻፕማን ላይ ተጽእኖ አሳድሯል፣ እርሱም ቢሊ ሰንደይን በወንጌል ያሳደገው ነው። የዘመናችንን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያጠና ማንም ሰው እነዚህ ሁሉ ሰዎች ኃያላን ወንጌላውያን እንደነበሩ ያውቃል። አንድ ላይ ሆነው ሚሊዮኖችን ለክርስቶስ አሸንፈዋል። ታሪኩ ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

መርዶክዮስ ሃም የሚባል የገጠር ሰባኪ የቢሊ ሰንደይ አገልግሎትን እንደ ምሳሌው ያይ ነበር። ከዚያም፣ በ1934፣ ሃም ቢሊ ግራሃምን ህይወቱን ለክርስቶስ እንዲሰጥ ያደረገውን መልእክት ሰብኳል። ቢሊ ግርሃም በታሪክ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች በበለጠ ለብዙ ሰዎች ወንጌልን ሳይሰብክ አልቀረም። ይህ ሁሉ የሆነው የሰንበት ትምህርት መምህር አንድን የጎዳና ልጅን ወደ ክርስቶስ በማምጣቱ ነው። የኤድዋርድ ኪምባል ታሪክ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ቤተክርስቲያኑን ወደ ውጤታማ የወንጌል አገልግሎት መምራት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። ይህ ምዕራፍ ይህን በተሻለ ሁኔታ እንዴት ማድረግ እንደምትችል ያብራራል።

# ትርጓሜዎች

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የወንጌል ስርጭት ምን እንደሆነ እና ከቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ተልእኮዎች ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግልጽ የሆነ መረዳት ሊኖርህ ይገባል። ሦስቱም ተግባራት ከክርስቶስ ታላቅ ተልዕኮ የሚወጡ ቢሆንም (ማቴ. 28፥18-20፤ ማር. 16፥15-16) አንዳንድ አስፈላጊ ልዩነቶች አሉዋቸው።

## የወንጌል ስርጭት

የወንጌል ስርጭት የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በማሰብ ወንጌልን በዓላማ ማካፈል ነው። ስለ ኢየሱስ እና በመስቀል ላይ ስላደረገው የማዳን ስራ ለሰዎች መንገርን እና በእርሱ ወዳለ እምነት መጥራትን ያካትታል (ሐዋ. 16፥31)። የወንጌል ስርጭት ማእከል የኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ ታሪክ ነው (1ቆሮ. 15፥1-4)። የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፕሮግራም በላይ ነው፣ የቤተክርስቲያኑ የመኖር ምክንያት ነው። ደግሞም የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው።

## የቤተ ክርስቲያን ተከላ

የቤተ ክርስቲያን ተከላ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ላይ ቢመሰረትም፣ ብዙ ነገሮችን ያካትታል። የቤተ ክርስቲያን ተከላ የዳኑትን አማኞች ወደ አካልነት ማደራጀትን ያካትታል። እነዚህ አማኞች ለሕብረት፣ ለጸሎት እና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘወትር ይሰበሰባሉ። እነዚህን አማኞች የክርስቶስን መልክ እንዲመስሉ የሚመሩዋቸውን መሪዎች ይመርጣሉ። አዲስ አማኞች እንዴት አሮጌውን የኃጢአተኛ ማንነታቸውን ትተው፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲኖሩ እና ለሌሎች ስለ ኢየሱስ እንዲናገሩ ይማራሉ።

## ተልዕኮ

ተልእኮ ብዘውን ጊዜ የወንጌል ስርጭት እና የቤተ ክርስቲያን መትከልን ያጠቃልላል። ሆኖም፣ አንዳንድ ጉልህ ልዩነቶች አሉ። ተልእኮ ባህል ዘለል ወንጌል ስርጭትን እና ባህል ዘለል አብያተ ክርስቲያናትን መትከልን ያካትታል። ሚስዮናውያን ቤታቸውን ትተው ወደ አዲስ ቦታ ሄደው አዲስ ቋንቋ እንዲማሩ እና ከአካባቢያቸው ሕይወት ጋር እንዲላመዱ ይጠበቅባቸዋል። በዚያ "ባዕድ" አውድ ውስጥ፣ የጠፉትን ለኢየሱስ አሸንፈው አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ይተክላሉ።

ጳውሎስ የሚስዮናውያን ምሳሌ ነው። ለጠፉት ክርስቶስን ለማወጅ ድንበርና ባህል ተሻገረ። አብያተ ክርስቲያናትን ተክሎ እድገታቸውን ይከታተል ነበር። አብያተ ክርስቲያናት እንዲያድጉ ጳውሎስ እነዚህን አጥቢያዎች የሚመሩ አካባቢ በቀል ሽማግሌዎችን እና መጋቢያን ሾመ። ከመጋቢዎቹ ሀላፊነት አንዱ አጥቢያቸውን መምራት፣ ለጠፉትን ወንጌልን መስበክ እና ሚስዮናውያንን መላክ ነበር። ይህም የስብከተ ወንጌል ሥራ፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ እና ተልእኮዎች እንዲቀጥሉ አድርጎል (1ተሰ. 1፥8)።

# መጋቢያዊ ኃላፊነት

ጳውሎስ ለእምነት ልጁ ለሆነው ጢሞቴዎስ እና በኤፌሶን ባለች ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ለነበረው "የወንጌል ሰባኪን ተግባር አከናውን" በማለት ጽፎለታል (2 ጢሞ. 4፥5)። የወንጌል ሰባኪ ሥራ የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ማምጣት እና ሌሎችም በተመሳሳይ እንዲያደርጉ ማሰልጠን ነው (ኤፌ. 4፥11-12)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተም ይህን ሃላፊነት ትሸከማለች። ቤተ ክርስቲያን በወንጌል አገልግሎት ውጤታማ ለመሆን የወንጌል ንቅናቄ እቅድ ማውጣት አለብህ። ይህ የንቅናቄ እቅድ ሶስት ስልቶችን ማካተት አለበት ማነሳሳት፣ ስልጠና እና ማሰማራት። እንደሚከተለው ይቀርባል።

## የሚያነሳሳ

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያን ለስብከተ ወንጌል በማነሳሳት ሂደት የመጀመሪያ ስራህ በእግዚአብሔር ህዝብ ልብ ውስጥ ለጠፉት ሰዎች ፍቅርን መትከል ነው። ይህን ማድረግ የምትችልበት አንዱ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጆች መጥፋት የሚናገረውን በማስተማር ነው። ከኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ውጭ፣ ሁሉም ሰዎች ተስፋ ቢስ እና ለዘላለማዊ ጥፋት የተዳረጉ ናቸው። በዚህ ህይወት እና በሚመጣው ህይወት ተስፋቸው ክርስቶስን ማወቅ ብቻ ነው። ይህን አስደናቂ እውነት በሰዎችህ ልብ እና አእምሮ ላይ ማስቀመጥ አለብህ። በተጨማሪም ለጠፉት ሰዎች ወንጌልን የማካፈል ግዴታቸውን ማሳሰብ አለብህ።

ይህንን ለመፈጸም፣ በእግዚአብሔር ሚስዮናዊ መንፈስ መደገፍ ያስፈልጋል። የቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን እና ለክርስቶስ ምስክር ለመሆን መታጠቃቸውን ማረጋገጥ አለብህ (ሐዋ. 1፡8)። በተጨማሪም የመንፈስ መገኘት እና ኃይል በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ መገለጡን ማረጋገጥ አለብህ። ዕድሉ ከተመቻቸለት፣ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብ ውስጥ ይንቀሳቀሳል፣ ይቀርጻቸዋል እና ወደ መከሩ ይጠቁማል።

## ስልጠና

ቤተ ክርስቲያንን ለስብከተ ወንጌል ለማስተባበር የምትጠቀምበት ሌላው ስልት ስልጠና ነው። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። ደቀ መዛሙርቱን፣ "ተከተሉኝ፤ ሰው አጥማጆች አደርጋችኋለሁ" (ማርቆስ 1፡17) ብሎ አዘዛቸው። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጌታቸውን ሲከተሉ፣ ትምህርቱን ሲያዳምጡ እና የእርሱን ዘዴዎች ሲለማመዱ፣ ውጤታማ የወንጌል ሰባኪዎች ሆኑ።

በጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናችንም ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ዛሬ መከሰት አለበት። ኢየሱስና ሐዋርያቱ እንዳደረጉት ለአባሎቻችን ለጠፉትን እንዴት ወንጌልን እንደሚያካፍሉ ማስተማር አለብን። ይህን በማድረግ፣ በመንፈስ እንዴት እንደሚመላለሱ እና የመንፈስን ቅዱስ በምስክርነት ሂደት ሲመራቸው እንዴት ድምጹን እንደሚለዩ ማስተማር አለብን (ሐዋ. 8፡29)። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን፣ ህዝቦቻችን ለሌሎች ስለ ክርስቶስ ሲያካፍሉ በእነርሱ እንዲናገር በማመን፣ ለመንፈስ ቅባት እንዴት እንደሚገዙ የበለጠ ማስተማር አለብን።

በተጨማሪም፣ ቅዱሳን ወንጌልን እንዲረዱ እና ለሌሎችም በግልጽ መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ አለብን። ሰዎችን ወደ ኢየሱስ እንዴት እንደሚመሩ፣ ወደ ንስሐና ወደ እምነት መጥራት እንዳለባቸው የበለጠ መረዳት አለባቸው። ይህንን የምናሳካበት አንዱ መንገድ በመንፈስ የታገዘ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ላይ ዓመታዊ አውደ ጥናቶችን ማካሄድ ነው።

## ማስማራት

የእግዚአብሔር ሕዝብ አንዴ ከተነሳሱና ከሠለጠኑ በኋላ መሰማራት አለባቸው። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። አንዱ የሥልጠና ፕሮግራሙ አካል፣ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን እንዲሰብኩ መላኩ ነበር። ከዚያም ለግምገማ ወደ እርሱ ተመለሱ (ሉቃስ 9፡6፤ 10፡1-20)። በኋላ፣ በምድር ላይ ያለው አገልግሎቱ ሊያበቃ ሲል፣ ደቀ መዛሙርቱን "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳም ሁሉ፣ በሰማርያ፣ በምድር ዳርቻም" (የሐዋርያት ሥራ 1፡8) ለምስክርነት በቋሚነት አሰማራ። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተም እንዲሁ ማድረግ አለብህ። በሕዝብህ ፊት የስብከተ ወንጌል ሕይወትን በምሳሌነት ማሳየት አለብህ። ከዚያም አሰልጥነህ በአገልግሎት ልታሰማራቸው ይገባል።

# የወንጌል ሥርጭት ዘዴዎች

እንደ ታማኝ የኤንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስትያንህ ይመጣሉ ብለህ ተስፋ በማድረግ እና ስራ ፈትቶ መቀመጥ ሞኝነት ነው። እንዲሁም አባላት ለጓደኞቻቸው እና ለጎረቤቶቻቸው ምስክሮች ይሆናሉ ብለው ማሰብ የለብህም። እንደ መጋቢ አርአያ መሆን አለብህ። ህዝቡን ወደ መከር መምራት አለብህ። የበለጠ ስልቶችን በመንደፍ ቤተ ክርስቲያንን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለስብከተ ወንጌል ለማነሳሳት መርሃ ግብሮችን መተግበር አለብህ።

የተለያዩ የወንጌል አገልግሎት ዘዴዎችን በመጠቀም ይህንን ማድረግ ትችላለህ። የስልት ምርጫው የሚወሰነው በማህበረሰቡ አውድ፣ በሰሚዎቹ ተጨባጭ ሁኔታ እና በመንፈስ ቅዱስ አመራር ላይ ነው። ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ጥቂት የወንጌል ሥጭት ዘዴዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## መደበኛ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች

የወንጌል ሥርጭት አገልግሎት በቤተክርስቲያኑ የመደበኛ የእሁድ አገልግሎቶች ማዕከል መሆን አለበት። በጉባኤ ያሉትን ያልዳኑ ሰዎች ሁል ጊዜ አስብ። ለእነርሱም በታማኝነት ወንጌልን መስበክ ይገባል። እንደ ጳውሎስ “ክርስቶስንና እርሱን የተሰቀለውን” ብቻ ለመስበክ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ አለብህ (1 ቆሮ. 2፡1-2)። አንድ አባል ያልዳነ ወዳጁን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ መጥቶ ወንጌል ማይሰበክ ከሆነ እንዴት ያሳዝናል። የምትሰብከው እያንዳንዱ መልእክት ስለ እግዚአብሔር ድነት እቅድ የሚያብራሪ እና ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ግብዣን የሚያካት መሆን አለበት።

## የግል የወንጌል ስርጭት

በመደበኛው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወንጌልን ከማወጅ በተጨማሪ፣ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ላሉ ሰዎች እንዴት ወንጌልን ማካፈል እንደሚችሉ እንዲያውቁ ማድረግ አለብህ። ይህ ዓይነቱ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት የግል የወንጌል ስርጭት ይባላል። እንደ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ የሚከተሉትን የግል የወንጌል ስርጭት ዓይነቶች ለጉባኤ ማካፈል ትችላለህ።

**የቤት ለቤት የስብከተ ወንጌል አገልግሎት።** ከቤት ወደ ቤት በሚደረገው የምሥክርነት ዘመቻ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሰልጥነው ወደ መንደር እንዲሄዱ ይላካሉ። ሲደርሱም ራሳቸውን ከሕዝቡ ጋር በማስተዋወቅ የክርስቶስን ወንጌል ለአካባቢው ሕዝብ ያጋራሉ። እንደ ሕዝቡ ፍላጎት ለመጸለይ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው። ፍላጎት ለሚያሳዩ ሰዎች በግል ወንጌልን ለመካፈል ዝግጁ መሆን አለባቸው።

**ጓደኝነት የወንጌል ስርጭት።** እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አባላት ለወዳጆቻቸው መዳን እንዲጸልዩ ማስታጠቅ እና ማበረታታት አለብህ። እግዚአብሔርን የጓደኞቻቸውን ልብ እንዲከፍት እና ወንጌልን እንዲያካፍሉ እድል እንዲሰጣቸው መጠየቅ አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን አባላት ጓደኞቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲጋብዙ ለማበረታታት አመታዊ "የጓደኛ ቀን" መርሐግብር ማስያዝ ትፈልግ ይሆናል። በዚያ ቀን፣ ሁሉም የሚሳተፉ ወዳጆች የተለየ ትኩረት እና ክብር ያገኛሉ። ከዚያም የወንጌል መልእክት በመስበክ ክርስቶስን እንደ አዳኝ እንዲቀበሉ እድል ትሰጣቸዋለህ።

**የአኗኗር ዘይቤ ወንጌላዊነት።** እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም ሳይሆን የሕይወት ዘይቤ መሆኑን ህዝቡን ማስተማር ያስፈልጋል። ጉባኤውን ሕይወታቸውን እና የግል ምስክርነታቸውን እንዲያጋሩ ልታበረታታቸው ይገባል። በዕለት ተዕለት የሕይወት ሁነቶች መካከል ወንጌልን ለሌሎች ለማካፈል እድሉን የሚጠቀሙ መሆን አለባቸው።

## የወንጌል ዘመቻ

የወንጌል ዘመቻ (አንዳንድ ጊዜ የመነቃቃት ኮንፈረንስ ይባላሉ) ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሌላው ጥሩ መንገድ ነው። የወንጌል ሥርጭት ዘመቻ/የመነቃቃት ኮንፈረንስ በሚከተለው መልኩ ሊቀጥል ይችላል። አንተ እና የቤተክርስቲያናችሁ መሪዎች የዘመቻውን/የኮንፈረንሱን ፕሮግራም ማዘጋጀት እና ቀደም ብሎ ለቤተ ክርስቲያን ማስታወቅ። ዝግጅቱ ሲቃረብ፣ ቤተ ክርስቲያን ለፕሮግራሙ ተደጋጋሚ ጸሎት ማድረግ። አባላት ቤተሰቦቻቸውን፣ ጓደኞቻቸውን እና ጎረቤቶቻቸውን ወደ ኮንፈረንሱ እንዲጋብዙ ማበረታታት። እንደ መጋቢ፣ ለማገልገል የምትጋብዘው ሰው ለጠፉት ፍቅር እና ወንጌልን በመስበክ መልካም ስም እንዳለው ማረጋገጥ አለብህ። በተጨማሪም ሰባኪው እውነተኛ ወንጌልን በታማኝነት እንደሚሰብክ እና በስብከቱ መጨረሻ ጥሪ እንደሚያቀርብ ማረጋገጥ አለብህ።

## የመንገድ ላይ አገልግሎቶች

እንዲሁም የወንጌል ዘመቻውን ተከትሎ የጎዳናዎች የወንጌል ሥርጭትን አብሮ ማቀናጀት ይቻላል። ብዙ ሰዎች ወደ የሚሰበሰቡባቸው ጎዳናዎች ወይም ገበያዎች የወንጌል ቡድንን ማደራጀት እና መላክ ይቻላል። በዚያ አጭር ጊዜ ኃይለኛ የወንጌል መልዕክት ማስተላለፍ ይገባል። በእነዚህ አገልግሎቶች ሕዝብን ለመሳብ መዝሙርን መዘመር፣ ስለ የእግዚአብሔርን ጸጋ የግል ምስክርነቶችን ማካፈል፣ እና አጭር የወንጌል መልእክት በማቅረብ ክርስቶስን ለመቀበል ግብዣን ማድረግ ይገባል።

## የስነ-ጽሁፍ ስርጭት

ወንጌልን ለማዳረስ ሌላው መንገድ የስነ ጽሑፍ ስርጭት ነው። የወንጌል ጽሑፎችን ለማሰራጨት ሠራተኞችን ወደ ስትራቴጂካዊ ቦታ ለመላክ ማቀድ እንደ አንድ ፕሮግራም ሊያዝ ይገባል። ጽሑፎቹ በጥንቃቄ የተመረጡ፣ ማራኪ እና በደንብ የተጻፉ መሆን አለባቸው ደግሞም የመዳንን እቅድ በግልፅ ማሳየት አለባቸው። እንዲሁም የቤተክርስቲያኗን ስም፣ ቦታ እና ስልክ ቁጥር እንዲሁም የቤተክርስቲያኗን ድህረ-ገጽ እና የኢ-ሜይል አድራሻዎችን ጨምሮ የመገኛ አድራሻዎችን መያዝ አለባቸው።

## የጸሎት ጉዞዎች

ለወንጌል ምስክርነት አስቸጋሪ ቦታዎችን ክፍት ለማድረግ የጸሎት ጉዞዎችን መጠቀም ይቻላል። አካባቢውን ለመድረስ በአማኞች ልብ ውስጥ ሸክም ለመፍጠር ጠቃሚ ስልት ሊሆን ይችላል። ቤተክርስቲያን ሁለት-ሁለት አድርጎ በማጣመር፣ ወደ ተመረጡ አካባቢዎች እየተጎዙ የሚጸልዩ ቡድኖችን ማደራጀት ትችላለች። ቡድኑ እየተጎዘ መንፈስ ቅዱስን በነዋሪዎች ላይ እንዲያንቀሳቅስ፣ ወንጌልን ለመቀበል ልባቸውን እንዲከፍትላቸው በጸሎት ይጠይቃል። እንዲሁም የአካባቢውን ሰዎች በመንፈሳዊ እና በሥጋዊ ባርነት ከሚገዛውን አጋንንታዊ ኃይላት ጋር መንፈሳዊ ጦርነት ማድረግ ያስፈልጋል።

ቡድኖቹ በየአካባቢው ሲጸልዩ፣ ከፈቃደኛ ሰዎች ጋር ለመጸለይ እና ወንጌልን ለማቅረብ እድሎች ክፍት መሆን አለባቸው። የጸሎት ጉዞዎች ለአዲስ የቤተ ክርስቲያን ተከላ አፈርን ለተክል እደማዘጋጀት አይነት ጥሩ መንገድ ናቸው።

## የሚዲያ ስርጭት

ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አቅም ካላት ሚዲያን በመጠቀም ወንጌልን ማሰራጨትን እንደ ስልት ልትይዝ ይገባል። የመገናኛ ብዙሃን ሲባል የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ስርጭቶችን ያካትታሉ። በይነመረብ እና ማህበራዊ ሚዲያ ወንጌልን ለማሰራጨት መጠቀምም ይቻላል። እንደዚህ አይነት ቅስቀሳ ሲታቀድ፣ ፕሮግራሞቹ ከፍተኛ ጥራት ከሌላቸው፣ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሳብ ይልቅ ወደ ኋላ ሊመልሳቸው እንደሚችል ማስታወስ ይገባል።

## የቤተ ክርስቲያን ተከላ

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ቤተ ክርስቲያንን መትከል እስካሁን ድረስ በጣም ውጤታማው የስብከተ ወንጌል ዘዴ ነው። ሰዎች ከነባር ቤተክርስቲያናት ይልቅ አዲስ ወደ ተመሰረቱ ቤተ ክርስቲያናት መምጣት ይቀላቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ተከላ ቤተ ክርስቲያን በቁጥር ማደግ ብቻ ሳይሆን በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ትስፋፋለች።[1]

## ሌሎች የፈጠራ ዘዴዎች

ለሌሎች የስብከተ ወንጌል ፈጠራ ዘዴዎች ክፍት መሆን ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አዲስ የጠፉትን የመድረሻ ፕሮግራሞችን ለመፍጠር እና ለማቀድ ሁል ጊዜ ለመንፈስ ቅዱስ መመሪያ ክፍት መሆን አለብህ።

# ወንጌል ሥርጭት እድሎች

ጳውሎስ በኤፌሶን የነበሩትን ክርስቲያኖች “ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን በሚገባ ዋጁ” ሲል መከሯቸዋል (ኤፌ. 5፡16)። ሁኔታዎች ሲለዋወጡ፣ አዳዲስ የወንጌል እድሎች ይመጣሉ። ስለዚህ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በመንፈስ ቅዱስ መመራት እና እድሎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ለፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለብህ። እነዚህን አራት የተለመዱ እድሎች እንደ ምሳሌ እንውሰድ፡-

## ለቀውሶች ምላሽ መስጠት

እንደ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ወረርሽኞች፣ ድርቅ፣ አውሎ ነፋሶች፣ የአንበጣ ወረራ እና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ያሉ ማኅበረሰባዊ አለመግባባቶች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ምሥራች እንድታካፍል ትልቅ እድሎች ይፈጥርላታል። በእነዚህ የችግር ጊዜያት ሰዎች መልሶችን ይፈልጋሉ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ያሉ ሰዎች ልባቸው ለጌታ የበለጠ ክፍት ነው። በእንደዚህ ዓይነት አውዶች ውስጥ የክርስቲያን የፍቅር መልእክት ለተጎዱ ሰዎች ተስፋን ይሰጣል። በዚህ ጊዜ፣ አንተ እና ቤተ ክርስቲያንህ በፍቅር እና በርኅራኄ ለመድረስ ዝግጁ ሁን። የተቸገሩትን ለማገልገል መንገዶችን መፈለግ አለብህ። ይሄን እያደረግክ ወንጌልን ለመካፈል እድሎችን በሚገባ መጠቀም አለብህ።

## ሙስሊሙ ማህበረሰብን መድረስ

በአፍሪካ የሙስሊሙ ማህበረሰብ እያደገ እና እየተስፋፋ ነው። አክራሪ እስላም እየጨመረ የተወሰኑ የአህጉሪቱን ክፍሎችንም እያወደመ ነው። በዚህ ምክንያት ብዙ ሙስሊሞች በሃይማኖታቸው ግር ተሰኝተዋል። ቤተ ክርስቲያናችሁ እነዚህን ግራ የተጋቡ ሙስሊሞችን ለመድረስ የተልእኮ እቅድ ማዘጋጀት አለባት።

## የግንኙነት መረቦችን መጠቀም

የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኞች፣ ጎረቤቶች እና የስራ ባልደረቦች ያሉ የግንኙነት መረቦች ለወንጌል መስበክ እንደ ተፈጥሯዊ ድልድይ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ይህ በተለይ በአፍሪካ ገጠራማ አካባቢዎች ጠቃሚ መንገድ ነው። በአፍሪካ ገጠራማ አካባቢዎች ሰዎች በማህበረሰብ ተቀራርበው ይኖራሉ እና ብዙ የሚያመሳስሏቸውን ነገሮች ይጋራሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የአንድን ወሳኝ መሪ ወደ ጌታ መለወጥ በእርሱ ወይም በእርሷ የግንኙነት መረብ ውስጥ ያሉትን የሌሎችን መለወጥ

[1] የቤተ ክርስቲያን መትከል በምዕራፍ 39፡ “አዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል " የሚለውን ተመልከት።

ሊያስከትል ይችላል። በግንኙነት መረቦች በኩል የሚመጣ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በአፍሪካ ውስጥ ትልቅ ስኬት ያስመዘግባል።

### ስልታዊ አጋርነት

ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው አብያተ ክርስቲያናት እና ድርጅቶች ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነት መፍጠር ሌላው የጠፉትን የመድረስ የወንጌል አገልግሎት ውጤታማ መንገድ ሊሆን ይችላል። ይህ በተለይ በጋራ ስምምነት ላይ የተመሰረተ የተልእኮ ስራን ለማከናወን አስፈላጊ ነው። ቤተ ክርስትያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እና ሚኒስትሪዎች ጋር በመተባበር ችላ የተባሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን እንደ ወላጅ አልባ ህጻናት፣ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆች ወይም የተፈጥሮ አደጋ ሰለባዎች ለመድረስ ያተኮሩ ልዩ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ ትችላለች።

## አስፈላጊ ጉዳዮች

ለወንጌል አገልግሎት ብዙ አቀራረቦች ሊኖሩ ቢችሉም፣ ለጴንጤቆስጤ መጋቢ፣ ሦስት መሠረታዊ ነገሮች ሁል ጊዜ ግድ ናቸው። ወንጌል ማወጅ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ እና ብርቱ ጸሎት።

### የወንጌል አዋጅ

የጠፉትን ለማዳን ወንጌል መሰበክ አለበት (ማር 16፡15፤ 1ቆሮ. 9፡16)። ጳውሎስ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" (ሮሜ. 10፡13) በማለት ተናግሯል። ቀጥሎም ተከታታይ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፡ - "ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስማት ይችላሉ?" (ቁጥር 14) ወንጌልን ሳንሰማ እና ሳናምን መዳን የለም። ስለዚህ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለጠፉት የምሥራቹን ለመስበክ ሁል ጊዜ ዝግጁ ሁን (ሮሜ. 1፡15-16)። እና አባላትህን ምሳሌህን እንዲከተሉ ማስታጠቅ አለብህ።

### የመንፈስ ቅዱስ ኃይል

ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ውጭ ምንም ዓይነት የወንጌል ሥራ መሥራት አይቻልም። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. 28፡19) በማለት አዘዛቸው። በመጀመሪያ ግን "ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ" ብሏል (ሉቃስ 24፡ 49፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡4-8)። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት-ሂደት እስከ ዛሬ ድረስ ይቀጥላል - መጀመሪያ መታጠቅ፣ ከዚያም ማወጅ።

የአዲስ ኪዳን የወንጌል ስብከት ሥርዓት በምልክቶችና ድንቆች ተከታይነት የሚረጋገጥ በመንፈስ የተቀባ ስብከት ነው (ማቴ. 10፡7-8፤ ማር. 16፡17)። ወንጌል መሰበክ ብቻ ሳይሆን ኃይሉም መገለጥ አለበት። ይህ በተለይ በአፍሪካ ተጨባጭ ሁኔታ ትርጉም ያለው ነው። አብዛኞቹ አፍሪካውያን ከጣዖት አምልኮ፣ ከጥንቆላ እና ከመናፍስታዊ አምልኮዎች የመጡ እደመሆናቸው በጨለማ ኃይሎች ላይ ሥልጣንን የሚሰጥ መንፈሳዊ ልምምድ ይፈልጋሉ።

ስለዚህ እንደ ጥበበኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን፣ የሃይል አገልግሎትን፣ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በወንጌል አገልግሎት ላይ እንዲገለጡ አጽንዖት መስጠት አለብህ። ሆኖም፣ አስደናቂ ተአምራትን ከመሻት ብዛት የወንጌል መልእክት እንዳይዛባም ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ።

## ብርቱ ጸሎት

በመጨረሻም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ በጸሎት መታጀብ ይኖርበታል። እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት ስኬት ቁልፍ ነው። ሁሉም የወንጌል እንቅስቃሴ ስኬቱን የሚያገኘው ከዚህ ነው። በጸሎት እግዚአብሔር ለቅዱሳን ኃይል እንዲሰጥ፣ አካሄዳቸውን እንዲመራ፣ ስብከታቸውን እንዲቀባ፣ ምልክትና ድንቅ እንዲያደርግ፣ የወንጌልን ስብከት ለሚሰሙት ሰዎች ልብ እንዲከፍት እንጠይቃለን (ሐዋ. 4፡29-30)።

---

የወንጌል ስርጭት የቤተ ክርስቲያን የመኖር ምክንያት ነው። ማንኛዋም ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የጠፉት ሰዎች መድረስ ከተሳነው ጴንጤቆስጤያዊ ተብሎ መጠራት አይችልም። ስለዚህ፣ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣የጠፉትን ለመድረስ ቤተክርስቲያንህን በድፍረት መምራት አለብህ።

# ~ ምዕራፍ 38 ~

# ማህበረሰብን ማገልገል

በምስራቅ አፍሪካ የምትገኝ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበረ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስቶ በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመር ተነሳሳ። ሁኔታውን እንዲህ ሲል ያስታውሳል፣ "ለሰፈር ልጆች የተሻለ ትምህርት መስጠት እንፈልግ ነበር። በማኅበረሰባችን ውስጥ መሃይምነትንና ድንቁርናን ለማስወገድ የበኩላችንን መወጣት ነበር አላማችን" ምንም እንኳን ገንዘብ ባይኖረውም፣ ደግሞም ትምህርት ቤት የመምራት ልምድ ባይኖረውም፣ ፓስተሩ እግዚአብሔር እንደመራው አምኖ ነበር። ስለዚህ፣ በእምነት፣ እቅዱን ይዞ ወደ ፊት ሄደ።

ትምህርት ቤቱ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማስቀመጥ ካቢኔት እንደሚያስፈልገው የተረዳው ፓስተሩ ቁም ሳጥኖቹን ከራሱ ቤት አውጥቶ ወደ ትምህርት ቤቱ ወሰዳቸው። ጠረጴዛዎችን፣ መጽሃፎችን እና የግንባታ ቁሳቁሶችን ለመግዛት ሌሎች የግል ንብረቶችን ሸጧል። ከዚያም ራዕዩን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ሥራ ገባ። ትምህርት ቤቱ ለጥበቃ ደሞዝ የመክፈል አቅም ስለሌለው እርሱ ራሱ በዚያ ቦታ ለማገልገል ፈቃደኛ ሆነ። በዚህ ጊዜ ሁሉ፣ እግዚአብሔር እንደሚደግፈውና እንደሚመራው ታምኗል ። ቀስ በቀስ ትምህርት ቤቱ እየበለጸገ እያደገ መጣ።

የአካባቢ ሰው ፓስተሩን ሲመለከቱ፣ በራዕዩ እና ለእነርሱ መሻሻል ባለው እውነተኛ አሳቢነት ተነኩ። በዚህም ምክንያት ትምህርት ቤቱን ለመርዳት ገንዘብ ማዋጣት ጀመሩ። ከጊዜ በኋላ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኒቱ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን እንድትሠራ አደረገ። እነዚህ አዳዲስ የመማሪያ ክፍሎች የተገነቡት በመንግስት የትምህርት ደረጃዎች መሰረት ነበር። በቅርብ፣ ት/ቤቱ የበለጠ የሚስፋፋበት ተጨማሪ መሬት ከመንግስት አግኝቷል። ፓስተሩ "ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን እና የልጆች መጫወቻ ሜዳ ለመገንባት አቅደናል። እኛ ገና እግዚአብሔር እንድንሆን በሚፈልግበት ቦታ ላይ አይደለንም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ታማኝ ነው። ወደ ፊት እንድንሄድ እየረዳን ነው። ትምህርት ቤታችን በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው ካሉት ምርጥ ትምህርት ቤቶች አንዱ ነው" በማለት መስክሮአል፡፡

የትምህርት ቤቱ መጋቢ እና ሰራተኞች ባደረጉት ነገር ሁሉ ወንጌልን ለጠፉት ለማካፈል ክርስቶስ የሰጠውን ትእዛዝ በታማኝነት እየፈጸሙ ነበር። በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ ተማሪዎች ክርስቲያን ሆነዋል። በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ የተፈጠረው በጎ ስራ በርካታ ወላጆችን ሕይወታቸውን ለኢየሱስ እንዲሰጡ ልብ ከፍቷል። እግዚአብሔር በተጨማሪ ትምህርት ቤቱን ለአካባቢው ሙስሊም ማህበረሰብ የምሥክርነት በር ከፍቷል።

ይህ አንተ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያንህ ማህበረሰብን ለመለወጥ የምትጠቀምበት ከብዙ መንገዶች አንዱ ምሳሌ ነው። ይህ ምዕራፍ ስለዚህ ጉዳይ ይመረምራል። ለማህበራዊ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይጥላል። ሁለንተናዊ አገልግሎት ሰውን፣ መንፈስን፣ ነፍስንና ሥጋን ለማገልገል የሚዘረጋ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ነው። ምዕራፉ በተጨማሪም ቤተ ክርስትያን በማህበረሰብ ልማት ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንደምትችል ተግባራዊ ምክሮችን ይሰጣል።

# መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትዕዛዝ

በሚስዮን ውይይቶች፣ አንዳንድ ጊዜ “ወንጌልን ለጠፉት ከመስበክ እና ችግረኞች ከመንከባከብ የትኛው ይበልጣል?” የሚል ጥያቄ ይነሳል። መልሱ ግን ኃጢአተኞችን ወደ ክርስቶስ ከመምራት የበለጠ ነገር ባይኖርም ቤተ ክርስቲያን ግን በወንጌል አገልግሎት እና በማህበረሰቡ ልማት ውስጥ መሳተፍ አለባት። ሁለቱም የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት መግለጫዎች ናቸው። በአፍሪካ ያለችው የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በመምራት እና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል የላቀ ብቃቷን አሳይታለች፣ በማህበረሰብ ልማት ረገድ ግን ውጤታማ አልነበረችም።

እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ሁለት ጽንፎችን ማስወገድ አለብህ። በመጀመሪያ፣ በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች አካላዊ ችግሮች ቸል ብለህ ወንጌልን ብቻ ከመስበክ መቆጠብ አለብህ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ ወንጌልን ሳታካፍል የሰዎችን አካላዊ ፍላጎት ብቻ ከመንከባከብ መቆጠብም አለብህ። አንድ ሰው “የክርስቶስን ፍቅር እስካልገለፅን ድረስ ወንጌልን ሙሉ በሙሉ አልሰበክንም፤ ወንጌልንም እስክንሰብክ ድረስ የክርስቶስን ፍቅር ሙሉ በሙሉ አላሳየንም” በማለት ተናግሯል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አስፈላጊ ርዕስ ምን እንደሚል በጥልቀት እንመርምር።

## የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል

ኢየሱስ የአገልግሎት አርአያችን ነው። የሰውን፣ መንፈስን፣ ነፍስንና ሥጋን በሙሉ አገለገለ። ኢየሱስ አገልግሎቱን ሊጀምር ሲል ዓላማውን ተናግሮል። “የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣እርሱ ቀብቶኛልና፤ለታሰሩት መፈታትን፣ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣የተጨቈኑትን ነጻ እንዳወጣ፣19 የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል” (ሉቃስ 4፡18-19)። በመሆኑም የኢየሱስ አገልግሎት ምሥራቹን በመስበክና የሰዎችን ፍላጎት በማሟላት ላይ ያተኮረ ነበር።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስን ምሳሌ ተከትላለች። ሐዋሪያት ወንጌልን ሰብከዋል፣ ድውያንን ፈወሱ፣ አጋንንትን አወጡ፣ የተቸገሩትንም ይንከባከቡ ነበር። ችግረኞችን የመንከባከብ አንዱ ምሳሌ በኢየሩሳሌም ላሉ ግሪኮች መበለቶች ያሳዩት አሳቢነት ነው (ሐዋ. 6፡1)። ሌላው ምሳሌ በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ላሉ ቅዱሳን የተራቡ ሰዎች የሰጠችው ምላሽ ነው። አጋቦስ የሰጠውን ትንቢታዊ ምክር ሲሰሙ፣ “ደቀ መዛሙርትም እያንዳንዳቸው ዐቅማቸው በፈቀደ መጠን አዋጥተው በይሁዳ የሚኖሩትን ወንድሞች ለመርዳት ወሰኑ፤ 30 ርዳታውንም በበርናባስና በሳውል እጅ ለሽማግሌዎቹ በመላክ፣ ይህንኑ አደረጉ" (ሐዋ 11፡29-30)።

### ሁለት ታላላቅ ግዴታዎች

ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ሁለት ታላላቅ አደራዎችን ትቶ ሄዷል። አንደኛው ታላቁ ተልእኮ ይባላል (ማቴ. 28፡18-20)። ሌላው ታላቁ ትእዛዝ ነው(ማቴ. 22፡34-40)። እንደ ታማኝ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ሁለቱንም ለመታዘዝ ቤተ ክርስቲያንህን መምራት አለብህ። በታላቁ ተልእኮ ውስጥ፣ ኢየሱስ "ሂዱ አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጉ" በማለት አዞናል። በታላቁ ትእዛዝ፣ እግዚአብሔርን በቅንነት እንድንወድ እና ጎረቤቶቻችንን እንደራሳችን እንድንወድ አዞናል። በደጉ ሳምራዊ ምሳሌ፣ የአንድ ሰው ጎሳ ወይም ሀይማኖት ምንም ይሁን ምን የእኛን እርዳታ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ባልንጀራችን እንደሆነ አስተምሯል። ደጉ ሳምራዊ የቆሰለውን ሰው ሲያይ በመቆም እና በመርዳት ጥሩ ወዳጅ መሆኑን አሳይቷል። ኢየሱስ "ሂድና እንዲሁ አድርግ" ብሎ አዞናል (ሉቃስ 10፡37)።

### ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤዎች

በሌሎች በርካታ ቦታዎች መጽሐፍ ቅዱስ የተቸገሩትን እንድንንከባከብ ይነግረናል። ለምሳሌ፣ ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "በእግዚአብሔር አብ ፊት ንጹሕና ነውር የሌለበት ሃይማኖት ይህ ነው፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው መርዳትና ከዓለም ርኵሰት ራስን መጠበቅ ነው" (ያዕቆብ 1፡27)። ኢየሱስ እንዳስተማረን የተቸገሩትን ስናገለግል (ማለትም፣ የተራቡትን፣ የተጠሙን፣ የታረዙን፣ የታመሙን፣ ቤት የሌላቸውን እና እስረኞችን) ራሱ ክርስቶስን እያገለገልን ነው (ማቴ. 25፡31-40)። ድሆችን ቸል ማለት፣ ክርስቶስን ቸል ማለት ነው (ቁ. 41-46)። የሰዎችን ሥጋዊ ፍላጎቶች በምታገለግልበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ ሰው በገነት ወይም በገሃነም ውስጥ ለዘላለም የሚኖር ዘላለማዊ ፍጡር መሆኑን ፈጽሞ መርሳት የለብህም። በመሆኑም ወንጌልን ከማካፈል እና ለመዳን እድል መስጠትን መርሳት የለብህም።

## ማህበረሰቡን የማገልገል ዋጋ

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ማህበረሰቡን ማገልገል ብዙ ዋጋ አለው። ሁለቱን እንመልከት፡-

### እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል

እግዚአብሔር ልጆቹ ማህበረሰባቸውን ሲያገለግሉ እና በዙሪያቸው ላሉ ሰዎች በርኅራኄ ሲደርሱ ይደሰታል። ይህን ስናደርግ፣ የእግዚአብሔርን የፍቅር ተፈጥሮ እናሳያለን በተጨማሪም፤ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ ብዙ ጊዜ የፈወሰውን (ማቴ. 8፡16) የኢየሱስን ምሳሌ እየተከተልን ነው። ኢየሱስ በተራራ ስብከቱ ላይ፡- "ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን ጥላ' እንደ ተባለ ሰምታችኋል።44 እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኋለሁ።45 እንደዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሓዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኀጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል" (ማቴ. 5፡43-45)። በዚህ ክፍል ኢየሱስ ሁሉንም ሰው፣ ጠላቶቻችንን እንኳን፣ እንድንወድ እና እንድንባርክ እየተናገረ ነው። ይህን ካደረግን እንደ የሰማይ አባታችን እንሆናለን፣ እናም ተግባራችን እግዚአብሔርን ያስደስታል።

### በሮች ይከፍታል።

ማኅበረሰብን መንከባከብ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያንና በማህበረሰቡ መካከል በጎ ግንኙነት ይገነባል። የእግዚአብሔር ሰዎች ለሌሎች በጎ ሲያደርጉ፣ ሰዎች ያስተውላሉ፣ እናም ቤተ ክርስቲያንን በበጎ መመልከት ይጀምራሉ። ኢየሱስ በአንድ ወቅት መስማት

የተሳነውን ዲዳ ሰው ፈወሰ። ሕዝቡም ይህን የርኅራኄ ድርጊት ሲሰሙ፣ “ሁሉን በመልካም አደረገ... ደንቆሮዎችንም እንዲሰሙ ዲዳዎችም እንዲናገሩ ያደርጋል” ብለው ተናገሩ። (ማር. 7፡37)። ሕዝቡ ኢየሱስ እንደሚያስብላቸው ባዩ ጊዜ ልባቸውን ወደ እርሱ መለሱ። ቤተክርስቲያናችሁ ማህበረሰቡን ማገልገል እና መባረክ ስትጀምር ህዝቡ “እነዚህ ጥሩ ሰዎች ናቸው” ይላሉ። የውጭ ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችሁን በመልካም መመልከት ሲጀምሩ፣ ለወንጌል በሮች ይከፈታሉ።

# ፍላጎቶችን መለየት

የማህበረሰብ አገልግሎት የሚጀምረው ፍላጎትን በመለየት እና ፍላጎቱን ለማሟላት በመንቀሳቀስ ነው። ቤተ ክርስቲያንህ የምታገለግልበት ጥቂት መንገዶች እንደሚከተሉ ይቀርባሉ።

## የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች

የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ቤተ ክርስቲያን ማህበረሰቡን የምታገለግልበት እና ወንጌልን የምታስፋፋበት ውጤታማ መንገድ ነው። በአፍሪካ የሚገኙ በርካታ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ትምህርት ቤቶችን በመስራት ለማህበረሰባቸው የበረከት ምክንያት እየሆኑ ነው። አንዳንዶች ችላ በተባሉ አካባቢዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ፍላጎት ለመቅረፍ ሰርተዋል። ሌሎች ደግሞ አሁን ካለው ዓለማዊ ወይም ኢስላማዊ የትምህርት ሞዴል ትውልድን ለመታደግ ክርስቲያናዊ እሴትን ያነገቡ ትምህርት ቤቶችን ጀምረዋል። ትምህርት ቤቶች በተለይ ሰዎች ወንጌልን በሚቃወሙባቸው አካባቢዎች ውጤታማ ናቸው። ትምህርት ቤት ለመጀመር አቅም የሌላት ቤተ ክርስቲያን አባላትን በመመልመል በትምህርታቸው እርዳታ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ነፃ ትምህርት እንዲሰጡ ማድረግ ትችላለች።

## የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች

አንዳንድ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ማህበረሰባቸውን የአገልግሎት ፕሮጀክቶች በማቅረብ የበረከት ምክንያት እየሆኑ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ ክፍተትን ይለያሉ እናም ይህንን ፍላጎት ለመቅረፍ ራሳቸውን ያደራጃሉ። ለምሳሌ፡- አንድ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው ላለው ክሊኒክ ቀለም ለማደስ ወይም አንዳንድ ቁሳቁስ ለማቅረብ ፈቃደኛ ልትሆን ትችላለች። ሌላዋ አጥቢያ በአካባቢው ላለ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰበረን መስታወቶች ለመጠገን ትችላለች። ወይም ደግሞ በአንዲት መበለት ቤት ላይ የሚያንጠባጥብ ጣሪያ መጠገን ወይም መለወጥ ይፈልጉ ይሆናል። በአንድ ቤተ ክርስቲያን አባላት "ቅዳሜ ሳምራውያን" ብለው የሚጠሩትን ቡድን አደራጅተው በየሳምንቱ ቅዳሜ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት መበለቶችንና ችግረኞችን በተለያዩ ሥራዎች ለመርዳት ይወጡ ነበር። እንደዚህ ባሉ የአገልግሎት ፕሮጀክቶች ቤተ ክርስቲያን በዙሪያ ያለውን ማህበረሰብ የምታገለግልበት በመቶዎች የሚቆጠሩ መንገዶች አሉ።

## የጤና አገልግሎት

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ብዙ ማህበረሰቦች በቂ የጤና አገልግሎት የላቸውም። ይህንን ፍላጎት ለመቅረፍ ቤተ ክርስቲያን ለማህበረሰቡ ክሊኒክ መገንባት ትፈልግ ይሆናል። ከዚያም ተፅኖውን ተጠቅማ በክሊኒኩን ክርስቲያን የጤና ባለሙያዎችን መቅጠር ትችላለች። ከዚህም በቀለለ ደረጃ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት አሳቢ ሰዎች እንዲሆኑ ማበረታታት ይቻላል። ለምሳሌ አካላዊ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች በመፈለግ አካባቢያቸውን መቃኘት ይችላሉ። ከዚያም የፈውስ ጸሎት፣ ማጽናኛ እና የገንዘብ ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይችላሉ።

## ንጹህ ውሃ

እንደ ቤተ ክርስቲያንህ የገንዘብ አቅም፣ የውሃ ጉድጓድ ስፖንሰር በማድረግ ንጹህ ውሃ ለማህበረሰብህ ማቅረብ ሌላ የማህበረሰብ አገልግሎት አማራጭ ነው። ወይም ያረጀ ወይም የማይሰራ ጉድጓድ መጠገን ወይም ማደስም ይቻላል።

## ምገባ እና የልጅ እንክብካቤ

የህጻናት የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በብዙ የአፍሪካ አካባቢዎች ትልቅ ፈተና ነው። ችግሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናትን እና ወጣቶችን አካላዊ እና አእምሯዊ እድገትን ይነካል ፣ እና ጉዳቱ የዕድሜ ልክ ነው። አንዳንድ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ልጆች በቀን አንድ ጊዜ የመመገብ ፕሮግራሞችን አሉዋቸው። ሌሎች ደግሞ በተመጣጣኝ ዋጋ የልጆች እንክብካቤ ፕሮግራሞችን (ደይ ኬር) ጀምረዋል። እነዚህ ፕሮግራሞች ወላጆች ልጆቻቸው በአግባቡ እንደሚንከባከቡ አውቀው ወደ ሥራ እንዲሄዱ ያስችላቸዋል። እንደዚህ አይነት የመመገብ እና የህጻናት እንክብካቤ ፕሮግራሞች ቤተ ክርስቲያን ከልጆች እና ከወላጆች ጋር ወንጌልን እንድታካፍል እድል ይሰጣል። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ልጆቹን ክርስቲያናዊ እሴቶችን እንድታስተምር ዕድል ይሰጣታል።

## የትምህርት ዕድል የማመቻቸት ፕሮግራሞች

በአፍሪካ ውስጥ ብዙ ልጆች እና ወጣቶች ብሩህ አይምሮ ያላቸው እና ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ናቸው፤ ሆኖም ወላጆቻቸው የትምህርት ቤት ክፍያ መክፈል አይችሉም። ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ክፍያ በመክፈል የትምህርት ዕድል በማመቻቸት ይህንን ፍላጎት ብትፈታ ትልቅ እገዛ ታደርጋለች። ይህም ተማሪዎች ህልማቸውን እንዲያሳኩ እና እራሳቸውን እና ህብረተሰቡን በአጠቃላይ ለማሳደግ የሚያስፈልጋቸውን ክህሎት እንዲቀስሙ ያስችላቸዋል።

## የወጣቶች ልማት

የአፍሪካ ወጣቶች የአህጉሪቱን የወደፊት ሁኔታ ይወክላሉ። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ብዙዎቹ ወደ አደንዛዥ ዕፅ እና ሌሎች አጥፊ ባህሪያት እየገቡ ነው። ቤተ ክርስቲያናችሁ ለወጣቶች አወንታዊ ተግባራትን ለማቅረብ የወጣት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ይህንን ፍላጎት መፍታት ትችላለች። እነዚህ ፕሮግራሞች የመዘምራን ቡድንን፣ የስፖርት ቡድኖችን እና ሌሎች ጠቃሚ እንቅስቃሴዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ። የወጣት አገልጋዮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወንድነት እና ሴትነት መርሆዎችን ለማስተማር እነዚህን እንቅስቃሴዎች እንደ መድረክ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። እነዚህ ፕሮግራሞች የወጣት አገልጋዮች ወንጌልን ለወጣቶች እንዲያቀርቡ እና ወደ ክርስቶስ እንዲመሩ እድል ይሰጣቸዋል።

## የአዋቂዎች ትምህርት

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ብዙ ጎልማሶች የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እድል ያመለጣቸው ናቸው። ቤተ ክርስትያንህ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን በማቋቋም ይህንን ፍላጎት መፍታት ትችላለች። እነዚህ ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ-

**የንባብ ስልጠና።** ቤተ ክርስቲያን አዋቂዎች ማንበብና መጻፍ የሚያስተምር ፕሮግራም ልትጀምር ትችላለች። እነዚህን ክህሎቶች መማራቸው ለራሳቸው ያላቸውን ግምት ያሳድጋል ደግሞም የተሻሉ ስራዎችን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ይህ ደግሞ የህብረተሰቡን ህይወት ያሳድጋል። መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች ክርስቲያናዊ ጽሑፎችን ቤተ ክርስቲያን ልትሰጣቸው የምትፈልገውን እንዲያነቡም ያዘጋጃቸዋል። ቤተ ክርስቲያኒቱም አዋቂዎች እንደ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ ወይም ፖርቹጋልኛ ሁለተኛ ቋንቋ እንዲማሩ ለመርዳት የቋንቋ ትምህርት መጀመር ትፈልግ ይሆናል።

***ጋብቻን ማበልጸግ።*** በአፍሪካ ውስጥ ያሉ በርካታ ትዳሮች በችግር የተሞሉ ናቸው ። በመሆኑም የፍቺ ቁጥር እየጨመረ ነው። ባለትዳሮች የመጽሐፍ ቅዱስን የጋብቻ መርሆች ማወቅ አለባቸው። ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ላሉትም ሆነ ከውጪ ያሉ ሰዎች እውነት ነው። ይህንን ፍላጎት ለመቅረፍ፣ የጋብቻ ማበልፀጊያ ክፍል ወይም ሴሚናር አዘጋጅተህ ለህዝብ ክፍት ማድረግ ትችላለህ። አባላት ጌታን የማያውቁ ጓደኞቻቸውን ወደ ፕሮግራሙ እንዲመጡ መጋበዝ ይችላሉ። ይህም እግዚአብሔር ለሕይወታቸውና ለትዳራቸው ያለውን ዓላማ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። በከፕሮግራሙ ወንጌል መቅረብ አለበት እና ጥንዶች ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው እንዲቀበሉ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።

***የኢንተርፕረነርሺፕ የንግድ ሥራ መርሆዎች።*** የሚቻል ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያንህ የጎልማሳ ተማሪዎችን እንዴት የራሳቸውን ሥራ መጀመር እና ማሳደግ እንደሚችሉ የማስተማር ሥራ መጀመር ጠቃሚ ነው። ፕሮግራሙ የጠንካራ የሥራ ሥነ ምግባርን አስፈላጊነት ጨምሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የንግድ እና የአስተዳደር መርሆዎችን ማስተማር ይችላል።

**ምርጥ የግብርና ልምዶች።** በገጠር አካባቢ፣ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መስጠት ወይም ስለ ምርጥ የግብርና ተግባራት ሴሚናር መስጠት ትችላለች። ሴሚናሩ በግብርና መስክ ባለሙያ ቢቀርብ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።

### ሌሎች ተነሳሽነት

እነዚህ ቤተ ክርስቲያናችሁ ማህበረሰቡን የምታገለግልባቸው ጥቂት መንገዶች ናቸው። እዚህ ያልተጠቀሱ ሌሎች ፕሮግራሞችን እና የአገልግሎት ፕሮጀክቶችን እንድትጀምር መንፈስ ቅዱስ ይመራሃል።

# ቤተ ክርስቲያንን ማንቀሳቀስ

ምናልባት፣ “እኔ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እነዚህን የማህበረሰብ ልማት ተነሳሽነቶች ተግባራዊ ለማድረግ እንዴት እችላለሁ?” ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። እግዚአብሔር የመረጠው የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደመሆንህ፣ በጉዳዩ ላይ ግንባር ቀደም መሆን ያስፈልግሃል። ራዕዩን መጀመር፣ እቅዱን ማዳበር እና የዕቅዱን አፈፃፀም መቆጣጠር አለብህ። ውጤታማ የድርጊት እቅድ ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ግምት ውስጥ አስገባ፤

### ፍላጎቱን ተመልከት

ኢየሱስ በመጀመሪያ በዙሪያው ያለውን ፍላጎት ተመልክቷል። በዙሪያው ያሉትን የሚቸገሩ ሰዎችን አይቶ ነበር "ሕዝቡም እረኛ እንደሌለው በግ ተጨንቀውና ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ጊዜ አዘነላቸው" (ማቴ. 9፡36)። ከዚያም አንድ ዕቅድ ተግባራዊ አድረገ። ደቀ መዛሙርቱን “የመከሩ ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት” (ቁ. 38) አላቸው። በሌላ ጊዜ ኢየሱስ “አዝመራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና ብላችሁ ማሳውን ተመልከቱ” ብሏል (ዮሐ. 4፡35)።

አስታውስ፣ እንደ ኢየሱስ ያለህን የማህበረሰብ ተሳትፎ እቅድ ከመተግበርህ በፊት መጀመሪያ ፍላጎቱን ማየት አለብህ። ፍላጎቱን ካየህ በኃላ፣ የቤተክርስቲያ አባላት በተመሳሳይ መንገድ ፍላጎቱን እንዲያዩ መርዳት ትችላለህ።

## የእግዚአብሔርን ፈቃድ መወሰን

በአካባቢህ ያሉትን ብዙ ፍላጎቶች ካየህ በኋላ፣ "ከእነዚህ ፍላጎቶች ውስጥ የትኛውን ፍላጎት ቤተ ክርስቲያናችን መፍታት ትችላለህ?" በማለት እግዚአብሔርን መጠየቅ አለብህ። ልብህን ለመንፈስ ቅዱስ ብትከፍት መንፈስ ቅዱስ ይመርሃል። እያደገ የሚሄድ ሸክም በልብህ ላይ ያደርጋል እና የትኛውን ፍላጎት ቤተ ክርስትያን እንድታሟላ እንደሚፈልግ ያሳይሀል።

## ነገሮችን ቀላል ማድረግ

ለአዲሱ ፕሮግራም የተግባር እቅድ ማዘጋጀት ስትጀምር፣ ነገሮችን ቀላል ማድረግህ አስፈላጊ ነው-ቢያንስ መጀመሪያ ላይ። በመደበኛነት በትንሽ እና ማስተዳደር በሚቻል ፕሮጀክት መጀመር ያስፈልጋል። የቤተክርስቲያኑ አባላት የዚህን ትንሽ ፕሮጀክት ስኬት ሲመለከቱ፣ የበለጠ ትልቅ አቅም ያላቸውን ፕሮጀክቶችን ለመስራት ይነሳሳሉ።

## እርምጃ ውሰድ

መንፈስ ቅዱስ ጊዜው ትክክል መሆኑን ሲያመለክትህ እግዚአብሔር ደረጃ በደረጃ እንዲመራህ በማመን ወዲያውኑ እርምጃ ወስደህ ፕሮግራሙን መጀመር አለብህ።

## መንፈሳዊ ፍላጎቶችን መንከባከብ

ቤተ ክርስቲያንን የሰዎችን አካላዊ ፍላጎት ለመንከባከብ ስትሰራ፣ መንፈሳዊ ፍላጎቶቻቸውን ችላ እንዳትል ማረጋገጥ አለብህ። ክርስቶስ በእያንዳንዱ ፕሮግራም እና እንቅስቃሴ ማዕከሉን መያዝ አለበት። በመንፈስ ቅዱስ ደጋግሞ ለመሞላት አንተ ሆነ ሰራተኞችህ ደጋግማችሁ መጸለይ አለባችሁ።

## ቤተ ክርስቲያን አቀፍ ተሳትፎን አበረታታ

ስራውን ብቻዎን ለመስራት መሞከር የለብህም። ይልቁንስ የቤተ ክርስቲያን አባሎቻችሁ እንዲሳተፉ ማሰባሰብ አለብህ። ሁሉም ሰው በሆነ መንገድ መሳተፍ ይችላል። እንደ መጋቢ፣ ህዝቡ ለተነሳሽነቱ በልግስና እንዲሰጥ ማበረታታት እና ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን በማቀናጀት በበጎ ፈቃደኝነት እንዲሰሩ ማነሳሳት አለብህ። ጥበበኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንደመሆንህ፣ የአባላት ስጦታዎችን መለየት እና በስጦታቸው የእግዚአብሔርን ስራ እንዲሰሩ ማበረታታት ይገባል።

## የእግዚአብሔርን ችሮታ ታመን

በመጨረሻም፣ ፍላጎትህን እንደሚያሟላ እግዚአብሔርን መታመን አለብህ። ወደ ተግባር ከመሄድህ በፊት ሁሉም ነገር በቦታው እስኪገኝ ድረስ መጠበቅ የለብህም። ይህን ካደረግክ በጭራሽ አትጀምርም። መጋቢው በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንዳደረገው፣ ባለህ ነገር የቻልከውን ማድረግ አለብህ፣ ከዚያም የቀረውን እንዲሰራ እግዚአብሔርን እመን። ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እና እርሱ ለሰጠህ ራእይ ታማኝ ሆነህ ከቀጠልክ፣ የሚያስፈልግህን ሁሉ ያሟላል (ፊልጵ. 4፡19)።

# ~ ምዕራፍ 39 ~

# አዲስ አጥቢያ ቤተክርስቲያ መትከል

ቻርልስ በምስራቅ አፍሪካ በሚገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበር። አንድ ቀን፣ ለመምህሩ፣ "ከመሞቴ በፊት፣ በጎሳዬ መካከል መቶ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል እፈልጋለሁ" አለው። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሳለ ከሚሲዮኖች ቡድን ጋር ይèዝ ስለነበር ይህ የቤተ ክርስቲያን የመትከል ሸክም በልቡ ውስጥ ወደቀ። ቡድኑ ራቅ ባሉ አካባቢዎች እና ወንጌልን ባልሰሙ ሰዎች መካከል በርካታ አዳዲስ ቤተክርስቲያኖችን ተክሏል። በዚህ ጉዞ ቻርልስ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል የሚያስችሉአንዳንድ ተግባራዊ ዘዴዎችን ተማረ።

የጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ወደ ሃገሩ በገባ ጊዜ፣ ሥራ የጀመረው በቻርልስ ጎሳ መካከል ነበር። ይሁን እንጂ ከብዙ ዓመታት ቆይታ በኋላ ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ነበር መትከል የተቻለው። ዛሬ ላይ ቻርለስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከተመረቀ ከአሥራ ስድስት ዓመታት ሆኖታል። ከሠላሳ በላይ አብያተ ክርስቲያናትን በግሉ ተከሏል። እንደ ቤተ እምነት መሪ ባደረገው ተጽእኖ በተዘዋዋሪ ወደ ሃምሳ የሚጠጉትን በድምሩ ወደ ሰማንያ የሚጠጉ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ተከሏል። አሁን ላይ ቻርለስ "በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ውስጥ 200 አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን ለመትከል አስባለሁ!" በማለት ግቡን አሻሽሏል።

ጤናማ እናቶች ጤናማ ልጆች እንደሚወልዱ ሁሉ ጤናማ አብያተ ክርስቲያናትም ሌሎች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ይተክላሉ። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ተካይ ቤተ ክርስቲያን መሆን አለበት። ይህ ምዕራፍ የቤተ ክርስቲያንን መትከል፣ የቤተ ክርስቲያንን መትከል አብነቶች፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሐዋርያዊ ማኅበረሰብ፣ በመንፈስ የተደገፈ የሚስዮናውያን አብያተ ክርስቲያናት፣ አገር በቀል የቤተ ክርስቲያን መርሆች፣ እና የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አብያተ ክርስቲያናትን የሚተክልበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን እንመለከታለን።

# ቅዱሳት መጻሕፍት ቀዳሚነት

ኢየሱስ “ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ” (ማቴ. 16፡18) ብሏል። ደግሞም “ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” (28፡19) በማለት አዘዘ። አንድ ሰው “ኢየሱስ አብያተ ክርስቲያናትን እንድንተክል አላዘዘንም አለ። ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ አዘዘን። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከላይ የተናገረው ሐሳብ እርስ በርስ እንዴት እንደሚዛመድ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን ሳይተከል እንዴት ደቀ መዛሙርት ማፍራት ይቻላል? ደቀ መዛሙት ሳያደርግ ቤተ ክርስቲያን ተከልኩ ማለትስ እንዴት ይቻላል? የዳኑትን በአጥቢያ በቤተ ክርስቲያን አለመያዝ ልጅ ወልዶ እርሷን በጫካ ውስጥ እንደመተው ነው። የቤተ ክርስቲያን መመስረት ለሥራው ዘላቂነት እና ለምእመናን እድገት አስፈላጊ ነው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የነበሩት ሐዋርያት፣ አገልጋዮች እና የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች አብያተ ክርስቲያናትን በጥንቃቄ ይመሰርቱ ነበር። ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ፊልጶስ፣ የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች፣ በርናባስ፣ ጳውሎስ፣ ዮሐንስ ማርቆስ፣ ሲላስ፣ ሉቃስ፣ ጢሞቴዎስ፣ ጵርስቅላ፣ አቂላ፣ ጋይዮስ፣ አርስጥሮኮስ፣ ኤራስጦስ እና ቲቶ እና ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናትን ተካዮች ነበሩ። እነዚህ ወንዶችና ሴቶች የክርስቶስን ትእዛዝ ተከትለው ደቀ መዛሙርት ያደርጉም ነበር፣ ይህንንም በማድረግ፣ አብያተ ክርስቲያናትን ተከሉ። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን።

# ቤተ ክርስቲያንን የመትከል ተምሳሌቶች

በአንድ ወቅት አንድ ወጣት መጋቢ በአንድ ከተማ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ስለመተከል ከቤተዕምነት ቀጠና አስተባባሪ ጋር ተወያየ። የቀጠና አስተባባሪውም “እግዚአብሔር እዚያ ቤተ ክርስቲያን እንድተክል አልነገረኝም፣ ነገር ግን ማድረግ ከፈለግክ ቀጥል። ከተሳካ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደነበረ እናውቃለን። ካልተሳካ ግን እንዳልሆነ እናውቃለን” ሲል መለሰ። ወጣቱ መንፈስ ቅዱስ እንደመራው ስለተሰማው ወደዚያ ቦታ ሄዶ የመጀመሪያ ቤተክርስቲያኑን ተከለ። ኃላም ከሃያ በላይ አብያተ ክርስቲያናትን ተክሏል።

በመላ አፍሪካ፣ ብዙ ወንዶችና ሴቶች፣ ቤተ ክርስቲያን እንዲተክሉ የእግዚአብሔር ጥሪ ሰምተው፣ ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል። ብዙ የውጭ ድጋፍ ሳያገኙ በራሳቸው አቅም አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል። ይህ "የመስጠም ወይም የመዋኘት" ዘዴ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። አባት ልጁን ያለ ምንም የዋና ትምህርት እና ስልጠና ወደ ጥልቅ ኩሬ ውስጥ እንደ መጣል ነው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በዚህ መንገድ የተጀመሩ ቢሆንም፣ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ግን ይሄ አይደለም። ይህንን እውነታ የቤተ ክርስቲያን አንድ የቤተ ክርስቲያን ተካይ ሲናገር “ከመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ተከላ ብዙ ተምሬያለሁ” ይላል። "የተማርኩት አንድ ነገር ቁርጠኛ የሥራ አጋር ከሌለህ ቤተ ክርስቲያን መትከል ፈጽሞ አዳጋች መሆኑን ነው"

የቤተ ክርስቲያን ተከላ ደጋፊ ቡድን ብዙ ጥቅሞች አሉት። አስቡት አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ሁለት ሰዎችን ቡድን ከመላክ አሥር ወይም ከዚያ በላይ ሰዎችን መላክ ጥሩ ነው። ቡድኑ መጋቢውን እና ቤተሰቡን ፣ የአምልኮ መሪዎችን፣ በዕድሜ የገፉ በሳል ጥንዶች እና ልጆች እና ወጣቶች ላይ የሚሰሩ ሰዎችን ሊያካትት ይችላል። እንዲህ ያለው ቡድን ለቤተ ክርስቲያን ተካዮች የሞራል እና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። የቤተ ክርስቲያን ተከላ በቡድን ሲሆን ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት ወደ መጽናት እንድትደርስ ይረዳታል። በፍጥነት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን የምትተከል ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች።

የቤተ ክርስቲያን ተከላ የቡድን ሞዴል በተለያዩ ቅርጾች ሊመጣ ይችላል። አንዲት እናት ቤተ ክርስቲያን አንድ መጋቢ እና አንዳንድ በአቅራቢያ የሚገኙ አባላት እዛው በማደራጀት ሌላ ቤተ ክርስቲያን ልትወልድ ትችላለች። ከዚያም አዲሲቷ ቤተ ክርስቲያን እስክትቋቋም ድረስ እንክብካቤና አመራር ልትሰጥ ትችላለህ። ጳውሎስና የእርሱ ሐዋርያዊ ሚስዮናውያን ብድን ጥሩ ምሳሌ ናቸው። ብድኑ በወንጌል ወዳልተደረሱ ሰዎች በመንዝ ክርስቶስ በማይታወቅባቸው ስፍራዎች አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል።

አንዳንዶች አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል የሚሰሩ ተካዮችን ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመት ያህል የሚደግፉበት ሥርዓት አዘጋጅተዋል። ከጊዜ በኋላ፣ አዳዲስ አማኞች ሥራውን ለማስቀጠል አሥራትን መባን መስጠት ሲጀምሩ ድጋፉቸው እየቀነሰ ይሄዳል። በመጨረሻም ይቋረጣል። የቤተ ክርስቲያን ተከላ ሞዴሎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ***ወላጅነት፦*** እናት ቤተ ክርስቲያን ከላይ እንደተገለጸው ያለ ቤተ ክርስቲያን ትተክላለች።
- ***ፈር ቀዳጅነት፦*** ተካዮች ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል ወደ አዲስ አካባቢዎች ይላካሉ።
- **ቀፎ ነቀላ፦** ከሩቅ አካባቢ ወይም ከተለየ ባሕል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ ቡድን አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር እና "ቀፎ ለመንቀል" ከቤተክርስቲያኑ ፈቃድ ሲጠይቅ።
- ***የሕዋስ ቡድኖች፦*** በቤት ለቤት የሚሰበሰቡ የቤት ህብረቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊያድጉ ይችላሉ።
- ***የአብያተ ክርስቲያናት ትብብር ፡*** ቀጠኛ፣ ክልል ወይም ቤተዕምነት ቤተ ክርስቲያን ለመትከል በትብብር ሲሰራ።
- ***የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት።*** የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን አዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተክሉ ሊንቀሳቅሱ ይችላሉ።
- ***ሌላ፡*** አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል ሌሎች የፈጠራ መንገዶችን ማዘጋጀት ይቻላል።

የትኛውንም ሞዴል ብንጠቀም፣ ቤተ ክርስቲያንን መትከል ቀላል አይደለም። አዲሱን ስራ ለመመስረት ከፓስተሩ እና ቤተሰቡ እና አብሮት ካለው ቡድን ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ጠላት አዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲቋቋሙ አይፈልግም ምክንያቱ ደግሞ የእርሱን ግዛት ሊያዝበት ስለሆነ ነው (ማቴ. 12፡29)። በዚህም ምክንያት የቤተ ክርስቲያንን ተከላን ለመቃወም ይዋጋል (ኤፌ. 6፡12)። የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ተካይ ግን ድሉን እንዲቀዳጅ የሚረዳው በውስጡ የሚኖር ታላቅ ጉልበት አለው (1 ዮሐንስ 4፡4)።

ልክ እንደሌላው የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በአካባቢም ይሁን፣ ወንጌል ባልደረሰበት በሃገርህ ክፍል፣ ወይም በአፍሪካ እና በዓለም ዙሪያ ባሉ ሌሎች ሀገራት ቤተ ክርስቲያን አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን እንድትተክል እንዴት መምራት እንዳለብህ መጸለይ እና ማቀድ አለብህ።

# ሐዋርያዊ ማኅበረሰብ

ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን የምትሰጥ ቤተ ክርስቲያን ናት። ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን በሥነ መለኮት ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን በተልእኮ ላይ ያተኮረች ቤተ ክርስቲያን ናት። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን የምትመሰክር ቤተ ክርስቲያን ናት። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ሌሎች ጤናማ አብያተ ክርስቲያናትን ትወልዳለች።ጥያቄው ቤተ ክርስቲያን ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ትወልዳለች? እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እንዴት ሌላ ቤተ ክርስቲያን መትከል ይቻላል?

ለጤናማና በተልእኮ ላይ ያተኮረ ቤተ ክርስቲያን አስመልክቶ በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ግሩም ምሳሌ ናት። ቤተ ክርስቲያኒቱ የተመሰረተችው ከኢየሩሳሌም፣ ከቆጵሮስ እና ከቀሬና በመጡ አይሁዳውያን ምእመናን ሲሆን ከመስራቾቹ መካከል እምነታቸውን በድፍረት ለሌሎች ያካፈሉ የሌላ ባህል ሰዎችም ነበሩ (ሐዋ. 11፡19-20)። በመንፈስ የታጠቁ ቤተ ክርስቲያን ነበሩ (ቁ. 21)። ደግሞም ጥሩ አመራር ነበራቸው (ቁ. 22-26)። ሰጪ ቤተ ክርስቲያን ነበሩ (ቁ. 27-30)፣ እናም ይጸልዩ፣ ይጾሙ እና እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር (13፡2)።

ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ፡- “በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ” በላቸው ጊዜ እንዲሁ አደረጉ (ሐዋ. 13፡1-2)። በነጻነት ምርጥ አገልጋዮቻቸውን እግዚአብሔር የጠራቸውን እንዲያደርጉ ላኩዋቸው። በርናባስንና ሳውልን የሚስዮናውያን የቤተ ክርስቲያን ተካዮች አድርገው ላኩዋቸው (ቁ. 3-4)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ እግዚአብሔር “ህዝቡን ለአገልግሎት ሥራ” እንድታስታጥቅ ሊጠቀምብህ ይፈልጋል (ኤፌ. 4፡12)። በአቅራቢያ፣ በአገር እና በዓለም ዙሪያ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል ሊጠቀምብህ ይፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተልእኮ እና የቤተ ክርስቲያንን የመትከል ባህል ለመፍጠር እግዚአብሔር መንገድ እና እድል ሰጥቶሃል። ይህን በማስተማር እና የሚስዮን ጸሎትን፣ አምልኮን፣ አመራርን፣ በመስጠት፣ በስብከተ ወንጌል እና በቡድን በመስራት ማሳካት ትችላለህ። እንደዚህ ዓይነት ድባብ ከፈጠርክ፣ እግዚአብሔር ህዝቡን ወንጌልን እንዲሰብኩ እና አዳዲስ ቤተክርስትያኖችን እንዲተክሉ ያደርጋል።

ለእግዚአብሔር ሥራ በልግስና ለመስጠት መጎትጎት እና እግዚአብሔር በአንተም እንዲሁ እንዲያደርግ መፍቀድ አለብህ። እግዚአብሔር ምርጥ የቤተ ክርስቲያን አባሎቻችሁን የቤተ ክርስቲያን ተካይ አድርጋችሁ እንድትልኩ ሊጠይቅ ይችላል። ለእግዚአብሔር ልትሰጡት ከምትችሉት ታላቅ ስጦታዎች አንዱ ሰዎችን እግዚአብሔር የሰጣቸው እንዲለዩ ማድረግ እና ከዚያም ለአገልግሎት ማሰማራት ነው። በርናባስን ከተመለከትን ጳውሎስን ማስነሳት ብቻ ሳይሆን (ሐዋ. 9፡26-27፤ 11፡25) የራሱን አገልግሎት እንዲከተል እና የራሱን የሚስዮናውያን ቡድን እንዲያዳብር አድርጎል (15፡36-41)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የምታሳድገው ሐዋሪያዊ ማህበረሰብ እንደ ማግኔት ይሰራል። ሐዋርያዊ ማኅበረሰብ በሀገር ውስጥ እና በዓለም ዙሪያ ታላቁን ተልእኮ ለመፈጸም ያተኮረ የአማኞች ስብስብ ነው። ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ ሲንቀሳቀስ ሲያዩ፣ እርሱ የሚያደርገው ነገር አካል መሆን ይፈልጋሉ።

በሐዋርያት ሥራ 6 ላይ፣ አንዳንድ ችላ የተባሉ መበለቶችን ስለመመገብ ክርክር ተነሳ። ሐዋርያቱ እነርሱን እንዲንከባከቧቸው በመንፈስ የተሞሉ ሰባት ሰዎችን በመሾም ግጭቱን ፈቱ። ይህ ድርጊት በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ከውጪ ያሉትን ሰዎች ደስ አሰኘ። በውጤቱም፣ “የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፤ የደቀ መዛሙርቱም ቍጥር በኢየሩሳሌም እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙዎቹ ለእምነት የታዘዙ ሆኑ” (ቁ. 7)። ቤተ ክርስቲያን ወደ ሐዋርያዊ ማህበረሰብ ስታሳድጉ ሰዎች ወደ ክርስቶስ እና ተልእኮው ይሳባሉ። የቤተ ክርስቲያን እድገት እና የቤተ ክርስቲያን ተከላ በተፈጥሮ ከእንደዚህ አይነት ድባብ ይመነጫል።

# በመንፈስ የተደገፉ የሚስዮናዊያን አብያተ ክርስቲያናት

የሐዋርያት ሥራ በኢየሩሳሌም ያለችውን ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ስለመታጠቁዋ ታሪክ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ 120ዎቹን ደቀ መዛሙርት ሲሞላቸው፣ ሕዝቡ አንድ አስደናቂ ነገር አዩ። ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ እንደፈቀደላቸው በልሳኖች ይናገሩ ጀመር (2፡1-4)። ክስተቱ የሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ ያለው የኢየሱስ ተስፋ ቃል ፍጻሜ ነበር። ሕዝቡም በመገረም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ቀረቡ። ይህም ጴጥሮስ ምሥራቹን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲሰብክ ዕድል ሰጠው ይህም 3,000 ሰዎች ወደ ጌታ እንዲመጡ አድርጓል።

ሰዎች ወንጌልን መልእክት እንዲሰሙ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ምልክቶችን እና ድንቆችን ይጠቀማል። በወንጌል እና በሐዋርያት ሥራ ከውስጥ ይልቅ በአምልኮ ስፍራው ከተደረጉ ታዕምራት የሚበዙት ከአምልኮ ስፍራው ውጭ የተደረጉት መሆኑ የሚገርም ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ተአምራት ብዙ ጊዜ ወንጌል ለመስበክ መድረክ ፈጣሪዎች ሆነው ቀርበዋል። ለምሳሌ በኢየሩሳሌም ጴጥሮስ (የሐዋርያት ሥራ 2)፣ በቆጵሮስ ጳውሎስና በርናባስ (13፡4-12)፣ በኤፌሶን ጳውሎስና ከሲላስ ጋር (16፡11-40) እና በሌሎች ብዙ አጋጣሚዎች (9፡32-35) 9፡36-43፤ 10፡1-11፡18፤ 14፡1-7፤ 14፡8-20፤ 19፡1-20፡1) ማየት ይቻላል።

እግዚአብሔር ተዓምራትን ከቤተ ክርስቲያን የሚሰራውን ኃይሉን እና ፍቅሩን እንዲያዩ እና እንዲከተሉት ነው። በመሆኑም ተአምር ሲከሰቱ በጭራሽ ሊባክኑ አይገባም።እግዚአብሔር ተአምር ባደረገ ጊዜ ሁሉ ለሰዎች ስለ ኢየሱስ ለመናገር እንደ አጋጣሚ መጠቀም ያስፈልጋል።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፡- "አብ እንደ ላከኝ እኔ እልካችኋለሁ" (ዮሐንስ 20፡21) አላቸው። ግን አብ ኢየሱስን የላከው እንዴት ነው? አብ ልጁን በመንፈስ ኃይል እንዲያገለግል ላከው። ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር፣ "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣እርሱ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታትን፣ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣የተጨቈኑትን ነጻ እንዳወጣ፣19 የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል" አለ (ሉቃስ 4፡18-19)። ኢየሱስ በመንፈስ ኃይል አገለገለ (ሐዋ. 10፡38)። ደቀ መዛሙርቱንም እንዲሁ እንዲያደርጉ ላከ (ሉቃስ 24፡46-49፤ የሐዋርያት ሥራ 1፡8)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በመንፈስ ቅዱስ መታጠቅ አለብህ፣ እና ቤተ ክርስቲያንን ሆን ብለህ በመንፈስ የታጠቀ የሚስዮናውያን አካል አድርግ። በተጨማሪም፣ ሆን ብለህ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚስዮናውያን አብያተ ክርስቲያናትን (ቤተ ክርስቲያን ተካይ ቤተ ክርስቲያን) መትከል አለብህ። በመንፈስ የታገዘ የሚስዮናውያን ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ የተከለው ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ነው። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የምናነበው የቤተ ክርስቲያን ዓይነት ነው።

በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ ኢየሱስ የዚህን ቤተ ክርስቲያን ምንነት ገልጿል፣ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ስለዚህ፣ በመንፈስ የታጠቀች ሚስዮናዊት ቤተ ክርስቲያን ሁለት ዋና ዋና ባህሪያት አሏት፡ አባሎቿ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተዋል፣ ደግሞም ለእግዚአብሔር ተልዕኮ የተሰጡ ናቸው። ሌሎች በመንፈስ የታጠቁ የሚሲዮናውያን አብያተ ክርስቲያናትን የምትተክል ቤተ ክርስቲያን ናት፡ በተጨማሪም በሀገሪቱ እና በዓለም ዙሪያ ያልተደረሱ ሰዎችን ለመድረስ ቁርጠኛ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት። ማሳደግ እና መትከል ያለብን ይህን መሰል ቤተ ክርስቲያንም ነው።

# አገር በቀል የቤተ ክርስቲያን መርሆዎች

በዓለም ዙሪያ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት በሚያስደንቅ ፍጥነት እያደጉ ነው። ለዚህ እድገት አስተዋፅዖ እያደረገ ያለው የንቅናቄው ቁርጠኛ አቋም "አገር በቀል የቤተ ክርስቲያን መርሆች" በመባል ይታወቃል። ይህ እያንዳንዱ አዲስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እራሱን የሚደግፍ፣ ራሱን የሚያስተዳድር እና ራሱን የሚያስፋፋ መሆን አለባት የሚል እምነት ነው። አንተ እና ቤተ ክርስትያንህ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል ስትወጡ፣ ራሳቸውን የሚደግፉ፣ የራሳቸውን ጉዳይ የሚከታተሉ፣ የጠፉትን ለመድረስ እና ሌሎች በመንፈስ የታጠቁ የሚሲዮናውያን አብያተ ክርስቲያናትን የሚተክሉ ቤተ ክርስቲያን ሆነው እንዲያድጉ ማድረግ አለባችሁ።

አዲስ ሕፃን በቤተሰብ ውስጥ ሲመጣ፣ ወላጆቹ ሁሉንም ፍላጎቶች ያሟላሉ። ነገር ግን፣ ህፃኑ ሲያድግ እና ሲጎለብት፣ ወላጆቹ እራሱን እንዴት መንከባከብ እንዳለበት ያስተምሩታል። ህጻኑ እንዴት መኖር እንዳለበት ይማራል እና ከጊዜ በኋላ እራሱን ለመንከባከብ የበለጠ ኃላፊነት ይሰጠዋል። ልጁ ውሎ አድሮ ጎልማሳ ሲሆን፣ ወላጆቹ በራሱ የሚተማመን እና ለህብረተሰቡ አስተዋፅዖ የሚያደርግ ሙሉ ሰው አድርገው ይለቁታል።

አዲስ ቤተ ክርስቲያን የመትከል ሂደትም ተመሳሳይ ነው። መጀመሪያ ላይ፣ ወላጅ ቤተ ክርስቲያን አዲስ የተተከለችን ክርስቲያንን በመንከባከብ ብዙ ጊዜ እና ብዙ ሀብቶችን ታጠፋለች። አዲሱን ቤተ ክርስቲያን በአመራር፣ በገንዘብ እና በሠራተኞች ልትረዳ ትችላለች። አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ግን ማደግ እና መጎልመስ ይጠበቅበታል። ዓላማው፣ በቅርቡ፣ እርሱም በራሱ የሚተማመን የእግዚአብሔር መንግስት አባል ሆኖ መቆም ነው።

## ቀጥሎስ?

እንዲህ ብለህ ትጠይቅ ይሆናል፣ "እነዚህን ቤተ ክርስቲያን የመትከል መርሆች በራሴ አገልግሎት እና በቤተ ክርስቲያኔ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ምን ላድርግ? ቤተ ክርስቲያን ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን ተከላ አካል እንድትሆን እንዴት ማሳደግ እችላለሁ? የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ አብህ።

### ጸልይ

በጸሎት ጀምር። ለምን። የመከሩን ጌታ ኢየሱስን "አዝመራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና ብላችሁ ማሳውን ተመልከቱ" (ዮሐ. 4፡35) እንደሚል እግዚአብሔርን ስለ ቤተ ክርስቲያን የመትከል ራዕይ እንዲሰጥህ ከልብ። በመንፈስ የታጠቀ የሚሲዮናውያን ቤተ ክርስቲያን የሌላቸው በዙሪያህ ላሉ ማህበረሰቦች ማልድ (ማቴ. 9፡38)። ግን በዚህ ብቻ ማቆም አያስፈልግም። ወንጌል እምብዛም ወይም በፍጽም ያልደረሰበትን የሃገርህ ሕዝቦች እና ቦታዎችን ተመልከት። በምትጸልይበት ጊዜ፣ "ከእነዚህ ሕዝቦችና ቦታዎች እንድንደርስ የምትፈልገው የትኛውን ነው?" በማለት እግዚአብሔርን ጠይቅ።

### ቁርጠኛ ሁን

በመቀጠል እራስህን እና ቤተ ክርስትያንህን ለእግዚአብሔር እና ለተልእኮው አደራ ስጥ። ቤተ ክርስቲያንህ ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን ተካይ እንድትሆን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወስን።

## በሰዎች ላይ ስራ

አንዴ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ከወሰንክ በኋላ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሙሉ በሙሉ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ስራ። ስለ እግዚአብሔር ተልእኮ እና አብያተ ክርስቲያናት የመትከል ኃላፊነት ስበክ፣ አስተምር እና ተናገር። በቤተ ክርስቲያን አመራር እና ምእመናን ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን መትከል ራዕይን አካፍል። ራዕይ በማካፈል ሂደት እምቅ አቅም ያላቸውን መሪዎችን ለማገልገል እና ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ስጦታዎች እንዲያዳብሩ እድሎችን ስጥ።

## ቡድን ሰብስብ

በትክክለኛው ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ቡድንህን ሰብስብ። ማን የአዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆኖ እንደሚያገለግል እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ተከላ ቡድን ውስጥ ከፓስተሩ ጋር አብረው የሚሰሩት ሰዎችን ምረጥ። እያንዳንዱ አባል የግል ኃላፊነቶቹን እንደሚያውቅ አረጋግጥ። እንዲሁም፣ የቡድን አባላት በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን አረጋግጥ። በተጨማሪም፣ አዲሱን ቤተ ክርስቲያን በማበረታቻ፣ በጸሎታቸው እና በገንዘብ ለመደገፍ በእናት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ የድጋፍ ቡድን ማፍራት አስፈላጊ ነው።

## እቅድ አውጣ

አሁን፣ ከቡድንህ ጋር፣ እቅድ ማዘጋጀት መጀመር ትችላለህ። በእቅድህ ውስጥ፣ ለሚከተሉት ጥያቄዎቹ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡- “አዲሲቱን ቤተ ክርስቲያን መቼ እና የት ነው የምንተክለው? ማን ይሳተፋል? ምን የተለየ ነገር እናደርጋለን?” እቅዱ ምን ያህል ገንዘብ እና ምን አይነት አቅርቦቶች ይፈልጋል እና እነዚህን አቅርቦቶች እንዴት በበጀት ማካተት እችላለሁ።

## ወደ ተግባር ሂድ

አንዴ ከጸለይክ እና እቅድህን ካዳበርክ፣ ስትራቴጂህን ተግባራዊ ለማድረግ በብርቱ ተንቀሳቀስ። የጌታ መንፈስ ሃይል እንደሚሰጥህ እና ለወንጌል ሥራ እንደሚቀባህ በማመን በእምነት ውጣ። የምታውጀውን ቃል በተአምራት እና በድንቅ ያጸና ዘንድ በእግዚአብሔር ታመን። ሰዎች በሚድኑበት ጊዜ፣በመንፈስ መሞላታቸውን እና ክርስቶስን ለማገልገል መሰረታዊ ነገሮችን መማራቸውን አረጋግጥ። ቤተሰቦቻቸውን እና ጓደኞቻቸውን በወንጌል ለመድረስ ራሳቸውን መጠቀም ያስፈልጋል።

## ገምግም

በመጨረሻም፣ የቤተ ክርስቲያንን የመትከል ጥረት ከጨረስክ በኋላ፣ ስራውን ለመገምገም ቡድንህን አንድ ላይ ሰብስብ እና የሚከተሉትን ጠይቅ፣ “ምን ጥሩ ነገር አደረግን? ከዚህ የተሻለ ምን ልናደርግ ይገባ ነበር?” ችግር ሁል ጊዜ ስለማይጠፋ ተስፋ አትቁረጥ። ይልቁንም ግምገማውን የሚቀጥለውን የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ለማጠናከር እንደ ትምህርት ተጠቀመው።

---

ጉባኤህን ወደ ቤተ ክርስቲያን ተከላ አካል መምራት የክርስቶስን ተልእኮ በምድር ላይ ለማራመድ ከመጥቀሙ በላይ ለቤተ ክርስቲያንም መነቃቃትን ያመጣል። ጉባኤህ አዳዲስ የቤተክርስቲን ተከላ አካል በመሆናቸው እና ሰዎች ኢየሱስን ሲያውቁ በማየታቸው ይደሰታሉ። እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ አዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል እራሱን ወይም እራሷን በደስታ መስጠት አለባቸው።

# ~ ምዕራፍ 40 ~

# የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተልዕኮ ፕሮግራምን ማጎልበት

ኢየሱስ ማንነቱንና ለምን እንደመጣ የሚገልጽበት ጊዜ ደረሰ። አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ከሄደ በኋላ ተልዕኮውን ለመቀጠል፣ እነዚህን እውነቶች መረዳት ያስፈልጋቸዋል። ኢየሱስ ከፊልጶስ ቂሣርያ ከተማ ወጣ ብሎ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ ሲደርስ ከእነርሱ ጋር ተቀመጠ። ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ፣ “ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?” ሲል ጠየቃቸው። ደቀ መዛሙርቱ አንድ በአንድ “አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ” ብለው መለሱ።

ከዚያም ኢየሱስ በቀጥታ “እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?” አላቸው። በመለኮታዊ መገለጥ፣ ጴጥሮስ “አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ” ብሎ ተናገረ።

ኢየሱስም የጴጥሮስን ዓይን እየተመለከተ፣ “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ብፁዕ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም አይደለም።18 አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም” (ማቴ. 16፡13-20)።

ስለዚህም ኢየሱስ ማንነቱን ለደቀ መዛሙርቱ እንደገለጸላቸው እርሱ ተስፋ የተደረገበት መሲሕ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ለምን እንደመጣም ገልጦላቸዋል። የመጣው ቤተክርስቲያኑን ሊሰራ ነው። እየገነባው ያለው ቤተ ክርስቲያን ከሰው ተቋም በላይ በመለኮታዊ ተልእኮ የሚደረግ እንቅስቃሴ እንደሆነም ገልጿል። ኃይለኛ የአጋንንት ተቃውሞ ይገጥመዋል፣ ነገር ግን በመጨረሻ ያሸንፋል።

# ከእግዚአብሔር ተልዕኮ ጋር መገናኘት

ጌታ ለቤተክርስቲያኑ ያለው ዋና አላማ በእርሱ የሆነውን የመዳንን ወንጌል ከሰማይ ከመመለሱ በፊት ለወደቀው ዓለም ማወጅ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል:- "ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል" (ማቴ. 24፡ 14)። ይህ እውነት ነው፣ እያንዳንዱ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ተልእኮ ውስጥ ለመሳተፍ ቤተክርስቲያኑን የመምራት ግዴታ አለበት። ይህ ምዕራፍ ይህንን የቤተክርስቲያኑ ዋና ተግባር እንዴት በተሻለ ሁኔታ ማከናወን እንደምትችል ይመክራል።

## የግል ዝግጅት

ቤተ ክርስቲያንህን ከእግዚአብሔር ተልእኮ ጋር ለማገናኘት ከመሞከርህ በፊት፣ እራስህን ለሥራው ማዘጋጀት አለብህ። ይህንን በሚከተሉት መንገዶች ማድረግ ትችላለህ።

**1. የእግዚአብሔርን ተልእኮ መረዳት።** በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔርን ተልእኮ ግልጽ መረዳት አለብህ። ይህንን ለማድረግ፣ የእግዚአብሔር ተልእኮ ምን እንደሆነ እና ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማወቅ አለብህ። የእግዚአብሔር ተልእኮ፣ አንዳንዴ ሚሲዮ ዴኢ ተብሎ የሚጠራው፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ማዕከላዊ ጭብጥ ነው። የእግዚአብሔር ተልእኮ በምድር ላይ ካሉ ነገዶች፣ ቋንቋ እና ሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ለመቤዠትና ለመጥራት የእግዚአብሔር እቅድ ነው (ራዕ. 5፡9፤ 7፡9)። የእግዚአብሔር እቅድ በክርስቶስ፣ የአብርሃም ዘር፣ "በምድር ያሉ ህዝቦች ሁሉ እንዲባረኩ" ነው(ዘፍ. 12፡ 3፤ 22፡18፤ ገላ. 3፡16)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ይህንን ተልእኮ ለመወጣት በታሪክ ውስጥ የሰራበት ታሪክ ነው።

**2. የቤተ ክርስቲያንን ሚና መረዳት።** በተጨማሪም፣ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በመፈጸም ረገድ የቤተ ክርስቲያንን ማዕከላዊ ሚና መረዳት አለብህ። ኢየሱስ ተከታዮቹን "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" ብሎ ባዘዛቸው ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ከእግዚአብሔር ተልእኮ ጋር አቆራኝቷል(ማቴ. 28:19-20፣ ማር. 16:15፣ ሉቃ. 24:46-48፣ ዮሐንስ 20:21፣ ሐዋ. 1:8)። ይህ የኢየሱስ ትዕዛዝ ታላቁ ተልዕኮ በመባል ይታወቃል። ተልዕኮ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን አላማ ነው።

**3. የመጋቢነት ሃላፊነትን መቀበል።** በመጨረሻም፣ እንደ እውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያንን በእግዚአብሔር ተልእኮ ውስጥ እንድትሳተፍ የማስተባበር ሀላፊነትህን መቀበል አለብህ። ጌታው ቤቱን እንዲንከባከብ "ምግባቸውን በጊዜው ሊሰጣቸው" የሾመው "ታማኝና ጠቢብ አገልጋይ" መሆን አለብህ (ማቴ. 24፡ 45)። አስታውስ፣ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንዳስተዳደርክ አንድ ቀን ለእግዚአብሔር መልስ ትሰጣለህ (ሉቃስ 16፡2)።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሞዴል

የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ምን መምሰል እንዳለባት መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ምሳሌ ይሰጠናል። በአጭሩ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን መሆን አለባት። ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተልእኮ በምድር ላይ ለማራመድ ቁርጠኛ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት። በአንጾኪያ፣ ሶርያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ያለ ቤተ ክርስቲያን ነበረች (ሐዋ. 11፡19-20፤ 13፡1-4)። ሉቃስ የዚህን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አንድ ቤተ ክርስቲያን እንዴት በተሻለ ሁኔታ

ከእግዚአብሔር ተልእኮ ጋር እንደምትገናኝ በአብነት አካቷል። የእነዚህን ሁለት ምንባቦች መፈተሽ የእውነተኛ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን ሰባት ባህሪያትን ያሳያል፡-

**1. የመንፈስ መገኘት እና ኃይል።** የእውነት ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስን መገኘት እና ኃይል ዋጋ ትሰጣለች። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር "የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረች" (ሐዋ. 11፡21)። መንፈስ ቅዱስ በመካከላቸው በኃይል ይሠራ ነበር የሚለው ሌላኛው መንገድ ነው (2ኛ ነገ. 3፡15፤ ሕዝ. 3፡14)። መንፈስ በአንጾኪያ አማኞች ውስጥ በመስራቱ እና የጠፉትን በወንጌል በመድረስ ላይ ባደረጉት ትኩረት፣ "ብዙ ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ"

**2. የተቀደሰ፣ የተቀባ፣ በእምነት የተሞላ አመራር።** እውነተኛ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በተቀደሰ፣ በመንፈስ በተቀቡ፣ እምነት በተሞላባቸው እንደ በርናባስ እና ሳውል ባሉ መሪዎች ነው (ሐዋ. 11፡22-26)። መጽሐፍ ቅዱስ በርናባስ "መንፈስ ቅዱስና እምነት የሞላበት ደግ ሰው" እንደነበረ ይናገራል (ቁ. 24)። እንዲሁም በአንጾኪያ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን የመራው ሳውል፣ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ እና በእምነት የተሞላ ነበር (13፡9፤ ዝከ. 9፡17-18)።

**3. ባለ ራዕይ ውጫዊ ትኩረት።** የእውነተኛ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን የከተማዋን ወይም የመንደሯን ነዋሪዎች ትኩረት ሰጥታ ትደርሳለች። በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ይህንኑ ነው። በተጨማሪም፣ አገልግሎታቸው ሕብረብሔራዊ ነበር። ያ ማለት አይሁድ እና አህዛብ ላይ ያተኮረ ብዙ ነበር (ሐዋ. 11፡19-21)። በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያንም በክልሉ ውስጥ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ተክላለች (15፡41)። በተጨማሪም፣ ሚስዮናውያንን ወደ አሕዛብ ልከዋል (13፡1-4)። ከዚያም ከላኩት ጋር በቅርበት ተያይዘው ይሰሩ ነበር (14፡27)።

**4. ደፋር አዋጅ።** የእውነተኛ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን በአንጾኪያ እንዳለችው ቤተ ክርስቲያን "የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል" በድፍረት ታውጃለች (ሐዋ. 11፡20)። ድፍረት የተሞላበት የወንጌል አዋጅ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የደቀ መዛሙርት መገለጫ ነበር (ዝከ. 8፡4-5፤ 16፡30-32፤ 28፡31)።

**5. ስልታዊ ተልዕኮዎች ላይ ያተኮረ ስልጠና።** የእውነተኛይቱ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን ስለ እግዚአብሔር ተልእኮ በዘዴ ታስተምራለች። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "በርናባስና ሳውል እዚያ ካለችው ቤተ ክርስቲያን ጋር በመሆን አንድ ዓመት ሙሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ አስተማሩ" (ሐዋ. 11፡26)። የክርስትናን መሠረታዊ ነገሮች አስተምረው ነበር። በተጨማሪም፣ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደምትሠራ በመመልከት፣ ስለ ጌታ ተልእኮ እና ክርስቲያኖች በዚህ ተልዕኮ ውስጥ እንዴት በብቃት መሳተፍ እንደሚችሉ ያስተምሩ እንደነበር ግልጽ ነው።

**6. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ነፃ አሠራር።** እውነተኛ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ ውስጥ የመንፈሳዊ ስጦታዎችን አሠራር ታበረታታለች። በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ያሉትን የመንፈስ አሰራሮችን አበረታታለች (ሐዋ. 11፡27-28)። በዚያ የነበሩት ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲመሩ በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ጥገኛ ነበሩ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነቢይነት ስጦታ መገለጡ በርናባስንና ሳውልን ሚስዮናውያን እንዲሆኑ እና ወደ አህዛብ እንዲላኩ አነሳሳ (13፡2)።

**7. በመንፈስ የሚመራ ልግስና።** የእውነተኛ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን ለጋስ ቤተ ክርስቲያን ናት። በአንጾኪያ ክርስቲያኖች የመንግሥቱን ሥራ ለማራመድ በልግስና ሰጥተዋል። በይሁዳ ለሚኖሩ ወንድሞችና እህቶች እርዳታ በመስጠት ለአጋቦስ ትንቢት ምላሽ ሰጥተዋል (ሐዋ. 11፡29)። ይህ በጴንጤቆስጤ ቀን ከመንፈስ መፍሰስ በኋላ የሆነውን ያስታውሰናል (2፡44-45)።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ በአንጾኪያ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እንደ አብነት ልትጠቀምበት ይገባል። እነዚህ ሰባት የተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን ባህሪያት በምትመራበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲጎለብቱ ለማድረግ መሥራት አለብህ።

# የእግዚአብሔርን ተልዕኮ መተግበር

ምናልባት፣ "በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ ውጤታማ የሆነ የሚስዮን ፕሮግራም እንዴት ማስጀመር እችላለሁ? ቤተ ክርስቲያኔን ዛሬ ካለችበት ደረጃ እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ቦታ ለማሸጋገር ምን ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ እችላለሁ? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል።

ይህንን ለማድረግ፣ ተልዕኮ መር ቤተ ክርስቲያን በቅጽበት ሊፈጠር እንደማይችል መረዳት አለብህ። እንደ ማብሪያ ማጥፊያ በቅጽበት "የተልእኮ ብርሃን" በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ማብራት አይቻልም። በጉባኤ ውስጥ የሚስዮናዊ ራዕይ መፍጠር ጊዜ እና ጥረት የሚጠይቅ ሂደት ነው። እቅድ ያስፈልገዋል። እና ያ እቅድ መተግበር አለበት።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚስዮናዊ ራዕይን ለመቅረጽ ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው አምስት ውጤታማ ስልቶች እዚህ አሉ። እነዚህን ስልቶች በተከታታይ የምትተገብር ከሆነ፣ ከጊዜ በኋላ፣ ቤተ ክርስቲያን ወደ ውስጥ የምታተኩር፣ ራስ ወዳድ ቤተ ክርስትያን ከመሆን ወደ ውጭ የምታተኩር ተልዕኮ መር ቤተ ክርስትያን ትሸጋገራለች። እግዚአብሔርን ደስ የምታሰኘው ቤተ ክርስቲያን ይህች ናት።

## የጋለ ስብከት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚስዮናውያንን ራዕይ ለመፍጠር ልትጠቀምበት የምትችለው የመጀመሪያው ስልት የጋለ ስብከት ነው። ስለ እግዚአብሔር ተልእኮ እና በዚያ ተልእኮ ውስጥ ለመሳተፍ ስለ ቤተክርስቲያኑ ሀላፊነት ደጋግመህ መስበክ አለብህ። መልእክትህን ስታስተላልፍ ለተልእኮዎ ያለህ ስሜት በመግለጥ መሆን አለበት። ሰዎች የሚነኩት ለርዕሰ ጉዳዩ ከምታቀርበው ክርክር ይልቅ ነገሩ ባለህ ፍቅር ነው። በመልእክትህ መደምደሚያ ላይ፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ለእግዚአብሔር ተልእኮ እንዲሰጡ መነትነትህን እርግጠኛ ሁን። ከዚያም ለመልእክቱ ምላሽ እንዲሰጡ ጥሪ አቅርብ።[1]

## ተልዕኮ ተኮር ጸሎት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተልእኮ ራዕይን ለመፍጠር ልትጠቀምበት የምትችለው ሁለተኛው ስልት በተልእኮ ላይ ያተኮረ ጸሎት ነው። ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ለመከሩ እንድትጸልይ መጋበዝ አለብህ (ማቴ. 9፡37-38)። በእያንዳንዱ የእሁድ አገልግሎት በተልእኮ ለሚሳተፉት የጸሎት ቡድኖች ጊዜ መመደብ አለብህ። በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ አንተ ወይም የምትወክለው መሪ ቤተ ክርስቲያን ለላከቻቸው ሚሲዮናውያን ወይም ቤተክርስቲያኗን ለሚደግፏቸው የተልእኮ ፕሮግራሞች ጸሎት ማድረግ ይገባል። እንዲሁም በአገርህ እና በዓለም ዙሪያ በወንጌል ላልተደረሱ ህዝቦች እና ቦታዎች ጸሎት መቅረብ አለበት።

በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ላይ እንዲወርድ ጉባኤውን በጸሎት መምራት አለብህ። ብዙ አባላት በእግዚአብሔር ሚስዮናዊ መንፈስ ሲታጠቁ፣ ልባቸው ፍቅር ይሞላል። መንፈስም

[1] ክርስቶስን ለአህዛብ ማወጅ፡ በመንፈስ የታገዘ ተልእኮ 100 የስብከት መግለጫዎች ፣ በአፍሪካ ተስፋ፣ የሐዋርያት ሥራ 1፡8 አነሳሽነት ይገኛል። ከ www.DecadeofPentecost.org ድህረ ገጽ በነፃ ማውረድ ይችላል።

የጠፉ ሰዎችን ከአካባቢ ጀምሮ እና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ለመድረስ የበኩላቸውን እንዲወጡ ያነሳሳቸዋል (ሐዋ. 1፡8)።[2]

## ሥርዓታዊ ትምህርት

በሶስተኛ ደረጃ፣ በእግዚአብሔር ተልእኮ ላይ ስልታዊ በሆነ መንገድ በማስተማር ለተልእኮዎ ፍቅርን በእግዚአብሔር ህዝብ ልብ ውስጥ ማስገባት ትችላለህ። ይህንን ለማድረግ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለውን ተልእኮ ለመፈጸም ዘመናት ሁሉ እንዴት እንዳደረገ የሚገልጽ ትምህርት ማሰናዳት ያስፈልጋል። በዚህ መልክ መጽሐፍ ቅዱስን በአዲስ መልክ ማየታቸው በሰዎች ልብ ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናዊ ተፈጥሮ ግልጽ ግንዛቤ ይፈጥራል። ይህ መረዳት በእግዚአብሔር ተልእኮ ውስጥ የበለጠ እንዲሳተፉ ያነሳሳቸዋል።

## ዓላማ ያለው ድርጅት

የሚስዮናዊ ራዕይን በአማኞች ውስጥ ለመትከል አራተኛው መንገድ ቤተክርስቲያንን ለተልእኮ ተሳትፎ ሆን ተብሎ ማደራጀት (ወይም እንደገና ማደራጀት) ነው። ይህንን ለማድረግ፣ የቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ተልእኮ ያላትን ቁርጠኝነት የምታንፀባርቅ መሆኗ'ን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን የቤተክርስቲያኑ ዘርፎች እና አገልግሎቶች ፕሮግራሞች በጥንቃቄ መገምገም ያስፈልጋል። አንተ፣ ከቤተ ክርስቲያን አመራር ቡድን ጋር፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱ አገልግሎት "ይህ ፕሮግራም ቤተክርስቲያናችን የእግዚአብሔርን ተልእኮ እንድትወጣ የሚረዳው እንዴት ነው?" ብለህ መጠየቅ አለብህ። ፕሮግራሙ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተልእኮ እንድታከናውን ካልረዳ፣ መሰረዝ ወይም መለወጥ አለበት።[3]

## ስልታዊ አጋርነት

በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚስዮን ራዕይ ለመፍጠር ልትጠቀሙበት የምትችሉት አምስተኛው ስልት ስትራቴጅያዊ በሆነ መንገድ ከታዋቂ ከሚሲዮናውያን እና ከሚስዮን ድርጅቶች ጋር አጋርነት መፍጠር ነው። የትኛውም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተልእኮ ብቻውን መወጣት አይችልም። ተልእኮዎ መላው የክርስቶስ አካል አንድ ላይ ማስተባበር ይፈልጋል። ስለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያናችሁን በቤተ ዕምነት አደረጃጀት ከሚቀርባችሁ የድጋፍ አካላት ጋር፣ እና ከሌሎች ሕጋዊ ተልእኮ ድርጅቶች ጋር እንድትተባበር መምራት አለባችሁ። ይህን በማድረግ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ የቤተ ዕምነቱን የተልእኮ መርሃ ግብር እና ቤተ ዕምነቱ የሚደግፋቸውን ሚስዮናውያን በታማኝነት እንድትደግፍ መምራት አለባችሁ። የቤተክርስቲያናችሁ አባላት በዚህ የትብብር ጥረት እየተከናወኑ ያሉትን ሁሉ ሲያዩ፣ በተልእኮዎ ላይ የበለጠ ተሳትፎ ለማድረግ ይነሳሳሉ።

## ተሞክሮን ለጉባኤ ማካፈል

በመጨረሻም፣ አባሎችህን ከተልእኮ መስክ አገልሎት ጋር በማገናኘት የወንጌል ራዕይን በቤተክርስቲያን ውስጥ መፍጠር ትችላለህ። ከዚህ በመቀጠል የተቀመጡት ይህን ማድረግ የምትችልባቸው አምስት ውጤታማ መንገዶች ናቸው።

---

[2] በእነዚህ ርዕሶች ላይ ለበለጠ መረጃ፣ ምዕራፍ 8ን "የጸሎት ቅድሚያ የሚሰጠው" እና ምዕራፍ 11፡ "የጴንጤቆስጤ ልምድንና ልምምድን ያበረታታል" የሚለውን ተመልከት።

[3] በፖል ዮርክ በአፍሪካ የተሰፋ ግኝት ተከታታይ መማሪያ መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር ተልእኮ የበለጠ ማወቅ ትችላለህ።

**1. ሚስዮናውያን እንግዶች።** አባላትን ለሚስዮን የመስክ የአግልግሎት ተጋላጭ የምናደርግበት አንዱ መንገድ የሚስዮናውያን እንግዶች መጥተው ለጉባኤያው እንዲሰብኩ መጋበዝ ነው። እነዚህ ሚስዮናውያን የጠፉትን የመድረስ ራዕያቸውን ለቤተ ክርስቲያን ያካፍላሉ። በመስክ ላይ ያለውን ሥራ ባህሪም ለጉባኤው ያካፍላሉ። ጉባኤው እነዚህን ሚስዮናውያን ሲያዳምጡ፣ የተልእኮዎች ፍቅር በልባቸው ውስጥ ይወለዳል። አንድ ሚስዮናዊ እንዲናገር ስትጋብዝ፣ ቤተ ክርስቲያንህ ሚስዮናዊውን በልግስና፣ በወርሃዊ የገንዘብ እና የጸሎት ድጋፍ በቁርጠኝነት እና ቀጣይነት እንደምትባርክ ማረጋገጥ አለብህ።

**2. አንድ እሁድን ለተልእኮዎ መለየት።** ቤተክርስቲያናችሁን ለተልእኮዎ የአግልግሎት ተጋላጭ የምናደርግበት ሌላው ውጤታማ መንገድ በየወሩ አንድ እሑድ "ተልእኮ እሁድ" በማለት በመመደብ ነው። በዕለቱ፣ አንተ ወይም የምትወክለው ሰው፣ የሚስዮናውያን ሪፖርት ታቀርባላችሁ እና በዛም ላይ ትጸልያላችሁ። ከዚያ የሚስዮን ተኮር ስብከት ይሰበካል እና የሚስዮን ስጦታ ይሰበሰባል። ይህ ስልት ቤተ ክርስቲያን ጤናማ የተልእኮ ፈንድ እንዲኖራት ያደርጋል።

**3. ተልዕኮዎች ኮንፈረንስ።** እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን አመታዊ የሚስዮን ኮንፈረንስ መርሐግብር ማስያዝ ያስፈልጋል። የሚስዮን ኮንፈረንስ ቤተ ክርስቲያንን ለተልእኮዎች ግንዛቤ ለመፍጠር የተነደፈ ተከታታይ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ነው። ኮንፈረንሱ የጠፉትን ለመድረስ ሸክም ይጨምራል። በጉባኤው ወቅት፣ ሚስዮናውያን እንዲሰብኩ እና አገልግሎታቸውን ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲያካፍሉ መጋበዝ እንዲሁም፣ በኮንፈረንሱ ወቅት፣ የቤተክርስቲያኗን ተልእኮዎ ስኬቶች ከመጪው አመት ግቦች ጋር በማዛመድ ማጉላት ያስፈልጋል። በተጨማሪም፣ ህዝቡ በየወሩ ለቤተክርስቲያኑ ተልእኮ መርሃ ግብር ቃል እንዲገባ ጥሪ ማቅረብ ያስፈልጋል።

**4. የተልዕኮዎ ሰሌዳ።** የሚስብ የሚስዮን ሰሌዳ በማዘጋጀት እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዓይን የሆነ ቦታ ላይ በመስቀል ቤተ ክርስቲያንን ለተልእኮዎ የበለጠ ምላሽ እንድትሰጥ ማድረግ ይቻላል። በዚህ ሰሌዳ ላይ የሚስዮናውያን ምስሎች ከአገልግሎት መግለጫዎች አያይዞ መለጠፍ ይገባል። የሚስዮናውያን፣ የሚስዮን ካርታዎች እና ሌሎች ከተልእኮዎች ጋር የተገናኙ መረጃዎችም፣ ደብዳቤዎች ጭምር ሊለጠፉ ይችላሉ።

**5. የተልእኮዎች መዳረሻዎች።** ጉባኤህን ከተልእኮ መስክ ጋር የምታገናኝበት ሌላው መንገድ አባላቶቻችሁ የቤተ ክርስቲያን የተልእኮዎች መስኮች ላይ እንዲሳተፉ በማበረታታት ነው። ለምሳሌ፣ የቤተክርስቲያኑ ሚሲዮን ዘርፍ ወንጌል እምብዛም ወዳልደረሰበት አካባቢ ወይም ሕዝብ ጉዞ ለማድረግ ማቀድ አልያም ወንጌል ጨርሶ በሌለበት አካባቢ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ፕሮግራምን ድጋፍ ማድረግ ይፈልጉ ይሆናል። ይህ ለተልእኮ ሥራ ቀጥተኛ ግንኙነት ይፈጥራል። የእግዚአብሔርን መንግሥት ያሳድጋል፣ በሰዎች ልብ ውስጥ ለተልዕኮዎ ፍቅርን ይፈጥራል፣ እና አባላት የተልእኮውን ሥራ እንዲረዱ ያግዛል።

# ሚስዮናውያንን መደገፍ

ጳውሎስ በሮም ላለች ቤተ ክርስቲያን፣ ሚስዮናውያን ሄደው ለጠፉት ወንጌልን መስበክ እንዲችሉ የሆነ አካል ሊልካቸው እንደሚገባ አሳስቧቸዋል (ሮሜ. 10፡13-15)። ስለዚህ፣ የማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ፕሮግራም ዋና አካል ሚስዮናውያን ወደ መስክ መላክ እና መደገፍ ወይም መርዳት ነው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ይህን የምታደርግባቸው ሦስት መንገዶች ታማኝ የገንዘብ ድጋፍ፣ ቀጣይነት ያለው የጸሎት ድጋፍ እና የሞራል ድጋፍ በማድረግ ነው። እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

### ታማኝ የገንዘብ ድጋፍ

በመጀመሪያ፣ ቤተ ክርስቲያንህ ሚስዮናውያንን በገንዘብ መርዳት አለባት። ጳውሎስ "ለመሆኑ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው?" እያለ በቆሮንቶስ ያሉትን አማኞች ስለ እንደዚህ ዓይነት ድጋፍ ሲሞግት እናያለን(1ኛ ቆሮ. 9:7)። በተጨማሪም "ወንጌልን የሚሰብኩ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲቀበሉ ጌታ አዞአል" (1ቆሮ. 9፡14) በማለት አሳስቧቸዋል።

ሚስዮናውያን በመስክ ላይ እንዲቆዩ፣ ታማኝ እና ቀጣይነት ያለው የገንዘብ ድጋፍ ከላኪ ቤተ ክርስቲያን ማግኘት አለባቸው። ይህ ድጋፍ በአብዛኛው የሚገኘው ከግለሰቦች፣ ለጋሾች እና ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ነው። አብዛኞቹ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቤተዕነት የሚስዮን ክፍል በኩል ለሚስዮናውያን ይሰጣሉ። እንደ መጋቢ፣ ሁሉም የሚስዮን አቅርቦቶች በታማኝነት መያዛቸውን እና ለተሰጡት አላማ ብቻ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አለብህ።

### ቀጣይነት ያለው የጸሎት ድጋፍ

ሁለተኛ፣ ቤተ ክርስቲያን በመስክ ላይ ላሉ ሚስዮናውያን ቀጣይነት ያለው የጸሎት ድጋፍ ማድረግ አለባት። ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲጸልዩለት ብዙ ጊዜ ያሳስባቸዋል። ለምሳሌ፣ በተሰሎንቄ ላሉ ክርስቲያኖች፣ "በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፤ በእናንተ ዘንድ እንደሆነው የጌታ ቃል በፍጥነት እንዲሠራጭና እንዲከበር ለእኛ ጸልዩልን" (2 ተሰ. 3፡1) በማለት ተማጽኗል። ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ጸሎት የጠየቀባቸው ሌሎች ምሳሌዎች በሮሜ 15፡30-32፣ ኤፌሶን 6፡19፣ ቆላስይስ 4፡3-4 እና 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡25 ላይ ይገኛሉ። ክርስቲያኖች በጸሎታቸው አማካኝነት በመስክ ላይ ያሉ ሚስዮናውያንን መርዳት እና መልካሙን የእምነት ገድል እንዲፈጽሙ ሊረዷቸው ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ለሚሲዮናውያን ጸሎት ማድረግ ኃይለኛ መንፈሳዊ ጦርነትን ያካትታል (ኤፌ. 6፡11-18፤ ማቴ. 12፡29)።

### የሞራል ድጋፍ

በመጨረሻም፣ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያንን የሞራል እና የስሜታዊ ድጋፍ ማድረግ አለባት። ሚስዮናውያን ብዙውን ጊዜ የሚኖሩት ከቤታቸው እና ከድጋፍ ሰጪዎቻቸው ርቀው ነው። አንዳንድ ጊዜ ብቸኝነት ይሰማቸዋል እናም የሞራል ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። በቤት ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች አበረታች ደብዳቤዎችን እና ኢሜሎችን በመጻፍ ይህንን ድጋፍ መስጠት ይችላሉ።

## ያልደረሱትን ማነጣጠር

የጳውሎስ የሚስዮናዊነት አገልግሎት ትኩረት በማያገኙ ሰዎች ላይ ነበር። እንዲህ ሲል ጽፏል፡- "ሌላው በጣለው መሠረት ላይ እንዳልገነባ ብዬ፣ ክርስቶስ ባልተጠራበት ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዘወትር ምኞቴ ነበር" (ሮሜ. 15፡20)።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እያንዳንዱ የአጥቢያ የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ መርሃ ግብር ባልተደረሱ ሰዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ያልተደረሰ ሕዝብ ማለት በአካባቢያው ምንም ዓይነት እራሱን የሚደግፍ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ የሚለው ማለት ነው። ተመራማሪዎች እንደሚሉት በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ከሰባት ሺህ በላይ ያልተደረሱ ሕዝቦች አሉ። እነዚህ ያልተዳረሱት ሕዝቦች ከሦስት ቢሊዮን የሚበልጡ ሲሆኑ ስለ ኢየሱስ የምስራች መስማት በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ

ያልተደረሱ ሰዎች አብዛኛዎቹ በአፍሪካ ውስጥ ይኖራሉ። የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን የሚስዮናዊነት አገልግሎት ትኩረት እነዚህን ያልተደረሱ ህዝቦች ላይ መሆን አለባት።[4]

[4] ስላልተደረሱ ሕዝቦች www.JoshuaProject.net ድሕረ ገጽ ላይ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።

# ~ ክፍል 10 ~

# የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እና ሥነ ሥርዓቶች፣ የጌታ ዕራት እና የጥምቀት ሥርዓት

# ~ ምዕራፍ 41 ~

# የጋብቻ እና የቀብር ሥርዓትን ማስፈጸም

ሳሙኤል ከኮሌጅ እንደጨረሰ አስቴርን እንድታገባው ጠየቃት፤ እርሷም ተቀበለች። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ወጣቶች በመሆናቸው፣ እስከ ትዳር ድረስ በፆታዊ ግንኙነት ንፁህ ሆነው ለመቀጠል ራሳቸውን ሰጥተው ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ከሠርጉ በፊት፣ በብሔራቸው ውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት ተነሳ። የእያንዳንዳቸው ቤተሰቦቻቸው በስደት ወደተለያዩ አገሮች ተሰደዱ። ከሁለት አመት መለያየት በኋላ ሳሙኤል እና አስቴር ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ተገናኙ። ሰርጋቸው ትልቅ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ በሥነ ሥርዓቱ ወቅት የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሳሙኤል እና አስቴር እግዚአብሔርን በታማኝነት እያገለገሉ እንዲሁም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውን ልጆች በማሳደግ አሉ።

በሌላ ታሪክ፣ ክሪስቶፈር እና እስጢፋኖስ ሁለት በጣም የቅርብ ወንድማማቾች ነበሩ። እስጢፋኖስ በድንገት ሲሞት ክሪስቶፈር ልቡ ተሰበረ። ክሪስቶፈር ክርስቲያን ባይሆንም ወንድሙ እስጢፋኖስ ግን ነበር። እስጢፋኖስ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ዲያቆን ሆኖ እግዚአብሔርን በታማኝነት ያገለግልም ነበር። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለእስጢፋኖስ ቤተሰብ በሰጠችው ትኩረት፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ክብር እና የመጋቢያን ቀጣይ ክትትል፣ ክሪስቶፈር እና ቤተሰቡ ሕይወታቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው በመስጠት የቤተ ክርስቲያን አባላት ሆኑ። ዛሬ ክሪስቶፈር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዲያቆን ነው። ወንድሙ እስጢፋኖስ በአንድ ወቅት ባገለገለበት የአገልግሎት ዘርፍ እያገለገለ ነው።

ይህ ምዕራፍ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሠርግና የቀብር ሥነ ሥርዓቶች የሚናገረውን እንዲሁም እነዚህ ሥርዓቶች ለቤተሰብ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለማኅበረሰቡ ስላላቸው ጥቅም ያብራራል። እንዲሁም ለጴንጤቆስጤያዊ መጋቢያን ስለ ሰርግ እና የቀብር ሥነ ሥርዓቶች የመምራት እና የመከታተል ዝግጅት

ግንዛቤዎችን ይሰጣል። አንድ መጋቢ እነዚህን የተቀደሱ ሥርዓቶች እንዴት እንደሚያከናውን የሚገልጽ ዝርዝር ሁኔታ እንደየአገሩ ባሕል ሊለያይ ቢችልም፣ ይህ ምዕራፍ እነዚህን አስፈላጊ ሥርዓቶች ለማከናወን አንዳንድ አጠቃላይ መመሪያዎችን ይሰጣል።

# የሠርግ ሥነ ሥርዓት

መጽሐፍ ቅዱስ የሠርግ ሥነ ሥርዓቶችን በሚመለከት በየትኛውም ቦታ ልዩ መመሪያዎችን አላስቀመጠም። ይሁን እንጂ መለኮታዊ ፈቃድ የተከናወኑ ጋብቻዎችን በርካታ ምሳሌዎችን ዘግቦል። የሠርግ ሥነ ሥርዓቶችን በማዘጋጀት እና በማስተዳደር ረገድ ከእነዚህ ምሳሌዎች የምንማረው መርሆች የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ሊማሩ ይችላሉ።

አንዱ ምሳሌ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን እንዴት እንደ ባልና ሚስት እንዳገናኘ የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ ነው (ዘፍ. 2፡18-25)። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከፈጠረ በኋላ “የመጀመሪያው የሠርግ ሥነ ሥርዓት” ተብሎ በሚጠራው ሥርዓት ውስጥ አንድ ላይ አድርጎቸዋል። አንድ በመሆናቸው ምክንያት፣ መጽሐፍ ቅዱስ “አንድ ሥጋ” እንደ ሆኑ ይናገራል (ቁ. 24፤ ማቴ. 19፡5-6)።

በኋላ በዘፍጥረት ውስጥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ይስሐቅና ርብቃ ጋብቻ ይናገራል (ዘፍ. 24፡1-67)። ታሪኩ እግዚአብሔር የአብርሃምን አገልጋይ ርብቃ ወደምትባል ቆንጆ ከለዳዊት ልጃገረድ እንዴት እንደመራው ይገልጻል። ርብቃ አገልጋዩ ለምን እንደመጣ ከነገራት በኋላ የይስሐቅ ሚስት ለመሆን ወደ ከነዓን ለመሄድ ተስማማች። ይስሐቅን ለመጀመሪያ ጊዜ ባገኘችው ጊዜ በአክብሮት መሸፈኛዋን ወስዳ በጊዜው በነበረው ልማድ እራሷን ሸፈነች። ከዚያም አገልጋዩ ለይስሐቅ ርብቃን እንዲያገኝ እግዚአብሔር እንዴት የረዳው ገለጸለት። ከዚያም ይስሐቅ ርብቃን ወደ ሟች እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አስገባና አገባት። ርብቃን በጣም ወደዳት እና ከእናቱም ሞት ተጽናና። ይህ የይስሐቅና የርብቃ ታሪክ የሚያሳየው አንድ ሰው ከጸለየና እግዚአብሔርን ከፈለገ፣ እግዚአብሔር ደስታና ምቾት የሚካፈሉበት ታማኝ የትዳር ጓደኛ ይመራል።

ሰሎሞን “ሚስት የሚያገኝ መልካም ነገርን ያገኛል፤ከእግዚአብሔርም ዘንድ ሞገስን ይቀበላል” (ምሳ. 18፡22) በማለት ተናግሯል። የተገላቢጦሹም እውነት ነው፤ ባልን ያገኘች መልካም ነገርን አግኝታለች ከጌታ ዘንድ ሞገስን ታገኛለች። ሰሎሞን ይህን እውነት በመኃልየ መሓልይ ላይ አስፍቷ አብራርቶታል፤ በመኃልየ መሓልይ በትዳር ውስጥ ያለ የፍቅር ግንኙነትን በሚያምር ሁኔታ ይገልጻል። ወደ ቅዱስ ጋብቻ መግባት የተባረከ ነገር ነው።

## በኢየሱስ የተባረከ ጋብቻ

ኢየሱስ ስለ ጋብቻ ቅድስና በርካታ ነገር ተናግሮል (ማቴ. 5፡31-32፤ ማር. 10፡1-12)። በቃና ዘገሊላ በምትገኘው መንደር ውስጥ በነበረ የሠርግ ሥነ ሥርዓት በመገኘት ለሥርዓቱ ምን ያህል ከፍ ያለ ዋጋ እንዳለው አሳይቷል። በዚያም ውኃውን በተአምራዊ መንገድ ወደ ወይን ጠጅ በመቀየር አስተናጋጆቹን ከውርደት አዳናቸው (ዮሐ. 2፡1-11) ይህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምራዊ ምልክት መሆኑ በጋብቻ ሥርዓት ላይ የሰጠውን አስፈላጊነት የበለጠ ያጎላል።

በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ለመግለጽ መጽሐፍ ቅዱስ የጋብቻ እና የሰርግ ዘይቤዎችን ይጠቀማል። ለምሳሌ፡- በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤልን የእግዚአብሔር ሙሽራ፣ ወይም ሚስት አድርጎ ይገልፃል (ኢሳ. 62፡5፤ ኤር. 3፡14)። በተመሳሳይ መልኩ፣

በአዲስ ኪዳን፣ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ ሙሽራ እንደሆነች ገልጿል (ኤፌ. 5፡23-32)። ነቢያት እና ሐዋርያት እነዚህን የመሰሉ ምሳሌዎችን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ፍቅር እና መሰጠትን ለህዝቡ ይገልጹ ነበር። ይሄ የሚያሳየው እግዚአብሔር የጋብቻን ተቋም ምን ያህል ከፍ አድርጎ እንደሚመለከተው ነው።

## የሠርግ ሥነ ሥርዓት ዋጋ

በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ የሰርግ ሥነ ስርዓት የጥንዶችን የቤተሰብነትን ስሜት ያሳድጋል። በተጨማሪም ጥንዶቹ እርስ በርስ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያጠናክራሉ። የአዳምን ብቸኝነት ለመቅረፍ እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረ። አዳምን በተመለከተ እግዚአብሔር “ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም” ብሎ ተናግሯል (ዘፍ. 2፡18)። አዲስ የተጋቡ ጥንዶች ሁኔታም ተመሳሳይ ነው። ብቻ መሆን የሚለው ሃሳብ ከምእመናን ማኅበረሰብ መለየትም ጥሩ አይደለም የሚለውን ይጨምራል። አንድ እግዚአብሔር ስንል የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ የማንነት ሕብረት እንደሆነ ሁሉ፣ የሰው ልጆችን በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ እንዲኖሩ የተፈጠሩ ናቸው።

በአፍሪካ ውስጥ የአንድ ወንድና የሴት ጋብቻ ሁኔታ የግል ጉዳይ አይደለም። መላው ህብረተሰብ በደስታ የሚያከብረው ማህበራዊ ዝግጅት ነው። ሰርጉ ጥንዶች የእምነት ማህበረሰብ፣ የቤተ ክርስቲያን አካል መሆናቸውን ያሳያል። ባል ወይም ሚስት ከሩቅ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ከሆኑ፣ በተቀባይ ቤተ ክርስቲያን የሚታየው ፍቅር እና እንክብካቤ የቤተሰብነት ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ክርስቲያናዊ ሰርግ ለሰፊው ማህበረሰብ ሥነ ምግባራዊ መልእክት ያስተላልፋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትክክል የተጋቡ ወጣት ባልና ሚስት እኩዮቻቸው የእነርሱን ምሳሌ እንዲከተሉ ይመክራሉ። በዘመናዊው ዓለም ወንድና ሴት ሳይጋቡ በአንድ ቤት አብረው መኖር በሚያሳፍር ሁኔታ የተለመደ ሆኗል። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሚጋቡ ባልና ሚስት ለማኅበረሰባቸው ሥነ ምግባራዊ እሴት ይጨምራሉ እንዲሁም ለእኩዮቻቸው ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ።

## ለሠርጉ ሥነ ሥርዓት ዝግጅት ማድረግ

የሠርጉ ሥነ ሥርዓት ስኬት በአብዛኛው የሚወሰነው በተገቢው ዝግጅት ላይ ነው። እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ አንተ፣ እንዲሁም ሙሽሪት እና ሙሽራውን በአራት መንገዶች ማዘጋጀት አለብህ፡-

**1. መንፈሳዊ ዝግጅት።** በመጀመሪያ የሠርጉን ተሳታፊዎች መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ አለብህ። በዓለም ካለው መረዳት በተቃራኒ ጋብቻ ከማኅበራዊ ውል በላይ ነው። በእግዚአብሔር እይታ ጋብቻ በወንድ፣ በሴት እና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ቅዱስ ቃል ኪዳን ነው። ስለዚህ ጋብቻ የተዘጋጀው ከጌታቸው ጋር በቃል ኪዳን ለሚኖሩ ወንድና ሴት ነው። የሠርጉ ሥነ ሥርዓት እነዚህን ቅዱስ እውነቶች የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት።

መጋቢ እንደመሆንህ፣ ጥንዶቹ ሊገቡት ያለው ቃል ምን ያህል ከባድ እንደሆነ እንዲገነዘቡ መምከር አለብህ። እንዲሁም ሁለቱም ሙሽሪት እና ሙሽራ ዳግም መወለዳቸውን ማረጋገጥ አለብህ። አንዳቸው ጌታን እንደማያውቁ ካወቅክ ወደ ክርስቶስ ልትመራቸው ይገባል። ጌታን አውቀው ፣ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ቁርጠኛ ሕይወት ካልኖሩ፣ ሕይወታቸውን ለክርስቶስ እንዲሰጡ በድጋሚ ልትጠይቃቸው ይገባል።

**2. የባህል ዝግጅት።** ሁለተኛ፣ እንደ መጋቢ፣ የባህል ዝግጅትን ጉዳይ ግምት ውስጥ ማስገባት አለብህ። የተለያዩ የአፍሪካ ባህሎች በሠርግ ዙሪያ የተለያዩ ወጎች እና ልማዶች አሏቸው። ለምሳሌ፣

በአንዳንድ የአፍሪካ ባሕሎች ጋብቻ ሥርዓቱ ቀደም ብሎ የጥሎሽ ክፍያ መፈፀም አለበት። በእንደዚህ ዓይነት አውድ ውስጥ ፣ ተሳታፊዎቹ ከሠርጉ ቀን በፊት ባህሉን ወጉን እንዳሟሉ ማረጋገጥ አለብህ። ይህ የሚሆነው ግን እነዚህ መስፈርቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን ወይም የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት እስካላጎደፉ ድረስ ነው። በቤተ ክርስቲያን ሠርጉ ዕለት ያልተፈታ የባህል ጉዳይ ከተነሳ አሳፋሪ ሊሆን ይችላል።

3. ***ህጋዊ ዝግጅት።*** በሶስተኛ ደረጃ አንተ እና የሠርጉ ተሳታፊዎች ለሠርጉ የሚያስፈልጉትን ማንኛውንም ህጋዊ ጉዳዮች እንደፈጸሙ ማረጋገጥ አለብህ። ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያን በጋብቻ ላይ ያለት ሕጋዊ ሥልጣን ምን እንደሆነ ማረጋገጥ አለብህ። በተጨማሪም እጩ ተጋቢዎቹ በህይወት ያለ ሌላ የትዳር ጓደኛ እንደሌላቸው ማረጋገጥ አለብህ። በአንዳንድ አገሮች የጋብቻን ህግ በሚጥስ መጋቢ ላይ ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይችላልና።

አንድ መጋቢ ይህንን ሃላፊነት ችላ ብሎ በራሱ እና በቤተክርስቲያኑ ላይ አሳፋሪ ነገር አመጣ። በሠርጉ ሥነ ሥርዓት ላይ “ማንም ሰው ይህ ሰው ከዚህች ሴት ጋር መጋባት የሚከለክለው ምክንያት ካለ አሁን መናገር ይችላል አለበለዚያ ከዚህ በኃላ ለዘለአለም ዝም ይበል” ይላል። ሁሉንም በሚያስገርም ሁኔታ አንዲት ወጣት እጇን አነሳች። እርሷም “እህቴ የምታገባ ስለሆነ ሰርጉን ማቆም አልፈልግም። ነገር ግን የምታገባው ሰው የልጄ አባት ነው" ሃሳቡን ቀይሮ ወደ እህቴ ከመሄዱ በፊት ሊያገባኝ ቃል ገብቶልኝ ነበር" አለች። ከብዙ ግራ መጋባት በኋላ ሰርጉ ተሰረዘ። ፓስተሩ ተገቢውን የጀርባ ምርመራ ቢያደርግ ኖሮ ይህን አሳፋሪ ትዕይንት ማስወገድ ይችል ነበር።

4. ***የሥርዓት ዝግጅት።*** በመጨረሻም፣ እንደ መጋቢ፣ ከሠርጉ በፊት ትክክለኛ የሥርዓት ዝግጅት መደረጉን ማረጋገጥ አለብህ። ከሠርጉ ተሳታፊዎች ጋር አስቀድሞ በመገናኘት የክርስቲያን የሠርግ ሥነ ሥርዓት በእግዚአብሔር ፊት የሚደረግ የአምልኮ ሥርዓት መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግ አለብህ።

የመጋቢ፣ የሙሽራው፣ የሙሽሪት እና የሁሉም ሚዜዎች የሰርግ አለባበስ ለበዓሉ ተስማሚ መሆን አለበት። ሙሽራው እና ሙሽሪት ለሥርዓቱ የሚመጥን ደግሞ የጨዋ አለባበስ ሊለብሱ ይገባል። ሱፍ ግድ ባይሆንም ግን ይመከራል። ሙሽሪት፣ ሙሽራ እና ሴት እንግዶች በሚያምር ግን ልከኛ በሆነ ሁኔታ መልበስ አለባቸው። ተጋቢዎች እና ሚዜዎች የባህል ልብስ ለመልበስ ከመረጡ ፓስተሩ የሚለብሰውን ልብስ ማስተካከል ያስፈልገዋል።

የሠርግ ሥነ ሥርዓቱን ሂደት በደንብ ማወቅ አለብህ።[1] በተጨማሪም ከሙሽሪት እና ከሙሽሪት ጋር በመሆን እያንዳንዱን ክፍል ከእነርሱ ጋር በመወያየት ሥነ ሥርዓቱን አስቀድመህ መለማመድ አለብህ። በዚህ መንገድ፣ በዕለቱ የሚገቡትን ቃል ኪዳን በግልጽ ይገነዘባሉ። ከሠርጉ በፊት የቤተክርስቲያኑ ሕንፃ እና ግቢ መጽዳት እና ማስጌጥ አለበት።

## ***የሠርግ ሥነ ሥርዓቱን ማካሄድ***

የሠርጉ ሥነ ሥርዓት በሦስት ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡ ስብከት፣ የጋብቻ ቃል ኪዳን መለዋወጥ እና ሕጋዊ ሰነዶች መፈረም። እንደሚከተለው በዝርዝር እንመልከተው።

**1. ስብከት።** ስብከቱ ወይም ማሳሰቢያው ባልና ሚስት ለእግዚአብሔር የተሰጡ እንዲሆኑ፣ አንዳቸው ለሌላው ባላቸው ታማኝነት እና ጌታን የሚወዱ ልጆችን በማሳደግ ላይ ሊያተኩር ይገባል። ምንም እንኳን ጥንዶቹ የጋብቻ ሥርዓቱ ትኩረት ቢሆኑም መልእክቱ ግን በቦታው ላሉት ሁሉ፣ ላገቡም ሆነ ላላገቡ

[1] የሠርግ ሥነ ሥርዓቶች በማይየር ፐርልማን በተዘጋጀው በሚኒስትር አገልግሎት መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ። የዚህ መጽሐፍ ቅጂ ወይም ቤተክርስቲያን ያሰናዳችው ሌላ ምንጭ ሊኖርህ ይገባል።

መሆን ይገባዋል። መልእክቱ አጭር መሆን አለበት፤ ከአስራ አምስት ወይም ከሃያ ደቂቃዎች ባይበልጥ ይመከራል።

**2. ሥነ ሥርዓቱ።** የቃል ኪዳን እና የቀለበት ልውውጥን የሚያካትት ትክክለኛው የሠርግ ሥነ ሥርዓት በክብር መካሄድ አለበት። ከጋብቻው ዕለት ቀደም ብሎ ከጥንዶች ጋር የቃል ኪዳን ልውውጥን እና የቀለበት ልውውጥን መለማመድ ይገባል። ይህ በጋብቻው ዕለት አሳፋሪ ስህተቶችን ለማስወገድ ይረዳል።

**3. ፊርማ።** እንደ ተሾመ አገልጋይ፣ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ በሠርጉ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ያለው ሚና መንፈሳዊ እና ሕጋዊ ነው። ሁለቱንም ሚናዎች በሙያዊ መንገድ መወጣት አለብህ። ከበዓሉ በፊት፣ ህጋዊ ሰነዶች ሁሉ በቅደም ተከተል መኖራቸውን ማረጋገጥ አለብህ። እነዚህን ሰነዶች ለመፈረም በህጋዊ መንገድ የሚጠየቁ ሰዎች አስቀድመው መታወቅ አለባቸው። እነዚህ ግለሰቦች መኖራቸውን እና ኃላፊነታቸውን እንደሚያውቁ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም የሰርተፊኬት ፊርማ ማካሄድ አለብህ። እያንዳንዱ አስፈላጊ ፊርማ ከተፈረመ በኋላ ሰነዶቹን በይፋ ለጋብቻው ስኬት ትልቁን ኃላፊነት ለተሸከሙት ሙሽሪት እና ሙሽራ ማቅረብ አለብህ። ሰነዶቹ ከቀረቡ በኋላ ጥንዶቹን ባልና ሚስት መጥራት ከዚያም ባልና ሚስቱ በእግዚአብሔር ፊት እንዲንበረከኩ መጠየቅ አለብህ። ከዚያም በእነርሱ ላይ እጅ በመጫን የበረከት ጸሎት በመጸለይ፣ በአንዳንድ ባሕል ሙሽራው ሙሽሪትን ግንባር እንዲስም በመጠየቅ ሥነ ሥርዓቱ ተጠናቀቀ ይቻላል።

# የቀብር ሥነ ሥርዓት

የእህት ገርትሩድ ሞት ሲታወጅ ከተማው በሙሉ ተናወጠ። ቤተሰቧ ብቻ ሳይሆን በመላ ማህበረሰቡ ዘንድ ከባድ ሃዘን ሆነ። ወንዶች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች እና ልጆች ሁሉም አለቀሱ። ገርትሩድ የጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ነበረች። በክርስቲያናዊ ባህሪዋና ልግስናዋ ምክንያት በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ነበረች።

በቀብሯ ወቅት ፓስተሩ የማጽናኛ መልእክት አስተላልፏል። በክርስቶስ ያለውን የተስፋ መልእክትም አካፍሏል። በስብከቱ መጨረሻ፣ ፓስተሩ ህዝቡ ክርስቶስን እንደ አዳኝነት እንዲቀበሉ ጋበዘ። ብዙዎች ምላሽ ሰጥተው ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ሰጡ። በጌርትሩድ ጥሩ ምስክርነት የተሞላበት ህይወት እና በመጋቢዋ ጥበብ የተሞላበት የቀብር ሥነ ሥርዓት ፣ በህይወቷ ብቻ ሳይሆን በሞቷም ጭምር ታላቅ መልካም ነገር እንዲሆን አደረገ።

## የቀብር ሥነ ሥርዓት ዋጋ

አፍሪካውያን ህይወታቸው በማህበራዊ ኹነት የተሞላ ነው። በሕይወታቸው ዋጋ የሚሰጡዋቸው ነገሮች በዙሪያቸው ካሉ ሰዎች ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ስለዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ሲሞት፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ሁሉንም ሰው ይመለከተዋል። ከየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ ሰዎች፣ ሃይማኖታቸው ምንም ይሁን ምን፣ ለሟቹ የመጨረሻውን ክብር ለመስጠት ይሰበሰባሉ። ለህዘንተኛው ቤተሰብ አጋርነታቸውን ለማሳየትም በሥርዓቱ ይገኛሉ።

በአፍሪካ ውስጥ ያለው የቀብር ሥነ ሥርዓት ለበርካታ ዓላማዎች ያገለግላል። በመጀመሪያ፣ ቤተሰብ እና ጓደኞች እንዲሰበሰቡ እና እንዲያዝኑ እድል ይሰጣል። ይህን ሲያደርጉ ቤተሰብ ልባቸው ይጽናና እና ይበረታል። በመቀጠልም የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ለሐዘንተኞች ሃዘንን የመርሳት ስሜት ለመፍጠር ይረዳል።

የሆነውን ለመቀበል እድል ይሰጣቸዋል፣ እና በእግዚአብሔር ጥንካሬ፣ ህይወታቸውን ይቀጥሉ። በመጨረሻም፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ለጴንጤቆስጤ መጋቢ የክርስቶስን መልእክት እንዲያካፍል ጥሩ እድል ይሰጣል። በመደበኛ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሊመጡ ፈቃደኞች ያይደሉ ብዙዎች ወደ ቀብር ሥነ ሥርዓት ይመጣሉ። ጥበበኛ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ይህንን እድል በዘዴ፣ነገር ግን በሚያስገድድ ሁኔታ የመዳንን መልእክት ለማካፈል ይጠቀምበታል።

## በሞት የተለዩንን ማገልገል

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ለሀዘንተኞች ያደረጋችሁት አገልግሎት የሚጀምረው ስለ ሰውዬው ሞት እንደተረዳችሁ ነው። የሞትን ዜና ስትሰማ ፕሮግራምህን ማቆረጥአለብህ እና ወዲያውኑ ለሟቹ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ማግኘት ያስፈልጋል። ይህ ለቤተሰቡ እንደምትንከባከባቸው የመጀመሪያው ምልክት ነው። ጥቂት የማጽናኛ ቃላቶች ተገቢ እና ጠቃሚ ቢሆኑም መጀመሪያ ላይ ብዙ ማለት አያስፈልግም። ቀላሉ ከሀዘንተኛ ቤተሰብ ጋር ተቀምጠህ ኃዘን መጋራት ነው። በአጠቃላይ መገኘትህ፣ ጥቂት የማጽናኛ ቃላት እና ጸሎት ማድረግ አብዛኛውን ጊዜ በዚህ ጊዜ የሚያስፈልጉት ነገሮች ናቸው።

በኋላ፣ ቤተሰቡን ደጋግሞ መጎብኘት ያስፈልጋል፣ በዚህ ጊዜ ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብሮ መምጣት ይገባል። በዚህ ጉብኝት ወቅት፣ አንድ ወይም ሁለት መዝሙር በጋራ መዘመር፣ አጭር ማሳሰቢያ መስጠት እና ደጋግሞ ለቤተሰብ ጸሎት ማድረግ ተገቢ ነው። እንዲሁም አንዳንድ ተስማሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማንበብ እና ማካፈል ተገቢ ነው። በተጨማሪም፣ አንተ እና የአመራር ቡድንህ ቤተክርስቲያኒቱን ወክለው የገንዘብ ድጋፍ ልትሰጡ ትችላላችሁ። በተለይም በሟች ቤተሰብ ውስጥ የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ወጪ መሸፈን በማይችሉበት ጊዜ ይህ በጣም ጠቃሚ ነው።

## ለአገልግሎቱ በመዘጋጀት ላይ

አንተ እና የአመራር ቡድንህ ሀዘን ከደረሰበት ቤተሰብ ጋር በመቀመጥ የቀብር አገልግሎቱን ማቀድ አለብህ። በዚህ ስብሰባ ወቅት፣ ቀብር ላይ ስብከት እና የሟቹን የሕይወት ታሪክ (የሕይወት ንድፍ) ለማንበብ ሥራዎችን ማከፋፈል ትችላለህ። እነዚህን ተግባራት ለማን እንደሚመደብ የቤተሰቡን ፍላጎቶች ማክበር ይገባል። የቀብር ሥርዓት ሂደቱ በመደበኛነት መጋቢ መመራት አለበት። ይሁን እንጂ ቤተሰቡ በሆነ ምክንያት ሌላ ክርስቲያን አገልጋይ የቀብር ሥነ ሥርዓቱን እንዲሰብክ ከጠየቁ ፈቃደኛ መሆን አለብህ።

## የቀብር አገልግሎት

የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ራሱ በርካታ ቁልፍ ነገሮችን ማካተት አለበት። በመጀመሪያ ለሥርዓቱ ተስማሚ የሆኑ መዝሙሮች መመረጥ አለባቸው። ሁለተኛ በሥነ ሥርዓቱ ላይ ብቁና የተከበሩ ሰው ቃል ማቅረብ አለበት። ሟቹ አርአያነት ያለው የክርስትና ሕይወት ከኖረ፣ ስብከቱ የሕይወት ታሪኩን ያካተተ ሊሆን ይችላል። ያለበለዚያ መዳንን እና ከሞት በኋላ ያለውን እውነታ የሚያጎላ ቀለል ያለ መልእክት ሊሰበክ ይገባል።

የቤተክርስቲያኑ አባላት እና ጓደኞች የሟቹን መታሰቢያ ፕሮግራም ላይ ቤተሰብን በሚያጽናና መልኩ ምስክርነታቸውን እንዲያካፍሉ ሊፈቀድላቸው ይገባል። የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ረዘም ላለ ጊዜ እንዳይራዘም እና ለቤተሰብ መጽናናት ሳይሆን ተጨማሪ ሃዘን እንዳይሆን ምስክርነት የሚያቀርቡ ሰዎች አጭር መልዕክት እንዲያስተላልፉ መበረታታት አለባቸው።

እንዲሁም የቀብር አፈጻጸሙ አጭር መሆን አለበት። ይህ ሥነ ሥርዓት በመደበኛነት ተገቢ የሆነ መዝሙር፣ ጸሎት፣ እና በመጋቢው አፈር የመመለስ ሥርዓት ያካትታል። አስቀድሞ የሟቹ አስከሬን ከመበላሸቱ በፊት በደንብ መገነዙን ማረጋገጥ እና ሰዓቱን መከታተል አለብህ።

## ክትትል ቡድን

እንደ መጋቢ ያለህ ሃላፊነት በቀብር አገልግሎት አያበቃም። አፈር ከተመለሰ በኋላ፣ አንተ እና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቤተሰቡን ወደ ቤታቸው አጅበው ማድረስ ይገባል። እዚያ፣ አንዳንድ የመጨረሻ የማጽናኛ ቃላትን ማቅረብ እና መጸለይ እና ቀናት እያለፉ ሲሄዱ አልፎ አልፎ ሟች ቤተሰብን መጎብኘት አለብህ። እናም ጌታን ከማያውቁ የቤተሰብ አባላት ጋር ወንጌልን ለመካፈል እድሎችን መፍጠር አለብህ።

---

ሰርግ እና የቀብር ሥነ ሥርዓቶች የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እና ቤተ ክርስቲያን ለቤተ ክርስቲያን አባላት እና ለሌሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ሰዎች ያላቸውን ፍቅር እና አሳቢነት የሚያሳዩበት ጥሩ እድሎች ናቸው። እርሱ ወይም እርሷ እነዚህን ሥርዓቶች በፍቅር፤ በተቆርቋሪነትና በክብር በማቀድና በመምራት ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

# ~ ምዕራፍ 42 ~

# የውሃ ጥምቀት፣ የጌታ ራትን፣ ልጆችን ማስረከብ እና ሹመትን ማከናወን

የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት እንዲያስተዳድር እና ሌሎች የተቀደሱ ሥርዓቶችን እንዲያካሂድ ይጠራል። እነዚህ ድርጊቶች በሚገባቸው ክህሎት እና ክብር መከናወን አለባቸው። ይህ ምዕራፍ የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢን በዚህ ጠቃሚ የአገልግሎት ዘርፍ ለመርዳት የቀረበ ነው።

## የውሃ ጥምቀት

የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ከታዘዙት ሁለት ቅዱሳት ስርዓቶች የመጀመሪያው ነው። ኢየሱስ ራሱ በውኃ ተጠምቆ ለሚከተሉትም ምሳሌ ሆኖላቸዋል (ማቴ. 3፡13-17)። በመቀጠልም ቤተ ክርስቲያንን ሄዳችሁ አሕዛብን ሁሉ "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው" (ማቴ. 28፡19-20፤ ማር. 16፡15-16) በማለት አዟል። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አዲስ አማኞችን በጌታ ካመኑ በኋላ በውኃ በማጥመቅ የኢየሱስን መመሪያ በጥንቃቄ ተከትላለች (ሐዋ. 13-15፣ 31-33፣ 18:8፣ 19:5)። የውሃ ጥምቀት መለኮታዊ ትእዛዝ እንጂ አማራጭ አይደለም። ስለዚህ፣ እንደ ጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ፣ ይህንን ስርዓት በታማኝነት እና በብቃት ለመፈጸም እራስህን ማዘጋጀት አለብህ።

### ትርጉሙ

የውሃ ጥምቀት አገልጋዩም ሆነ አዲሱ አማኝ ሊታዘዘው የሚገባ ተግባር ነው። አዲሱ ደቀ መዝሙር በክርስቶስ ያለውን እምነት እና ጌታን ሙሉ በሙሉ ለመከተል ያለውን ቁርጠኝነት በአደባባይ የመናዘዝ ምሳሌ ነው። ጥምቀት በራሱ አያድንም። ከዚህ ይልቅ የዳነውን ሰው "በንጹሕ ኅሊና በእግዚአብሔር

ፊት የሚቀርብ መማፀኛ" ነው (1ጴጥ. 3፡21)። የውሃ ጥምቀት የኢየሱስን ሞት፣ መቀበር እና ትንሳኤ ያሳያል (ሮሜ. 6፡3-11)። እርሱም የአዲሱን አማኝ ለዓለም መሞት እና በክርስቶስ ለአዲስ ሕይወት ትንሣኤውን ያሳያል (2ቆሮ. 5፡17)። በተጨማሪም፣ የውሃ ጥምቀት የሚያመለክተው አዲሱ አማኝ ተልዕኮውን ለመፈጸም ከክርስቶስ ጋር ለመተባበር ያለውን ቁርጠኝነት ነው (ማቴ. 3፡15)።

## ተሳታፊዎች

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታ እና አዳኝ በቅንነት የሚያምን ማንኛውም ሰው በውሃ መጠመቅ ይችላል፣ ደግሞም አለበት። ሥርዓቱ ሰው ጌታን ካገኘ በኋላ ብዙም ሳይቆይ መከናወን አለበት። ነገር ግን፣ አንድን ሰው በውሃ ከማጥመቅህ በፊት፣ በእውነት ዳግመኛ መወለዱን እና የሥርዓቱን ትርጉም ሙሉ በሙሉ መረዳቱን በመጀመሪያ መጠይቅ አለብህ።

## ዘዴው

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥምቀት ዘዴ ሙሉ በሙሉ በውኃ ውስጥ ማጥለቅ ይጠይቃል። "ማጥመቅ" የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም ማጥለቅ ማለት ነው። በተጨማሪም፣ የመጥለቅ ከሥርዓት ከክርስቶስ ጋር የሞት፣ የመቀበር እና የትንሣኤ ምሳሌያዊ ትርጉም ጋር ይስማማል (ሮሜ 6፡2-4)።

አዲስ ክርስቲያኖችን በውኃ ለማጥመቅ የሚከተለውን ዘዴ መጠቀም ትችላለህ። ከሚጠመቀው ሰው ጋር ወደ ውሃ ውስጥ መግባት። ቀጥሎ እጩው ክርስቶስን እንዴት አዳኝ ሆኖ እንዳገኘው አጭር ምስክርነት እንዲያካፍል እድል መስጠት። በመቀጠል እጩውን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡-

- "ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታህና አዳኝህ እንደሆነ በነጻ ትመሰክራለህ?"
- "ዓለምን፣ ሥጋንና ዲያብሎስን ከደሃል፣ እናም ራስህን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ እና ሕይወትህ ለፈቃዱ ትሰጣለህን?"
- "ለጌታ በሚገባ መንገድ በአዲስ ህይወት እንድትመላለስ በእግዚአብሔር እና በቤተክርስቲያኑ ፊት ራስህን ትሰጣለህ?"
- "ሌሎችን በክርስቶስ እንዲያምኑ ለመመስከር ለክርስቶስ እና ለተልእኮው ሙሉ በሙሉ ትሰጣለህ?"

እጩው ለእያንዳንዱ ለእነዚህ ጥያቄዎች "አዎ" የሚል መልስ መስጠት አለበት። ከዚያም እጩውን በውሃ ውስጥ ታጠልቀዋለህ፣ "በክርስቶስ ጌታህ እና አዳኝህ እንደሆነ ስላመንክ፣ እና እርሱን ለመከተል ሁሉንም ለመካድ ቃል ስለገባህ፣ እኔ (ሙሉ ስም) በስመ አብ እና ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አጠምቅሃለሁ። አሜን።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች

በጥምቀት አገልግሎት ወቅት የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ጥቂቱን ወይም ሁሉንም ለማንበብ አስፈላጊ ነው።

- የኢየሱስ ጥምቀት (ማቴ. 3፡13-17፤ ማር. 1፡9-11)
- ታላቁ ተልዕኮ (ማቴ. 28፡18-20፤ ማር. 16፡14-20)
- የጴንጤቆስጤያዊ ቀን (የሐዋርያት ሥራ 2፡36-41)

- ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ (ሐዋ. 8፡36-39)
- የጳውሎስ ትምህርት ስለ ጥምቀት (ሮሜ 6፡3-11፤ ገላ. 3፡26-29፤ ቆላ. 2፡11-15)።

# የጌታ እራትን

ቅዱስ ቁርባን በጌታ በኢየሱስ ከተመሠረቱት ሁለት የተቀደሱ ሥርዓቶች ሁለተኛው ነው (ማቴ. 26፡ 26-29፤ ሉቃ. 22፡14-20፤ 1 ቆሮ. 11፡23-26)። እርሱም "እንጀራ መቁረስ" (ሐዋ. 2:42) እና "የጌታ እራት" (1ቆሮ. 11:20) ተብሎም ተጠርቶል። “ቁርባን” የሚለው ቃል ሴና ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም “የምሽት ምግብ/እራት” ማለት ነው። ኢየሱስ ይህን ሥርዓት ያቋቋመው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሰገነት ላይ በነበረው የመጨረሻ መዓድን በወሰደበት ወቅት ነው። የውሃ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ እና አማኙ በክርስቶስ ወደ አዲሱ ህይወቱ መግባቱን የሚያመለክት ሲሆን፣ ቁርባን በመደበኛነት ይከናወናል እና ክርስቲያኑ ከጌታ ጋር ስላለው ቀጣይነት ያለው ጉዞ ይናገራል።

## የጌታ እራትን ትርጉም

የጌታ እራትን አማኙን የኢየሱስን የመስቀል መስዋዕትነት ያስታውሳል። የተቆረሰው እንጀራ የተወጋውን ሥጋውንና የፈሰሰውን ደሙን ያስታውሳል (ሉቃስ 22፡19-20)። በ1ኛ ቆሮንቶስ 11 ላይ፣ ጳውሎስ በጌታ እራት አገልግሎት ወቅት ልናደርጋቸው ስለሚገቡ አምስት ነገሮች ተናግሯል።

1. ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱን ማስታወስ አለብን (ቁ. 24-25).
2. የአዲስ ኪዳንን ትርጉም ማጤን አለብን (ቁ. 25፤ ማቴ. 26፡28)።
3. በቅርቡ እንደሚመጣ ማወጅ አለብን (ቁ. 26፤ ማቴ. 26፡29፤ ሉቃ. 22፡16-18)።
4. በአንድነት መንፈስ መሰባሰብ አለብን (ቁ. 18-21፣ 33)።
5. እራሳችንን ለክርስቶስ የማዳን ተልዕኮ መስጠት አለብን (ቁ.26)።

## ተሳታፊዎች

አብዛኞቹ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ለሁሉ ክፍት የሆነ የጌታ እራትን ሥርዓት ያደርጋሉ። ይህ ማለት ክርስቶስን በእውነት እንደ አዳኝ የተቀበሉ እና እርሱን በታማኝነት የሚያገለግሉትን ሁሉ ወደ ሥርዓቱ እዲቀርብ ይፈቀዳል ማለት ነው። ተሳታፊው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት አባል መሆን አይጠበቅበትም። አንዳንድ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት የጌታ እራትን መውሰድ ያለባቸው በውሃ የተጠመቁ መሆን አለባቸው ይላሉ። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የቤተ ዕምነት ፖሊሲ በተመለከተ ግልጽ መሆን አለበት እና ያንን ወግ መከተል ይገባል። የጌታ እራትን የሚቀበል ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ ለመራቅ ልብን እንዲመረምር ሊታዘዝ ይገባል (1ቆሮ. 11፡27-29)።

## ድግግሞሽ

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በምን ያህል ጊዜ የጌታ እራትን ማድረግ እንዳለባት የተለየ መመሪያ አይሰጥም። ይሁን እንጂ ሥርዓቱ በመደበኛነት እና በተደጋጋሚ መከናወን እንዳለበት ያመለክታል። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በየ እሁዱ ጥዋት የጌታን እራት ይወስዳሉ፣ ሌሎች ደግሞ በየወሩ በየሩብ አመትም ያደርጋሉ። ዋናው ነገር በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የጌታን እራት በመደበኛነት ማቀድ ነው።

## ሥነ ሥርዓቱ

የጌታ እራትን የተቀደሰ ሥርዓት ነው። ስለዚህ በሥርዓትና በክብር መከናወን እንጂ መቸኮል የለበትም። መጋቢውን የሚረዱ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ መንፈሳዊ ወንዶች እና ሴቶችን መምረጥ

ያስፈልጋል። ይህ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን፣ ዲያቆናትን ወይም ረዳት መጋቢያንን ሊያካትት ይችላል። መጋቢው የጌታ እራትን ሥነ ሥርዓቱ እንዴት እንደሚካሄድ አስቀድሞ አገልጋዮቹን ማስተማር አለበት።

ሥርዓቱን በአጭር ማሳሰቢያ ወይም ተስማሚ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማንበብ ትጀምራለህ። ከዚያም ጸልየይህ ኅብስቱንና ጽዋውን ለዲያቆናት ታከፋፍላለህ። ከዚያም ዲያቆናቱ ኅብስቱንና ጽዋውን ለጉባኤው ያከፋፍላሉ። ሁሉም ሰው ኅብስቱንና ጽዋውን ከተቀበለ በኋላ ተገቢውን ጥቅስ ታነባለህ (ማለትም፣ 1ቆሮ. 11፡23-26)። ከዚያም ጉባኤው አብሮ ይወስዳል።

በማቴዎስ 26፡26-29 ላይ የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል፣ በሥነ ሥርዓቱ ውስጥ አምስት ነገሮችን ማካተት ያስፈልጋል፡- ምስጋና፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ፣ የንባብ ስርጭት፣ መዝሙር እና ጸሎት። ሥነ ሥርዓቱ በአገልግሎት ወቅት በማንኛውም ተገቢ ሰዓት ሊከናወን ይችላል።

### የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች

በጌታ እራት አገልግሎት ጊዜ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ማንበብ ትችላለህ፡-

- ኢየሱስ የጌታ እራትን ትዕዛዝ ሰጠ (ማቴ. 26፡17-29፤ ማር. 14፡12-25፤ ሉቃ. 22፡7-20)
- የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን አሠራር (ሐዋ. 2፡42-46፤ 20፡7)
- ጳውሎስ የጌታ እራትን ያብራራበት ክፍል (1ቆሮ. 10፡16፤ 11፡18-31)።

## ልጆች ለጌታ ማስከብ

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ የጴንጤቆስጤያዊ አብያተ ክርስቲያናት ልጆችን ለጌታ በቤተ ክርስቲያን የመስጠትን ሥርዓት አላቸው። እንደ የውሃ ጥምቀት ወይም እንደ የጌታ እራትን ያለ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ባይሆንም ትርጉም ያለው ተግባር ነው።

በብሉይ ኪዳን፣ ልጆች ለእግዚአብሔር ማቅረብ እና በሙሴ ሕግ የመግረዝ ልማድ ነበር (ዘጸ. 13፡ 2፣ 12-13፣ 15፤ 22፡29፤ 1 ሳሙ. 1፡20፣ 24-28፤ 3: 19) ሐና ልጇን ሳሙኤልን ለእግዚአብሔር ስትቀድሰ የሚከተለውን ብላለች፡- “ስለዚህ እኔም ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ፤ በሕይወት ዘመኑም ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል” (1ሳሙ. 1፡28)። የኢየሱስ ወላጆች ኢየሱስን ለጌታ በመቀደስ ይህንን ልማድ ተከትለዋል (ሉቃስ 2፡22-38፣ 40)። ኢየሱስ ራሱ “ሕፃናቱንም ዐቀፋቸው፤ እጁንም ጭኖ ባረካቸው” ይላል (ማር.10፡16)።

### ትርጉሙ

በሥነ ሥርዓቱ ወቅት ልጆች ለጌታ መሰጠት ከሕፃን ጥምቀት ጋር አንድ ዓይነት እንዳልሆነ አጽንዖት መስጠት አስፈላጊ ነው። ልጆች ለጌታ ማስረከብ ልጁን አያድነውም ወይም ልጁን ክርስቲያን አያደርገውም። ይልቁንም ድርጊቱ ልጁን “በጌታ ምክርና በተግሣጽ” (ኤፌ. 6፡4) ለማሳደግ ወላጆች ራሳቸውን የሰጡበት የመቀደስ ተግባር ነው።

ልጆች ለጌታ ማስከብ ለወላጆች እግዚአብሔር ለሰጠው አስደናቂ ስጦታ በአደባባይ ምስጋና መስጠት ነው። መላው ጉባኤ ከወላጆች ጋር የሚደሰትበት ወቅት ነው። አንድ ላይ ሆነው ልጁን በፍቅር ለመከበብ እና እርሱን በእምነት ለመምከር የሚወስኑበት ሥርዓት ነው።

## ሥነ ሥርዓቱ

ልጆች ለጌታ ማስረከብ ሥነ ሥርዓት ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን እና ከባህል ወደ ባህል ሊለያይ ይችላል። በአብዛኛው በተለምዶ የእሁድ ጠዋት የአምልኮ አገልግሎት አካል ሆኖ ይከናወናል። አራት ክፍሎችን ሊያካትት ይችላል፡ (1) ፓስተሩ በልጁ ላይ እጁን ጭኖ የእግዚአብሔርን በረከት በእርሱ ላይ እዲሆን ይጸልያል፤ 2) ፓስተሩ ልጁ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ለማሳደግ ለወላጆች ጥበብ እንዲሰጥ ይጸልያል። (3) ፓስተሩ ልጁን ጌታን እንዲወድ እና እንዲያገለግል እንዲያሳድጉ ለወላጆች ማሳሰቢያ ይሰጣል። እና (4) ፓስተሩ ቤተ ክርስቲያን ልጁን በእግዚአብሔር መንገድ እንዲያሳድጉ ወላጆችን እንድትደግፍ ጥሪ ያቀርባል።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች

ልጅ በሚሰጥበት ወቅት የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ሊነበቡ ይችላሉ፡-

- እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን (ዘፍ. 18፡19)
- ልጅን መምራት (ምሳ. 22፡6)
- ልጆችን የተመለከተ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት (ዘዳ. 6፡6-9)
- ሐና ሳሙኤልን ለእግዚአብሔር ስለ መስጠቷ (1ሳሙ. 1፡20-2፡26)
- ኢየሱስ ሕፃናትን መባረኩ (ማቴ. 19፡13-15፤ ማር. 10፡13-16፤ ሉቃ. 18፡15-16)
- ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ስለ ማቅረባቸው (ሉቃ. 2፡22-38፣ 40)
- ልጆችን ማሰልጠን (ኤፌ. 6፡4)።

# የመሪዎች ሹመት

የብሉይም ሆነ የአዲስ ኪዳን መሪዎችን ስለ ሹመት ይናገራሉ። እግዚአብሔር አሮንንና ልጆቹን ለክህነት እንዲቀድሳቸው ሙሴን አዘዘው (ዘጸ. 29፡1-27፤ ዘሌ. 8፡1-36፤ ዘኁ. 3፡3)። በኋላም ሙሴን በቤተ መቅደሱ ከሚያገለግሉት ሌዋውያን ጋር ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርግ አዘዘው (ዘኁ. 8፡5-22)።

በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት በመጀመሪያ ዲያቆናት ለመሾም እጃቸውን ጫኑ (ሐዋ. 6፡6)። በተመሳሳይም በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በበርናባስና በሳውል ላይ እጃቸውን ጭነው ለጌታ ሥራ ለይተዋቸዋል (ሐዋ. 13፡2-3)። በተጨማሪም ጳውሎስ ቲቶ በተለያዩ ከተሞች ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችን እንዲሾም አዘዘው (ቲቶ 1፡5)። በዚህ ክፍል ውስጥ “መሾም” ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ግስ *kathistēmi* ሲሆን ትርጉሙም “መሾም” ወይም “በቢሮ ውስጥ ማስቀመጥ” ማለት ነው።

የሹመት ሥነ ሥርዓቱ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አገልጋይን በጸጋው ለመለየት ይረዳል። የአገልግሎት ኃላፊነትን ለማወቅም ይረዳል። የተሾመው ሰው በጉባኤው ዘንድ ያለውን ተቀባይነት የበለጠ ያሳድጋል። የሹመት ሥነ ሥርዓቱ እጩው የክርስቶስ አገልጋይ መሆኑን የምናስተዋውቅበት ጊዜ ነው፣ በዚህም ምክንያት ሥልጣን እየሰጠነው ነው። ስለዚህ እርሱ የመንጋው ባለቤት የሆነ የጌታ አገልጋይ ነው እንጂ ገዥ አይደለም (1ጴጥ. 5፡1-4)።

### *ሥነ ሥርዓቱ*

እንደ መጋቢ፣ አዲስ የሚሾመውን አገልጋይ በመድረክ ፊት ለፊት በመጥራት የሹመት ሥነ ሥርዓቱን ትጀምራለህ። ከዚያም ተስማሚ የሆነ የቅዱሳት መጻህፍት ምንባብ ታነባለህ እና የሚሾመውን አገልጋይ ከጉባኤው ጋር ታስተዋውቃለህ። የአገልግሎቱን ኃላፊነት ለጉባኤው በአጭሩ ማስረዳት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር በመንፈስ እንዲሞላቸው እና በአገልግሎታቸው እንዲባርካቸው በመጠየቅ በተሾመው አገልጋይ ላይ እጅህን ትጭናለህ።

በዚህ አውድ ውስጥ እጆችን መጫን ከሥነ-ሥርዓት በላይ ሊሆን ይችላል። በአዲስ ኪዳን ሰዎች ብዙ ጊዜ እጅን መጫን በመንፈስ ከመሞላት ጋር ይያያዛል (ሐዋ. 8፡17፤ 9፡17-19፤ 19፡6)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "በእጆቼ መጫን የተቀበልኸውን በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታቀጣጥል " በማለት አሳስቦታል (2 ጢሞ. 1፡6)። ሐዋርያው ጢሞቴዎስ በዚያ ወቅት የተቀበለውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እየተናገረ ነው። ስለዚህ፣ "እጄን በእናንተ ላይ በምጭንበት ጊዜ፣ በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞሉ ልባችሁን ለእግዚአብሔር ክፈቱ" በማለት እጩዎቹን አስቀድመው ማዘጋጀት አለብህ።

### የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚሾሙበት ጊዜ ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ማንበብ ትችላለህ:-

- የሰባቱን መምረጥ (የሐዋርያት ሥራ 6፡1-7)
- የክርስቶስ የአገልግሎት ስጦታዎች (1ኛ ቆሮ. 12፡28-31)
- የእግዚአብሔር ስጦታዎች መጋቢዎች (1ጴጥ. 4፡10-11)
- ስጦታህን ቸል አትበል (1ጢሞ. 4፡9-16)
- የእግዚአብሔርን ስጦታ አነሳሱ (2ጢሞ. 1፡1-8)።

# የሕንፃዎች ምረቃ

የሕንፃዎች ምረቃ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሕንፃዎች የመለየት ቅዱስ ተግባር ነው። ህንጻዎችን ለጌታ የመሰጠት ልምምድ ትርጉሙን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እናገኛለን። በተለያዩ አጋጣሚዎች እስራኤላውያን ሕንፃዎችን ለእግዚአብሔር ለይተው ነበር። በምድረ በዳ ሙሴና ጉባኤው የማደሪያውን ድንኳን ለእግዚአብሔር አምላክ ሰርተው ለዩ (ዘጸ. 40፡1-38)። መሠዊያውንም ለእግዚአብሔር ሰርተው ለዩ (ዘኍ. 7፡10-11፣ 84-88)። ከብዙ ዓመታት በኋላ ዕዝራ "የእግዚአብሔርን ቤት መመረቅ በደስታ አከበረ" (ዕዝራ 6፡16)።

በኢየሩሳሌም የሚገኘው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ መመረቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት የሕንጻ ምረቃ ሥነ ሥርዓቶች ከሁሉ የተሻለው ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ገንብቶ እንደጨረሰ፣ ታላቅ በዓል አዘጋጀ (1 ነገ. 8)። በበዓሉ ወቅት ንጉሥ እግዚአብሔር ወደ ሕንፃው እንዲመጣ እንዲያድር በመጋበዝ የምረቃ ሥነ ሥርዓት መርቷል (1ኛ ነገ 8፡13-53)።

## ዓላማው

ዛሬ፣ የቤተ ክርስቲያን ህንጻዎችን ለጌታ ስንሰጥ፣ እንደ ሙሴ፣ ዕዝራ እና ሰሎሞን ለእርሱ ብቻ እና ለእርሱ ብቻ እንለያቸዋለን። ለእግዚአብሔር:- “ይህንን ህንጻ ለአንተ ወስነናል፣ ለስምህም ክብር ለመስጠትና በምድር ላይ ሥራህን ለማስፋት እንጠቀምበታለን”።

እንደ ጴንጤቆስጤያዊ ክርስቲያኖች፣ የጌታ መንፈስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ እንደሚኖር (1ቆሮ. 3:16)፣ እና ለአገልግሎት ኃይል እንደሚሰጣቸው እንረዳለን (ሐዋ. 1:8)። ሆኖም፣ የእግዚአብሔር መገኘት አንዳንድ ጊዜ ህንጻን ወይም ስፍራን እንደሚሞላ ቃሉ እንደሚገለጽም እንረዳለን። በበዓለ ሃምሳ “ድንገት እንደ ዓውሎ ነፋስ ንፋስ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት ሁሉ ሞላው” (ሐዋ. 2:2) የሆነውም ይኸው ነው። ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሙ ሲሰበሰቡ ጌታ መገኘቱን እንደሚገልጥ ቃል ገብቷል (ማቴ. 18:20)።

የምረቃ ሥርዓቱ ዓላማ አዲሱን ሕንፃ ግንባታ እንዲያጠናቅቁ ቤተ ክርስቲያንን ስለረዳ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው። እንዲሁም የአዲሱን ሕንፃ ለእርሱ እና ለዓላማው መስጠት ነው። በፕሮግራሙ፣ ጉባኤው በእግዚአብሔር ቃል እንደሆነው ጌታ እንዲገኝ ይጋብዛል። በተጨማሪም፣ የቤተክርስቲያኑ አባላት ለእግዚአብሔር እና የማዳን ተልእኮው ራሳቸውን ለመስጠት ቃላቸውን ያድሳሉ።

## የሕንጻን የማስረከብ አገልግሎት

የውዳሴ አገልግሎቱ በመጋቢ ወይም በተጋበዘ የቤተ እምነት መሪ መመራት አለበት። የተከበሩ እንግዶች ሊገኙ በሚችሉበት ልዩ ቀን ሥነ ሥርዓቱን ማድረጉ ጥሩ ነው። የህጻናት ማስረከብ አገልግሎት የሚከተሉትን ተግባራት ማንኛውንም ወይም ሁሉንም ሊያካትት ይችላል።

- ሪባን መቁረጥ
- የመቀደስ ጸሎት
- ለእንግዶች እውቅና መስጠት
- የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ
- ምስክርነቶች
- አምልኮ
- የምስጋና መስዋዕት ነው።
- ስብከት
- የአዲሱን ሕንጻ ጉብኝት
- የጋራ ምግብ ወይም ሻይ ቡና ጊዜ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች

በግንባታ ምርቃት ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ሊነበቡ ይችላሉ።

- የቤተመቅደስ መመረቅ (2ዜና. 6:1-2፣ 17-20፣ 40፤ 7:1-5)
- የእግዚአብሔር አደባባይ (መዝ. 84)
- ወደ እግዚአብሔር ቤት መሄድ (መዝ. 122)።

## ምዕራፍ 42 የውሃ ጥምቀት፣ የጌታ ራትን፣ ልጆችን ማስረከብ እና ሹመትን ማከናወን

---

የጌታ እራት ሥርዓትን ማክበር፣ ሕፃናትን ለጌታ ማስረከብ ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሹመት እና የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች ምረቃ እያንዳንዳቸው የጴንጤቆስጤያዊ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ወሳኝ አካል ናቸው። የጴንጤቆስጤያዊ መጋቢ እነዚህን ስርዓቶች በሚገባቸው ክብር እና ስነ ስርዓት መምራት አለበት።

# አባሪዎች

# ~ አባሪ 1 ~
# የእምነት መግለጫ
# የዓለም ጉባኤ እግዚአብሔር ህብረት

ይህ የእምነት መግለጫ በመካከላችን ለእምነት፣ ኅብረት እና ትብብር መሠረት እንዲሆን የታሰበ ነው። በዚህ እምነት መግለጫ ያለው ጹሑፍ እስትንፋሰ እግዚአብሔር አይደለም፣ ነገር ግን የተቀመጠው ሃሳብ እውነት እደሆነ እና ለእውነተኛ የጴንጤቆስጤያዊ አገልግሎት አስፈላጊ ነው ተብሎ ይታሰባል። ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ለማንሳት ሳይሆን ወሳኝ አስተምህሮዎች ብቻ ለመሸፈን ታቅዶ የተዘጋጀ ነው።

## 1. የቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔርነት

ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ብሉይ እና አዲስ ኪዳን፣ በቃል በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ እና የእግዚአብሔር መገለጥ፣ የማይሳሳት፣ ሥልጣን ያለው የእምነት እና የምግባር ገዢ እንደሆኑ እናምናለን። እስትንፋሰ እግዚአብሔር ወደ በእናት መዝገብ ሁሉ በእኩል እና በተሟላ ሁኔታ አለ፣ ይህም ታማኝነታቸውን ሁሉ ያረጋግጣል (2ጢሞ. 3፡15-17፤ 2 ጴጥ. 1፡21)።

## 2. የዘላለም አምላክ

እውነተኛና ሕያው በሆነው ዘላለማዊ፣ በራሱን ሕልው የሆነ፣ እና ራሱን በአንድ ሕላዌ እና በሦስት አካላት በገለጠው በአንድ አምላክ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እናምናለን (ማቴ. 3፡16-17፤ ማቴ. 28፡19)።

ሀ. እግዚአብሔር አብ። የሥላሴ የመጀመሪያ አካል በሆነ ለዘላለም የሚኖር፣ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣ሕግ ሰጪ፤ ሁሉ በሁሉ ይሆኑ ዘንድ ሁሉ የሚታዘዙለት በእግዚአብሔር አብ እናምናለን (ዘፍ. 1፡1፣ ዘዳ. 6፡4፣ 1 ቆሮ. 15፡28)።

ለ. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ። የሥላሴ ሁለተኛ አካል በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ይህም የእግዚአብሔር ልጅ ዘላለማዊ ነበር፤ በመንፈስ ቅዱስ ሥጋ ሆኖ ከድንግል ማርያም መወለዱን እናምናለን።

ኃጢአት በሌለበት ሕይወቱ፣ በተአምራዊ አገልግሎቱ፣ በምትክ የሥርየት ሞት፣ በአካል ትንሣኤ፣ በክብር ማረጉን፣ በማያቋርጥ ምልጃው እናምናለን (ኢሳ. 7፡14፤ ዕብ. 7፡25-26፤ 1 ጴጥ. 2፡22፤ ሐዋ. 1፡9፤ 2፡22፤ 10፡38፤ 1ቆሮ. 15፡4፤ 2 ቆሮ. 5፡21)።

ሐ. መንፈስ ቅዱስ። የሥላሴ ሦስተኛ አካል በሆነው በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፣ እርሱ ከአብ እና ከወልድ የሚወጣ፣ እና ኃጢአተኛውን በመውቀስ እና የመንፈስ ልደት በመስጠት እና አማኙን ወደ

እውነት ሁሉ በመለየት ሥራ ሁል ጊዜም ሆነ ንቁ ነው (ዮሐ. 14:26፤ 16:8-11፤ 1 ጴጥሮስ 1:2፤ ሮሜ. 8:14-16)።

# 3. የሰው ውድቀት

የሰው ልጅ መልካም እና ቅን ሆኖ እንደተፈጠረ እናምናለን። ነገር ግን አዳም እና ሔዋን በፈቃዳቸው በፈጸሙት በደል ከአምላክ እንዲርቁ ሆኖል፤በዚህም ምክንያት ሥጋዊ ሞት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሞትም አስከትሏል ይህም ከእግዚአብሔር መለየት ነው (ዘፍ. 1:16-27፤ 2:17፤ 3:6፤ ሮሜ 5:12-19)።

# 4. የሰው መዳን

ስለ ኃጢአታችን በሞተው፣ በተቀበረውና በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣው በክርስቶስ በማመን መዳንን እናምናለን። በማስተሰረያ ደሙ፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባቀረበው መስዋዕትነት ለሰው ልጆች ሁሉ ድነት ተዘጋጅቷል። ይህ ልምምድ አዲስ ልደት በመባልም ይታወቃል፣ እናም ቅጽበታዊ እና ሙሉ በሚያደርግ የመንፈስ ቅዱስ አሰራር ያመነ ኃጢአተኛ እንደገና ይታደሳል፣ ይጸድቃል እና ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ይቀላቀላል በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት እና የዘላለም ሕይወት ወራሽ ይሆናል (ዮሐ. 3፡5-6፤ ሮሜ 10፡8-15፤ ቲቶ 2፡11፣ 3፡4-7፤ 1ዮሐ. 5፡1)።

# 5. መለኮታዊ ፈውስ

በክርስቶስ የስርየት ሞት ከበሽታ መዳን እንደቀረበ እና የአማኞች ሁሉ ዕድል ፈንታ እንደሆነ እናምናለን (ኢሳ. 53፡4-5፤ ማቴ. 8፡16-17፤ ያዕ. 5፡14-16)።

# 6. ቤተ ክርስቲያን እና ተልዕኮው

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እና በመንፈስ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንደሆነች እናምናለን። ቤተ ክርስቲያን አሁን ባለው ዓለም የእግዚአብሔር መንግሥት መገኘት ትመሰክራለች። ዓለም ዓቀፉ ቤተ ክርስቲያን ዳግመኛ የተወለዱትን ሁሉ ያጠቃልላል (ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡22፤ ሮሜ. 14፡17-18፤ 1 ቆሮ. 4፡20)።

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ (1) የመዳንን ወንጌል ለሰው ልጆች ሁሉ ማወጅ፣ (2) አማኞችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማነጽ እና ማሠልጠን፣ (3) በአምልኮ ጌታን ማመስገን እና (4) ክርስቲያናዊ ርሕራሔን ማሳየት እንደሆነ እናምናለን (ማቴ. 28፡19-20፤ 10፡42፤ ኤፌ. 4፡11-13)።

# 7. የቤተ ክርስቲያን መመሪያዎች

በውኃ ጥምቀት መጠመቅ ንስሐ ከገቡና ካመኑት ሁሉ እንደሚጠበቅ እናምናለን። በዚህም ከክርስቶስ ጋር መሞታቸውንና በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ ከርሱ ጋር መነሣታቸውን ለዓለም ይናገራሉ (ማቴ. 28፡19፤ ሐዋ. 10፡47-48፤ ሮሜ. 6፡4)።

የጌታ ራት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስቃይና ሞት አዋጅ ጌታ እስኪመጣ ድረስ አማኞች ሁሉ የሚካፈሉት መሆኑን እናምናለን (ሉቃ. 22፡14-20፤ 1ቆሮ. 11፡20-34)።

# 8. መቀደስ

መቀደስ ከክፉ ነገር የመለየት እና ለእግዚአብሔር የመወሰን ተግባር እንደሆነ እናምናለን። በተግባር፣ ቅጽበታዊ እና ሂደትን የያዘ ነው። በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚፈጠረው የክርስቶስን ደም ኃይል እና ከሞት በተነሣው ሕይወቱን በመንፈስ ቅዱስ አካል አማካኝነት ነው። እርሱ የአማኙን ትኩረት ወደ ክርስቶስ ይስባል፣ በቃሉ ያስተምረዋል እናም የክርስቶስን ባህሪ በውስጡ ያፈራል (ሮሜ. 6:1-11፤ 8:1-2፣ 13፤ 12:1-2፤ ገላ. 2:20፤ ዕብ. 10:10፣ 14)።

# 9. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአማኙ ለሕይወት እና ለክርስቶስ አገልግሎት ኃይል እንደሚሰጠው እናምናለን። ይህ ልምምድ ከአዲስ ልደት የተለየ እና የሚከተል ነው። ደግሞም በእምነት የምንቀበለው እና መንፈስም ንግግርን እንደ መጀመሪያ ማስረጃ ሲሰጥ በልሳን የመናገር መገለጥ አብሮ ይመጣል (ሉቃስ 24:49፤ የሐዋርያት ሥራ 1:8፤ 2:1-4፤ 8:15-19፤ 11:14—17፤ 19:1-7)።

# 10. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

ዘጠኙን ከልዕለ ተፈጥሮ በላይ የሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎች (1ቆሮ. 12) እና የክርስቶስ የአገልግሎት ሥጦታዎች (ኤፌ. 4፡11-13) ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እና ለማስፋፋት በዘመናችን ያሉ አሠራር እንደሆኑ እና እንደተሰጡ እናምናለን።

# 11. የጊዜ መጨረሻ

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ህዝቦቹን ወደ እርሱ ለመሰብሰብ ቅድመ-ሚሊኒየም፣ በቅርብ እና በግላዊ ዳግመኛ መምጣት እናምናለን። ይህንን የተባረከ እና የጠበቀ ተስፋ ስላለን፣ እርሱ ንፁህ እንደሆነ ራሳችንን እናነጻለን ይሄውም እርሱ ሲመጣ እርሱን ለመቀበል የተዘጋጀን እንሆን ዘንድ ነው(ዮሐ. 14:1-3፤ ቲቶ 2:13፤ 1 ተሰ. 4:15-17፤ 1 ዮሐንስ 3:2-3፤ ራዕ. 20:1-6)።

የሰው ልጆች ሁሉ በሥጋዊ ትንሣኤ እንደሚነሱ እናምናለን። የዘላለም ህሊናዊ ደስታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ነው። ስማቸው በህይወት መጽሐፍ ያልተፃፈ ደግሞ ዘላለማዊው ህሊናዊ ቅጣት የሁሉም እጣ ፈንታ ነው (ዮሐ. 5፡28-29፤ ቆሮ.15፡22-24፤ ራዕ. 20፡10-15)።

# ~ አባሪ 2 ~
# 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10 የመገለጥ ስጦታዎች

**የመገለጥ ስጦታዎች** (የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለማወቅ የተሰጡ)

- የእውቀት ቃል (መልእክት)፡- በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የሚሰጥ የእግዚአብሔር እውቀት
- የጥበብ ቃል (መልእክት)፡-በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ጥበብ
- በመናፍስት መካከል መለየት፡- በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የሚሰጥ ምን አይነት መንፈስ ወይም ሃሰብ መሆኑን የመለየት ጸጋ

**ትንቢታዊ ስጦታዎች** (የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር የተሰጡ)

- የትንቢት ስጦታ፡- ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክትን በመንፈስ አነሳሽነት መናገር ነው።
- የተለያዩ ልሳኖች፡- በመንፈስ አነሳሽነት ተናጋሪው በማያውቀው ቋንቋ ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክት ወይም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ጸሎት ማድረግ ነው።
- የቋንቋዎች ትርጓሜ፡- በልሳኖች ስለሚነገረው መልእክት ወይም ጸሎት በመንፈስ አነሳሽነት ፍቺውን ተረድቶ መናገር ነው።

**የኃይል ስጦታዎች** (የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የተሰጡ)

- የእምነት ስጦታ፡- እግዚአብሔር የፈቀደውን ተግባር ለመፈፀም በመንፈስ አቅም የሚሆን እምነትን እምርታ ነው
- የፈውስ ሥጦታዎች፡- በመንፈስ የአቅም የሚሆን የበሽታዎችንና የአካል ጉዳቶችን ፈውስ ነው
- ተአምራዊ ኃይላት፡- የእግዚአብሔርን ልዩ ሥራ ለማከናወን የመንፈስ አቅም የኃይል መለቀቅ። (ማስታወሻ፡- ይህ ስጦታ በትክክል “የኃይል ሥራዎች” ወይም ከግሪክኛ (ኢነርጌማታ ዱናሞን) “የኃይል ሥራዎች” ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

# ~ አባሪ 3 ~
# የመጽሐፍ ቅዱስ አጽሮተ ቃላት

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ብሉይ ኪዳን** | | መኃልየ መኃልይ | መኃልየ |
| ዘፍጥረት | ዘፍ | ኢሳያስ | ኢሳ. |
| ዘጸአት. | ዘጸ | ኤርምያስ | ኤር. |
| ዘሌዋውያን | ዘሌ. | ሰቆቃወ | ሰቆ. |
| ዘኍልቁ | ዘኍ | ሕዝቅኤል | ሕዝ. |
| ዘዳግም | ዘዳ | ዳንኤል | ዳንኤል. |
| ኢያሱ | ኢያሱ | ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| መሳፍንት | መሳ. | ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| ሩት | ሩት | አሞጽ | አሞጽ |
| 1ኛ ሳሙኤል | 1 ሳሙ | አብዲዩ | አብ |
| 2ኛ ሳሙኤል | 2 ሳሙ | ዮናስ | ዮናስ |
| 1 ነገሥት | 1 ነገ | ሚክያስ | ሚክ |
| 2 ነገሥት | 2 ነገ. | ናሆም | ናሆም |
| 1ኛ ዜና | 1ኛ ዜና. | ዕንባቆም | ዕንባ |
| 2ኛ ዜና | 2ኛ ዜና. | ሶፎንያስ | ሶፎ. |
| ዕዝራ | ዕዝ. | ሐጌ | ሐጌ |
| ነህምያ | ነህ. | ዘካርያስ | ዘካ. |
| አስቴር | አስቴር | ሚልክያስ | ሚል. |
| ኢዮብ | ኢዮ | | |
| መዝሙረ ዳዊት መ | ዝ | **አዲስ ኪዳን** | |
| ምሳሌ | ምሳ | ማቴዎስ | ማቴ. |
| መክብብ | መክ. | ማርቆስ | ማር |

አባሪ 3 የመጽሐፍ ቅዱስ አጽሮተ ቃላት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሉቃስ | ሉቃስ | 2 ጢሞቴዎስ | 2 ጢሞ. |
| ዮሐንስ | ዮሐ. | ቲቶ | ቲቶ |
| የሐዋርያት ሥራ | ሐዋ. | ፊልሞን | ፊልሞን |
| ሮሜ. | ሮሜ | ዕብራውያን | ዕብ. |
| 1 ቆሮንቶስ | 1 ቆሮ. | ያዕቆብ | ያዕቆ |
| 2 ቆሮንቶስ | 2 ቆሮ. | 1ኛ ጴጥሮስ | 1 ጴጥ. |
| ገላትያ | ገላ. | 2ኛ ጴጥሮስ | 2 ጴጥ. |
| ኤፌሶን | ኤፌ. | 1ኛ የዮሐንስ መልእክት | 1 ዮሐ |
| ፊልጵስዩስ | ፊሊ. | 2ኛ የዮሐንስ መልእክት | 2 ዮሐ |
| ቆላስይስ | ቆላ. | 3ኛ የዮሐንስ መልእክት | 3 ዮሐ |
| 1 ተሰሎንቄ | 1 ተሰ. | ይሁዳ | ይሁዳ |
| 2 ተሰሎንቄ | 2 ተሰ. | ራዕይ | ራዕ. |
| 1 ጢሞቴዎስ | 1 ጢሞ. | | |

AFRICA'S HOPE